## ማውጫ

ክፍል ዘጠኝ ........ 1

ጉምሩክ እና ገቢዎች ........ 1

ሀ/ ጉምሩክ፣ የወጪና የገቢ ዕቃዎች ታክስ ........ 1

የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 252/1954 ዓ.ም ........ 1

የዲፕሎማቲክና የቆንሲል መብት ደንብ ........ 1

የመንግስት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 7/1981 ........ 7

ለምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ አገሮች ልዩ የንግድ ቀጠና ተፈፃሚ የሚሆን የትራንዛክሽን ታክስና የጉምሩክ ቀረጥ ለመወሰን የወጣ የመንግስት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ........ 7

ደንብ ቁጥር 122/1985 ........ 9

የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 9

ደንብ ቁጥር 24/1990 ........ 10

የጉምሩክ መጋዘን ስራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 10

ደንብ ቁጥር 37/1990 ........ 15

የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 15

ደንብ ቁጥር 88/1995 ዓ.ም ........ 21

ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 21

ደንብ ቁጥር 108/1996 ........ 24

የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 24

አዋጅ ቁጥር 567/2000 ........ 30

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል በተዘጋጀ ቆዳናሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣ አዋጅ ........ 30

አዋጅ ቁጥር 768/2004 ........ 33

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ........ 33

አዋጅ ቁጥር 859/2006 ........ 50

የጉምሩክ አዋጅ ........ 50

ለ/ የሀገር ውስጥ ገቢ ........ 151

አዋጅ ቁጥር110/1990 ........ 151

የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ........ 151

ደንብ ቁጥር 221/1951ዓ.ም (የሕግ ክፍል ማስታወቂያ) ........ 160

የቴምብር ቀረጥ ለማስከፈል በ1950 ዓ.ም ድንጋጌ መሠረት የወጣ ደንብ ........ 160

አዋጅ ቁጥር 285/1994 ዓ.ም ........ 164

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ........ 164

ደንብ ቁጥር 79/1995 ዓ.ም ........ 224

የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 224

አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ........ 272

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ........ 272

አዋጅ ቁጥር 308/ 1995 ዓ.ም ........ 348

የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ........ 348

ደንብ ቁጥር 139/1999 ........ 370

በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታየወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 370

አዋጅ ቁጥር 767/2004 ዓ.ም ........ 384

የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ........ 384

አዋጅ ቁጥር 979/2008 ........ 387

የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ........ 387

ደንብ ቁጥር 410/2009 ........ 467

ስለፌደራል የገቢ ግብር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ........ 467

አዋጅ ቁጥር 983/2008 ........ 498

የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ........ 498

ደንብ ቁጥር 407/2009 ........ 601

ስለ ፌደራል የታክስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 601

## ክፍል ዘጠኝ

## ጉምሩክ እና ገቢዎች

### ሀ/ ጉምሩክ፣ የወጪና የገቢ ዕቃዎች ታክስ

### የሕግ ክፍል ማስታወቂያቁጥር 252/1954 ዓ.ም

### የዲፕሎማቲክና የቆንሲል መብት ደንብ

1. ይህን ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መክሮበት ካጸደቀው በኋላ በ1935 ዓ.ም ወጥቶ በተሻሻለው የገቢና ወጭ ዕቃ ቀረጥ አከፋፈል አዋጅ በአንቀጽ 5(ለ) በተመለከተው መሠረት፣ የገንዘብ ሚንስትር ያወጣው ደንብ ነው፡፡
2. ይህ ደንብ "በ1954 ዓ.ም የወጣ የዲፕሎማቲክና የቆንሲል መብት ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
3. ትርጉም

   በዚህ ደንብ የተነገሩት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቃላት የሚከተለው ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፡፡

   ሀ/ "የጉምሩክ ቀረጥ" ማለት ስለ ገቢና ወጭ ዕቃ ቀረጥ አከፋፈል በ1935 ዓ.ም በወጣውና በተሻሻለው አዋጅ መሠረት የሚከፈሉትን ወይም እንዲከፈሉ የታዘዙትን ቀረጥና ታክሶች ሁሉ ማለት ነው፡፡

   ለ/ "የዲፕሎማቲክና የቆንሲላ መልእክተኞች (ሚሲዮን)" ማለት በክብር ሹመት የሚጠሩትን ሚሲዮኖች ሳይጨምር የውጭ አገር መንግሥታት በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ ያቋቋሙዋቸው መልእክተኞች (ሚሲዮኖች) ማለት ነው፡፡

   ሐ/ "የዲፕሎማቲክ ሹማምንት" ማለት አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ነዋሪ ጉዳይ ፈጻሚዎች፣ አማካሪዎች (ካውንስለርስ)፤አንደኛ፤ሁለተኛና፤ ሦስተኛ ጸሐፊዎች፤ አታሼዎች ማለት ነው፡፡

   መ/ "የቆንስላ ሹማምንት" ማለት ዋና ቆንሲሎች፣ ቆንሲሎች፣ ምክትል ቆንሲሎች፣ ማለት ነው፡፡

   ሠ/ "ቤተሰብ" ማለት ባልና ሚስት፣ የተባለው ሰው ልጅ ሆኖ ዕድሜው ከአሥራ ስምንት (18) ዓመት በታች የሆነ ሰው ጭምር ማለት ነው፡፡

ረ/ "ገቢ ዕቃ" ማለት ከውጭ አገር በቀጥታ የመጣ ማናቸውም ዕቃ፣ መሣሪያ፣ ዝርዝር ነገርና ማቴሪያል ጭምር ነው፡

ሰ/ "የመልእክተኛ መሪ" ማለት መልእክተኛ ሆኖ ለተላከበት የውጭ አገር መንግሥት ሚሲዮን መንግሥቱ የበላይ አላፊ አድርጐ የሾመው ማንኛውም አምባሳደር፣ ሚኒስትር፣ ነዋሪ ጉዳይ ፈጻሚ ዋና ቆንሲል ወይም ቆንሲል ማለት ነው፡፡

ሸ/ "የቤት ዕቃዎችና መሣሪያዎች" ማለት ለባለጉዳዩ መኖሪያ ቤት አገልግሎት እንዲውሉ የሚገቡ ዕቃዎች ማለት ነው፡፡

ቀ/ "የዲፕሎማቲክና የቆንሲላ መልእክተኞች" ማለት በዲፕሎማቲክና በቆንሲላ ሹማምንት ደረጃ ያልተመደቡ፣ የዲፕሎማቲክና የቆነሲላ መልእክተኞች የቀጠሩዋቸው ሠራተኞች ማለት ነው፡፡

በ/ "ለሥራው መጀመሪያ የደረሰበት ጊዜ" ማለት ባለ ጉዳዩ የመጣበትን ተግባር ለመጀመር ኢትዮጵያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት (6) ወር ያለው ጊዜ ማለት ነው፡፡

ተ/ "የግል ዕቃ ጓዝ" ማለት አንድ የዲፕሎማቲክ ወይም የቆንሲላ ሹምና ቤተሰቡ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ የሚያጉዘው የእጅ ሻንጣ ወይም ሌላ የመንገደኛ ዕቃ ማለት ነው፡፡

ቸ/ "የግል አገልግሎት" ማለት ለባለጉዳዩ ወይም ለቤተሰቡ የሚውለው አገልግሎት ማለት ነው፡፡

4. <u>መብቱ የሚሰጥበት ሁኔታ፣</u>

ሀ/ በዚህ ደንብ የሚሰጠው መብት ተመሳሳይ መብት መደራረግን (ሬፕሮሲቲ) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ መሰል መብት ያልተሰጠበት ሁኔታ ሲያጋጥም ግን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የውጭ አገር መንግሥታት በሚሰጡት መብት መጠን እንዲሆን የሚሰጠውን መብት ለመቀነስ የገንዘብ ሚኒስቴር[1] አስፈላጊውን ተግባር ይፈጽማል፡፡

ለ/ በዚህ ደንብ መሠረት የተፈቀዱትን መብቶች ለማግኘት የሚችሉ፣

1. የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግስት ያልሆኑ፤

[1] በ25/8 (2008) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴርበሚል ይነበብ፡፡

2. የላኪው መንግሥት ነዋሪ ሠራተኞች የሆኑ፣ ወይም በተቀጠሩበት ጊዜ በኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ውስጥ ነዋሪ ያልነበሩና፣
3. በኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ውስጥ ምንም ዓይነት መተዳደሪያ ወይም ሥራ ያልያዙ፤

   ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

5. <u>ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ስለመሆን፣</u>

ሀ/ በዚህ ደንብ የተነገሩት ውሳኔዎች ሁሉ የተከበሩ ሆነው፣ ከዚህ በታች በተወሰነው አኳኋን ቀጥሎ ለተዘረዘሩት የውጭ አገር መልእክተኞች፣ ሹማምንትና ሠራተኞ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ የመሆን መብት በዚህ ደንብ ተሰጥቷል፡፡

1. <u>1ኛ መደብ፡-</u> የዲፕሎማቲክና የቆንሲላ መልእክተኞች ለመደበኛው ሥራቸው ጉዳይ የሚያስመጡዋቸው ዕቃዎች ሁሉ፤ ተሽከርካሪ መኪናዎችም ጭምር፡፡
2. <u>2ኛ መደብ፡-</u> የዲፕሎማቲክ ሹማምንት ለግል አገልግሎታቸው በማንኛውም ጊዜ የሚያስመጡዋቸው የቤት ዕቃዎችና መሣሪያዎች፤ ዕቃዎች ተሽከርካሪ መኪናዎችም ጭምር፤
3. <u>3ኛ መደብ፡-</u> የቆንሲል ሹማምንት ለሥራው መጀመሪያ በደረሱበት ጊዜ ውስጥ ለግል አገልግሎታቸው ያስመጡዋቸው የቤት ዕቃዎችና መሣሪያዎች፤ ተሽከርካሪ መኪናዎችም፤

ለ/ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 5 በክፍል (ሀ) የተወሰነው ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ የመሆን መብት፤ የተጠቀሱትን ዕቃዎች ያለቀረጥ ለማስመጣት መብት የተሰጣቸው ሰዎች፤ ከዲፕሎማቲክና ከቆንሲላ መልእክተኞች፤ ከዲፕሎማቲክና ከቆንሲላ ሹማምንት ለሚገዙዋቸው ዕቃዎችም ይጸናል፡፡

6. <u>በዚህ ደንብ የተፈቀዱት መብቶች መወሰን</u>

ማናቸውም በዚህ ደንብ ውስጥ የተነገረው፤ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት እንዳይገቡ ወይም ከኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት እንዳይወጡ በሕግ የተከለከሉትን ዕቃዎች የሚፈቅዱ ነው ተብሎ ወይም ስለ አንዳንድ ዓይነት ዕቃዎች ማስመጣት ወይም አላላክ በሕግ የተወሰኑትን አግባቦች ላለመፈጸም መብት የሚሰጥ ነው ተብሎ አይተረጐምም፡፡

7. <u>ስለ ተሽከርካሪ መኪናዎች ልዩ ውሳኔዎች፣</u>

ሀ/ ለዲፕሎማቲክና ለቆንሲላ መልእክተኞች መደበኛ ሥራ ጉዳይ ወይም ለመልእክተኞቹ መሪዎች የግል አገልግሎት ተሽከርካሪ መኪናዎች በማስመጣት አንዳችም ውሳኔ አይኖርም፡፡

ለ/ ሌሎች የዲፕሎማቲክና የቆንሲላ ሹማምንት ሁሉ፤ በየሶስት ዓመት አንድ (1) ተሽከርካሪ መኪና የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፍሉ በነጻ ማስመጣት ይፈቀድላቸዋል፡፡ ነገር ግን የሶስቱ ዓመት ጊዜ ከማለፉ በፊትም ቢሆን የተባለው ተሽከርካሪ መኪና በጣም የተበላሸ መሆኑን የጉምሩክ መሥሪያ ቤት ሲያረጋግጥ በምትኩ ሌላ ተሽከርካሪ መኪና የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈል በነጻ ለማስመጣት ይቻላል፡፡

ሐ/ መጀመሪያውኑ የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልበት የገባውን ማናቸውንም ተሽከርካሪ መኪና የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፍል ተሽከርካሪ መኪና ለማስመጣት መብት ለሌለው ሰው ወይም እንደዚህ ያለው መብት ቢኖረውም፣ ባለፉት ሶስት (3) ዓመታት ውስጥ በመብቱ ለተጠቀመበት ሰው ሲሸጥ፤ ሲያጨ በሚያስተላልፈበት ወይም በሚያስረክብበት ጊዜ የሚከፍለው የጉምሩክ ቀረጥ መኪናው አገር ውስጥ መጀመሪያ በገባበት ጊዜ በነበረው የጉምሩክ ቀረጥ ታሪፍ መሠረት ነው፡፡

8. <u>ከፍተኛ ነጻ ስለመሆን</u>

የዲፕሎማቲክ መልእክተኞች ለመደበኛ ሥራቸው አገልግሎት የሚያስመጡዋቸውን ዕቃዎችና እንዲደዚሁም ደግሞ የዲፕሎማቲክ ሹማምንት፤ ተከታይ ቤተሰቦች በማንኛውም ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ሲገቡና ከኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ሲወጡ የሚያመጡዋቸውን ወይም የሚያወጡዋቸውን የግል ዕቃ ጓዝና ሌላም ዕቃዎችን ከፍተኛ ነፃ እንዲሆኑ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የጉምሩክ መሥሪያ ቤቶች ዳሬክተር አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡ ስለሆነም አንዳችም ማስታወቂያ በቅድሚያ ሳይሰጥ አልፎ አልፎ በየጊዜው ዕቃዎችን የመፈተሹ ተግባር የጉምሩክ መሥሪያ ቤቶች መብት እንደተጠበቀ ነው፡፡

9. <u>የጉምሩክ ዴክላራሲዮን አሞላል ሥርዓት፣</u>

ሀ/ ለአንድ የዲፕሎማቲክ ወይም የቆንሲላ መልእክተኛ መደበኛ ሥራ አገልግሎት ስለሚገቡት ዕቃዎች የሚሞሉት ዴክላራሲዮኖች ሁሉ በመልእክተኛው መሪ ወይም በምክትሉ ይፈረማሉ፡፡

ለ/ ለዲፕሎማቲክና ለቆንሲላ ሹማምንት ወይም ለዲፕሎማቲክና ለቆንሲላ መልእክተኞች ሠራተኞች ለግል አገልግሎት ስለሚገቡ ዕቃዎች የሚሞሉት ዴክላራሲዮኖች ሁሉ ዕቃዎቹ በመጡለት ሰው ስም ይዘጋጃሉ፤ የመጡትም ዕቃዎች ለመልእክተኛው መሪ ሳይሆን ለሌላ ሰው አገልግሎት የሆን እንደሆነ፤ የመልእክተኛው መሪ ዴክላራሲዮኑን አብሮ ይፈርማል፡፡

ሐ/ ስለ ገቢ ወይም ስለ ወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ መሥሪያ ቤቶች እንዲፈጸም የሚጠይቁትን የጉምሩክ ሥርዓት ጉዳይ የሚመለከተው መልእክተኛው መሥሪያ ቤት ወይም ሰው ይፈጽማ፡፡

10.<u>ከቀረጥ ነጻ የገቡትን ዕቃዎች መልሶ በሚሸጥበት ጊዜ ስለሚከፈለው ቀረጥ፣</u>

ሀ/ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት የገቡት ዕቃዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ሶስት (3) ዓመት ሳያልፍ የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈል በነጻ ለማስወጣት መብት ለሌለው ለማናቸውም ሰው የተሸጡ ወይም የተሰጡ እንደሆነ፣ በ1947 ዓ.ም በወጣው የጉምሩክ አዋጅ በአንቀጽ 83[2]መሠረት፤ በዚህ አኳኋን በሚተላለፉበት ጊዜ በሚሠራበት የጉምሩክ ቀረጥ ታሪፍ ልክ ቀረጥ ይከፈልባቸዋል፡፡

ለ/ እያንዳንዱ የዲፕሎማቲክና የቆንሲላ መልእክተኛ የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው የገቡትን ዕቃዎች ከአንድ ወደ ሌላው መተላለፍ ጉዳይ መቆጣጠርና በዚህ በ10ኛው አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) በተነገረው መሠረት ሲሸጡና የጉምሩክ ቀረጥ የሚያስከፍላቸው በሆነ ጊዜ ቀረጡን እንዲከፍሉ ማድረግ፤ ወይም ከዕቃዎች መካከል እንደዚህ ያሉትን ዕቃዎች ለማስመጣት የቀረጥ ነጻ መሆን መብት ላለው ለማንኛውም ሰው ሲሸጡ ገዥው ሰው አባል የሆነበት መልእክተኛ እንዲያውቅና ያው ዕቃ ወደፊት ሲተላለፍ በበኩሉ አስፈላጊውን የመቆጣጠር ተግባር እንዲፈጽም ማስታወቅ አለበት፡፡

11.<u>የደንቡ ወሰን</u>

በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም የሚወስን የጋራ ስምምነት ወይም ውል ካልኖረ በቀር ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ላሉት የዲፕሎማቲክና የቆንስላ

---

[2] በስራ ላይ ያለው የጉምሩክ አዋጅ 20/82(2006) አ.859 ነው፡፡ ለተመሳሳይ ድንጋጌ አንቀፅ 131ን ተመልከት፡፡

መልእክተኞች፣ እንደዚሁም ለዲፕሎማቲክና ለቆንስላ መልእክተኞት ሹማምንትና ሠራተኞች የጸና ይሆናል፡፡

12. ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 21 ቀን 1950 ዓ.ም**

**ይልማ ዴርሣ**

**የገንዘብ ሚኒስትር**

## የመንግስት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 7/1981
## ለምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ አገሮች ልዩ የንግድ ቀጠና ተፈፃሚ የሚሆን የትራንዛክሽንታክስና የጉምሩክ ቀረጥ ለመወሰን የወጣ የመንግስት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ
## "ኢትዮጵያ ትቅደም"

ለምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ አገሮች ልዩ የንግድ ቀጠና ለማቋቋም ታኅሳስ 12 ቀን 1974 በሉሳካ የተፈረመውን ስምምነት ኢትዮጵያም ተቀብላ ያጸደቀችው በመሆኑ፤

አባል ሀገሮች በጋራ ሊስቱ ውስጥ ለተመዘገቡት ዕቃዎች በሶስት ደረጃ የተመደበ የታሪፍ ቅነሳ እንዲያደርጉ የልዩ የንግድ ቀጠናው የሚኒስትሮች ምክር ቤት መጋቢት 22 ቀን 1979 የተወሰነ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ምክር ቤትም ህዳር 16 ቀን 1981 ባደረገው ስብሰባ ይህንኑ ቅነሳ የተቀበለው በመሆኑ፤

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 83(1) መሰረት የሚከተለው ተደንግጓል፡፡

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ ልዩ ድንጋጌ "ለምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ አገሮች ልዩ የንግድ ቀጠና ተፈፃሚ የሚሆን የትራንዛክሽን ታክስና የጉምሩክ ቀረጥ የመንግስት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 7/1981" ተብሎ ሊተቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ልዩ ድንጋጌ ውስጥ፤

   1. "ልዩ የንግድ ቀጠና" ማለት በስምምነቱ አንቀፅ 2 መሰረት የተቋቋመው የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ አገሮች ልዩ የንግድ ቀጠና ነው፡፡
   2. "ስምምነት" ማለት ታኅሳስ 12 ቀን 1974 በሉሳካ የተፈረመውና ከመስከረም 20 ቀን 1975 ጀምሮ የጸናው ልዩ የንግድ ቀጠና የተቋቋመበት ስምምነት ነው፡፡

3. **የትራንዛክሽን ታክስና የጉምሩክ ቀረጥ መወሰን**

1. በትራንዛክሽን ታክስ አዋጅ ቁጥር 205/1955 (እንደተሻሻለው) እና በጉምሩክ ቀረጥ ደንብ ቁጥር 42/1968[3] (እንደተሻሻለው) የተወሰነው ቢኖርም፤ ከልዩ የንግድ ቀጠናው አባል አገሮች ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ የሚከፈለው የትራንዛክሽን ታክስና የጉምሩክ ቀረጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በማውጣት በስምምነቱ መሰረት የሚወስነው ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ተፈፃሚ የሚሆነው ሸቀጦቹ በስምምነቱ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

4. <u>ደንብ የማውጣት ስልጣን</u>

ለልዩ የንግድ ቀጠናው አባል አገሮች ተፈፃሚእንዲሆን በስምምነቱ መሰረት በተከታታይ የሚወሰነውን የትራንዛክሽን ታክስና የጉምሩክ ቀረጥ ቅናሽ ስራ ላይ ለማዋል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የማውጣት ስልጣን በዚህ ልዩ ድንጋጌ ተሰጥቶታል፡፡

5. <u>ልዩ ድንጋጌው የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ ልዩ ድንጋጌ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 15 ቀን 1981**

**መንግስቱ ኃይለማርያም**

**የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

---

[3]እንደቅደምተከተላቸው በ4/18(1990) አ.99 እና በ54/23(1987) ደ.122 ተሽረዋል፡፡8/35(1994) አ.287 መሰረት ከአገልግሎት ውጪ የሆነ

## ደንብ ቁጥር 122/1985

## የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትረነና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2 እና የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 67/1985 አንቀጽ 4 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 122/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የተሻረ ሕግ**

   የጉምሩክ ቀረጥ ደንብ ቁጥር 42/1968 ከነማሻሻያዎቹ ተሽሮ በዚህ ደንብ እና ከዚሁ ጋር በተያያዙት የጉምሩክ የዕቃ ቀረጥ ደንብ ሥርዓትና ተመኖች ተተክቷል፡፡

3. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ ከነሐሴ 10 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 8 ቀን 1985 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 24/1990**

**የጉምሩክ መጋዘን ስራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣየሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ትግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 40(4) እና አንቀጽ 84 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጉምሩክ መጋዘን ስራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 24/1990" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ

   1. “የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን" ማለት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈፀመባቸዉ ዕቃዎች እንዲከማቹበት በጉምሩክ ባለሥልጣን ፈቃድ የሚቋቋም የጠቅላላ ወይም የግል ዕቃ መጋዘን ነው፤
   2. "ፈቃድ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የጉምሩክ መጋዘን ለማቋቋም የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
   3. "የጠቅላላ ዕቃ የጉምሩክ መጋዘን" ማለት የተለያዩ አስመጪዎች ወይም ላኪዎች ዕቃ ላይ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ የሚቀመጡበት መጋዘን ነው፤
   4. “የግል ዕቃ የጉምሩክ መጋዘን" ማለት ማንኛውም ሰው በስሙ ለሚያስመጣቸው ወይም ለሚልካቸዉ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እስከሚጠናቀቅለት ድረስ የሚከማቹበት መጋዘን ነው፤
   5. "ሰው" እና "ባለሥልጣን" ማለት የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና

አሠራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅቁጥር 60/1989[4] የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡

3. **<u>በፈቃድ የሚቋቋሙ የመጋዘን ዓይነቶች</u>**
   1. በባለስልጣኑ በሚሰጥ ፈቃድ የሚቋቋም የጉምሩክ መጋዘን በተለያዩ ሰዎች ስም የመጣን ወይም የሚላክን ዕቃ ለማከማቸት የሚያገለግል የጠቅላላ ዕቃ የጉምሩክ መጋዘን ወይም ባለፈቃዱ በራሱ ስም ያመጣውን ወይም የሚልከውን ዕቃ ለማከማቸት የሚያገለግል የግል ዕቃ መጋዘን ተብሎ በሁለት ይመደባል፡፡
   2. የጠቅላላ ዕቃ ማከማቻ እና የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ለመስጠት የሚያበቁት መስፈርቶች በፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡ ቦርዱ የሚያወጣው መመሪያ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡
4. **<u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>**
   1. የጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ መመሪያዎች ውስጥ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ለሚያሟላ ማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ጠያቂ ባለስልጣኑ የመጋዘን ፈቃድ ይሰጣል፡፡
   2. ባለሥልጣኑ የመጋዘን ሥራ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻውን በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ የሥራ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል ያሳለፈውን ውሣኔ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት ፡፡
5. **<u>የጉምሩክ መጋዘን የሚቋቋምባቸው ቦታዎች</u>**
   1. የጉምሩክ መጋዘን የጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያዎችን በመከተል በአገሪቷ የአየር፣ የየብስና የውሃ ላይ ማጓጓዣዎች መግቢያና መውጫ በሆኑ የጉምሩክ ወደቦች ወይም የመተላለፊያ መንገዶች ላይ የሚቋቋም ይሆናል፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ሲያምንበት በሌሎች በማናቸውም ሥፍራ መጋዘን እንዲቋቋም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

[4] ይህ አዋጅበ15/27(2001) አ.622 የተሻረ ሲሆን 622/2001 በ20/82(2006) አ.859 ተሽሯል፡፡ በመሆኑም ለአቻ ትርጓሜ የ859/2006 አንቀፅ 2(55) እና (56)ን ተመልከት፡፡

6. **የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን ስራ ቀንና ሰዓት.**

   1. የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን በህግ በተወሰነው መደበኛ የስራ ቀንና ሰዓት ዕቃ ለማስገባትና ለማስወጣት ክፍት ይሆናል ፡፡
   2. ከመደበኛ የስራ ቀንና ሰዓት ውጭ ዕቃ ወደ መጋዘን ለማስገባትና ከመጋዘን ለማስወጣት ቢያስፈልግ ባስሥልጣኑን በጽሁፍ መጠየቅና ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

7. **ለባለስልጣኑስለሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ**

   1. በፈቃድ የተቋቋመ የጉምሩክ መጋዘንን የሚቆጣጠር የጉምሩክ ሹም ባለሥልጣኑ ይመድባል፡፡
   2. በፈቃድ ለተቋቋመ መጋዘን ቁጥጥርና ባለሥልጣኑ የሚያወጣውን ጠቅላላ ወጭ መሠረት በማድረግ ባለፈቃዱ በየዓመቱ ለባለሥልጣኑ ገቢ የሚያደርገው የአገልግሎት ክፍያ መጠን በቦርዱ ይወሰናል፡፡

8. **የፈቃድና የዕድሣት ክፍያ**

   1. የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ የሚሰጠው ማንኛውም ሰው ከዚህ እንደሚከተለዉ የፈቃድና የዕድሣት ክፍያ ይከፍላል፤

      ሀ/ለጠቅላላ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ብር 1250

      ............................... ለዕድሳት ብር 500

      ለ/ለግል ዕቃ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ብር 1250

      ....................................ለዕድሳት ብር500

      ይከፈላል፡፡

9. **ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

   1. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 10 መሠረት በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፈቃዱ ካልተሠረዘ በስተቀር የተሰጠ የመጋዘን ፈቃድ ለአንድ የበጀት ዓመት የፀና ይሆናል ፡፡
   2. የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከሐምሌ 1 እስከ ሐምሌ 30 ባለዉ ግዜ ውስጥ በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 መሠረት ተገቢው ክፍያ ተፈጽሞ መታደስ አለበት፡፡
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ያላሳደሰ ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 30 ባለው ጊዜ የማደሻውን 100 ፐርሰንት ቅጣት በመክፈል ያሳድሳል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ሳያሳድስ ከቀረ የተሰጠው የመጋዘን ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

## 10.ፈቃዱን የሚያሰርዙ ምክንያቶች

ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት የሰጠውን ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰርዝ ይችላል፡፡

1. ያለማስጠንቀቂያ፣

ሀ/ በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ያልተመዘገበ ወይም ፈቃድ ያልተሰጠው ዕቃ በመጋዘኑ እንዲገባ ወይም እንዲወጣ ያደረገ፣ ወይም

ለ/ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ከመጋዘን እንዲወጣ ያደረ፣ ወይም

ሐ/ ስለዕቃ የሚገልጹ ሠነዶችን የሰረዘ ወይም የደለዘ፣ ወይም

መ በመጋዘን ያልገባን ዕቃ እንደገባ አስመስሎ የሀሰት ማስረጃ የሰጠ፣ ወይም

ሠ/ ወደ መጋዘን ለመግባት በመጣው ዕቃ መግለጫ ሰነዶች ላይ የሰፈረው መረጃ ወደ መጋዘን ለመግባት ከመጣው ዕቃ በዓይነት ወይም በብዛት፣ በመጠን፣በክብደት የማይመሳሰሉ መሆናቸው ወይም በሰነድ ውስጥ ያልተገለጹ ዕቃዎች መኖራቸውን እያወቀ ለጉምሩክ ያልገለጸ፣ ወይም

ረ/ ወደ መጋዘኑ በገቡ ዕቃዎች ላይ ስርቆት የፈፀመ፣ መሆኑ ሲረጋገጥ ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የመጋዘን ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

2. በማስጠንቀቂያ

ከዚህ በታች ለተገለጹት ምክንያቶች በባለሥልጣኑ በቅድሚያ የሰባት ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመጋዘን ፈቃድ ይሰረዛል፣ ሆኖም በማስጠንቀቂያው ውስጥ የተገለጸው ሁኔታ እንዲስተካከል ከተደረገ የፈቃዱ መሠረዝ ይቀራል፣

ሀ/ በህግ ወይም ባለስልጣኑ ባወጣቸው መመሪያዎች ውስጥ የተደነገጉትን የሚጥስ ተግባር መፈጸም፣ ወይም

ለ/ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የዕለት ተግባራቸውን እንዲፈጽሙ ትብብር አለማድረግ፣ ወይም

ሐ/በጥንቃቄ ጉድለት በዕቃዎች ላይ ጉዳት ማድረስ፣ ወይም

መ/የጉምሩክ ፎርማሊቲ ያልተፈፀመባቸው ወይም በባለቤቱ የተተዉ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገዱ፣ የተወረሱ እና የመሳሰሉት ዕቃዎች ወደ ባለሥልጣኑ መጋዘን በወቅቱ አለማስተላለፍ፤ ወይም፣

ሠ/ለተፈቀዱ ምክንያቶች ናሙና አስመስጠት፤ የተሰጡ ናሙናዎችን ተከታትሎአለማስመሰስ፤ በወቅቱ ሪፖርት አለማድረግና በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶችለባለእቃዉና ለባለሥልጣኑ ሹሞች ቀና አገልግሎት አለመስጠት፣ ወይም፤

ረ/ እነዚህን የመሳስሉ ሌሎች ድርጊቶችን መፈጸም።

11.<u>ስለፈቃድ መሠረዝና ስለ ቅጣት</u>

1. ከዚህ በላይ በተመስከቱት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ በተገለጹት ምክንያቶች የመጋዘን ፈቃድ ሲሰረዝ በመጋዘኑ ውስጥ ያሉትን እቃዎች ባለፈቃዱ በራሱ ወጪና ኪሳራ ወደባለስሥልጣኑ መጋዘን እንዲገቡ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው ወደ ባስሥልጣኑ መጋዘን እስከሚዛወርበት ጊዜ ድረስ መጋዘኑ በጉምሩክ ቁልፍ ታሽጐ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን ፈቃድ የሚያሰርዙ ድርጊቶችን ለመፈጸሙ ሲረጋገጥ በተፈጸመው ድርጊት በጉምሩከ ሕግና አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ተገቢው ቅጣት ይፈጸማል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው አንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ(4) እና በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ፈቃዱ የተሰረዘበት በድጋሚ የመጋዘን ሥራ ፈቃድ አይሰጠዉም፡፡

12.<u>የተሻሩ ደንቦችና መመሪያዎች</u>

1. የ1936 ዓ.ም የጉምሩክ(መጋዘን) ደንቦች ቁጥር 47/36
2. ይህን ደንብ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ፣ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

13.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 11 ቀን 1990 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክጠቅላይ ሚኒስቴር**

**ደንብ ቁጥር 37/1990**

**የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድየሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀጽ47 መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 37/1989 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "ዕቃ አስተላላፊነት" ማለት በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይንወይም ዕቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት፡ የወደብ ሥነ-ሥርዐት እና ሌሎች ሥነ-ሥርዓቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች በወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ ሲሆን ዕቃን የማጓጓዝንና የማስረከብን ሥራ ይጨምራል፡፡
   2. "ዕቃ አስተላላፊ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የዕቃ አስተላላፊነት ለመሥራት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡
   3. "ወደብ" ማለት የፌዴራል **ገቢዎች ቦርድ** የሚወስነው ክልል ወይም ቦታ ነው፡፡[5]
   4. "የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ማስፈጸም" ማለት ዕቃ ላኪዎችን ወይም አስመጪዎችን በመወከል በጉምሩክ ጣቢያ ውስጥ ለወጪ ወይም ለገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸም ነው፡፡

[5]በ14/44(2000) አ.587 መሰረት “የገቢዎች ቦርድ” የነበረው በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(19) መሰረትየገቢዎች ሚኒስቴርተተክቷል፡፡

5. "የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት" ማለት ወደ ሀገር የሚገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ ጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እንደአግባብነቱ አስመጪው እስከሚረከበው ወይም ከኢትዮጵያ እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውም ሂደት ነው፡፡
6. "የወደብ ሥነ ሥርዓት ማስፈጸም" ማለት የወጪ ዕቃን በተመለከተ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ በወደብ ዕቃው በመርከብ ላይ እስከሚጫንበት ወይም ገቢ ዕቃን በተመለከተ ዕቃው ከተራገፈ በኋላ ከወደብ እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ ለወጪ ወይም ለገቢ ዕቃ ማናቸውንም ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸም ነው ፡፡
7. "ዕቃዎችን በአንድ ላይ ማቀናጀት" ማለት በአንድ ላይ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ባለንብረቶች ዕቃዎችን በአንድ ሙሉ ኮንቴይነር አንድ ላይ የማሰባሰብ ተግባር ነው፡፡
8. "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
9. "የተቆጣጣሪ ውክልና" ማለት ወደብ ውስጥ ያለ መርከብ ባለንብረትን በመወከል የባለመርከቡን ጥቅም ለመጠበቅ የመርከብ ወኪሉን ሥራ የመቆጣጠር ተግባር ነው፡፡
10. "መርከብ" ማለት ማናቸውም ለማሪታይም ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውል ተንሳፋፊ የጭነት ወይም የሰው ማጓጓዣ መሣሪያ ሲሆን ጀልባን ይጨምራል፡፡
11. "የመርከብ ውክልና" ማለት የመርከብ ባለንብረትን፣ ተከራይን፣ ወይም ኦፕሬተርን በመወከል፤ መርከቡ የሚያጓጉዘውን ዕቃ ወይም መንገደኛ ማግኘትንና መመዝገብን፣ በባህር ወደብ ላይ እና በአገር ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ ለመርከቦች አገልግሎት መስጠትን ዕቃ የመጫንና የማራገፍን፣ እንዲሁም ዕቃን አጓጉዞ የማከማቸትን ሥራ ማስተባበርን ይጨምራል፡፡
12. "የመርከብ ወኪል" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የመርከብ ውክልና ለመሥራት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡
13. "የንግድ ሥራ ፈቃድ" ማለት በዕቃ አስተላላፊነት ወይም በመርከብ ውክልናአገልግሎት ሥራ ለመሠማራት ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር[6] የሚሰጥ ፈቃድነው፡፡
14. "የውጭ ንግድ ረዳት" ማለት በንግድ ሕግ ከአንቀጽ 44 እስከ 62 እንደተተረጎመዉ የንግድ ወኪል፡ የንግድ ደላላ እና የኮሚሽን ወኪል ነው ፡፡

---

[6]በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (7) መሰረት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርበሚል ይነበብ፡፡

3. **<u>የዕቃ አስተላላፊነት ሥራ</u>**

የዕቃ አስተላላፊነት ሥራ የሚከተሉትን ይጨምራል

1. የወደብ ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸም፤
2. የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸም፤
3. ዕቃዎችን በአንድ ላይ አቀናጅቶ የመላክ አገልግሎት መስጠት፤
4. የመጋዘን አገልግሎት መስጠትና ዕቃ የማድረስ፤
5. የዕቃ ማስተናገጃ መሣሪያዎች አገልግሎት መስጠት፤
6. የራሱ ትራንስፖርት ካለው እንደአጓጓዥ ሆኖ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤
7. ባለዕቃው ራሱ ማጓጓዣ ካላቀረበ በስተቀር፡ የራሱ ትራንስፖርት የሌለው እንደሆነየትራንስፖርት አገልግሎት ተከራይቶ ዕቃውን ማጓጓዝ፤
8. የዕቃዎች ማጠን አገልግሎት መስጠት፤
9. ዕቃዎችን ማሸግ፤
10. ሠነዶችን ማዘጋጀትና መስጠት፤
11. የውጭ ንግድ ደንብና የሌተር ኦፍ ክሬዲት ትእዛዞችን ተግባር ላይ ማዋል፤
12. አመቺ ማጓጓዣ መምረጥ የዕቃ ማጓጓዣ ስምምነት መዋዋል፤
13. የዕቃዎችን እንቅስቃሴ መከታተል፤
14. የዕቃ መተላለፍን በተመለከተ ምክር መስጠት።

4. **<u>የመርከብ ዉክልና ሥራ</u>**

የመርከብ ዉክልና ሥራ የሚከተሉትን ይጨምራል፤

1. ከተለያዩ የመርከብ ባለንብረቶች ጋር ግንኙነቶች በማድረግ ለመጫንና ለማራገፍ ስለሚመጡ መርከቦች አስፈላጊ መረጃዎችን በቅድሚያ ማጠናቀር፤
2. መርከቦች በየቀኑ ያሉበትን ሁኔታ በተመለከተ መግለጫ ማውጣትና ለላኪዎችና ላስመጪዎች መላክ፤
3. ለመርከብ ዕቃ የመፈለግ፣ የመደልደልና የማስተባበር አገልግሎት መስጠት ፡
4. የመርከቦችን አመጣጥና አካሔድ ሁኔታ የማቀናጀትና የአገሪቱ የዉጭ ንግድ ዕቃዎች ብቃት ባላቸው አጓጓዦች መስተናገዱን ማረጋገጥ ፤
5. የወጭ ዕቃዎች መርከቡ ወደብ ከመድረሱ በፊት ወደብ ለመድረሳቸው መከታተል፤ ዕቃዎች በመርከብ ላይ በአግባቡ መጫናቸውን ማረጋገጥ፤
6. ዕቃ አስመጪዎች ዕቃቸ ውን እንዲወሰዱ ማስታወቅ፤

7. የወደብ መጨናነቅን እንዲሁም የአገልግሎት መዘግየትን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ አግባብ ያላቸውን አካላት መርዳት፤
8. የመርከብ መከራየትን በተመለከተ ብቃት ያላቸውን መርከቦች ለመከራየት እንዲቻል ድጋፍ መስጠት፤
9. የመርከብ ዕቃ ማጓጓዣ ኪራይ መሰብሰብና የሒሳብ መግለጫ ሠነድ እንዲሁም የገቢና ወጪ መግለጫ ዝግጅት አገልግሎት መስጠት፤
10. የዕቃ መጫንና ማራገፍ አገልግሎት እና የዕቃ ተቆጣጣሪነት ተግባር ማስተባበር፤
11. ወደብ ውስጥ ለመርከቡ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ አገልግሎቶችን ማለት ለመርከቡ ሠራተኞች ምግብ ውሃ የመሳሰሉትን መስጠት ወይም የሚሰጥበትን ሁኔታ ማቀናጀት፤
12. ባሕረኞችን የማቀያየርና ወደ መጡበት የመመለስ አገልግሎት መስጠት፤
13. የመርከብ ዕቃ መጫኛ ሠነድ፣ የዕቃ ማስረከቢያ ሠነድ ማዘጋጀትና መስጠት፣ እንዲሁም ሌሎች የመርከብ ሠነዶችን ማዘጋጀት፤
14. ባለዕቃዎች የሚያቀርቡት የክፍያ ጥያቄ እንዲፈጸም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
15. የተቆጣጣሪ ውክልና አገልግሎት መስጠት፤
16. የኮንቴይነር እንቅስቃሴ መከታተል።

5. <u>ስለፈቃድ አስፈላጊነት</u>

1. ማንኛዉም ሰው የዕቃ አስተላላፊነት ወይም የመርከብ ውክልና አገልግሎት ሥራ ለመሥራት በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ማውጣት ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በውጭ ንግድ ረዳትነት ፈቃድ የመርከብ ውክልናና የዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ለመሥራት በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ማውጣት ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ ደንብ መሠረት የዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ እንደተሰጠው ይቆጠራል።

6. <u>ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶ</u>

1. ለዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ወይም ለመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ ለማግኘት አመልካቹ ፡

ሀ/ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም አንደኛው ወገን ለሚሰጠው ጥቅም ሌላኛው ወገንበተመሳሳይ አጸፋውን የሚሰጥበት ስምምነት ኢትዮጵያ የተፈራረመችበት አገር ሰው፤

ለ/ለዕቃ አስተላላፊነት ከብር 1,500,000፤ ለመርከብ ወኪልነት ከብር 1000,000ሚሊዮን ወይም ሁለቱንም ሥራዎች ለማካሄድ ከብር 2,200,000 ሺህ ያላነሰ መነሻ ካፒታል ያለው፡

ሐ/ እራሱ ወይም የቀጠረው ሰው በኢንተርናሽናል ትራንስፖርት በተለይም በባሕር ትራንስፖርት ሥራ አስፈላጊው የሙያ ዕውቀትና ልምድ ያለው፤ ለዚህም ከትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የችሎታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚያቀርብ፡

መ/በቴሌፎን፣በፋክስ፣ በቴሌክስ እና በሌሎች ለሥራው አስፈላጊ በሆኑ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች የተደራጀ ቢሮ ያለው፤እና

ሠ/ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን መመሥረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ የሚያቀርብ፤

መሆን አለበት፡፡

2. ለዕቃ አስተላላፊነት ሥራ የሚያመለክት አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) የተመለከተውንና ከጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አስተላላፊነት መሥራት የሚያስችለው የችሎታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት ፡፡

3. የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ ያለው አመልካች የችሎታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አያስፈልገዉም።

## 7. <u>የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር[7] ሥልጣን</u>

1. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴርከዚህ በላይ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1)ሐ) ለተጠቀሱት መስፈርቶች መመሪያ ያወጣል።
2. ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) የተጠቀሱትን መስፈርቶች ላሟላ አመልካች የችሎታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 8. <u>የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርሥልጣን</u>

[7]በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (9)መሰረት ትራንስፖርት ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአንቀጽ 6 የተዘረዘሩት ተሟልተው ሲቀርቡለት የዕቃ አስተላላፊነት ወይም የመርከብ ውክልና የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

9. <u>የጉምሩክ ባለሥልጣን[8] ሥልጣን</u>

የጉምሩክ ባለሥልጣን በዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ለሚሠራ ሰው የጉምሩክ አስተላላፊነትን በተመለከተ በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/1986[9] በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) መሠረት የችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

10. <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥልጣን</u>

1. የመርከብ ዕቃ ማስጫኛ ሰነድ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 13 እንደተመለከተው የመርከብ ወኪሉ የሚያዘጋጀውና የሚሰጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣዉ መሰረት ይሆናል፡፡
2. በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ዉክልና ስራ የሚገኘዉን እና የሚወጣውን የዉጭ ምንዛሬ ቁጥጥር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፡፡

11. <u>የችሎታ ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ እና ስለመሰረዝ</u>

አንድ ዕቃ አስተላላፊ ወይም የመርከብ ወኪል ስራዉ የሚጠይቀዉን የሙያ ግዴታ እና ስነ ምግባር ካላከበረ የችሎታ የምስክር ወረቀቱ ምስክር ወረቀቱን በሰጠዉ አካል ሊታገድበት ወይም ሊሰረዝበት ይችላል፡፡ ምስክር ወረቀቱም መሰረዙን ወይም መታገዱን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲያዉቀዉ ይደረጋል፡፡

12. <u>የዕቃ አስተላላፊ ወይም የመርከብ ወኪል ተጠያቂነት</u>

1. ዕቃ አስተላላፊ ወይም የመርከብ ወኪል ተግባሩን በጥንቃቄ ማከናወን አለበት፡፡
2. ዕቃ አስተላላፊዉ ወይም የመርከብ ወኪሉ ተግባሩን ባለማከናወኑ ጥፋት ቢፈፅም በተለይም ዕቃዉ ቢጠፋበት፤ቢጎድልበት ወይም ዕቃዉን በወቅቱ ባያስረክብ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

13. <u>የሌሎች ህጎች ተፈፃሚነት</u>

---

[8] በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (19)የገቢዎች ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[9] በ10/65(1996) ደ.108 ተሻረ፡፡ (አንቀፅ 5 እና 6ን ተመልከት) ፡፡

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር67/1989፣ የጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩንም እንደገና ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 60/1989 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ ህጎች በዚህ ደንብ ላይ እንደአግባቡ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

14. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሰኔ 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 12 ቀን 1990 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክጠቅላይ ሚኒስቴር**

## <u>ደንብ ቁጥር 88/1995 ዓ.ም</u>

## <u>ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ዕቃዎች</u>

   በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉት የሚከተሉት ዕቃዎች ብቻ ናቸው።

   1. የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚሲዮኖች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የዕርዳታ ድርጅቶች ለታወቁ አገልግሎቶች የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፤
   2. የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚሲዮኖች፤ የአለም አቀፍ ድርጅቶችና የዕርዳታ ድርጅቶች ሹማምንቶችና ሠራተኞች ለግልና ለቤት ውስጥ መገልገያ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣
   3. የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች፣ የሲቪል ማኅበራት በስጦታ፣ በዕርዳታ ወይም በልገሳ የሚያስገቧቸው ከሥራቸው ጋር የተያያዘ ለተግባራቸው አጋዥ ዕቃዎች፣

4. የሃይማኖት፣ የትምህርት፣ የሕክምና ወይም የሞያ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ለተቋሞቹ ወይም ለድርጅቶቹ ተግባራት ብቻ የታቀዱ በስጦታ ወይም በዕርዳታ ከውጭ አገር የሚያስገቧቸው ለንግድ የማይውሉ ዕቃዎች፣
5. ለቤተሰብ፣ ለዘመድና ለጓደኛ ከውጭ አገር በስጦታና በልገሳ የሚገቡ ለንግድ የማይውሉ ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች፣
6. በማንኛውም መስክ ላለ ተመራማሪ አግባብ ካለው አካል ማስረጃ የሚያቀርብ፣ ከምርምር ሥራው ጋር የተያያዘ በስጦታና በልገሳ የሚገቡ መሣሪያዎች፣
7. በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ ግለሰቦች የሚያስገቧቸው ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች፣
8. በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ጠቅልለው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች የሚያስገቧቸው የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች እንዲሁም ለግል ሥራቸው የሚያውሏቸውና የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች፣
9. አግባብ ባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙ በውጭ አገር በዘላቂነት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የውጭ ዜግነት ያላቸው የኢትዮጵያ ተወላጅ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ሥራቸው የሚሆን የካፒታል ዕቃ፣ ጥሬ ዕቃ እስከ ኮሚሽኒንግ ደረጃ የሚበቃ እና ለግል መገልገያ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣
10. በስፖርት በኪነትና በመሳሰሉት ለግለሰቦችና ድርጅቶች የሚላኩ ሽልማቶች፣ ለሽያጭ ያልመጡ ለስጦታ ብቻ የሚውሉ ዋንጫዎች ሜዳሊያዎች እና ሌሎች ሽልማቶች፣
11. ወደ ውጭ አገር ለሚላኩ ዕቃዎች በግብአትነት የሚያገለግሉ ዕቃዎች እንደ መለያ፣ ዘሮች እንዲሁም መጠቅለያዎችና እና መያዣዎች የመሳሰሉ፣
12. ለሽያጭ ያልመጡ ስጦታዎች፣ የንግድ ናሙናዎች እና የማስታወቂያ ዕቃዎች፣
13. አገር ውስጥ ገብተው የማይቆዩ በተደጋጋሚ ዕቃ የሚመጣባቸው ኮንቴነሮች፣ ሳጥኖች፣ ጣሳዎች፣ ጠርሙሶች፣ ማድጋዎች እና ሌሎች መያዣዎች፤
14. ለአካል ጉዳተኞች የሚመጡ ወይም የሚላኩ ለንግድ የማይውሉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች፣

15. የጐደሉ ወይም ብልሽት ያለባቸውን ዕቃዎች ለመተካት አቅራቢው ከአስመጪው ጋር ባለው የዋስትና ስምምነት መሠረት የሚገቡ ዕቃዎች፣
16. ለአንድ ተቋም መደበኛ ሥራ እና ለግሰለብ ጤና እጅግ አስፈላጊ የሆኑ በአፋጣኝ ሊገቡ ካልቻሉ ሥራው ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ ወይም ሕይወትንአደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ዕቃዎች፣
17. መንገደኞች ይዘዋቸው የሚመጡት የግል መገልገያዎች፣
18. በጊዜያዊነት ወደ አገር ገብተው ተመልሰው የሚወጡ ዕቃዎች።

3. **የገቢዎች ሚኒስቴር ሥልጣን**[10]
   1. ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ያወጣል፤
   2. ሚኒስቴሩ በቂ ምክንያት ሲኖር በልዩ ሁኔታ ዕቃዎች ያለውጭ ምንዛሪ እንዲገቡ ለመፍቀድ ይችላል።
4. **የተሻረ ደንብ**

   ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 8/1988 በዚህ ደንብ ተሽሯል።
5. **ቅጣት**

   ይህንን ደንብ የጣሰ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡
6. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ ከሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

---

[10] በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (19)የገቢዎች ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

**ደንብ ቁጥር 108/1996**

**የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 60/1989 እንደተሻሻለ በአንቀጽ 90(1) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 108/1996" ተብሎ ሊጠቀስይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   ሀ/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን[11] ነው፡፡

   ለ/ "የፀና ንግድ ሥራ ፈቃድ" ማለት በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ለመስራት ከንግድናኢንዱስትሪ ሚኒስቴር[12] የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

   ሐ/ "የብቃት ማረጋገጫ" ማለት የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ለማከናወን የሚያበቃ የሰው ኃይል እና የቢሮ አደረጃጀት መሟላቱን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው።

   መ/ "የሙያ ማረጋገጫ" ማለት በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ለመሰማራት የሚያስችል

[11] በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (19)የገቢዎች ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[12] በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (7) መሰረት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርበሚል ይነበብ፡፡

በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው።

ሠ/ "የጉምሩክ አስተላላፊ" ማለት በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል ተወስኖ ዕቃዎችን ወደ አገርከማስገባት ከአገር ከማስወጣት በአጠቃላይ ዕቃዎች በጉምሩክ ክልል ውስጥ ከሚኖራቸውእንቅስቃሴና መጋዘን ከሚከማቹበት ሁኔታ ጋር የጉምሩክ ስነሥርዓትስለሌላ ሰው ሆኖ የማስፈጸም ተግባር ለማከናወን የሚያስችል የውክልናሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፡፡

ረ/ "የጉምሩክ ስነ-ሥርዓት" ማለት ወደ አገር የሚገባ፣ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ ከጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እንደአግባብነቱ አስመጪው እስከሚረከበው ወይም ከኢትዮጵያ እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውም የጉምሩክ አፈፃፀም ሂደት ነው፡፡

ሰ/ "የመታወቂያ ማስረጃ" ማለት የጉምሩክ አስተላላፊ በባለሥልጣኑና በጣቢያዎችየጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት መፈጸም እንዲችል ወደ ግቢ ለመግባት የሚያስችለው ማስረጃነው፡፡

ሸ/ “ሰዉ" ማለት የሕግ ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው።

ቀ/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።[13]

በ/ "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989[14] እንደተሻሻለ ነው፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ሥልጠና፣ የሙያ፣ የብቃት ማረጋገጫ፣ የመታወቂያ ማስረጃ አሰጣጥ፣ እገዳ እና ስረዛ</u>

4. <u>ሥልጠና</u>

1. ባለሥልጣኑ

ሀ/ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ

ለ/ ዕድሜው ከ 21 ዓመት ያላነሰ

---

[13] በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (19)የገቢዎች ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[14] ይህ አዋጅ በ15/27(2001) አ.622 የተሻረ ሲሆን 622/2001 በ20/82(2006) አ.859 ተሽሯል፡፡ በመሆኑም በስራ ላይ ያለው የጉምሩክ አዋጅ 20/82(2006) አ.859 ነው፡፡

ሐ/ በማንኛውም የጉምሩክ ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ ሰው፣ በየጊዜው በሚያወጣውየሥልጠና ፕሮግራም መሠረት እየመለመለ በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥልጠና ይሰጣል፡፡

2. ለጉምሩክ አስተላላፊነት ሥልጠና የሚያበቃው የትምህርት ደረጃ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. ባለስልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፡፡
4. ባለሥልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ የጉምሩክ አስተላላፊነት ሙያ ሥልጠና ብቃቱ በተረጋገጠ ተቋም ሥልጠና እንዲሰጥ ማድረግ ይችላል፡፡

5. <u>***የሙያ ማረጋገጫ***</u>

ባለሥልጣኑ የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥልጠናውን በብቃት ላጠናቀቀ ሰልጣኝ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

6. <u>***የብቃት ማረጋገጫ***</u>

ባለስልጣኑ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 10 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟላቱ ለተረጋገጠ ማንኛውም ሰው በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ለመሰማራት የሚያስችለውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

7. <u>***የንግድ ሥራ ፈቃድ***</u>

1. የሙያ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ማንኛውም ሰው በጉምሩክአስተላላፊነት ሥራ ለመስራት የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም በአዋጁ አንቀጽ 86(3) መሰረት ዕቃዎችን ወደ አገር የሚያስገቡ ወይም ከአገር ውጭ የሚልኩ ድርጅቶች ላይተፈጻሚ አይሆንም።

8. <u>***የሙያ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ እና ስለመሰረዝ***</u>

ባለሥልጣኑ ለማንኛውም ሰው የሰጠውን የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

ሀ/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 4 እና 6 ላይ የተደነገጉትን ተፃርሮ ማግኘቱ ከተረጋገጠ

ለ/ ከሙያው ጋር የተዛመዱ ህጎችን መተላለፉ ከተረጋገጠ

ሐ/ በዚህ ደንብ፣ በአዋጁ እና ባለሥልጣኑ በሚያስፈፅማቸው ህጎቹ መሰረት የተጣለበትን ግዴታ ወይም ያለበትን ኃላፊነት ካልተወጣ እንደሁኔታው ለጊዜው ለማገድ ወይም ለመሰረዝ ይችላል፡፡

9. <u>የጉምሩክ አስተላላፊነት መታወቂያ</u>

በባለስልጣኑ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲያወጣ ወይም ከቀጠረው የጉምሩክ አስተላላፊ ድርጅት ሲጠየቅ ወይም በዚህ ደንብ በአንቀጽ 7(2) መሰረት የሚሰራበት ድርጅት ሰራተኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ የመታወቂያ ማስረጃ ይሰጠዋል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርት</u>

10. <u>የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት የሚያበቁ መስፈሮች</u>

1. በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989[15] የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጉምሩክ አስተላላፊነት ስራ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በተጨማሪ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡

   ሀ/ ለሚያከናውነው ሥራ ቋሚ ቢሮ ከበቂ የቴሌፎን፣ የፋክስ የኮምፒዩተር እናተዛማጅ የመገናኛ መሣሪያዎች፣

   ለ/ ማናቸውንም መጻጻፎች የሂሣብና የጉምሩክ ሠነዶችን የሚያስቀምጥበት ሥፍራ፣

   ሐ/ የጉምሩክ ሥነሥርዓት የሚያስፈጽሙ የሙያ ማረጋገጫ ማስረጃ ያላቸው ቢያንስ ሁለት ሠራተኞች እና

   መ/ ባለስልጣኑ በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ በባንክ ሂሳብ ውስጥ እንዲቀመጥ የሚወስነው የገንዘብ መጠን ወይም ተቀባይነት ያለው ዋስትና፡፡

2. <u>የባለስልጣኑ ሥልጣን</u>

   ባለስልጣኑ የመታወቂያ ማስረጃ አሰጣጥ ሁኔታ፣ አጠቃቀም፣ እድሳት፣ እገዳ እና ስረዛ አስመልክቶ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።

---

[15] አሁን በስራ ላይ ያለው ሕግ 22/101(2008) አ.980 ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጉምሩክ አስተላላፊ ኃላፊነትና ግዴታ

### 3. የጉምሩክ አስተላላፊ ኃላፊነት

ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ፡-

ሀ/ የወከለው ደንበኛ ስለሰጠው ሥልጣን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሲጠይቅ ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

ለ/ ደንበኛው በሠነዶች ላይ ማንኛውም ስህተት ወይም ግድፈት በመፈጸም ሕግን አለማክበሩን ካወቀ ሕግ በሚያዘው መሠረት እንዲፈጽም ወዲያውኑ የማማከር ግዴታ አለበት።

ሐ/ የጉምሩክን ሥራ አስመልክቶ ለደንበኛው የሚሰጠው መረጃ ትክክለኛነት ላይ አስፈላጊውን ትጋት የማድረግ ግዴታ አለበት።

መ/ በጉምሩክ በኩል የሚጠየቀውን የቀረጥ፣ የታክስ እና ሌሎች ክፍያዎችን ወዲያውኑ ለጉምሩክ ይከፍላል፣ ለቀረጥና ታክስ ክፍያውም ከደንበኛው ጋር በተናጠል እና በአንድነት ተጠያቂ ይሆናል።

ሠ/ በማንኛውም የጉምሩክ ጣቢያ ላይ የሚሰራን የጉምሩክ ሹም ወይም ፖሊስ ከማስፈራራት፣ ከሐሰት ክስ፣ ከመግባባት ስጦታ፣ ውለታዎችን ወይም ጥቅም ከመስጠት ወይም ለመስጠት ከመሞከር የመታቀብ ግዴታ አለበት።

ረ/ አግባብነት ያላቸውን የጉምሩክ መረጃዎችን ከትክክለኛው ሥርዓት ውጭ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማግኘት፣ ወይም ለማግኘት ከመሞከር የመታቀብ ግዴታ አለበት፡፡

### 4. ማስረጃዎችን መያዝ

1. ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ስላስፈፀመባቸው ጉዳዮችበሙሉ፣ ስላከናወናቸው የገንዘብ እንቅስቃሴዎች፣ ስላደረጋቸው የደብዳቤ ልውውጥ እና በአጠቃላይ ከጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ጋር የተዛመዱ የተሟሉ ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ አለበት።
2. ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን ሠነዶች በማናቸውም ጊዜ በባለሥልጣኑ የጉምሩክ ሹም እንዲታይና እንዲመረመሩ አስፈላጊ ሲሆንም ቅጂዎችን እንዲወስድ የመፍቀድ ግዴታ አለበት።

3. ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ ከስራው ጋር የተዛመዱ ሠነዶችን ለጉምሩክ ስራ አፈጻጸም እስከ አምስት ዓመታት ድረስ ይዞ የማቆየት ግዴታ አለበት።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

5. **ስለ ክፍያዎች**

1. ባለስልጣኑ ለጉምሩክ አስተላላፊዎች ለሚሰጠው የምስክር ወረቀት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወስነው መሰረት ያስከፍላል፡፡
2. ባለስልጣኑ ለጉምሩክ አስተላላፊዎች ለሚሰጠው ቋሚ ያልሆነ ስልጠና ሚኒስቴሩ በመመሪያ በሚወስነው መጠን ያስከፍላል፡፡

6. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከባለስልጣኑ አስቀድሞ አግኝቶ በስራ ላይ በሚገኝ የጉምሩክ አስተላላፊ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

7. **የተሻረ ደንብ**

የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/1986 በዚህ ደንብ ተሽሯል።

8. **መመሪያ ስለማውጣት**

የገቢዎች ሚኒስቴር ይህንን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል።

9. **ቅጣት**

ይህንን ደንብ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡

10. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ 9 ቀን 1996 ዓ/ም

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 567/2000

## ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል በተዘጋጀ ቆዳናሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣ አዋጅ

ጥሬ ቆዳና ሌጦ ብዙም ተጨማሪ እሴት ሳይታከልበት ወደ ዉጭ አገር መላኩ የአገሪቱን አንፃራዊ ጥቅም የሚጎዳ ስለሆነ፣

በቆዳና የቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ጥሬና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ወደ ውጭ ከመላክ ይልቅ ያለቀለትን ቆዳና ሌጦ እና የቆዳ ውጤቶችን እንዲልኩ በማበረታታት ረገድ የታክስ ሥርዓቱ አጋዥ መሣሪያ ሊሆን እንደሚችል ስለታመነበት፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (11) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ «ለዉጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር 567/2000 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፦

   1. "ጥሬ ቆዳና ሌጦ" ማለት ትኩስ ወይም ሳይበላሽ እንዲጠበቅ የተደረገ የበሬ ቆዳ ወይም የፍየልና የበግ ሌጦ ማለት ነው፣

2. "በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ" ማለት የበሬ ጥሬ ቆዳ ወይም የፍየልና የበግ ጥሬ ሌጦን በግብዓትነት በመጠቀም በፒክል ወይም በዌት ብሉ ወይም በልፍ /ክረስት/ ደረጃ ደርሶ የተመረተ ምርት ነው፣
3. "ዌት ብሉ የበሬ ቆዳ" ማለት በክሮም የተለተተ ነገር ግን በዘይት ያልተጠመቀና ያልደረቀ ቆዳ ማለት ነው፣
4. “ፒክል የበግ ሌጦ " ማለት በዉሀ የተበጠበጠ አሲድ /ሰልፈሪክ፣ ፎርሚድ፣ ኃይድሮ ክሎሪክ አሲድ፣...ወዘተ/ እና ጨዉ ተዘፍዝፎ የተጠበቀ፤
5. "ዌት ብሉ የበግ ሌጦ" ማለት በክሮም የተለተተ ነገር ግን በዘይት ያልተጠመቀና ያልደረቀ ሌጦ ነው፣
6. "ዌት ብሉ የፍየል ሌጦ" ማለት በክሮም የተለተተ ነገር ግን በዘይት ያልተጠመቀና ያልደረቀ ሌጦ ነው፣
7. "ታክስ " ማለት በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ወደ ዉጭ በሚላክ ቆዳና ሌጦ ላይ የሚከፈል ታክስ ነው።

3. <u>ታክስ የሚከፈልበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቆዳና ሌጦዎች ወደውጭ አገር በሚላኩበት ጊዜ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ታክስ ይከፈልባቸዋል፦

1. ጥሬ ቆደና ሌጦ፣
2. ዌት ብሉ የበሬ ቆዳ፣
3. ፒክልድ የበግ ሌጦ፣
4. ዌት ብሉ የበግ ሌጦ፣
5. ዌት ብሉ የፍየል ሌጦ፣

4. <u>የማስከፈያ ልክ እና የስሌቱ መሠረት</u>

ወደውጭ አገር የሚላኩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ቆዳና ሌጦዎች በሚከተለው የማስክፈያ ልክታክስ ይከፈልባቸዋል፦

1. ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከዋጋው 150%
2. ዌት ብሉ የበሬ ቆዳ ከዋጋው 20%
3. ፒክል የበግ ሌጦ ከዋው 10%
4. ዌት ብሉ የበግ ሌጦ ከዋጋው 5%
5. ዌት ብሉ የፍየል ሌጦ ከዋጋው 5%

5. <u>የታክሱ አከፋፈል</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን ቆዳና ሌጦዎች ወደ ውጭ አገር የሚልክ ማናቸውም

ሰው ወይም ድርጅት ዕቃዎቹን ከመላኩ በፊት የጉምሩክ ፎርማሊቲን በማጠናቀቅ ታክሱን

መክፈል አለበት፡፡

6. <u>የታክሱ ባለሥልጣን</u>

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን[16] የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989[17] /እንደተሻሻለዉ/ በተደነገገው መሠረት በዚህ አዋጅ የተጣለውን ታክስ ይሰበስባል፡፡

7. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን[18]</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፡

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተመለከተውን የማስከፈያ ልክ ለማሻሻል፤
2. በዚህ አዋጅ ከተወሰነው ታክስ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ የማድረግ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

8. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

ማናቸውም ፀንቶ ያለ ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 በተዘረዘሩ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን ታክስ በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

9. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

በዚህ አዋጅ የተጣለው ታክስ አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት ሌተር ኦፍ ክሬዲት ተከፍቶ ወደውጭ አገር ለመላክ በተዘጋጀ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

10. <u>አዋጁ የሚፀናበት ግዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

---

[16] በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (19)የገቢዎች ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[17] በስራ ላይ ያለው ሕግ 20/82(2006) አ.859 ነው፡፡

[18] በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (4)የገንዘብ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

አዲስ አበባ የካቲት 11ቀን 2000 ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክፕሬዚዳንት

**አዋጅ ቁጥር 768/2004**

**የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ**

የአገሪቱን የኢንዱስትሪ እድገት በማፋጠን የኢኮኖሚ ልማትን ማረጋገጥ እና ለልማትና ኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር እንዲቻል እሴት መጨመር የሚያስችል የምርት ሂደት ሰንሰለትን የሚያጠናክር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የሚሰማሩትን ባለሀብቶች የሚያበረታቱ አዳዲስ ሥርዓቶችን በመዘርጋት እንዲሁም ነባሮቹን በማሻሻል የአገሪቱን ምርቶች በዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ ውስጥ ብቁና ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) እና (11) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፡-

1. "ተመላሽ ቀረጥ" ማለት ወደ ዉጭ ለሚላኩ ሸቀጦች ማምረቻ በሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች እና አላቂ የምርት መገልገያዎች ላይ የተከፈለ እና ሸቀጡ ተመርቶ ወደ ውጭ በሚላከበት ጊዜ ለከፋዩ ተመላሽ የሚደረግ ቀረጥ ነው፤
2. "ቀረጥ" ማለት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ በሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎች፣ ሸቀጦች ወይም አላቂ የምርት መገልገያዎች ላይ የሚከፈል ቀጥተኛ ያልሆነ ማንኛውም ታክስ ወይም ቀረጥ ነው፤
3. "ወደ ውጭ መላክ" ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ ሸቀጦችን መላከ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ ለመሄድ በተዘጋጁ ማጓጓዣዎች ላይ ሸቀጦችን መጫንን ይጨምራል፤
4. "ሸቀጥ" ማለት ወደ አገር በገባበት ሁኔታ ተመልሶ የተላከ ወይም ለውጭ ገበያ እንዲውል የተመረተ ዕቃ ሲሆን ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦችን ለመያዣ፣ ለመጠቅለያ ወይም ለማሸጊያ የሚውለውን ይጨምራል፤
5. "ጥሬ ዕቃ" ማለት በማምረት ወይም በመሥራት ሂደት ውስጥ ተደባልቆ ወይም ተገጣጥሞ ለውጭ ገበያ የሚውል ሸቀጥ ለማምረት የሚውል ዕቃ ሲሆን ለውጭ ገበያ የሚውሉ ሸቀጦችን ለመያዣ፣ ለመጠቅለያ ወይም ለማሸጊያ የሚውለውን ይጨምራል፤
6. "አላቂ የምርት መገልገያ" ማለት በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ወይም በምርት ዓይነት ለውጥ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ የሚሆን ዕቃ ሲሆን ምርቱን ሙሉ ለሙሉ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተቋቋመ አምራች በቀጥታ በማምረት ተግባር ላይ እንዲውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ዘይቶች፣ ቅባቶችና ሌሎች ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገሮችን ይጨምራል፤
7. "ዕቃ" ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲሆን ጥሬ ዕቃን፣ አላቂ የምርት መገልገያን እና ሸቀጥን ይጨምራል፤
8. “ላኪ" ማለት በአገር ውስጥ የተመረቱ ሸቀጦችን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤
9. "አምራች" ማለት አምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ነው፤
10. "አምራች ላኪ" ማለት ያመረተውን ምርት ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

11."ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ" ማለት ያመረተዉን ምርት በጥሬ ዕቃ ወይም በከፊልበተፈበረከ ወይም ባለቀለት ዕቃ መልኩ ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለሌላ ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ፣ ለአምራች ላኪ ወይም ለላኪ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

12."'ጥሬ ዕቃ አቅራቢ" ማለት ከውጭ ያመጣውን ጥሬ ዕቃ በምርት ሂደት ውስጥ እንዲያልፍ ሳያደርግ ባለበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለአምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ላልሆነ አምራች ላኪ የሚያቀርብ ሰው ሲሆን የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነን ሰው አይጨምርም፤

13 "የቫውቸር ደብተር" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ለውጭ ገበያ የሚውሉ ሸቀጦችን ለማምረት ወደ አገር በሚያስገባቸው ወይም ከቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዘን በሚገዛቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የቀረጥ ልክ ለመመዝገብ እንዲያገለግል በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚታተም ሰነድ ነው፤

14 "የግብዓት ምርት ጥምርታ" ማለት በተወሰነ መለኪያ አንድ የወጪ ምርት ለማምረት የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ የምርት መገልገያ ፍጆታ መጠን የሚያሳይ ነው፤

15 "የአጠቃላይ ኢንዱስትሪ ተመላሽ ቀረጥ ምጣኔ" ማለት አንድን የወጪ ምርት ለማምረት የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ አማካይ ፍጆታ በመለየት በእነዚህ ላይ የተከፈለውን ቀረጥ ምርቱ ለውጭ ገበያ ከቀረበበት የፎብ ዋጋ አንፃር በማስላት ተመላሽ የሚደረግበት የመቶኛ ምጣኔ ነው፤

16 "ቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ" ማለት ለምርት አገልግሎት ከቀረጥ ነጻ የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀም ያመረተውን ምርት ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቁጥጥር የሚደረግበት ፋብሪካ ነው፤

17 "ቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን" ማለት ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ምርት ማምረቻ የሚውሉ ከቀረጥ ነጻ ሆነው የገቡ ጥሬ ዕቃዎችና በእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱ ምርቶች የሚቀመጡበትና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና በፋብሪካው በጋራ ቁጥጥር የሚደረግበት መጋዘን ነው፤

18 "ቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዘን" ማለት ፈቃድ በተሰጠው አቅራቢ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ የምርት መገልገያ ለአምራቾች እስከሚሸጥ

ድረስ የሚቀመጥበት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና በአቅራቢው ቁጥጥር የሚደረግበት መጋዘን ነው፤

19 "ኢንዱስትሪ ቀጠና" ማለት ማናቸውም የተቀናጀ መሠረተ ልማት የተሟላለትና የፖሊሲ ማበረታቻዎች ያሉት ለኢንዱስትሪ የተከለለ ቦታ ነው፤

20 "ቀጥተኛ ላኪ" ማለት አምራች ላኪ ወይም ላኪ ነው፤

21 "ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ" ማለት ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ነው፤

22 "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

23 ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶች**

1. የሚከተሉት የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

ሀ/ የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት፤

ለ/ የቫውቸር ሥርዓት፤

ሐ/ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት፣

መ/ የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘንሥርዓት፤

ሠ/ የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘንሥርዓት፤እና

ረ/ የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት፡፡

2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት ተጨማሪ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት በሥራ ላይ እንዲውል ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት

4. **የስርዓቱ ተጠቃሚዎች**

የተመላሽ ቀረጥ ስርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት የሚከተሉት ይሆናሉ፡

1. አምራች ላኪዎች፤
2. ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፤
3. ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች፤ እና
4. ላኪዎች፡፡

5. **ቀረጥን ተመላሽ ስለማድረግ**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተመለከቱት የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ከውጭሚያስመጧቸው ወይም በአገር ውስጥ በሚገዟቸው ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ቀረጥ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[19] በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የተከፈለው ቀረጥ ልክ ከብር 1000 በታች ከሆነ ተመላሽ አይደረግም።
   3. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ገንዘብ የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄው ተሟልቶ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ ለመብቱ ተጠቃሚ ተመላሽ ያደርጋል፡፡
   4. ለተመሳሽ ቀረጥ የሚውለው በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

5. **<u>የተመላሽ ቀረጥ ልክ</u>**

1. የወጭ ምርት ለማምረት በጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎችንና አላቂ የምርት መገልገያዎችን በሚመለከት ተመላሽ የሚደረገው ቀረጥ መጠን በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ የተመላሽ ቀረጥ ምጣኔ መሰረት የሚሰላ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የአጠቃላይ የኢንዱስትሪ የተመላሽ ቀረጥ ምጣኔ በሥራ ላይ እስከሚውል ድረስ ተመላሽ የሚደረገው ቀረጥ መጠን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22(2) መሠረት በሚወሰነው የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ ተመሥርቶ ይሰላል።

6. **<u>የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ አቀራረብ</u>**

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ አቀራረብንና ተያይዘው መቅረብ የሚገባቸዉን ማስረጃዎች የሚመለከት መመሪያ ያወጣል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የቫዉቸር ስርዓት</u>

7. **<u>የስርዓቱ ተጠቃሚዎች</u>**

የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው የሚከተሉት ሰዎች ይሆናሉ፡-

---

[19] በ28/8 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9 (4)የገንዘብ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

1. አምራች ላኪዎች፤
2. ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፤እና
3. ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች።

8. <u>የቫዉቸር ስርዓት ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች</u>

1. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በቫዉቸር ስርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚችሉ የስርዓቱ ተጠቃሚዎች መሟላት የሚገባቸዉን ቅድመ ሁኔታዎች የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገዉ ቢኖርም የሥርዓቱ ተጠቃሚ ጥሬ ዕቃዎችን አቅራቢዎች በሚሰጡት ዱቤ ወይም በፍራንከ ቫሉታ ወደ አገር የሚያስገባ ከሆነ፡-

   ሀ/ተፈላጊው ምርት በአገር ውስጥ ከተመረተ በኋላ የምርቱ ተቀባይ መኖሩን የሚያረጋግጥከገዢው የተላከ ትዕዛዝ ወይም ከገዢው ጋር የተደረገ ውል ማቅረብ የሚችል፤ ወይም

   ለ/ ጥሬ ዕቃው የወጪ ምርቶችን ለማምረት ውጭ አገር ከሚገኝ ተባባሪ ኩባንያ የተላከለት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

   መሆን አለበት፡፡

9. <u>የቫዉቸር ስርዓት አፈፃፀም</u>

1. በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሰዎች በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቫውቸር ደብተር ይሰጣቸዋል።
2. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ አገር በሚያስገቡት ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው

   ቀረጥናታክስ በቫውቸር ደብተሩ ላይ ተመዝግቦ ዕቃውን እንዲረከቡ ይደረጋል፡፡
3. በቫውቸር ሥርዓት ወደ አገር የገባ ጥሬ ዕቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ መላክ አለበት፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሲፈቅድ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት

የሚፈልግ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የመጠቀሚያው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሠረት ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ 50 በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
6. ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች በቫውቸር ሥርዓት ተጠቅመው ዕቃዎችን ወደአገር ማስገባት የሚችሉት በሚያስገቡት ዕቃ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የኢንሹራንስ ቦንድ ሲያቀርቡ ይሆናል፡፡
7. የኢትዩጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የቫውቸር ስርዓት የጉምሩክ ሥርዓት አፈፃፀምን፣ የቫውቸር ደብተር ይዘትን እና የቫውቸር ደብተር ጥያቄ አቀራረብን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት</u>

### 10.<u>የስርዓቱ ተጠቃሚዎች</u>

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ስርዓት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት፡-

   ሀ/ ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ፣

   ለ/በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀትየተሰጣቸው፣ እና

   ሐ/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ የማምረቻ ፋብሪካ ያላቸው፣

   ሰዎች ይሆናሉ።
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገባቸዉ መስፈርቶችን፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጠቃሚዎቹ የማምረቻ ፋብሪካዎች ሊያሟሏቸዉ የሚገቡ መስፈርቶችን የሚወስኑ መመሪያዎችን ያወጣሉ፡፡

### 11.<u>የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ስርዓት አፈፃፀም</u>

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደ አገር ያስገባዉ ጥሬ ዕቃ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ወደ ፋብሪካው ይጓጓዛል፡፡
2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወደ ቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ የሚገባውን ጥሬ ዕቃ እና ከፋብሪካው ለውጭ ገበያ የሚላከውን ምርት ይቆጣጠራል።
3. በቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ወደ አገር የገባ ጥሬ ዕቃ ወደ ፋብሪካው ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ መላክአለበት፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ ማንኛውም የሥርዓቱ ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የመጠቀሚያው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሠረት ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ 50 በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
6. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ ተጨማሪ መስፈርቶችን፣ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሥርዓትን እና የሥርዓቱን አፈፃፀም የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት

### 12.የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

1. የኢንዱትሪ ቀጠና ስርዓት ተጠቃሚዎች የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚያወጣውን መስፈርት የሚያሟሉ በኢንዱስትሪ ቀጠና ውስጥ የሚቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች ይሆናሉ።
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉ ኢንዱስትሪዎች ሊያሟሏዋቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

13.<u>የስርዓቱ አፈፃፀም</u>

1. የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደ አገር ያስገባው ጥሬ ዕቃ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ከጉምሩክ ጣቢያዎች ወደ ኢንዱስትሪው ቀጠና ይጓጓዛል፡፡
2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገባውን ጥሬ ዕቃ እና በኢንዱስትሪ ቀጠናው ተመርቶ ለውጭ እና ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርበውን ምርት ይቆጣጠራል።
3. በኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ወደ አገር የገባ ጥሬ ዕቃ ወደ ኢንዱስትሪው ቀጠና ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ወይም ለአገር ውስጥ ገበያ መቅረብ አለበት፡፡
4. የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰዉ፡-

   ሀ/ ካመረተው ሸቀጥ ውስጥ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውንና ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውለውን ለይቶ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማሳወቅ፤ እና

   ለ/ ለውጭ ገበያ እንዲውል ከኢንዱስትሪው ቀጠና የወጣው ምርት ለውጭ ገበያ መላኩንየሚያሳይ መረጃ ምርቱ ከኢንዱስትሪው ቀጠና በወጣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቅረብ፤

   አለበት፡፡
5. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአጠቃላይ ኢንዱስትሪ ተመላሽ ቀረጥ ምጣኔን መሠረት በማድረግ በኢንዱስትሪ ቀጠና ተመርቶ ለአገር ውስጥ ገበያ በሚውለው ምርት ላይ ምርቱ ከኢንዱስትሪው መንደር ከመውጣቱ በፊት ቀረጥ ያስከፍላል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ ማንኛውም የሥርዓቱ ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት ሲያመለክት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ የጊዜ ገደቡን ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝምለት ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የመጠቀሚያ የጊዜ ገደብ ያልተራዘመለት የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና በተጨማሪም የቀረጡን 50 በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል።

8. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንየኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት አፈፃፀምን የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት

### 14.የስርዓቱ ተጠቃሚዎች

1. በቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት መጠቀም የሚችሉት ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው እና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚወጣውን መስፈርት የሚያሟሉ የማምረቻ መጋዘኖች ያሏቸው አምራቾች ይሆናሉ።
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችለውን የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶችን፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጠቃሚዎቹ የማምረቻመጋዘኖች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የሚወስኑ መመሪያዎችን ያወጣሉ፡፡

### 15.የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ስርዓት አፈፃፀም

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደ አገር ያስገባዉ ጥሬ ዕቃ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ወደ ማምረቻ መጋዘኑ ይጓጓዛል፡፡
2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወደ ቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን የሚገባውንና ከመጋዘኑ የሚወጣውን ጥሬ ዕቃ እንዲሁም በፋብሪካው ተመርቶ ወደ ማምረቻ መጋዘኑ የሚገባውንና ከመጋዘኑ የሚወጣውን ምርት ይቆጣጠራል።
3. ወደ ቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን የገባ ጥሬ ዕቃ ወደ መጋዘኑ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ

መላክ አለበት፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሠረት ታክሱን ከፍሎ አገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና በተጨማሪም የቀረጡን 50 በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል።
6. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት አፈፃፀምን የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ስርዓት

### 16.የስርዓቱ ተጠቃሚዎች

1. የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የሰጣቸው እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ መጋዘን ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ።
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶችን፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጠቃሚዎቹ የግብዓት አቅርቦት መጋዘኖች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የሚወስኑ መመሪያዎችን ያወጣሉ።

### 17.የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓትአፈፃፀም

1. የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ አገር የሚያስገቡት ግብዓት ከቀረጥ ነፃ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ከጉምሩክ ጣቢያዎች ወደ መጋዘኑ ይጓጓዛል፡፡

2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወደ ቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን የሚገባውን እና ከመጋዘኑ የሚወጣውን ግብዓት ይቆጣጠራል።
3. በቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ወደ አገር የገባ ግብዓት ወደ መጋዘን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ለአምራች ካልተላለፈ የሥርዓቱ ተጠቃሚ በግብዓቱ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና በተጨማሪም የቀረጡን 50 በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የግብዓቱን ባህሪ መሠረት በማድረግ የጊዜ ገደቡ ለተጨማሪ አንድ አመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ አምራች ላኪዎችና ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች በግብዓቱ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ በቫውቸር ደብተር ላይ እንዲመዘገብ በማድረግ ከቦንድድ ግብዓት መጋዘን ግብዓቶችን መግዛት ይችላሉ፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓትን አፈፃፀም በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 18.<u>የንግድ ድርጅት ባለቤትነት መተላለፍ</u>

1. በዚህ አዋጅ የተዘረጋው የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ድርጅቱን በማንኛውም ሁኔታ ለሌላ ወገን ሲያስተላልፍ በሥርዓቱ ተጠቅሞ ላስገባቸው ጥሬ ዕቃዎች ደጋፊ ሰነዶችን አቅርቦ የቀረጥና ታክስ ሂሳቡን ማወራረድ አለበት፡፡
2. ተተኪው ባለቤት የሥርዓቱ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልግ ከሆነ ለሚመለከተው አካል አመልክቶ በዚህ አዋጅ መሰረት አዲስ የምስክር ወረቀት ማውጣት ይኖርበታል፡፡

### 19.<u>በአገር ዉስጥ ስለሚገዙ ጥሬ ዕቃዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18(4) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ በተፈቀዱ የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶች ተጠቃሚ የሆኑ አምራች ላኪዎችና ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች በአገር ውስጥ በሚገዟቸዉ ጥሬ ዕቃችዎች ላይ ቀረጥ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም የከፈሉት ቀረጥ በተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት መሠረት እንዲመለስላቸዉ የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል።

2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተከፈለውን ቀረጥ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣዉ የተፋጠነ ስነ ስርዓት መሰረት ተመላሽ ያደርጋል፡፡

20.**ጥሬ ዕቃና ምርትን ስለማስተላለፍና የቀረጥ ሂሳብን ስለማወራረድ**

1. ከቀረጥ ነጻ ሆኖ በገባ ጥሬ ዕቃ የተመረተ ሸቀጥ በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ውጭ የተላከ እንደሆነ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ ይወራረዳል፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ የሆነ ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ጥሬ ዕቃ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ለሆነ አምራች ካስተላለፈ ጥሬ ዕቃውን በመጠቀም የተመረተን ሸቀጥ ወደ ውጭ እንደላከ ተቆጥሮ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ ሂሣብ ይወራረድለታል፡፡
3. በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ የሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወደ አገር ያስገባውን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተረከበውን ጥሬ ዕቃ ተጠቅሞ ያመረተውን ምርት ጥሬ ዕቃውን በተረከበ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ፡-

   ሀ/ በግብዓትነት ለሚጠቀምበት ተመሣሣይ መብት ላለው ለሌላ ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ወይም ለአምራች ላኪ ያስተላለፈ፤ ወይም

   ለ/ በሸቀጥነት ለላኪ ያስተላለፈ፤

   እንደሆነ ጥሬ ዕቃውን በመጠቀም የተመረተን ሸቀጥ ወደ ውጭ እንደላከ ተቆጥሮ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ ሂሣብ ይወራረድለታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ለግብዓትነት የሚውል ምርት የተላለፈለት አምራች ግብዓቱን ተጠቅሞ ያመረተውን ሸቀጥ በአንድ ዓመት ውስጥ እንደ አግባቡ ወደ ውጭ ከላከ ወይም ካስተላለፈ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ ይወራረድለታል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት ምርት የተላለፈለት ላኪ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርቱን ወደ ውጭ የመላክ ኃላፊነት አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ መሠረት ጥሬ ዕቃ ወይም ምርት የተላለፈለት ሰው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ኃላፊነቱን ካልተወጣ በስተቀር አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ቀረጡን ከነቅጣቱ ይከፍላል።
7. በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀረጥ ሂሳብ የሚወራረድበት ሥርዓት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

21.<u>**የግብዓት ምርት ጥመርታ እና የአጠቃላይ የኢንዱስትሪ የተመላሽ ቀረጥ ምጣኔ**</u>

1. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የግብዓት ምርት ጥመርታን መመሪያ አውጥቶ ሥራ ላይ ያዉላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የግብዓት ምርት ጥመርታ መመሪያ ሥራ ላይ እስከሚውል ድረስ ላኪዎች ወይም አምራቾች የሚያቀርቡት የግብዓት ምርት ጥመርታ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እየታየ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡
3. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የግብዓት ምርት ጥመርታ መመሪያ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የአጠቃላይ ኢንዱስትሪ ቀረጥ ምጣኔን መመሪያ አውጥቶ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

22.<u>**በምርት ሂደት ውስጥ ስለሚባክን ጥሬ ዕቃ**</u>

1. ለወጪ ንግድ ዕቃዎች ማምረቻ የዋለው ጥሬ ዕቃ ወይም ጥሬ ዕቃውን ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለው ጥሬ ዕቃ መጠን በሚሰላበት ጊዜ በምርት ሂደት ውስጥ የባከነው ወይም የተበላሸው ግምት ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡
2. አምራቹ በምርት ሂደት ውስጥ በባከነዉ ጥሬ ዕቃ እና ተረፈ ምርት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ ከፍሎ የባከነውን ጥሬ ዕቃ እና ተረፈ ምርት አገር ውስጥ መሸጥ ይችላል፡፡
3. በምርት ሂደት ጉድለት የተገኘባቸው ምርቶች ለውጭ ገበያ መላክ የማይችሉ መሆኑ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲረጋገጥ ተገቢው ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሆኖ አገር ውስጥ ሲሸጡ ይችላሉ፡፡

23.<u>**ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ወይም ምርቶች አጠቃቀም የግዜ ገደብ ስለማራዘም**</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቀረጥ ያልተከፈለባቸው ጥሬ ዕቃዎች ወይም ምርቶች በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለው ለውጭ ገበያ ካልተላኩ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 መሠረት ካልተላለፉ የጊዜ ገደቡን ለተጨማሪ አንድ ዓመት ማራዘም የሚቻልበትን ሥርዓት የሚመለከት መመሪያ ያወጣል።

24.**<u>በአገር ዉስጥ ስለመሸጥ</u>**

1. አምራቹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የማምረት ወይም የመላክ ንግድ ሥራውን ያቋረጠ እንደሆነ ወይም የተረከበው ጥሬ ዕቃ ወይም ምርት ለወጪ ምርት ደረጃውን ያልጠበቀ በመሆኑ ወይም ለምርት ተግባር እንዳይውል የሚከለክሉ ነገሮች ሲያጋጥሙት ወይም ምርቱ ከተላከ በኋላ ጉድለት ኖሮት ቢመለስ ለዚህም ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንን በማስፈቀድ ቀረጡን ከፍሎ ጥሬ ዕቃውን ወይም ምርቱን በአገር ውስጥ መሸጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከተው ውጭ ቀረጥ ያልተከፈለበትን ጥሬ ዕቃ ወይም ጥሬ ዕቃውን በመጠቀም የተመረተ ምርትን በአገር ውስጥ መሸጥ የሚቻለው አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ቀረጡ ከነቅጣቱ ከተከፈለ በኋላ ይሆናል፡፡

25.**<u>ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎችና ምርቶች አጠቃቀም የግዜ ገደብን በተደጋጋሚ አለማክበር</u>**

ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ወይም ምርቶች ተጠቅሞ ያመረተውን ምርት ወደ ውጭ ለመላክ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 መሠረት ለማስተላለፍ የተፈቀደለትን የማራዘሚያ ጊዜ ጨምሮ የተወሰነውን የጊዜ ገደብ በተከታታይ ለሦስተኛ ጊዜ ያላከበረ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ በሥርዓቱ የመጠቀም መብቱን ያጣል።

26.**<u>ወደአገር የገባን ሸቀጥ ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ መጣበት ስለመመለስ</u>**

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ የገቡ ጥሬ ዕቃዎችና ምርቶች በግዥ ትዕዛዙ የተመለከተውን ስፔስፊኬሽን የማያሟሉ፣ የተበላሹ፣ የጎደሉ ወይም በገበያ ተፈላጊ የሆነ ምርት ሊመረትባቸው የማይችልና ተጠቃሚው ወደ መጡበት አገር መልሶ የሚልክ ከሆነ ሳይከፈል የቀረው ቀረጥ 5

በመቶ ይከፈልባቸዋል፡፡ በተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት የገቡ ከሆነ ግን በተመለሰው ጥሬ ዕቃ ወይም ምርት መጠን ተሰልቶ ከተከፈለው ቀረጥ ላይ 95 በመቶ ይመለሳል፡፡

27.**<u>ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ላይ የተጣለ ገደብ</u>**

1. በዚህ አዋጅ በተዘረጋው የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ጥሬ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር ማስገባት ወይም በእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ላይ የከፈለው ቀረጥ እንዲመለስለት መጠየቅ የሚችለው ወደ አገር ከሚገባው ጥሬ ዕቃ ጋር በጥራት ተመሳሳዩ በአገር ውስጥ የማይገኝ ከሆነ ነው፡፡
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም ሥርዓት የሚደነግግ መመሪያ ያወጣል።

28.**<u>የወንጀል ጥፋቶችና ቅጣቶች</u>**

1. ማንኛውም ሰው ቀረጥ ላለመክፈል ወይም አሳንሶ እንዲከፈል ለማድረግ ስለአመራረቱ ወይም ስለሸቀጡ ዋጋ ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ፣ ትክክለኛ ያልሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ወይም ደጋፊ ሰነዶችን ያቀረበ፣ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የደበቀ ወይም የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን አፈፃፀም በማናቸውም ሁኔታ ያደናቀፈ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ፡-

   ሀ/ ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 30,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

   ለ/ ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ከስድስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 60,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

   ሐ/ ጥፋቱ ለሦስተኛ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ከዘጠኝ እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 90,000 እስከ ብር 150,000በሚደርስ መቀጮ ተቀጥቶ የቀረጥ ማበረታቻ መብቱ ይሰረዛል፡፡

2. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ያስገባውን ጥሬ ዕቃ ወይም በዚህ ጥሬ ዕቃ ያመረተውን ሸቀጥ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉት ሥርዓቶች ውጭ በአገር ውስጥ ገበያ ላይ ከሸጠ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሰባት እስከ አሥራ አምስት

ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 70,000 እስከ ብር 150,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ 587/2000 አንቀጽ 6(10) የተሰጠው ወንጀልን የመመርመር እና በፍርድ ቤት የወንጀል ክስ የማቅረብና የመከራከር ሥልጣን በዚህ አንቀጽ ለተደነገጉት የወንጀል ጉዳዮችም ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## 29. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች

1. የተሻሻለው የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 543/1999 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልማድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 30.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በቀድሞው የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ መሠረት ተጀምረው ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ፍፃሜ ያላገኙ ሽቀጦችን ወደውጭ ከመላክ ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተገናኙ የጥሬ ዕቃ እና የሽቀጥ አቅርቦት ግብይቶች በቀድሞው አዋጅ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 የተደነገገዉ ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ወደ አገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን ወይም ጥሬ ዕቃዎቹን በመጠቀም የተመረቱ ምርቶችን ማስተላለፍን በተመለከተ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 31.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ በግልጽ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለሌሎች መንግሥታዊ አካላት የተሰጠው መመሪያ የማውጣት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 32.አዋጁ የሚፀናበት ግዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 29 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 859/2006

## የጉምሩክ አዋጅ

ዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣምና በአገራችን እያደገ የመጣውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍ እንዲሁም ሕጋዊ ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ዘመናዊ የጉምሩክ ሕግ ማዕቀፍ ስራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

አገሪቱ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና አካባቢያዊ የንግድ ስምምነቶች ወቅታዊ የጉምሩክ ሕግና የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር የሚያስገድዱ በመሆናቸው፤

ኮንትሮባንድና ሌሎች የንግድ ማጭበርበር ወንጀሎች በሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴ፣ በሕዝብ ደህንነት፣ በመንግስት ገቢና በሌሎችም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቶች ላይ የሚያስከትሉትንና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል የተጠናከረ የሕግ ማስከበሪያ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የጉምሩክ አዋጅ 859/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**[20]

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

[20]የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (49)፤ (52)፣ (54) እና (55)በ25/92 (2006) አ. 1160 አንቀጽ 2(1) ተሻሻለ

1. "ዕቃ" ማለት ማናቸውም ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲሆን ግዙፍነት የሌላቸው በሕግ እንደተንቀሳቃሽ ንብረት የሚታወቁትን ንብረቶች፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን በአገልግሎት ላይ የዋሉ የተፈጥሮ ኃይልንና ሀብቶችን የሚያካትት ሲሆን ገንዘብን ይጨምራል፤
2. "ጭነት" ማለት በማናቸውም የማጓጓዣ ዓይነት ወደ አገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ዕቃ ሲሆን የንግድ ማጓጓዣ የጉዞ ዕቃ ክምችትንና የመንገደኞች ሻንጣዎችን አይጨምርም፤
3. "ቀረጥ" ማለት ይህን አዋጅና የዓለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓትን ተከትሎ በወጣው የጉምሩክ የታሪፍ ደንብ መሠረት በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፤
4. "ታክስ" ማለት ፀንተው በሥራ ላይ ባሉ የታክስ ሕጎች መሠረት በገቢና በወጪ ዕቃዎች ላይ እየተጣለ የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፤
5. "ዕቃ ወደ አገር ማስገባት" ማለት ማናቸውንም ገቢ ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማምጣት ወይም እንዲገባ ማድረግ ነው፤
6. "ዕቃ ወደ ውጭ አገር መላክ" ማለት ማናቸውንም ዕቃ ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ወይም እንዲወጣ ማድረግ ነው፤
7. "የጉምሩክ ክልል" ማለት የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ነው፤
8. "የጉምሩክ ጣቢያ" ማለት በመግቢያና በመውጫ ወደብ ወይም በመተላለፊያ መንገድ ወይም በጉምሩክ ክልል የሚገኝ በገቢና በወጪ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቁጥጥርና ሥነ ሥርዓት የሚፈፀምበት እና ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ሥፍራ ነው፤
9. "የጉምሩክ መጋዘን" ማለት ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻን፣ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘንን እና የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘንን ይጨምራል፤
10. "ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ" ማለት፡-

    ሀ/ ገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ስርዓት አፈጻጸም ተከናውኖባቸው እስከሚለቀቁወይም እንደሁኔታው ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ወይም ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እስኪዛወሩ፣ እና

    ለ/ ወጪ እና ተላላፊ እቃዎች አግባብነት ያለው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም እስከሚከናወንባቸው ወይም አንደሁኔታው ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ወይም

ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እስከሚዛወሩ፣

በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነው የሚቆዩበት ዝግ ወይም ክፍት የእቃ ማከማቻ ሥፍራ ሲሆን ደረቅ ወደብን ይጨምራል፡፡

11."ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን" ማለት ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸውና የጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረገባቸው የሚከማቹበት መጋዘን ሲሆን የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብሮችን እና ቦንድድ ፋብሪካዎችን ይጨምራል፤

12."ቦንድድ ፋብሪካ" ማለት ጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረገበት ለምርት አገልግሎት ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ጥሬ ዕቃዎችንና ግብዓቶችን በመጠቀም እቃዎችን የሚያመርት ፋብሪካ ነው፤

13."የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን" ማለት የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ የተያዙ ወይም የተወረሱ እንዲሁም የተተው እቃዎች በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ እስከሚወገዱበት ጊዜ ድረስ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የሚከማቹበት መጋዘን ነው፤

14."የመጋዘን ኃላፊ" ማለት የጉምሩክ መጋዘንን የሚያስተዳድር ሰው ነው፤

15."ማጓጓዣ" ማለት በየብስ፣ በአየር ወይም በውሃ ላይ ሰውን ወይም ዕቃን የሚያጓጉዝ ማንኛውም የማጓጓዣ ዘዴ ሲሆን እንስሳትን፣ የኤሌክትሪክ መስመሮችንና የፈሳሽ ማስተላለፊያዎችን ይጨምራል፤

16."አጓጓዥ" ማለት ዕቃን በማጓጓዝ ላይ ያለ ወይም የማጓጓዣውን እንቅስቃሴ የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው፤

17."የመተላለፊያ መሥመር" ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ገቢና ወጪ ዕቃዎች እንዲጓጓዙበት በባለሥልጣኑ የተወሰነ ማናቸውም መንገድ ነው፤

18."የጉምሩክ አስተላላፊ" ማለት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣ ደንብ መሠረት የጉምሩክ አስተላላፊነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሆን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትን ለማስፈጸም የሚያስችል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በባለስልጣኑ የተሰጠውን የዲክላራሲዮን አቅራቢ ሠራተኛ ይጨምራል፤

19."ማጓጓዣ በመቀየር ዕቃን ማጓጓዝ" ማለት ዕቃን ጭኖ ወደ ጉምሩክ ወደብ ከገባ ማጓጓዣ ዕቃውን ከዚያው ወደብ ጭኖ ከአገር ወደሚወጣ ሌላ ማጓጓዣ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆኖ የሚተላለፍበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ነዉ፤

20."የዕቃ ዲክላራሲዮን" ማለት ወደ አገር የሚገቡ፣ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ወይም ተላላፊ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትና ለአፈጻጸሙ ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸውን ዝርዝሮች አስመልክቶ በዲክላራሲዮን አቅራቢ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚሰጥ መግለጫ ነው፤

21."የዲክላራሲዮን አቅራቢ" ማለት የዕቃ ዲክላራሲዮን የሚያቀርብ ወይም የዕቃ ዲክላራሲዮን በስሙ የሚቀርብለት ማንኛውም ሰው ነው፤

22."የጉምሩክ ሥነሥርዓት" ማለት የጉምሩክ ሕግን ለማክበር በሚመለከታቸው ሰዎችና በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የጉምሩክ ሂደቶችን ያጠቃልላል፤

23."የኤሌክትሮኒክ ፊርማ" ማለት የኤሌክትሮኒክ መዝገቦች ወይም ሰነዶች ትክክለኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ በዚህ አዋጅ ወይም ተጠቃሚው በገባው ስምምነት ላይ በተቀመጡ መመዘኛዎች መሰረት ለተመዘገቡ ተጠቃሚዎች የሚፈቀድ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፤

24."ለንግድ ዓላማ የማይውል ዕቃ" ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ በሚኒስቴሩ መመሪያ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ሆኖ ለአስመጪው ወይም ለባለይዞታው ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ ወይም ፍጆታ የሚውል ዕቃ ወይም የስጦታ ቁሳቁስ ነው፤

25."ሰነድ" ማለት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀምን ለማከናወን በአካል ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የሚቀርብ ማናቸውም ሰነድ ነው፤

26."የዋጋ ሰነድ" ማለት በአምራች ወይም በአቅራቢ የተሰጠ ስለዕቃ ዋጋ የሚገልፅ ሰነድ ነው፤

27."አንድ ዓይነት ዕቃዎች" ማለት በአካላዊ ባህሪያቸው፣ በጥራታቸውና በተፈላጊነታቸው አንድ የሆኑና በአንድ አገር የተመረቱ ዕቃዎች ናቸው፤

28."ተመሳሳይ ዕቃዎች" ማለት በሁሉም አንፃር ባይመሳሰሉም ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው፣ ከተመሳሳይ ማቴሪያል የተመረቱ፣ ተመሳሳይ ተግባር ማከናወንየሚችሉና ተመሳሳይ የገበያ ተፈላጊነት ያላቸው ዕቃዎች ሲሆኑ ጥራታቸው፣ በአንድ አገር የተመረቱ መሆናቸው፣ ተፈላጊነታቸውና የንግድ ምልክታቸውስለተመሳሳይነታቸው ከግምት ውስጥ ይገባል፤

29."ዕቃ ማስወገድ" ማለት ማናቸውንም ዕቃ በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ወይ በማቃጠል ወይም በሌላ መንገድ እንዲወድም ማድረግነው፤

30."የተከለከለ ዕቃ" ማለት በኢትዮጵያ ሕግ ወይም ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ወደ አገር እንዳይገባ ወይም ከአገር እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ የተከለከለ ማንኛውም ዕቃ ነው፤

31. "ገደብ የተደረገበት ዕቃ" ማለት በሕግ በተደነገገ ሥነ ሥርዓት መሠረት ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ወደ አገር እንዳይገባ ወይም ከአገር እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ ገደብ የተደረገበት ዕቃ ነው፤

32. "የጭነት መግለጫ" ማለት የዕቃ ላኪን፣ ተቀባይን፣ ምልክትን፣ ዕሽግ ቁጥርን፣ ዓይነትን፣ ብዛትን፣ ክብደትን፣ የጭነት ዲክላራሲዮን ቁጥርንና የመሳሰሉትንዝርዝሮች የሚያመለክት ሰነድ ነው፤

33."ማካካሻ ምርት" ማለት የምርት ሂደቱ በአገር ውስጥ ተጠናቆ እንዲወጣ ወይም የምርት ሂደቱ በውጭ አገር ተጠናቆ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባና ለነጻ ዝውውር እንዲለቀቅ በተፈቀዱ አሰራሮች መሰረት የተመረተ ወይም ጥገና የተደረገበት ምርት ነው፤

34. "የስሪት አገር የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ ዕቃ ስለተመረተበት አገር ትክክለኛነት በተመረተበት አገር ሥልጣን ባለው አካል የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰነድነው፤

35. "የስሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች" ማለት በዓለም አቀፍ፣ በአካባቢያዊ ወይም በሁለትዮሽ የንግድ ስምምነቶችመሠረት ዕቃዎች የተሠሩበትን አገርለመወሰን የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓትና መመዘኛ ነዉ፤

36. "ኮንቴይነር" ማለት ዕቃን ለመያዝ የተሰራ፣ ለተደጋጋሚ አገልግሎት የሚውልና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ የመጓጓዣ ዓይነት ዕቃን በቀላሉ ለማጓጓዝ እንዲቻል ተደርጎ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ዝርግ፣ ክፍት ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ዝግ የሆነ የዕቃ መያዣ ነው፤

37. "የጉምሩክ ትራንዚት" ማለት ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነው ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ የሚተላለፉበት የጉምሩክ ሥነሥርዓት ነው፤

38. "የጉምሩክ ቁጥጥር" ማለት የጉምሩክ ህግ መከበሩን ለማረጋገጥ በባለሥልጣኑ የሚወሰድ ማናቸውም እርምጃ ነው፤

39. "የጉምሩክ ሕግ" ማለት ይህንን አዋጅ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን እና ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች ህጎች ያጠቃልላል፤
40. "የጉምሩክ ወደብ" ማለት ለጉምሩክ ህግ አፈፃፀም ሲባል የገቢ፣ የወጪ ወይም ተላላፊ ወይም ማጓጓዣ ቀይረው የሚወጡ ዕቃዎች የሚራገፉበት፣ የሚቆዩበትና የሚጫኑበት በባለሥልጣኑ የሚወሰን ማናቸውም ስፍራ ሲሆን ደረቅ ወደብና በባለሥልጣኑ የሚወሰኑ ሌሎች ቦታዎችን ይጨምራል፤
41."የዕቃ ምርመራ" ማለት የዕቃውን የስሪት አገር፣ የመጣበትን አገር፣ ባህሪ፣ ሁኔታ፣ አይነት፣ ብዛት፣ ዋጋና የታሪፍ አመዳደብ በዕቃ ዲክላራሲዮን ቅጽ ውስጥ በቀረበው ዝርዝር መሠረት የተሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ በጉምሩክ ሹም የሚፈፀም አካላዊ ምርመራ ሲሆን በመንገደኞች የሻንጣ ዲክላራሲዮን መሠረት የሚደረግ የዕቃ ምርመራን ይጨምራል፤
42."የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር" ማለት ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ክፍያ ነፃ የሆነ ዕቃ ለዓለም አቀፍ መንገደኞችና ለሌሎች የቀረጥ ነፃ ባለመብቶች የሚሸጥበት በዓለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሌሎች ቦታዎች በባለሥልጣኑ ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች የሚቋቋም መደብር ነው፤
43. "የጉምሩክ ማቋረጫ" ማለት ሰውንና ማጓጓዣን እንዲሁም የገቢ፣ የወጪና ተላላፊ ዕቃዎችን ለማስገባት፣ ለማስወጣትና ለማሸጋገር የተፈቀደ የድንበር መስመር ሲሆን ዓለም አቀፋዊ የድንበር ትራፊክ እንቅስቃሴ የሚፈፀምባቸውን ሥፍራዎች ይጨምራል፤
44. "የጉምሩክ የጠረፍ መስመር" ማለት ከኢትዮጵያ የጉምሩክ ድንበር መስመር ወደ ውስጥ እስከ 15 ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ የሚገኝ ሥፍራ ነው፤
45. "የሥጋት ሥራ አመራር" ማለት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ፣ በሚወጡና በሚተላለፉ እቃዎች ላይ አገልግሎት አሰጣጡንና የቁጥጥር ሥርዓቱን ሚዛናዊ ባደረገ ሁኔታ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የተለያየ የሥጋት ደረጃ በማውጣት የሚከናወን የአሠራር ሥርዓት ነው፤
46."ዕቃን መልቀቅ" ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያለ ዕቃ ለተገለፀለት ዓላማ እንዲውል የሚለቀቅበት ሥርዓት ነው፤
47."የጉምሩክ ሹም" ማለት የጉምሩክ ሥራን በሃላፊነት እንዲያከናውን የተመደበ ሃላፊ ወይም ሰራተኛ ሲሆን የምርመራ ሹምን ይጨምራል፤

48."መያዝ" ማለት የጉምሩክ ሕግን ከማስከበር ጋር በተያያዘ ዕቃን ወይም ሰነድን በቁጥጥር ስር ማድረግ ነው፤

49."በሕጋዊ ዕቃ ከለላነት መጠቀም" ማለት የዕቃ ዲክላሪሲዮን ከቀረበበት ህጋዊ ዕቃ ጋር የዓይነት፣ የመጠን፣ የመለኪያ፣ የጥራት፣ የብዛት፣ የአገላለጽ እና የስሪት አገር ልዩነት ያለውን ወይም በዲክላራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ዕቃ ቀላቅሎ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ከአገር የማስወጣት ድርጊት ነው፤

50."መንገደኛ" ማለት፡-

ሀ/ መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ ያልሆነና ወደ አገር የሚገባ ወይምከአገርየሚወጣ፤ ወይም

ለ/ መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ከአገር የሚወጣ ወይም ወደ አገር የሚመለስ፤

ሰው ነው፤

51."የተተወ ዕቃ" ማለት የዕቃው ባለቤት በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን አጠናቆ ያልተረከበው ዕቃ ነው፤

52."የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ" ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ሆኖ መንገደኛው የሚይዘው ዕቃ ነው፡፡

53."የጉምሩክ ወንጀል" ማለት ከመደበኛ ስራው ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ሹም ከሚፈጽመው ጥፋት ውጪ በማንኛውም ሰው የሚፈፀሙ በዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት ምዕራፍ ሁለት የተዘረዘሩት ጥፋቶች ናቸው፤

54."ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለትየገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

55."ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር" ማለትየጉምሩክ ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር ነው፡፡

56."ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

57.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በመላው የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ፣ በጉምሩክ ክልል በሚወጡ፣ በጉምሩክ ክልል በሚተላለፉና የጉምሩክ

ቁጥጥር በሚደረግባቸው ዕቃዎች እንዲሁም ከጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ጋር በተያያዘ መብት በተሰጣቸውና ግዴታ በተጣለባቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. **ወደ አገር እንዳይገቡና ከአገር እንዳይወጡ ስለተከለከሉ ወይም ገደብ ስለተደረገባቸው ዕቃዎች**

   1. ማንኛውም ሰው የተከለከሉ ዕቃዎችን ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት ወይም ማስተላለፍ አይችልም።
   2. ማንኛውም ሰው ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች የተጣለው ገደብ የሚጠይቃቸውን መሥፈርቶች ካላሟላ በስተቀር ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት ወይም ማስተላለፍ አይችልም።

## ክፍል ሁለት

## የጉምሩክ አሰራር መርሆዎች

5. **ጠቅላላ**

የጉምሩክ አሰራር፡-

   1. አስመጪዎችና ላኪዎች በራሳቸው አነሳሽነት የዕቃዎችን ዋጋ እንዲሁም የቀረጥና ታክስ ስሌት መግለጫ በማቅረብ ራሳቸው ወስነው ቀረጥና ታክስ የሚከፍሉበትን ስርዓት ማጎልበት፤
   2. የሥጋት ሥራ አመራር መርህን በተከተለ ሁኔታ ለተቀላጠፈ የንግድ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲሁም ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ ፍትሐዊ፣ ፈጣን፣ ተገማች እና አመኔታን ያተረፈ የጉምሩክ አገልግሎት በመስጠትና የጉምሩክ ቁጥጥር በማካሄድ ረገድ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራርን ማስፈን፤
   3. የአምራች ኢንዱስትሪን እና የኢኮኖሚ ልማትን መደገፍ፤
   4. ለተገልጋዮች ግልጽ መረጃን መስጠት እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስፈርትን የተከተለና ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር በመደጋገፍና በመመካከር የተደራጀ መረጃ መሰብሰብ መተንተን፣ መጠቀምና መጠበቅ፤እና
   5. ህግ አክባሪነትን በማበረታታት ህገ-ወጥነትን መከላከል፤ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

6. **የስጋት ስራ አመራር**

1. በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የጉምሩክ አገልግሎት እና የሚከናወን የቁጥጥር ስርዓት በመረጃ በተደገፈ መመዘኛ የገቢ፣ የወጪ እና የተላላፊ እቃዎችን የስጋት ደረጃበመለየት የአገልግሎት አሰጣጥን እና የቁጥጥር ስርዓቱን ሚዛናዊነት ጠብቆ የሚከናወን ይሆናል፡፡
2. የዕቃ አወጣጥን፣ ቁጥጥርን፣ የሕግ ተገዥነትን እንዲሁም አገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ ተግባራት እና ባለስልጣኑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች የስጋት ስራ አመራርን መሰረት ያደረጉ ይሆናሉ፡፡
3. ባለሥልጣኑ የስጋት ስራ አመራርን መሰረት በማድረግ በተሰጠ አገልግሎት ላይ የታዩ የሕግ ጥሰቶችን በመለየት ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ኦዲትን እና ሌሎች የቁጥጥር ስልቶችን መሠረት ያደረገ ቁጥጥር ተግባራዊ እንዲደረግ ሊወስን ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ የገቢ፣ የወጪና ተላላፊ እቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

7. <u>**በጉምሩክ አሰራር ተቀባይነት ያገኘ የዕቃ አያያዝ ወይም አጠቃቀም**</u>

1. በዕቃው ባህሪ፣ ብዛት፣ የሥሪት አገር፣ በመድረሻ ሥፍራው ወይም በአላላክ ሁኔታው ላይ ልዩነት ሳይደረግ በዚህ አዋጅ መሠረት በተቀመጡ መስፈርቶች በጉምሩክ አሰራር ተቀባይነት ያገኘ የዕቃ አያያዝ ወይም የአጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የዕቃ አያያዝ ወይም አጠቃቀም ከሕዝብ ሞራል አጠባበቅ፣ ከሰዎች፣ ከእንስሳት ወይም ከዕፅዋት ጤንነትና ሕይወት አጠባበቅ፣ ከታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች አጠባበቅ ወይም በሌላ ሕግ ከተፈቀደ የዕቃዎች አያያዝ ወይም አጠቃቀም ጋር የሚቃረን ከሆነ በሥራ ላይ አይውልም፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

## ምዕራፍ አንድ

## የዕቃ ዲክላራሲዮን

8. <u>**ዲክላራሲዮን አቅራቢ**</u>

1. በዕቃው ላይ የማዘዝ መብት ያለው ማንኛውም ሰው ዲክላራሲዮን አቅራቢ የመሆን እንዲሁም በጉምሩክ አስተላላፊ የመወከል መብት ይኖረዋል።

2. ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዕቃው ዲክላራሲዮን ውስጥ ለሰፈሩት ዝርዝሮች መሟላትና ትክክለኛነት እንዲሁም ለቀረጥና ታክስ ክፍያው ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡
3. የዕቃ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የዕቃውን ዲክላራሲዮን ከማቅረቡ በፊት በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰነውን ሁኔታ ተከትሎ ዕቃውን ለመመርመርና ናሙና ለመውሰድ ይፈቀድለታል።
4. የተወሰደ ናሙና ለሚመለከተው ጭነት በቀረበው የዕቃ ዲክላራሲዮን ውስጥእስከተካተተ ድረስ የተለየ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብበት አይደረግም።

9. <u>**የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ**</u>

1. የዕቃ ዲክላራሲዮን በቃል፣ በአካል እንቅስቃሴ፣ በፅሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. በፅሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚቀርብ ዲክላራሲዮን ለዚሁ ተብሎ በባለሥልጣኑ በተዘጋጀ ቅጽ መሞላት፣ መፈረምና ለጉምሩክ ፎርማሊቲ አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮችን ብቻ መያዝ አለበት፡፡

10.<u>**የዕቃ ዲክላራሲዮን ደጋፊ ሰነዶች**</u>

1. በፅሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የዕቃ ዲክላራሲዮን በሚቀርብበት ጊዜ አስፈላጊነቱ በባለሥልጣኑ የሚወሰን ሆኖ የሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ዋና ቅጂዎቻቸው ወይም የኤሌክትሮኒክስ ቅጂዎቻቸው በአባሪነት መቅረብ አለባቸው፡-

   ሀ/ የማጓጓዣ ሰነድ፤

   ለ/ የዋጋ ሰነድ፤

   ሐ/ የባንክ ፈቃድ፤

   መ/ የዕቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፤

   ሠ/ የስሪት አገር የምስክር ወረቀት፤ እና

   ረ/ ከጉምሩክ ህግ መከበር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁኔታዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች፡፡
2. ባለሥልጣኑ በቂ ምክንያት ሲቀርብለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተዘረዘሩትን ደጋፊ ሰነዶች ቅጂ ብቻ ሊቀበል ይችላል፡፡

3. ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ የሚጠየቀው የማጓጓዣ ሰነድ ዕቃውን ከኢትዮጵያ መውጫ እስከሆነው የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ የወጣውን ወጪ የሚያሳይ የአገር ውስጥ ማጓጓዣ ሰነድ ነው፡፡
4. በአባሪነት የሚቀርቡ ሰነዶችን በበቂ ምክንያት በወቅቱ ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ ባለሥልጣኑ ተገቢውን ዋስትና በመጠየቅ ሰነዶቹ በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ በሚወሰን ጊዜ ውስጥ እንዲቀርቡ በመፍቀድ አገልግሎቱን ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. የዕቃ ዲክላራሲዮን ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ ከዲክላራሲዮኑ ጋር አባሪ ሆነው የቀረቡ ሰነዶችና ዲክላራሲዮኑ እንደ አንድ የማይነጣጠል ሕጋዊ ሰነድ ሆነው ያገለግላሉ፡፡
6. ባለሥልጣኑ በውጭ አገር ቋንቋ የቀረበ ደጋፊ ሰነድ በህጋዊ ተርጓሚ ወደ አማርኛ ወይም ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገውቢኖርም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትለመፈፀም አስፈላጊ ከሆኑት አባሪ ሰነዶችመካከል የተወሰኑትን ማቅረብ በማይቻልበትጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ሰነዶቹ ሳይቀርቡየጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈፀምኮሚሽኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡[21]

11.<u>ጊዜያዊ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ ስለመፍቀድ</u>

1. የዕቃ ዲክላራሲዮን አቅራቢ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባለው ምክንያት የዕቃ ዲክላራሲዮኑን ለመሙላት የሚያስችል የተሟላ መረጃ ከሌለውና ያለው መረጃም የጉምሩክ ቀረጡን ለመወሰን የሚያስችል ከሆነ የተሟላውን የዕቃ ዲክላራሲዮን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማቅረብ የዋስትና ግዴታ እንዲገባ በማድረግ ጊዜያዊ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል፡፡
2. ጊዜያዊ የእቃ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ ባለሥልጣኑ ሲፈቅድ የቀረጥና ታክስ አወሳሰኑ የተሟላና ትክክለኛ ዲክላራሲዮን መጀመሪያውኑ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ከሚኖረው አፈጻጸም የተለየ አይሆንም፡፡
3. ባለሥልጣኑ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን መመሪያ ያወጣል።

12.<u>የዕቃ ዲክላራሲዮን ስለሚቀርብባቸዉ ዕቃዎች</u>

[21]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (2) የተጨመረ ነው፡፡

1. በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ወደ አገር የሚገባ፣ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ የዕቃ ዲክላራሲዮን ይቀርብበታል፡፡
2. የዕቃ ዲክላራሲዮን የቀረበበት ማናቸውም እቃ፡-

ሀ/ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የመጣ ነው ተብሎ የተመዘገበ ከሆነ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ወይም ከቀረጥና ታክስ ነፃ የተደረገ መሆኑ ወይም በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት መሠረት ወደ አገር የገባ መሆኑ፤

ለ/ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ነው ተብሎ የተመዘገበ ከሆነ በሄደበት አገር የሚቀር ወይም በጊዜያዊነት ከአገር ወጥቶ ተመልሶ ወደ አገር የሚገባ መሆኑ፤

ሐ/ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ እሴት ጨምሮ ተመልሶ የሚወጣ ከሆነ የቀረጥ ተመላሽ የሚጠየቅበት መሆኑ፤

መ/ ወደ ውጭ አገር ተልኮ እሴት ጨምሮ ተመልሶ የሚገባ ከሆነ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል መሆኑ ወይም የቀረጥ ተመላሽ የሚጠየቅበት መሆኑ፤ ወይም

ሠ/ በጊዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር የሚገባ መሆኑ፤ተለይቶ መመልከት አለበት፡፡

3. ባለሥልጣኑ ዕቃዎች በባህሪያቸው ወይም በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በፅሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ዲክላራሲዮን ሳይቀርብ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸምባቸው በመመሪያ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

13.<u>ስለዕቃ ዲክላራሲዮን ተቀባይነት ማግኘት</u>

1. የዕቃ ዲክላራሲዮን ተቀባይነት የሚያገኘው ዲክላራሲዮኑ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10(1) የተዘረዘሩት ደጋፊ ሰነዶች ተሟልተው በጉምሩክ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ ከተመዘገቡ በኋላ ትክክለኛነታቸው በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡
2. የዕቃ ዲክላራሲዮንን ትክክለኛ መሆን የማረጋገጥ ስራ ዲክላራሲዮኑ ከቀረበ በኋላ ወዲያውኑ መከናወን አለበት፡፡
3. የእቃ ዲክላራሲዮንን ወይም ደጋፊ ሰነድን ያልተሟላ ወይም ጉድለት ያለበት የሚያደርግ ማንኛውም ግድፈት ዲክላራሲዮኑ ከመመዝገቡ በፊት በዲክላራሲዮን አቅራቢው መታረም አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም ዲክላራሲዮኑ ከተመዘገበ በኋላ ለማጭበርበር በማሰብ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የተፈጸመ ግድፈት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

5. ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የዕቃ ዲክላራሲዮን ያልተቀበለው ከሆነ ምክንያቱን በፅሑፍ ለዲክሳራሲዮን አቅራቢው መግለጽ አለበት፡፡

## 14. ዲክላራሲዮን ስለማሻሻል

1. የዕቃ ዲክላራሲዮን ከተመዘገበ በኋላ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዲክላራሲዮኑ ውስጥ ከተዘረዘሩት መግለጫዎች መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላይየሆኑትን ሊያሻሻል ይችላል፡፡ ሆኖም የሚደረገው ማሻሻያ አስቀድሞ መግለጫ ለተሰጠባቸው ዕቃዎች ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ዕቃዎች ላይ ዲክላራሲዮኑተፈጻሚነት እንዲኖረው የሚያደርግ አይሆንም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ባለስልጣኑ ሰነዶቹን ወይም ዕቃዎቹን እንደሚፈትሽ ለዲክላራሲዮን አቅራቢው ካስታወቀው ወይም በቀረበው የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ውስጥ የሰፈሩት ዝርዝሮች ትክክለኛ አለመሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ በቂ በሆነ ምክንያት ላይ ተመሥርቶ ባለሥልጣኑ ካልፈቀደበስተቀር ማሻሻያ ማድረግ አይፈቀድም።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌ ቢኖርም የስጋት ደረጃው ዝቅተኛበመሆኑ ዕቃ ሳይፈተሽ ከተለቀቀ በኋላበአስመጪው መጋዘን ወይም የስራ ቦታፍተሻ ወይም የድህረ ዕቃ ኦዲት ሲደረግበዲክላራሲዮን ላይ የተሰጠ መግለጫየተሳሳተ ሆኖ ከተገኘ አሳማኝ በሆኑምክንያቶች ዲክላራሲዮን እንዲሻሻልኮሚሽኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡[22]

## 15. ዲክላራሲዮንን ስለመሰረዝ

1. ዲክላራሲዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራሲዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ 5 የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ካልጀመረ ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል፡፡
2. የዕቃ ዲክላራሲዮን የቀረበው በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ወይም ከጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ውጪ መሆኑ እና ክፍያ ያለመፈፀሙ ከተረጋገጠ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ሊሰረዝ ይችላል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ዕቃው ከተለቀቀ በኋላ የሚቀርብ የዲክላራሲዮን ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

---

[22] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (3) የተጨመረ ነው፡፡

4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ፣ (2) እና (3) ድንጋጌ ቢኖርም ዕቃ ከመለቀቁ በፊትአስመጪው በሌላ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትለመስተናገድ ጥያቄ ያቀረበ ከሆነናበመመሪያ በሚወሰነው መሰረት ኮሚሽኑአሳማኝ ምክንያት ሲኖረው ቀረጥና ታክሱከተከፈለም በኋላ ዲክላራሲዮን ተሰርዞበሌላ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲስተናገድሊፈቅድ ይችላል፡፡[23]

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲሰረዝ መፍቀድ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዚህ አዋጅ መሠረት ሊፈጸምበት የሚችልን ቅጣት አያስቀርም፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የጉምሩክ ትራንዚት እና ማጓጓዣ በመቀየር ዕቃን የማጓጓዝ የጉምሩክ ሥነሥርዓት

### 16. ጠቅላላ

1. ባለሥልጣኑ ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው በጉምሩክ ክልል ውስጥ፦
   ሀ/ ከመግቢያ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ መዉጫ የጉምሩክ ጣቢያ፤
   ለ/ ከመግቢያ የጉምሩክ ጣቢያ አገር ውስጥ ወደሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ፤
   ሐ/ በአገር ውስጥ ከሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ መውጫ የጉምሩክ ጣቢያ፤ወይም
   መ/ በአገር ውስጥ ከሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ አገር ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ፤
   እንዲጓጓዙ ይፈቅዳል።
2. በባለሥልጣኑ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች እስከተሟሉና የሚያስፈልገው ዋስትና እስከቀረበ ድረስ በጉምሩክ ትራንዚት የሚጓጓዝ ዕቃ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡
3. የጉምሩክ ትራንዚት ዕቃዎች በባለሥልጣኑ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ተከብረውና ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ ጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያ ስለመድረሳቸው ዲክላራሲዮን አቅራቢውና አጓጓዡ በጋራና በተናጠል ኃላፊነት አለባቸው።
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ በመመሪያ የወሰናቸው ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ:-

[23] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (4) ተሻሻለ፡፡

ሀ/ የዕቃ ተቀባይ ዕቃውን ወደ ጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ ወደ ራሱ የሥራ ቦታ መጥቶለት እንዲረከብ፤ ወይም

ለ/ የዕቃ ላኪ ዕቃዉን ወደ መነሻ የጉምሩክ ጣቢያ ማቅረብ ሳያስፈልገው ከራሱ የሥራ ቦታ በቀጥታ መላክ እንዲችል፤

ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 17.የጉምሩክ ትራንዚት ዕቃ ዲክላራሲዮን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(1) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ተፈላጊ ዝርዝሮችን በግልጽ ያካተተ የንግድ ወይም የማጓጓዣ ሰነድ እንደ ጉምሩክ ትራንዚት ዕቃ ዲክላራሲዮን ገላጭ ክፍል ሆኖ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል፡፡ በዚህ አይነት ተቀባይነት ማግኘቱም በሰነዱ ላይ መገለጽ አለበት፡፡

## 18.ጭነትን ስለማሸግና ተለይቶ እንዲታወቅ ስለማድረግ[24]

1. የጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያው ጭነቱን ለይቶ ለማወቅና ያልተፈቀደ ጣልቃ ጉብነት ተፈጽሞበት ከሆነም ይህንኑ ለይቶ ማወቅ እንዲችል የመነሻ ጉምሩክ ጣቢያው አስፈላጊዉን የጥንቃቄ እርምጃ ሁሉ መውሰድ አለበት፡፡
2. የጉምሩክ ማሸጊያ የሚያስፈልገው ጭነት በማጓጓዣ የተወሰነ ክፍል ውስጥ ተደርጎ የሚጓጓዝ ሲሆንና የማጓጓዣ ክፍሉ አሠራርና ይዘት፡-

   ሀ/ የጉምሩክ ማሸጊያ በቀላሉና በአግባቡ ሊደረግበት የሚያስችል ከሆነ፤

   ለ/ የመነካካት ምልክት ሳይታይበት ወይም ማሸጊያዉ ሳይወገድ ዕቃ ወደ ማጓጓዣዉ የተወሰነ ክፍል ለማስገባት ወይም ከማጓጓዣው የተወሰነ ክፍልለማዉጣት የማያስችል ከሆነ፤

   ሐ/ ዕቃን ለመሰወር የሚያስችል ድብቅ ክፍል የሌለዉ ከሆነ፤ እና

   መ/ ዕቃን መያዝ የሚችሉ ክፍሎቹ ሁሉ ለጉምሩክ ቁጥጥር ተደራሽነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ከሆነ፤

   የጉምሩክ ማሸጊያው በማጓጓዣ ክፍሉ በራሱ ላይ መደረግ አለበት፡፡
3. የማጓጓዣ የተወሰነ ክፍል ለጉምሩክ ትራንዚት ደህንነት ምቹ መሆን ወይም አለመሆን በባለሥልጣኑ ሊወሰን ይችላል፡፡
4. ተያይዘው የቀረቡት ሰነዶች ዕቃውን በማያሻማ ሁኔታ ለመለየት የሚያስችሉ ከሆነ፡-

---

[24]የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 እና 10 በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (5) የተጨመሩ ናቸው፡፡

ሀ/ በጉምሩክ ጣቢያው ሥጋትን ከመቀነስ አንፃር አስፈላጊ ነው ተብሎ ካልተወሰነ፣

ለ/ አጠቃላይ የጉምሩክ ትራንዚት ለማፋጠን የሚያግዝ ካልሆነ፣ ወይም

ሐ/ የዓለም አቀፍ ስምምነት የሚያስገድድ ካልሆነ፣

በስተቀር ዕቃው በጉምሩክ ማሸጊያ ሳይታሸግ ወይም በጉምሩክ ማሰሪያ ሳይታሰር እንዲጓጓዝ ማድረግ ይቻላል፡፡

5. ጭነቱ በጉምሩክ ማሸጊያ ታሽጎ መጓጓዝ የሚገባዉ ሆኖ ሳለ ነገር ግን የማጓጓዣው የተወሰነ ክፍል በአግባቡ ሊታሸግ የማይችል ከሆነ ዕቃዉን በሚገባ ለመለየትና ያልተፈቀደ ጣልቃ ገብነት ቢኖር በቀላሉ ለማወቅ፡-

   ሀ/ የዕቃዉ ሙሉ ምርመራ መደረግና ዉጤቱም በጉምሩክ ትራንዚት ሰነዱ ላይ መመዝገብ፣

   ለ/ እያንዳንዱ የዕቃ እሽግ በጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ማሠሪያ መታሸግ ወይም መታሰር፣

   ሐ/ በናሙና፣ ፕላን፣ ንድፍ፣ ፎቶግራፍ ወይም በተመሳሳይ ዘዴ የተደገፈ የዕቃዉ ትክክለኛ መግለጫ ከጉምሩክ ትራንዚት ሰነዱ ጋር መያያዝ፣

   መ/ ዕቃው የሚጓጓዝበት የማያወላውል የጉዞ መስመርና የመድረሻ ጊዜ ገደብ መወሰን፣ወይም

   ሠ/ እቃዉ በጉምሩክ ታጅቦ እንዲጓጓዝ መደረግ፣

   አለበት፡፡

6. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ፊደል ተራ (መ) መሠረት የሚወስነው የጊዜ ገደብ የጉምሩክ ትራንዚቱን ለመፈጸም የሚያስችል በቂ ጊዜ መሆን አለበት፡፡ የጊዜ ገደቡም በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ወይም በአጓጓዡ ሲጠየቅና ተቀባይነት ያለው ምክንያት መኖሩ በባለሥልጣኑ ሲታመን ሊራዘም ይችላል፡

7. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ፊደል ተራ (መ) ወይም (ሠ) መሠረት ዕቃው የሚጓጓዝበትን የማያወላዉል የጉዞ መስመር እንዲከተል ወይም በጉምሩክ ታጅቦ እንዲጓጓዝ ሊወስን የሚችለው እንደዚህ ዓይነቱ እርምጃ ለጉምሩክ ቁጥጥር አማራጭ የሌለዉ ሆኖ ሲገኝ ነዉ፡፡

8. በዚህ አንቀጽ መሠረት የማጓጓዣ የተወሰነ ክፍል መታሸግ አያስፈልገውም ብሎ መወሰን የሚችለው ባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

9. በወጪና ገቢ ወይም ተላላፊ ዕቃ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው በጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያዎችና መተላለፊያ መሰመሮች የጭነቶችን እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችል የጭነት እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ መሳሪያ በማጓጓዣው ላይ መግጠም አለበት፡፡
10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 መሠረትበማጓጓዣው ላይ ተፈላጊውን የጭነትእንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ መሳሪያያልተገጠመለት ማጓጓዣ በወጪና ገቢወይም ተላላፊ ዕቃ ትራንስፖርትአገልግሎት ማሰማራት ወይም መሰማራትአይችልም፡፡

## 19. ስለጉምሩክ ማሽነሪያዎች

1. ለጉምሩክ ትራንዚት አገልግሎት የሚዉሉ የጉምሩክ ማሸጊያዎችና ማሰሪያዎች በባለሥልጣኑ መመሪያ የተወሰኑ ዝርዝር መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርባቸዋል።
2. በዉጭ አገር ጉምሩክ አማካይነት የተደረጉ የጉምሩክ ማሸጊያዎችና መለያ ምልክቶች፡-

   ሀ/ በቂ አይደሉም ካልተባሉ፤

   ለ/ አስተማማኝ ካልሆኑ፣ ወይም

   ሐ/ ባለሥልጣኑ ዕቃውን ለመመርመር ካልወሰነ፤

   በስተቀር ለጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸም ተቀባይነት ይኖራቸዋል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተቀባይነት ያገኙ የውጭ አገር የጉምሩክ ማሸጊያዎችና ማሰሪያዎች ባለሥልጣኑ እንደሚጠቀማቸው የጉምሩክማሸጊያዎችና ማሰሪያዎች ተመሣሣይ የሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡

## 20. በጉዞ ወቅት ስለሚፈፀም ስነ ስርዓት

1. በቅድሚያ ፈቃድ መገኘት አለበት ተብሎ በባለሥልጣኑ ካልተወሰነ በስተቀር በመዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያ ላይ የሚደረግ ለውጥ አስቀድሞ ማስታወቅ ሳያስፈልግ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
2. የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ማሰሪያ እንዲወገድ እስካልተደረገ ወይም እስካልተነካካ ድረስ ባለሥልጣኑንማስፈቀድ ሳያስፈልግ ዕቃን ከአንድ ማጓጓዣ ወደ ሌላ ማጓጓዣ ማዛወር ይቻላል፡፡

3. በጉምሩክ ትራንዚት ላይ ያለውን ዕቃ ለይቶ ለማወቅ የሚቻል እስከሆነና ሌሎች የጉምሩክ ፎርማሊቲዎች እስከተሟሉ ድረስ ሌሎች ዕቃዎች በተጫኑበት የማጓጓዣ የተወሰነ ክፍል ውስጥ ተጭኖ እንዲጓጓዝ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. በጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸሙ ላይ በቀጥታ ተጽኖ የሚያመጣ አደጋ ወይም ያልተጠበቀ ሁኔታ ሲከሰት ዲክሳራሲዮን አቅራቢው ወይም አጓጓዡ ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኘው የጉምሩክ ጣቢያ ወይም አግባብ ላለው ሌላ የመንግስት አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## 21.<u>ስለጉምሩክ ትራንዚት መጠናቀቅ[25]</u>

1. የጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸምን ለማጠናቀቅ ዕቃዎቹ ምንም ለውጥ ሳይደረግባቸውና አገልግሎት ላይ ሳይዉሉ፣ የጉምሩክ ማሸጊያው፣ ማሰሪያው ወይም መለያ ምልክቱ ሳይነካካ ከሚመለከተው የዕቃ ዲክላራሲዮን ጋር ለመዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ አለባቸው።
2. የመዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያው ዕቃዎቹ በቁጥጥሩ ሥር እንደገቡ ወዲያውኑ ሁሉም ቅደመሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የጉምሩክ ትራንዚት አፈጸጸሙን ለማጠናቀቅ ሁኔታውን ማመቻቸት አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ በሚያወጣዉ መመሪያ በሚዘረዘሩ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር በጉምሩክ ትራንዚት የሚጓጓዙ ዕቃዎች በባለሥልጣኑ በተወሰነዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ መዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያዉ ዘንድ ያልደረሱ ከሆነ በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጥ (1) እና (2) ድንጋጌ ቢኖርም በትላልቅ ኩባንያዎችወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ በአስመጪውመጋዘን ወይም የሥራ ቦታ ትራንዚትእንዲጠናቀቅበት ኮሚሽኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌእንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ጉምሩክ መዳረሻጣቢያ መግባት ሳያስፈልገው በድርጅቱመጋዘን ወይም የስራ ቦታ ትራንዚትእንዲያጠናቅቅ የተፈቀደለት አስመጪየዕቃ መልቀቂያ ሳይሰጠው እሽጉንመነካካት፣ መፍታት ወይም ዕቃ ማራገፍ አይችልም፡፡

## 22.<u>ማጓጓዣ በመቀየር ዕቃን ስለማጓጓዝ</u>

[25] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (6) የተጨመሩ ናቸው፡፡

1. በአስመጪው፣ በአጓጓዡ ፣ ወይም በጉምሩክ ሥነስርዓት አስፈፃሚዉ ጥያቄ ዕቃ ከአንድ ማጓጓዣ ወደ ሌላ ማጓጓዣ በመቀየር ሊጓጓዝ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ተፈላጊ ዝርዝሮችን የያዘ የንግድ ወይም የማጓጓዣ ሰነድ ለዚህ አንቀጽ ተፈጻሚነትእንደ ዕቃ ዲክላራሲዮን ተቆጥሮ ተቀባይነት ይኖረዋል።
3. ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማጓጓዣ በመቀየር፤ የሚጓጓዘዉን ዕቃ ከአገር በሚወጣ ጊዜ ለመለየትና ያልተፈቀደ ጣልቃ ገብነትን ወዲያውኑ ለማጋለጥ የሚያስችል የጥንቃቄ እርምጃ ዕቃው በሚገባበት ወቅት ሊወስድ ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ ማጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዝ ዕቃ ከአገር የሚወጣበትን በቂ የሆነ የጊዜ ገደብ ሊወስን ይችላል፡፡
5. ማጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዣ ዕቃ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡

## <u>ምዕራፍ ሶስት</u>

## <u>የዕቃ አወጣጥ የጉምሩክ ሥነስርዓት</u>

### 23.<u>ስለሰነድና ዕቃ ምርመራ</u>

1. ባለሥልጣኑ የሚለቀቁ ዕቃዎች በተመዘገበ ዲክላራሲዮን የተሸፈኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እቃዎቹን መመርመርና የምርመራና ትንተና ናሙናዎችን ለመውሰድ ይችላል፡፡
2. ዕቃዎቹ በሚመረመሩበት ወይም ናሙናዎች በሚወሰዱበት ወቅት ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሥፍራው የመገኘት መብት ይኖረዋል፤ ሆኖም ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሥፍራው ካልተገኘ የመጋዘኑ ሃላፊ ባለበት ባለስልጣኑ ዕቃ የመመርመር ወይም ናሙና የመውሰድ ተግባሩን ያከናውናል።
3. ዕቃዎቹ ወደ ሚፈተሹበት ወይም ናሙናዎቹ ወደ ሚወሰዱበት ሥፍራ ለማጓጓዝ፣ ናሙናዎችን ለመውሰድ እና ለምርመራ የሚያስፈልገው ወጪ እንዲሁም ማናቸውም ከዚህ ሥራ ጋር የተያያዘ ወጪ የዲክላራሲዮን አቅራቢው ኃላፊነት ይሆናል፡፡
4. በጉምሩክ ህግ መሰረት ለተወሰዱ ናሙናዎች ባለሥልጣኑ ለዲክላራሲዮን አቅራቢው የካሳ ክፍያ የመፈፀም ኃላፊነት የለበትም፡፡
5. ምርመራ የተደረገባቸው ዕቃዎች በዕቃ ዲክላራሲዮን ከተሸፈኑት ዕቃዎች ውስጥ ከፊል ብቻ ከሆነ የምርመራው ውጤት በዚያ ዲክላራሲዮን ለተሸፈኑት ዕቃዎች ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

6. ዲክላራሲዮን አቅራቢው የተደረገው ከፊል ምርመራ የቀሩትን ዕቃዎች በተመለከተ ተቀባይነት እንደሌለው ካሰበ በዕቃዎቹ ላይ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ሲጠይቅ ይችላል፡፡ ለተጨማሪው የምርመራና የትንተና ሥራ የሚያስፈልገውን ወጪ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ይሸፍናል።
7. የዕቃ ዲክላራሲዮኑ ማጣራት የማይከናወንበት ከሆነ፣ የጉምሩክ ፎረማሊቲው ዲክላራሲዮኑ ላይ በተገለፀው ዝርዝር መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
8. ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱ ሁኔታዎችን የሚያሟሉ ዕቃዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ሥነሥርዓት እንዲፈፀምባቸው ሊደረግ ይችላል፡፡

## 24.<u>በዕቃዎች ላይ የመለያ ምልክት ስለማድረግ</u>

1. ለዕቃው በቀረበው ዲክላራሲዮን የተገለጸውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለማስፈፀም ዕቃውን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በዕቃው ላይ መለያ ምልክት ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. በባለሥልጣኑ በሚወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የማጓጓዣውን ወይም የዕቃውን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የምልክቶቹን መወገድ አስፈላጊ ካላደረጋቸው በስተቀር በዕቃው ወይምበማጓጓዣው ላይ የተለጠፉ ምልክቶች ሊወገዱ ወይም ሊነሱ የሚችሉት በባለሥልጣኑ ወይም በባስሥልጣኑ በተፈቀደለት ሰው ይሆናል፡፡

## 25.<u>ዕቃዎችን ስለመልቀቅ</u>

1. ዲክላራሲዮን የቀረበላቸው ዕቃዎች በባለሥልጣኑ የሚደረግ ምርመራ ሲያበቃ ወይም ባለሥልጣኑ እንደማይመረምራቸው ሲወስን፡-

   ሀ/ የተከለከሉ ካልሆኑ ወይም ከዕቃዎቹ ጋር በተያያዘ የተፈፀመ ወንጀል ከሌለ፤

   ለ/ ዕቃዎች የተመደቡበት አግባብነት ያለው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከተሟላ፤

   ሐ/ ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎችን በሚመለከት አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ፈቃድ ከቀረበ፤ እና

   መ/ መከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ከተከፈለ ወይም ዋስትና ከቀረበ፤

   ወዲያውኑ መለቀቅ አለባቸው።

2. 2.ሚኒስቴሩ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረትኮሚሽኑ ለቀረጥና ታክስ ክፍያ ዋስትናበመቀበል ዕቃ ሊለቅ ይችላል፡፡ ሆኖምቀረጥና ታክሱ የሚከፈልበት ጊዜ ከአስራሁለት ወራት ሊበልጥ አይችልም፡፡[26]
3. ቀረጥና ታክስ ለመወሰን ናሙናዎች ተወስደው የቴክኒክ ሰነዶችና የባለሙያ አስተያየት የሚያስፈልግ በሚሆንበት ጊዜ የምርመራው ውጤት ከመታወቁ በፊት ባለሥልጣኑ ዋስትና እንዲቀርብ በማድረግ ዕቃውን መልቀቅ ይችላል፡፡
4. የተለየ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በአንድ ዲክላራሲዮን የሚሸፈኑ እቃዎች መለቀቅ ያለባቸው በአንድ ላይ ነው፡፡

## 26.<u>በምትክነትና በማሚያነት ስለሚገቡ እቃዎች</u>

1. ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲባል ወደ አገር ውስጥ የገባ እቃ በስህተት ወይም በብልሽት ለታለመለት ዓላማ መዋል ካለመቻል ወይም የተሟላ ካለመሆን የተነሳ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመልሶ እንዲወጣ በአስመጪው ጥያቄ ከቀረበ እቃው ከአገር እንዲወጣ ተደርጎ በምትክነት የሚመጣው ተመሳሳይ ዕቃ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር እንዲገባ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በምትክነት የሚመጣው ተመሳሳይ ዕቃ ወደ አገር ከመግባቱ በፊት በስህተት ወይም በብልሽት ለታለመለት ዓላማ ሊውል ያልቻለውን ወይም ያልተሟላውን ዕቃ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ባለሥልጣኑ ሲያምበት ዕቃው በተወሰነ ጊዜ ከአገር እንዲወጣ ለማድረግ አስመጪው ዋስትና እንዲያቀርብ በማድረግ ወይም ዕቃው ለአገልግሎት የማይውል ከሆነ አስመጪው ዕቃውን ለባለሥልጣኑ እንዲያስረክብ በማድረግ የሚመጣው ተመሳሳይ ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በምትክነት ወደ አገር እንዲገባ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲባል ወደ አገር የገባው ዕቃ በዲክላራሲዮኑ ላይ ከተገለፀው መጠን ጋር ሲነፃፀር ጉድለት ያለበት መሆኑ በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ ባለሥልጣኑ የቀረዉ ዕቃ ተሟልቶ እንዲገባ ወይም ባልገባው ዕቃ ላይ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

[26] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (7) ተሻሻለ

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌቢኖርም ወደ አገር ውስጥ የገባውን ዕቃባህሪ መሠረት በማድረግ ኮሚሽኑበምትክነት የሚገቡ ዕቃዎችን የጊዜ ገደብሊያራዝም ይችላል፡፡ ሆኖም የሚራዘመውጊዜ የዕቃው ላኪ ከተሰጠው የዋስትና ጊዜሊበልጥ አይችልም፡፡[27]

27.<u>ዕቃዎችን ለነፃ ዝውውር ስለመልቀቅ</u>

1. በህግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ለነፃ ዝውውር አይለቀቅም፡፡
2. የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖ ለነፃ ዝውውር የተለተቀቀ ማናቸዉም የገቢ ዕቃ አገር ዉስጥ እንደተመረተ ዕቃ ይቆጠራል።
3. ለነፃ ዝወውር የተለቀቀ ዕቃ እንደ አገር ውስጥ ዕቃ የሚታይበትን ሁኔታ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያጣ ይችላል፡-

ሀ/ ዕቃዎቹ ከተለቀቁ በኋላ ለነፃ ዝውውር የተለቀቀበት የዕቃ ዲክላራሲዮን ህጋዊነቱን ካጣ፤

ለ/ ወደ ውጭ የሚላክ ምርት ለማምረት በጥሬ ዕቃነት የገባና በቀረጥ ተመላሽ ወይም በቫዉቸር ስርዓት የሚስተናገድ ሲሆን፤

ሐ/ የተበላሸ ወይም ጥራቱን ያልጠበቀ በመሆኑ ምክንያት በተገባዉ ዉል መሰረት ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ የሚደረግ ሲሆን፤ ወይም

መ/ ዕቃው ተመልሶ ሲወጣ ወይም በባለስልጣኑ ለተፈቀደ አገልግሎት ብቻ ሲዉልና ቀረጥና ታክስ ተመላሽ የሚደረግበት ሲሆን።

28.<u>ዕቃ ሳይደርስ የዕቃ አወጣጥ ሥርዓትን ስለመፈፀም</u>

1. አስመጭዉ ወይም ወኪሉ ዕቃው ከመድረሱ በፊት የዕቃ ዲክላራሲዮን እና አባሪ ሰነዶችን በማቅረብ አስቀድመው እንዲመረመሩለት እና የዕቃ መልቀቂያ እንዲሰጠዉ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ዕቃዎች ከመድረሳቸው በፊት የቀረበለትን የዕቃ ዲክሊራሲዮን እና ደጋፊ ሰነዶች ከመረመረ በኃላ ዕቃው እንደደረሰ እንዲወጣ የሚያስችል መልቀቂያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

29.<u>ዕቃ ከተለቀቀ በኋላ የእቃ አወጣጥ ሥርዓትን ስለመፈጸም</u>

[27] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (8) የተጨመረ ነው፡፡

ባለሥልጣኑ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዕቃው ከተለቀቀ በኋላ የዕቃ አወጣጥ የጉምሩክ ሥነስርዓት ሊያጠናቅቅ እንደሚችል ካመነበትና በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያለው የጭነቱን ዋና ዋና ዝርዝሮች የያዘ የንግድ ወይም ኦፊሲላዊ ሰነድ እና እንደአስፈላጊነቱም ተከፋይ ሊሆን የሚገባው ቀረጥና ታክስ ሊሰበሰብ መቻሉን የሚያረጋግጥ ዋስትና ከቀረበለት የዕቃ አወጣጥ ሥነሥርዓቱ ከመጠናቀቁ በፊትዕቃውን ሊለቅለት ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ለመንገደኞች ተፈፃሚ ስለሚሆን የጉምሩክ ሥኑሥርዓት

### 30.በመንገደኞች ስለሚቀርብ የዕቃ ዲክላራሲዮን

1. ማንኛውም መንገደኛ ስለያዘው ዕቃ በቃል ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት ይችላል፤ ሆኖም መንገደኛው ወደ አገር ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ የያዘው ዕቃ የንግድ ባህሪ ያለው ሲሆን በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ መደረግ አለበት፡፡
2. ወደ አገር ውስጥ የገባ መንገደኛ ከሚከተሉት የማለፊያ መስመሮች አንዱን መርጦ በማለፍ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት ይችላል፡-

   ሀ/ በዋጋ ወይም በብዛት ቀረጥና ታክስ ከማይከፈልበት መጠን በላይ ያልሆኑ ወይም ክልከላ ወይም ገደብ ያልተደረገባቸውን ዕቃዎች የያዙ መንገደኞች እንዲጠቀሙበት በአረንጓዴ ምልክት የተለየውን የማለፊያ መስመር፤ ወይም

   ለ/ በዋጋ ወይም በብዛት ቀረጥና ታክስ ከማይከፈልበት መጠን በላይ የሆኑ ወይም ክልክላ ወይም ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች የያዙ መንገደኞች እንዲጠቀሙበት በቀይ ምልክት የተለየውን የማለፊያ መስመር፡፡
3. ባለሥልጣኑ በመንገደኞች ላይ የሚፈጸመውን የጉምሩክ ቁጥጥርና የያዛቸውን ዕቃዎች የመልቀቅ ተግባር ለማቀላጠፍ አግባብ ካላቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና በቅድሚያ ሊገኙ የሚችሉ የተሳፋሪዎች መረጃዎች ካሉ እነዚህኑ ሊጠቀም ይችላል፡፡

### 31.በመንገደኞች የተያዙ ዕቃዎች መጋዘን ተከማችተዉ እንዲቆዩ ስለማድረግ

በመንገደኞች የተያዙ ዕቃዎች፡-

1. መንገደኛው ሲጠይቅ፤
2. ዕቃዎቹ ወዲያውኑ ሊለቀቁ የማይችሉ ሲሆን፤ ወይም

3. ዕቃዎቹ በዚህ ምዕራፍ ሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ሊስተናገዱ የማይችሉ ሲሆን፣ አግባብ ባለው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እስከሚስተናገዱ ወደ ውጭ ተመልሰው እስከሚወጡ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሌላ መንገድ እስከሚወገዱ ድረስ ባለሥልጣኑ የሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በመጋዘን ተከማችተው እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡

32.<u>ከመንገደኛው ተለይቶ ስለሚጓጓዝ ሻንጣ</u>[28]

1. ከመንገደኛው ቀድሞ ወይም ዘግይቶ የሚደርስ ወይም የሚጓጓዝ የመንገደኛ ሻንጣ ከመንገደኛ ጋር አብሮ ለሚጓጓዝ ሻንጣ ተፈጻሚ በሚሆነው ወይም በሌላ ቀለል ባለ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት መሠረት ይስተናገዳል፡፡
2. ማንኛውም ውክልና የተሰጠው ሰው ከመንገደኛው ተለይቶ የተጓጓዘን ሻንጣ መንገደኛውን ወክሎ የጉምሩክ ሥነሥርዓት እንዲፈጸምበት ለማድረግ ይችላል፡፡
3. 3.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌእንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው በካርጎ ተርሚናልወይም በየብስ ማጓጓዣ የመጣ እንደሆነየመንገደኛው ዕቃ የሚስተናገደው በጭነትማጓጓዣ ወደ አገር ውስጥ የመጣ ዕቃ በሚስተናገድበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትይሆናል፡፡
4. 4.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌቢኖርም የመንገደኛው ዕቃ ከአቅም በላይበሆነ ምክንያት በጭነት ማጓጓዣ ወደአገር ውስጥ የገባ እንደሆነ ዕቃው እንደመንገደኛ ዕቃ ተቆጥሮ የመንገደኛ ዕቃበሚስተናገድበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትመሠረት ይስተናገዳል፡፡
5. 5. ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (4) አፈጻጸም"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለትበዉጭ አገር የሚኖሩ ዜጎች በሚኖሩበትአገር በተፈጠረ አስገዳጅ ሁኔታ ነዉ፡፡

33.<u>ለንግድ ዓላማ የማይውሉ ዕቃዎችና የግል መገልገያዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ ክፍል አራት በሌላ ሁኔታ የተደነገገው ቢኖርም አግባብ ያለው ሆኖ ሲገኝ ለንግድ ዓላማ የማይውሉ በመንገደኞች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጪ የሚወጡ ዕቃዎችን ቀረጥና ታክስ አወሳሰን በሚመለከት ወጥ የሆነ የታሪፍ ምጣኔ ሥርዓት ተፈጻሚ ሊደረግ ይችላል፡፡

---

[28]የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3፣ 4 እና 5 በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (9) የተጨመረ ነው፡፡

2. መንገደኞች የግል መገልገያዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር ውስጥ ይዘው ለመግባት ወይም ወደ ውጪ ይዘው ለመውጣት የሚፈቀድላቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረትይሆናል፡፡[29]
3. ተመላሽ ነዋሪ መንገደኞች በጉምሩክ ክልል ውስጥ ለነፃ ዝውውር ተለቀው የነበሩና ይዘዋቸው የወጡ የግል መገልገያዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር ውስጥ መልሰው ለማስገባት ይፈቀድላቸዋል።
4. ነዋሪ ላልሆነ መንገደኛ የግል መገልገያዎችን በጊዜያዊነት የማስገቢያ ዲክላራሲዮን ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ መንገደኛው በጉምሩክ ክልል ውስጥ የሚቆይበትን ጊዜ በማገናዘብ የግል መገልገያዎቹ ተመልሰው የሚወጡበትን የጊዜ ገደብ ሊወስን ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ መንገደኛው በበቂ ምክንያት ሲጠይቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የተወሰነውን የጊዜ ገደብ ሊያራዝመው ይችላል፡፡
6. ወደ ጉምሩክ ክልል የሚገቡ ወይም ከጉምሩክ ክልል የሚወጡ መንገደኞች የራሳቸውን መጓጓዣ መጠቀም የሚችሉበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
7. ነዋሪ ያልሆነ መንገደኛ በጊዜያዊነት ይዞት የገባውን የግል መገልገያ ከገባበት ውጭ በሆነ ሌላ የጉምሩክ ወደብ መልሶ ይዞ ለመውጣት ይችላል፡፡
8. ባለሥልጣኑ በአደጋ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የወደመን ወይም በጣም የተጎዳን የግል መገልገያ ነዋሪ ያልሆነው መንገደኛ መልሶ ይዞ እንዲወጣ ማስገደድ የለበትም፡፡

## 34.<u>ስለተላላፊ መንገደኞች</u>

ተላላፊ መንገደኞች የትራንዚት አካባቢውን እስካልለቀቁ ድረስ የጉምሩክ ቁጥጥር አይደረግባቸውም፤ ሆኖም ባለሥልጣኑ በትራንዚት አካባቢው ላይ አጠቃላይ ቁጥጥር ማድረግና የጉምሩክ ወንጀል ተፈጽሟል የሚል ጥርጣሬ ሲኖር አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡

## 35.<u>ለመንገደኞች የሚሰጡ የጉምሩክ አገልግሎቶችን ስለሚመለከቱ መረጃዎች</u>

[29]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (10) ተሻሻለ

ባለሥልጣኑ ለመንገደኞች የሚሰጡ የጉምሩክ አገልግሎቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅተው አግባብነት ባላቸው መንገዶች ለመንገደኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## በፖስታ ስለሚገቡና ስለሚወጡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

### 36.ስለ ጉምሩክ ቁጥጥር

በፖስታ አገልግሎት በኩል ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡

### 37.ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

የፖስታ አገልግሎት ሥራ እንዲሠራ የተፈቀደለት ማንኛውም ሰው በፖስታ ወደ አገር ውስጥ ስለገቡትና ወደ ውጭ አገር ስለሚላኩ ዕቃዎች የዕቃ ዝርዝር መግለጫ በማቅረብ ወይም ሌላ የተፈቀደ የማሳወቂያ ዘዴ በመጠቀም ለሚመለከተው የጉምሩክ ሹም ማሳወቅና ዕቃዎቹንም ለክሊራንስ ማቅረብ አለበት፡፡

### 38.የፖስታ ዕቃዎች ዲክላራሲዮን

1. በፖስታ አገልግሎት በኩል ወደ አገር ሲገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ ዕቃ በላኪው የተሰጠ መግለጫ፣ በዕቃው ላይ የተለጠፈ ምልክት ወይም ከዕቃው ጋር የቀረበ ማናቸውም ደጋፊ ሰነድ፡-

   ሀ/ የዕቃው ዋጋ በባለሥልጣኑ ከተወሰነው በላይ ያለመሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነ፤

   ለ/ ዕቃውን ወደ አገር ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ ሠርተፊኬት የማያስፈልገው መሆኑን ሊያረጋግጥ የሚችል ከሆነ፤ እና

   ሐ/ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ ከአገር ውስጥ ፍጆታ ውጪ ባለ ሌላ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የማይመደብ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነ፤

   ተቀባይነት ያገኘ ዲክላራሲዮን እንደቀረበበት ዕቃ ተቆጥሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ይከናወንበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ውጪ ለሆነና በፖስታ አገልግሎት በኩል ወደ አገር ውስጥ ለገባ ወይም ወደ ውጭ ለሚላክ ዕቃ ራሱን የቻለ የዕቃ ዲክላራሲዮን ተሞልቶ መቅረብ አለበት፡፡

### 39.ውክልና ስለመስጠት

ባለሥልጣኑ ለፖስታ አገልግሎት ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ በሚገቡና ከአገር በሚወጡ ዕቃዎች ላይ ቀረጥ እና ታክስ እንዲሰበስቡ የውክልና ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## በንግድ አገልግሎት ማጓጓዣዎች እና በጉዞ እቃዎች ክምችት ላይ ስለሚፈጸም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

### 40.የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣን በግዚያዊነት እንዲገባ ስለመፍቀድ[30]

1. ማንኛውም ጭነት የያዘ ወይም ያልያዘ የንግድአገልግሎት ማጓጓዣ፡-
   ሀ/ በጉምሩክ ክልል ውስጥ ለአገር ውስጥ ማጓጓዣ አገልግሎት የማይውል ከሆነ፤ እና
   ለ/ በአጠቃቀም ምክንያት ከሚደርስበት መደበኛ እርጅና፣ ከቅባቶችና ነዳጅ መደበኛፍጆታና ከአስፈላጊ ጥገናዎች በስተቀር ምንም ለውጥ ሳይደረግበት ተመልሶ ከአገርእንዲወጣ ለማድረግታስቦ ከሆነ፤

   ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በጊዜያዊነት ወደ ጉምሩክ ክልል እንዲገባ ይፈቀዳል።
2. የውጭ አገር የንግድ ማጓጓዣ ወደ አገርውስጥ በጊዜያዊነት ሊገባ የሚችለውማጓጓዣው በተመዘገበበት አገርናበኢትዮጵያ መካከል በተደረገ ስምምነትመሠረት ወይም የትራንስፖርት ሚኒስቴርሲፈቅድ ብቻ ይሆናል፡፡[31]
3. ባለሥልጣኑ የማጓጓዙ ሥራ ሂደት የሚጠይቃቸውን ሁኔታዎች በማገናዘብ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣው ተመልሶ የሚወጣበትን የጊዜ ገደብ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ በሚመለከተው ሰው ጥያቄና ተቀባይነት ባለው ምክንያት ላይ ተመሥርቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተወሰነውን የጊዜ ገደብ ሊያራዝም ይችላል፡፡
5. .በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረትወደ አገር ውስጥ የገባ የውጭ አገርየንግድ ማጓጓዣ በአገር ውስጥ ጭነትናበወጪ ዕቃ ትራንስፖርት አገልግሎትመሰማራት አይችልም፡፡

---

[30]የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5፣ 6 እና 7 በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (12) የተጨመሩ ናቸው፡፡
[31]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (11) ተሻሻለ

6. 6.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌቢኖርም በልዩ ሁኔታ የትራንስፖርትሚኒስቴር አገር ውስጥ የገባ የውጪ አገርየንግድ ማጓጓዣህጋዊ የወጪ ዕቃ ጭኖከአገር እንዲወጣ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

7. 7.በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ የውጭአገር የንግድ መጓጓዣ በተወሰነለት ጊዜተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ ወይም በአገር ውስጥ ጭነትና በወጪ ዕቃትራንስፖርት አገልግሎት ተሰማርቶ የተገኘ እንደሆነ በአስተዳደራዊ መንገድመቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ማጓጓዣውከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

41.<u>መለዋወጫዎችና መሣሪያዎች በጊዜያዊነት እንዲገቡ ስለ መፍቀድ</u>

1. ለጭነት መጫኛ፣ ማራገፊያ፣ አያያዝ ወይም አጠባበቅ የሚያስፈልግ ልዩ መሣሪያ ከንግድ አገልግሎት ማጓጓዣው ተነጥሎ አገልግሎት ላይ ሊውል የሚችል ቢሆንም ባይሆንም ከንግድ አገልግሎት ማጓጓዣው ጋር ተመልሶ የሚወጣ እስከሆነ ድረስ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ከንግድ አገልግሎት ማጓጓዣው ጋር በጊዜያዊነት ወደ ጉምሩክ ክልል እንዲገባ ይፈቀዳል፡፡ሆኖም አስመጪው የተቀየረውን አካል ከአገር የማስወጣት ወይም ለባለሥልጣኑ ማስረከብ ይኖርበታል።
2. በጊዜያዊነት ወደ ጉምሩክ ክልል አስቀድሞ የገባ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣን በመጠገን ወይም በማደስ ሂደት በማጓጓዣው ላይ የተገጠሙ አካላትንና በማጓጓዣው ላይ አገልግሎት የሚሰጡ መሣሪያዎችን ለመተካት የሚያገለግሉ መለዋወጫዎችና መሣሪያዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ ጉምሩክ ክልል እንዲገቡ ይፈቀዳል።

42.<u>የመድረሻ ዲክላራሲዮን</u>

ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን የያዘ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣ ስለመድረሱ ዲክላራሲዮን እንንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

43.<u>የመውጫ የጉምሩክ ሥነሥርዓት</u>

1. የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣን የሚመለከተው የመውጫ የጉምሩክ ሥነሥርዓት እንደ አግባቡ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ/ የመውጫ ዲክላራሲዮን ለባለሥልጣኑ ማቅረብን፤

ለ/ የማጓጓዣውን ጭነት በጉምሩክ ማሸጊያ እንዲታሸግ ማድረግን፤

ሐ/ ጉዞው የተወሰነ የጉምሩክ መስመርን እንዲከተል ማድረግን፤ እና

መ/ያልተፈቀደ የመውጫ መዘግየትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎች መውሰድን፡፡

2. የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣ ወደ ጉምሩክ ክልል ከገባበት የጉምሩክ ጣቢያ ውጪ በሆነ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ ተመልሶ እንዲወጣ ይፈቀድላታል።

## 44.<u>በሚገባ አውሮፕላን ወይም ባቡር ላይ የተጫነ የጉዞ ዕቃ ክምችት</u>

1. ወደ ጉምሩክ ክልል በገባ አውሮፕላን ወይም ባቡር ላይ የተጫነ ለመንገደኞችና ለማጓጓዣው ሠራተኞች ፍጆታ እንዲውል የተጫነ ዕቃ ወይም ለማጓጓዣው አገልግሎት አሰጣጥ ወይም ጥገና አስፈላጊ የሆነ ዕቃ ከማጓጓዣው ሳይራገፍ እስከቆየ ድረስ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በዓለም አቀፍ የባቡር ማጓጓዣ ላይ ለመንገደኞችና ለባቡሩ ሠራተኞች ፍጆታ እንዲውል የተጫነ እቃ፡-

   ሀ/ የተገዛው የባቡሩ ጉዞ ካቋረጣቸው አገራት ከሆነ፤ እና

   ለ/ በተገዛበት አገር ተከፋይ የሆነው ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ከሆነ፤ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡
3. ባለሥልጣኑ በአውሮፕላኑ ወይም በባቡሩ ላይ ስለተጫነው የጉዞ ዕቃ ክምችት የተለየ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ መጠየቅ የለበትም፡፡
4. አውሮፕላኑ በጉምሩክ ክልል ውስጥ በሚገኝ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አውሮፕላን ማረፊያ የሚያርፍ ከሆነ በአውሮፕላን ማረፊያው ለሚቆይበትና ከአንዱ ወደ ሌላው ማረፊያ በሚያደርገው በረራ ወቅት ለፍጆታ የሚያስፈልገውን የጉዞ ዕቃ ክምችት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲያሟላ ይፈቅድለታል፡፡
5. አጓጓዡ ዕቃውን ላልተፈቀደ ዓላማ እንዳያውል ለመከላከል እንደአስፈላጊነቱ ክምችቱን መቆለፍን ጨምሮ አግባብ ያላቸውን እርምጃዎች እንዲወስድ ባለሥልጣኑ ሊያዘው ይችላል፡፡
6. ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አውሮፕላኑ ወይም ባቡሩ በጉምሩክ ክልል በሚቆይበት ወቅት የጉዞ ዕቃ ክምችቱ ተራግፎ በሌላ ቦታ እንዲቆይ ለማዘዝ ይችላል፡፡

## 45.<u>የጉዞ እቃ ክምችት አቅርቦት</u>

1. ወደ ውጭ አገር መጨረሻ መዳረሻ የሚጓዝ አውሮፕላን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ የሚከተሉትን የጉዞ ዕቃ ክምችቶች ጭኖ ለመሄድ ይችላል፡-

   ሀ/ ባለሥልጣኑ የመንገደኞችንና የአውሮፕላኑን ሰራተኞች ቁጥር፣ በረራው የሚሸፍነውን ርቀት እንደዚሁም በአውሮፕላኑ ውስጥ አስቀድሞ የሚገኘውን የጉ ዕቃዎች ክምችት መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት በቂ ነው ብሎ የሚወስደው የጉዞዕቃዎች ክምችት፤

   ለ/ በአውሮፕላኑ ውስጥ አስቀድሞ የሚገኘውን የጉዞ ዕቃዎች ክምችት ግምት ውስጥ በማስገባት ለአውሮፕላኑ በረራና ጥገና አገልግሎት ያስፈልጋል ተብሎ የሚገመት መጠን ያለው የጉዞ ዕቃዎች ክምችት፡፡

2. ወደ ጉምሩክ ክልል የገባ አውሮፕላን በጉምሩክ ክልል ውስጥ ለመጨረሻ መዳረሻ ጉዞው የሚያስፈልገውንና የተጓደለበትን የጉዞ ዕቃ ክምችት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ለማሟላት ይችላል፡፡

3. ወደ ጉምሩክ ክልል የገባ አውሮፕላን በጉምሩክ ክልል ውስጥ በሚቆይበት ወቅት ለሚኖረው ፍጆታ የሚያስፈልገው የጉዞ ዕቃዎች ክምችት በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች መሠረት ይዞ እንዲገባ በሚፈቀድለት ተመሳሳይ አኳኋን እንዲቀርብለት ባለሥልጣኑ ይፈቅድለታል፡፡

4. ባለሥልጣኑ ከጉምሩክ ክልል የሚወጣ አውሮፕላን የጫነውን የጉዞ ዕቃዎች ክምችት በሚመለከት ለጉምሩክ ቁጥጥር የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ብቻ የያዘ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብለት ሊያዝ ይችላል፡፡

## 46.<u>የጉዞ ዕቃ ክምችትን በሌላ መንገድ አገልግሎት ላይ እንዲውል ስለማድረግ</u>

ወደ ጉምሩክ ክልል ውስጥ በገባ አውሮፕላን ወይም ባቡር ላይ የሚገኝ የጉዞ ዕቃ ክምችት፡-

1. አግባብነት ያላቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ፎርማሊቲዎች መሟላት እንደተጠበቁ ሆነው ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሊለቀቅ ወይም ሌላ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትሊፈጸምበት፤ወይም

2. በባለሥልጣኑ አስቀድሞ ሲፈቀድ ዓለም አቀፍ ጉዞ ወደሚያደርግ ሌላ አውሮፕላን ወይም ባቡር እንደየአግባቡ እንዲተላለፍ ሊደረግ፤

   ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች

### 47.የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች

ለዚህ ምዕራፍ አፈጻጸም "የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃ" ማለት በሚመለከተው የመንግሥት አካል ጥያቄ መሠረት ለአደጋ ተጎጂዎች መርጃ እንዲውሉ የሚሰጡዕቃዎችን፣ተሽከርካሪዎችንና ሌሎች መጓጓዣዎችን፣ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችን፣አልባሳትን፣ ብርድ ልብሶችን፣ ድንኳኖችን ተገጣጣሚ ቤቶችን፣ የውሃ ማጣሪያና ማጠራቀሚያዎችን እና ሌሎች ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ ዕቃዎችን ያጠቃልላል፡፡

### 48.የአስቸኳይ ግዜ የዕርዳታ ዕቃዎች ስለሚስተናገዱበት የጉምሩክ ሥነሥርዓት

1. የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎችን በሚመለከት፦

   ሀ/ ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ እንዲኖር ወይም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የመጨረሻው ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጊዜያዊ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ፤

   ለ/ ዕቃዎቹ ከመድረሳቸው በፊት ዲክላራሲዮኑና ደጋፊ ሰነዶቹ እንዲቀርቡ፣ እንዲመረመሩና እንዲመዘገቡ በማድረግ ዕቃዎቹ እንደደረሱ እንዲለቀቁ፤

   ሐ/ ዕቃዎቹ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ ወይም ከጉምሩክ ጣቢያ ውጭ ሆነው እንዲስተናገዱ እና በዚህም ምክንያት ማንኛውም ክፍያ እንዳይጠየቅባቸው፤ መፍቀድ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎችን በሚመለከት ምርመራ ለማካሄድና ናሙና ለመውሰድ የሚችለው ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ይሆናል፡፡
3. ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ተላላፊ የሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች ምንጊዜም ቅድሚያ ተሰጥቷቸው መስተናገድ አለባቸው።

### 49.ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ስለማድረግ

በሚመለከተው የመንግስት አካል ውሳኔ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ወደ ውጭ የሚላኩ የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች ሊከፈልባቸው ይችል ከነበረው ቀረጥና ታክስ ነፃ ይደረጋሉ።

## ምዕራፍ ስምንት

## የጉምሩክ መጋዘን ሥነ ሥርዓት

## 50. ዕቃዎችን ወደ ጉምሩክ መጋዘን ስለማስገባት

1. ጉምሩክ ወደብ የደረሰ ማናቸዉም ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን መግባት አለበት፡፡
2. ማናቸውም ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የገባ ዕቃ ዝርዝር ሁኔታው እየተገለፀ በመጋዘኑ መዝገብ ላይ ይመዘገባል።
3. ማናቸውም ወደ ቦንድድ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ በመጋዘን ዲክላራሲዮን ተመዝግቦ ለባለሥልጣኑ መቅረብና መፈቀድ አለበት፡፡
4. በጊዜያዊ የጉምሩክ ማከማቻ ውስጥ የሚከማቹ ዕቃዎች ቅርጽና ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው መቆየታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ መያዝ አለባቸው።
5. አደጋ ሊያስከትሉ፣ በሌሎች ዕቃዎች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ወይም አያያዛቸው ልዩ የመጋዘን ዝግጅት የሚጠይቅ ዕቃዎች ለዚሁ ዓላማ ተብለው በተለየ ሁኔታ ዲዛይን በተደረጉ የጉምሩክ መጋዘኖች ብቻ ይስተናገዳሉ።
6. ወደ መጋዘን መግባት ያለባቸው ዕቃዎች ወደ ተባለው መጋዘን ያልገቡ እንደሆነ የመጋዘኑ ኃላፊ ይህንኑ እንዳወቀ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
7. ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ በሚገባበት ጊዜ ሊጠየቅ የሚገባው ሰነድ ዕቃው ለባለሥልጣኑ በቀረበ ጊዜ ዕቃውን ለመለየት ያገለገለው ሰነድ ይሆናል፡፡
8. በጭነት መግለጫው ወይም በሌላ የንግድ ሰነድ የተገለጹት ዕቃዎች በሙሉ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የሚገቡ ከሆነ ባለሥልጣኑ የሚጠይቀው ሰነድ የጭነት መግለጫውን ወይም የንግድ ሰነዱን ይሆናል፡፡

## 51. ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ዉስጥ ስለሚቆዩበት ግዜ[32]

1. ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥአስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፡፡
2. ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአስር ቀናት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፡፡

[32]የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 5፣ 6፣ 8 እና 11 በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (13) የተጨመሩ ናቸው፡፡

3. የቀረጥ ነፃ መሸጫ መደብርን ሳይጨምር ወደጉምሩክ ቦንድ መጋዘን የገባ ማናቸውም የንግድ ዕቃ ወደመጋዘን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በ4 ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞበት ከመጋዘን መውጣት አለበት፡፡ ወደ ቀረጥ ነፃ መደብር የገባ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምበት ጊዜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
4. ወደጉምሩክ ቦንድ መጋዘን የገባ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ለሚዉሉ ምርቶች ማምረቻ የሚውል መሳሪያ፣ መለዋወጫ እና ግብዓት ወደመጋዘን ከገባበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞበት ከመጋዘን መውጣት አለበት፡፡
5. ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን መግባትየነበረበት በስህተት ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ገብቶየተገኘ እንደሆነ በአምስት የስራ ቀናትውስጥ ወደ ጉምሩክ ቦንድድ መጋዘንመተላለፍ አለበት፡፡
6. ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከተፈጸመበት በኋላበሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ከመጋዘንመውጣት አለበት፡፡
7. ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2)፣(3)፣ (4) እና (5) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ካልወጣ ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወር ይደረጋል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች ከመወገዳቸው በፊት የዕቃው ባለቤት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችንና አስተዳደራዊመቀጫውን በመክፈል ዕቃዎቹን በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ የመረከብ መብት ይኖረዋል፡፡
9. ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ የተወሰነለት የመቆያ ጊዜው ከመድረሱ በፊት የመጋዘን ፈቃዱ ከተሰረዘ ቀሪውን ጊዜ ለማጠናቀቅ ወደ ሌላ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን እንዲዛወር ይደረጋል፡፡

10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) መሰረት ዕቃዎችን ወደ ሌላ የጉምሩክ መጋዘን ማዘዋወር የሚያስከትለውን ማናቸውንም ወጪ ፈቃዱ የተሰረዘበት የማከማቻ ባለቤት ይከፍላል።
11. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ የተወሰኑ የጊዜ ገደቦችን በበቂ ምክንያት ሊያራዝም ይችላል፡፡
12. የዚህ አንቀፅ (7) ድንጋጌ ቢኖርም ዕቃውንመልሶ ከአገር ለማስወጣት ጥያቄ ያቀረበአስመጪ በአዋጁ የተወሰነውን 5 በመቶቀረጥና ታክስ በመክፈል ዕቃውን ከአገርመልሶ ማስወጣት ይችላል፡፡[33]

## 52. ዕቃዎች ከጉምሩክ መጋዘን ስለሚወጡበት ሁኔታ

1. ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች በጉምሩክ ሕግ መሠረት ካልሆነና እንደአግባቡ ለሚከተሉት ዓላማዎች ሲባል ተመዝግበው ካልወጡ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ከማከማቻው ወይም ከመጋዘኑ ሊወጡ አይችሉም፡-

   ሀ/ የሚፈለግባቸዉ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ ሲለቀቁ፤

   ለ/ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ለሚያመርት ፋብሪካ እንዲዛወሩ ሲፈቀድ፤

   ሐ/ ወደ ሌላ የጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወሩ ወይም በተላላፊነት እንዲወጡ ሲፈቀድ፤

   መ/ ወደ ውጭ እንዲላኩ ሲፈቀድ፤ ወይም

   ሠ/ ወደ ቀረጥ ነፃ መሸጫ መደብር እንዲገቡ ሲፈቀድ፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 132(9) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከጉምሩክ መጋዘን ከመውጣቱ በፊት በአደጋ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የጥራት ደረጃው የቀነሰ፣ የተበላሸ ወይም የተጎዳ ዕቃ የጥራት ደረጃው መቀነሱ፣ መበላሸቱ ወይም መጎዳቱ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ የጥራት ደረጃው እንደቀነሰ፣ እንደተበላሸ ወይም እንደተጎዳ ይቆጠራል።

## 53. በትርፍነት ስለተገኘ ዕቃ

[33] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (14) የተጨመሩ ናቸው፡፡

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 143(2)ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም የቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ሃላፊ በዕቃ ዲክላራሲዮኑ፣ በጭነት ማኒፌስት ወይም በትራንዚት ሰነድ ከተገለፀው መጠን በላይ ዕቃ ያገኘ እንደሆነ በትርፍ የተገኘውን ዕቃ ዲክላራሲዮኑ ለቀረበለት የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሪፖርት በቀረበበት ትርፍ ዕቃ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ ወዲያውኑ መከፈል አለበት፡፡
3. የቀረጥና ታክስ ክርክር የተነሳባቸውበዋስትና የማይለቀቁ ዕቃዎች ወደ መንግስት የጉምሩክ መጋዘን መዛወርአለባቸው፡፡ ሆኖም በፍርድ ሰጪው አካልየዕቃዎቹ ባለቤት ዕቃዎቹን እንዲወስድየተወሰነ እንደሆነ ክርክር ከተነሳበት ቀንጀምሮ የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔለኮሚሽኑ እስከ ደረሰበት ቀን ድረስዕቃዎቹ በመጋዘን ለቆዩበት ጊዜ መከፈልያለበት የመጋዘን ኪራይ በኮሚሽኑይሸፈናል፡፡[34]

## 54. በጉምሩክ መጋዘን ዉስጥ ስለሚፈቀዱ ስራዎች

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወስድ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የገቡ ዕቃዎች ባለቤት ወይም ባለይዞታ ወይም ዕቃዎችን የመቆጣጣር መብት ያለው ማንኛውም ሰው የዕቃዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚረዱ ሥራዎችን ወይም ዕቃዎቹንእንደገና የማሸግ፣ የመከፋፈል ወይም በየፈርጁ የመመደብ ሥራዎችን እንዲያከናውን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 55. ለናሙና ወጪ ስለሚደረጉ ዕቃዎች

1. ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎችን በሚከተሉት ምክንያቶች ለናሙና በሚሆን መጠን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከመጠናቀቁ በፊት ወጪ ማድረግ ይቻላል፦
   - ሀ/ ዕቃውን በተገቢው ታሪፍ ለመመደብ ዓይነቱንና የተሰራበትን ጥሬ ዕቃ ማረጋገጥአስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤
   - ለ/ የዕቃዉን ዋጋ ለመተመን የዕቃውን ዓይነት፣ ጥራትና የተመረተበትን አገር ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤
   - ሐ/ የዕቃው ናሙና ለፍርድ ቤት ወይም ለፖሊስ ምርመራ እንዲቀርብ ሲታዘዝ፤

[34] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (15) ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ ይተካ ቢልም አንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 3 የሌለው በመሆኑንዑስ አንቀጽ 3 ሆኖ ተጨምሯል ናቸው፡፡

መ/ በዋጋ ሰነዱ ላይ የተሰጠው ዋጋ ለተጠቀሰው ዕቃ መሆኑን ለማረጋገጥ፣

ሠ/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በሚፈቅዳቸዉ ሌሎች ምክንያቶች፡፡

2. ለናሙና የተወሰዱ ዕቃዎች በወጡበት መጠንና ሁኔታ ሥራው እንደተጠናቀቀ ወደ መጋዘን መመለስ አለባቸው። ሆኖም በተፈጥሯቸው ወይም ለማንፃፀሪያ የሚፈለጉ በመሆናቸው ምክንያት ሊመለሱ የማይችሉ ሲሆን ለቀረጥና ታክስ እንዲሁም ለሌሎች ሂሳቦች አተማመን በመጋዘን ውስጥ እንዳሉ ይቆጠራል።

56. <u>በጉምሩክ መጋዘኖች ላይ ስለሚፈፀም የጉምሩክ ቁጥጥር</u>

1. ማንኛውም የጉምሩክ መጋዘንና ወደ መጋዘኑ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡
2. በባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ጉምሩክ መጋዘን መግባት አይችልም።
3. በጉምሩክ መጋዘኖችና ወደ ጉምሩክ መጋዘን በገቡ ዕቃዎች ላይ የሚፈፀም የጉምሩክ ቁጥጥር የሚከተሉትን ለማረጋገጥ የሚወሰድ ማናቸውንም እርምጃ ይጨምራል፡-

ሀ/ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገቡና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞባቸው የሚለቀቁዕቃዎች ባለሥልጣኑ በወሰነው የመዝገብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መመዝገባቸውንና በየጊዜው ሪፖርት የተደረጉ መሆኑን፣

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51(7) የተመለከቱት ዕቃዎች ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እንዲተላለፉ መደረጋቸዉን፣

ሐ/ ዕቃዎች እንደየአይነታቸዉና እንደየባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለጉምሩክ ቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን፣

መ/ የጉምሩክ መጋዘኑ በተሰጠው ፈቃድ መሰረት እየተሠራበት መሆኑን።

57. <u>ዕቃዎችን ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ስለማስተላለፍ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51(7) መሠረት ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን መተላለፍየሚገባቸው ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙበት ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ሃላፊ ዕቃዎቹን፡-

ሀ/ ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን፣ ወይም

ለ/ ባለሥልጣኑ ወደ ሚወስነው ሌላ ማከማቻ ቦታ ማዛወር፣

አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ሃላፊ ዕቃዎቹን ወደ መንግሥትመጋዘን ወይም ባለሥልጣኑ ወደ ሚወስነው ሌላ ማከማቻ ቦታ ማዛወር ያልቻለ

እንደሆነ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ/ በመጋዘን ሃላፊው ወጪ ዕቃዎቹን ራሱ ማዛወር፤ ወይም

ለ/ አስቀድሞ የሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ዕቃዎቹበነበሩበት መጋዘን እንዲቆዩ መወሰን፤

ይችላል፡፡

3. ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ የተያዙ ዕቃዎች፡-

ሀ/ ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እንዲተላለፉ ሊያደርግ፤ ወይም

ለ/ ተከማችተው በሚገኙበት የንግድ ቦታ እንዲቆዩ ለመወሰን፤

ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት ዕቃዎች የተዛወሩበት ማከማቻ ቦታወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) (ለ) መሠረት እንዲቆዩበት የተደረገ መጋዘን ወይም የንግድ ቦታ እነዚህኑ ዕቃዎች በሚመለከት እንደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ይቆጠራል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት እንደ መንግሥት ጉምሩክ መጋዘን የተቆጠረ መጋዘን፣ ማከማቻ ቦታ ወይም የንግድ ቦታ ሃላፊ ለዕቃዎቹ ደህንነትና ለቀረጥና ታክሱ ሃላፊ ይሆናል፡፡

58. <u>የመንግስት የጉምሩክ መጋዘን መዝገብ</u>

1. ባለሥልጣኑ በመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ወይም እንደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን በሚቆጠር መጋዘን፣ ማከማቻ ቦታ ወይም የንግድ ቦታ የተከማቹ ዕቃዎችን በሚመለከት የሚከተሉትን መረጃዎች መዝግቦ መያዝ አለበት፡-

ሀ/ የዕቃውን ዝርዝር፤

ለ/ የዕቃውን መለያ ምልክት፤

ሐ/ የአስመጪዉን ወይም የላኪውን ስምና አድራሻ፤

መ/ ያጓጓዡን ስምና አድራሻ፤

ሠ/ ዕቃዎቹ የተከማቹበትን የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ወይም እንደ

መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የተቆጠረውን መጋዘን፣ የማከማቻ ቦታ ወይም የንግድ ቦታ ስያሜና አድራሻ፤ እና

ረ/ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን፡፡

2. ባለሥልጣኑ ከዕቃዎቹ ወደ አገር ውስጥ መግባት ወይም ወደ ውጭ መላክ እና መጓጓዝ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ቅጅ መውሰድና መያዝ አለበት፡፡

59. <u>ስለመጋዘን ኪራይ</u>

1. የመጋዘን ኪራይ እንደሚከተለው ይታሰባል፡-

ሀ/ ለኪራይ አገልግሎት ወደ ተቋቋመ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸውእስከሚለቀቁ ወይም ወደ ሌላ የጉምሩክ መጋዘን እስከሚዛወሩ ለቆዩበት ጊዜ፤

ለ/ ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች፡-

1) የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ ተይዘው ወይም በባለቤቱ ተትተው የተወረሱ ከሆኑ ከተሸጡበት ጊዜ ጀምሮ ገገርው እስከሚረከብ ለቆዩበት ጊዜ፤

2) የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ ተይዘውና ተወርሰው ከሽያጭና ከስጦታ ውጪ በሌላ መንገድ የሚወገዱ ከሆነ ወደ መጋዘኑ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚወገዱ ለቆዩበት ጊዜ፤

3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51(7) መሠረት ወደ መጋዘኑ የገቡ ከሆነ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው እስከሚለቀቁ ወይም ተሽጠው ገገርው እስከሚረከብ ለቆዩበት ጊዜ፡፡

2. ጉምሩክ መጋዘን ኪራይ ማስከፊያ ተመን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

3. በዋስትና ሊለቀቁ የማይችሉ የተያዙ ዕቃዎች ባለቤቱ እንዲወስዳቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ ውሳኔው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ በመጋዘን ለቆዩበት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ አይከፈልባቸውም፡፡ በዚህ አይነት ባለቤቱ እንዲወስዳቸው የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጣቸው ዕቃዎች ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞባቸው ከመጋዘን መውጣት አለባቸው።

4. በዋስትና ሊለቀቁ የማይችሉ የተያዙ ዕቃዎች በተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን የነበሩ ከሆነ ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ተዛውረው መቆየት አለባቸው።

60. ***ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን እያሉ የባለቤትነት መብት ስለማስተላለፍ***

1. ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ እያሉ የባለቤትነቱ መብት ወደ ሌላ ሰው እንዲተላለፍ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 130 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ እያሉ የባለቤትነት መብቱ የተላለፈለት ሰው ከዕቃዎቹ ጋር በተያያዘ በቀድሞው ባለቤት ላይ በህግና በውል የተጣሉ ግዴታዎችንና ገደቦችን እንዲሁም በህግ መሠረት የተሰጡ ውሳኔዎችን ማክበር ይኖርበታል።

61. ***የተተው ዕቃዎችን ስለማስወገድ***

1. የጉምሩክ ህግ መተላለፍ ያልተፈጸመባቸውና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51(1)፣(2) ወይም (3) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ባለቤቱ በጽሑፍ እንደማይወስዳቸው ገልጾ የተዋቸው ዕቃዎች፡-

   ሀ/ የገበያ ዋጋ ያላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሽያጭ ያስወግዳቸዋል፣ ወይም

   ለ/ የገበያ ዋጋ የሌላቸው ከሆኑ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ዘዴዎች እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡
2. የጉምሩክ ህግ መተላለፍ ያልተፈጸመባቸውና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51(7) መሠረት ወደመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች የአንቀጽ 51(5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

   ሀ/ የገበያ ዋጋ ያላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሽያጭ ያስወግዳቸዋል፣ ወይም

   ለ/ የገበያ ዋጋ የሌላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሚያወጣዉ መመሪያ በሚወሰኑ ዘዴዎች እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

62. ***የተወረሱ ዕቃዎችን ስለማስወገድ***

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተወረሱ ዕቃዎች፡-

   ሀ/ የገበያ ዋጋ ያላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሽያጭ ያስወግዳቸዋል፣ወይም

   ለ/ በህግ በተደነገገ ክልከላ ወይም ገደብ ምክንያት በጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ወይም የገበያ ዋጋ የሌላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያበሚወሰኑ ዘዴዎች እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ፡-

ሀ/ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ቅርስ ሊባሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ወይም ሚኒስቴሩ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል የሚላቸውን ዕቃዎች አግባብነት ላለው የመንግስት አካል ያስተላልፋል፤

ለ/ ለሰብዓዊ እርዳታ ሊውሉ የሚችሉ እቃዎችን አግባብ ላላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

63. <u>የሽያጭ ሥርዓት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61 ወይም አንቀጽ 62 መሠረት የሚፈጸም የዕቃዎች ሽያጭ የሃራጅ ወይም የግልጽ ጨረታ ሥርዓትን የተከተለ ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅት አማካኝነት የሚፈፀም ይሆናል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሸጡ ዕቃዎች የባለቤትነት መብት ለገዥዉ እንዲተላለፍ የሚያስችል ማስረጃ መስጠት አለበት፡፡

64. <u>የሽያጭ ገቢና የማስወገጃ ወጪዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61(1) (ሀ)ወይም 62 (1) (ሀ) መሠረት የተገኘ የሽያጭ ገቢ ከዕቃዎቹ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ የከፈላቸው ወጪዎች ተቀንሰው ተራፊው ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61(2)(ሀ) መሠረት የተገኘ የሽያጭ ገቢ:-

   ሀ/ የቀረጥና ታክስ ሂሳብ፤

   ለ/ ከዕቃዎቹ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ የከፈላቸው ወጪዎች፤

   ሐ/ የመጋዘን ኪራይ እና የማጓጓዣ ወጪ፤ እና

   መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ)፤(ለ) እና (ሐ) በተመለከቱት ሂሳቦች ላይ በባንክ የማበደሪያ ተመን መሠረት የሚሰላ ወልድ፤

   እንደ ቅደም ተከተሉ ተቀንሶ ተራፊው ለዕቃዎቹ ባለቤት ተመላሽ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተመላሽ የሚደረገው ገንዘብ ባለመብት ሽያጩ በተፈፀመ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልጠየቀ ገንዘቡ ለመንግሥት ፈሰስ ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61(1)(ለ) ወይም (2)(ለ) ወይም አንቀጽ 62(1)(ለ) መሠረት ዕቃዎችን ለማስወገድ ባለሥልጣኑ ያወጣውን ወጪ እንደሁኔታው ከዕቃዎቹ ባለቤት ወይም ጥፋተኛ ከሆነው ሰው የማስመለስ መብት ይኖረዋል።

<u>ምዕራፍ ዘጠኝ</u>

## የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው ወደ ዉጭ ተመልሰው ስለሚላኩ ወይም ወደ አገር ውስጥ ተመልሰው ስለሚገቡ እቃዎች

65. **የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን ኢጠናቀው ወደ ዉጭ ለመላክ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች**

1. የምርት ሂደታቸውን በአገር ውስጥ እንዲያጠናቅቁ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡና ከነዚሁ የተገኙ የማካካሻ ምርቶች ወደ ውጭ አገር እንዲላኩ የሚፈቀድበት ሁኔታ በውጭ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት መሠረት ይፈጸማል፡፡
2. ዕቃዎች የጥገና ሂደታቸውን በአገር ውስጥ እንዲያጠናቅቁ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው መውጣት አለባቸው። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ባለሥልጣኑ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

66. **የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው እንዲመለሱ ወደ ዉጭ አገር ስለሚላኩ ዕቃዎች**

1. ዕቃዎች የምርት ሂደታቸውን በውጭ አገር እንዲያጠናቅቁ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር ሊላኩ ይችላሉ፡፡
2. ዕቃዎች በአገር ውስጥ ለመጠገን የማይችሉ መሆናቸው ተረጋግጦ በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ በውጭ አገር ተጠግነው እንዲመለሱ በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር ሊላኩ ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት በጊዜያዊነት ወደ ውጭ የተላኩ ዕቃዎች የምርት ወይም የጥገና ሂደት ውጤት የሆኑ የማካካሻ ምርቶች ዕቃዎቹ በጊዜያዊነት ከተላኩ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ አገር ውስጥ ተመልሰው መግባት አለባቸው፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ቢኖርም ወጪ ዕቃዎችን የሚመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን

አጠናቀው እንዲመለሱ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር የተላኩበትን ሥነ ሥርዓት የቀጥታ ወደ ውጭ መላክ የዕቃ ዲክላራሲዮን በማቅረብ እንዲቋረጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

67. <u>የቀረጥና ታክስ ክፍያ</u>

1. የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውንአጠናቀው እንዲመለሱ በጊዜያዊነት ወደውጪ የሚላኩ እቃዎች ቀረጥና ታክስአይከፈልባቸውም፡፡ ሆኖም የማካካሻምርቶቹ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 66 (3) መሰረት ተመልሰው ወደ አገር ውስጥካልገቡ በእቃዎቹ ላይ የሚፈለገው ቀረጥናታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረትአስተዳደራዊ ቅጣት ይከፈልባቸዋል፡፡[35]
2. በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማካካሻ ምርቶች ወደ ውጭ አገር ሲላኩ ወይም ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ በዕቃዎቹ ላይ የሚፈለግባቸው ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ አወሳሰን ዘዴ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡ ሆኖም የጥገና ውጤት የሆኑ ማካካሻ ምርቶችን የሚመለከት ቀረጥና ታክስ የሚሰላው በጥገና ወጪው ላይ ተመሥርቶ ይሆናል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው እንዲመለሱ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር የተላኩ ዕቃዎች ለውጥ ሳይደረግባቸው በነበሩበት ሁኔታ የሚመለሱ ወይም ያለክፍያ ተጠግነው የሚመለሱ ከሆነ ቀረጥና ታክስ አይከፈልባቸውም፡፡

<u>ምዕራፍ አሥር</u>

<u>ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ለአገር ውስጥ ፍጆታ የምርት ሂደታቸዉን እንዲያጠናቅቁ ስለሚደረግበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት</u>

68. <u>ሥነ-ሥርዓቱ በጥቅም ላይ እንዲውል ስለመፍቀድ</u>

1. ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊትበጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ በባለሥልጣኑ ሊፈቀድ የሚችለው፡-

---

[35]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (16) ተሻሻለ

ሀ/ አሠራሩ የሂደቱ ውጤት የሆኑትን ምርቶች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ከተደረጉት ዕቃዎች የተገኙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሲሆን፤ እና

ለ/ የምርት ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ዕቃዎቹን ቀድሞ ወደነበሩበት ሁኔታ መልሶ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲሰጡ ለማድረግ የማይቻል ሲሆን፤

ነው፡፡

2. ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የምርት ግዴታቸውን እንዲያጠናቅቁ በማድረግ ተግባርላይ በመደበኛነት ለሚሠማራ ሰው ሂደቱን የሚሸፍን አጠቃላይ ፈቃድ ባለሥልጣኑ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ሊደረጉባቸው የሚችሉ ዕቃዎች ዓይነት፣ ፈቃድ ለመስጠት መሟላት የሚገባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች እና የጉምሩክ ቁጥጥሩን የሚመለከቱ እርምጃዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያይወስናሉ።

4. ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ የማድረግ ተግባርየዕቃዎቹ አስመጪ ከሆነው ሰው ውጪ በሌላ ሰው እንዲከናወን የሚፈቀድበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

69.<u>የቀረጥ እና ታክሱ አከፋፈል</u>

ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው ምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ ሲደረግ እነዚህ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሊለቀቁ የሚችሉት ምርቶቹን ለማምረት ወደአገር ውስጥ በገቡት ጥሬ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል በሚገባው ታሪፍ መሠረት ቀረጥና ታክስ ከተከፈለ በኋላ ይሆናል፡፡

70.<u>ሥነ-ሥርዓቱ ስለሚቋረጥባቸዉ ሁኔታዎች</u>

1. ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቀጥጥር ሥር ሆነው የምርት ሂደታቸዉን እንዲያጠናቅቁ የሚደረጉበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ወደአገር የገቡት ጥሬ ዕቃዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ69 መሠረት ቀረጥና ታክሱ ተከፍሎባቸው ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲለቀቁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 68 መሠረት የተፈቀደው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ይቋረጣል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ምክንያት ኖሮ ወደአገር የገቡት ጥሬዕቃዎች ሌላ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈጸምባቸው በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 መሠረት የተፈቀደው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ይቋረጣል፤ ሆኖም ተፈጻሚ እንዲሆን የሚፈቀደውን ሌላውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦች መከበር ይኖርባቸዋል።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ወይም ወደ ውጭ ስለሚ ላኩበት እና ተመልሰው ስለሚገቡበት ወይም ስለሚላኩበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

### 71.በጊዜያዊነት ዕቃዎችን ስለማስገባት

1. ንግድን ከማስተዋወቅ፣ ከቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ከቱሪዝምና ከባሕል ልውውጥ፣ ከግንባታ ሥራ፣ ከምክር አገልግሎት ወይም ከዕርዳታ ሥራ ጋር የተያያዙ ዕቃዎች የመጡበት ምክንያት እንደተጠናቀቀ በመጡበት አኳኋን እንዲወጡ ሆኖ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በዋስትና በጊዜያዊነት እንዲገቡ በባለሥልጣኑ ሊፈቀድ ይችላል፤ ሆኖም መለዋወጫዎችና ሌሎች አላቂ እቃዎች በጊዜያዊነት ሊገቡ አይችሉም።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(1) ከተመለከቱት ውጪ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደአገር ውስጥ የሚገቡባቸው ሌሎች ሁኔታዎች የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡[36]
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ዕቃዎች በሌላ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተመደቡ ዕቃዎችንም እንዲጨምር ሊደረግ ይችላል፡፡
4. በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባን ዕቃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ከተደረገበት ዓላማ ውጪ በጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ነው፤ ሆኖም በጉምሩክ ክልል ቆይታ ጊዜው የዕቃውን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ተግባራት ሊከናወኑበት ይችላል፡፡

[36]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (17) ተሻሻለ

5. ከግንባታ ሥራዎች ወይም ከምክር አገልግሎት ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎች አገር ውስጥ እንዲቆዩ በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ ዕቃዎቹን በጊዜያዊነት ለማስገባት መብት ላላቸው ሰዎች እንዲተላለፉ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
6. በጊዜያዊነት ገብተው ተመልሰው በሚወጡ ያገለገሉ ዕቃዎች እርጅና ዋጋ ላይ ዕቃዎቹ ሲወጡ ባለው ታሪፍ መሰረት ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡
7. በጊዜያዊነት ያስገባውን ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ለሌላ የሚያስተላልፍ ሰው ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እስከተላለፈበት ጊዜ ድረስ በሚታሰበው የእርጅና ቅናሽ ላይ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
8. ከፕሮጀክት ሥራዎች ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች አገልግሎት ላይ የዋሉበት ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ለተከናወነው ስራ የመጨረሻ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ወይም የፕሮጀክቱ ጊዜ ከተራዘመ ይህንኑ የፕሮጀክቱ ባለቤት ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት፡፡
9. በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች በአገር ውስጥ የሚቀሩበት ሁኔታና የቀረጥና ታክስ ክፍያው አፈፃፀም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 72.ዕቃዎች በጊዜያዊነት እንዲገቡ ስለማይፈቀድበት ሁኔታ

1. ዕቃዎች ተለይተው በማይታወቁበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ፈቃድ ላይሰጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ የዕቃዎቹ ተለይተው አለመታወቅ ዕቃዎቹ ካላቸው ተፈጥሯዊ ባህሪና ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ በሥርዓቱ ያለአግባብ የመጠቀም ሁኔታ ሊከሰት ያለመቻሉን ካረጋገጠ ዕቃዎቹ በጊዜያዊነት እንዲገቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 73.በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎች አገር ዉስጥ ስለሚቀዩበት ጊዜ[37]

1. ከቱሪዝምና ከባህል ልውውጥ ወይም ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር የተያያዙ ዕቃዎችወደ አገር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው መውጣት አለባቸው።

[37]የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (18) ተሻሻሉ እንዲሁም በአንቀጽ 2 (19) ንዑስ አንቀጽ (7)፣ (8)፣ (9)፣ (10)፣(11): (12) እና (13) ተጨምረዋል

2. ንግድ ለማስተዋወቅ የገቡ ዕቃዎች የማስተዋወቁ ተግባር በተጠናቀቀ በሁለት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ መውጣት አለባቸው።
3. ለግንባታ ሥራ፣ ለምክር አገልግሎት፣ ከእርዳታ ሥራ ጋር በተያያዘ ወይም በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች በፕሮጀክቱ ስምምነት የተገለፀው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ወይም ፕሮጀክቱ ወይም የእርዳታ ሥራው እንደተጠናቀቀ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ተመልሰው መውጣት አለባቸዉ፡፡
4. በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ በዚህ አዋጅ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ተመልሶ ከአገር ሊወጣ የማይችል መሆኑን አስመጪው ከጠየቀና በቂ ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ባለሥልጣኑ የጊዜ ገደቡን ሊያራዝምለት ይችላል፡፡
5. በአዋጁ አንቀጽ 73 (4) መሠረት ዕቃው አገር ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በሕግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ከአገር መውጣትአለበት፡፡ ሆኖም ዕቃው ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ በእርጅና ቅናሹ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ እንዲሁም አስተዳደራዊ መቀጫ ሲከፈል የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ተደርጎ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
6. ማንኛውም ቱሪስት ተሽከርካሪን ጨምሮ የያዘውን የግል መገልገያ ዕቃ፣ በዋስትና በማስመዝገብ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
7. ወደ አገር ውስጥ የገባ ቱሪስት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልገጠመው ወይም የመቆያ ጊዜው ካልተራዘመለት በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 73 (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ማውጣት ያለበት ሲሆን ዕቃውን ከአገር ያላስወጣ እንደሆነ ዕቃው ውርስ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡
8. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት አግባብነት ባለው ማስረጃ የሚረጋገጥ ከባድህመም ወይም በህግ ቁጥጥር ሥር መዋል ወይም ከአገር እንዳይወጣ መታገድ ወይም የዕቃው መጥፋት ወይም መጐዳት እና ከነዚህ ጋር ተመሣሣይ የሆነ ቱሪስቱ እንዳይመለስ የሚያደርግ ማንኛውም አስገዳጅ ሁኔታ ማለት ነው፡፡
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ቱሪስቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ፈቃድ ያገኘ እንደሆነ ወደ አገር ውስጥ ያስገባው ዕቃ የመኖሪያ ፈቃድ

በተገኘበት ቀን ወደ አገር ውስጥ እንደገባ ተቆጥሮ የጉምሩክ ሥነ- ሥርዓት በመፈጸም ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ዕቃው አገር ውሰጥ እንዲቀር ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

10. በጊዜያዊነት ዕቃ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ሰው ዕቃውን ከአገር ለማስወጣት የማይችልበት በቂ ምክንያት ካቀረበ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በመፈጸም በዕቃው ላይ ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቀር ሊፈቀደለት ይችላል፡፡
11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 የተመለከተው ቢኖርም ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቀር የቀረበው ጥያቄ ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቆይ የተፈቀደለት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ከሆነ በዕቃው ላይ ሊከፍል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ አስመጪው ያስያዘው ዋስትና ተመላሽ ተደርጎ የቀረጥና ታክሱን 25 በመቶ መቀጫ ከፍሎ ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቀር ይደረጋል፡፡
12. በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ በዚህ አንቀጽ መሠረት ተመልሶ ከአገር ያልወጣ ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞበት አገር ውስጥ እንዲቀር ያልተፈቀደለት እንደሆነ ዕቃው ይወረሳል፡፡
13. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ቱሪስት" ማለት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየት ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን ለሥራ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባን ሰው አይጨምርም፡፡

## 74. በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነፃ ስለማድረግ[38]

የገንዘብ ሚኒስቴር በጊዜያዊነት ወደ አገርውስጥ የገቡ ዕቃዎች በከፊል ወይምሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነፃ ሊሆኑስለሚችሉበት ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡

## 75. በጊዜያዊነት ወጥቷው የሚመለሱ ዕቃዎች[39]

1. የሚከተሉት ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው በጊዜያዊነት ከአገር ከወጡ በኋላ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ

[38] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (20) ተሻሻለ
[39] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (21) ተሻሻለ

ሀ) ወደ ውጭ አገር ለሥራ ወይም ለጉብኝት የሄደ ሰው የሄደበትንሥራ ለማከናወን የሚጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች፣ መሣሪያዎችናማሽነሪዎች፤

ለ) ለንግድ ማስተዋወቅና ለባህልልውውጥ ወይም በማናቸውም ዓይነትትርዒት ወይም ኤግዚቢሽን ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች፤

ሐ) በፕሮጀክት ስምምነት መሠረትለሥራ ወደ ውጭ የሚወጡ ዕቃዎች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በጊዜያዊነት ከአገር የወጡዕቃዎች የሄዱበትን ዓላማ አጠናቀውወደ አገር ውስጥ ሲመለሱ ቀረጥና ታክስየማይከፈልባቸው በአንድ ዓመት ጊዜውስጥ ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ የገቡእንደሆነ ብቻ ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም በፕሮጀክት ስምምነት ለሥራ ወደ ውጭ አገር ወጥተው የሚመለሱ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው በፕሮጀክት ስምምነቱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ገደብ ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ ያልገቡ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ በቂ ምክንያት ሲቀርብለት ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበትን ጊዜሊያራዝም ይችላል፡፡

## 76.ተመልሰው ስለሚወጡና ተመልሰው ስለሚገቡ ዕቃዎች

1. ለአገር ውስጥ ፍጆታ ተብሎ ወደ አገር የገባ ዕቃ ያልተከለከለ ወይም አገባቡ የጉምሩክ ሕግን የማይፃረር ከሆነ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከመከናወኑ በፊት ወይም ከተከናወነ በኋላ ዕቃው ለነፃ ዝውውር ከመለቀቁ በፊት ወደውጭ አገር ተመልሶ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ 5 በመቶ ተከፍሎበት እንዲወጣ ሊፈቀድ ይችላል፡፡[40]

2. የአገር ውስጥ ምርት ሆነው ወደ ውጭ ከተላኩ በኋላ በሽያጭ ውሉ ወይም በንግድ ግንኙነት የተመለከተውን የጥራት ደረጃ ባለሟሟላታቸው ምክንያት በአንድ ዓመት

[40]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (22) ተሻሻለ

ጊዜ ውስጥ ተመልሰው ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ። ሆኖም ለእነዚህ ዕቃዎች ማምረቻ በዋለው ግብዓት ላይ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ በተደነገገው መሠረት ሳይከፈል ቀርቶ የነበረው ቀረጥና ታክስ መከፈል አለበት፡፡

3. በባለጉዳዩ ጥያቄ መሠረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በአሳማኝ ምክንያት ሊራዘም ይችላል፡፡

77. <u>**ዕቃን በጊዜያዊነት የማስገባት ወይም የማስወጣት የጉምሩክ ሥነሥርዓት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ**</u>

እንደ አግባቡ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎችን የሚመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ዕቃዎች በጊዜያዊነት የገቡበትን ወይም የወጡበትን ሥነ-ሥርዓት የቀጥታ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ወደ ውጭ የመላክ የዕቃ ዲክሳራሲዮን በማቅረብ እንዲቋረጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

## <u>ምዕራፍ አስራ ሁለት</u>

## <u>የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትን በኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልዉዉጥ ሥርዓት ስለማከናወን</u>

78. <u>**ጠቅላላ**</u>

1. በባለሥልጣኑ በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲጠቀም የተፈቀደለት ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማከናወን ይችላል፡-

ሀ/ ማጓጓዣዎች ስለመድረሳቸው ወይም ስለመነሳታቸው እና በነዚሁ ላይ ስለተሳፈሩ መንገደኞች ወይም ስለተጫኑ ዕቃዎች ሪፖርቶችን ማቀነባበርና ማቅረብ፤

ለ/ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ማከናወን፤

ሐ/ ክፍያዎችን መፈጸም፤ እና

መ/ የዕቃ መልቀቅያ ትዕዛዝ መቀበል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረግ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት አጠቃቀም ደጋፊ ሰነዶች በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዲቀርቡ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡

3. የወጪና ገቢ ዕቃዎችን በሚመለከት የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የሚመለከታቸዉ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የፋይናንስ ተቋማት

በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባለሥልጣኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡

79.<u>ተጠቃሚዎችን ስለመመዝገብ</u>

ማንኛውም በባለሥልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን እንዲፈቀድለት የሚፈልግ ሰው፡-

1. በባለስልጣኑ የተወሰነውን ደረጃ የጠበቀ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ፋሲሊቲበማሟላት፤
2. የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓቱን የአጠቃቀምና የደህንነት መመሪያዎች የሚያከብር ስለመሆኑ ማረጋጫ በመስጠት፤
3. ዲጂታል ፊርማውን ከተፈቀደለት ውጪ ሌላ ሰው እንደማይጠቀም ማረጋገጫ በመስጠት፤
4. ከተፈቀደለት ውጪ ሌላ ሰው ዲጂታል ፊርማውን ተጠቅሞ ቢገኝ ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ የማስታወቅ ሃላፊነቱን እንደሚወጣ በማረጋገጥ፤ እና
5. በባለስልጣኑ ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ስምምነት በመፈረም፤

በባለሥልጣኑ መመዝገብ አለበት፡፡

80.<u>መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ስለመላክና ስለመቀበል</u>

1. የባለሥልጣኑን የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመጠቀም የሚላክ ማንኛውም መረጃ ከተፈቀደው የዲጂታል ፊርማ ጋር ተያይዞ መላክአለበት፡፡
2. ማንኛውም መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ተልኳል የሚባለው በላኪው በራሱ ወይም መልዕክቱን በሚመለከት ጉዳይ ላኪውን ወክሎ ለመሥራት ሥልጣን በተሰጠው ሰው የተላከ ሲሆን ነው፡፡
3. በባለሥልጣኑና የተፈቀደለት የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓትተጠቃሚው መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ስለመቀበላቸው መተማመኛ አሰጣጥን በተመለከተ የተወሰነ ፎርም ለመከተል ያደረጉት ስምምነት በሌለ ጊዜ የመልዕክቱ መድረስ መተማመኛ በማንኛውም ዘዴ ሊሰጥ ወይም መድረሱን በበቂ ደረጃ ሊያመላክት በሚችል ድርጊት ሊገለጽ  ይችላል።
4. ባለስልጣኑና የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ ተጠቃሚ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ መልዕክት አስገዳጅነት የሚኖረው መልዕክቱ ስለመድረሱ መተማመኛ ሲስጥ

ነው የሚል ስምምነት ካላቸው ይኸው መተማመኛ በስምምነቱ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ካልተሰጠ መረጃው እንዳልተላከ ይቆጠራል።

81.**<u>በኤሌክትሮኒክስ የሚላኩ መረጃዎችን ስለማረጋገጥ</u>**

በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የተላኩ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ ኦሪጅናል ዶኩሜንቶችን አስቀርቦ ማየት ይችላል፡፡

82.**<u>የወረቀት ሰነድ ስለመጠቀም</u>**

1. የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ ባለመሥራቱ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ መላክ ወይም መቀበል በማይቻልበት ጊዜ ተጠቃሚውና ባለሥልጣኑ መረጃዎችን በወረቀት መለዋወጥ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) የተደነገገው ቢኖርም የኤሌክትሮኒክስ ስርዓቱ በሚሰራበት ጊዜ ተጠቃሚው የተለመደውን የጉምሩክ ሥነሥርዓት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማከናወን አለበት፡፡

83.**<u>የተጠቃሚነት መብትን ስለማገድና ምዝገባን ስለመሠረዝ</u>**

1. ማንኛውም የባለሥልጣኑ የኤሌክትሮነክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚ ከባለሥልጣኑ ጋር ባደረገው ስምምነት የተመለከቱ ግዴታዎችን ያላከበረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን አስከሚያስተካክል ድረስ በሥርዓቱ የመጠቀም መብቱ ታግዶ ይቆያል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ምክንያቶች የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚን ምዝገባ ሊሠርዝ ይችላል፡-

   ሀ/ ምዝገባው የተከናወነው ተጠቃሚው ባቀረበው የሀሰት ማስረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

   ለ/ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለእግዱ ምክንያት የሆኑትን ጉድለቶች ያላስተካከለ እንደሆነ፤

   ሐ/ ተጠቃሚው የጉምሩክ ህጎች በመጣስ ወይም በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሶየተቀጣ ከሆነ፤ወይም

   መ/ በማናቸውም ምክንያት የተጠቃሚዉ የንግድ ድርጅት የተዘጋ ከሆነ፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት በኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት የመጠቀም መብትን ከማገዱ ወይም ምዝገባውን ከመሠረዙ በፊት እርምጃው

የሚወሰድበትን ምክንያት ለተጠቃሚው በጽሑፍ በማሳወቅ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ ስርዓት

84. ሥነ-ሥርዓቱ ስለሚፈቀድላቸው ሰዎች

1. ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብና የዕቃ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ተፈጻሚ እንዲሆን የሚፈቀደው ባለሥልጣኑ ያወጣውን መመዘኛ አሟልተው ለተመረጡና ለተመዘገቡ ሰዎች ነው፡፡
2. ሥነ-ሥርዓቱ ተፈጻሚ እንዲሆንላቸው የሚፈቀድላቸውን ሰዎች ለመምረጥ ባለሥልጣኑ የሚያወጣው መመዘኛ ለላኪዎችና ለኢንዱስትሪ አምራቾች ልዩ ትኩረት የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

85. ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ

ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ ሥነ ሥርዓት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

1. ዕቃዎችን ለመለየት የሚያስፈልጉ ውስን መረጃዎች እስከቀረቡ ድረስ የተሟላው የዕቃ ዲክላራሲዮን በቀጣይነት እንዲቀርብ በመፍቀድ ዕቃዎቹን መልቀቅን ፤
2. ዕቃዎችን አዘወትሮ ከውጭ ለሚያስመጣ ወይም ወደ ውጭ ለሚልክ በሥርዓቱ እንዲጠቀም ለተፈቀደለት ሰው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለሁሉም ዕቃዎች የተጠቃለለ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ መፍቀድን፤
3. በሥርዓቱ እንዲጠቀም በተፈቀደለት ሰው መዝገብ ላይ በሠፈሩ መረጃዎች አማካይነት የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብና በቀጣይነትም በሚቀርብ ተጨማሪ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲደገፍ መፍቀድን፡፡

86. ቀለል ያለ የዕቃ አወጣጥ ሥነ ስርዓት

ቀለል ያለ የዕቃ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት የዕቃ አወጣጥ ሥርዓቱ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የሥራ ቦታ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው ሌላ ቦታ እንዲፈጸም የሚፈቅድ ሥርዓት ይሆናል፡፡

87. የቀረጥና ታክስ ዕዳዎችን በራስ ትመና ስለመወሰን

በሥርዓቱ እንዲጠቀም የተፈቀደለት ሰው የቀረጥና ታክስ ዕዳውን የንግድ መዝገቦቹን ተጠቅሞ እራሱ እንዲተምንና አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ሌሎች የጉምሩክ ግዴታዎቹን ማክበሩን እራሱ እንዲያረጋግጥ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

88. <u>ኦዲትን መሰረት ያደረገ የጉምሩክ ቁጥጥር</u>

ባለሥልጣኑ ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን ትክክለኛና ተዓማኒነት ያለው መሆኑን እና ሌሎች የጉምሩክ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በሥርዓቱ እንዲጠቀም የተፈቀደለትን ሰው መዝገቦችን፣ ሪከርዶችን፣ የንግድ አሠራር ሥርዓቶችን እና የንግድ መረጃዎችን በመመርመር ኦዲትን መሠረት ያደረገ የጉምሩክ ቁጥጥር ያካሂዳል።

## ክፍል አራት

## ስለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ

## ምዕራፍ አንድ

## የቀረጥና ታክስ መስከፈያ ዋጋ አተማመን

89. <u>መርህ</u>

1. ቀረጥንና ሌሎች በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጠየቁ ክፍያዎችን ለማስላት እንዲሁም የውጭ ንግድን በሚመሩ ህጎች የተዘረዘሩትን ታሪፍ ያልሆኑ እርምጃዎች በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል የሚተመነው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል፡፡
2. ወደ አገር ለሚገባ ማናቸውም ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ ጠቅላላ ወጪ ነው፡፡
3. ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው ዕቃው የተሸጠበትና ከኢትዮጵያ መውጫ እስከሆነው የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ የሚያስፈልገው ወጪ ድምር ይሆናል፡፡
4. በዚህ አዋጅ ስለተዘረዘሩት የዋጋ መተመኛ ዘዴዎች አፈፃፀም እና በእነዚሁ ዘዴዎች መሠረት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መወሰን በማይቻልበት ጊዜ እንዲሁምላገለገሉ ዕቃዎች ተፈጻሚ ስለሚሆኑት የዋጋ መተመኛ ዘዴዎች ባለሥልጣኑ መመሪያ ያወጣል።

5. ባለሥልጣኑ በግብይት ዋጋ መሠረት ቀረጥና ታክሱን መወሰን ባልተቻለ ጊዜ በዚህ አዋጅ መሰረት ቀረጥና ታክሱን ለመወሰን የሚያስችል መረጃ ያደራጃል፡፡

## 90.የግብይት ዋጋ

1. ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ዕቃ የግብይት ዋጋ ተደርጎ የሚወስደው ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ለተሸጠው ዕቃ በትክክል የተከፈለው ወይም የሚከፈለዉ ዋጋ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96[41] የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች የታከለበት ይሆናል፡፡ ሆኖም፡-

   ሀ/ በህግ ወይም ህግን መሰረት ባደረገ ልዩ ውሳኔ ከተጣሉ ገደቦች ዕቃዎቹ እንደገና ሊሸጡ የሚችሉበትን መልካ ምድራዊ አካባቢ ከሚወስኑ ገደቦች ወይም በዕቃዎቹ ዋጋ ላይ የጎላ ተፅዋ ከማያሳድሩ ገደቦች በስተቀር ገዥው የገዛቸውን ዕቃዎች ለሌላ የሚያስተላልፍበትን ሁኔታ ወይም አጠቃቀሙን አስመልክቶ ሌሎች ተጨማሪ ገደቦች ሊደረጉ አይችሉም፤

   ለ/ የዕቃው ሽያጭ ወይም ዋጋው ሊተመኑ የማይችሉ ሁኔታዎች ወይም ገደቦች የተጣለበት ሊሆን አይችልም፤

   ሐ/ በገዥው ከሚፈጸም የመልሶ ሽያጭ፣ ማስተላለፍ ወይም አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከሚገኝ ገቢ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሻጩ የሚከፈል ገንዘብ ሊኖር አይችልም፤

   መ/ገዥውና ሻጩ ግንኙነት ያላቸው ከሆነ የግብይት ዋጋው የቀረጥና ታክስ መተመኛ ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

2. ገዥና ሻጭ ግንኙነት አላቸው ሊባል የሚችለው፡-

   ሀ/ አንዱ የሌላው የንግድ ድርጅት ባለሥልጣን ወይም ዳይሬክተር ከሆነ፤

   ለ/ በሕጋዊ መንገድ ዕውቅና ያገኙ የንግድ ሸሪኮች ከሆኑ፤

   ሐ/ የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ካላቸው፤

   መ/ አንዱ የሌላውን የንግድ ድርጅት አክስዮኖች ከ5 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በባለቤትነት ከያዘ፤

   ሠ/ አንዱ ሌላውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠር ከሆነ፤

   ረ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሶስተኛ ወገን ቁጥጥር የሚደረግባቸው ከሆነ፤

   ሰ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሶስተኛ ወገን ላይ ቁጥጥር የሚያደርጉ ከሆነ፤

[41]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (23) ተሻሻለ

ወይም

ሸ/ እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ካላቸው፤

ነው፡፡

3. ሻጭና ገዥው ግንኙነት ሲኖራቸው በሽያጩ ዙሪያ ያሉት ሁኔታዎች ተመርምረው በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በዋጋው ላይ ተፅኖ እንዳላሳደረ ሲታመን የግብይት ዋጋው ተቀባይነት ያገኛል።
4. የሻጭና ገዥው ግንኙነት በዋጋው ላይ ተፅኖ ማሳደሩን ለማመን የሚያስችል ምክንያት ሲኖር ባለሥልጣኑ ይህንኑ ለአስመጭው መግለጽ አለበት፡፡
5. ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል በተፈጸመ ሽያጭ የዕቃዎቹ ዋጋ፡-

   ሀ/ በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት በሌላቸው ገዥና ሻጭ መካከል በተከናወነ ሽያጭ ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይነት ካላቸው ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር፤

   ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 93 በተወሰነው መሠረት ከአንድ ዓይነት ወይም ከተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር፤ ወይም

   ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 94 በተወሰነው መሠረት ከአንድ ዓይነት ወይም ከተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር፤

   የሚቀራረብ መሆኑን አስመጪው ለማረጋገጥ ከቻለ የዕቃዎቹ የግብይት ዋጋ ተቀባይነት ይኖረዋል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተጠቀሱትን ማነፃፀሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ የንግድ ደረጃ ልዩነት፣ የብዛት ልዩነት፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96 መሠረት በዋጋ ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች እና ሻጩ ከገዢው ጋር ባልተዛመደበት ሁኔታ ያወጣቸው ወጪዎች እና ሻጩ ከገዢው ጋር በተዛመደበት ሁኔታ ደግሞ እነዚህ ወጪዎች በሻጩ ያልተከፈሉ መሆናቸው ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተጠቀሱት ማነፃፀሪያዎች በአስመጪው አነሳሽነት በጥቅም ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡

91.<u>አንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን</u>

1. ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 90 መሠረት ሊወስን ካልቻለ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡና

በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ አንድ ዓይነት ዕቃዎች የግብይት ዋጋ መስረት ይወሰናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ካልተቻለ የንግድ ደረጃው ወይም የብዛቱ ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ በተለየ የንግድ ደረጃ ወይም ብዛት ወደ አገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ መጠቀም ይቻላል፡፡
3. የግብይት ዋጋው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96(1) የተጠቀሱትን ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዣ ዋጋ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ የገቡትንና አንድ ዓይነት የሆኑትን ዕቃዎች አስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከሰቱ የማጓጓዣ፣ የመጫን፣ የማዉረድ የአያያዝና የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

## 92.<u>የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን</u>

1. ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 90 እና አንቀጽ 91 መሠረት ሊወስን ካልቻለ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡና በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ ተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ መሠረት ይወሰናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ካልተቻለ የንግድ ደረጃው ወይም የብዛቱ ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ በተለየ የንግድ ደረጃ ወይም ብዛት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ መጠቀም ይቻላል፡፡
3. የግብይት ዋጋው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96(1) የተጠቀሱትን ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዣ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ የገቡትንና ተመሳሳይ የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ ወጪ የተደረገውን የማጓጓዣ፣ የመጫን፣ የማውረድ፣ የአያያዝና የኢንሹራስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

## 93.<u>ወደ ኋላ የማስላት ዘዴ</u>

1. ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 90 እስከ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሰረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ በተቀራራቢ ወቅት ወደ አገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ወይም

ተመሳሳይ ዕቃዎች ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል በገቡበት ሁኔታ በከፍተኛ ብዛት በተሸጡበት ነጠላ ዋጋ ላይ በመመሥረትና የሚከተሉትን ከዋጋው ላይ በመቀነስ ይወሰናል፡-

ሀ/ ለዕቃዎቹ አብዛኛውን ጊዜ የሚከፈለውን ኮሚሽን ወይም የሚደመረውን የጠቅላላ ወጪና የትርፍ መጠን፤

ለ/ ለዕቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚከፈሉትን የማጓጓዣ፣ የኢንሹራንስና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች፤ እና

ሐ/ ዕቃዎቹ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ የሚከፈለውን ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች፡፡

2. ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃና ወደ አገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በተቀራራቢ ጊዜ በአገር ውስጥ ካልተሸጡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወሰነው የግብይት ዋጋ ከሶስት ወራት ባልበለጠ የጊዜ ልዩነት ውስጥ ወደ አገር ውስጥ በገቡና በተሸጡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች ነጠላ ዋጋ ላይ ይመሠረታል።

3. ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ እና አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በገቡበት ሁኔታ ካልተሸጡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወሰነው የግብይት ዋጋ በዕቃዎቹ ላይ የተከናወነው ቀጣይ የምርት ሂደት ያስከተለው ተጨማሪ ዕሴት ተቀንሶ ይተመናል፡፡

## 94.<u>በወጪ ስሌት ላይ የተመሰረተ ዋጋ</u>

1. ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 90 እስከ አንቀጽ 93 በተደነገገው መሰረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ፡-

ሀ/ የዕቃዎቹን የማምረቻ ወይም የማዘጋጃ ወጪዎች፤

ለ/ ዕቃዎቹ ወደ ኢትዮጵያ በተላኩበት አገር ተቀራራቢ ደረጃ ወይም ዓይነት ያላቸው ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ አብዛኛውን ጊዜ የሚያስከትሉትን ጠቅላላወጪና የሚያስገኙትን የትርፍ መጠን፤ እና

ሐ/ ዕቃዎቹን እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ለማድረስ የሚያስወጣውን የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪን፤በሚያካትት ስሌት ላይ ተመሥርቶ ይወሰናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት የግብይት ዋጋን ለመወሰን በአምራቹ ፈቃድ የሚገኘውን መረጃ ለማረጋገጥ ፣ የሚመለከተው የአምራቹ አገር መንግስታዊ አካል ጉዳዩን በቅድሚያ እንዲያውቀው በማድረግ የማይቃወመው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

95.**ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ዋጋ መወሰን**

1. በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 90 እስከ አንቀጽ 94 በተደነገገው መሰረት ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎችን የግብይት ዋጋ ለመወሰን ካልተቻለ በአገር ውስጥ ያለውን ወቅታዊ መረጃ በመጠቀምና ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች አጠቃላይ መርህ ጋር የተጣጣመ ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ይወሰናል፡፡
2. አስመጭው ሲጠይቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተተመነው ዋጋና የአተማመን ዘዴው በጽሁፍ ይገለጽለታል፡፡

96.**በግብይት ዋጋ ላይ የሚጨመሩ ክፍያዎች**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 90 መሰረት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ላይ የሚከተሉት መደመር አለባቸው፡-

ሀ/ በገዥው የሚሸፈኑ ወጪዎች ሆነው ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ ያልተካተቱ፡-

1) ከግዥ ኮሚሽን በስተቀር ማናቸውም ዓይነት የኮሚሽንና የድለላክፍያ፤
2) ከዕቃዎቹ ተነጥለው ሊታዩ የማይችሉ የዕቃ መያዣዎች ወጪ፤
3) ዕቃዎቹን ለማሸግ የወጣ የጉልበትም ሆነ የማቴሪያል ወጪ፤
4) ዕቃዎቹን እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪ፤
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)(4) የተደነገገው ቢኖርም ዕቃዎቹ በአየር የተጓጓዙ በሚሆንበት ጊዜ ለአየር ትራንስፖርት የተከፈለው አንድ ሦስተኛ ወጪ፤

ለ/ ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ አስቀድመው ያልተካተቱወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ለማምረት በአስመጪው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ

ያለ ክፍያ ወይም በአነስተኛ ክፍያ የቀረቡና አስፈላጊው የወጪ ማስተካከያ የተደረገባቸው ግብዓቶች፣ ክፍሎችና ሌሎች ዕቃዎች፣ የእጅ መሣሪያዎች፣ ቅርጽ ማውጫዎችና ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች፣ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ የዋሉ አላቂ ዕቃዎች፣ ከኢትዮጵያ ውጪ ለተከናወኑየኢንጂነሪንግ፣ የሥነ-ጥበብ፣ የዲዛይንና የፕላን ሥራዎች የተደረጉ ወጪዎች፤

ሐ/ ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ ያልተካተቱና በገዢው በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲከፈሉ በሽያጭ ውሉ የተደነገጉ የአዕምሯዊ ንብረት ሮያሊቲና ፈቃድ ክፍያዎች፤

መ/ ዕቃዎቹን መልሶ በመሸጥ ፣ ለሌላ በማስተላለፍ ወይም በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለሻጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚከፈሉ ክፍያዎች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት በግብይት ዋጋ ላይ የሚደመሩ ማናቸውም ተጨማሪክፍያዎች በተጨባጭና ሊለኩ በሚችሉ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው።

3. የግብይት ዋጋ ለመወሰን በዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ዋጋ ላይ የሚደመር ክፍያ በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡ ክፍያውም በሌተር አፍ ክሬዲት ወይም በህግ በተፈቀደ ሌላ የክፍያ ሥርዓት አማካይነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊፈጸም ይችላል፡፡

97.<u>በግብይት ዋጋ ዉስጥ የማይካተቱ ክፍያዎች</u>

1. ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ውስጥ ተለይተው እስከተቀመጡ ድረስ የሚከተሉት ክፍያዎች በግብይት ዋጋ ውስጥ አይካተቱም፡-

ሀ/ የፋብሪካ መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች ወይም መሳሪያዎች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለተከናወነ ወይም ለሚከናወን የግንባታ፣ የማሻሻያ፣ የተከላ ወይም የጥገና ሥራ ወይም ለቴክኒክ ድጋፍ የሚከፈል ክፍያ፤

ለ/ ዕቃዎች ወደ ጉምሩክ ክልል ከገቡ በኋላ የሚከፈል የትራንስፓርት ክፍያ፤

ሐ/ ወደ አገር ውስጥ ከገቡት ዕቃዎች ግዥ ጋር በተያያዘ ገዢው ለገባው የብድር ወይም የፋይናንስ ስምምነት የሚከፈል የወለድ ክፍያ፤

መ/ የግገዢ ኮሚሽን፤

ሠ/ ወደ አገር ውስጥ ከገቡት ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከፈሉ ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች፡፡

2. የግብይት ዋጋ ሲወሰን የሚከተሉት ክፍያዎች ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ላይ አይደመሩም፦
   ሀ/ ወደ አገር ውስጥ የገቡትን ዕቃዎች በአገር ውስጥ እንደገና ለማምረት መብት የሚከፈሉ ክፍያዎች፤
   ለ/ ዕቃዎቹን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ ካልሆነ በስተቀር ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ለማከፋፈል ወይም እንደገና ለመሸጥ በገዢው የሚሚከፈሉ ክፍያዎች፡፡

98.<u>ከግብይት ዋጋ ላይ ስለሚቀነሱ ሂሳቦች</u>

ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡ ዕቃዎች ከግብይት ዋጋ ላይ የሚከተሉት ሂሳቦች ተቀናሽ ይደረጋሉ፦

1. ዕቃዎቹ በጉዞ ላይ ሳሉ የደረሰ ጉዳት፤
2. ዕቃዎቹ በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ሳሉ የደረሰ ጉዳት፤
3. አደገኛ በመሆኑ ምክንያት እንዲቃጠል ወይም በሌላ አኳኋን እንዲወገድ የተደረገ ዕቃ ዋጋ፡፡

99.<u>ተጨማሪ መግለጫና መረጃ ስለማቅረብ</u>

1. ባለሥልጣኑ በቀረበው የዲክላራሲዮን ዝርዝሮች ወይም ደጋፊ ሰነዶች ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበት የሚያደርግ ማናቸውም ምክንያት ሲኖረው የተገለጸው የግብይት ዋጋ ለዕቃው የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ትክክለኛ ዋጋ መሆኑን የሚያሳይ ተጨማሪ መግለጫ ወይም ማስረጃ እንዲያቀርብ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን ሊጠይቀው ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ተጨማሪ መግለጫ ወይም ሰነድ ከዲክላራሲዮን አቅራቢው ከተቀበለ በኋላ ስለግብይት ዋጋው ትክክለኛነት ያለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ካልቻለ ወይም ዲክላራሲዮን አቅራቢው ምላሽ ካልሰጠ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 90 መሠረት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋን መወሰን እንዳልተቻለ ይቆጠራል። የቀረበው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት በጽሑፍ ለአስመጪዉ ወይም ለወኪሉ ይገለጽለታል፡፡

100. <u>የዋጋ አተማመን ዘዴዎች ተፈጻሚ የሚሆኑባቸው ሌሎች ሁኔታዎች</u>

በዚህ አዋጅ ክፍል አራት የተመለከቱት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን ዘዴዎች በሚከተሉትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፦

1. ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ከጉምሩክ ቁጥጥር ከተለቀቁ በኋላ በድጋሚ ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚፈፀምበት ሁኔታ ሲያጋጥም፤
2. የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው ከተለቀቁ በኋላ ኦዲት የሚካሄድባቸውን ዕቃዎች በሚመለከት፤
3. ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን እና በጊዜያዊነት ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን ዋጋ አተማመን በሚመለከት፡፡

101. <u>**የገንዘብ ምንዛሬ**</u>

ወደ አገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ከአገር የሚወጡ ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚሰላው ስለዕቃዎቹ የቀረበው የዕቃ ዲክላራሲዮን በተመዘገበበት ቀን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገለጸውን የገንዘብ ምንዛሪ ልክ በመጠቀም ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የታሪፍ አመዳደብ</u>

102. <u>**መርህ**</u>

1. ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት ይሆናል፡፡
2. ጭነቱ በተለያየ የታሪፍ አመዳደብ ላይ የሚመደቡ ዕቃዎችን የያዘ በመሆኑ ምክንያት ዕቃዎችን የመመደብ ወይም የዕቃ ዲክላራሲዮን የማዘጋጀት ሥራው አድካሚ ሆኖ ሲገኝና የጉምሩክ የታሪፍ ምጣኔ ልክ የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ በዲክላራሲዮን አቅራቢው ጥያቄ መሠረት ሚኒስቴሩ አጠቃላይ ጭነቱን ከፍተኛ ታሪፍ በሚመደብበት የታሪፍ መደብ ላይ በመመደብ የታሪፍ ምጣኔ ልኩ እንዲወሰን ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. የዓለም የጉምሩክ ድርጅት ስለሸቀጦች አመዳደብ የሚያወጣው ሰነድ ስለዕቃዎች የታሪፍ አመዳደብ ወሳኝ ማስረጃ ተደርጎ ይወሰዳል።

103. <u>**የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ አስገዳጅ መረጃዎች ስለመስጠት**</u>

1. ከአስመጪው ወይም ከወኪሉ በሚቀርብ ጥያቄ መስረት የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ ባለሥልጣኑ አስገዳጅ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀውን መረጃ የሚጠቀም ሰው ያቀረበው የዕቃ ዝርዝር መግለጫ አስገዳጅ መረጃውን ለማግኘት አስቀድሞ ከሰጠው መረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ መቻል አለበት፡፡

3. የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ የተሰጠ አስገዳጅ መረጃ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተቀባይነቱን ያጣል፡-

ሀ/ አስገዳጅ መረጃው በአመልካቹ በቀረበ የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ መረጃ ላይ የተመሰረተ ከሆነ፤

ለ/ በደንቦች ወይም መመሪያዎች መለወጥ ምክንያት አስገዳጅ መረጃው በሥራ ላይ ካሉት ደንቦች ወይም መመሪያዎች ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤

ሐ/ አስገዳጅ መረጃው የተሰጠው ተገቢው ሥልጣን በሌለው ሰው ከሆነ፤

መ/ አስገዳጅ መረጃው ከተሻረ ወይም ከተሰረዘና መሻሩ ወይም መሰረዙ ለመረጃው ባለቤት የተገለፀ ከሆነ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) የተገለፀው ሁኔታ ሲከሰት ደንቡ ወይም መመሪያው በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ መረጃው የማያገለግል ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የዕቃዎች የሥሪት አገር

### 104. የዕቃዎች ሥሪት አገር አወሳሰን

1. አንድን ምርት በማምረት ሂደት ሁለትና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው አገሮች ተሳታፊ በሚሆኑበት ሁኔታ የምርቱ የሥሪት አገር ነው የሚባለው የመጨረሻው መሠረታዊ የምርት ሥራ የተካሄደበት ወይም የኢኮኖሚያዊ እሴት መሠረታዊ ለዉጥ የተደረገበት አገር ይሆናል፤ ሆኖም የምርት ሂደቱ በዚሁ አገር ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ፋብሪካ ውስጥ የተከናወነና ሂደቱም በወሳኝ መልኩ በምርቱ ላይ ለውጥ ያስከተለ ወይም አዲስ ምርት ያስገኘ መሆን አለበት፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም ሲባል የዕቃውን የሥሪት አገር ለመወሰን የሚከተሉት መስፈርቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡-

ሀ/ የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ፤

ለ/ የተጨማሪ እሴት መቶኛ መመዘኛ፤ እና

ሐ/ የማምረቻ ወይም የዝግጅት ሥራ ሂደት መመዘኛ፡፡

3. በምርት ግብዓቶች ላይ የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎችና የምርት ሂደቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተደነገገው የተሟላ የሥራ ሂደት ሆነው ይቆጠራሉ።

4. ማናቸውም የሥራ ወይም የምርት ክንዉን የዚህን አዋጅ የስሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ዓላማ በማድረግ የተከናወነ መሆኑ ከተረጋገጠ ከሥሪት አገር ድንጋጌዎች አንፃር ትክክለኛ ክንውን ሆኖ አይቆጠርም።
5. ኮሚሽኑ አስገዳጅ ለኤክስፖርት እቃዎችየስሪት አገር መረጃ ሊሰጥይችላል፡፡[42]

## 105. የዕቃዎች የሥሪት አገርን ለመወሰን ግምት ዉስጥ የማይገቡ ሁኔታዎች

የሚከተሉት የአሰራር ሂደቶች የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ የሚያስከትሉ ሆነም አልሆነ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የሥሪት አገር ለመወሰን ከግምት ውስጥ አይገቡም፡

1. በምርት ማጓጓዝ ወይም ክምችት ወቅት ምርቱን ባለበት ሁኔታ ለማቆየት የሚከናወኑ ተግባራት፤
2. ዕቃዎችን የማጓጓዝ ሂደት ለማቀላጠፍ ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፤
3. ዕቃዎችን ለማሸግ ወይም ለሽያጭ ለማዘጋጀት ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፤
4. ዕቃዎችን በአየር የማናፈስ፤ የማስጣት፣ የማድረቅ፣ የማቀዝቀዝ፣ የተበላሹ ክፍሎችን የመቀየር፣ ማለስለሻ የመቀባት ወይም ዝገት የማስወገድ፣ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች በዕቃው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቀለም የመቀባት፣ የማጠብ፣ የማጽዳት፣ የማበጠር፣ የመፈተግ፣ የመለየት፣ የመመዘን፣ የመሞከር፣ የመለካት፣ የማሸግ፣ እሽጎችን የመፍታት፣ መልሶ የማሸግ፣ የመከፋፈል፣ ምልክት የማድረግ፣ በውሃ ወይም በሌላ ፈሣሽ ነገር አያያዝ ማድረግ፣ በጨው የመንከር፣ የመላጥ፣ የመከካት፣ የመውቃት እና የእንስሳት ዕርድ የመሳሰሉ ቀላል ሂደቶች ክንውን፤
5. የተሟላ የምርት ውጤት ለማስገኘት የሚከናወን ቀላል የመገጣጠም ሥራ፤
6. ከላይ የተዘረዘሩትን የሥራ ሂደቶች በማጣመር የሚከናወን ማንኛውም የሥራ ሂደት፡፡

## 106. የሥሪት አገርን ለመወሰን የሚረዱ ሰነዶችን ስለማቅረብ

1. ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ህጎችን ለማስፈፀም ሲባል የዕቃዎችን የሥሪት አገር የሚያረጋግጥ ሰነድ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በቀረበለት ስነድ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረዉ የዕቃውን የሥሪት አገር በተመለከተ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 107. የዕቃዎች የሥሪት አገር መግለጫ

[42]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (24) የተጨመረ ነው፡፡

1. ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች እና የእነዚህ ዕቃዎች ማሸጊያ የተሠሩበትን አገርየሚያስረዳ መግለጫ በቀላሉ ሊፋቅ፣ ሊነሳና ሊለወጥ በማይችል አኳኋን በእንግሊዝኛቋንቋ የተጻፈባቸው ሊሆን ይገባል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘረውን የማያሟላ ዕቃ ወደመጣበት አገር እንዲመለስ ይደረጋል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የሥሪት አገር መግለጫ የሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

108. <u>የታሪፍ ቅናሽ ከሚሰጣቸው አገሮች የሚመጡ ዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች</u>

በዓለም አቀፍ፣ በአካባቢያዊ ወይም በሁለትዮሽ የንግድ ስምምነት መሰረት የታሪፍ ቅናሽ ወይም የቀረጥ ነፃ መብት የሚሰጣቸው አገሮች የስሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች በስምምነቶቹ መሰረት የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

<u>**ምዕራፍ አራት**</u>

<u>**ስለቀረጥ፣ ታክስ እና የአገልግሎት ክፍያዎች**</u>

109. <u>ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ</u>

በህግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ ወይም በሚኒስቴሩ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር በማናቸውም የገቢ ወይም የወጪ ዕቃ ላይ ቀረጥና ታክስ ይከፈላል፡፡

110. <u>ቀረጥና ታክስ የመክፈል ሃላፊነት</u>

1. ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዕቃው ላይ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሳይከፈል በቀረ ቀረጥና ታክስ ላይ የሚወሰነውን ቅጣትና ወለድ የመክፈል ሃላፊነት አለበት፡፡
2. የጉምሩክ አስተላላፊ ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል የሚያደርግ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ላልተከፈለው ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሳይከፈል በቀረው ቀረጥና ታክስ ላይ ለተወሰነው ቅጣትና ወለድ ከዲክላራሳዮን አቅራቢው ጋር በአንድነትና በነጠላ ሃላፊ ይሆናል፡፡

111. <u>የቀረጥና ታክስ ክፍያ ስለሚወሰንበትና ስለሚከፈልበት ግዜ</u>

1. በዚህ አዋጅ ወይም በማናቸውም ሌላ ህግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በገቢ ወይም በወጪ ዕቃ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ የዕቃው ዲክላራሲዮን ተቀባይነት ባገኘበት ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 93 የተመለከተው እርማት በተደረገበት ቀን ተፈጻሚነት ያለውን ህግ መሠረት በማድረግ ይወሰናል፡፡
2. የዕቃ ዲክላራሲዮን የቀረበበትን ወይም ተቀባይነት ያገኘበትን ቀን መወሰን ባልተቻለ ጊዜ በዕቃው ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ ባለሥልጣኑ በሚወስነው ቀን ተፈጻሚነት ያለውን ህግ መሠረት በማድረግ ይወሰናል፡፡
3. በዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ የተጠቀሰው ቀረጥና ታክስ በስሌት ከተገኘው ቀረጥና ታክስ የተለየ ካልሆነ በስተቀር የጉምሩክ ሹም ተከፋይ የሚሆነውን ቀረጥና ታክስ ለዲክላራሲዮን አቅራቢው ሲያስታውቀው ወዲያውኑ መክፈል አለበት፡፡

112. <u>በቅድሚያ የተሰጠ መረጃን መሰረት በማድረግ ቀረጥና ታክስ ስለመወሰን</u>

1. ዲክላራሲዮን አቅራቢው ሲያመለከት ዕቃው ወደ ጉምሩክ ወደብ ከመግባቱ በፊት ለባለሥልጣኑ የሚቀርበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በዕቃው ላይ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስ መወሰን ይቻላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዕቃው ወደ ጉምሩክ ወደብ ከመግባቱ በፊት ለባለሥልጣኑ የቀረበውን መረጃ መሠረት በማድረግ የተወሰነው ቀረጥና ታክስ ዕቃው ወደ ጉምሩክ ወደብ ከገባ በኋላ ከተወሰነው ቀረጥና ታክስ ብልጫ ያለው ቢሆንም ተፈፃሚነቱን አያስቀረውም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰነ ቀረጥና ታክስ ዕቃዉ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ጉምሩክ ወደብ ካልገባ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

113. <u>ስህተት እንዲታረም ስለማድረግ</u>

ባለሥልጣኑ በቀረጥና ታክስ አወሳሰን ላይ ስህተት መኖሩን ሲያረጋግጥ ለስህተቱ መፈጸም ሃላፊ የሆነው ሰው በህግ መሠረት የሚኖርበት ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ስህተቱ እንዲታረም ለማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

114. <u>ክፍያ ስለሚፈጸምበት መንገድ</u>

በዕቃዎች ላይ የተወሰነው ቀረጥና ታክስ በጥሬ ገንዘብ ወይም በህግ በሚታወቅ ማንኛውም የክፍያ መንገድ ይፈጸማል፡፡

115. <u>የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

ባለሥልጣኑ ከጉምሩክ ፎርማሊቲ ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለው የአገልግሎት ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**ምዕራፍ አምስት**

**የቀረጥና ታክስ ክፍያን ለመሸፈን ስለሚሰጥ ዋስትና**

116. **ዋስትና ስለማቅረብ**

ባለሥልጣኑ የቀረጥና ታክስ ክፍያ መከፈሉን ወይም ከቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ጋር የተያያዙ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ዋስትና እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

117. **ዋስትና የሚጠየቅባቸው ሁኔታዎች**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 116 አጠቃላይ አነጋገር እና ዋስትናን የሚመለከቱ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለሥልጣኑ ዋስትና እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፦

1. የጉምሩክን ፎርማሊቲ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ለማሟላት ተጨማሪ ጊዜ ሲያስፈልግ የጉምሩክ ፎርማሊቲው ሳይከናወን ዕቃዎቹን ለመልቀቅ፤
2. ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ተመልሰው መውጣታቸውን ወይም ካልወጡ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን ለማረጋገጥ፤
3. ተላላፊ ዕቃዎች በተወሰነው መስመር ተጓጉዘው በተፈቀደ መውጫ በር ከአገር መዉጣታቸውን ወይም መራገፊያቸው ወደሆነው የጉምሩክ ጣቢያ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ፤
4. በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትየሚሸፈኑ ዕቃዎችን ሳይጨምር የምርትወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው ወደውጭ ለመላክ ቀረጥና ታክስሳይከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡዕቃዎች የተገኙ ማካካሻ ምርቶች ወደውጭ መላካቸውን ወይም ካልተላኩቀረጥና ታክሱ መከፈሉን ለማረጋገጥ፤[43]
5. በታሪፍ አመዳደብ እና በዋጋ አተማመን ረገድ በአስመጪውና በባለሥልጣኑ መካከል የተፈጠረው ያለመግባባት የመጨረሻ ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው እንዲለቀቁ ለማድረግ፤
6. የቀረጥና የታክሱ ክፍያ ከሚፈፀምበት ጊዜ እንዲዘገይ የተፈቀደ ሲሆን ክፍያው እስከሚፈፀም ድረስ።

[43] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (25) ተሻሻለ

118. <u>የዋስትና ዓይነት</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠየቅ ዋስትና የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ፣ የባንክ የዋስትና ሰነድ፣ የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ መሥሪያ ቤቶችን የሚመለከት ሲሆን በጽሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት ሊሆን ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ለአንድ የቀረጥና ታክስ እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያዎች አንድ ዋስትና ብቻ ይጠይቃል፤ ሆኖም በባለዕዳው ጥያቄ መሠረት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ አፕሬሽኖች ምክንያት የሚከሰት ክፍያን የሚሸፍን ዋስትና እንዲሰጥ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ዋስትናውን እዳው ከሚመለከተው ሰው ውጪ በሆነ በሌላ ሰው እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. ዋስትና እንዲያቀርብ የሚጠየቅ ሰው በዚህ አዋጅ ከተደነገጉት የዋስትና ዓይነቶች አንዱን መምረጥ ይችላል፤ ሆኖም ባለሥልጣኑ የተመረጠው ዋስትና ከሚፈጸመው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ጋር የማይጣጣም ከሆነ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

119. <u>ዋስትናን የተመለከቱ መብትና ግዴታዎች</u>

1. ባለሥልጣኑ የተቀበለው የዋስትና ዓይነት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲያገለግል ሊወስን ይችላል፡፡
2. ዋስትና የተገባለት ግዴታ ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸመ ዋስትናው ቀሪ ይሆናል፡፡ ባለሥልጣኑ ዋስትና የተገባለት ግዴታ የተፈፀመ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
3. ባለዕዳው ግዴታውን ሳይወጣ በቀረ ጊዜ ዋስትና ሰጪው ክፍያውን ወዲያውኑ መፈጸም አለበት፡፡
4. ዋስትና ሰጪው እና ባለዕዳው በአንድነትና በነጣላ እዳውን ከነወለዱና ወጪው የመክፈል ግዴታ አለባቸው።
5. ዋስትና ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (3) መሠረት ክፍያውን ሳይፈጽምየቀረ እንደሆነ ኮሚሽኑ በታክስ አስተዳደርአዋጁ በተመለከተው ሥነ-ሥርዓትመሠረት የባለዕዳውን ወይም የዋስትናሰጪውን ንብረት ወይም የባንክ ሂሳብበመያዝ ክፍያው እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡[44]

[44] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (26) ተሻሻለ

120. <u>**የዋስትና መጠን**</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ ዋስትና መጠን ዋስትናዉ በሚቀርብበት ጊዜ የሚፈለገዉን ቀረጥ ፣ ታክስና የአገልግሎት ክፍያ መጠን በእርግጠኝነት የሚታወቅ ከሆነ ከዚሁ ማነስ የለበትም፡፡
2. የሚፈለገዉን የቀረጥ፣ የታክስና የአገልግሎት ክፍያ መጠን በእርግጠኝነት ማወቅ ባልተቻለ ጊዜ ዋስትናው ባለሥልጣኑ በገመተው ከፍተኛ የቀረጥ፣ የታክስና የአገልግሎት ክፍያ መጠን ይሆናል፡፡
3. የቀረበው ዋስትና በማናቸውም ምክንያት የእዳ ክፍያውን የማይሸፍን ሆኖ ከተገኘ ባለዕዳው ተጨማሪ ዋስትና ማቅረብ ወይም የመጀመሪያውን ዋስትና በሌላ መተካት አለበት፡፡

<u>**ምዕራፍ ስድስት**</u>

<u>**ስለ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ በልዩነት ስለሚፈለግ ቀረጥና ታክስ እና ስለቀረጥና ታክስ ተመላሽ**</u>

121. <u>**የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት**</u>

1. ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቀው የተለቀቁ ዕቃዎችን ዲክላራሲዮን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ዕቃውን ለማስመጣት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በተሳተፈ ሰው እጅ የሚገኙ መዛግብትን፣ ሪኮርዶችን፣ የንግድ አሰራሮችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉምሩክ ነክ የንግድ መረጃዎችን በመመርመር የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የሚያደርገው የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት በባለሥልጣኑ ጽሕፈት ቤት ወይም ዕቃዎቹን በማስመጣትና በመላክ የንግድ ሥራ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በተሳተፈው ሰው ቅጥር ግቢ ወይም ለምርመራ የተፈለጉት መረጃዎችና ሰነዶችን በያዘ ሌላ ማናቸውም ሰው ቅጥር ግቢ ሊከናወን ይችላል፡፡
3. በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲቱ ግኝት የጉምሩክ ፎርማሊቲ የሚመራባቸው ድንጋጌዎች መጣሳቸው ከተረጋገጠ የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ወይም የሁለቱንም ኃላፊነት የሚያስከትል ዉጤት ይኖረዋል።
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሊካሄድ የሚችለው የዕቃ ዴክላራሲዮን ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

5. አዲተሩ በዚህ አዋጅ ለጉምሩክ ሹም የተሰጠው ሥልጣን ይኖሩታል።

## 122. በልዩነት ስለሚፈለግ ቀረጥና ታክስ[45]

1. ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክንያት ያልተከፈለ ወይም ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት እንደሆነ ባለሥልጣኑ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን ያልተከፈለውን ወይም በልዩነት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያስከፍል ይችላል፡፡
2. ለቀረጥና ታክሱ ያለመከፈል ወይም በማነስ መከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሆነ እንደሆነ ሳይከፈል በቀረው ቀረጥና ታክስ ላይ 10 በመቶ ቅጣትና የባንክ ወለድ ተጨምሮ ይከፈላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚከፈለው ወለድ መጠን ቀረጥና ታክሱ እንዲከፈል በተጠየቀበት ወቅት በሥራ ላይ ባለው ከፍተኛው የንግድ ባንክ የማበደሪያ ወለድ ተመን መሠረት የሚሰላ ይሆናል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ ኦዲት የሚያደርግ መሆኑ በጽሑፍ ካሳወቀ በኋላ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ መኖሩን ከገለጸና ለመክፈል ፍቃደኛ ከሆነ ከቀረጥና ታክሱ እና ወለዱ ክፍያ በስተቀር ቅጣት እንዳይጣልበት ባለሥልጣኑ ሊወስን ይችላል፡፡
5. ያልተከፈለውን ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው በቂ ምክንያት ሲያቀርብ ዕዳው ከነወለዱ በተወሰነ ጊዜ ተከፍሎ እንዲያልቅ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ያችላል፡፡
6. በዚህ አንቀፅ መሰረት የተጠየቀዉን ቀረጥና ታክስ ከነመቀጫና ወለዱ ያልከፈለ ባለዕዳ በሥራ ላይ ባለው የታክስ አስተዳደር አዋጅ የተመለከተው ንብረትን ይዞ የማስፈፀም ስርዓት ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ(1) የተደነገገው ቢኖርም ከቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችንበሚመለከት ወይም ኮሚሽኑ የጉምሩክማጭበርበር የተፈጸመ መሆኑን ያመነእንደሆነ በአምስት ዓመት ጊዜ ሳይገደብኦዲት ማድረግ ይችላል፡፡

## 123. በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ

[45]የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (26) ተሻሽሏል፤ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በማሻሻያ አዋጁ አንቀጽ 2(28) መሰረት ተጨምሯል፡፡

1. በዕቃዎች አሰያየም፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሳብ አሰራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ለከፋዩ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሊታይ የሚችለው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተከናውኖበት ዲክላራሲዮን ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከቀረበ ብቻ ነው፡፡[46]

## 124. <u>የዕቃ ዲክላራሲዮን ውድቅ በመደረጉ ምክንያት ተመላሽ ስለሚሆን የቀረጥና ታክስ ክፍያ</u>

1. የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ የሚደረገው፡-
   ሀ/ የዕቃ ዲክሳራሲዮን በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰረዘና በዚሁ ዲክሳራሲዮን መሠረት የተከፈለ ቀረጥና ታክስ የነበረ ሲሆን፤እና
   ለ/ የዕቃ ዲክላራሲዮንን ለማሠረዝ ማመልከቻ ሊቀርብ በሚችልበት የጊዜ ገደብ ውስጥ በሚመለከተው ሰው ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም በዕቃው ላይ የቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ሌላ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሊፈፀምበት የሚገባ ሆኖ ከተገኘ ቀረጥና ታክሱ ተመላሽ ሳይደረግ አግባብነት ያለው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀምበት ይደረጋል፡፡
3. ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወደ አገር ውስጥየገባ ዕቃ ያልተከለከለ ወይም አገባቡየጉምሩክ ህግን የማይጻረር መሆኑሲረጋገጥና አስመጪው ዕቃውን እንደማይወስደው በጽሑፍ ሲያረጋገጥአስቀድሞ ለዕቃው የከፈለው ቀረጥና ታክስተመላሽ እንዲደረግለት የጠየቀ እንደሆነዲክላራሲዮኑ ተሰርዞ ለዕቃው የተከፈለውቀረጥና ታክስ ተመላሽ ተደርጎ ዕቃውእንዲወገድ ይደረጋል፡፡[47]

## 125. <u>የጥራት ደረጃቸው በቀነሰ፣ በተበላሹ፣ በተጎዱ፣ ጉድለት በታየባቸው ዕቃዎች ምክንያት ተመላሽ ስለሚሆን ቀረጥና ታክስ</u>

---

[46] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (29) ተሻሻለ
[47] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (30) የተጨመረ ነው፡፡

1. ዕቃ በጉዞ ላይ ወይም በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እያለ የጥራት ደረጃው ከቀነሰ፣ ከተበላሸ፣ ከተጎዳ፣ ከወደመ ወይም ከጎደለ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ በዚሁ መጠን ተመላሽ ይደረጋል፡፡
2. ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ አስመጪው ከሻጩ ጋር ባደረገው ውል ላይ በተገለጸው መጠን ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ የቀረ ከሆነ በጐደለው ዕቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የቀረጥና ታክስ ክፍያ ተመላሽ ጥያቄ ቀረጥና ታክሱ በተከፈለ በ12 ወራት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል።
4. 4.ገደብ የተደረገበት ዕቃ በሚመለከተውፈቃድ ሰጪ አካል ወደ አገር እንዲገባባልተፈቀደ ጊዜ አስቀድሞ የተከፈለቀረጥና ታክስ ተመላሽ ይደረጋል፡፡[48]

126. <u>የቀረጥና ታክስ እዳን ቀሪ ስለማድረግ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 125(1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃ በጉዞ ላይ ወይም በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እያለ ከተበላሸ ወይም ከወደመ የሚፈለግበት ቀረጥና ታክስ ቀሪ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቀረጥና ታክሱ ቀሪ የተደረገው ዕቃው በአስመጪው ጥፋት በመበላሸቱ ምክንያት ከሆነ ዕቃው በአስመጪው ኪሳራ በባለሥልጣኑ እንዲወገድ ወይም እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

127. <u>በስህተት ተመላሽ ወይም ቀሪ የተደረገን ቀረጥና ታክስ ስለማስከፈል</u>

በስህተት ተመላሽ ወይም ቀሪ የተደረገ ቀረጥና ታክስ ለባለሥልጣኑ ተመልሶ ይከፈላል፡፡

128. <u>ስለማቻቻል</u>

ባለሥልጣኑ የተመላሽ ጥያቄ ያቀረበው ሰው ያለበትን የቀረጥና ታክስ እዳ ከባለሥልጣኑ በሚጠይቀው ተመላሽ ክፍያ እንዲቻቻል ሊወስን ይችላል፡፡

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

<u>የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት</u>

129. <u>የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አሰጣጥ</u>[49]

[48] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (31) የተጨመረ ነው፡፡

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ. (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የቀረጥ ነፃ መብት የሚሰጠው የገንዘብ ሚኒስቴር ብቻ ይሆናል፡፡
2. ከዲፕሎማሲ ግንኙነት ጋር በተያያዘኢትዮጵያ በፈረመችባቸው እና ተቀብላባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችመሰረት የሚሰጡ የቀረጥና ታክስ ነፃመብቶች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርእየተረጋገጠ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት እንዲፈቅዱበህግ ለሌሎች የመንግስት አካላትየተሰጠው ስልጣን ለገንዘብ ሚኒስቴርተላልፏል፡፡
4. ማንኛውም የመንግስት አካል በሚዋዋለውየፕሮጀክት ስምምነት መሠረት የሚፈቀድየቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ተፈፃሚየሚሆነው በገንዘብ ሚኒስቴር ሲፀድቅብቻ ይሆናል፡፡
5. ኮሚሽኑ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ከአገርየሚወጡ ዕቃዎች ለታለመላቸውዓላማ ስለመዋላቸው መረጃ ይይዛል፣ይከታተላል፣ እርምጃ ይወስዳል፡፡
6. የቀረጥና ታክስ ነፃ መብትስለሚፈቀድበት ሁኔታና ስለአፈጻጸሙ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣውደንብ ይወሰናል፡፡

130. <u>ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር ዉስጥ ስለገባ ዕቃ</u>

1. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባን ዕቃ ቀረጥና ታክሱ ሳይከፈልበት ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ማንኛውም ሰው ማስተላለፍ ወይም የቀረጥ መብት ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ መገልገል ወይም በሌሎች ሰዎች ይዞታና አገልግሎት እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
2. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባ ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ተመልሶ ከአገር ሊወጣ ወይም ተመሳሳይ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ላለው ሰው ሊተላለፍ ወይም ቀረጥና ታክሱ ተከፍሎበት ለሌላ ሰው ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ቀረጥና ታክሱም የሚሰላው ዕቃው በተላለፊበት ጊዜ በሚያወጣው ዋጋና ፀንቶ ባለው የታሪፍ ልክ መሠረት ይሆናል፡፡

---

[49]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (32) ተሻሻለ

3. ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጠፋ ወይም ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ አስመጪው ለባለሥልጣኑ ይህንኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ለኢንቨስትመንት ሥራ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት የተሰጠው ሰው ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው የገቡ ዕቃዎችን ለሌላ ሰው ሲያስተላልፍ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሲመልስ በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የክሊራንስ ሰነድ የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል።
5. የሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ ወይም መዝጋቢ አካልም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገዉ ሁኔታ መሟላቱን የማረጋገጥ እና ክትትል የሚያስፈልጋቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን እንዳወቀ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
6. ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር የገባን ዕቃ በዋስትና ማስያዝ የሚቻለው ከባለሥልጣኑ ጋር በቀረጥና ታክሱ አከፋፈል ረገድ ስምምነት ላይ ሲደረስ ይሆናል፡፡
7. የባለቤትነት ስም ዝውውር የሚመዘገብ ማናቸውም አካል ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበትን ዕቃ ሲመዘግብ ይህንኑ በባለቤትነት የምስክር ወረቀት ላይ መግለጽ ያለበት ሲሆን ዕቃው ለሦስተኛ ወገን በሚተላለፍበት ጊዜ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ከጉምሩክ ሥራ ጋር የተያያዙ ግዴታዎች

### 131. የአጓጓዥ ግዴታዎች

1. የዚህ አዋጅ ክፍል ሦስት ምዕራፍ ስድስት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም አጓጓዥ፡-

   ሀ/ ወደ አገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ማጓጓዣን በባለሥልጣኑ ከተፈቀደው የጉዞ መስመር ውጭ ማንቀሳቀስ፣ ማቆም፣ መንገደኛ ማሳፈር፣ ዕቃ ማውረድ ወይም ማራገፍ የለበትም፤

   ለ/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጠውና ጉምሩክ ሹም በስፍራው ሳይገኝ መንገደኛ ማሳፈር ወይም ማውረድ ወይም ዕቃ መጫን ውይም ማራገፍ አይችልም፤

   ሐ/ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንኛውም ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲገባ መፍቀድ የለበትም፤

መ/ በባህሪያቸው ምክንያት ተቀጣጣይ ወይም አደገኛ የሆኑ ዕቃዎች ከማጓጓዣው ከመራገፋቸው በፊት ማስታወቅ አለበት፤

ሠ/ ማጓጓዣው ጉምሩክ ወደብ ከመድረሱ በፊት ስለጫነው ዕቃ፣ ስለ መንገደኞች እና በማጓጓዣው ውስጥ ስለሚቀረው ዕቃ ዝርዝር መግለጫ ለጉምሩክ ሹም ማቅረብ አለበት፤

ረ/ ማጓጓዣው በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል ውስጥ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የተፈጸመበትን ዕቃ ጭኖ እንዲንቀሳቀስ ከተፈቀደለት በኋላ በማናቸውም ምክንያት የሚያዘገይ ከሆነ ይህንኑ ለጉምሩክ ሹም ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም አጓጓዥ ማጓጓዣውን ከጉምሩክ ወደብ ውጪ ሊያሳርፍ ወይም ሊያቆም ይችላል፡፡ይህ በሚሆንበት ጊዜ አጓጓዡ ሁኔታውን በአቅራቢያው ላለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ወይም በአካባቢው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ከሌለ ለአካባቢው አስተዳደር ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

132. <u>የጉምሩክ መጋዘን ባለፍቃድ ግዴታዎች</u>

የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችን፣ መሣሪያዎችን፣ ቴክኖሎጂዎችንና ሠራተኞችን የማሟላት፤
2. ወደ መጋዘኑ የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችን ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መመዝገብና በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፤
3. በመጋዘኑ የሚቀመጡትን ዕቃዎች እንደዓይነታቸውና እንደባህሪያቸው በመለየት ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች ሁኔታ የማስቀመጥ፤
4. የጉምሩክ ሹም ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠትና ለቁጥጥርና ለምርመራ ሥራው የመተባበር፤
5. በባለሥልጣኑ ያልተፈቀደ ዕቃ ወደ መጋዘን እንዳይገባ ወይም ከመጋዘን እንዳይወጣ የመቆጣጠር፤
6. የተሰጠውን የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ በወቅቱ የማሳደስ፤
7. ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ወደ መጋዘን እንዳይገቡ የመቆጣጠር፤

8. የጤና ምርመራ ሊደረግበት የሚገባ ዕቃ ከማጓጓዣው እንደተራገፈ አስፈላጊው የጤና ምርመራ እስከሚፈጸም ድረስ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይቶ በኳራንቲን ክልል የማቆየት፤
9. በአያያዝ ጉድለት የጠፉ ወይም የተበላሹ ዕቃዎችን በሚመለከት የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ የመክፈል፤
10. ወደ መጋዘኑ መግባት ያለባቸው ዕቃዎች ያልገቡ እንደሆነ ያለመግባታቸውን ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፤
11. መጋዘኑ ጊዜያዊ የጉምሩክ ማከማቻ ሲሆን፦
    ሀ/ የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተከናወነበት ዕቃ ወዲያውኑ እንዲወጣ የማድረግ፤
    ለ/ በዚህ አዋጅ የተፈቀደው የጊዜ ገደብ ያለፈባቸውን በመጋዘኑ የተከማቹ ዕቃዎችን ለባለሥልጣኑ ማሳወቅና ዕቃዎቹን ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የማስተላለፍ፤
12. መጋዘኑ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ከሆነ ዕቃዎቹ ለተፈቀደላቸው ዓላማ ሳይውሉ ሲቀሩ ቀረጥና ታክሱን ለመክፈል የሚያስችል ዋስትና የማቅረብ፡፡

133. <u>መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>

1. የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ወይም በአነስተኛ ምጣኔ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ወይም የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃ መኖሩን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ወይም የህግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሰው ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል የሚሰጠው መረጃና ማንነቱ በሚስጥር ይጠበቃል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተገለጸው መሠረት ለባለሥልጣኑ ወይም ለህግ አስከባሪው በአካል በተሰጠ መረጃ መሠረት የተገኙትን ዕቃዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ለማድረግ ከተቻለ መረጃና ድጋፍ ለሰጡ ሰዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ወሮታ ይከፈላል፡፡

134. <u>መረጃዎችን ይዞ ስለማቆየት</u>

1. ለጉምሩክ ፎርማሊቲ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ወይም መረጃዎችን የያዘና ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው መረጃዎቹን ለአምስት ዓመት ይዞ ማቆየት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት ሰነዶችና መረጃዎች የሚቆዩበት ጊዜ የሚታሰበው፡-

   ሀ/ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው ከተለቀቁበት ቀን፤

   ለ/የወጪ ዕቃዎች ዲክላራሲዮኑ ተቀባይነት ካገኘበት ቀን፤

   ሐ/ ከቀረጥ ነፃ ሆነው በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከተከናወነበት ቀን፤

   ጀምሮ ይሆናል፡፡

135. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ በሥራ ላይ ያሠማራቸው ሠራተኞች ሃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዲችሉ ትብብር ማድረግ አለበት፡፡
2. የፌደራልና የክልል የመንግሥት አካላት ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር በሚከናወን ስራ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ሃላፊነት አለባቸው።
3. ኮንትሮባንድንና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የሚደረግ ጥረት ባለሥልጣኑ ከአቅሙ በላይ ሲሆን ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት የፀጥታ አስከባሪ አካላት ጋር በመሆን በጣምራ ሥራውን ሊያከናውን ይችላል፡፡
4. የጉምሩክ ሹም ተግባሩን ለማከናወን ዕርዳታ ሲጠይቅ ማናቸውም ህግ አስከባሪ አካል ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱት አካላት ተገቢና ተመጣጣኝ ሃይል ተጠቅመው ህገወጥ ሥራን ማስቆም ይችላሉ፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለጉምሩክ ቁጥጥርና ህግን ስለማስከበር</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>የጉምሩክ ቁጥጥር</u>

136. <u>የጉምሩክ ቁጥጥር ዓላማ</u>

የጉምሩክ ቁጥጥር ዓላማ፡-

1. ቀረጥና ታክስ በአግባቡ መሰብሰቡን የማረጋገጥ፤ እና

2. የጉምሩክ ህጎችን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ጥፋቶችን የመከላከል፣ የመመርመርና በጥፋተኞች ላይ አግባብ ያለው እርምጃ የመውሰድ ወይም የማስወሰድ፤ ይሆናል፡፡

137. **<u>የጉምሩክ ቁጥጥር አፈፃፀም</u>**

ማንኛውም የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ቁጥጥር እርምጃዎች ሲወስድ የጉምሩክ ህጎችን ለማስከበር በሚያስፈልጉ እርምጃዎች ዓይነትና መጠን መወሰን አለበት፡፡

138. **<u>በገቢ፣ በወጪና ተላላፊ ዕቃዎች ላይ ስለሚደረግ የጉምሩክ ቁጥጥር</u>**

1. የሚከተሉት ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ፡-

ሀ/ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ጉምሩክ ወደብ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው እስከሚለቀቁ፤

ለ/ ወደ ቦንድድ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ለተፈቀደላቸው ዓላማ እስከሚለቀቁ፤

ሐ/ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች ወደጉምሩክ ወደብ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው እስከሚላኩ፤

መ/ ተላላፊ ዕቃዎች እንዲንቀሳቀሱ ከተፈቀደበት ጊዜ ጀምሮ ወደተፈቀደው መድረሻ ቦታ እስከሚደርሱ ድረስ፤

ሠ/ ባለቤት የሌላቸው፣ የተተው፣ የተወረሱ ወይም በኮንትሮባንድ የተያዙ ዕቃዎች እስከሚወገዱ ድረስ።

2. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተገለፀው መሠረት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች ወደተከማቹበት ሥፍራ መግባት፣ ዕቃዎችን መክፈት ወይም ማናቸውንም ተግባር በዕቃዎቹ ላይ መፈፀም አይችልም።

139. **<u>የጉምሩክ የጠረፍ ቁጥጥር</u>**

1. የጉምሩክ ጠረፍ መስመርና የጉምሩክ ማቋረጫ በህግ ወይም በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ድንበር ለማቋረጥ ወይም ዕቃን ለማጓጓዝ መብት ለተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ያገለግላል፡፡
2. በጉምሩክ የጠረፍ መስመር ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በጉምሩክ ማቋረጫዎች በኩል ለኑሯቸው አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችንና በዓለም አቀፍ ስምምነት ድንጋጌዎች መሠረት የተፈቀዱ ሌሎች ዕቃዎችን የማጓጓዝ መብት ይኖራቸዋል።

3. በጉምሩክ የጠረፍ መስመር አካባቢ የሚኖሩ ሐኪሞች፣ የእንስሳት ሐኪሞች፣ ሌሎች የሕክምና ሠራተኞች እና የሕዝብን ሕይወትና ንብረት በማዳን ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ለሥራቸው የሚያስፈልጓቸውን መድሃኒቶችና መሣሪያዎች አግባብ ያለው የመንግሥት አካል በሚሰጣቸው ፈቃድ መሠረት በጉምሩክ ማቋረጫዎች በኩል ማጓጓዝ ይችላሉ፡፡

140. <u>የጉምሩክ ወደቦችና የመተላለፊያ መስመሮች</u>

1. ገቢ፣ ወጪና ተላላፊ ዕቃዎች በተወሰነ የጉምሩክ ወደብ ወይም ማቋረጫ በኩል መግባት ወይም መውጣት እና በተፈቀዱ የመተላለፊያ መንገዶች ብቻ መጓጓዝ አለባቸው።
2. የጉምሩክ ወደቦች፣ ማቋረጫዎችና የመተላለፊያ መንገዶች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የህዝብ ማስታወቂያ ይወስናሉ።

141. <u>በጉምሩክ የቁጥጥር ሂደት የሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ፎርማሊቲ መከናወኑን ለማረጋገጥ በሥራ ላይ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት አግባብነት ያላቸውን ማናቸውንም ዓይነት እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ባለስልጣኑ ዕቃዎች ከጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ጀምሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ እስከሚከናወን ድረስ በአይነት፣ በቅርፅ፣ በይዘትና በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ያልተለወጡ ሆነው መቆየታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. በጉምሩክ የቁጥጥር ሥርዓት መሠረት የሚወስዱት እርምጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

   ሀ/ ዕቃዎችን በጉምሩክ ወደብ፣ በጉምሩክ ጣቢያ፣ በጉምሩክ መጋዘን፣ በመተላለፊያ መንገድ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው ማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ የመመርመር፣ የመከታተልና ጥበቃ የማድረግ፤

   ለ/ በመረጃና በስጋት ሥራ አመራር ላይ ተመስርቶ ምርመራ የተከናወነበትን ወጪ ወይም ገቢ ዕቃ በድጋሚ እንዲመረመር የማድረግ፤

   ሐ/ ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ ከአገር ወጥቷል ብሎ ማረጋገጫ የመስጠት፤

   መ/ የጉምሩክ ማህተሞችን ማድረግ፣ የጉምሩክ ሰነዶችን የመስጠትና የማረጋገጥ፤

ሠ/ የዕቃዎች ዓይነትና ሁኔታ አለመለወጡን ለማረጋገጥ ናሙናዎችን፣ መግለጫዎችን፣ ፎቶዎችንና ሌሎች መረጃዎችን የመውሰድ፤

ረ/ የመንገደኞችን ሻንጣዎችና ሌሎች ዕቃዎች የመመርመር፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሐ) መሠረት ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ ከአገር ወጥቷል ተብሎ በባለሥልጣኑ ማረጋገጫ የሚሰጠው ከኢትዮጵያ መውጫ በሆነው የመጨረሻ ጣቢያ ከሚገኘዉ የጉምሩክ ሹም ዕቃው ከአገር መውጣቱን የሚገልጽ ማረጋገጫ ወደ ባለሥልጣኑ አውቶሜሽን ሲስተም ሲገባ ወይም በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በጽሁፍ ሲደርስ ብቻ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ህግ ስለማስከበር

### 142. የመፈተሽ ሥልጣን

1. የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ጥፋት የተፈጸመባቸው ዕቃዎች ለመኖራቸው በቂ መረጃ ወይም ጥርጣሬሲኖረው ዕቃዎቹን የጫነውን ማጓጓዣ በማስቆምወይም ዕቃዎቹ ወደ ተከማቹበት ማናቸውም ሥፍራ በመግባት የመፈተሽና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 143(1)(ሀ) መሠረት ዕቃዎቹንና ማጓጓዣውን የመያዝ ሥልጣን ይኖረዋል።
2. የጉምሩክ ሹም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የፍተሻ ሥራ ሲያከናውን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታሸገ ካልሆነ በስተቀር የዕቃዎችን እሽግ የማንሳትና በቁልፍ የተዘጉ ዕቃዎችን የመክፈት ሥልጣን ይኖረዋል።
3. የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ጥፋት የተፈጸመበትን ዕቃ ደብቋል ብሎ ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው ማንኛውንም ሰው ማስቆምና መፈተሽ ይችላል፡፡
4. አካላዊ ፍተሻ ተመሳሳይ ጾታ ባለው ሰው ይከናወናል፡፡
5. የአካላዊ ፍተሻው አፈፃፀም በትህትና እና የሚፈተሸውን ሰው ስብዕና በማይነካ፣ ጤናውን ወይም ንብረቱን በማይጎዳ መልኩ እና ተደብቋል ተብሎ የተጠረጠረውን ህገወጥ ዕቃ ለማግኘት በሚስችል ደረጃ መፈፀም አለበት፡፡
6. የጉምሩክ ሹሙ ውስጣዊ የአካል ፍተሻ ለማድረግ በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን ይኸው ፍተሻ ብቃት ባለው የህክምና ባለሙያ አማካኝነት እና በሚፈተሸው ሰው ላይ ጉዳት በማያስከትል መልኩ ይከናወናል፡፡
7. የጉምሩክ ሹሙ በማንኛውም ሰው ላይ ውስጣዊ አካላዊ ፍተሻ ለማድረግ በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ሆኖም በፍርድ ቤት የተፈቀደን ፍተሻ

እንዳይፈፀምበት የተቃወመ ሰው ያለመፈተሽ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ደብቋል ተብሎ የተጠረጠረውን ዕቃ ደብቆ እንደያዘ ይቆጠራል፡፡

8. የጉምሩክ ሹም በዚህ አንቀጽ መሠረት ፍተሻ ሲያደርግ ዩኒፎርም ማድረግና በቅድሚያ ማንነቱን የሚያስረዳ መታወቂያ ለሚመለከተው ሰው ማሳየት አለበት፡፡
9. የጉምሩክ ሹም በዚህ አንቀጽ መሠረት ፍተሻ ለማድረግ የሚመለከተውን ሰው ጠይቆ ፈቃድ ካላገኘ የፖሊስ ሀይል ሊጠቀም ይችላል፡፡
10. በቂ ምክንያት ሲኖረው የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ሥነሥርዓት አጠናቀው የተለቀቁ ዕቃዎችን በድጋሚ ለመፈተሽ ይችላል፡፡

143. <u>ዕቃዎችንና መጓጓዣዎችን የመያዝ ሥልጣን</u>

1. ባለሥልጣኑ እቃዎች እና ማጓጓዣዎችን፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 147 መሠረት ሊወረሱ የሚችሉ ከሆነ፤ ወይም

ለ/ በቀጣይ ሂደት በማስረጃነት የሚፈለጉ ከሆነ፤

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደልተራ (ሀ) ከተመለከተው የተለየ አስተዳደራዊቅጣት የሚወሰንባቸው ከሆነ ቅጣቱእስከሚከፈል ወይም በቂ ዋስትናእስከሚቀርብ ድረስ፤[50]

ሊይዛቸው ይችላል፡፡

2. ከጭነቱ ውስጥ ከፊሉ ዕቃ የጉምሩክ ህጎችን የመተላለፍ ድርጊት የተፈፀመበት በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ዲክላራሲዮን የቀረበባቸውን ዕቃዎች በመልቀቅ ጥፋቱ የተፈፀመባቸው ዕቃዎች እንዲያዙ ያደርጋል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የመያዝ እርምጃ ሲወስድ፡-

ሀ/ የተያዘውን ዕቃ ወይም ማጓጓዣ ዓይነትና ብዛት የሚያመለክት፤ እና

ለ/ የመያዝ እርምጃው የተወሰደበትን ምክንያትና ተፈፀመ የተባለውን የጉምሩክ ህግን የመተላለፍ ድርጊት ዓይነት የሚገልጽ፤ሰነድ ለሚመለከተው ሰው መስጠት አለበት፡፡

4. የተያዘው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ ባለቤት ወይም ሃላፊ የሆነ ሰው ያልታወቀ ሲሆን ባለሥልጣኑ የዕቃው ባለቤት ወይም ሃላፊነቱን የሚወስድ ሰው እንዲቀርብ የጋዜጣ ማስታወቂያ በማውጣት ወይም ማስታወቂያውን ዕቃው ወይም ማጓጓዣው

[50] በ25/92 (2006) አ. 1160 አንቀጽ 2 (33) የተጨመረ ነው፡፡

በተያዘበት አካባቢ በሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ ለህዝብ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ በመለጠፍ ይጠራል፡፡

144. <u>*የፖስታ ዕቃን የመክፈትና የመመርመር ሥልጣን*</u>

1. የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ህጎችን ለማስፈጸም ሲባል የፖስታ እቃዎችን ባለቤቱ ወይም ወኪሉ ወይም የፖስታ ድርጅቱ ተወካይ ባለበት መክፈትናመመርመር ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ምርመራ የጉምሩክ ህግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመባቸው ዕቃዎች የተገኙ እንደሆነ የዚህ አዋጅአንቀጽ 143 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም "ባለቤት" ማለት ለገቢ ዕቃ ተቀባዩ ወይም ለወጪ ዕቃ ላኪው ነው፡፡

145. <u>*የተያዙ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን በዋስትና ስለመልቀቅ*</u>

ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 143 መሠረት የተያዙ ዕቃዎችን ወይም መጓጓዣዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች በቂ ዋስትና በመያዝ ሊለቃቸው ይችላል፦

1. ዕቃዎች ያልተከለከሉ፣ ገደብ ያልተደረገባቸው ወይም በቀጣይ ሂደት በማስረጃነት የማያስፈልጉ ከሆኑ፡
2. መጓጓዦዎቹ ዕቃዎችን ለመደበቅ እንዲያስችሉ ሆነው የተሠሩ፣ የተለወጡ ወይም መደበቂያ አካል የተገጠመላቸው ካልሆኑ ወይም በቀጣይ ሂደት ለፍርድ ቤት በማስረጃነት የማያስፈልጉ ከሆኑ፤ ወይም
3. የውርስ ውሣኔ የሚተላለፍባቸው ካልሆነ፡፡

146. <u>*ሰነዶችን የመመርመርና የመያዝ ሥልጣን*</u>

1. ባለሥልጣኑ፡-

ሀ/ የጉምሩክ ህጎችን ከማስፈጸም ጋር በተያያዘ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኝ ሰነድ አስቀርቦ ለመመርመርና የሰነዶቹን ቅጂ የመውሰድ፤

ለ/ ወደ አገር ከሚገባ ወይም ከአገር ከሚወጣ ዕቃ ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ጥፋት ተፈጽሟል ብሎ ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖር ዕቃውን የሚመለከት ማናቸውንም ሰነድ የመመርመር፤

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የተመረመሩ ሰነዶች ለቀጣይ ሂደት በማስረጃነት የሚፈልጉ ሲሆን ሰነዶቹን የመያዝ፤

ሥልጣን ይኖረዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) የተመለከቱት ሰነዶች በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ የተያዙ ሲሆንና የሰነዶቹ ባለይዞታ በሚፈለገው መንገድ አጠናቅሮ ለማቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ባለሥልጣኑ ሰነዶቹ የሚገኙበትን የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ መያዝ ይችላል፡፡

## 147. ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ስለመውረስ[51]

1. የሚከተሉት ዕቃዎች ውርስ ሆነው ለመንግሥት ገቢ ያያደረጋሉ፡-

ሀ) በኮንትሮባንድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡወይም ወደ ውጪ የሚላኩ ዕቃዎች፣

ለ) መከፈል የነበረበት ቀረጥና ታክስበህጋዊ ዕቃው ላይ መከፈል ከሚገባው ወይም አስቀድሞ ከተከፈለው ጠቅላላቀረጥና ታክስ 50 በመቶ በላይ ሆኖ በህጋዊዕቃ ከለላነት ወደ አገር ውስጥ ሲገባወይም ከአገር ሲወጣ የተገኘ ዕቃ

ሐ/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ወይም ወደ ውጭ ሊላኩ በማጓጓዣ ላይ የተጫኑ ወይም ወደ ጉምሩክ ጣቢያ የገቡ የተከለከሉ ዕቃዎች፤

መ/ ገደብ የተደረገባቸው ሆኖ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር ወደ አገር ውስጥ የገቡና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 156(3) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደመጡበት አገር እንዲመለሱ ያልተደረጉ ዕቃዎች፤

ሠ/ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እያሉ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጪ በባለቤቱ እሽጋቸው ተከፍቶና ተለያይተው፣ ወደ ሌላ ሥፍራ ተዛውረው፣ ተለውጠው ወይም ተነካክተው የተገኙ ዕቃዎች፤

ረ/ የዕቃው ባለቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 143(4) መሰረት በማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎለት ማስታወቂያ በወጣ በአንድ ወር ውስጥ ያልቀረበ ወይም አቤቱታ ያላቀረበ እንደሆነ።

ሰ/ መቀጫ ተወስኖበት በአዋጁ በተወሰነውጊዜ ውስጥ መቀጫው ያልተከፈለበት እናበአዋጁ አንቀጽ 147(1) ፊደል ተራ(ሐ) መሰረት ጥሪ ተደርጎለት ባለቤቱያልቀረበበት ማጓጓዣ፣

[51]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (35) የተጨመረ ነው፡፡ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሰ እና ሸ በአዋጁ አንቀጽ 2(35) መሰረት የተጨመረ ነው፡፡

ሸ/ አገር ውስጥ እንዲቀር ያልተፈቀደለትየቱሪስቱ ዕቃ የመቆያ ጊዜ በተጠናቀቀበሰላሳ ቀን ውስጥ ተመልሶ ያልወጣእንደሆነ፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የዕቃ ውርስ የዕቃውን መያዣ ወይም መጠቅለያ ይጨምራል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወረሱ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የዋለ ማንኛውም ማጓጓዣ፡-[52]

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 161 መሠረትመቀጫ የተወሰነበት የመጓጓዣ ባለቤትበአስተዳደራዊ መንገድ የተወሰነበትንየገንዘብ ቅጣት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ማጓጓዣውን ያልወሰደ እንደሆነማንጓጓንዣው ውርስ ተደርጎ እንዲወገድይደረጋል፡፡

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው ማጓጓዣ እንስሳ ከሆነ ባለቤቱ መቀጫውን በአንድ ሳምንት ጊዜውስጥ ከፍሎ እንስሳውን ያልተረከበእንደሆነ ኮሚሽኑ እንስሳውን ወርሶእንዲወገድ ይደረጋል፡፡

ሐ/ የማጓጓዣው ባለቤት ወይም ሃላፊ በአንቀጽ 143(4) መሠረት በማስታወቂያ ተጠርቶ ያልቀረበ እንደሆነ፣

መ) ውርስ የሚደረግ ማጓጓዣ ባለቤቶችከአንድ በላይ በሚሆኑበት ጊዜ ባለቤቶቹለመቀጫው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነትይኖርባቸዋል፡፡

ከዕቃዎቹ ጋር ውርስ ሆኖ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት ውርሱ የሚመለከተው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 145 መሠረት በዋስትና የተለቀቀ ከሆነ የተያዘው ዋስትና ውርስ ሆኖ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚፈጸም የዕቃዎች ወይም ማጓጓዣዎች ውርስ በቅን ልቦና የዕቃዎቹ ወይም የማጓጓዣዎቹ ባለቤትነት የተላለፉላቸውን ሦስተኛ ወገኖች መብት የሚነካ አይሆንም።

6. ባለሥልጣኑ ማንኛውም ዕቃ ወይም ማጓጓዣ በዚህ አንቀጽ መሠረት ውርስ ሆኖ ለመንግሥት ገቢ ከመደረጉ በፊት የዕቃው ወይም የማጓጓዣው ባለቤት በዚህ አዋጅ

---

[52]የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሀ እና ለ በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (36) የተሻሻለ ሲሆን ፊደል ተራ መ ደግሞ በአንቀጽ 2 (37) የተጨመረ ነው፡፡

አንቀጽ 143(3) ወይም (4) መሠረት የመያዝ እርምጃውን እንዲያውቀው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ተቃውሞውን እንዲያቀርብ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

7. የዕቃዉ ወይም የማጓጓዣው ባለቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቃወሚያውን ካላቀረበ ወይም ያቀረበው መቃወሚያ በባለሥልጣኑ ተመርምሮ ተቀባይነት ካላገኘ የዕቃዉ፤የመጓጓዣው ወይም የቀረበው ዋስትና ዉርስ መሆንና ለመንግሥት ገቢ መደረግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
8. የዕቃው ወይም የማጓጓዣው ባለቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ያቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት ካገኘ ባለሥልጣኑ ዕቃውን፣ ማጓጓዣውን ወይም የተያዘውን ዋስትና ወዲያውኑ መልቀቅ አለበት፡፡
9. የዕቃው፣ የመጓጓዣው ወይም የዋስትናው በዚህ አንቀጽ መሠረት ውርስ መሆንና ለመንግሥት ገቢ መደረግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 149 መሠረት በተካሄደው የወንጀል ምርመራ ውጤት ላይ ተመሥርቶ በአጥፊው ላይ ሊቀርብበት የሚችለውን የወንጀል ክስ አያስቀርም፡፡

148. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት የመጣልና የማስፈፀም ሥልጣን</u>

1. ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ጥፋቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ በዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት ምዕራፍ አንድ ድንጋጌዎች መሠረት የገንዘብ መቀጮ የመጣልና የማስፈጸም ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ባለሥልጣኑ የሚጥለው መቀጫ ተፈፃሚ የሚሆነው መቀጫው እስከሚከፈል ድረስ ጥፋት የተፈጸመበትን ዕቃ በመያዝ ይሆናል፡፡ ሆኖም የተያዘው ዕቃ መቀጫውን ለማስፈፀም በቂ ካልሆነ ባለሥልጣኑ በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የአስመጪውን ንብረት በመያዝ ቅጣቱን ሊያስፈፅም ይችላል፡፡

149. <u>የጉምሩክ ወንጀልን የመመርመርና ክስ የመመሥረት ሥልጣን</u>[53]

1.
2.

[53] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 በ22/63(2008) አ.943 በግልፅ ሳይነገሩ የተሻሩ ሲሆን ባለስልጣኑ በንዑስ አንቀፅ 3 የተሰጡት ስልጣኖች ለፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ እና ለፌዴራል ፖሊስ ተላልፈዋል፡፡

3. ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ወንጀልን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊሰወሩ ወይም ሊጠፉ ይችላሉ የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖር በማናቸውም ቦታ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፍተሻ እንዲካሄድ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በተካሄደ ፍተሻ የተገኘ ማስረጃ በፍርድ ቤት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

150. <u>ክስ እንዳይመሠረት ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>[54]

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 147(9) ድንጋጌ ቢኖርም የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ምክንያቶች ሲኖሩ የወንጀል ክስ እንዳይመስረት መወሰን ይችላል፡

1. ወንጀሉን ፈፅሚል የተባለው ሰው በዕድሜ መጃጀት ወይም በበሽታ ምክንያት ጉዳዩን በፍርድ ቤት መከታተል የማይችል ከሆነ፤
2. ጉዳዩ በክስ ሂደት ዉስጥ ቢያልፍ ብሔራዊ ጥቅምን ወይም ዓለም አቀፍ ግንኙነትን ይጎዳል ተብሎ ከታመነ፤
3. የክሱ መመስረት ተመጣጣኝና ሚዛናዊ ያልሆነ የጎንዮሽ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ከታመነበት፤
4. ወንጀሉ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በመቆየቱ አስፈላጊነቱን ያጣ ከሆነ፡፡

151. <u>የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር</u>

የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የጉምሩክ ህጎችን በማስከበር ረገድ፡-

1. የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎችን ይከላከላል፣ የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ይይዛል፣ ለባለሥልጣኑ ያስረክባል፤
2. ተላላፊ የጉምሩክ ዕቃዎችንና የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችን ያጅባል፤
3. የጉምሩክ ሹም በህግ የተሰጠውን ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት የፖሊስ ሀይል ለመጠቀም ሲጠይቅ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
4. የፍተሻ ሥራ በጉምሩክ ሹም እንዳይከናወን የሚፈጠርን ሁከት በቁጥጥር ሥር ለማዋል ተገቢና ተመጣጣኝ የሆነ ሀይል ይጠቀማል፤
5. ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው የባለሥልጣኑ ተቋማት፣ የጉምሩክ ጣቢያዎችና የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘኖች ጥበቃ ያደርጋል፤

---

[54] በ22/63(2008) አ.943 ይህ ስልጣን ለፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ተላልፏል፡፡

6. ህገወጥ ዕቃ ሊተላለፍባቸው በሚችሉ የአገሪቱ የድንበር ኬላዎች ጥበቃ ያደርጋል፤
7. የወንጀል ተጠርጣሪዎችን በመያዝ ለህግ ያቀርባል፤
8. የዐቃቤ ህግ ምስክሮችን ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

**<u>ምዕራፍ ሦስት</u>**

**<u>ስለአቤቱታና ስለይግባኝ</u>**

152. **<u>አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ስለማቋቋም</u>**

ባለሥልጣኑ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እና በዋናው መሥሪያ ቤት ደረጃ የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍሎች ያቋቁማል፡፡

153. **<u>የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍሎች፡-

ሀ/ በዕቃዎች የስሪት አገር አወሳሰን፣ ዋጋ አተማመን፣ አሰያየም፣ አመዳደብና በታሪፍ ልክ፤

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተካሄደ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲትን ተከትሎ በተሰጡ ውሳኔዎች፤ እና

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ለ) እና (ሐ) ከተመለከቱት ውጪ በሆኑ ከጉምሩክ ፎርማሊቲ ጋር በተያያዘ በሚሰጡ ሌሎች አስተዳደራዊ ውሳኔዎች፤

ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የመመርመርና የመወሰን ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል።

2. በባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት የሚቋቋም የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን የመመርመርና የመወሰን፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 147(6) መሠረት የሚቀርቡ የዕቃ ወይም የማጓጓዣ ውርስ መቃወሚያዎች ተቀባይነት ማጣት ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የመመርመርና ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ለወከለው ሃላፊ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ፤ እና

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 148 መሠረት በሚሰጡ አስተዳደራዊ የቅጣት ውሳኔዎች

ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የመመርመርና ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ለወከለው ሃላፊ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ፡፡

154. **የአቤቱታ አቀራረብና የዉሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 153 መሠረት ለማንኛውም የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ ቅሬታውን ያስከተለው ውሳኔ በፅሑፍ በተሰጠ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ በፅሑፍ መቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ የአቤቱታ ወይም የይግባኝ ማመልከቻ አቤቱታው በሚመለከተዉ ሰው ወይም በወኪሉ ተፈርሞ ሊቀርብ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል የቀረበለትን አቤቱታ ባለሥልጣኑ በመመሪያ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መርምሮ ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡
4. ማንኛውም አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል የቀረበለትን አቤቱታ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ካደረገው አቤቱታ አቅራቢው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይግባኝ ማቅረብ የሚችል መሆኑን በውሳኔው ውስጥ መግለጽ አለበት፡፡

155. **ስለይግባኝ ስነ-ስርዓት**

1. የባለሥልጣኑ አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም የተወከለው ሃላፊ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በተሰጠ በአንድ ወር ውስጥ ይግባኙን በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የግብር ይግባኝ ጉባዔ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የቀረጥና ታክስ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የግብር ይግባኝ ጉባዔው ክርክር ያስነሳው የቀረጥና ታክስ ክፍያ መፈጸሙን ሳያረጋግጥ ይግባኙን አይቀበልም፡፡
3. የግብር ይግባኝ ጉባዔው የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት አለበት በማለት የሚቃወም ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በአንድ ወር ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ ይችላል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በገቢ ግብር አዋጁ የይግባኝ ሥነ ሥርዓትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚቀርቡ ይግባኞችም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የጉምሩክ ጥፋቶችና ቅጣቶች

### ምዕራፍ አንድ

### የጉምሩክ ጥፋቶችና አስተዳደራ ቅጣቶች

**156. በወጪና ገቢ ዕቃዎች ላይ የተጣለ ገደብን አለማክበር**

1. ማንኛውም ሰው ገደብ የተደረገበትን ዕቃ ፈቃድ ሳይኖረው ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ከአገር ያስወጣ ወይም ለማስወጣት የሞከረ እንደሆነ እና ከሚመለክተው አካል በአንድ ወር ውስጥ ፈቃድ ማቅረብ ካልቻለ ከብር 100,000 በማያንስና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም መንገደኛ ይዞት የተገኘ ዕቃ በብዛት ወይም በዋጋ በህግ ወይም በሚኒስቴሩ መመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ የሆነ እንደሆነ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃውን ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መቀጮ ያስከተለው ዕቃ የገቢ ዕቃ ከሆነ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ለማቅረብ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ በአንድ ወር ውስጥ በአስመጪው አማካይነት ተመልሶ እንዲወጣ፣ የወጪ ዕቃ ከሆነም ከአገር እንዳይወጣ ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረትተመልሶ እንዲወጣ የተወሰነበት ዕቃ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ የአስተዳደራዊ መቀጫው መከፈል እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው ውርስ ተደርጎ ይወገዳል፡፡[55]

**157. ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል ወይም አንሶ እንዲከፈል ስለማድረግ[56]**

[55] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (38) የተጨመረ ነው፡፡

1. ማንኛውም ሰው ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም በቀረበ የዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በህጋዊ ዕቃ ከለላነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ያደረገ ወይም የሞከረ እንደሆነ የተገኘው የቀረጥና ታክስ ልዩነት በዲክላራሲዮን በተመዘገበው ዕቃ ላይ መከፈል ከነበረበት ቀረጥና ታክስ ሃምሳ በመቶ የማይበልጥ ወይም ከብር አንድ ሚሊዬን በታች መሆኑ ሲረጋገጥ ያልተከፈለው የዕቃው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩነቱ ላይ ያልተከፈለው ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በልዩነት የተገኘዉ ቀረጥና ታክስ መከፈል ከሚገባው ጠቅላላቀረጥና ታክስ ከ 5 በመቶ የማይበልጥናድርጊቱ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥለአንድ ጊዜ ብቻ የተፈፀመ እንደሆነአስመጪው በልዩነት የተገኘውን ቀረጥናታክስ ያለቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ሰው በዲክላራሲዮን ሳይመዘገብ በህጋዊ ዕቃ ከለላነት ወደ አገር ውስጥ ያስገባው ወይም ለማስገባት የሞከረው ዕቃ በአስመጪው የንግድ ፈቃድ የማይሸፈን ዕቃ የሆነ እንደሆነ አስመጪው የዕቃው ቀረጥና ታክሰ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖየዕቃውን ዋጋ 100 ፐርሰንት መቀጫይከፈልበታል፡፡

4. ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ሞተርወይም ሻንሲ የተገጠመለት ተሽከርካሪባለንብረት የቀረጥና ታክስ መከፈልእንደተጠበቀ ሆኖ በሞተሩ ወይምበሻንሲው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥናታክስ እጥፍ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

5. የተሽከርካሪው ባለቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ 4 በተወሰነው መሰረትቀረጥና ታክስ ከነመቀጮው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ያለተረከበ እንደሆነ ተሽከርካሪው ይወረሳል፡፡

[56]በ25/92 (2011) አ.1160 አንቀጽ 2 (39) ተሻሻለ እንዲሁም የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3. 4 እና 5 በአንቀጽ 2 (40) መሰረት የተጨመሩ ናቸው፡፡

158. **እሽጎችን ስለመፍታትና ምልክቶችን ስለማንሳት**

ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የጉምሩክ ሹም ፈቃድ ሳያገኝ በመተላለፍ ላይ ያለ ወይም የጉምሩክ ወደብ የደረሰ፡-

1. ማጓጓዣ ወይም ኮንቴይነር ላይ የተደረገውን የጉምሩክ ማሸጊያ የፈታ ወይም ያላቀቀ እንደሆነ፤
2. ዕቃ ወይም የዕቃው መያዣ ላይ የተደረገውን ምልክት ያነሳ፣ የፋቀ፣ የሰረዘ ወይም የለወጠ እንደሆነ፣ ወይም
3. የዕቃን መያዣ የከፈተ ወይም የበተነ እንደሆነ፤

ከብር 10,000 በማያንስና ከብር 500,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

159. **ናሙናዎችን አለመመለስ**

ማንኛውም ሰው ለናሙና የወሰደውን ዕቃ ያልመለሰ ወይም በዕቃው የተገለገለ ወይም ዕቃው እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ የዕቃውን ዋጋ፣ ቀረጡንና ታክሱን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

160. **ስለ አጓጓዥ ግዴታዎች እና ኮንትሮባንድ በማጓጓዝ ድርጊት ስለመሳተፍ**[57]

1. ማንኛውም አጓጓዥ፥

(ሀ) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመንገደኞች ወይም የጭነት መግለጫ ካላቀረበ፣

(ለ)ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲገባካደረገ፣ ወይም

(ሐ) ማጓጓዣው ከጉምሩክ ወደብእንዲወጣ ከተወሰነ በኋላ ምክንያቱንለጉምሩክ ሹም ሳያስረዳና ፈቃድሳያገኝ እንዲቆይ ካደረገ፣ ከብር 2ሺ.ባላነሰ እና ከብር 5ሺ. በማይበልጥመቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም አጓጓዥ ጉምሩክ ወደብበደረሰ ማጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሹም በሌለበት ዕቃ የጫነ፣ ያራገፈ ወይምለመጫን ወይም ለማራገፍ ሙከራ ያደረገእንደሆነ ከብር 7ሺ. በማያንስና ከብር 10ሺ.በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም የኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነ ማጓጓዣ ባለቤት በኮንትሮባንድ ወንጀል ተሳትፎ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ በወንጀል የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ

---

[57]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (41) ተሻሻለ

በወንጀሉ ተሳትፎ ቢኖረውም ባይኖረው የኮንትሮባድ ዕቃው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጫነውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ዋጋ አንድ መቶ ፐርሰንት ወይም ብር አንድ መቶ ሺህ ከሁለቱ አነስተኛውን የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ቢኖርም ሲጓጓዝ የተያዘው የኮንትሮባንድ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የማይወጣለት የሆነ እንደሆነ የማጓጓዣው ባለቤት ብር 100 ሺህ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ማጓጓዣ እንስሳ ከሆነ ባለቤቱ የተጫነውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ዋጋ አንድ መቶ ፐርሰንት ወይም የእንስሳውን ወቅታዊ ዋጋ የሚያክል የገንዘብ መቀጫ ከሁለቱ አነስተኛውን የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

6. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተመለከተው ቢኖርም በማንኛውም ሁኔታ በማጓጓዣው ባለቤት ላይ የሚጣለው መቀጫ ከማጓጓዣው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መብለጥ የለበትም፡፡

7. ማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያላከበረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 178(3) መሠረት በሚወጣ መመሪያ ላይ ተመሥርቶ ሊወሰድ የሚችል ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር 50ሺ በማያንስና ከብር 100ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

8. ወደ ጉምሩክ ቦንድ መጋዘን መግባት ያለበት ዕቃ ወደ ጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ገብቶ የተገኘ በሚሆንበት ጊዜ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ወደ ተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን ያልተላለፈ ዕቃ አሰመጪ ብር ሦስት ሺህ መቀጫ ከፍሎ ዕቃውን ወደ ቦንድድ መጋዘን እንዲያስተላልፍ ወይም ዕቃው በጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ እያለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀምበት ይደረጋል፡፡

9. የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የተፈፀመበት ዕቃ በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ከመጋዘኑ ያልወጣ እንደሆነ አስመጪው መቀጫ ከፍሎ ዕቃው ከመጋዘን እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

10. ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ ዕቃ ከመወገዱ በፊት አስመጪው ዕቃውን መረከብ የሚፈልግ ከሆነ አስመጪው ሊከፍል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎች መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን 20 በመቶ የገንዘብ መቀጫ መክፈል አለበት፡፡

11. ወደ አገር ውስጥ በጊዜያዊነት የገባ ዕቃ በአዋጁ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ አሰመጪው በእርጅና ቅናሹ ላይ የሚከፍለው ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎች መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህኑ ቀረጥና ታክስ 25 በመቶ መቀጫ ከፍሎ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ተደርጎለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## 161. <u>የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ግዴታዎችን አለማክበር</u>

በማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን ያላከበረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 176(3) መሠረት በሚወጣ መመሪያ ላይ ተመሥርቶ ሊወሰድ የሚችል ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 162. <u>የጉምሩክ የትራንዚት ሥነ ሥርዓትን አለማክበር</u>[58]

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በጉምሩክ ደንብ ወይም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተደነገገውን የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት ያላከበረ እንደሆነ ከብር 5 ሺህ በማያንስና ከብር 20 ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተላላፊ የትራንዚት ዕቃ የሚያጓጉዝ ማጓጓዣበተወሰነለት ጊዜና መስመር ተጓጉዞከአገር መውጣቱ ያልተረጋገጠ እንደሆነየተያዘው ዋስትና ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

3. ተላላፊ የትራንዚት ዕቃ የሚያጓጉዝማጓጓዣ ዕቃው ተራግፎ ወይም ተደብቆ የተገኘ እንደሆነ ዕቃውይወረሳል፡፡

---

[58]በ25/92 (2006) አ. 1160 አንቀጽ 2 (42) ተሻሻለ

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2) ቢኖርም ዕቃው የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በጉዞ ላይ እያለ መሆኑከተረጋገጠ የተያዘው የዋስትና ገንዘብተመላሽ ይደረጋል፡፡

5. ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (4) አፈፃፀም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በማጓጓዣው ላይ የደረሰ ብልሽት ወይም አደጋ ወይም በአጓጓዡ ላይ የደረሰ ከባድ ህመም ወይም የመንገድ መዘጋት ወይም ክልከላ ወይም በፀጥታ ምክንያት የተፈጠረ የጉዞ ወይም ከእነዚህ ጋር የሚመሳሰል ሌላ ማንኛውም አስገዳጅ ሁኔታ ማለት ነው፡፡

## 163. ከቀረጥ ነፃ በገባ ዕቃ ያለአግባብ ስለመገልገል

1. ማንኛውም ሰው ከቀረጥ ነፃ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባን ዕቃ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚቃረን ሁኔታ፡-
   ሀ/ የቀረጥ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ በሌላ አገልግሎት ላይ ያዋለ ወይም ለሌላ ሰው ያስተሳለፈ እንደሆነ፤
   ለ/ ዕቃው ለግል አገልግሎት እንዲውል የገባ ሲሆን በማናቸውም መልኩ ከቤተሰብ ውጪ በሌሎች ሰዎች አገልግሎት ወይም ይዞታ ሥር እንዲውል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም፤
   ሐ/ ዕቃው ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የገዛ፣ የተቀበለ፣ የተገለገለ፣ ያስተላለፈ ወይም ለሌሎችሰዎች አገልግሎት እንዲውል ያደረገ እንደሆነ፤ዕቃው በተያዘበት ጊዜ ወደ አገር እንደገባ ተቆጥሮ ለዕቃው ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖየቀረጥና ታክሱን 50በመቶየገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) አፈፃፀም "ቤተሰብ" ማለት የባለመብቱን የትዳር ጓደኛ፣ ልጆችና የባለመብቱንና የትዳር ጓደኛውን ወላጆችን ብቻ ያጠቃልላል፡፡

## 164. በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባን ዕቃ ያለአግባብ ስለመገልገል[59]

1. ማንኛውም ሰውቀረጥና ታክስሳይከፈልበት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን ዕቃ ተመሣሣይመብት ለሌለው ሶስተኛ ወገን በኪራይ

[59]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (43) ተሻሻለ

ወይም በሽያጭ ወይም በሌላማንኛውም ሁኔታ ያስተላለፈ እንደሆነ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግሥትገቢ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ መከፈል ያለበትን ቀረጥና ታክስመክፈል አለበት፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው ከገባበት ዓላማ ውጪ ሲጠቀምበት የተገኘ ማንኛውም ሰው በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ 50 በመቶ በመቀጫ ይከፍላል፡፡

3. በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ የውጭ አገር የንግድ መጓጓዣ በተወሰነለት ጊዜ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ ወይም በአገር ውስጥ ጭነትና በወጪ ዕቃ ትራንስፖርት አገልግሎት ተሰማርቶ የተገኘ እንደሆነ ብር 50 ሺህ ቅጣት ከፍሎ ማጓጓዣው ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

### 165. <u>ሌሎች ጥፋቶች</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ክልከላዎች ወይም ግዴታዎችን ባለማክበር በዚህ ምዕራፍና በዚህ ክፍል ምዕራፍ ሁለት ከተመለከቱት ውጪ ሌላ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የጉምሩክ ወንጀሎችና ቅጣቶች</u>

### 166. <u>የጉምሩክ ቁጥጥርን ስለማሰናከል</u>

1. ማንኛውም ሰው የጉምሩክ ሹም ሰነዶችን እንዳይመረምር ወይም ማጓጓዣዎችን ወይም ዕቃዎችን እንዳይፈትሽ ወይም ወደ መጋዘን፣ የንግድ መደብር ወይም መኖሪያ ቤት እንዳይገባ ያደረገ ወይም ሁከት የፈጠረ ወይም ለሚጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ያልሰጠ ወይም ለምርመራ ያልተባበረ ወይም በማናቸውም መንገድ ሥራውን ለማደናቀፍ ጣልቃ የገባ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ሃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የእስራት ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ከፍ ይደረጋል፡፡

## 167. ሰነዶችንና መለያዎችን ወደ ሀሰተኛነት ስለመለወጥና አስመስሎ ስለመሥራት

ማንኛውም ሰው፡-

1. በባለሥልጣኑ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማገኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣ ባለሥልጣኑ የሚጠቀምበትን ቅፅ፣ ማህተም፣ መታወቂያ፣ ዓርማ፣ የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ማንኛውንም ስነድ ወይም ምልክት ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሠራ ወይም ይህንኑ ያከፋፈለ፣ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ አስራት እና ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤
2. ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገነት ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፣ ባለሥልጣኑ የሚጠቀምበትን የደንብ ልብስ አስመስሎ የሠራ ወይም ይህንኑ ያከፋፈለ፣ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 168. የኮንትሮባንድ ወንጀል

1. ማንኛውም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የጉምሩክ ህጎችን በመተላለፍ የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ያስገባ ወይም ከጉምሩክ ክልል ያስወጣ ወይም ለማስወጣት ወይም ለማስገባት የሞከረ እንደሆነ የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 50 ሺህ በማያንስና ከብር 200 ሺህበማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡[60]
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ሕገወጥ መንገድ የተገኙ ዕቃዎች መሆናቸውን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ዕቃዎቹን ያጓጓዘ፣ ያከማቸ፣ የያዘ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ማንኛውም ሰው ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት እና ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

---

[60] በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (44) ተሻሻለ

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ሃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የፅኑ አስራት ቅጣቱ ከ10 ዓመት አስከ 15 ዓመት ከፍ ይደረጋል፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም በህገወጥ መንገድ ከአገር ለመውጣት በጉምሩክ የጠረፍ መስመር ውስጥ የተያዘ ወጪ ዕቃ የኮንትሮባንድ ዕቃ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።

169. **የማጭበርበር ወንጀል**[61]

1. ማንኛውም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው በህጋዊ ዕቃ ከለላነት፣ ክልከላ የተደረገበትን ዕቃ ወደ አገር ካስገባ፣ ከአገር ካስወጣ ወይም ከአገር ለማስወጣት ወይም ወደ አገር ለማስገባት የሞከረ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 200,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. የዚህ አዋጅ አንቀፅ 157 ድንጋጌእንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በዲክላራሲዮን ያልተመዘገበ ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ በህጋዊ ዕቃ ከለላነት ወደ አገር ያስገባ ወይም ከአገር ያስወጣ ወይም ወደ አገርለማስገባት ወይም ከአገር ለማስወጣት የሞከረ እንደሆነ የተገኘው የቀረጥና ታክስ ልዩነት ህጋዊ በሆነው ዕቃ ላይ ከተከፈለው ወይም ሊከፈልከሚገባው ጋር ሲነፃፀር ከሃምሣ በመቶበላይ ከሆነ እና በልዩነት የተገኘው ቀረጥና ታክስ መጠን ከብር አንድ ሚሊዬን በላይ ከሆነ የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሦስት አስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትይቀጣል፡፡
3. የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ሳይኖረውየቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ያለው በማስመሰል በማንኛውም የተጭበረበረሁኔታ ቀረጥ ሳይከፈልበት ዕቃ ወደአገር ውስጥ ያስገባ ወይም ከአገርያስወጣ ወይም ወደ አገር ለማስገባትወይም ከአገር ለማስወጣት የሞከረእንደሆነ ከሰባት ዓመት በማያንስናከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትእና ከብር 100 ሺህ በማያንስና ከብር 200ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮይቀጣል፡፡

[61]በ25/92 (2011) አ. 1160 አንቀጽ 2 (45) የተሻሻለ ሲሆን የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3፣ 4 እና 5 በማሻሻያ አዋጁ አንቀጽ 2(46) የተጨመሩ ናቸው፡፡

4. መከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስላለመክፈል ወይም ለማሳነስ በማሰብ፦
   ሀ) ማንኛውንም ሐሰተኛ ሰነድለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀምያቀረበ እንደሆነ፤
   ለ) ሐሰተኛ መረጃ ወይም መግለጫለጉምሩክ ያቀረበ እንደሆነ፤
   ሐ) ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚቀርቡሰነዶችን የሰረዘ፣ የደለዘ፣ የፋቀወይም አስመስሎ የሰራ እንደሆነወይም፤

   መ)ሌሎች ማናቸውንም የማጭበርበርተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤

   ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስርዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እናበብር 200 ሺህ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡"

5. በአዋጁ አንቀጽ 163 የተደነገገውቢኖርም የኢንቨስትመንት ዕቃከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥያስገባ ማንኛውም ሰው ከቀረጥና ታክስነፃ ያስገባውን የኢንቨስትመንት ዕቃ፡-

   ሀ)ተመሳሳይ መብት ለሌለው ሦስተኛወገን ያስተላለፈ ወይም መብቱ ከተሰጠበት ዓላማ ውጭ አገልግሎትላይ ያዋለ እንደሆነ፣

   ለ)ለኢንቨስትመንት ከተፈቀደው ቦታውጭ ለሽያጭ አከማችቶ የተገኘእንደሆነ፣

   የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖበብር ሁለት መቶ ሺ የገንዘብ መቀጮና ከአምስት እስከ ሰባት ዓመትበሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

170. <u>እሽጎችን በመፍታትና ምልክቶችን በማንሳት ስለሚፈጸም ወንጀል</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 158 የተመለከተው ጥፋት የተፈጸመው ዕቃውን ለማጉደል፣ አንዱን ዕቃ ከሌላው ለመደባለቅ፣ ለማበላሸት፣ ለመስረቅ ወይም በማናቸውም አኳኋን እራሱን ወይም ሌላውን ሰው ለመጥቀም ወይም ማንኛውንም ሰው ለመጉዳት በማሰብ ከሆነ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 200,000 በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ሃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የፅኑ እስራት ቅጣቱ ከአሥር እስከ አስራ አምስት ዓመት ከፍ ይደረጋል፡፡

171. **የአጓጓዥ ግዴታዎችን በመጣስ ስለሚፈጸም ወንጀል**

ማንኛውም አጓጓዥ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎችን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖር ከጉምሩክ ወደብ ውጪ ካራገፈ ወይም ከጫነ ወይም ለማራገፍ ወይም ለመጫን ከሞከረ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር 7,000 በማያንስና ከብር 15,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

172. **የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ያለአግባብ መጠቀም**

ማንኛውም ሰው ያለባለሥልጣኑ ፈቃድ የባለሥልጣኑን የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት የተጠቀመ ወይም ያልተፈቀደለት ሌላ ሰው እንዲጠቀም ያደረገ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 20,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

173. **በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ ስለሚፈፀም ቅጣት**

በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በወንጀል ህግ አንቀጽ 34 በተደነገገው መሠረት በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱ የጉምሩክ ወንጀሎች ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 90 መሠረት ይቀጣል፡፡

174. **የማስረጃ ተቀባይነት**

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ተቀባይነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ማስረጃዎች በፍርድ ቤት በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡-

1. ዲጂታል ወይም ኤሌክትሮኒክስ ማስረጃዎች፤
2. በውጭ አገር የህግ አስከባሪ አካላት የተገኙ ማስረጃዎች፤
3. በጉምሩክ ቁጥጥርና ህግን በማስከበር ሂደት በባለሥልጣኑ የተሰባሰቡ ማስረጃዎች፤
4. ከዕቃዎች ምደባ ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ጉምሩኮች ድርጅቶች የተዘጋጁ ሰነዶች፡፡

**ክፍል ስምንት**

**ልዩ ድንጋጌዎች**

175. **የጉምሩክ መጋዘኖች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ**

1. ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ እና ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን የኪራይ ወይም የግል አገልግሎት የሚሰጡ ሆነው ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡
2. የወል ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም የወል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን፡-

   ሀ/ ዕቃ የማጓጓዝ ሥራ በሚያካሂድ የንግድ ድርጅት፤

   ለ/ የመጋዘን አገልግሎት ሥራ ለመሥራት በተቋቋመ የንግድ ድርጅት፤

   ሐ/ የኢንዱስትሪ ዞን አገልግሎት ለመስጠት በተቋቋመ ድርጅት፤

   መ/ ዕቃ የማስተላለፍ ሥራ በሚያካሂድ የንግድ ድርጅት፤ ወይም

   ሠ/ በባለሥልጣኑ መመሪያ በሚወሰን ማንኛውም ሌላ ሰዉ፤

   ለኪራይ አገልግሎት ሊቋቋም ይችላል፡፡
3. የግል ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ፡-

   ሀ/ በመንግሥት ፕሮጀክት ላይ በተሠማራ የሥራ ተቋራጭ፤ ወይም

   ለ/ ባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ በሚፈቅድለት ሌላ ሰው፤

   ለግል አገልግሎት ሊቋቋም ይችላል፡፡
4. የግል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን፡-

   ሀ/ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ለመሸጥ በተቋቋመ ድርጅት፤

   ለ/ ለእርዳታ ወይም ለንግድ ዓላማ ባልተቋቋመ ድርጅት፤

   ሐ/ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎችንና ግብዓቶችን በመጠቀም ዕቃዎችን በሚያመርት ድርጅት፤ ወይም

   መ/ በባለሥልጣኑ መመሪያ በሚወሰን ማንኛውም ሌላ ሰው፣

   ለግል አገልግሎት ሊቋቋም ይችላል፡፡
5. የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የሚቋቋመውና የሚተዳደረው በባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡
6. የጉምሩክ መጋዘኖች ደረጃ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

176. <u>የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ</u>

1. ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ለኪራይ አገልግሎት ለማቋቋም ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የሚጠይቅ ሰው፡-

   ሀ/ የሚያከናውነውን የሥራ ዓይነት የሚገልፅ ማስረጃ፤

   ለ/ሥራውን ለማከናወን የተሰጠውን ፈቃድ፤

ሐ/ አመልካቹ ድርጅት ከሆነ የሕግ ሰውነት የተሰጠው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣

መ/ የመጋዘኑን የህንፃ ፕላን፣

ሠ/ ለመጋዘኑና በመጋዘኑ ለሚከማቹ ዕቃዎች የመድን ዋስትና የሚገባ ለመሆኑ የተሰጠ ማረጋገጫ፣

ረ/ መጋዘኑ ለዕቃዎች አቀማመጥና ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን ማሟላቱን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ሰ/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን፣እና

ሸ/ በባለሥልጣኑ መመሪያ የሚጠየቁ ሌሎች ሰነዶችን፣ ከማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ለግል አገልግሎት ለማቋቋም ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የሚጠይቅ ሰው ባለሥልጣኑ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ ሰነዶችን ከማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
3. የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ ፈቃዱ የሚታደስበት ሁኔታ እና የሚሠረዝበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
4. የጉምሩክ መጋዘን የሚቋቋምበትን ዝርዝር ሁኔታ፣ አጠቃቀሙን እና የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ማውጫና ማሳደሻ ክፍያ ተመን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

177. <u>የመረጃ ተደራሽነት</u>

1. ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ሕጎች እና የታሪፍ አመዳደብንና ሌሎች የጉምሩክ አሠራርን የሚመለከቱ አግባብ ያላቸው መረጃዎች ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት መረጃዎች እንደአግባቡ በሕትመቶችና በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ሥርዓት አማካይነት ተደራሽ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተደራሽ በተደረገ መረጃ ላይ ማሻሻያ ወይም ለውጥ የተደረገ እንደሆነ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ተጠቃሚዎች በተመሳሳይ መንገድ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

178. <u>የጉምሩክ ቅፆችን ስለማሳተምና ማሰራጨት</u>

1. ለጉምሩክ ፎርማሊቲ የሚያስፈልጉ ቅፃትን ማዘጋጀትና ማሳተም የሚችለው ባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡
2. በባለሥልጣኑ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው የጉምሩክ ቅፆችን መያዝና ማሰራጨት አይችልም፡፡

179. <u>የጉምሩክ ሹም መብት</u>

ማንኛውም የጉምሩክ ሹም፡-

1. ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ በፈፀመዉ ድርጊት ምክንያት ለሚቀርብበት ክስ በባለሥልጣኑ ወጪ የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኝ ወይም የባለሥልጣኑ ነገረፈጅ እንዲከራከርለት ይደረጋል፤
2. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በቅን ልቦና በፈፀመዉ ተግባር ለሚደርስ ጉዳት ካሳ እንዲከፍል አይጠየቅም፡፡

180. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለስሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

181. <u>ስለተሻሩ ሕጎችና ስለሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

1. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ነባር ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ አዲስ ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸዉ ይቀጥላል።

182. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

በሌሎች ህጎች የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በነበረው ህግ መሰረት ፍጻሜ ያገኛሉ።

183. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 30 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ለ/ <u>የሀገር ውስጥ ገቢ</u>**

## አዋጅ ቁጥር110/1990

## የቴምብር ቀረጥ አዋጅ[62]

በሰነዶች ላይ የተጣለው የቴምብር ቀረጥ የኪነጥበብ ዕድገትን፣የፋይናንስ ተቋሞችን እንቅስቃሴ እና የካፒታል ንብረት ዝውውርን ለማገዝ በሚያስችል አኳኋን እንዲሻሻል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና (11) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ አዋጅ "የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "ግልግል" ማለት ስለግልግል፣ ስለዕርቅ፣ ስለስምምነት ወይም ስለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በተደረገ ስምምነት መሠረት በፍርድ ቤት ሳይሆን በገላጋዮች አልቆ በጽሁፍ የተሰጠ ውሳኔ ነው፤
   2. "ማገቻ" የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውንም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ፣ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጪው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል፤
   3. "የኅብረት ስምምነት" ማለት በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ የሠራተኞች ማኅበራት፣ ወኪሎች እና በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ አሠሪዎች ወይም

---

[62]በአዋጁ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን" ወይም "የፌዴራል ገቢዎች ቦርድ" የሚለው ስያሜ በ15/9 (2001) አ.612 መሰረት "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን" በሚል ተተክቷል።

የአሠሪ ማኅበራት ወኪሎች ወይም አሠሪዎችን በሚወክሉ ተጠሪዎች መካከል ስለሥራ ሁኔታዎች የሚደረግ በጽሁፍ የሠፈረ ስምምነት ነው፤

4. “የሥራ ውል” ማለት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው፣ በአሠሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመሥራት ሲስማማ በሁለቱ መካከል የሚመሠረት ውል ነው፤
5. “ሰነድ” ማለት ማናቸውም መብት ወይም ግዴታ የተመሠረተበት፣ የተመዘገበበት፣ የተላለፈበት፣ የተወገደበት፣ ልኩ የተወሰነበት፣ ወይም የተስፋፋበት ወይም የተጠቀሰው ድርጊት ተፈጽሟል የተባለበት ማንኛውም የጽሁፍ መረጃ ነው፡፡
6. “ሚኒስትር” ማለት የገንዘብ ሚኒስትር[63]ነው፤
7. “ማረጋገጫ” ማለት የሕዝብ ጉዳዮችን ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው ሰው በሰነዶች ላይ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤
8. “ሰው” ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ቢሆንም ባይሆንም ማናቸውም ድርጅት ነው፤
9. “ሰነድ ማስፈጸም” ማለት ሰነድ መስራት፣ ማውጣት በሰነዱ የተመከለተውን ማስፈጸም ወይም ሰነዱን ማዛወር ነው፡፡
10. “የመያዣ ሰነድ” ማለት ተበዳሪው ወይም ዋሱ ለአበዳሪ በሙሉ ወይም በከፊል ንብረቱን በመያዣነት የሚሰጥበትሰነድ ነው፤
11. “የመተዳደሪያ ደንብ” እንደአግባብነቱ የመመስረቻ ጽሁፍን ይጨምራል።

3. <u>**የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች**</u>

የሚከተሉት ሰነዶች የቴምብር ቀረጥ ይከፈልባቸዋል፤

1. የማንኛውም ንግድ ማኅበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም የማንኛውም ዓይነት ማኅበር መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣
2. ግልግል፣
3. ማገቻ፣
4. የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ፣

[63] በ25/8 (2011) አ.1097አንቀጽ 9 (4) የገንዘብ ሚኒሰቴር በሚል ይነበብ፡፡

5. ውል፣ ስምምነትና የእነዚህ መግለጫ፤
6. የመያዣ ሰነዶች፣
7. የሕብረት ስምምነት፣
8. የሥራ (ቅጥር) ውል፣
9. የኪራይ፤ የተከራይ አከራይና መሰል መብት የማስተላለፊያ ሰነዶች ጭምር፣
10. ማረጋገጫ፣
11. የውክልና ሥልጣን፣
12. የንብረት ባለቤትነትን ማስመዝገቢያ ሰነድ፡፡

4. **<u>የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል ልክ</u>**

1. በአንቀጽ 3 ስር በተመለከተው በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ መከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ከዚህ ጋር በተያያዘውና የዚህ አዋጅ አንድ አካል ሆኖ በሚቆጠረው ሠንጠረዥ ውስጥ እንደተዘረዘረው ይሆናል፡፡
2. አንድ ሰነድ በተደጋጋሚ ተፈጻሚ ሲሆን ሊከፈል የሚገዛው የቀረጥ መጠን በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው ነው።

5. **<u>የቀረጡ አተማመን</u>**

1. በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የሚችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቀረጥ መጠን በሠንጠረዡ ላይ እንደተመለከተውየዋጋው መቶኛ ይሆናል፡፡
2. በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የማይችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ሰነድ በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው የቀረጥ መጠን ይሆናል።
3. አንድ ሰነድ ላይ ተከፋይ የሚሆነው ቀረጥ በብር ሳይሆን በሌላ ገንዘብ ከሆነ፤ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱበተፈጸመበት ቀን በዋለው የምንዛሪ ልክ ነው።
4. በስቶክ ወይም ሌላ ዋስትና ባለው ነገር ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዋጋው ላይ ተመስርቶ ከሆነ፣ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው አማካኝ ዋጋ መሠረት ነው፡፡
5. ብዙ የተለያዩ ነገሮች የተጠቃለሉበት ወይም ለብዙ ልዩ ሰነዶች የቆመ ማናቸውም ሰነድ በያዛቸው ልዩ ልዩ ሰነዶች መጠን በዚህ አዋጅ መሠረት በእያንዳንዱ ሰነድ ላይየሚከፈለው ቀረጥ በመጠቃለል ተደምሮ ይከፈልበታል።

6. ሀ/ ንብረትን በባለቤትነት ለማስመዝገብ በተቋቋመ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብርቀረጥ የሚተመነው በንብረቱ ሰነድ ውስጥ በተወሰነው የንብረቱ ዋጋላይ ሆኖ ዋጋው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ነው።

ለ/ በንብረቱ ሰነድ ላይ የተመለከተውን ዋጋ የፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ተገቢው የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት የንብረቱ ዋጋ ለዚሁ ጉዳይ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንበሚሰይመው ኮሚቴ ይወሰናል፡፡

6. <u>የክፍያ ግዴታ</u>

1. ከዚህ በታች በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር በአንድ ሰነድ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሰነዱ ላይ የሚተመነውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት።
2. በኢትዮጵያ ውስጥ ሰነዱን የሚሠራው ወይም የሚሰጠው ሰው ሰነዱ እንደተፈጸመ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ አለበት። ሆኖም አንድ ሰነድ የተሠራው ወይምየተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆነ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰነዱን በኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ ያስፈጸመው ሰው ነው።
3. በኪራይ ውል ውስጥ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በኪራይ ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ ያለበት ተከራይ ነው።
4. በመያዣ ሰነድ ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ ተበዳሪው የመክፈል ግዴታ አለበት።
5. በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቴምብር ቀረጥ ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የመክፈል ግዴታ ያለበት የንብረቱ ባለቤትነት የሚመዘገብለት ሰው ይሆናል፡፡
6. ውል ወይም ስምምነት የሚመሰርቱ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።
7. በቅጥር ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የአሠሪው ይሆናል፡፡

8. ጉዳያቸውን በግልግል የሚያስወስኑ ወገኖች ለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።
9. በኅብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አሠሪውና ሠራተኞቹ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

7. <u>ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ</u>

1. የቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በሚከተለው ጊዜና ሁኔታ ነው፤
   ሀ/ በመመስረቻና መተዳደሪያ ጽሑፎች፤ ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ፣
   ለ/ በግልግል፣ ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ፤
   ሐ/ በውል ወይም በስምምነት ሰነዶች ላይ ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚፈረሙበት ጊዜ፤
   መ/ በኪራይ ወይም በተከራይ አከራይ ውል ላይ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ፤
   ሠ/ በማረጋገጫ ሰነድ ላይ፣ ማረጋገጫው በሚሰጥበት ጊዜ፣
   ረ/ በመያዣ ሰነድ ላይ፤ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ፤
   ሰ/ በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ፣ የማስመዝገቡ ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ወይም በሚፈጸምበት ጊዜ፤
2. ሀ/ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50 በታች በሚሆንበት ጊዜ፣ ክፍያው ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ ይፈጸማል፡፡
   ለ/ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50 የበለጠ ሲሆን ወይም የሰነዱ ዓይነትና ሁኔታ ለየት ያለ አሠራርን ሲጠይቅ፤ የየኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቴምብር ከመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ሀ/ የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ የሚሠራ ወይም የሚቀበል ሰው በዚህቴምብር ሁለተኛእንዳይሠራ መሠረዝ አለበት፡፡
   ለ/ ቴምብር የተለጠፈበትን ሰነድ የሚቀበሉ ሰዎች ስለቴምብሩ አሰራረዝ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንበሚወስነው መሠረት ይፈጽማሉ፡፡
   ሐ/ በሰነድ ላይ የተለጠፈ ቴምብር የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚወስነው መሠረት ካልተሠረዘ ሰነዱ ቴምብር እንዳልተለጠፈበት

ይቆጠራል። በዚህ ምክንያት የሚመጣው ኃላፊነት የሚወድቀው በባለጉዳዩ ላይ ሳይሆን የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ በሚሠራ ወይም በሚቀበል ሰው ላይ ይሆናል።

8. <u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ስልጣን</u>

የኢትዮጳያ ገቢዎችና ጉምሩክባለሥልጣን፡-

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰነውን ቀረጥ ለመሰብሰብና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም፣
2. ቀረጥ ከፋዮች ስለቀረጡ አወሳሰን የሚረዱ መዛግብትንና ደብተሮችን፣ ወረቀቶችን፣ ማናቸውንም ልዩ ልዩ ሰነዶችንና ውሳኔዎች እንዲያቀርቡ ለማድረግና ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው እራሱ ቀርቦ እንዲያስመረምር ወይም እንዲያሰረዳ ለማዘዝ፤
3. ጉዳዩ የሚመለከተው ቀረጥ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሳይሆን በቀረ ጊዜ ቀረጡን በግምት ለመወሰንና ለመሰብሰብ፣

ሥልጣን ተሰጥቶታል።

9. <u>ይግባኝ የማቅረብ መብት[64]</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በወሰነው የቴምበር ቀረጥ መጠን ላይ የማይስማማ ቀረጥ ከፋይ ባለስልጣኑ ውሳኔውን በጽሁፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ቡድን ወይም ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል፡፡

10. <u>መቀጫን ስለማንሳት[65]</u>

በቀረጥ ከፋይ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጫ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይቻላል፡፡

11. <u>ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>

---

[64] በ15/9(2001) አ.612 አንቀጽ 2 ተሻሻለ፡፡

[65]አንቀጽ 10,11 እና 12 15/9(2001) አ. 612 አንቀጽ 3 መሰረት አዲስ የገቡ ሲሆን ቀድሞ አንቀጽ 10, 11, 12, 13, 14 እና 15 የነበሩት አንቀጽ 13, 14, 15, 16, 17 እና 18 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

1. በማንኛውም የቴምብር ቀረጥ አወሳሰን ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ይግባኝ፣
   ሀ/ ቀረጥ ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የቴምብር ቀረጥ መጠን ሃምሳ በመቶ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ካላስያዘ፤ እና
   ለ/ የቀረጥ ውሳኔ ማስታወቂያው ወይም በአቤቱታ አጣሪ ቡድን የተሰጠው ውሳኔ ለግብር ከፋዩ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ካልቀረበ፤ በግብር ይግባኝ ጉባኤው ተቀባይነት አይኖረውም።
3. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994[66] ስለይግባኝ የተደነገጉትእንደአግባብነታቸው በዚህአዋጅ መሠረት ለሚቀርብ ይግባኝም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

12. <u>የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔን በመቃወም ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>
   1. የይግባኝ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የግብር ይግባኝ ጉባኤው ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ኖልኺባን ላለው ይግባኝ ሰሚ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።
   2. ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሕግ ረገድ የተነሳውን ክርክር መር ምሮ ውሳኔ በመስጠት ጉዳዩን ብር ይግባኝ ጉባኤው ይመልስለታል።
   3. በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀን ውስጥ ለበላይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

13. <u>የቴምብር ቀረጥ አለመከፈል የሚስከትለው ውጤት</u>
   1. ማንኛውም ሰነድ በዚህ አዋጅ መሠረት ትክክለኛ የቴምብር ቀረጥ ካልተከፈለበት በስተቀር በውል ወይም በሕግ ማስረጃ የመቀበል ሥልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም፤ ምልክት አይደረግበትም፤ ወይም ማረጋገጫ አይሰጥበትም፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው በወንጀል ፍርድ ቤት በሚታይ ክርክር በማስረጃነት የሚቀርቡ ሰነዶችን አይመለከትም።

[66] በ22/103(2008) አ.979 ተሻረ፡፡

3. በዚህ አዋጅ መሠረት በመረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ በሁለት እጥፍ ተከፍሎባቸው በመረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በዚህ ሁኔታ የሚከፈለው ቀረጥ ከ10 ብር ማነስ የለበትም፡፡
4. ከዚህ በላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች የተወሰነው ቅጣት ተፈጻሚ መሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሰረት ከመከሰስ አያግድም፡፡

14. <u>ከቀረጥ ነጻ ስለመሆን</u>

1. ሚኒስትሩ በቂ ምክንያት ሲቀርብለት ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊያደረግ ይችላል፡፡
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/1989[67] ተፈጻሚ የሚሆንባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ናቸው።
3. የአስመጪነት የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ለሽያጭ የሚያስመጡት ንብረት በአስመጪዎቹ ስም በሚመዘገብበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥአይከፈልበትም።
4. መንግሥት በጸደቃቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖች መሠረት ሰነዶች ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊደረጉ ይችላሉ።
5. ተመሳሳይ መብት የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ኤምባሲዎችን፣ ቆንስላዎችን፣ እና ደፕሎማቲክ ሚሲዮኖችን ሚኒስትሩ ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡
6. የአክሲዮን ድርሻ የምስክር ወረቀት ሲመዘገብ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልበትም፡፡

15. <u>ቅጣት</u>

1. ማንኛውም ሰው፤
   ሀ/ ማናቸውንም ቀረጥ ሊከፈልበት የሚገባውን ሰነድ ተገቢው ቴምብር ሳይለጠፍበት ያስፈጸመ ወይም ከምስክርነት በስተቀር የፈረመ እንደሆነ፣
   ለ/ ተገቢውን ቀረጥ እንዳይከፍል ለማድረግ በማሰብ የአንድን ሰነድእውነተኛ ሁኔታ የደበቀ እንደሆነ

[67] 15/56(2001) አ.648 ተሻረ፡፡

ጥፋተኝነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 25,000 በማያንስ እና ከብር 35,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ10 ዓመት በማያንስ እና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

2. ማንያውም ሰው፡-

ሀ/ ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ተፈቅዶለት በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን የጣሰ እንደሆነ ፣ ወይም

ለ/ ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ሳይፈቀድለት የሸጠ ወይም ለመሸጥ ያቀረበ እንደሆነ፣

ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 20,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ10 ዓመት በማይበልጥ ጸኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

16. <u>የተሻረና ጸንቶ የሚቆይ ሕግ</u>

1. የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 334/1979 ዓ.ም ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል።
2. የቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር 221/1951 ዓ.ም ድንጋጌዎች ይህን አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ ጸንተው ይቆያሉ።

17. <u>መመሪያ</u>

የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

18. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

ከዚህ ቀጥሎ ሰንጠረዥ አለ

**ደንብ ቁጥር 221/1951ዓ.ም (የሕግ ክፍል ማስታወቂያ)**

**የቴምብር ቀረጥ ለማስከፈል በ1950 ዓ.ም ድንጋጌ መሠረት የወጣ ደንብ**

1. የገንዘብሚኒስትርይህን ደንብ ያወጣው የቴምብር ቀረጥ ስለማስከፈል በ1950 ዓ.ም (የድንጋጌ ቁጥር26/50 ዓ.ም[68]፤ከዚህ በኋላ"ድንጋጌው" ተብሎ በሚጠቀሰው) በ83ኛው አንቀጽ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡
2. ይህ ደንብ "በ1951 ዓ.ም የወጣ የቴምብር ቀረጥ ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

**የገቢ ባለሥልጣኖች**

3. በድንጋጌው በ21ኛው አንቀጽ እንደተመለከተው በድንጋጌው መሠረት የሚከፈለውን ቀረጥ ለመሰብሰብ የሚቀጥሉት የገቢ ባለሥልጣኖች ተሹመዋል፡፡[69]

   ሀ/ በድንጋጌው በአሥረኛው አንቀጽ ለተመለከቱት ጉዳዮች ያገር ውስጥ ገቢመሥሪያ ቤት ዋና ዳይሬክተር ወይም ምክትሉ፤

   ለ/ በአንቀጽ 82 ለተመለከቱት ጉዳዮች፣

   1) የገንዘብ ሚኒስቴር ያገር ውስጥ ገቢ መስሪያ ቤት ዋና ዳሬክተር ወይም ምክትሉ፣
   2) የጠቅላይ ግዛት ያገር ውስጥ ገቢ መስሪያ ቤት ሹም ወይም ምክትሉ
   3) የወረዳና ምክትል ወረዳ ግብር ሰብሳቢዎች

**ስለ ቴምብር ቀረጥ አከፋፈል ሁናቴ**

4. ለህዝብ የሚታዩ ነገሮች በሚደረጉበት ሥፍራ የመግቢያ ፈቃድ ወረቀቶች በስተቀር በማናቸውም ሌላ ሰነድ ላይ የሚከፈል የቴምብር ቀረጥ ዋጋው ከኢ.ት/ብር50 የማይበልጥ ሲሆን፣ ቀረጡ የሚከፈለው የገንዘብ ሚኒስቴር የሚያወጣውን የቀረጥ ቴምብር በሰነዱ ላይ በመለጠፍ ነው፡፡

---

[68] ስራ ያለው አዋጅ 4/36(1990) አ.110 ነው፡፡

[69] በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱት ባለስልጣኖችን በ4/36(1990) አ.110 (በ15/9(2001) አ.612 እንደተሻሻለ) በአዋጅ ቁጥር 1097/ 2011 መሰረት ገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጠ በመሆኑ ተተክቶ ይነበብ፡፡

5. የሚለጠፉት የቀረጥ ቴምብር ዋጋ ዓይነት እንደሚከተለው ነው፡፡ ባለ የኢ.ት/ብር 0.05፣ 0.10፣0.20፣0.25፣0.50፣1.00፣ 2.00፣ 3.00፣ 5.00፣ 10፣00
6. በድንጋጌው አንቀጽ16 መሠረት የቀረጥ ቴምብሩን የሚለጥፈው ሰው በቴምብሩ ላይ በቀጥታ ሆነ በአግዳሚ ስሙን ወይም አጭር ፊርማውን ወይም የኩባያውን ስም ወይም አጭር የመለያ ስሙንና ቀኑን ጭምር ይጽፍበታል፡፡
7. ከአንቀጽ 4 እስከ 6 በተመለከቱት ጉዳዮች ከሚያደርገው አስተያየት በስተቀር ያገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ዋና ዳይሬክተር በኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት መንግስት ግዛት የሚሰሩ ባንኮች እንደ ቼክ በመሳሰለ በአንዳንድ ሰነድ ላይ የሚከፈሉት የቴምብር ቀረጦች አከፋፈሉ በተለየ ሁኔታ እንዲፈጸም ለማድረግ ይቻላል፡፡
8. በአንዳንድ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ዋጋ በኢ.ት/ብር 50 በላይ ሲሆን የቀረጡ ገንዘብ ለገቢ ባለሥልጣን ወይም ይህን የመሳሰለውን ገንዘብ ለመሰብሰብ ከአገር ውስጥ ገቢ መስሪያ ቤት ባለሥልጣን ለተወከለው ስለ መከፈሉም ለማረጋገጥ ሥልጣን ለተሰጠው ሰው ይከፈላል፡፡
9. በአንቀጽ 8 የተመለከተውን ቀረጥ በመሰብሰብ የገቢ ባስልጣን ወይም እርሱ የወከለው ሰው ለተከፈለው ገንዘብ በደንበኛው ሰነድ ወይም በግልባጩ ወይም በግልባጮቹ ላይ የገንዘቡን ልክ የተከፈለበት ቀን፤ የደረሰኝ ቁጥር፤እንዚህን የመሳሰሉትን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ ቀረጡ ለመከፈሉ ራሱ ፈርሞ የገቢ ባለስልጣን ወይም ስለ እርሱ ሆኖ የሚሠራውን መሥሪያ ቤት ማህተም አትሞ ደረሰኙን ይሰጣል፡፡ በገቢ ባለሥልጣን ተወክለው የሚሰሩ ሰዎች በደረሰኙና በሰነዱም ላይ ከፊርማቸው በታች የሚቀጥለውን መግለጫ ይጽፋሉ፡፡

   “የቴምብር ቀረጥ ለመሰብሰብ በ......የተፈቀደ፤.........ቀን......ዓ.ም ቁጥር......”
10. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 8 ላይ ለተመለከቱት ጉዳዮች በገቢ ባለሥልጣን የቴምብር ቀረጥ ለመሰብሰብ ፈቃድ የተቀበሉ ሰዎች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን መፈጸም አለባቸው፡፡

    ሀ/ በገቢ ባለሥልጣን በተዘጋጀው ፎርም ላይ በየቀኑ የተሰበሰበውን ገንዘብ ልክ የሚያሳይ ዝርዝር መዝገብ መያዝና፤

    ለ/ በየሳምንቱ መጨረሻ በሶስት ቀን ውስጥ ላይ በተመለከተው ሁናቴ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለገቢ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ገቢ ማድረግ አለባቸው፣

11.ለህዝብ የሚታዩ ነገሮች ለሚደረጉበት ስፍራዎች የመግቢያ ፍቃድ ወረቀቶች ሲሆኑ፣ የቀረጡ ገንዘብ ለገቢ ባለሥልጣን ከተከፈለ በኋላ እርሱም ለተቀበለው ገንዘብ ደንበኛ ደረሰኝ ይሰጥና በተከፈለው ገንዘብ መጠን እቲኬቶቹ ላይ የመሥሪያ ቤቱን ማህተም ያትማል፡፡

**በድንጋጌው ቁጥር 64 በተመለከተው ኮሚሲዮን፡፡**[70]

12. በድንጋጌው አንቀጽ 64 በመለከተው መሠረት ኮሚሲዮኑ ቀጥሎ የተረዘሩት አባሎች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ በሥፍራው የሚገኙ ያገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ወይም ምክትሉ የኮሚሲዮኑ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

ለ/ በሥፍራው የሚገኘው ያገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በሚጠራበት ጊዜ ሁለት አባሎች ይላካሉ፣ እነዚሁም 1ኛው በስፍራው ማ/ቤት ወይም ከከተማው ጽ/ቤት 2ኛው በሥራ ሚኒስቴር ወይም በቀበሌው በሚገኘው ቅርጫፍ መ/ቤት የሚወከሉናቸው፣ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ የገንዘብ ሚኒስትር አንድ ወይምሁለትተጨማሪ አባሎች ሊሾም ይችላል፡፡

**የቀረጥ ቴምብር ማውጣትና መሸጥ**

13.ለቴምብር ቀረጥ የሚለጠፈውን ቴምብር የገቢ ባሥልጣኖች ያወጣሉ፡፡

14.ዋጋቸው የኢ.ት/ብር 0.20 የማይበልጥ የሚለጠፉ የቀረጥ ቴምብሮችን ከሚሸጡ ሰዎች በስተቀር ዋጋቸው ከዚያ በላይ የሆኑትን የቀረጥ ቴምብሮች ለህዝብ ለመሸጥ ማናቸውም ሰው ባገር ውስጥ ላለው የገቢ ባለስልጣን የመሸጫውን ፈቃድ ለመቀበል ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡ጥያቄውም የገቢ ባለስልጣን ባወጣው ፎርም ተሞልቶ መቅረብ አለበት፡፡

15.ዋጋው ከኢ.ት/ብር 0.20 የማይበልጥ የቀረጥ ቴምብር ለመሸጥ ፈቃድ መጠየቅ አያስፈልግም፡፡ ይሁን እንጂ የገቢ ባሥልጣን ሳይፈቅድለት ይህንን የመሳሰሉት ቴምብሮች የሚሸጥ ማናቸውም ሰው ከገቢ ባለሥልጣን ለሥራው የሚከፈለው አበል ወይም ደመወዝ የለም፡፡

16. የቀረጥ ቴምብር ለመሸጥ የተፈቀደላቸው ሰዎች ቀጥሎ የተመለከቱትን ግዴታዎች መፈጸም አለባቸው፡፡

---

[70] በ4/36(1990) አ.110 (በ15/9(2001) አ.612 እንደተሻሻለ) ጉምሩክ ኮሚሽን ስልጣን በመስጠት በግልፅ ሳይነገር ተሻረ፡፡

ሀ/በሱቃቸው መስኮት ወይንም በሌላ በግልጽ ሊታይ በሚችልበት ቦታ "የቀረጥ ቴምብር ሻጭ" የሚል ማስታወቂያ በዝርዝር መግጫው ጋር መለጠፍ፣

ለ/ የሚሸጡትን የቀረጥ ቴምብር የሚገዙት ባገር ውስጥ የገቢ ባሥልጣን ብቻ እንዲሆን፣

ሐ/ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 5 የተዘረዘሩት የቀረጥ ቴምብሮች ሁሉ በየዓይታቸው በእስቶክ እንዲገኙ ወይንም እጅግ ቢያንስ የገቢ ባሥልጣን በወሰነው መጠን በየዓይቱ እንዲገኝ ማድረግ ፣

17. በአንቀጽ16 የተመለከቱት ሰዎች ለሥራው ድካም ዋጋ እንዲሆን ከገቢ ባለስልጣን ለሚገዙት የቀረጥ ቴምብር በመቶ አምስት(5%)ቅናሽ ሊያገኙ መብት አላቸው፡፡

18.የገንዘብ ሚኒስቴር ያገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ዋና ዲሬክተርና በየጠቅላይ ግዛቶቹ፤ ባውራጃዎቹ ያገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣኖች ከማናቸውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይንም ከማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣኖች ጋር በመስማማት ቀጥሎ በተመለከተው ግዴታ መሠረት በየመሥሪያ ቤቶቹ ባሉ ገንዘብ ያዢዎች ዘንድ የቀረጥ ቴምብር እንዲያገኝና የተለየም ሂሳብ እንዲያዝ ማድረግ ይችላሉ፡፡

ሀ/ ስለ ቴምብር ቀረጥ የሚቀርብ ጥያቄ ማመልከቻ የገቢ ባሥልጣን በሚያወጣው ፎርም ላይ መሞላት አለበት፡፡

ለ/ የቀረጥ ቴምብር የሚይዝ ሰው የተቀበለውንና የሸጠውን የቀረጥ ቴምብር ሂሳብ ከገቢ ባሥልጣን በሚሰጠው መዝገብ ላይ መያዝ አለበት፡፡

ሐ/የተቀማጬን ቀረጥ ቴምብር እንደ አስፈላጊነቱ ከተፈቀደው ገንዘብ ልክ ሳይልፍበየጊዜው ለመግዛት ይቻላል፡፡ ነገር ግን በዚህ አኳኋን የሚቀመጠው የቀረጥቴምብር ዋጋው ከኢ.ት/ብር100 መብለጥ የለበትም፡፡

መ/የቀረጡን ቴምብር የገቢ ባለሥልጣን በጽሁፍ የሚፈቀድለት ማናቸውም ሹም በማናቸውም ጊዜ ሊመረምር ይችላል፡፡ እንዲሁም ደግሞ የገቢ ባሥልጣን በማቸውም ጊዜ ሊመረምር ይችላል ፡፡ እንዲሁም ደግሞ የገቢ ባለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ የጠቀረጥ ቴምብር የሚገኝባቸውን መሥሪያ ቤቶች ለማስቀረት ይችላል፡፡ በዚህ አኳኋን የቀረጥ ቴምብር ማስቀመጥ የሚቀርበት መሥሪያ ቤት ወዲያውኑ የቴምብሩን ጠቅላላ ዋጋ በገንዘብ ወይንም በቴምብር ወይንም በሁለት ዓይነት እንዲከፍ ይጠየቃል፡፡

ሠ/ የቀረጥ ቴምብር የሚይዙ ሰዎች ከአገሩ የገቢ ባለሥልጣን ከተቀበሉት ቴምብር

በስተቀር ከሌላ ዘንድ ተቀብለው መሸጥ አይችሉም፡፡

19. ይህ ደንብ ከመስከረም 1 ቀን 1952 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 24 ቀን 1951 ዓ.ም**

**ባላምባራስ ማህተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልየገንዘብ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 285/1994 ዓ.ም

## የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ

አሁን በሥራ ላይ ያለው የሽያጭ ታክስ የሽያጭ እንቅስቃሴ በተከናወነ ቁጥር በሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት ላይ ታክስ መሰብሰብ ስለማያስችል፤

የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ታክስን ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል እንዲሁም ግብር ከፋይ ያገኘውን ትርፍ ለማረጋገጥ ስለሚረዳ፤

በካፒታል ዕቃዎች ላይ የማይጣል የፍጆታ ታክስ በመሆኑ ቁጠባንና ኢንቬስትመንትን ስለሚያበረታታ፤

የሽያጭ ታክስ በተጨማሪ እሴት ታክስ መተካት ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚያግዝና የመንግሥት ገቢ ከጠቅላላ ምርት ጋር ያለውን የመጠን ግንኙነት የሚያሳድግ ስለሆነ፤በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55(1) እና (11) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**[71]

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. “የሂሳብጊዜ” ማለት:-[72]

      ሀ) በማናቸውምየ12ወራትጊዜውስጥ ያከናወነውጠቅላላሽያጭብር 70 ሚሊዮን (ብርሰባሚሊዮን) እናከዚህ በላይለሆነታክስከፋይእያንዳንዱወር፤

[71]የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (25) እና (26) በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(2) መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡፡

[72]ይህ ንዑስ አንቀጽ በ25/81 (2011) አ.1157 አንቀጽ 2(1) ተሻሻለ

ለ) በማናቸውምየ12ወራትጊዜውስጥያከናወነውጠቅላላሽያጭከብር70 ሚሊዮን (ከብርሰባሚሊዮን) በታችየሆነ ታክስከፋይ3 ወርሲሆን፣የነሐሴናየጳጉሜ ወራትእንደ አንድወርይቆጠራሉ፡፡

2. “ወኪል” ማለት በሌላ ሰው ስም እና ትዕዛዝ የሚሠራ ማናቸውም ሰው ነው፤
3. “የሰዎች ኅብረት” ማለት ግለሰቦች አባል የሆኑበት ማኅበር ወይም ግለሰብ ያልሆኑ አንድ ወይም ከአንድ በላይ አባላትን የሚጨምር ማኅበር ሲሆን፤ ለ“ድርጅት” በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ማኅበራትን አይጨምርም፤
4. “ባለስልጣን”ማለትየገቢዎችሚኒስቴር ነው፡፡፣[73]
5. “ድርጅት” ማለት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ማናቸውም ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር፣ ወይም ከኩባንያ ወይም ከተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ጋር ተመሳሳይ የሆነና በውጭ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመድርጅት፣ ወይም ማናቸውም የመንግሥት የልማት ሥራድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት ሲሆን፣ በውጭ ሀገር ያለን አካል በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያካሂደውን ወኪል እና ፀንቶ በሚሠራበት በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ሕግ የተመሠረተ ወይም ዕውቅና ያገኘ ቢሆንም ባይሆንም እንደ ድርጅት የሚንቀሳቀስን ይጨምራል፤
6. “ዕቃዎችን ወደውጭ መላክ” ማለት ዕቃዎችን ከኢትዮጵያ ውጪ መውሰድ ነው፤
7. “ዕቃ” ማለት ግዙፋዊ ህልዎት ያለው ማናቸውም ዓይነት ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት፤ የእንፋሎት ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ጋዝ እና ውሃ ሲሆን ገንዘብን አይጨምርም፤
8. “ገንዘብ” ማለት፤
   1) በኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ መገበያያ የሆነ ሣንቲም ወይም ወረቀት፣
   2) የሀዋላ ወረቀት፣ የባንክ ድራፍት፣ የቃል ኪዳን ሰነድ፣ የፖስታ ቤት ሀዋላ፣ ወይም የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ፣ ወይም
   3) የገንዘብ ዋጋ ያለው እና በሕግ መሠረት መንግሥት ለሚሰበስባቸው ክፍያዎች የሚያገለግል ለሽያጭ የሚውል ቴምብር፣ ቅጽ፣ ወይም ካርድ፤ ነው፤

[73]ይህ ንዑስ አንቀጽ በ25/81 (2011) አ.1157 አንቀጽ 2(2) ተሻሻለ

9. “ዕቃዎችን ወደአገር ማስገባት” ማለት የጉምሩክ ሕግን በመከተል ዕቃዎችን ወደ ኢትዮጵያ ማምጣት ነው፤
10. “በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት” ማለት የማናቸውም ሰው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል የሚከናወንበት ቋሚ የሥራ ቦታ ሲሆን፣ በተለይም የአስተዳደር ጽ/ቤት፣ ቅርንጫፍ ፣ፋብሪካ፣ ወርክሾፕ ፣ የማዕድን ማምረቻ ወይም ማናቸውም የተፈጥሮ ሀብት ልማት ማካሄጃ ቦታ፣ የሕንፃ ወይም የግንባታ እና/ ወይም የመገጣጠም ሥራ የሚከናወንበት ቦታ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ተደርጎ ይቆጠራል፤
11. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው፣ የግል ባለሀብት፣ ድርጅት፣ የጋራ ልማት ማኅበር ወይም የሰዎች ኅብረት ሲሆን፣ ሌላን ሰው በመወከል ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የንግድ ሥራ የሚያካሂድ የንግድ ወኪልን ይጨምራል፤
12. “ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን” ማለት ፈቃድ፣ የምስክር ወረቀት፣ ኮንሴሽን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ፈቃዶችን ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤
13. “ግንኙነት ያላቸው ሰዎች” ማለት
    1) የተፈጥሮ ሰው እና
       ሀ/ የዚህ የተፈጥሮ ሰው ማናቸውም ዘመድ ወይም
       ለ/ ዘመዱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ወይም ሊሆንበት የሚችል የባለአደራ ተቋም ወይም
    2) ባለአደራ ተቋም እና የዚሁ ባለአደራ ተቋም ተጠቃሚ የሆነ ወይም ሊሆን የሚችል ሰው፣
    3) የሽርክና ማኅበር፣ የጋራ ልማት ማኅበር፣ በሕግ የሰውነት መብት ያላገኘ ድርጅት ወይም የግል የኩባንያ እና
       ሀ/ የእነዚህ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው፤
       ለ/ እንደሁኔታው የሽርክና ማኅበር፤ የጋራ ልማት ማኅበር ወይም በሕግ የሰውነት መብት ያላገኘ ድርጅት ወይም የግል ኩባንያ አባል የሆነና ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በሚል በተተረጎመው የሚሸፈን ሌላ ሰው፣
    4) ዝግ ከሆነ ኮርፖሬሽን በስተቀር በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት እና፣

ሀ/ በሕግ የሰውነት መብት ከተሰጠው ድርጅት በስተቀር ማናቸውም ሰው ወይም ይህ ሰው እና በዚህ ትርጉም መሠረት ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች፣

1) በአንድ ኩባንያ ውስጥ ያለውን ድምጽ የመስጠት መብት፣
2) የአንድን ኩባንያ ካፒታል ወይም ትርፍ የመከፋፈል መብት በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች መካከል ባለ አገናኝ ኩባንያ፣ የሽርከና ማኅበር ወይም ባለአደራ ተቋም አማካኝነት፣10 ፐርሰንት (አሥር በመቶ) እና ከዚያ በላይ የያዙ በሚሆንበት ጊዜ፣

ለ/ በተራ ፊደል (ሀ) በመጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ወይም ይህ ሰው እና በዚህ ትርጉም መሠረት ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያለው ሰው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ኩባንያ ውስጥ፣

1) በኩባንያው ውስጥ ያለውን ድምጽ የመስጠት መብት፣
2) በመጀመሪያ የተጠቀሰውን ኩባንያ ካፒታል ወይም ትርፍ የመከፋፈል መብት፣

በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች መካከል ባለ አገናኝ ኩባንያ፣ የሽርከና ማኅበር ወይም ባለአደራ ተቋም አማካኝነት10 ፐርሰንት (አስር በመቶ) እና ከዚያ በላይ የያዘ በሚሆንበት ጊዜ፣

ሐ/ ማናቸውም ሰው፣ ይህ ሰው እና በተራ ፊደል (ሀ) የተመለከተው ሰው ወይም በተራ ፊደል (ለ) የተመለከተው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ትርጉም መሠረት ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ሆነውየተቆጠሩ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወይም

መ/ ማናቸውም ሰው፣ በዚህ ትርጉም መሠረት በተራ ፊደል (ሐ) ከተመለከተው ሰውጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ የተቆጠረ በሚሆንበት ጊዜ፣

5) የተመዘገበ ሰው እና በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ(5) መሠረት ተለይቶ የተመዘገበ የዚሁ ሰው ቅርንጫፍ ወይም የሥራ ክፍል፤

6) ማናቸውም በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ተለይቶ የተመዘገበ ሰውቅርንጫፍ ወይም የሥራ ክፍል፤

14.“ዝምድና” ማለት፤

1) ግለሰብ እና የትዳር ጓደኛ፤

2) በቀጥታ ወደላይ ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ዘመዶች፣ ወንድም፣ እህት፣ አጎት፣ አክስት፣ የአክስት ወይም የአጎት ልጅ፣ የእንጀራ አባት፣ የእንጀራ እናት፣ የእንጀራ ልጅ ወይም የግለሰቡ ወይም የትዳር ጓደኛው የጉዲፈቻ ልጅ፤ እና የጉዲፈቻ ልጅን በተመለከተ የጉዲፈቻ አሳዳጊዎች፣ ወይም

3) በንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ማናቸውም ሰው የትዳር ጓደኛ እና ለዚህ ትርጉም አፈፃፀም ማናቸውም የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አሳዳጊው ጋር የመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና እንዳለው ይቆጠራል፡፡

15.“ነዋሪ” በገቢ ግብር አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

16.“አገልግሎት” የዕቃን ዝውውር የማይጨምር በክፍያ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው፤

17.“አቅርቦት” ማለት ዕቃን ለሽያጭ የማቅረብ ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባር ነው፡

18.“የዕቃ አቅርቦት” ከዚህ በታች በአንቀጽ 4 የተሰጠውትርጉም ይኖረዋል

19.“አገልግለሎት መስጠት” ከዚህ በታች በአንቀጽ 4 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል

20.“ታክስ” ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡

21.“ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ” ከዚህ በታች በአንቀጽ 6 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

22.“ታክስ የሚከፈልበት ግብይት” ከዚህ በታች በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (3) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

23.“የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ” ማለት ይህንን አዋጅ የሚያስፈጽም፡

1) የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም

2) የባለሥልጣኑ ወይም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ሠራተኞች፡ ወይም

3) በዚህ አዋጅ መሠረት ባለሥልጣኑን በመወከል የሚሠራ ማናቸውም የፖሊስ መኮንን ወይም የፖሊስ ኃይል አባል፤ ወይም

4) በዚህ አዋጅ መሠረት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለ ሥልጣንን በመወከል የሚሠራ ማናቸውም የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ነው፤

24.“የታክስ ደረሰኝ” ከዚህ በታች በአንቀጽ 22 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

25.“የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ” ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ነው፣

26.“አቅራቢ” ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ወይም በመሣሪያው ላይ ተጭኖ አገልግሎት የሚሰጥ ሶፍትዌርን ወይም ሁለቱንም በአንድ ላይ የሚያቀርብ ሰው ነው።

27.“የካፒታልዕቃ” ማለትለሽያጭየሚውሉ ምርቶችንለማምረትወይምአገልግሎቶችን ለመስጠትበቀጥታወይምበተዘዋዋሪመንገድ ጥቅምላይየሚውልከአንድዓመትበላይ አገልግሎትሊሰጥየሚችልንብረትሲሆን፣ ህንፃን፣ተሽከርካሪን፣መሣሪያንእናእነዚህን የመሳሰሉግዙፋዊህልዎትያላቸውንሌሎች ንብረቶችይጨምራል፡፡”[74]

3. <u>ታክስ ከፋዮች</u>

1. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች ታክስ ከፋዮች ናቸው፡፡

ሀ/ የተመዘገበ ሰው በመባል የሚጠቀስ ማናቸውም የተመዘገበ ወይም መመዝገብ ያለበት ሰው፡

ለ/ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባ ሰው እነዚህን ዕቃዎች ወደአገር ማስገባትን በተመለከተ፡

ሐ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይመዘገብ የአገልግሎት መስጠት ሥራ የሚያከናውን በአንቀጽ 23 መሠረት ታክሱ የሚመለከተው ሰው፣ እነዚህን አገልግሎቶች በሚመለከት፤

2. የተመዘገበ ሰው ምዝገባው ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ ታክስ ከፋይ ነው።

3. መመዝገብ ያለበት ሆኖ ያልተመዘገበ ሰው ለምዝገባ ማመልከቻ የማቅረብ ግዴታ ከሚጀምርበት ቀጥሎ ያለው የሂሣብ ጊዜ ከሚጀምርበት አንስቶ ታክስ ከፋይ ነው።

4. <u>የዕቃ አቅርቦት እና አገልግሎት መስጠት</u>

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤

ሀ/ “የዕቃ አቅርቦት” ማለት

---

[74]ይህ ንዑስ አንቀጽ በ25/81 (2011) አ.1157 አንቀጽ 2(3) ተሻሻለ

1) የዕቃ ሽያጭ ወይም
2) በኪራይ፤ በዱቤ፣ በጭነት ውል፤ በቻርተር ስምምነት ወይም በማናቸውም በዕቃ የመጠቀም ወይም የመጠቀም መብት በተሰጠበት ሌላ ውል ዕቃውን ለመጠቀም ከሚያስችል ከሾፌር፤ ከፓይለት፣ አጋዥ ከሆኑ ሠራተኞች፣ አንቀሳቃሾች ጋር የተሰጠ ቢሆንም ባይሆንም በዕቃ መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት መፍቀድ፡
3) የእንፋሎት ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የጋዝ ወይም የውሃ አቅርቦት፣ እና

ለ/ "አገልግሎት ማቅረብ" ማለት የዕቃ ወይም የገንዘብ ያልሆነ ማናቸውም አቅርቦት ሲሆን፤

1) ማናቸውንም መብት መስጠት፣ ማስተላለፍ፡ማቋረጥ ወይም መልቀቅ፡
2) አንድን ተግባር ለመፈፀም የሚያስችሉ ነገሮችን ማመቻቸት፡፡

2. የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የገዛ እና ተገቢውን የታክስ ተቀናሽ ያገኘ ወይም የማግኘት መብት ያለው የተመዘገበ ሰው የገዛቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ያልዋሉ ቢሆንም ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን የዋሉ እንደሆነ ተደርገው ይቆጠራሉ።
3. አሠሪው ለሠራተኞቹ በስጦታ ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን የዋሉ እንደሆነ ተደርገው ይቆጠራሉ።
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሲሠረዝ በንዑስ አንቀጽ 8 እንደተደነገገው የካፒታል ዕቃዎችን ጨምሮ ሥረዛው በተከናወነበት ጊዜ በተመዘገበው ሰው እጅ የሚገኙ ዕቃዎች ፤ የተመዘገበው ሰው በአንቀጽ 21 መሠረት የታክስ ማቀናነሻ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የመጠየቅ መብት ያለው እንደሆነ፣ በዚያን ጊዜ በተከናወኑ ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች በወጪ ዋጋ የተሸጡ ተደርገው ይቆጠራሉ።
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚከፈልበት ግብይት የተገኘን እቃን የሚያቀርብ ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 21 መሠረት ለአቀረበው ዕቃ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግ

ያልተፈቀደ በሚሆንበት ጊዜ ግብይቱ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ተደርጎ አይቆጠርም። ዕቃዎቹን ለማግኘት የተከፈለው ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግ የተፈቀደው በከፊል በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ተቀናሽ እንዲሆን ባልተፈቀደው መጠን ያነሰ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

6. በችርቻሮ ደረጃ ከሚካሄደው ሽያጭ በስተቀር የሚመለስ የዕቃ መጠቅለያ ዋጋ፣ ታክስ ከሚጣልበት ሂሣብ ውስጥ አይካተትም። ስለሆነም በችርቻሮ ንግድ ሥራ የተሠማሩለሚመለስ መጠቅለያ ተከፍሏል ተብሎ በተያዘውና እንደሚመለስ በሚጠበቀው ሂሣብ መጠን ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት መጠን ዝቅ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡
7. በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው የሚከናወኑ የዕቃ አቅርቦት እና አገልግሎት የመስጠት ሥራዎች ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚደረግባቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ በሆነ ድርጅት ወይም በኢንተርኔት የተከናወኑ ሲሆን ብቻ ነው።
8. ለንዑስ አንቀጽ (4) አፈፃፀም ምዝገባው በተሠረዘበት ጊዜ እንደተሸጠ ተደርጎ የሚወሰድ የካፒታል ዕቃ ዋጋ የሚደረስበት የእንደዚህ ያለውን ንብረት ዋጋ እያንዳንዱን ሀብት በተናጠል በማስላት ሲሆን፤ የንብረቱን ቀሪ የአገልግሎት ዘመን የላይኛው ተካፋይ ቁጥር፡ የንብረቱን ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመን የታችኛው አካፋይ በማድረግ የዕቃውን ወጪ በዚህ ክፍልፋይ በማባዛት ከሚገኘው ሂሳብ ጋር ዕኩል ይሆናል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም የንብረት የአገልግሎት ዘመን በገቢዎች ሚኒስትር በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡
9. ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ድርጅት ወይም ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አንድ ክፍል ሆኖ ተለይቶ በራሱ የሚንቀሳቀስ ክፍል የተሸጠ እንደሆነ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት እንደተሸጠ ዕቃ ይቆጠራል፡፡ የተላለፈውን ንብረት በሚመለከት ንብረቱ የተላለፈለት ሰው የአስተላላፊው መብትና ግዴታ ይኖረዋል።
10. ለንዑስ አንቀጽ (9) አፈፃፀም ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ክፍል ሆኖ ተለይቶ በራሱ የሚንቀሳቀስ ክፍል በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ድርጅት እንደተሸጠ የሚቆጠረው

ሀ/ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ ክፍል በቀጣይነት እንዲሠራ ለማድረግ የሚያስፈልገው ማናቸውም ዕቃ እና አገልግሎት ለተላለፈለት ሰው የተሰጠ ከሆነ፡

ለ/ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ ክፍል አስተላላፊው ለተላለፈለት ሰው እስካስረከበበት ቀን ድረስ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን ማካሄድ የቀጠለ ወይም በማካሄድ ላይ የነበረ ከሆነ ነው፤

11.በንዑስ አንቀጽ (12)የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤

ሀ/ የተመዘገበ ሰው የሚያስተላልፈው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ክፍል ሆኖ ተለይቶ በራሱ የሚንቀሳቀስን ክፍል ጨምሮ ማናቸውም ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በንዑስ አንቀጽ (9) መሠረት የዕቃ አቅርቦት ሆኖይወሰዳል፡፡

ለ/ አቅርቦቱ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ይሆናል፡፡

ሐ/ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚውሉት ዕቃዎችና አገልግሎቶች የተገኙት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ሂደት ለፍጆታ ለጥቅም ወይም ለአቅርቦት እንዲውሉ ለማድረግ ካልሆነ፤

በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የሚገኘው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ተቀባዩ ያከናወነው የአቅርቦት ሥራነው የሚባለው ለንግድ ሥራው እንቅስቃሴየሚውሉት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ታክስ የሚከፈልባቸውን አቅርቦቶች ሠርቶ በማውጣት ሂደት ለፍጆታ፡ ለጥቅም፡ ወይም ለአቅርቦት የማይውሉ ከሆነ ብቻ ነው።

12.በንዑስ አንቀጽ (11) (ሐ) የተጠቀሰው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ክፍል ከንግድ ሥራው እንቅስቃሴ 10 ፐርሰንት (አሥር በመቶ) በታች ከሆነ የንዑስ አንቀጽ (11) ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም።

13.ሌሎች እንደ ዕቃና አገልግሎት አቅርቦት የሚታዩ እንቅስቃሴዎች ወይም የዕቃና የአገልግሎት አቅርቦትተደርገው የማይቆጠሩ የሚመሩበት ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 5. <u>ቅይጥ አቅርቦቶች</u>

1. የዋና ዕቃ አቅርቦት ወይም አገልግሎት የመስጠት ንግድ ሥራ ተጓዳኝ የሆኑ የዕቃ እና የአገልግሎት አቅርቦቶች የዋናው ዕቃ አቅርቦትና አገልግሎት የመስጠት ሥራ አንድ ክፍል ሆነው ይቆጠራሉ፡፡
2. ዕቃን ወደ አገር ከማስገባት ሥራ ጋር ተጓዳኝ ሆነውየተሰጡ አገልግሎቶች ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች አካል ይሆናሉ፡፡
3. አንድ ግብይት አንድ ወይም ከአንድ የበለጡ ከታክስ ነፃ የሆኑ የተለያዩ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን አቅርቦት የሚጨምር በሚሆንበት ጊዜ የተለያዩ ግበአቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ ከታክስ ነጻ የሆነ አንድ ግብይት ታክስ የሚከፈልባቸው የተለያዩ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የማቅረብ ሥራዎችን የካተተ ሲሆን ተለያዩ ግብይቶች ተደረገው ይቆጠረሉ፡፡

6. <u>ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራእንቅስቃሴ</u>[75]

"ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ" ማለት ለትርፍ የተከናወነ ቢሆንም ባይሆንም ጥቅም ለማግኘት ሲባል ለሌላ ሰው ወይም በከፊል ዕቃ የመሸጥ ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባርን ለማከናወን በማሰብ ወይም በትክክል በማከናወን በማንኛውም የተመዘገበ ሰው፡-

1. በኢትዮጵያ ውሰጥ፣
2. በከፊል በኢትዮጵያ ውስጥ በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚያከናውነው የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡

<u>**ክፍል ሁለት**</u>

<u>**ታክስ ስለመጣል እና ከታክሱ ነፃ**</u>

<u>**ስለሆኑ ግብይቶች**</u>

7. <u>ታክስ ስለመጣል</u>

1. በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቁ ሆነው፡
   ሀ/ በተመዘገቡ ሰዎች በሚከናወን ታክስ በሚክፈልበት ግብይት
   ለ/ ነፃ ክተደረጉት በስተቀር ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ፣

[75] በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(3) ተሻሻለ፡፡

ሐ/ በአንቀጽ 23 መሠረት ወደ አገር በሚገቡ አገልግሎቶች ዋጋ ላይ በ15 ፐርሰንት የማስከፈያ ልክ የተጨማሪ እሴት ታክስ በመባል የሚታወቅ ታክስ ይከፈላል፡፡

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ታክስ የማይከፈልባቸው ግብይቶች ዜሮ በመቶ የማስከፈያ ልክ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡

   ሀ/ ወደ ውጪ የሚላኩ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ፡በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በሚወሰነው መሠረት ፡

   ለ/ ዓለም አቀፍ የዕቃዎች ወይም የሰዎች ማጓጓዝ ተግባር ወይም ከዚሁ ጋር በቀጥታ የተገናኙ አገልግሎቶች፡ እንዲሁም በዓለም አቀፍ በረራ ወቅት ለፍጆታ የሚውሉ የቅባት ዘይቶች እና ሌሎች አላቂ የቴክኒክ ዕቃዎች፡

   ሐ/ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ፡

   መ/ በአስተላላፊውእና በተላለፈለት ሰው በጽሑፍ ተዘጋጅቶ የተፈረመ ማስታወቂያ አቅርቦቱ በተፈጸመ በ21 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ የደረሰው እና ይህም ማስታወቂያ ስለአቅርቦቱ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ ከሆነ አንድ የተመዘገበ ሰው ለሌላ የተመዘገበ ሰው በነጠላ ግብይት የአንድን ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም ራሱን ችሎ የሚሠራ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ክፍል አብዛኛው ሀብት ላልተወሰነ ጊዜ ይንቀሳቀሳል ተብሎ የተቋቋመ ድርጅት ሆኖ ሲተላለፍ፡

3. በአንቀጽ8 ነፃ ከተደረጉት አቅርቦቶች በስተቀር ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀርብ ዕቃ ወይም አገልግሎት ታክስ የሚካፈልበት ግብይት ነው።

4. በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀፆች በተለየ ሁኔታ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር በንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው ታክስ የሚከፈለው ፡

   ሀ/ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) ተፈፃሚ የሚሆንበትን አቅርቦት በሚመለከት አቅርቦቱን በሚሰጠው የተመዘገበ ሰው፤

   ለ/ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎችን በሚመለከት በአስመጪው

   ሐ/ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) ተፈፃሚ የሚሆንበቸውን ወደ አገር የሚገቡ አገልግሎቶችን በሚመለከት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በሆነ ሰው

ነው ፡፡

5. የዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ1 (ሀ) ተፈፃሚየሚሆንበትግብይትሲከናወን:-

ሀ)

የገንዘብሚኒስቴርበሚያወጣውመመሪያበሚወሰነውመሠረትታክሱግዥውንበሚፈጽ መውአካልተይዞለባለሥልጣኑይከፈላል፡፡

ለ)

በዚህአንቀጽመሠረትበገዥውተይዞየሚከፈለውየተጨማሪእሴትታክስተከፋይየሆነው ታክስ50ፐርሰንትሲሆንቀሪውለሻጩይከፈላል፡፡[76]

8. <u>ከታክስ ነፃ የሆኑ ግብይቶች</u>

1. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም

ሀ/ “በንግድ መልክ ለማረፊያነት የሚከራዩ ክፍሎች” ማለት

1) በሆቴል ፤ በሞቴል ፤ በገጠር ማረፊያ ፤ በማደሪያ ቤት፣ በሆስቴል ወይም በተመሳሳይ ተቋምለአምስት እና ከአምስት በላይ ለሆኑ ሰዎች በየቀኑ፤ በየሣምንቱ፣ በየወሩ፤ ወይም በሌላ የተወሰነ ጊዜ ክፍያ በመጠየቅ የሚሰጥ የማረፊያ አገልግሎት፤

2) በንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) በተመለከተውትርጉም የማይሸፈን ለእያንዳንዱ ተከራይ በተከታታይ ከ45 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ የሚከራይ ማናቸውም ቤት ፣ በፎቅ ውስጥ ያለ መኖሪያ አፓርትመንት፣ ወይም ክፍል ሲሆን ፤ ዓመታዊ የኪራይ ገቢው ከብር 24,000 የሚበልጥ ወይምይበልጣል ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለ፡

3) የንግድ ሥራ ድርጅት የተከራየውን ንብረት ወይም ተለይቶ የሚታወቅ የአንድ የንግድ ሥራ ድርጅት ንብረት ጨምሮ፤ ለመኖሪያ የሚያገለግል ማናቸውም ቤት፣ በፎቅ ውስጥ ያለ መኖሪያ፣ አፓርትመንት፣ ክፍል፣ ተንቀሳቃሽ ቤት፣ የጀልባ ቤት፤ ድንኳን፤ የመስክ ሥፍራ የሚያስተዳድር ሰው፤

   1. የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን በማከናወን ሂደት አምስት እና ከአምስት በላይ የሆኑ ቤቶችን ፣ በፎቅ ውስጥ ያሉ ክፍሎችን ፣ አፓርትመንቶችን ፣ ክፍሎችን፣ ተንቀሳቃሽ ቤቶችን ፤ የጀልባ ቤቶችን ፣ ወይም ተንቀሳቃሽ ለመዝናኛ የተዘጋጁ ሥፍራዎችን የሚያከራይ ወይም ለኪራይ የያዘ ፤

---

[76] ይህ ንዑስ አንቀጽ በ25/81 (2011) አ.1157 አንቀጽ 2(2) ተሻሻለ

2. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ለመዝናኛ በማከራየት የሚያገኘው ዓመታዊ የኪራይ ገቢ ከብር 24,000 በላይ ከሆነ ወይም ይህ ዓመታዊ ገቢ ከተጠቀሰው ገንዘብ መጠን ይበልጣል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ካለ ፤
3. በመደበኛ ሁኔታ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የሚያከራይ ወይም ለማከራየት የያዘ ከሆነ፣ ወይም
4. ሌላ ማናቸውም ለመኖሪያ የሚውል እና የገቢዎች ሚኒስትር በንግድ መልክ ለማረፊያነት የተቋቋመ ነው በሚል የሚመድበው ድርጅት ነው ፡፡ ሆኖም በአንቀጽ በአንቀጽ (4) የተገለጸው ከዚህ በታች በነዑስ አንቀጽ (5) (6) (7) የተዘረዘሩትን አይጨምርም ፡፡
5. ለቀጣሪው ወይም ከቀጣሪው ጋር ግንኙነት ላላቸው ሰዎች ጥቅም ለማስገኘት ሳይሆን ድርጅቱ ወይም ሆስቴሉ ለቀጣሪው ወይም ከቀጣሪው ጋር ግንኙነት ላላቸው ሰዎች ጥቅም የሚያውለው ማናቸውም የማደሪያ ተቋም ወይም ሆስቴል፤
6. በየአካባቢ ባለሥልጣኖች የሚተዳደሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የማረፊያ ተቋሞች ወይም ሆስቴሎች ፤
7. በማናቸውም የተመዘገበ ሆስፒታል፣ የማዋለጃ ድርጅት ወይም ክሊኒክ የሚሰጥ አገልግሎት ፡፡

ለ/ “መኖሪያ ቤት” ማለት ማናቸውም በዋንኛነት ለመኖር የሚያገለግል ወይም ለመኖሪያነት እንዲውል የታቀደ ሕንፃ ፤ ወይም ሌላ ማናቸውም ቦታ እና የእነዚሁ ተቀፅላዎች ሲሆን በንግድ መልክ ለማረፊያነት የሚከራዩ ክፍሎችን አይጨምርም፡፡

2. ወደ ውጪ ከሚላኩት ዕቃዎች በስተቀር ዓይነታቸው ቀጥሎ የተመለከቱት የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች አቅርቦት እንዲሁም ገቢ ዕቃዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ነፃ ናቸው፤

ሀ/ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ የመኖሪያ ቤት ሽያጭና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፣[77]

ለ/ የፋይናንስ አገልግሎቶች ፤

[77] (በ21/6/92001) አ.609 አንቀፅ 2(5) ተሻሻለ፡፡

ሐ/ ለሣንቲሞች እና ሜዳሊያዎች ጥናት አገልግሎት ከሚውሉት በስተቀር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ገንዘቦችን እና የዋስትና ሠነዶችን ማሰራጨት ወይም ወደ አገር ማስገባት፡

መ/ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ወደ አገር ማስገባት፡

ሠ/ በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች፣

ረ/ የሕክምና አገልግሎት እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች፣

ሰ/ በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶች፣ እንደዚሁም ለሕፃናት ጥበቃ በመዋዕለ ሕጻናት የሚሰጡ አገልግሎቶች ፣

ሸ/በሰብዓዊ ዕርዳታ መልክ የሚቀርቡ ዕቃዎች እና የሚሰጡ አገልግሎቶች ፣ እንደዚሁም በተፈጥሮ አደጋ፤ የኢንዱስትሪ አደጋዎች እና በድንገት ለደረሱ ጉዳቶች መልሶ ማቋቋሚያ ተግባር እንዲውሉ ለመንግሥት አካላት እና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጡ ከውጪ አገር የሚገቡ ዕቃዎች፣

ቀ/ የኤሌክትሪክ ፤ የኬሮሲን እና የውሃ አገልግሎት ፤

በ/ በሕግ ወይም በስምምነት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ከሌሎች ታክሶች ነፃ የተደረጉ ድርጅቶችተቋሞችና ፕሮጀክቶች ወደ አገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣

ተ/ ከልዩ ልዩ የአገልግሎት ወይም የኮሚሽን ክፍያዎች በስተቀር የፖስታ አገልግሎት ድርጅት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣

ቸ/ የትራንስፖርት አገልግሎት፤

ነ/ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግሥት የሚፈጸም ክፍያ፤

ኘ/ በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ 2ኛ መደብ የተዘረዘሩ ዕቃዎችን ወደ አገር ማስገባት ፡

አ/ ከስድሳ በመቶ (ፐርሰንት) በላይ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ ድርጅት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣

ወ/ ወደ አገር የሚገቡና በአገር ውስጥ የሚሸጡ መጻሕፍት እና የታተሙ ጽሑፎች ፡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት፣

3. በንዑስ አንቀጽ (2)መሠረት ከታክሱ ነጻ ባይደረግ ኖሮ በንዑስ አንቀጽ 7(2) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክሱ ይሰበሰብበት የነበረ ዕቃ ወይም አገልግሎት በዚህ አንቀጽ መሠረት ከታክሱ ነፃ መሆኑ ቀርቶ በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ ይከፈልበታል ፡፡
4. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር[78] በሚያመባው መመሪያ ሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከታክሱ ነጻ እንዲሆኑ ሊፈቅድ ይችላል ፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የሚከናወኑበት ቦታ፣ ጊዜ እና ዋጋ</u>

9. <u>ዕቃዎች የሚሸጡበት ቦታ</u>
   1. አቅርቦቱ ዕቃዎችን ማጓጓዝን የሚጨምር ሲሆን ሽያጩ ተከናወነ የሚባለው ዕቃውን ማጓጓዝ የሚጀምርበት ቦታ ይሆናል፡፡ በሌሎች ሁኔታዎች የተሸጠው ዕቃ ርክክብ የሚፈጸምበት ቦታ ይሆናል፤
   2. የኤሌክትሪክ፣ የእንፋሎት፣ ኀይል፣ የጋዝ ወይም የውሃ አቅርቦት በሚሆንበት ጊዜ አገልግሎቱ ተሰጠ የሚባለው አገልግሎቶቹ ተቀባዩ ዘንድ በደረሱ ጊዜ ነው። እነዚህ አቅርቦቶች ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ የሚላኩ ከሆነ ግን እቅርቦቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከናወነ ይቆጠራል፡፡

10. <u>አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ</u>
   1. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በሌላ አኳኋን የተወሰነ ካልሆነ በስተቀር አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ተደርጎ የሚወሰደው አገልግሎት የሚሰጠው ሰው የንግድ ሥራተግባሩን የሚያከናውንበት ቦታ ነው፡፡
   2. በመሆኑም አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ፡-
      ሀ/ የሚሰጠው አገልግሎት ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በቀጥታ የተገናኘ ከሆነ ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ፤
      ለ/ የሚሰጠው አገልግሎት ከሚንቀሳቀስ ንብረት ጋር በቀጥታ የተገናኘ ሲሆን አገልግሎት መስጠቱ የተከናወነበት ቦታ፤

---
[78] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9 (4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስትር በሚል ይነበብ፡፡

ሐ/ የተሰጠው አገልግሎት በባህል፡ በሥነጥበብ  በትምህርት፣ የሰውነት ማጐልመሻ ወይም በስፖርት ወይም በሌሎች መሰል ዘርፎች ሲሆን አገልግሎቱ የተሰጠበት ቦታ፤

መ/ አገልግሎት መስጠቱ ከማጓጓዝ ተግባር ጋር የተገናኘ ሲሆን የማጓጓዙ ተግባር የተከናወነበት ቦታ ነው፡፡ለአንቀጽ 7(2) (ለ) አፈፃፀም የግብይቱ ተግባር ታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ ውጭ ከሰጠው አገልግሎት ጋር የተገናኘ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከናወነይቆጠራል ።

ሠ/ አገልግሎቱን የገዛው ሰው ዘላቂ ድርጅት የሚገኝበት ቦታ የሚሆነው አገልግሎቶቹ ከሚከተሉት አገልግሎቶች ጋር በይበልጥ የተያያዙ በሆነ ጊዜ ነው፡፡

1) የባለቤትነት መብት ማስተላለፍ፡ የፈጠራ ባለቤትነት፡ የንግድ ፈቃድ፡ የንግድ ምልክት፡ የቅጂ መብት እና ሌሎች መሰል መብቶችን ማከራየት
2) የምክር የሕግ  የሂሳብ የምህንድስና እና የማስታወቂያ አገልግሎት እንዲሁም መረጃዎችን የማጠናቀር አገልግሎትና ሌሎች መሰል አገልግሎቶች
3) ከትራንስፖርት ድርጅት ተሸከርካሪዎች በስተቀር የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች የማከራየት፡
4) በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተመለከቱትን አገልግሎቶች ለመስጠት የተገባው ውል ዋና ተሳታፊ በሆነው ሰው ስም በውሉ የተገለፀውን አገልግሎት የሚሰጥን ሰው የሚያሰማራ ወኪል ፤ አገልግሎት

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አፈፃፀም አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ተብሎ በንዑስ አንቀጽ (2) ከአንድ በላይ በሆኑ ፌደላትሥር የተገለጸው ቦታ የተራ ፊደሎቹን ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ይወስናል፡፡

## 11.<u>አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ</u>

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ከተገለፁት በስተቀር ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ተከናወነ የሚባለው ለግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሲሰጥ ነው፡፡
2. ከዚህ በታች የተገለፁት ድርጊቶች በተከናወኑ በአምስት ቀናት ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካልተሰጠ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እንደተከናወነ ይቆጠራል።

ሀ/ ዕቃዎች ለተረካቢው ዝግጁ ሆነው በተቀመጡ፣ የዕቃዎች ርክክብ፣ ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ በተፈፀመበት ወይም አገልግሎቶቹ በሚሰጡበትጊዜ፣

ለ/ የዕቃዎች ርክክብ ዕቃዎችን ማጓጓዝ የሚያካትትሲሆን የዕቃዎች ማጓጓዝ ሲጀምር ነው፡፡

3. ክፍያ የተፈፀመው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና(ለ) ከተጠቀሱት ጊዜያት በፊት ሆኖ ክፍያው በተፈፀመ በአምስት ቀናት ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካልተሰጠ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ቢኖሩም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እንደተከናወነ ይቆጠራል፡፡

4. የንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) አፈፃፀም ለአቅርቦቱ ግብይትአንድ ወይም ከአንድ የበለጡ ክፍያዎች የተፈጸሙ እንደሆነ በእያንዳንዱ ክፍያ መጠን የተለያዩ ግብይቶች እንደተደረጉ ይቆጠራል፡፡

5. አገልግሎቶች በመደበኛነት ወይም በተከታታይ በሚሰጡበት ሁኔታ እነዚህን አገልግሎቶች በሚመለከት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ በተሰጠ ጊዜ ሁሉ አገልግሎቶች እንደተሰጡ ይቆጠራል ክፍያውአስቀድሞ የተፈፀመ ከሆነ ግን ክፍያ የተፈፀመባቸውአገልግሎቶች ክፍያው በተፈፀመ ጊዜ እንደተሰጡይቆጠራል፡፡

6. የአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ተፈፃሚ ሲደረግ አቅርቦቱ የተከናወነበት ጊዜ ተደርጎ የሚቆጠረው በዕቃው ወይም በአገልግሎቱ መጠቀም የተጀመረበት ጊዜ ይሆናል፡፡[79]

7. በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (3) የተዘረዘሩትን በሚመለከት አቅርቦቱ የተከናወነበት ጊዜ ተደርጎ የሚቆጠረው ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ለተቀጣሪዎች የሚሰጡበት ጊዜ ነው።[80]

8. የአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (4) ተፈጻሚ ሲደረግ የአቅርቦት ጊዜ የሚባለው የምዝገባው መሠረዝ ከሚፀናበት ቀን በፊት ያለው ጊዜ ነው።[81]

9. ለጥቅም ሲባል በተደረገ አቅርቦት አቅራቢው ክፍያውን የተቀበለው በሣንቲም ወይም በወረቀት ገንዘብ በሚሠራ መሣሪያ፣ ቆጣሪ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መሣሪያ

[79] በ21/6/92001) አ.609 አንቀፅ 2(6) ተሻሻለ፡፡

[80] በ21/6/92001) አ.609 አንቀፅ 2(7) ተሻሻለ፡፡

[81] በ21/6/92001) አ.609 አንቀፅ 2(8) ተሻሻለ፡፡

የሆነ እንደሆነ ማንቲሙ ወይም የወረቀት ገንዘቡ በአቅራቢው ስም ከመዝገቢያው ፣ ወይም ከቆጣሪው ወጪ ሲደረግ፤

10.ሌሎች አቅርቦቶች ተፈፀሙ የሚባልበት ጊዜ በገቢዎች ሚኒስትር በሚወጣ መመሪያ ይወስናል፡፡

## 12.<u>ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እሴት</u>

1. ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እሴት የሚወሰነው ታክስ ከፋዩ ለአቀረባቸው ዕቃዎች ወይም ለሰጣቸው አገልግሎቶች (ማናቸውም ቀረጥ፣ ታክስ ወይም ሌሎችክፍያዎች ጨምሮ) ከደንበኛው ወይም ከማናቸውም ሌላ ሰው የተቀበለውን ወይም ለመቀበል የሚችለውን ዋጋ መሠረት በማድረግ ሲሆን፤ የተጨማሪ እሴትታክስን አይጨምርም፡፡
2. ታክስ ከፋዩ ለአቅርቦቱ እሴት በለውጡ የሚቀበለውወይም ለመቀበል የሚችለው ዕቃ ወይም አገልግሎትበሚሆንበት ጊዜ፤ የአቅርቦቱ እሴት የእነዚህ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የገበያ ዋጋ (ማናቸውም ቀረጥ፣ ታክሶች ወይም ሌሎች ክፍያዎች ጨምሮ) የሚጨምርሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስን አይጨምርም፡፡
3. ታክስ ከፋዩ ላከናወነው አቅርቦት በለውጡ የሚቀበለው ወይም ሊቀበለው የሚችለው ምንም ነገር ከሌለ (ምዝገባው በተሠረዘ ጊዜ በእጅ የቀሩትን ዕቃዎችጭምር) ታክሱ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ የቀረቡት ወይም የተሰጡት አገልግሎቶች የገበያ ዋጋ የማናቸውም ቀረጥ ታክሶች ወይም ሌሎች ክፍያዎች ጭምርን ሲሆን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስን አይጨምርም፡፡
4. በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላልሆነ ተግባር የዋሉ የፍጆታ ዕቃዎችን ወይም የተሰጡ አገልግሎቶችን በሚመለከት እንዲሁም በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ መሠረት ለቀጣሪው ሠራተኛ የተደረጉ አቅርቦቶች ወይም የተሰጡ አገልግሎቶችን በሚመለከትየአቅርቦቱ እሴት ነው የሚባለው ዕቃዎቹ ወይምአገልግሎቶቹ የቀረቡበት፤ የተሰጡበት ወይም እንዲሟሉ የተደረገበት ዋጋ (ማናቸውም ቀረጥ፡ ታክሶች ወይም ሌሎች ክፍያዎች ጨምሮ) ሲሆን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስን አይጨምርም፡፡
5. የገቢዎች ሚኒስትር በዚህ አንቀጽ ያልተሸፈኑ የዕቃ አቅርቦትና አገልግሎት የመስጠት ተግባሮችን ዋጋ ስሌት ለማከናወን የሚያስችል መመሪያ ያወጣል ፡፡

## 13.ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ዋጋ ስለማስተካከል

1. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው የተመዘገበው ሰው ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ጋር በተያያዘ፡-

   ሀ/ ግብይቱ ሲሠረዝ፣

   ለ/ የግብይቱ ተፈጥሮ ሲቀየር፣

   ሐ/ በዋጋ መቀነስም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት አስቀድሞ ለግብይቱ የተጠየቀው ገንዘብ መጠን ሲለወጥ ወይም

   መ/ ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ በከፊል ወይም በሙሉ ለታክስ ከፋዩ የተመለሱ ሲሆን ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንዱ ወይም ከአንድ በላይ በማጋጠማቸው ምክንያት የተመዘገበው ሰው፡-

   ሀ/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የሰጠ እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ላይ የተገለጸው ዋጋ የተሳሳተ ሲሆን፣ ወይም

   ለ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የተጨማሪ እሴት ታክስ የተሳሳተ ሲሆን፤

3. በንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) በተገለጸው አኳኋን የታክስ ደረስኝ የተሰጠ እንደሆነ እና በታክስ ደረሰኙ ላይ የተመለከተው የተከፈለው ታክስ የገንዘብ መጠን በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ የበለጠ እንደሆነ፣ የተመዘገበው አቅራቢ ለገዥው በንዑስ አንቀጽ (9) የተገለፀውን ዝርዝር የያዘ የታክስ ክሬዲት ሠነድ መስጠት አለበት፡፡

4. ማናቸውም የተመዘገበ ሰው በንዑስ አንቀጽ 3 ከተገለጸው በስተቀር በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የታክስ ክሬዲት ሠነድ መስጠት የለበትም፡፡

5. በንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) በተገለፀው አኳኋን የታክስ ደረስኝ የተሰጠ እንደሆነ እና በታክሱ ደረስኝ ላይ የተመለከተው የተከፈለው ታክስ የገንዘብ መጠን በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ያነሰ እንደሆነ፣የተመዘገበው አቅራቢ ለገዥው በንዑስ አንቀጽ (10) የተገለፀውን የታክስ ዴቢት ሠነድ መስጠት አለበት ፡፡

6. ማናቸውም የተመዘገበ ሰው በንዑስ አንቀጽ (5) ከተገለፀው በስተቀር በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የታክስ ዴቢት ሠነድ መስጠት የለበትም፡፡

7. ማናቸውም የተመዘገበው ሰው በንዑስ አንቀጽ (3)እና (5) በተገለጸው ሁኔታ በትርፍ ወይም በማነስ ለተከፈለ ታክስ የሚሰጠው አንድ የታክስ ክሬዲት ወይም የታክስ ዴቢት ሠነድ ብቻ ነው፡፡
8. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም የተመዘገበው ሰው የታክስ ክሬዲት ወይም የታክስ ዴቢት ሠነድ ዋናው ቅጂ የጠፋበት መሆኑን በመግለጽ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ያቀረበው የተመዘገበ ሰው "ቅጂ" የሚል ጽሑፍ የሠፈረበት ቅጂ ሊሰጠው ይችላል፡፡
9. ባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ እንዲፈጸም ካልፈቀደ በስተቀር በንዑስ አንቀጽ (3) የተገለፀው የታክስ ክሬዲት የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፡፡

   ሀ/ በሚታይ ቦታ "የታክስ ክሬዲት ሠነድ" የሚል ጽሑፍ፤

   ለ/ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ያቀረበውን ሰው ስም፤ አድራሻ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

   ሐ/ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን የገዛውን ሰው ስም፤ አድራሻ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

   መ/ የታክስ ክሬዲት ሠነዱ የተፃፈበትን ቀን፣

   ሠ/ በታክስ ደረሰኙ ላይ የተመለከተውን የአቅርቦቱን ዋጋ ፣ የአቅርቦቱን ትክክለኛ ዋጋ፣በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት፣ በልዩነቱ ምክንያት የተከፈለውን ታክስ፣

   ረ/ የታክስ ክሬዲት ሠነድ መስጠት ያስፈለገበትን ሁኔታ የሚያስረዳ አጭር መግለጫ፤ እና

   ሰ/ ለታክስ ክሬዲት ሠነድ አግባብነት ያለውን ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ለይቶ የሚያሳይ በቂ መረጃ፣
10. ባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ እንዲፈጸም ካልፈቀደ በስተቀር በንዑስ አንቀጽ (5) የተገለጸው የታክስ ዴቢት የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፤

   ሀ/ በሚታይ ቦታ "የታክስ ዴቢት ሠነድ" የሚል ጽሑፍ፤

   ለ/ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ያቀረበውን ሰው ስም፣ አድራሻ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤

   ሐ/ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን የገዛውን ሰው ስም፣ አድራሻ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

   መ/ የታክስ ዴቢቱ የተፃፈበትን ቀን፤

ሠ/ በታክስ ደረሰኙ ላይ የተመለከተውን የአቅርቦቱን ዋጋ፣ የአቅርቦቱን ትክክለኛ ዋጋ፣ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት፣ በልዩነቱ ምክንያት የተከፈለውን ታክስ፤

ረ/ የታክስ ዴቢት ሠነድ መስጠት ያስፈለገበትን ሁኔታየሚያስረዳ አጭር መግለጫ፤እና

ሰ/ ለታክስ ዴቢቱ ሠነድ አግባብነት ያለው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ለይቶ የሚያሳይ በቂ መረጃ፡፡

## ክፍልአራት

## ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች እሴት እና የገቡበት ጊዜ

### 14.ዕቃዎች ወደ አገር ገቡ የሚባልበት ጊዜ

ዕቃዎች ወደአገር ውስጥ ገብተዋል የሚባለው በጉምሩክዲክላራሲዮን ላይ ሲመዘገቡ ነው፡፡

### 15.ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች እሴት

1. ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች ታክስ የሚጣልበት እሴትበእነዚህ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስጨምሮ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ሕግ መሠረት በጉምሩክ የሚወሰነው የዕቃዎች ዋጋ ሲሆን፤ የተጨማሪ እሴትታክስንና ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የገቢ ግብር ቅድሚያ ክፍያ አይጨምርም።
2. በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ዕቃን ወደአገር ከማስገባት ጋር ተጓዳኝ ሆነው የተሰጡ አገልግሎቶችን በሚመለከት የአገልግሎቶቹ ዋጋ የተጨማሪ እሴትታክስን ሳይጨምር በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተወሰነ ዋጋ ላይ ተጨማሪ ይሆናል፡፡

## ክፍልአምስት

## ምዝገባ

### 16.የመመዝገብ ግዴታ

1. ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ሆኖ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ማናቸውም ሰው ከዚህ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ለተጨማሪ እሴትታክስ ለመመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡

ሀ/ በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ)በላይ ከሆነ ወይም

ለ/ በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ መጀመሪያ በዚህ የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ የሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከብር500,000 (አምስት መቶሺ) በላይ ይሆናል ብሎ ለመገመት የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት እንደሆነ፡

2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ከፍ ወይምዝቅ ማድረግ ይችላል፡፡

3. ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተመለከተው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው ወር እስከ መጨረሻ ቀን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተመለከተው ጊዜ በተጠናቀቀበት ወር እስከ መጨረሻ ቀን ለምዝገባ ማመልከቻ ማቅረብና መመዝገብ አለበት።[82]

4. በንዑስ አንቀጽ(5) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን በቅርንጫፎች ወይም በሥራ ክፍሎች የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው ቅርንጫፎች ወይም የሥራ ክፍሎች መመዝገብ ያለባቸው በዋናው ተመዝጋቢ ስም ይሆናል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም ሕጋዊ ሰውነት ባለው የተመዘገበ ሰው በሚቀርብለት ማመልከቻ መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ቅርንጫፎቹ ወይም የሥራ ክፍሎቹ ራሱን የቻለ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ያላቸው፡ በንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ዓይነት ወይም በሚገኙበት ቦታ ተለይተው የሚታወቁ ከሆነ፤የተመዘገበው ሰው አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ቅርንጫፎች ወይም የሥራ ክፍሎች በተናጠል እንዲመዘገቡ መፍቀድ ይችላል፡፡

6. በንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሚፈጸመው የቅርንጫፎች ወይም የሥራ ክፍሎች የተናጠል ምዝገባ የሚፈፀመው የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ ከተቀመጡት ሁኔታዎች እና ገደቦች ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

7. ማናቸውም ሰው በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ለመወሰን፡

ሀ/ ሁለት ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በሚሆኑበት ጊዜ ባለሥልጣኑ አንዱ ያከናወነውን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ሌላው ካከናወነው ጋር እንዲደመር ማድረግ ይችላል፡፡

---

[82] በ21/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(9) ተሻሻለ፡፡

ለ/ የማናቸውም ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋየሚወሰነው በአንቀጽ 12 መሠረት ነው።

17.<u>በፈቃደኝነት ስለመመዝገብ</u>

ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገቢያ ግዴታ የሌለበት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ሰው ቢያንስ 75 ፐርሰንት (ሰባ አምስት በመቶ) የዕቃ ማቅረብ እና አገልግሎት የመስጠት ሥራ የሚያከናውነው ለተመዘገቡ ሰዎች ከሆነ በፍላጎቱ የምዝገባ ማመልከቻውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

18.<u>የምዝገባ ሥርዓት</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ የሚቀርብ ማናቸውም ሰው ማመልከቻውን የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው የአፈፃፀም መመሪያ ውስጥ በተመለከተው ቅጽ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ የሚጣልበትን ግብይት የሚያከናውን ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ያመለከተ እንደሆነ ባለሥልጣኑ አመልካቹን በተጨማሪ እሴት ታክስ መዝገብ ከመዘገበ በኋላ ከምዝገባው ዕለት ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ የሚከተለውን መረጃ የያዘ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

   ሀ/ የተመዘገበውን ሰው ሙሉ ስም እና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮች፡

   ለ/ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበትን ቀን፡

   ሐ/ የምዝገባው ተፈጻሚነት የሚጀምርበትን ቀን፡

   መ/ የተመዘገበውን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፡
4. ምዝገባው ከዚህ ቀጥሎ ካሉት ቀናት ውስጥ ቀድሞ በደረሰው በአንዱ ቀን ይከናወናል፡፡

   ሀ/ መመዝገብ ግዴታ ሲሆን፡ ለምዝገባ የማመልከቻ ማቅረብ ግዴታ ከሚጀምርበት ወር ቀጥሎ ባለው የሂሣብ ጊዜ የመጀመሪያ ቀን፡

   ለ/ ምዝገባ በፍቃደኝነት ሲሆን፡ አመልካቹ ለምዝገባ ማመልከቻ ካቀረበበት ወር ቀጥሎ ባለው የሂሣብ ጊዜ የመጀመሪያ ቀን፡

   ሐ/ በተመዘገበው ሰው የምዝገባ ማመልከቻ የምዝገባ ቀን እንዲሆን የተመረጠው ቀን፡

5. ባለሥልጣኑ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ሰዎችን የሚመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች የሚመዘገቡበት መዝገብ ያቋቁማል፡፡
6. ባለሥልጣኑ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሆኖ ነገር ግን የምዝገባ ማመልከቻ ያላቀረበን ሰው ራሱ በመመዝገብ ለተመዘገበው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ 2 የተገለጸውን የምዝገባ ሰርቲፊኬት መላክ ይችላል፡፡
7. ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን በሁሉም የተጨማሪ እሴት ታክስ ኢንቮይሶች፣ በታክስ ማስታወቂያዎች እና ከባለሥልጣኑ ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ መጠቀም ይኖርበታል፡፡
8. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 17 መሠረት በፈቃደኝነት ለመመዝገብ ሲያመለክት፣ ባለሥልጣኑ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

   ሀ/ አመልካቹ የተወሰነ የመኖሪያ ወይም የንግድ ሥራ አድራሻ የሌለው ሲሆን፣

   ለ/ አመልካቹ በዚህ አዋጅ መሠረት ተገቢውን የሒሣብ መዝገብ ለመያዝ ጊዜውን ጠብቆ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የታክስ ማስታወቂያ ለማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ ባለሥልጣኑ አሳማኝ ምክንያት ካለው፡፡

19.<u>ምዝገባን ስለመዘረዝ</u>

1. የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚጣልባቸውን ግብይቶች ሲያቆም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያደረገው ምዝገባ እንዲሠረዝለት ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተመዘገበው ሰው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ያለው የሦስት ዓመት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት አሥራ ሁለት ወራት ውስጥ የሚያከናውናቸውታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ጠቅላላ ዋጋ ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ) የማይበልጥ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ምዝገባው እንዲሠረዝለት ለመጠየቅ ይችላል፡፡
3. ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተደረገው ምዝገባ መሠረዝ ተፈጻሚነት የሚጀመረው የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልባቸውን ግብይቶችማከናወን ካቆመበት ጊዜ ጀምሮ ወይም የተመዘገበው ሰው ግብይቶቹን ያላቋረጠ በሚሆንበት ጊዜ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያደረገው ምዝገባ እንዲሠረዝለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለባለሥልጣኑ ካመለከተበት የሒሣብ ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡

4. ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተደረገ ምዝገባ በተሠረዘ ጊዜ የባለሥልጣኑ መ/ቤት የተመዘጋቢውን ስም እና ሌሎች ዝርዝሮች ኩተጨማሪ እሴት ታክስ መዝገብ ይሠርዛል። የተመዘገበው ሰውም የተሰጠውን የምዝገባ ሰርቲፊኬት መመለስ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## የታክስ ስሌት

20. **በአንድ የታክስ ዘመን መከፈል ያለበት ታክስ**

1. በተመዘገበ ወይም የመመዝገብ ግዴታ ባለበት ሰው በማናቸውም የሂሳብ ጊዜ የሚከፈለው ታክስ በአንቀጽ 7 መሠረት ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ላይ በሚከፈለው ታክስ እና በአንቀጽ 21 መሠረት ተቀናሽ በሚደረገው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡
2. በአንቀጽ 13 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት መከፈል የሚገባው ታክስ በታክስ ከፋዩ ከተገለጸው የበለጠ በሚሆንበት ጊዜ በብልጫ የታየው ሂሣብ በአንቀጽ16 የተጠቀሰው ሁኔታ ባጋጠመበት የሂሣብ ጊዜ በተከፋይነት ተይዞ፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ 1 በተጠቀሰው የሂሣብ ጊዜ ከሚከፈለው ታክስ ጋር ተዳምሮ ይከፈላል፡፡

21. **ታክስን ስለማቀናነስ**

1. በዚህ አንቀጽ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፤ ዕታዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ጥቅም ላይ የዋሉት ወይም የሚውሉት ለተመዘገበው ሰው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሲሆን፡ ታክሱ የሚጣልበት ግብይት የተከናወነበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ ተቀናሽ የሚደረገው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ የተመዘገበው ሰው በቀረበለት የታክስ ኤንቮይስ ወይም ዲክላራሲዮን መሠረት የሚከፍለው ወይም የከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡

   ሀ/ በአንቀጽ 14 በተመለከተው የሂሣብ ጊዜ ወደአገር ውስጥ ላስገባቸው ዕቃዎች እና ለ/በአንቀጽ 11 በተመለከተው የሂሣብ ጊዜ እንደተከናወኑ በሚቆጠሩ ታክስ የሚጣልባቸው የዕቃ እና አገልግሎቶች አቅርቦት የከፈለው ታክስ ነው።
2. በአንድ የታክስ ዘመን ውስጥ የተመዘገበ ሰው ካከናወነው የዕቃ ወይም አገልግሎት አቅርቦት ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከፊሉ ብቻ የሆነ እንደሆነ በንዑስ

አንቀጽ (1) መሠረት ለዚህ የታክስ ዘመን ተቀናሽየሚደረገው ታክስ በሚከተለው አኳኋን ይወሰናል፡፡

ሀ/ በቀጥታ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት የዋለውን አቅርቦት ወይም ወደአገር የገባ ዕቃ በሚመለከት፣ ለአቅርቦቱ ወይም ወደአገር ለገባው ዕቃ የተከፈለው ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ለ/ ከታክሱ ነፃ ለሆነው ግብይት የዋለውን አቅርቦት ወይም ወደአገር የገባ ዕቃ በሚመለከት፣ ለአቅርቦቱ ወይም ወደአገር ለገባው ዕቃ የተከፈለው ታክስ ተቀናሽ አይደረግም።

ሐ/ ታክስ ለሚከፈልበት እና ከታክሱ ነፃ ለሆኑ ግብይቶች በጋራ የዋለውን አቅርቦት ወይምወደአገር የገባ ዕቃ በሚመለከት ለአቅርቦቱ ወይም ወደአገር ለገባው ዕቃ የተከፈለው ታክስ እንዲቀናነስ ለማድረግ ሂሳቡ የሚከፋፈልበት ደንብ የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3. ቀጥሎ ለተመለከቱት የተከፈለ ታክስ ተቀናሽ አይደረግም፡፡

ሀ/ አነስተኛ የመንገደኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ያለው ሰው ወደአገር ላስገባው ወይም በአገር ውስጥ ላከናወነው ግብይት የከፈለውን ታክስ በሚመለከት፣

1) እንደዚህ ያሉትን ተሽከርካሪዎች በመሸጥ ወይም በማከራየት የንግድ ሥራ የተሠማራወይም ተሽከርካሪውን የገዛው ለዚሁ ንግድ ሥራ እንዲውል ካልሆነ በስተቀር፣

2) መንገደኞቹን በማጓጓዝ የንግድ ተግባር ላይ የተሠማራ ወይም ተሽከርካሪውን የገዛው እና ፈቃድ የተሰጠው ለዚሁ ንግድ ሥራ እንዲውል ካልሆነ በስተቀር

ለ/ ከአገር ውስጥ የተገዙት ወይም ወደአገር የገቡት ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ለመዝናኛ ወይም ለመዝናኛ አገልግሎት የዋሉ በሚሆንበት ጊዜ፡

1) ታክስ ከፋዩ በመዝናኛ አገልግሎት ንግድ ሥራ ውስጥ የተሠማራ ወይም አቅርቦቱ ወይም ወደአገር የገባው ዕቃ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ሂደት ታክስ ለሚከፈልባቸውየመዝናኛ ሥራዎች የሚውል ካልሆነ በስተቀር፡

2) ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት የንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ እና የመዝናኛው አገልግሎት ለመንገደኞች የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት አካል ካልሆነ በስተቀር፡

4. ለንዑስ አንቀጽ (3) አፈፃፀም

ሀ/ “የመንገደኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ” ማለት 8 እና ከ 8 በታች የሆኑ መንገደኞችን ማጓጓዝ የሚችል ተሽከርካሪ ሲሆን፤ ድርብ ጋቢና ያላቸውን ተሽከርካሪዎች ይጨምራል።

ለ/ “መዝናኛ” ማለት በተመዘገበ ሰው የሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ አንድ ክፍል ሆኖ፡ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለማናቸውም ሌላ ሰው የሚቀርብ ምግብ፣ መጠጥ፣ ትምባሆ፡ ማረፊያ፣ መደሰቻ ወይም ማናቸውም ዓይነት መስተንግዶ ነው፡፡

5. በአንቀጽ 13 በተመለከቱት ሁኔታዎች፣ በአንድ ግብይት የታክስ ኢንቮይስ ወይም የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ላይ የተመለከተው ታክስ በዚህ ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በልጦ የተገኘ እንደሆነ በብልጫ የታየው የገንዘብ መጠን በአንቀጽ 13 የተመለከተው በተፈፀመበት የሂሣብ ጊዜ ውስጥ ለተመዘገበው ሰው እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡ ይሁን እንጂ አቅርቦቱ ላልተመዘገበ ሰው የሆነ እንደሆነ፣ በብልጫ የታየው ታክስ ለገዥው ካልተመለሰ በስተቀር ማቀናነስ እንዲደረግ አይፈቀድም።

6. ሀ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ወይም መመዝገብ ያለበት ሰው ከመመዝገቡ በፊት ባሉት 6ወራት ጊዜ ውስጥ ለገዛቸውና በይዞታው ሥር ለሚገኙ ዕቃዎች የከፈለው ታክስ፣ ዕቃዎቹ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የዋሉ ወይም የሚውሉ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ታክስ ከፋዩ በተመዘገበበት ወይም መመዝገብ በነበረበት የመጀመሪያ የሂሣብ ጊዜ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

ለ) በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከብር 100 ሚሊዮን (ከብር አንድ መቶ ሚሊዮን) በላይ የሆነ ታክስ ከፋይ በተመዘገበበት ጊዜ በእጁ የሚገኙ ወይም ከተመዘገበበት ጊዜ በኋላ ባለው የሂሣብ ጊዜ የገዛቸው የካፒታል ዕቃዎች ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚውሉ መሆኑ ከተረጋገጠ በካፒታል ዕቃዎቹ ላይ የተከፈለው

የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚቀጥለው የሂሣብ ጊዜ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡[83]

7. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻቻ ሥርዓት ለማቋቋም በወጠው አዋጅ ቁጥር 249/1994[84] በተደነገገው መሠረት የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው በዚሁ ሥርዓት ወደአገር ባስገባው ዕቃ ላይ በዚህ አንቀጽ መሠረት የታክስ ማቀናነስ ጥያቄ ካቀረበበተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት መሠረት የታክስ ተመላሽ ማግኘት አይችልም፡፡

22. **ደረሰኞች**[85]

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) እና (7) በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበና ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያካሂድ ሰው ደረሰኝ ወዲያውኑ መስጠት አለበት፡፡ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው እሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት አይችልም።[86]
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የገቢዎች ሚኒስትር በሚወስነው ዓይነት የሚዘጋጅ ሆኖ፣ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን መረጃዎች የሚይዝ ይሆናል፡፡
   ሀ/ የተመዘገበውን ሰው እና የገዥውን ሙሉ ስም እንዲሁም ከሕጋዊ መጠሪያው የተለየ ከሆነ የተመዘገበውን ሰው የንግድ ስም፤
   ለ/ የተመዘገበውን ሰው እና የገዥውን መለያ ቁጥር፤
   ሐ/ የተጨማሪ እሴትታክስ የምዝገባ ሠርቲፊኬት እና የተሰጠበትን ቀን፣
   መ/ የተጓጓዘውን ዕቃ ወይም የተሰጠውን አገልግሎት መጠሪያ፤
   ሠ/ ታክሱ የሚከፈልበትን ግብይት ዋጋ፤
   ረ/ ግብብይቱ የተፈጸመበት ዕቃ የኤክሣይዝ ታክስ የተከፈለበት ሲሆን የኤክሣይዝ ታክሱን መጠን፤
   ሰ/ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ የሚፈለገውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ፡
   ሸ/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተሰጠበትን ቀን፤

---

[83] ይህ ንዑስ አንቀጽ በ25/81 (2001) አ.1157 አንቀጽ 2(5) ተሻሻለ

[84] በስራ ላይ ያለው አዋጅ 18/62 (2004) አ. 768 ነው ተተክቶ ይነበብ፡፡

[85] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(11) መሰረት ተሰርዞ ንዑስ አንቀፅ (4)፣ (5)፣(6) እና (7) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀፅ (3)፣ (4)፣ (5) እና (6) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

[86] በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(10) ተሻሻለ፡፡

ቀ/ ቀን የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተከታታይ ቁጥር፤

3. በንዑስ አንቀጽ (6) እና (7) በተደነገገው መሠረት ግብይቱ የታክስ ደረሰኝ የማይጠየቅበት ካልሆነ በስተቀር በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የታክስ ደረሰኝ ያልተሰጠው የተመዘገበ ገዥ፣ አቀርቦቱ ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ በ8 ቀን ጊዜ ውስጥ ደረሰኙን መጠየቅ ይችላል፡፡ ይህ ጥያቄ የደረሰው የተመዘገበው አቅራቢ ጥያቄው በደረሰው በ12 ቀን ጊዜ ውስጥ ለተፈጸመው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት ፡፡
4. የተመዘገበው ገዥ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት የተሰጠው የታክሱ ደረሰኝ ዋና ቅጂ የጠፋበት እንደሆነ የተመዘገበው አቅራቢ "ቅጂ" የሚል ግልጽ ምልክት በማድረግ ቅጂውን ሲሰጠው ይችላል፡፡
5. በንዑስ አንቀጽ (7) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተመዘገበው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ላልሆኑ ገዢዎች በችርቻሮ ደረጃ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በሚያቀርብበት ጊዜ በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ምትክ በክፍያ ደረሰኝ ወይም ለአሠራር ቀላል ሆኖ በተዘጋጀ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ እንዲጠቀም የገቢዎች ሚኒስትር በመመሪያ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
6. ለአቅርቦት የሚከፈለው ጠቅላላ ዋጋ ከብር 10 የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ የተመዘገበ ሰው ለዚህ ዓይነቱ የጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ደረሰኝ የመስጠቱ ግዴታ ቀሪ እንዲሆን የገቢዎች ሚኒስትር በመመሪያ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

23.<u>በገዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ</u>

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ለተገለፀው ደንበኛ በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ የተሰጠው አገልግሎት በዚህ አንቀጽ መሠረት ታክስ ይከፈልበታል።
2. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ደንበኛ" የሚባለው በኢትዮጵያ ውስጥ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ማንኛውም የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ነው፡፡
3. በንዑስ አንቀጽ (7) በተደነገገው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው የሚቀርብ አገልግሎት በአንቀጽ 8 መሠረት ከታክስ ነፃ ካልተደረገ ደንበኛው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነው ሰው ከሚከፈለው ገንዘብ ላይ ታክሱን ቀንሶ ማስቀረት

አለበት፡፡ ሊከፈል የሚገባው ታክስ የሚወሰንበት ዘዴ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

4. ደንበኛው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ከሆነ ተቀናሽ የተደረገው ታክስ ግብይቱ ለተካሄደበት የሂሳብ ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ በሚቀርብበት ወቅት ለባለሥልጣኑ ገቢ መደረግ አለበት። የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ የተፈፀመበት ሠነድ እንደተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የሚቆጠር እና በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለደንበኛው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ መብት የሚያስገኝለት ነው ፡፡
5. ደንበኛው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ በሚሆንበት ጊዜ ተቀናሽ ያደረገውን ታክስ ነዋሪ ላልሆነው ሰው ክፍያውን በፈፀመ በ30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ የገቢዎች ሚኒስትር ባወጣው የአፈፃፀም መመሪያ በተመለከተው መሠረት ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት።
6. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ንብረት የሆነ መሣሪያ ወይም ዕቃ ለኪራይ ወደ አገር በሚገባበት ጊዜ እና ለኪራዩ የሚከፈለው ክፍያ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ሲሆን ተከራዩ የባለንብረቱን ስምምነት ሲያገኝ ዕቃው ወይም መሣሪያው ወደ አገር በሚገባበት ጊዜ የከፈለው ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግለት ሊጠይቅ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ተከራዩ እንደ ታክስ ከፋይ የሚቆጠር ሲሆን በቀጣይ በሚደረገው የንብረት ማስተላለፍ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ኃላፊ ይሆናል።
7. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው አገልግሎት ሰጪ በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ወደ አገር በሚገቡ አገልግሎቶች ላይ የተጣለውን ታክስ የከፈለ አንደሆነ ይህ አንቀጽ በእነዚህ አገልግሎቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም ፡፡

24.<u>በወኪል አማካኝነት ስለሚከናወን ግብይት</u>

1. አንድ ወኪል ወካይ በሆነው ሰው ስም እና በወካዩ ትዕዛዝ ዕቃዎችን የማቅረብ ወይም አገልግሎቶችን የመስጠት ሥራ ያከናወነ እንደሆነ በወካዩ የተከናወነ ግብይት ሆኖ ይቆጠራል፡፡ ወኪሉ እና ታክስ ከፋይ የሆነው ወካይ ሁለቱም በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚከፈለው ታክስ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡
2. ወኪሉ ለወካዩ የሰጠውን አገልግሎት በተመለከተ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም።

3. ነዋሪ ላልሆነና ለተጨማሪ እሴት ታክስ በኢትዮጵያ ውስጥ ላልተመዘገበ ሰው ነዋሪ በሆነ ወኪል አማካኝነት ከውጪ ወደ ኢትዮጵያ ለገቡ እቃዎች የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ አይሆንም።

## 25.<u>ልዩድንጋጌ</u>

በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ ተመስርቶ የዕድል ሙከራ ጨዋታን ፣ የሎተሪን፣ የጉዞ ወኪሎችን አገልግሎት፣ በኮሚሽን የሚደረግን ሽያጭ፣ ያገለገሉ ዕቃዎችን ሽያጭ፣ እንዲሁም የሌሎች ኢንዱስትሪዎች ታክስ የመክፈል ግዴታ ማስላት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ እነዚህ አቅራቢዮች እና አቅርቦቶች የሚመሩበት አሰራር በገቢዎች ሚኒስትር በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል ፡፡

## <u>ክፍልሰባት</u>

## <u>የታክሱ አስተዳደር ሥርዓት</u>

## 26.<u>ታክስ ስለማስታወቅ እና ስለመክፈል</u>

1. እያንዳንዱ የተመዘገበ ሰው፣[87]
   ሀ/ በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ግብር ባለሥልጣኑ ዘንድ በመቅረብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ ወይም ባለሥልጣኑ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ማስታወቅ፣ እና
   ለ/ ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተሰጠውን የመጨረሻ ታክስ መክፈያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ለባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑ ለወከለው ሰው ከገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ታክሱን መክፈል አለበት።
2. ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ መቅረብ ያለበት ከሂሳብ ጊዜው ቀጥሎ ያለው ወር የመጨረሻ ቀን ከማለፉ በፊት ነው፡፡
3. በአንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (4) “ሐ” እንደተደነገገው የምዝገባው ተፈጻሚት ወደ ኋላ የሚሠራ በሚሆንበት ጊዜ የተመዘገበው ሰው ምዝባው ከሚጸናበት ጊዜ አንስቶ ታክስ ለሚከፈልባቸው ግብቶች ታክሱን የመክፈል ግዴታ ያለበትሲሆን የታክስ አቀናነስ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ሥርዓት መሠረት በማድረግ የታክስ ቅናሽ ይፈቀድለታል፡፡

[87] በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(12) ተሻሻለ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ ጋር የተያያዙ ግብይቶች የተመዘገበው ሰው በመጀመሪያ በሚያቀርበው የሽያጭ ገቢ ማስታወቂያ ላይ መታየት የሚኖርባቸው ሲሆን፣ ግብይቶቹ የሽያጭ ማስታወቂያው በሚያመለክተው ወር እንደተካሄዱ ይቆጠራል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የተመዘገበው ሰው የሽያጭ ገቢ ማስታወቂያዎቹ ላይ ለተመለከቱት ግብይቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረስኝ ማዘጋጀት ይችላል፡፡

4. በገቢ ዕቃዎች ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰበሰበው በዚህ አዋጅ እና በኢትዮጵያ የጉምሩክ ሕግ የጉምሩክ ቀረጥ ለመወሰን በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በጉምሩክ

   ባለሥልጣን ነው ፡፡

## 27.ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ[88]

1. የዚህ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ (በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2)(መ) ከተመለከተው በስተቀር) ካከናወነውታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ውስጥ ቢያንስ 25 ፐርሰንት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ከሆነ የተመዘገበው ሰው በብልጫ የተከፈለውን ታክስ ከሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ጋር በማያያዝ ጥያቄውን ባቀረበ በሁለትወር ጊዜ ውስጥ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በዚህ የሂሳብ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ የተከፈለውንና እንዲመለስ የተጠየቀውን ታክስ መመለስ አለበት።
2. የዚህ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች የተመዘገቡ ሰዎችን በሚመለከት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ ተቀናሽ እንዲደረግ የተጠየቀው ታክስ ለቀጣዮቹ 5 (አምስት) የሂሳብ ጊዜዎች እንዲተላለፍ ሆኖ ፡ በእነዚህ ጊዜዎች ከሚደረግ ክፍያ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡ ይህ የአምስት ወር ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ቀሪ ሂሳብ ቢኖር የተመዘገበው ሰው በብልጫ የተከፈለውን ታክስ ከሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ጋር በማያያዝ ጥያቄውን ባቀረበ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ሂሳቡን ተመሳሽ ያደርጋል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ለተመዘገበው ሰው ተመላሽ የተደረገው ሂሳብ የተሳሳተ መሆኑን ሲደርስበት ከተገቢው በላይ የተወሰደው ሂሳብ እንዲመለስለት በማናቸውም ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል ።

---

[88]የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 በ25/81 (2011) አ.1157 አንቀጽ 2(6) የተጨመረ ነው፡፡

4. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ለተመላሽ ሂሳብ የሚውለው ገንዘብ በዚህ አዋጅ መሠረት ከተሰበሰበው ታክስ ላይ ተቀንሶ የሚያዝበትን ሁኔታ እና በዚህ ዓይነት የሚያዘውን የገንዘብ መጠን ይወስናል ፡፡
5. ባለሥልጣኑ በንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የተመላሽ ጥያቄ ያቀረበው ሰው ሊከፈል ከሚገባው በላይ የከፈለ መሆኑን ሲያረጋግጥ ፡
   ሀ/ ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን በመጀመሪያ በዚህ አዋጅ፣ በጉምሩክ አዋጅ፣ በገቢ ግብር አዋጅ ወይም በኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት የተመዘገበው ሰው ሊከፍል ለሚገባው ማናቸውም ታክስ፣ ቀረጥ፣ ወለድ ወይም መቀጫ እንዲውል ያደርጋል፡፡
   ለ/ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ከተካካሰ በኋላ ተመሳሽ ሊደረግ የሚገባው ቀሪ ገንዘብ ከብር 50 ያላነሰ ከሆነ ለተመዘገበው ሰው ይመለስለታል ፡፡
6. የተመዘገበው ሰው በንዑስ አንቀጽ (5) መሠረትተመሳሽ ሊደረግለት የሚገባው ገንዘብ ያለው መሆኑ ተረጋግጦ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2)በተመለከተው ጊዜ ባለሥልጣኑ ቀሪውን ገንዘብ ያልመለሰ ከሆነ ተመላሹ እስከሚከፈል ድረስ፤ ባለፈው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ ላይ 25 ፐርሰንት ታክሎበት ለተመዘገበው ሰው እንዲከፈለው ይደረጋል፡፡
7. በዚህአዋጅአንቀጽ21 (6) (ለ) የተደነገገውቢኖርምበካፒታልዕቃላይየተከፈለታክስበሚቀጥለውየሂሣብጊዜእንዲቀናነስ ከተደረገበኋላቀሪሂሣብቢኖርባለሥልጣኑይህንንቀሪሂሣብከሂሣብጊዜውቀጥሎባለውየአን ድወርጊዜውስጥለታክስከፋዩተመላሽማድረግአለበት::
8. ባለሥልጣኑበዚህአንቀጽመሠረትየሚከፈለውየታክስተመላሽየሚመራበትየሥጋትሥራ አመራርመርህንየተከተለየተመላሽሥርዓትዘርግቶተግባራዊማድረግአለበት፡፡”

28.<u>የማስተዳደር እና ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት</u>

1. ታክሱን በትክክል የማስላት፣ በወቅቱ የመክፈል እና በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የተመዘገበው ሰው ኃላፊነት ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክሱ አሰባሰብ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በኃላፊነት የተሰጠ በሚሆንበት ጊዜ በጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚመራ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አዋጅ እና በጉምሩክ ሕግ በተደነገገው መሠረት የታክሱ አስተዳደር እንደ አግባብነቱ የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ወይም የጉምሩክ ባለሥልጣን ኃላፊነት ይሆናል፡፡

29.**የታክሱ አወሳሰን**

1. የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሂሳቡን ከመረመረ በኋላ የተመዘገበው ሰው ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አሳንሶ ያስታወቀ መሆኑን የደረሰበት እንደሆነ ተጨማሪ የታክስ ውሣኔ ይሰጣል ፡፡ ሆኖም የዚህ ዓይነቱን ውሣኔ ሊሰጥ የሚችለው ፡
   ሀ/ በተራ ፊደል "ለ" በተመለከተው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር አግባብ ያለው የሂሳብ ጊዜ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ፡ወይም
   ለ/ ታክሱን አሳንሶ የማስታወቁ ተግባር በማጭበርበር ወይም በከባድ ቸልተኝነት ተፈጽሞ ከሆነ በሌሎች ሕጐች ያለ የጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ በማናቸውም ጊዜ ይሆናል ፡፡
2. ባለሥልጣኑ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጨማሪ የታክስ ውሣኔ የሰጠ እና የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ እንዲከፍል የተጠየቀውን ተጨማሪ ታክስ ያልከፈለ ወይም በውሣኔው ላይ ቅሬታ ካለው በአንቀጽ 43 መሠረት ይግባኝ ያላቀረበ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው ፡፡

**ክፍልስምንት**

**የታክስ አሰባሰብ አፈፃፀም**

30.**የግብር አስገቢ ባለስልጣን ሥልጣን እና ተግባር**[89]

1. ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን በሥራ ላይ የማዋል እና የማስፈጸም ኃላፊነት የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ይሆናል ፡፡
2. በማንኛውም ሌላ ሕግ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፤ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ በታክስ ከፋይ የቀረቡ ማናቸውንም መግለጫዎች፤

   ሠነዶችና የሂሳብ መዝገቦች ለማረጋገጥ፤

   ሀ/ ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጣቸው ተቆጣጣሪዎችን ወደ ተመዘገበው ሰው የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ቦታ በመላክ የመክፈያና የመቀበያ ሰነዶችን ፡ የሂሳብ

[89] ንዑስ አንቀፅ (3)፣ (4) እና (5) በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(13) አዲስ የገቡ ናቸው፡፡

መግለጫዎችን ሠነዶችን እና፣ እና የሂሳብ መዝገቦችን ለማመሳከር ለንግድ የተከማቹ ዕቃዎችን ወይም ሌሎች ዕቃዎች ለመመርመር፤

ለ/ ታክስ ከፋዩን ወይም የሂሳብ መዝገቦችን እና ሰነዶችን ወይም መረጃን ለማግኘት የሚችለውን ወይም እነዚህኑ የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠውን ማንኛውንም የታክስ ከፋዩን ተቀጣሪ በአመቺ የግብር አስገቢ መሥሪያ ቤት የሥራ ሰዓቶች እና ጽ/ቤት ተገኝቶ ለሚቀርቡለት ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥና የተባሉትንም ሰነዶች እንዲያቀርብ ለማደረግ፤

ሐ/ ማዘጋጃ ቤት፣ ድርጅት፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውንም የፌዴራል መንግሥት ወይም የክልል መሥሪያ ቤት ጨምሮ ማናቸውም ሰው ስለታክስ ከፋይ የሚያውቀውን መረጃ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ እንዲገልጽ ለማድረግ ይችላል፡፡

3. በታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ ቦታ በመገኘት ምርመራ ለማድረግ ሥልጣን የተሰጣቸው የባለሥልጣኑ ሠራተኞች ማናቸውንም ሕገ ወጥ ደረሰኝ ወይም የሂሳብ ሰነድ ወይም የሂሳብ መዝገብ ካገኙ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳያስፈልግ ሕገወጥ የሆነውን ደረሰኝ ወይም ሰነድ መያዝ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ የተያዘ ወይም የተገኘ ሰነድ በማስረጃነት በፍርድ ቤት ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል።

4. ሕገወጥ ደረሰኞችን ወይም ሰነዶችን ለመስጠት ፍቃደኛ ባልሆነ ግብር ከፋይ ላይ የፖሊስ ኃይል በመጠቀም ማስገደድ ይቻላል።

5. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) አፈፃፀም በባለሥልጣኑ ሠራተኛ ትብብር የተጠየቀ ማናቸውም የፖሊስ ኃይል አባል የመተባበር ግዴታ አለበት።

31.**<u>ታክስ ለመሰብሰብ ሀብት ስለመያዝ</u>**

1. በንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም በዚህ አዋጅ የተጣለው ታክስ የሚፈለግበት ሰው በአንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም በአንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ (2) በተደነገገው መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን የዚህን ታክስ ከፋይ ሀብት በመያዝ ለሚፈለግበት ታክስ እና ንብረቱን ለመያዝ ለተደረገው ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን እንዲውል ለማድረግ ሕጋዊ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

2. ለዚህ ክፍል አፈፃፀም "መያዝ" በማናቸውም መንገድ መያዝን፡ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚፈለግበት ሰው የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት በእጁ

ከሚገኝ ሰው ታክስ መሰብሰብን ይጨምራል፡፡ በንዑስ አንቀጽ(3)እና (6) በተነገረው መሠረት ካልሆነ በስተቀር መያዝ የሚቻለው የመያዙ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በይዞታ ሥር የሚገኝ ንብረት እና የመያዙ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ፀንቶ ያለ ግዴታን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ የታክሱ ባለሥልጣን የታክስ ከፋዩን ሀብት በሚይዝበት ጊዜ የፖሊስ ሠራዊት አባል እንዲገኝሊጠይቅ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሀብቱን ከያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር ከ10 ቀናት ጊዜ በኋላ በሐራጅ ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደ በማናቸውም ሌላ ዘዴ የያዘውን ንብረት መሸጥ ይችላል ፡፡ ሆኖም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ መስሎ በሚታየው ጊዜ ሊሸጠው ይችላል ፡፡

3. ማናቸውም የተያዘ ንብረት ለመያዙ ምክንያት የሆነውን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን በቂ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ፣የታክሱ ባለሥልጣን ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው የታክስ ዕዳ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍለው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የታክስ ዕዳው የሚፈለግበትን ሰው ሌሎች ሀብቶች መያዝ ይችላል ።
4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ ምክንያት ንብረት መያዝ የሚቻለው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሀብቱን የመያዝ ሀሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ካስታወቀው በኋላ ይሆናል ፡፡ በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ማስታወቂያ ሀብቱ ከመያዙ ከ30 ቀን በፊትለታክስ ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል ፡፡
5. የታክሱ ባለሥልጣን የታክሱን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ እና በንዑስ አንቀጽ(4) የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ ታክሱ ወዲያውኑ እንዲከፈል ለማድረግ ጥያቄ ከቀረበና ታክስ ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ንብረትን በመያዝ ታክስ የመሰብሰቡ አፈፃፀም ሕጋዊ ይሆናል ፡፡
6. ማናቸውም ንብረት የተያዘ ወይም እንዲያዝ የታሰበ ከሆነ ስለዚሁ ንብረት ማስረጃ የሚሆን ወይም መግለጫ የያዘ ሰነድ ወይም መዝገብ በእጁ የሚገኝ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ጥያቄ ሲቀርብለት ሰነዱን ወይም መዝገቡን ለማስረጃነት ማቅረብ አለበት፡፡

7. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈፃፀም ላይ ያለ ወይም በዋስትና የተያዘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም በግብር ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጁ የሚገኝ ወይም ለግብር ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሲጠይቀው የያዘውን ሀብትለግብር አስገቢው ባለሥልጣን የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡
8. ማናቸውም ሰው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሲጠይቀው አንድን የተያዘ ንብረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በተያዘው ንብረት መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጠያቂነቱ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት ከሆነው የታክስ ዕዳ መጠን (በታክሱ ዕዳ ላይ የሚታሰበውን ወጪ እና ወለድ ጨምሮ) ሊያልፍ አይችልም፡፡
9. በንዑስ አንቀጽ (8) ከተመለከተው የግል ተጠያቂነት በተጨማሪ ንብረቱን የያዘው ሰው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነው ያለበቂ ምክንያት ከሆነ በንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት የሚፈለገውን የገንዘብ መጠን 50 ፐርሰንት በተጨማሪ እንዲከፍል ይደረጋል።
10. በዚህ አንቀጽ መሠረት በይዞታው ሥር ያለውን ንብረት ያስረከበ ወይም በታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ገንዘብ ከግብር አስገቢው ባለሥልጣን በተጠየቀው መሠረት ገቢ ያደረገ ማናቸውም ሰው ካስረከበው ንብረት ወይም ገቢ ካደረገው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የታክስ ግዴታውን ባልተወጣው ታክስ ከፋይ ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው ከሚፈለግበት ዕዳ ወይም ካለበት ግዴታ ነፃ ይሆናል፡፡

32. <u>በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ</u>

1. ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስ ተከፋይ ከሚሆንበት ቀን አንስቶ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሀብት ላይ ባለሥልጣኑ የቀደምትነትመብት ይኖረዋል።
2. ማናቸውም ሰው ታክስ የመክፈል ግዴታውን ባለመወጣት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በጥፋት ምክንያት ያልተከፈለውን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚደረገው እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል የታክሱ ዕዳ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ንብረቱን

ለመዘገበው አካል የጽሑፍ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ለተመዘገበው ሰው ይሰጣል፡፡

3. በንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው ማስጠንቀቂያ የደረሰው የተመዘገበው ሰው ማሰጠንቀቂያው በደረሰው በ 30 ቀን ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ለመዝጋቢው ባለሥልጣን የተመዘገበው ሰው ሀብት ይሰጣል
4. በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን ፤ መዝጋቢው ባለሥልጣን ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ ንብረቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን ትዕዛዝ እንደማናቸውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የመያዣ ሰነድ ይመዘግባል ፤ ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ታክስ ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በሕግ እንደተጠበቀ መያዣ ወይም እንደማናቸውም ሌላ ዕዳ ወይም ክፍያ ይቆጠራል፡፡

33.<u>ከገዥ ታክስ ስለመሰብሰብ</u>

1. ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ከተመዘገበ ሰው የገዛ ማናቸውም ሰው በፈፀመው የማጭበርበር ተግባር ወይም ያልሆነውን እንደሆነ አደርጐ በመቅረቡ ምክንያት የተመዘገበው ሰው በስህተት ግብይቱ ከታክስ ነፃ እንደሆነ ወይም በዜሮ የማስከፈያ ልክእንደሚከፈልበት አድርጐ የወሰደ እንደሆነ ፤ የታክሱ ባለሥልጣን ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ ገዥው በአቅርቦቱ ላይ ያልተከፈለውን ታክስ እንዲከፍል የታክስ ውሣኔው ማስታወቂያ ይልክለታል፡፡
2. የታክሱ ባለሥልጣን በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለገዥው የሚልከው ማስታወቀያ የሚከተሉትን መረጃዎች የሚይዝ መሆን አለበት፡፡

   ሀ/ ተከፋይ የሆነውን ታክስ፣

   ለ/ ታክሱ መከፈል ያለበትን ቀን፤

   ሐ/የታክሱን ውሣኔ መቃወም የሚቻልበትን ጊዜ፣ ቦታ እና አኳኋን፤
3. በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ የታክስ ውሣኔ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም እንደማናቸውም የታክስ ውሣኔ ሆኖ ይቆጠራል፡፡
4. የንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የታክሱ ባለሥልጣን ታክሱን፣ ወለዱን እና መቀጫውን ከተመዘገበው ሰው ከመጠየቅ አያግደውም፡፡

5. ለንዑስ አንቀጽ (4) አፈፃፀም ከገኘው የተሰበሰበ ታክስ ከተመዘገበው ሰው የታክስ ግዴታ እንዲሁም ከተመዘገበው ሰው የተሰበሰበ ታክስ ከገኘው የታክስ ግዴታ ጋር እንዲካካስ ይደረጋል፡፡
6. በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ታክስ፣ ወለድ ወይም መቀጫ የተመዘገበው ሰው የከፈለ እንደሆነ፣ ይህንን የገንዘብ መጠን የተመዘገበው ሰው ከገኘው መጠየቅ ይችላል፡፡

34. **<u>የታክስ አወሳሰንን ሊያደናቅፍ የሚችል ሁኔታ መኖር</u>**

የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የታክሱን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ እና አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ትዕዛዙን የሚደግፍ መግለጫ በማያያዝ የታክስ ከፋዩ የባንክ ሂሳብ እንዲታገድ እና ስለታክስ ከፋዩ የፋይናንስ እንቅስቃሴ መረጃ እንዲሰጠው የአስተዳደር ትዕዛዝ ለባንኩ ሊሰጥ እና ታክሱን ወዲያውኑ መወሰን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከዚህ በላይ የተመለከተውን አስተዳደራዊ ትዕዛዝ ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ ፍ/ቤት ትዕዛዙን እንዲያፀድቅለት ማድረግ አለበት፡፡ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ሥልጣን መጠቀም የሚችለው የታክሱን አወሳሰን ግልጽለማድረግ የሚረዳ መረጃ ለማግኘት ብቻ ነው፡፡

35. **<u>ታክስ ከፋዩ ስላለው ጥበቃ</u>**

በዚህ ክፍል 8 መሠረት የተያዘ ማናቸውም ንብረት የሚያዘው የሚጠበቀው፡ እና የሚመዘገበው በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ብቻ ይሆናል፡፡ ማናቸውም ሌላ የመንግሥት አካል በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘውን ንብረት ማናቸውንም ሌላ ምክንያት መሠረት በማድረግ እንዲሰጠው ወይም እንዲተላለፍለት መጠየቅ አይችልም፡፡ የተያዘ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ በላይ የሆነው ገንዘብ ለንብረቱ ባለቤት ወዲያውኑ ይመለሳል፡፡

36. **<u>የተረካቢው ግዴታ</u>**

1. በዚህ አንቀጽ ውስጥ "ተረካቢ" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝን የተመዘገበ ሰው ሀብት በተመለከተ፤

ሀ/ የኩባንያ የንብረት አጣሪ ሆኖ የተሰየመ፤

ለ/ ከፍርድ ቤት ውጪ ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ ተረካቢ፤

ሐ/ በኪሣራ ውስጥ የሚገኝ ድርጅት ባለአደራ፤

መ/ መያዣ በይዞታው ሥር የሚገኝ፣

ሠ/ የሞተን ሰው ንብረት የሚያስተዳድር፣ ወይም

ረ/ በሕግ ችሎታ የሌለውን ሰው የንግድ ሥራ የሚያካሄድ፣ ማናቸውም ሰው ነው፡፡

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ንብረት ተረካቢ ሆኖ የተሾመ ወይም ንብረት በይዞታው ሥር የተደረገ ተረካቢ ከተሾመበት ወይም ንብረቱ በይዞታው ሥር ከተደረገበት ከሁለቱ ከቀደመው ቀን ጀምሮ በ14 ቀን ጊዜ ውስጥ የተሾመ ወይም ንብረት በይዞታው ሥር ያለመሆኑን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

3. የታክሱ ባለሥልጣን ንብረቱ በተረካቢው ይዞታ ሥር ያለ ሰው የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ለተረካቢው በጽሑፍ ያስታውቃል፡፡

4. ተረካቢው፣

ሀ/ በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በታክስ ባለሥልጣኑ የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ወይም ከማስታወቂያው በኋላ በስምምነት የተደረሰበትን ሌላ የገንዘብ መጠን ከንብረቱ ሽያጭ ላይ ቀንሶ ለብቻው ያስቀምጣል፡፡

ለ/ ተቀንሶ ለብቻው በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ልክ የተረከበው ንብረት ባለቤት ከሆነው ሰው ለሚፈለገው የታክስ ዕዳ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም ከታክስ ቀደምትነት ያለውን ማናቸውንም ዕዳ ሊከፍል ይችላል፡፡

5. ተረካቢው በንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰውን ታክስ በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ተቀንሶ ለብቻው እንዲቀመጥ የተደረገውን የገንዘብ መጠን በዚህ አንቀጽ ለተጠቀሰው ታክስ ካላዋለ ተቀንሶ ለብቻ በተቀመጠው ገንዘብ ልክ በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍልዘጠኝ

## የሂሳብ ሰነዶች

### 37.የሂሳብ ሰነዶችን ስለመያዝ

1. የተመዘገበ ሰው ወይም በዚህ አዋጅ ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ማናቸውም ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሂሳብ ሰነዶች ለ10 ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ማስቀመጥ አለበት፡፡

ሀ/ የተቀበላቸውን የታክስ ደረሰኞቹ ዋንኛ ቅጂ ፣

ለ/ የሰጣቸውን ማናቸውንም የታክስ ደረሰኞችቅጂ፣

ሐ/ ወደአገር ያስገባቸውን ወይም ወደውጭ የላካቸውን ዕቃዎች የሚያሳይ የጉምሩክ ሰነድ፣

መ/ የሂሳብ መዝገቦች፤ እና

ሠ/ ሌሎች የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ የተዘረዘሩ የሂሳብ ሰነዶችን፡፡

2. ለንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም የሂሳብ ሰነድ ማለት የሂሳብ መረጃዎች፣ መዝገቦች፣ በኮምፒውተር ውስጥ የተከማቹ ወይም ሌላ ማናቸውም መረጃ ነው፡፡

## 38.ለውጦችን ስለማሰታወቅ

ማናቸውም የተመዘገበ ሰው፣

1. ስሙ፣ አድራሻው፣ የንግድ ሥራው ቦታ፣ አደረጃጀቱ ወይም ታክስ የሚከፈልበት ዋንኛው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም ግለሰቡ የሚያከናውናቸው ተግባራት ዓይነት፤

2. ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚከናወንበትን አድራሻ ወይም ስም፣የቀየረ እንደሆነ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በ21 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማስታወቅ አለበት፡፡

## 39.ማስታወቂያዎች ስለሚደርሱበት ሁኔታ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን የሚሰጣቸው ማስታወቂያዎች ወይም ሌሎች ሰነዶች በሚከተለው ሁኔታ በፅሑፍ ይደርሳሉ፤

   ሀ/ ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሆነ ሰው በአደራ ፖስታ፣ ወይም በቀጥታ ለግብር ከፋዩ በእጁ በመስጠት ወይም እሱ የሌለ እንደሆነ፤ ከቤተሰቦቹ ውስጥ ለማንኛውም አካለ መጠን ለደረሰ ወይም በመኖሪያው ወይም የሙያ ወይም የንግድ ሥራ በሚሰራበት ሥፍራ ቀጥሮ ለሚያሰራው ማንኛውም ሰው በመስጠት ሆኖም ማስታወቂያውን የሚቀበል ሰው ካልተገኘ ይኸው ማስታወቂያ በግብር ከፋዩ መኖሪያ ቤት በር ላይ ወይም የመኖሪያ ቤቱ ክፊል በሆነ ወይም በንግድ ሥራ አመቺ ሥፍራ በመለጠፍ ፤

   ለ/ ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሆነ ድርጅት በአደራ ፖስታ አማካኝነት በተመዘገበውየድርጅቱ አድራሻ በመላክ ወይም በድርጅቱ የንግድ ሥራ ቦታ ለሚገኘው ማንኛውም የሥራ መሪ ወይም ተቀጣሪ በመስጠት፤

ሐ/ ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ ላልሆኑ ሰዎችበኢትዮጵያ ላለው ወኪል ወይም ወኪሎች በእጅ በመስጠት ወይም የማይገኙ ከሆነ ወኪሉ በሚሰራበት የንግድ ሥራ ቦታ ወይም በሌላ አመቺ በሆነ ሥፍራ በመኖሪያ ቤቱ ላይ በመለጠፍ፤

2. በንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት እርምጃዎች አንዱም በማንኛውም ምክንያት ካልተሳካ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ማንኛውም ጋዜጣ ላይ በማሳተም ሊፈፀም ይችላል። ለማሳተሚያ የወጣው ወጪ በግብር ከፋዩ ላይ ይታሰባል።

## ክፍልአሥር

## ይግባኝ የሚቀርብበት ሥርዓት

### 40. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በታክስ ባለሥልጣኑ ኃላፊ አቅራቢነት በገቢዎች ሚኒስትር ይሰየማሉ፡፡

### 41.ኮሚቴው ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር

1. ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለታክሱ ባለሥልጣን ሆኖ፣

ሀ/በታክስ ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ፣ ወለድ ቀሪእንዲደረግ ወይም የታክስ ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመመርመርና ውሣኔ ለመስጠት፤

ለ/ ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውንም የፅሑፍ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች መሰብሰብ፤

ሐ/ በምርመራ ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ረገድ ቀርቦ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ከታክሱ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው የመጥራት፡

መ/ የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው የታክስ ውሣኔ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ይህንን አዋጅ ጠብቆየተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሥልጣን ይኖረዋል።

2. የአቤቱታ ኮሚቴ ከታከስ ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ካቀረበ ነው፡፡

3. የታክሱ ባለሥልጣን፣ ኃላፊ የኮሚቴውን የውሣኔ ሀሳብ ሊያፀድቅ ወይም በውሣኔ ሀሳቡ ካልተስማማ ምክንያቱን በመግለፅ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል፡፡

42. **መቀጫን ስለማንሳት**[90]

1. መቀጫን ስለማንሳት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚነሳው መቀጫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 47 መሠረት የሚታሰበውን ወለድ አይጨምርም።

43. **ይግባኝ**

1. በባለሥልጣኑ የተላለፈውን የተጨማሪ ታክስ ውሣኔ የሚቃወም ማናቸውም ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም በአቤቱታ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን ተጨማሪ ታክስ 50% (ሃምሳ በመቶ) ባለሥልጣኑ ዘንድ በማስያዝ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቦ የግብር ይግባኝ ጉባዔ ታክስ ከፋዩ በተጨማሪ የተወሰነበትን ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ውሣኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ተጨማሪ ታክስ ካልከፈለ ወይም ይግባኝ ካላቀረበ ጥፋተኛ ነው፡፡[91]
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ካልቀረበ በባለሥልጣኑ የተወሰነው ተጨማሪ ታክስ ትክክለኛና የመጨረሻ ሆኖ ወዲያውኑ ተከፋይ ይሆናል።
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በገቢ ግብር አዋጅ ስለይግባኝ የተደነገጉ አንቀፆች አንደአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰኑታክሶችን በሚመለከት ለሚቀርቡ ይግባኞች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

44. **የማስረዳት ኃላፊነት**

---

[90] በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(14) ተሻሻለ፡፡

[91] በ21/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(15) ተሻሻለ፡፡

የተወሰነው ግብር በዝቷል ወይም የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው ውሣኔ ትክክል አይደለም በሚል በሚቀርብ ክርክር የማስረዳቱ ኃላፊነት የተወሰነውን ታክስ ወይም የባለሥልጣኑን ውሣኔ የሚቃወመው ሰው ይሆናል።

## ክፍል አሥራ አንድ

## አስተዳደራዊ ቅጣቶች

**45. ቅጣቶች**[92]

ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥፋቶች የፈፀመ ታክስ ከፋይ፣

1. ሀ/ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሆኖ ሳይመዘገብ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያከናውን ማናቸውም ሰው ምዝገባው ሳያደርግ በቆየበት ጊዜ ሁሉ ላከናወነው የንግድ ሥራ መክፈል ያለበትን ታክስ 100 ፐርሰንት (አንድ መቶ ፐርሰንት)፤

   ለ/ ተከፋይ የሚሆነው ታክስ እንዲቀንስ ወይም የሚፈቀደው ተቀናሽ እንዲጨምር የሚያደርግ ሀሰተኛ የሆነ የታክስ ደረሰኝ አዘጋጅቶ ያቀረበ ወይም የታክስ ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ በደረሰኙ ላይ የተመለከተውን ወይም በግብይቱ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ100 ፐርሰንት (አንድ መቶ ፐርሰንት) ፤

   ሐ/ ለተጨማሪ ታክስ ያልተመዘገበ ሰው የታክስ ደረሰኝ ሰጥቶ የተገኘ እንደሆነ በሰጠው ደረሰኝ ላይ የተመለከተውንና ገቢ ማድረግ የነበረበትን ነገር ግን ገቢ ሳያደርግ የቀረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ 100 ፐርሰንት (አንድ መቶ ፐርሰንት)በመቀጫነት ይከፍላል።

   መ/ በአንቀጽ 37 በተደነገገው መሠረት ሊይዝ የሚገባውን የሂሳብ ሰነድ ያልያዘ ሰው የሂሳብ ሰነዶቹን ላልያዘበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የዚሁ ክፊል ለሆነው ጊዜብር 2,000 ይቀጣል፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም "ሀሰተኛ ደረሰኝ" ማለት በባለሥልጣኑ ሳይፈቀድ የታተመ ወይም በኮምፒውተር የተዘጋጀ ደረስኝ ወይም የግዢውን ወይም የሽያጩን ሂሣብ ለማሳነስ ወይም ለመጨመር በማሰብ ወይም በቸልተኛነት በሰነዱ ላይ አሀዝ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም ተመሳሳይ

---

[92] መሰረት በቀድሞ ንዑስ አንቀፅ ከ(ሀ) እስከ (መ) የነበሩት የንዑስ አንቀፅ (1) ከ(ሀ) እስከ (መ) ሆነው በ15/6 (2001) አ.609 አንቀፅ 2 (16) ንዑስ አንቀፅ (2) እንደ አዲስ የገባ ነው፡፡

ቁጥር ያለው ደረሰኝ በማትም ወይም በማባዛት ወይም ሁሉንም ቅጂዎች እንደበራሪ መጠቀም ወይም የሚፈቀደው የታክስ ተቀናሽ ወይም የተመላሽ ሂሣብ እንዲጨምር ወይም የማይገባውን ተመላሽ ለማግኘት ወይም ሌላ ማናቸውም የማጭበርበር ተግባር ለመፈጸም የተዘጋጀ ሰነድ ነው።

46.<u>የታክስ ማስታወቂያን በጊዜው ባለማቅረብ ስለሚፈፀም ቅጣት</u>

1. በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም ከተወሰነው በስተቀር፣ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቅ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ፣ ያልተከፈለውን ታክስ 5 ፐርሰንት (አምስት በመቶ) 25 ፐርሰንት (ሃያ አምስት በመቶ) እስኪሞላ ድረስ መቀጫ ይከፍላል።
2. ለመጀመሪያ ወር ወይም የወሩ ክፊል በሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚከፍለው መቀጫ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) አይበልጥም።
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ያልተከፈለ ታክስ ነው የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክሱ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡
4. በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው ቅጣት ቀጥሎ ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም።

   ሀ/ ብር 10,000

   ለ/በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100 ፐርሰንት (አንድ መቶፐርሰንት)
5. ማናቸውም ታክስ ከፋይ በማንኛውም የሂሳብ ጊዜ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ባይኖረውም የታክስ ማስታወቂያ ካላቀረበ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ይቀጣል።[93]

47.<u>ዘግይቶ በተከፈለ ታክስ ላይ ስለሚታሰብ ወለድ</u>

ሀ/ መከፈል በነበረበት ቀን ላልተከፈለ ታክስ፣ መከፈል ከነበረበት ቀን እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

[93] በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2 (17) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚከፈለው ወለድ የማስከፈያ ልክ ባለፈው የሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያወለድ ምጣኔ ላይ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ታክሎበት ይሆናል።

47ሀ.የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ[94]

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፣

1. ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር ሲጠቀም ከተደረሰበት ለተጠቀመበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ ብር 50,000 ይቀጣል፣
2. መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ብር 50,000 ይቀጣል፤
3. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ብር 100,000 ይቀጣል፤
4. የባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናክል ከፈጠረ ወይም በመሳሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ካላስደረገ ብር 25,000 ይቀጣል፣
5. በንግድ ሥራው ለሚጠቀምበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የምርመራ መዝገብ ከመሣሪያው ጎን እንዲቀመጥ ካላደረገ ወይም በሽያጭ መመዝገቢያ የተመዘገበው ዕቃዎች ተመላሽ መደረጋቸው ወይም ደንበኛው የተመላሽ ጥያቄ ማቅረቡ በተመላሽ መዝገብ ላይ በትክክል መመዝገቡ ሳይረጋገጥ የተመሳሽ ደረሰኝ ከሰጠ ብር 25,000 ይቀጣል፣

[94]አንቀጽ 47ሀ፣ 47ለ እና 47ሐ በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2 (18) መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡፡

6. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በስርቆት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ በሦስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ብልሽት ባጋጠመው በሁለት ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 10,000 ይቀጣል፤
7. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚቀመጥበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር 50,000 ይቀጣል፣
8. የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ሲያደርግ ወይም የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ሲሆን ከሦስት ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር 25,000 ይቀጣል፣
9. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ጥቅም ላይ በሚውልበት የንግድ ሥራ ቦታው፣
   ሀ/ የተጠቃሚውን ስም፣ የንግድ ስም፣ የንግዱ ሥራ የሚካሄድበትን አድራሻ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን የዕውቅና እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፣
   ለ/ "የሽያጭ ሠራተኞች መሣሪያው የተበላሸ ከሆነ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኛው የመስጠት ግዴታ አለባቸው" የሚል ማስታወቂያ፣ እና
   ሐ/ "ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ" የሚል ጽሁፍ ያለበት ማስታወቂያ በግልጽና በሚታይ ቦታ ለጥፎ ካልተገኘ ብር 10,000 ይቀጣል፣
10. ሥራ ላይ የዋለውን የሽያጭ ነቁጣ ሶፍት ዌር ባለሥልጣኑ ዕውቅና ባልሰጠው ሰው እንዲቀየር ወይም እንዲሻሻል ካደረገ ብር 30,000 ይቀጣል።

**47ለ.<u>የአቅራቢነት ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ</u>**

ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅናና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፣

1. የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 100,000 ይቀጣል፤
2. በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ብር 500,000 ይቀጣል፣

3. ለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምዝገባ ከባለሥልጣኑ የመሣሪያ መለያ ቁጥር ካልወሰደ ወይም የወሰደውን የመሣሪያ መለያ ቁጥር ለእይታ በሚያመች ቦታ በመሣሪያው ላይ ካልለጠፈ ብር 50,000 ይቀጣል፣
4. በሥራ ላይ ባለ፡ የሽያፅኔጊ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም ስለ መሣሪያው አጠቃቀም በሚያብራራው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ብር 10,000 ይቀጣል፤
5. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመስረቃቸው ወይም ሊጠገኑ በማይቻልበት ሁኔታ በአደጋ ምክንያት ብልሽት የደረሰባቸው መሆኑን አስታውቀው እንዲተኩላቸው ለሚጠይቁ የአገልግሎት ማዕከላት በሦስት ቀናት ውስጥ ለማቅረብ አለመቻሉን ለባለ ሥልጣኑ አስቀድሞ ካላስታወቀ ብር 50,000ይቀጣል፤
6. ውል ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት መረጃ ካልያዘ ወይም ውላቸውን ስላቋረጡ ወይም አዲስ ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 50,000 ይቀጣል፤

### 47ሐ.<u>የአገልግሎት ማዕከል ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ</u>

ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል፣

1. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፊሲካል ማስታወሻ በተተካ በሁለት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 20,000 ይቀጣል፤
2. ውል የገባባቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ካላደረገ ብር 20,000 ይቀጣል፤
3. አቅራቢው ዕውቅና ሳይሰጠውና በባለስልጣኑ ዘንድ ሳይመዘገብ በሥራ ላሰማራው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ብር 50,000 ይቀጣል።

## <u>ክፍል አስራ ሁለት</u>

## <u>የወንጀል ጥፋቶች</u>

### 48.<u>በታክስ ላይ የሚፈጸሙ ወነወጀሎች ስለሚመሩበት ሥነ-ሥርአት</u>

በዚህ አዋጅ ክፍል 12 የተዘረዘሩት በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በመተላለፍ የሚፈፀሙ በመሆኑ ክሱ የሚመሠረተው፣ የሚታየው እና ይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነግሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

49.**<u>ሕግን በመጣስ ታክስ ስላለመክፈል</u>**

ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ታክስ ያላስታወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ወይም መንግሥትን ለማጭበርበር በማሰብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ማናቸውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል። ስለሆነም በዚህ አዋጅ ክፍል 11 መሠረት ከሚጣልበት መቀጫ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ5 ዓመት በማያንስ እሥራት ይቀጣል፡፡

50.**<u>የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ ስለማቅረብ</u>**

1. ማናቸውም ታክስ ከፋይ፡-

   ሀ/ ለታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ አንድን ነጥብ በተመለከተ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ ወይም

   ለ/ለታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ ሊቀርብ ከሚገባው መግለጫ ውስጥ መግለጫውን አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያስቀረ እንደሆነ፣

   የወንጀል ክስ ይመሠረትበታል፡፡

2. የሐሰት መግለጫው የተሰጠው ወይም መካተትየሚገባው ነጥብ የተተወው ያለበቂ ምክንያት የሆነእንደሆነ፣

   ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር 1,000 በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር 10,000 በማያንስ እና ከብር 20,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ1ዓመት በማያንስ እና ከ3 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

   ለ/ አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ታክስ ከብር 1,000 የሚበልጥ ከሆነ ከብር 20,000 በማያንስ እና ከብር 100ሺ.ህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

3. የሐሰት መግለጫ የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ እንዲካተት ያልተደረገው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ

   ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበትያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር 1ሺ.ህ በማይበልጥ እንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር 50,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ5 ዓመት በማያንስ እና ከ10 ዓመት በማይበልጥ እሥራት፣

ለ/ አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ታክስ ከብር 1ሺህ የሚበልጥ ከሆነ ከብር 75,000 በማያንስ እና ከብር 200,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት በማያንስ እና ከ15 ዓመት በማይበልጥ እሥራትይቀጣል፡፡

**50ሀ. <u>ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት አለመመዝገብ</u>**[95]

ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሆኖ ሳይመዘገብየተገኘ ግብር ከፋይ ጥፋተኝነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10,000 እስከ ብር50,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል።

**50ለ. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ባልሆነ ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ማካሄድ</u>**

1. ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ሲያካሂድ ከተገኘ ጥፋተኝነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ክብር 10,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከሁለት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው ሕገወጥ ደረሰኝ ላይ በተመለከተው የገንዘብ መጠን መሠረት መከፈል የነበረበት ታክስ ከብር 100,000 በላይከሆነ የሚጣለው የገንዘብ ቅጣት የታክሱን መጠን ያህል ይሆናል፡፡

**50ሐ. <u>ያልተፈቀደ ደረሰኝ መጠቀም ወይም ማተም</u>**

ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጥ በኮምፒውተር የተዘጋጀ ደረስኝ ወይምደረሰኝ በማሳተም የተጠቀመ ወይም የደረሰኝ ሕትመት አገልግሎት የሰጠ ሰው ጥፋተኝነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና ከሁለት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ያስቀጣል።

**50መ. <u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት ስለሚፈጸም ጥፋት</u>**

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፡-

---

[95] አንቀፅ 50(ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) (ሠ) እና (ረ) በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(19) መሰረት አዲስ የተጨመሩ ናቸው፡፡

1. በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም ያልተመዘገበ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከተጠቀመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፤
2. መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፤
3. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የፊሲካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያን ስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፤
4. የባለሰልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናከል የፈጠረ ወይም በመሣሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ያላስደረገ ከሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፤
5. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የሚገኝበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ስባስሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

50ሠ. <u>በአቅራቢያዎች የሚፈጸሙ ጥፋቶች</u>

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅናና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፦

1. የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፤
2. በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፣

3. በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም በመሣሪያው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሂሥራት ይቀጣል።

50ረ. <u>በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከልና ሠራተኞች የሚፈጸሙ ጥፋቶች</u>

1. ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል አቅራቢው ዕውቅና ያልሰጠውንና በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ ሠራተኛ በሥራ ላይ አሰማርቶ ከተገኘ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።
2. ማናቸውም የሽያጭጋ መመዝገ ቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ያለአገልግሎት ማዕከሉና ያለባለሥልጣኑ ዕውቅና ከፈታታ ወይም ከገጣጠመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሳይበላሽ ሆን ብለ እሽጉን ካነሳ ወይም አካሉን ከቀየረ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ አድራጎቶች ከፈጸመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥ ራት ይቀጣል።

51.<u>የታክሱን ባለሥልጣን ሥራ ስለማሰናከል</u>

1. ማናቸውም ሰው፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይያለን የታክስ ባለሥልጣን ሠራተኛ ተግባር ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ፣ ወይም

ለ/ የአዋጁን አፈፃፀም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ እንደሆነ፣ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ ሲፈረድበት ከብር 1ሺህ በማያንስ እና ከብር 100ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡[96]

[96]በ15/6(2001) አ. 609 አንቀፅ 2(20) ተሻሻለ፡፡

2. የሚከተሉት እና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ተግባሮች የታክሱን ባለሥልጣን ሥራ የማሰናከል ተግባራት ሆነው ይወሰዳሉ፤
   ሀ/ የታክስ ከፋዩን ገቢ አስገኚ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሰነዶችን ሪፖርቶችን፣ ወይም ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ለመመርመር የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቅ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣
   ለ/ የታክሱ ባለሥልጣን ለጥያቄ እንዲቀርብ ሲያዝ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣
   ሐ/ የታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ ቦታ ለመግባት ያለውን መብት መገደብ።

52.<u>ለውጥን ያለማስታወቅ</u>

አንቀጽ 38 በሚያዘው መሠረት በሁኔታዎች ላይ የተደረጉ ለውጦችን ለታክሱ ባለሥልጣን ያላስታወቀ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፣

ሀ/ ጥፋቱ የተፈፀመው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከብር 10ሺ,ህ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና በ1 ዓመት እሥራት፤

ለ/ በሌሎች ሁኔታዎች ከብር 5ሺ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና በ6 ወር እሥት ይቀጣል።

53.<u>በታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኞች የሚፈፀሙ ጥፋቶች</u>[97]

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም በታክስ ባለሥልጣኑ የተቀጠረ ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ተቀጣሪየነበረ፦
   ሀ/ በሕግ መሠረት ሊያገኘው ከሚገባ ክፍያ ወይም ሽልማት ውጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ለክፍያው ወይምለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይምየተቀበለ፣ ወይም
   ለ/ ከታክስ በሚገኘው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ

---

[97]በ15/6(2001) አ.609 አንቀፅ 2(21) የዚህ አንቀጽ ቀድሞ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የነበሩት ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ሆነው ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) አዲስ ገብተዋል፡፡

በታክስ ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ ወይም በምሥጢር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50,000 የማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት በማያንስ ከ20 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. የባሥልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ደንብና መመሪያዎችን በመተላለፍ፤

   ሀ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፊታታ ወይም የገጣጠመ ወይም የሰርቪስ ሠራተኛ በሌለበት ሥራ ላይ እንዲውል የፈቀደ ወይም የመሣሪያውን መለያ ቁጥር ያቀያየረ እንደሆነ፣ ወይም

   ለ/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚው ወይም በአገልግሎት ማዕከሉ ወይም በሠራተኛው ወይም በአቅራቢው የተፈጸመን ማናቸውንም ሕገ ወጥ አድራጎት እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለባስሥልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ፣

ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

3. የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ ያለበቂ ምክንያት ጉዳይን በማጓተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

4. የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የተቀጠረ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ በንግድ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፣

   ሀ/ ታክስን በማስፈፀማ ረገድ ባለው ሥልጣን ወይም ግዴታ ምክንያት ያወቀውን የሌላ ሰው ማናቸውንም መረጃ ለማናቸውም ሌላ ሰው ወይም የዚያ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፤

   ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስን በማስፈፀም ረገድ ያለውን ሥልጣን ለማስፈፀም ወይም የሥራ ግዴታውን ለመወጣት እንዲያስችል በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድ

የሚገኘውን ማናቸውንም መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10ሺህ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ2 (ሁለት) ዓመትበማያንስ ከ5 (አምስት) ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ፣

ሀ/ ማናቸውም ሰነድ ወይም መረጃ:-

i. ለዚህ አዋጅ ወይም ለማናቸውም ገንዘብ ነክ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፤

ii. በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነትለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለዋናው ኦዲተር፣

iii. መረጃ ለመለዋወጥ፣ ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር ባደረገችው ስምምነት መሠረት አግባብ ላላቸው የሌሎች አገሮች ባለሥልጣኖች፣

iv. በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነትለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለሥነ-ምግባርና ለፀረ ሙስና ኮሚሽን፣

v. ከዚህ በላይ ላልተገለፀ ለማናቸውም ሕግ አስፈፃሚ መ/ቤት ግዴታውን ለመፈፀም የሚያስችለው መረጃ እንዲሰጠው ከገቢዎች ሚኒስቴር በፅሑፍ ሲታዘዝ፡፡

ለ/ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ አንድን ሰው ለይተው የማይጠቅሱ መረጃዎችን ለማናቸውም በመንግሥት ገቢ ሥራ ላይ ለሚያገለግል እና ለስታትስቲክስ መ/ቤት ሠራተኛ ከመስጠት አያግደውም፡፡

## 54.<u>ሳይፈቀድ ታክስ ስለመሰብሰብ</u>

ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ሳይፈቀድለት ታክስወይም እንደታክስ የሚታይ ሌላ ክፍያ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ ወንጀል የፈፀመ ሆኖ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50,000 የማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ5 ዓመት በማያንስ ከ10 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

**55.መርዳት ወይም ማበረታታት**

ማናቸውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ የረዳ፣ያበረታታ፣ ያነሳሳ ወይም በምሥጢር የተባበረ እንደሆነ እንደዋንኛው ጥፋተኛ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ ጥፋት ይፈፅማል፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የፈፀመ ሰው፤ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ዕርዳታውን ወይም ትብብሩን ለሰጠበት ጥፋት ከተወሰነው የገንዘብ እና የእሥራት ቅጣት ባልበለጠ በገንዘብ እና በእሥራት ይቀጣል፡፡

**56.በድርጅቶች የሚፈፀም ጥፋት**

1. በንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አሥኪያጅ የሆነ ማናቸውም ሰው በድርጅቱ የተፈፀመውን ጥፋት እንደፈፀመ ተቆጥሮ በዚህ አቀጅ የተጣለው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ወይም አዋጁ እንደ ታክስ የሚቆጥረውን ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ገቢ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመበት ጊዜ ወይም ጥፋቱ ከተፈፀመበት ጊዜ አስቀድሞ በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የነበሩ ሰዎች ከድርጅቱ እና ከሌላው ሰው ጋር በአንድነትና በተናጠል የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለሚፈልገው ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች ተጠያቂ ይሆናሉ።
3. በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገጉት፡-

   ሀ/ ጥፋቱ የተፈፀመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ፡

   ለ/ አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን፣ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግለሰቡ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ፣ ተፈፃሚ አይሆኑበትም።
4. ለንዑስ አንቀጽ (1)እና (2) አፈፃፀም “ሥራ አስኪያጅ” ማለት

   ሀ/ የሽርከና ማኅበርን በሚመለከት የሽርክናው ማኅበር አባል ወይም የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም ከሁለቱ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ለ/ ኩባንያን በሚመለከት የኩባንያው የሥራ መሪ፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከእነዚህ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ

ሐ/ የሰዎችን ኅብረት በሚመለከት የኅብረቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በዚሁ ኃላፊነት እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ነው።

57. <u>በተረካቢዎች የሚፈፀም ጥፋት</u>

1. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ (4) በተደነገገው መሠረት ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ፣ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ብር 5ሺ የገንዘብ መቀጫ እና በ1 (አንድ) ዓመት እሥራት ይቀጣል።
2. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ለታክስ ክፍያ የሚውለውን ገንዘብ ለይቶ ባለማስቀመጡ ምክንያት በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ከገንዘብና እሥራት መቀጫው በተጨማሪ ለይቶ ያላስቀመጠውን የገንዘብ መጠን ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲያደርግ ሊያዝ ይችላል፡፡

58. <u>የታክስ ዴቢት እና የታክስ ክሬዲት ሰነዶችን ያለመስጠት</u>

1. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የታክስ ዴቢት ወይም የታክስ ክሬዲት ሰነድ ያልሰጠ የተመዘገበ ሰው፡ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ በብር 10,000 የገንዘብ መቀጫ እና በ1 (አንድ) ዓመት እሥራት ይቀጣል።
2. በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጪ የታክስ ዴቢት ወይም የታክስ ክሬዲት የሰጠ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፣

   ሀ/ ጥፋቱን የፈፀመው ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ በብር 20,000 የገንዘብ መቀጫ እና በ3 (ሦስት) ዓመት እሥራት፣ ወይም

   ለ/ በሌሎች ሁኔታዎች በብር 10,000 የገንዘብ መቀጫ እና በ1 (አንድ) ዓመት እሥራት ይቀጣል።

59.<u>የጥፋተኞችን ስም በጋዜጣ አትሞ ስለማውጣት</u>

1. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 48-58 የተደነገጉትን የወንጀል ጥፋቶች በመፈፀም የተፈረደባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር በየጊዜው በዕለታዊ ጋዜጦች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ታትሞ የሚወጣው ዝርዝር፡-

ሀ/ የድርጅቱን ወይም የግለሰቡን ስም እና አድራሻ፣

ለ/ ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን የወንጀሉን አፈፃፀም ዝርዝር፣

ሐ/ ጥፋቱ የተፈፀመበትን የግብር ዘመን ወይም ዘመኖች፣

መ/ ሳይከፈል የቀረውን ግብር መጠን፣

ሠ/ በተጨማሪ እንዲከፍል የተወሰነበት ግብር ካለ ይህንኑ፡፡

## ክፍል አሥራ ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 60.ታክስ ያለመክፈል ዕቅድ

1. በዚህ አንቀጽ ውስጥ፣ "ዕቅድ" በግልፅ ወይም ግልፅ ባልሆነ መንገድ የተደረገ ቢሆንም ባይሆንም፣ በሕግ ሥርዓት ውስጥ ተፈፃሚ ሊደረግ የማይችል ወይም ተፈፃሚ እንዲሆን የታቀደ ቢሆንም ባይሆንም ስምምነትን፣ ማመቻቸትን፣ ቃልኪዳን መግባትን ወይም አንድ ነገር ለመፈፀም መስማማትን እንዲሁም ዕቅድ፣ ሀሳብ ማቅረብ፣ የአንድ ድርጊት ሂደት ወይም የአንድን ድርጊትአካሔድን ይጨምራል፤

"ታክስ ያለመክፈል"

ሀ/ ማናቸውም ሰው ሊከፍል የሚገባውን ታክስ መቀነስን፣

ለ/ በአንቀጽ 21 መሠረት አንድ ታክስ ከፋይ ሊያገኝ የሚገባውን የታክስ ማካካሻ ወይም ተመላሽ የሚደረግለትን ታክስ ማሳደግን፣

ሐ/ ማናቸውንም ሌላ ታክስ ያለመክፈል ድርጊት ወይም የታክስ ክፍያን ማዘግየትን፣

ይጨምራል።

2. በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀፆች የተደነገገው ቢኖርም የታክሱ ባለሥልጣን፤

ሀ/ ማናቸውም ሰው በተዘረጋው ዕቅድ ታክስ ላለመክፈል የቻለ መሆኑን የተረዳ፣ ወይም

ለ/ የተዘረጋውን ዕቅድ ይዘት በሚመረምርበት ጊዜ ዕቅዱ የተዘረጋው በዕቅዱ ተሳታፊ ለሆነ ሰው ወይም ከተሳታፊዎቹ ሰዎች ለአንዱ ታክስ ያለመክፈል ጥቅም ለማስገኘት መሆኑን ያመነ እንደሆነ፣ ዕቅዱን እንዳልነበር አድርጎ በመቁጠር ታክስ ያለመክፈል ጥቅም ያገኘው እና በዕቅዱ ተሳታፊ የሆነው ማናቸውም ሰው ሊከፍል የሚገባውን ታክስ እንዲከፍል የመወሰን ወይም

ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ በሚያምንበት አኳኋን ታክስ ባለመከፈል የተገኘውን ጥቅም ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የሚያስችል ውሣኔ ለመስጠት ይችላል፡፡

61.**<u>የገንዘብምንዛሪ</u>**

1. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ማናቸውም የገንዘብ መጠን በብር መገለፅ አለበት።
2. የገንዘቡ መጠን የተገለፀው በብር ያልሆነ እንደሆነ፣

ሀ/ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎችን በሚመለከት፣ በኢትዮጵያ የጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው የምንዛሪ ስሌት መሠረት የገንዘቡ መጠን ይወሰናል፡፡

ለ/ በሌሎች ማናቸውም ሁኔታዎች የገንዘቡ መጠን ወደ ብር የሚለወጠው፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የታክሱ ስሌት በሚከናወንበት ጊዜ የሚሠራበትን የምንዛሪ ተመን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

62.**<u> ምዝገባ እንዳይፈፀምባቸው የተከለከሉ ዕቃዎች</u>**

በማናቸውም ሕግ ምዝገባ እንዲፈፀምባቸው የታዘዘ ዕቃዎችን እንዲመዘግብ ኃላፊነት ለተሰጠው ባለሥልጣን የባለቤትነት ስም ለውጥ የሚደረግባቸውን ወይም ወደአገር የገቡ መመዝገብ ያለባቸው ዕቃዎች ምዝገባ አንዲደረግለት የሚጠይቅ ሰው፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባው ታክስ ወደአገር በገቡት የሚመዘገቡ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ መሆኑን ወይም በዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባ ታክስ ያለመኖሩን የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ወይም ሌላ ማናቸውም የጉምሩክ ሰነድ፣ ወይም

ለ/ ዕቃዎቹን ያቀረበ የተመዘገበ ሰው የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው ፎርም መሠረት የሰጠው በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ታክስ የከፈለ ወይም የሚከፍል መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣ ወይም

ሐ/ መመዝገብ ያለባቸው አቅርቦቶች ወይም ወደአገር የገቡ ዕቃዎች ከታክሱ ነፃ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ በታክሱ ባለሥልጣን የተሰጠ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር መዝጋቢው ባለሥልጣን ምዝገባ ማከናወን የለበትም፡፡

63.**<u> የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

1. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት ባሉት ስድስት ወራቶች በሥራ ላይ ባለው የሽያጭና ኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት ታክስ የተከፈለባቸው ዕቃዎች በእጁ

የሚገኙ የተመዘገበ ሰው በሸያጭ ታክሱ የማስከፈያ ልክ መሠረት በአንቀጽ 21 የተመለከተው የታክስ ተቀናሽ ተጠቃሚ ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው ተቀናሽ ተፈፃሚ የሚሆንበት አኳኋን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

64.<u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ትክክለኛ አተረጓጎም የሚያግዙ ወይም በዚህ አዋጅ በውክልና የተሰጠውን ሥልጣን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦችን፣ እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ መልካም አፈጻጸም መመሪያ ያወጣሉ።

65.<u>ስለመሻር</u>

1. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 68/85/እንደተሻሻለ/ ተሠርዟል፡፡
2. በሽያጭና ኢክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት መከፈል ሲገባው ይህ አዋጅ በሥራ ላይ እስከዋለበት ቀን ድረስ ያልተከፈለ የሽያጭ ታክስ በዚያው አዋጅ መሠረት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

66.<u>የአዋጁ ተፈፃሚነት</u>

ይህ አዋጅ ከታኅሣሥ 23 ቀን 1995 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 27 ቀን 1994 ዓ.ም.**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 79/1995 ዓ.ም

## የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 64 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል 1

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡—

   1. "ባለሥልጣን" ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነው፤
   2. "የጉምሩክ ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፤
   3. "ሚኒስትር"እና "ሚኒስቴር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገቢዎች ሚኒስትር እና የገቢዎች ሚኒስቴር ነው፤
   4. "አዋጅ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/1994 ነው፤
   5. "ታክስ"ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው።

3. **የዕቃ አቅርቦት እና አገልግሎት መስጠት**

   1. ለአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (3) አፈፃፀም ለሠራተኞች የሚቀርብ ዕቃ እና የሚሰጥ አገልግሎት የሚባለው የታክሱ መሠረት የሆነውን ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ትርፋማነት ከፍ በማድረግ ሂደት ወይም እንቅስቃሴውን ለማሻሻል ለሠራተኞች የሚቀርብ እና የሚሰጥ አገልግሎት

ሲሆን፣ ይህ እንቅስቃሴ በአዋጁ አንቀጽ 8 ነፃ ካልተደረገ በስተቀር ታክስየሚከፈልበት ይሆናል፡፡

2. ለሠራተኞች የሚቀርብ ዕቃ እና የሚሰጥ አገልግሎት ያለክፍያ ወይም ከገበያ ዋጋ በታች በሆነ ክፍያ የተሰጠ ቢሆንምበተገቢ ክፍያ እንደተገኘ ተቆጥሮ ታክስ ይከፈልበታል፡፡

3. አሠሪው በማበረታቻ መልክ ለሠራተኛው በሚያቀርበው ዕቃ እና አገልግሎት ምትክ፤

   ሀ/ ለሠራተኛው አስቀድሞ በጥሬ ገንዘብ የከፈለ፣

   ለ/ ስለሠራተኛው ሆኖ ለአቅራቢው ክፍያ የፈፀመ፣

   ሐ/ ሠራተኛው አስቀድሞ ያወጣውን ወጪ የተካለት እንደሆነ በዚህ ዓይነት የተሰጡት ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ከታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ አቅርቦቶች ስላልሆኑ ታክስ ከፋዩ ማናቸውንም የዚህ ዓይነቱን ወጪ የታክስ ማካካሻ ሊጠይቅበት አይችልም፡፡

4. አሠሪው በገዛቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ (እንደ መንገደኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ላሉ) የታክስ ማካካሻ ካላገኘ፣ እንደዚህ ያሉትን አቅርቦቶች ለሠራተኞች የሰጠ እንደሆነ እንዲህ ያለው አቅርቦት ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ጋር የተያያዘ አቅርቦት ተደርጎ ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም፡፡

5. የተመዘገበው ሰው ከታክሱ ነፃ የሆነ አገልግሎት (በኩባንያው በሚካሄድ ክሊኒክ ውስጥ የሚሰጥን የሕክምና አገልግሎት የመሳሰሉትን) የሚሰጥ ከሆነ ፣ አገልግሎቱ ታክስ አይከፈልበትም፡፡ አሠሪው ከታክሱ ነፃ ለሆኑ አገልግሎቶች ለዋሉ ገዥዎች ለተከፈለው ታክስ በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት ማካካሻ የማግኘት መብት አይኖረውም።

6. የዕቃው ዋጋ ክፍያ በየጊዜው በሚፈጸምበት ሽያጭ ወይም ተከራዩ በኪራዩ የውል ዘመን መጨረሻ የዕቃው ባለቤት በሚሆንበት የኪራይ ውል (በአንድነት የዱቤ ሽያጭ ውል በሚል በሚጠቀሱት) የተሸጠ ዕቃ የተመለሰ እንደሆነ የዱቤ ግዥ ፈጽሞ የነበረው ሰው ዕቃውን መልሶ ለሚረከበው ሰው በዱቤ ሽያጭ ስምምነት መሠረት ዕቃ እንዳቀረበ ይቆጠራል ፡፡ ስለሆነም የዱቤ ግዥ ፈጽሞ የነበረው ሰው የተመዘገበ ከሆነ ዕቃው የዱቤ ግዥ የፈጸመው ሰው የንግድ ሥራ ሀብት አካል ያለመሆኑ ወይም ታክስ ከሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ

ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ያለመዋሉ ካልተረጋገጠ በስተቀርበዚህ ዓይነት የቀረበው ዕቃ የዱቤ ግዥ የፈጸመውን ሰው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለማካሄድ እንደዋለ ይቆጠራል፡፡

7. በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የሚሸጠው የሎተሪ ቲኬት አገልግሎት መስጠት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል ፡፡
8. አንድ አቅርቦት በተወሰነ መቶኛ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት እና በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት በማጣመር የያዘ በሚሆንበት ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አንደኛው አቅርቦት ዋንኛውን አቅርቦት ለማሟላት ሲባል የሚፈጸም ካልሆነ በስተቀር እያንዳንዱ አቅርቦት ራሱንየቻለ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ ይወስዳል።
9. በቅጥር ውል መሠረት ተቀጣሪ ለአሠሪው የሚሰጠው አገልግሎት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት አይደለም ።
10. በአደራ ሽያጭ ውል መሠረት የሚቀርብ እና በውክልና አቋም ለሚሠራ የሚተላለፍ ዕቃ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት አይደለም ።
11. በአዋጅ ቁጥር 249/1993[98] የተዘረጋው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች ከማምረቻ መጋዘን ወጥተው ለገበያ ከዋሉ ወይም ሌሎች በአዋጁ በተዘረጋው ሥርዓት የሚሸፈኑ ዕቃዎች ለገበያ የዋሉ እንደሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደዋሉ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ስለሆነም ዕቃዎቹ በአገር ውስጥ ገበያ ሲሸጡ በመደበኛው የማስከፈያ መጣኔ መሠረት ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች የሚሆኑ ሲሆን ፤ ለውጭ ገበያ ሲሸጡ በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይች ይሆናሉ፡፡
12. በወካዩ ስም ለሚሠራ ወኪል የሚቀርብ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለወካዩ የቀረበ ሆኖ ይቆጠራል።

4. <u>ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ</u>

[98] ስራ ላይ ያለው አዋጅ 18/62(2004) አ.768 ነው፡፡

1. በአዋጁ አንቀጽ 6 ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለተሰጠው ትርጉም አፈፃፀም ማናቸውንም ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከመጀመር ወይም ከማቋረጥ ጋር በተያያዘ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር በዚሁ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃቀሴ ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደተከናወነ ተግባር ይቆጠራል፡፡
2. ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚከተሉትን አይጨምርም ፤
   ሀ/ በአመዛኙ ለግል መዝናኛ ወይም ትርፍ ጊዜን ለማሳለፍ በግለሰብ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ወይም በግለሰብ ቢከናወኑ ኖሮ እንደ ግል መዝናኛ ወይም ትርፍ ጊዜን ማሳለፊያ ሆነው የሚቆጠሩ በድርጅቶች የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፣
   ለ/ ከታክሱ ነፃ የተደረጉ አቅርቦቶችን ማከናወንን የሚጨምር እስከሆነ ድረስ ማናቸውም ሌላ እንቅስቃሴ፡፡

5. <u>ዕቃዎች ወደ አገር ሲገቡ ስለሚከፈል ታክስ</u>

1. አዋጁ በተለየ ሁኔታ እንዲፈጸም ካልወሰነ በስተቀር፣ ዕቃዎችን ወደ አገር ስለማስገባት፣ ስለማስተላለፍ፣ ወደ ጠረፍ ስለማጓጓዝ፣ የጉምሩክ ፎርማሊቲን ስለማስፈጸም፣ ስለቀረጥና ታክስ ክፍያ፣ የተከፈለን ቀረጥ ስለመመለስ በጉምሩክ አዋጅ የተደነገጉት በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ በልዩ ሁኔታ እንዲፈጸሙ፣ ተሻሽለው እንዲሠራባቸው እና ከሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣሙ የተደረጉት እንደተጠበቀ ሆነው፣ አግባብነት እስካላቸው ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስ በሚከፈልባቸው ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2. ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደ አገር በሚገቡበት ጊዜ አስመጪው ለጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን ማቅረብ እና በዚሁ መሠረት ተገቢውን ታክስ መክፈል አለበት፡፡
3. ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ዲክላራሲዮን ፣
   ሀ/ የጉምሩክ ባለሥልጣን በሚወስነው ቅፅ የተዘጋጀ፣
   ለ/ ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ለማስላት የሚያስችሉ አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ፣
   ሐ/ የጉምሩክ ባለሥልጣን በተለይ በሚወስነው አኳኋን የሚቀርብ፣ መሆን አለበት።

4. የጉምሩክ ባለሥልጣን፣

   ሀ/ ስለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሆኖ ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ በአዋጁ የተጣለውን ታክስ የመሰብ ሰብ፣ የአስመጪውን ስም እና የታክስ ከፋይመለያ ቁጥር (ካለው) ወደአገር የገቡትን ዕቃዎች የኢንቮይስ ዋጋ መያዝ እና

   ለ/ በፖስታ ቤቶች በኩል ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ የጉምሩክ ባለሥልጣንን ወክሎ እንዲሰበሰብ ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ጋር ስምምነት ማድረግ፣ አለበት።

5. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ አስመጪዎች ዕቃዎች ወደአገር በሚገቡበት ጊዜ ታክሱን ከሚከፍሉ በስተቀር በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 249/1993 የተዘረጉት ሌሎች ሥርዓቶች ተጠቃሚ የሆኑ ሌሎች አስመጪዎች ወደአገር የሚያስገቧቸው ታክስ አይከፈልባቸውም።

6. <u>**አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ**</u>

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ(3) ንዑስ አንቀጽ 3 በዱቤ ሽያጭ ውል የተሸጠ ዕቃ የተመለሰ እንደሆነ የዕቃ አቅርቦት እንደሆነ እንደሚቆጠር ያመለክታል። ስለሆነም አቅርቦት ተፈፀመ የሚባለው፤

   ሀ/ ዕቃዎቹ ተመላሽ በተደረጉበት ቀን፣ ወይም

   ለ/ በዱቤ የገዛው ሰው በማናቸውም ሌላ ሕግ በዱቤ ሽያጭ ውሉ ያለበት ግዴታና መብት እንዲፀና የተደረገ ከሆነ፣ በዚህ ዓይነቱ ሕግ በዱቤ የገዛው ሰው ግዴታና መብት እንዲፀና ከተደረገበት የመጨረሻ ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን፣ ነው፡፡

2. የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (9) ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ (ወይም ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ክፊል) በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ድርጅት የተላለፈ እንደሆነ የዕቃ አቅርቦት እንደሆነ እንደሚቆጠር ያመለክታል። ስለሆነም አቅርቦቱ ተፈፀመ የሚባለው በንዑስ አንቀጽ (9) መሠረት የመተላለፉ ተግባር ሲፈፀም ነው።

3. የዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (11) በአዋጅ ቁጥር 249/1993 የተዘረጋው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች የተሸጡ እንደሆነ (በአገር ውስጥ ገበያ ላይ የተሸጡትን ጭምር) በኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ወይም ይህንኑ

እንቅስቃሴ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደዋሉ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ያመለክታል። አቅርቦቱ ተከናወነ የሚባለው ዕቃዎቹ ለአገር ውስጥ ገበያ ሲውሉ ወይም ለውጭ ገበያ ሲላኩ ይሆናል።

7. <u>የአቅርቦት እሴት</u>

   1. ለአንድ የተለየ ደንበኛ በልዩ አስተያየት የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር ዕቃው በቀረበበት ወይም አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ በሂሳብ በታየው የዋጋ ቅናሽ ወይም የዋጋ ተመላሽ መጠን የአቅርቦቱ እሴት ሊቀንስ ይችላል።አቅርቦቱ ከተፈፀመ በኋላ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ በአዋጁ አንቀጽ 13 በተደነገገው መሠረት በሂሳብ መታየት ይኖርበታል።
   2. የአቅርቦቱ ዋጋ በአዋጁ የተጣለውን እና ተለይቶ በሂሳብ ያልታየውን ታክስ የሚያካትት ከሆነ፣ የአቅርቦቱ እሴት የሚሆነው ከዋጋው ላይ በዋጋው ውስጥ የተካተተው የታክስ መጠን ተቀንሶ ይሆናል፡፡
   3. የተመዘገበ ሰው የታክስ ቅናሽ ያገኘባቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በሙሉ ወይም በከፊል ታክስ ከሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውጪ ለሌላ ተግባር ያዋላቸው እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) በዚህ ዓይነት ለተለየ ጥቅም የዋሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ታክስ በሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደዋሉ እንደሚቆጠር ያመለክታል። የገቢዎች ሚኒስትር በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ለሌላ አገልግሎት የዋሉ አቅርቦቶችን እሴት የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
   4. የዕቃው ዋጋ ክፍያ በየጊዜው በሚፈፀምበት ሽያጭ ወይም ተከራዩ በኪራዩ የውል ዘመን መጨረሻ የዕቃው ባለቤት በሚሆንበት የኪራይ ውል (የዱቤ ሽያጭ ውል) የሚቀርቡ ዕቃዎች እሴት የአቅርቦቶች የጥሬ ገንዘብ እሴት ነው፡፡ በዱቤ ሽያጭ ውል የሚቀርቡ ዕቃዎች “የጥሬ ገንዘብ እሴት”ማለት የሚከተሉት ድምር ይሆናል፡፡

      ሀ/ ሻጩ ወይም አከራዩ ባንክ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም በሚሆንበት ጊዜ፣

      i. ባንኩ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም ለዕቃዎች የፈፀመው ትክክለኛ ክፍያ ወይም የዕቃዎቹ የገበያ ዋጋ ከሁለቱ ከፍ ያለው፣ እና

ii. ባንክ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም ወጪውን የሸፈነው የዕቃዎቹ የተከላ፣ የግንባታ እና የመገጣጠም ሥራ ወጪ፣ ወይም

ለ/ ሻጩ ወይም አከራዩ ሌላ አቅራቢ የሆነ እንደሆነ፣

i. አቅራቢው በመደበኛ አፈፃፀም ዕቃዎቹን እጅ በእጅ የሚሸጥበት ዋጋ፣

ii. አቅራቢው ለተከላ፣ ለግንባታ እና ለመገጣጠም ያወጣው ወጪ፣

5. በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (6)መሠረት በዱቤ ግዥ ውል የተገዛ ዕቃ ለሻጩ በመመለሱ በዱቤ የገዛው ዕቃ እንዳቀረበ የሚቆጠር ሲሆን፣ የአቅርቦቱ ዋጋ ዕቃው በተመለሰበት ጊዜ ተመላሽ ያልተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቀሪ ሂሳብ ይሆናል፡፡

6. በንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተው የአቅርቦቱ ቀሪ ሂሳብ የዱቤ ገዥው በዱቤ ሽያጭ ውሉ መሠረት የከፈለው ሂሳብ ከአቀርቦቱ ዋጋ ላይ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ነው፡፡ በመሆኑም በውሉ መሠረት ተዋዋይ ወገኖች ባላቸው መብትና ግዴታ መጠን የተከፋፈለው ሂሳብ በሚደርሳቸው ልክ የአቅርቦቱ የጥሬ ገንዘብ ዋጋ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡

7. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር249/1993 ተፈፃሚ የሚሆንባቸው፣

ሀ/ ለውጭ ገበያ የቀረቡ፣ ወይም

ለ/ በአገር ውስጥ ለሽያጭ የዋሉ ነገር ግን ወደ ውጭያልተላኩ ዕቃዎች ዋጋ የገበያ ዋጋ ይሆናል፡፡

8. በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) (መ) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ የሚተላለፍን በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት የሚገዛ ሰው፣ ከገዛው ዕቃ ውስጥ ከፊሉን ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት ሳይሆን ለሌላ ተግባር ያዋለው እንደሆነ የዚህ ዓይነቶች አቅርቦቶች ገዥው ታክስ በሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንዳዋላቸው እንደሚቆጠር የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (11) ይደነግጋል፡፡

9. በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (8) የተመለከተው አቅርቦትዋጋ ነው ተብሎ የሚወሰደው ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለመግዛት ከተፈፀመው ክፍያ ላይ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው እንዲውል ለታቀደበት

ጠቅላላ ተግባር ከተከፈለው ወጪ ላይ ለዚሁየንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ባልዋለው መጠን ተቀንሶ የሚቀረው ነው።

8. <u>የግዴታ ወይም የፈቃደኝነት ምዝገባ እናሥርዓቱ</u>

1. የታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ(1) ከተመለከተው የገንዘብ መጠን የሚበልጥ ወይም ሊበልጥ የሚችል መሆኑን የታክሱ ባለሥልጣን ያመነበት ቢሆንም ለሚከተሉት ምክንያቶች ታክስ ከፋዩን ከምዝገባ ነፃ ሊያደርገው ይችላል፡፡
   ሀ/ በታክስ ከፋዩ የሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከተቋረጠ፣ ወይም የንግድ ሥራው እንቅስቃሴ አቅም እና ስፋት በከፍተኛ ደረጃ እና በዘላቂነት እየቀነሰ ከሄደ ወይም
   ለ/ በታክስ ከፋዩ በሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት በጥቅም ላይ የሚውሉ የካፒታል ዕቃዎችን ለመተካት የሚውሉ የካፒታል ዕቃዎች አቅርቦት ያለ እንደሆነ ነው ፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (4) ምዝገባው የፀና የሚሆንበት ቀን ተደንግጓል። ተመዝጋቢው ምዝገባው የሚጸናበትን ቀን ሊመርጥ የሚችል ቢሆንም፣ የታክሱ ባለሥልጣን ለራሱ ምክንያቶች ምዝገባው ከሂሳብ ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ የፀና እንዲሆን ሊወስን ይችላል።

9. <u>በተናጠል ስለመመዝገብ</u>

1. ለአዋጁ አፈፃፀም የተመዘገበ ሰው እና በተናጠል የተመዘገቡ የዚሁ ሰው የንግድ ሥራ ክፍሎች እንዲሁም በተናጠል የተመዘገቡ የአንድ የተመዘገበ ዋና መ/ቤት አካል የሆኑ ክፍሎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ሆነው ይቆጠራሉ ፡፡
2. በተናጠል የተመዘገበ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አካል በእያንዳንዱ የታክስ ዘመን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት (የአዋጁ አንቀጽ26)። እያንዳንዱ በተናጠል የተመዘገበ የአንድ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አካል የተመዘገበ ሰው ያለበት ግዴታዎች ሁሉ የሚኖሩት ሲሆን፣ የዋናው ድርጅት አካል እንደሆነ ይቀጥላል።
3. የተመዘገበ ሰው እንደ አንድ ድርጅት መመዝገቡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ እና ሌሎች የታክስ ግዴታዎችን በመፈጸም ረገድ

ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትልበት ከሆነ የንግድ ሥራው አካል የሆኑ ክፍሎች በተናጠል እንዲመዘገቡለት መጠየቅ ይችላል፡፡ የታክሱ ባለሥልጣን የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ሲቀርብለት አንድ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ እና ሌሎች የታክስ ግዴታዎችን መፈፀም በተመዘገበው ሰው ላይ በትክክል ችግር የሚያስከትሉ መሆኑን መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል።

4. የተመዘገበ ሰው ከንግድ ሥራ ክፍሎቹ ውስጥ ከፊሎቹ በተናጠል እንዲመዘገቡለት የጠየቀ እንደሆነ፣ የተናጠል ምዝገባ ያልተጠየቀባቸው በዋናው ድርጅት ሥር እንደተመዘገቡ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡
5. የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ5(ሀ) የተመለከተውን ተመላሽ ሂሳብ በተናጠል ለተመዘገበው ታክስ ከፋይ ከመክፈሉ በፊት የዚሁ ታክስ ከፋይ ክፍሎች የግብር፣ የታክስ፣ የወለድ ወይም የመቀጫ ዕዳ የሌለባቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።
6. በተናጠል የተመዘገቡ ክፍሎች ለዋናው መ/ቤት ወይም አንዱ ለሌላው የሚያቀርቧቸው ዕቃዎች እና የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ለታክስ ዓላማ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል እንደተደረጉ አቅርቦቶች ይቆጠራሉ።ስለሆነም አቅራቢው ለእነዚህ ግብይቶች የታክስ ደረሰኝ መስጠት ያለበት ሲሆን፣ ገዥው በአዋጁ አንቀጽ 21 በተፈቀደው መሠረት ታክሱ እንዲቀናነስለት መጠየቅ ይችላል።
7. የተመዘገበው ዋና መ/ቤት በተናጠል በተመዘገቡ ክፍሎች አንፃር በወጪነት የሚይዘው ሂሳብ ዋናው መ/ቤት የፈፀመው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ሆኖ ይቆጠራል።
8. በተመዘገበው ዋና መ/ቤት እና በተናጠል በተመዘገቡ የዚሁ አካል የሥራ ክፍሎች ወይም በሥራ ክፍሎች መካከል የሚፈፀመው ግብይት በአዋጁ አንቀጽ 8 በተመለከተው መሠረት ተገቢ ያልሆነ የታክስ ጥቅም ለማግኘት እንዳይውል ለመከላከል የታክሱ ባለሥልጣን የቅርብ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡
9. በተናጠል የሚደረግ የሥራ ክፍሎች ምዝገባ የታክሱ ባለሥልጣን ሲፈቅድ ብቻ የሚከናወን ስለሆነ፣ ለተናጠል ምዝገባ ብቁ ለመሆን ዋናው መ/ቤት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ/ አመልካቹ በአዋጁ አንቀጽ 17 መሠረት በፈቃደኝነት የሚመዘገብ ሳይሆን ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆን አለበት፤

ለ/ ማመልከቻው በጽሑፍ ሆኖ፣ የታክስ ከፋዩን መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቁጥር መያዝ አለበት፤

ሐ/ አመልካቹ የንግድ ሥራውን በድርጅት አቋም የሚያከናውነው መሆን አለበት፤

መ/ አመልካቹ ለጠቅላላ የንግድ ሥራው አንድ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቡ ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትልበት መሆኑን ማስረዳት አለበት፡፡ አመልካቹ የተናጠል ምዝገባ ባይፈቀድ የሚያጋጥመውን ችግር እና ለጠቅላላ የንግድ ሥራው በእያንዳንዱ የሂሳብ ዘመን የተጠቃለለ የታክስ ማስታወቂያ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ማቅረብየማይችልበትን ምክንያት ማስረዳት አለበት ፤

ሠ/ በተናጠል እንዲመዘገብ የተጠየቀለት የንግድ ሥራው ክፍል የራሱ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ያለው መሆን አለበት፡፡ ይህም የሥራ ክፍሉ ገቢና ወጪውን በራሱ የሚመዘገብ እና ከሌሎች የሥራ ክፍሎች የተለየ የሂሳብ መግለጫ የሚያዘጋጅ መሆንን ይጠይቃል፤

ረ/ አመልካቹ ሂሳቡን ከማጠቃለሉ በፊት እያንዳንዱ ክፍል የራሱ የሂሳብ ሥርዓት እንዲኖረው ያደረገመሆን አለበት፤

ሰ/ በተናጠል እንዲመዘገብ የተጠየቀለት የሥራ ክፍል በንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ዓይነት እና በሚገኝበት ቦታ ተለይቶ የሚታወቅ መሆን አለበት ፤

ሸ/ የእያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት እና መዝጊያው ቀን አንድ ዓይነት መሆን አለበት፡፡

10. የታክሱ ባለሥልጣን የተናጠል ምዝገባውን ከማጽደቁ በፊት በዚህ ደንብ ከተዘረዘሩት ሌላ ተጨማሪ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ለመጠየቅ እና አዲስ ለሚመዘገብ ድርጅት የተለዩ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲኖሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

11. የተመዘገበ ሰው ለእያንዳንዱ በተናጠል እንዲመዘገብ ለሚጠይቅበት የሥራ ክፍል የተለየ ማመልከቻ ማቅረብ እና በቅጹ ላይ የታክሱ ባለሥልጣን የሚጠይቀውን መረጃ መሙላት አለበት፡፡ አዲስ የምዝገባ ጥያቄ የሚያቀርብ

ሰው የምዝገባ ማመልከቻውን እና የተናጠል ምዝገባ ማመልከቻውን በአንድነት ሊያቀርብ ይችላል።

12. እያንዳንዱ በተናጠል የተመዘገበ የሥራ ክፍል የዋናው ድርጅት አካል መሆኑን የሚያሳይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት ቁጥር ይሰጠዋል።
13. እያንዳንዱ በተናጠል የተመዘገበ የሥራ ክፍል የራሱን የተለየ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት ቁጥር የያዘ የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት።
14. በአዋጁ አንቀጽ 16 ለተመለከተው ለምዝገባ ብቁ ለሚያደርገው የገንዘብ መጠን አወሳሰን የእያንዳንዱ በተናጠል የተመዘገበ የሥራ ክፍል አቅርቦት የዋናው ድርጅት አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
15. የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) የተፈቀደው የታክስ ማቀናነስ በእያንዳንዱ የሥራ ክፍል ሳይሆን በዋናው መ/ቤት ደረጃ እንዲከናወን ለማድረግ ይችላል፡፡
16. የተመዘገበው ዋና መስሪያ ቤት በተናጠል የተደረገው የአንድ የሥራ ክፍል ምዝገባ እንዲሠረዝ ሊጠይቅ ወይም የታክሱ ባለሥልጣን በራሱ አነሳሽነት የተናጠል ምዝገባው እንዲሠረዝ ማድረግ ይችላል። ምዝገባ በሚሠረዝበት ጊዜ የሚከተሉት ደንቦች ተፈፃሚነት ይሆናሉ፤
    - ሀ/ የታክሱ ባለሥልጣን ከዚህ ያነሰ ጊዜ እንዲሆን ካልፈቀደ በስተቀር የአንድ የሥራ ክፍል የተናጠል ምዝገባ ለሁለት ዓመት የፀና ሆኖ መቆየት አለበት፤
    - ለ/ ማናቸውም ድርጅት ወይም በተናጠል የተመዘገበ ክፍል የተናጠል ምዝገባ በሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች መሥራቱን ያቋረጠ እንደሆነ ዋናው መ/ቤት የሁኔታዎቹ መሟላት መቀጠሉ ከተቋረጠበት ቀን አንስቶ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፤
    - ሐ/ የታክሱ ባለሥልጣን የተናጠል ምዝገባ የሚፈቅድባቸው ሁኔታዎች መሟላት መቋረጡን ያወቀ እንደሆነ ወይም ሥረዛው የታክሱን ገቢ ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ምዝገባውን ለመሠረዝ ይችላል፤
    - መ/ የታክሱ ባለሥልጣን የሥራ ክፍል የተናጠል ምዝገባ እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ ለማድረግ ብቸኛ ሥልጣን አለው፤

ሠ/ የሥራ ክፍል የተናጠል ምዝገባ ሥረዛ የፀና የሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን ከሚወስነው ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

10.<u>የምዝገባ መሠረዝ</u>

1. የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ምዝገባው እንዲሠረዝ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ምዝገባ እንዲሠረዝ የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሑፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ያቋረጠበትንቀን እና ታክስ ከፋዩ ግብይቱን ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ ባለው የ12 ወር ጊዜ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለማከናወን ያቀደ መሆን ያለመሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት።
3. የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ታክሡየሚከፈልበት ግብይት ማከናወን ካቋረጠበት ቀን አንስቶ ካለው የ12 ወር ጊዜ ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ያከናውናል ለማለት በቂ ምክንያት ከሌለው በስተቀር በንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ምዝገባ እንዲሠረዝ የቀረበውን ማመልከቻ ማጽደቅ አለበት፡፡
4. ምዝገባ የሚሠረዘው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ቢሆንም፣ የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ምዝገባውን ካከናወነበት ቀን ጀምሮ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ያመለፈፀሙን ካረጋገጠ ወደኋላ በመመለስ ምዝገባው ከፀናበት ቀን ጀምሮ እንዲሠረዝ ማድረግ ይችላል፡፡
5. በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት ምዝገባ ሲሠረዝ፣ የተመዘገበው ሰው በእጁ የሚገኙትን ዕቃዎች ታክስ በሚከፈልበት ግብይት እንደሸጣቸው ይቆጠራል።
6. የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብን ጨምሮ ምዘገባው የፀና በሆነበት ጊዜ ውስጥ ባከናወነው ማናቸውም ተግባር ምክንያት ታክስከፋዩ በአዋጁ የተጣለበት ግዴታ ወይም ኃላፊነት ምዝገባ በመሠረዙ ምክንያት የሚቋረጥ አይሆንም።

11.<u>የታክስ ማቀናነስ ደንቦች</u>

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ካልተሟሉ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት የታክስ ማቀናነስ ሊደረግ አይችልም።

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 22፣ 23 ወይም 13 መሠረት ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ የታክስ ደረሰኝ ወይም የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ሠነድ የተሰጠ እና የታክስ ማቀናነስ እንዲፈቀድለት የሚጠይቀው የተመዘገበ ሰው የታክስ ማስታወቂያ በሚያቀርብበት ጊዜ እነዚህን ደጋፊ ሠነዶች(ደረሰኝ አስፈላጊ ካልሆነበስተቀር) ካላቀረበ፣

ለ/ የታክስ ማቀናነስ እንዲፈቀድለት የሚጠይቀው የተመዘገበ ሰው ወደ አገር ያስገባውን ዕቃ በሚመለከት የታክስ ማስታወቂያ ሲያቀርብ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ በጉምሩክ አዋጅ መሠረት የተዘጋጀ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ወይም በጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠ ሌላ ሠነድ ካላቀረበ ፣

2. ታክስ የሚከፈልበት ወይም ከታክሱ ነፃ የሆነውን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለመጀመር ወይም ለማቋረጥ የወጡወጪዎች በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት የተፈቀዱ የታክስ ተቀናሾች ስሌት በሚከናወኑበት ጊዜ ከግምት ውስጥ የሚገቡ ይሆናል።

3. በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) ለመንገደኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች የታክስ ማቀናነስ እንደማይደረግ የተደነገገው በዋንኛነት ዕቃ ለማጓጓዝ የሚውሉ የንግድ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ወይም ሌሎች ተሽከርካዎችን አይጨምርም።

4. ለአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ3 (ለ) አፈፃፀም የተመዘገበ ሰው ኃላፊዎች፣ ሠራተኞች ወይም ደንበኞች በሬስቶራንት የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ ወይም ሠራተኞች ለመዝናናት ከሥራ ቦታቸው ውጪ በሚጓዙበት ጊዜ ለመኝታ እና ለምግብ በሚፈፅመው ግዥ ላይ የሚከፍለው ታክስ እንዲቀናነስ አይፈቀድም። ይሁን እንጂ የተመዘገበው ሰው "የመዝናኛ አገልግሎት" በመስጠት የንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ (ለምሳሌ ሬስትራንት) ታክስ ለሚከፈልበት የመዝናኛ ንግድ ሥራ በቀጥታ እንዲውሉ በሚገዛቸው የመዝናኛ ዕቃዎች ላይ የከፈለው ታክስ እንዲቀናነስ ይደረጋል።

5. የተጨማሪ እሴት ታክስ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የተመዘገበ ሰው በተመዘገበ ጊዜ በእጁ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ ታክስ እንዲቀናነስለት ሊጠይቅ የሚችለው ዕቃዎቹን የገዛው ምዝገባው ከፀናበት ቀን በፊት ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ

ውስጥ ከሆነ እና እነዚህን ዕቃዎች ከምዝገባው በኋላ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያውላቸው ከሆነ ነው።

6. የተመዘገበ ሰው በአንድ የታክስ ዘመን ውስጥ እንዲቀናነስለት ሊደረግ የሚችለው የታክስ መጠን ድምር በዚሁ የታክስ ዘመን ውስጥ ባከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ የበለጠ እንደሆነ በብልጫ የሚታየው ሂሳብ በአዋጁ አንቀጽ 27 ስለተመላሽ በተደነገገው መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

12.<u>በገዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ</u>

1. አገልግሎት ሰጪው እና ተቀባዩ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ምክንያት ወደአገር የሚገባ አገልግሎት ዋጋ የገበያ ዋጋ እንዲሆን ካልተደረገ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 23 መሠረት ታክስ የሚከፈልበት ወደአገር ውስጥ የሚገባ አገልግሎት ዋጋ አገልግሎት ተቀባዩ ለአገልግሎቱ መክፈል ያለበት ዋጋ ነው፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 23 መሠረት ታክስ የሚከፈልበት ወደአገር ውስጥ በሚገባ አገልግሎት ላይ መከፈል ያለበት ዋጋ ተለይቶ ያልተጠየቀ ታክስን የሚጨምር ከሆነ፤ የአገልግሎቱ ዋጋ ተደርጐ የሚወሰደው በንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ዋጋ ላይ የታክስ ሂሳብ ከተቀነሰ በኋላ ይሆናል፡፡

13. <u>በወኪል አማካኝነት ስለሚከናወን ግብይት</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ወኪል ወካይ በሆነው ሰው ስም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የፈፀመ እንደሆነ እና ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ገዥ የሆነው የተመዘገበ ሰው ከሆነ ወኪሉ ለግብይቱ የታክስ ደረሰኝ መስጠት ያለበት ሲሆን፡ ወካዩ ደረሰኝ መስጠት የለበትም።
2. ወካይ በሆነው ሰው ስም ለወኪሉ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የተፈፀመ እና ወካዩ የተመዘገበ ሰው ከሆነ፣ በወኪሉ ጥያቄ በግብይቱ ለተሳተፈው ወኪል የታክስ ደረሰኝ መሰጠት ያለበት ሲሆን፤ ከግብይቱ ጋር በተያያዘ ለወካዩ ጭምር ደረሰኝ መሰጠት የለበትም።

14.<u>የታክስ ማስታወቂያ ቅፅ እና የሚቀርብበት አኳኋን</u>

በአዋጁ አንቀጽ 26 የተደነገገው የታክስ ማስታወቂያ ባለሥልጣኑ በሚወስነው ቅፅ የሚዘጋጅ ሆኖ፤

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 20 መሠረት በታክስ ዘመኑ ውስጥ መክፈል ያለበትን ታክስ ለማስላት የሚያስችለውን አስፈላጊ መረጃ የሚይዝ፤

ለ/ ባለሥልጣኑ በሚወስነው አኳኋን የሚቀርብ መሆን አለበት።

15.<u>ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 5(ለ) የተከፈለ ታክስ ከተቀናነሰ በኋላ የሚቀረው ተመላሽ ሊደረግ የሚገባ ሂሳብ ከብር 50 ያልበለጠ ከሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ይህንን የገንዘብ መጠን ተመላሽ እንደማያደርግ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ተመላሽ ሊደረግ የሚገባው ሂሳብ ብር 50 ወይም ከዚህ በታች ከሆነ ይህ የገንዘብ መጠን ለወደፊት እንዲሸጋገር ተደርጐ በቀጣይ የሂሳብ ዘመን ሊከፈል ለሚገባው ታክስ እንዲታሰብ ይደረጋል።
2. ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ጥያቄ የሚያቀርብ የተመዘገበ ሰው ተገቢውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን የተመዘገበው ሰው ማስታወቂያውን እስከሚያቀርብ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ሂሳብ ይዞ ለማቆየት ይችላል፡፡
3. የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (6) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ሂሣብ ያልመለሰ እንደሆነ ሂሣቡ ተመላሽ ሊደረግ ከሚገባው ቀን አንስቶ እስከተመለሰበት ቀን ድረስ ላለው ጊዜ ወለድ ይከፍላል።

16.<u>ታክስ ስለመወሰን</u>

1. የታክሱ ባለሥልጣን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የተጨማሪ ታክስ ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፤

   ሀ/ ታክስ ከፋዩ የአዋጁ አንቀጽ 26 በሚያዘው መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ወይም የዚህ ደንብ አንቀጽ 5 በሚያዘው መሠረት እቃዎችን ወደ አገር ያስገባበትን ዲክላራሲዮን ያላቀረበ እንደሆነ፤

   ለ/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የታክስ ማስታወቂያ ወይም እቃዎች ወደ አገር የገቡበትን ዲክላራሲዮን የታክሱ ባለሥልጣን አጥጋቢ ሆኖ ያላገኘው እንደሆነ፤

   ሐ/የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ያልከፈለ መሆኑን የሚያሣምን በቂ መረጃ ያገኘ እንደሆነ፤

መ/ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው ባቀረበው ዕቃ ወይም በሰጠው አገልግሎት ላይ ታክስ እንደተከፈለበት አድርጎ ያቀረበ እንደሆነ፣

ሠ/ የተመዘገበ ሰው ያቀረበው ዕቃ ወይም የሰጠው አገልግሎት ታክስ የማይከፈልበት ግብይት ወይም በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ሆኖ ሳለ ከዜሮ በላይ በሆነ የማስከፈያ ልክ ታክስ እንደተከፈለበት አድርጎ ያቀረበ እንደሆነ፣

ረ/ በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን ግዴታ በሚመለከት ውሣኔ የሰጠ እንደሆነ፣

2. የግብር ውሣኔ የሚሰጠው፣

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (መ) ወይም (ሠ) የተደነገገውን በሚመለከት አቅርቦቱን ባከናወነው ሰው ላይ፣

ለ/ በንዑስ አንቀጽ 1(ረ) የተደነገገውን በሚመለከት በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ላይ፣

ሐ/ በሌሎች ሁኔታዎች በአዋጁ መሠረት ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ላይ ይሆናል፡፡

3. የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ 29 መሠረት ታክስ ከፋዩ በተጨማሪ እንዲከፍል የሚጠይቀውን ታክስ በግምት ሊወስን ይችላል።

4. በአዋጁ አንቀጽ 29 መሠረት የተጨማሪ ታክስ ውሣኔ የተሰጠ እንደሆነየታክሱ ባለሥልጣን ለታከስ ከፋዩ የውሣኔ ማስታወቂያ ይልክለታል፡፡ ይህም የውሣኔ ማስታወቂያ፣

ሀ/ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ፣ እና

ለ/ታክሱ መከፈል የነበረበትን ቀን ጭምር የሚይዝ መሆን አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የተሰጠ የውሣኔማስታወቂያ ወይም የዚሁ ውሣኔ ማስታወቂያ የተረጋገጠ ቅጂ በትክክል የተሰጠ ውሣኔ እንደሆነ ተቆጥሮ በማናቸውም የክርክር መድረክ በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል።

6. በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የተዘጋጀ ወይም የተሰጠ የውሣኔ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ማናቸውም ሰነድ በይዘት እና በውጤት በአዋጁ የተደነገገውን የሚያሟላ እና በውሣኔ ማስታወቂያ የተጠቀሰው ወይም

ማስታወቂያው እንዲሰጠው የታሰበ ሰው ግብሩ የሚፈልግበት ሰው መሆኑ ከታወቀ ሰነዱ፤

ሀ/ በትክክለኛ ቅጽ ያልተዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት ሊሠረዝ ወይም የሚሠረዝ ሊሆን አይችልም፤

ለ/ በሰነዱ ላይ በተፈፀመ ስህተት ወይም ጉድለት ወይም ሊካተት የሚገባው ነጥብ ያልተካተተ በመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት ሊያጣ አይችልም።

## 17.ንብረትን ስለመያዝ

1. በአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ታክስ ከፋይ ንብረት ከመያዙ ከ30 ቀን በፊት ለታክስ ከፋዩ ማስታወቂያ መላክ ያለበት ቢሆንም ተገቢውን ጥረት አድርጎ ማስታወቂያ ሊደርሰው የሚገባውን ሰው አድራሻ ማግኘት ያልቻለ እንደሆነ ማስታወቂያው እንደተሰጠ ተቆጥሮ ንብረቱን መያዝ ይችላል፡፡
2. ታክስ ከፋዩ ንብረቱን ለመያዝ ምክንያት የሆነውን የታክስ እዳ እና ንብረቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የከፈለ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ 31 መሠረት የተያዘው ንብረት ለንብረቱ ባለቤት ወይም ንብረቱ ከመያዙ በፊት ንብረቱ በጥበቃው ወይም በይዞታው ሥር ለነበረው ሰው እንዲመለስ ያደርጋል።

## 18.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በዚህ አንቀጽ ውስጥ፡-

   ሀ/ "ብቁ የሆኑ እቃዎች" ማለት የካፒታል እቃዎችን ጨምሮ ወደ አገር የገቡ ወይም በአገር ውስጥ የተገዙ ዕቃዎች ናቸው፤

   ለ/ "የታሻረ ህግ" ማለት የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 68/85 ነው፤

   ሐ/ "የሽያጭ ታክስ" ማለት በሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የተጣለው ታክስ ነው።
2. አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በአገር ውስጥ የተገዙ እና ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎችን በሚመለከት፤ ታክስ ስለመጣል፣ ስለመክፈል፣ ስለመወሰን፣ ሪፖርት ስለማድረግ፣ የተከፈለን ታክስ ስለማስመለስ የተደነገጉትን ጨምሮ በተሻረው ሕግ ውስጥ ያሉ ድንጋጌዎች በሙሉ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

3. በተሻረው ሕግ መሠረት የተሰጠና አዋጁ ሥራ ላይ እስከዋለበት ቀን ድረስ ፀንቶ የነበረው የውክልና ሥልጣን በአዋጁ መሠረት የተሰጠ ሥልጣን እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
4. በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም የተመዘገበው ሰው ታክሱ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባለው የመጀመሪያ የሂሳብ ጊዜ ሊከፍል የሚገባው ታክስ ስሌት ሲከናወን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሰረት የሚሰላው እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አነቀጽ (7) መሰረት ተቀናሽ የሚደረገው የሽያጭ ታክስ መጠን በአቀንጽ 21 መሰረት ተቀናሽ እንደሚደረግ ሂሳብ እንዲያዝለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡
5. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(5) አፈጻጸም፤
    i. የተመዘገበው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ባለው የስራ ቀን መጨተሻ ታክሱ ስራ ላይ ከዋበት ከ6 ወር በፊት የተገዙ ብቁ የሆኑ እቃዎች በእጁ የተገኙ እንደሆነ፣ እና
    ii. የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ የእነዚህን ዕቃዎች ግዥ ሲፈጽም በሽያጩ ደረሰኝ ላይ ወይም ዕቃዎቹን ወደ አገር ሲያስገባ በዲክላራሲዮን ላይ የሽያጭ ታክስ የከፈለ እናየታክስ ተመላሽ ያላገኘ መሆኑን ካረጋገጠ፤

    ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው የሽያጭ ታክስ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ታክስ ይሆናል። ሆኖም ለእያንዳንዱ ብቁ ስለሆነ ዕቃ ተቀናሽ የሚደረገው የሽያጭ ታክስ ዕቃዎቹ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስ የሚከፈልባቸው ቢሆን ሊከፈል ከሚገባው ታክስ የበለጠ ሊሆን አይችልም።
6. በማናቸውም የታክስ ዘመን ውስጥ የተመዘገበው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ተቀናሽ የሚደረግ የሽያጭ ታክስ ያለው እንደሆነ፣ ተቀናሽ የሚደረገው የገንዘብ መጠን በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት ተቀናሽ የሚደረግ ሆኖ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም በአዋጁ አንቀጽ 27 በታክስ ዘመኑ ውስጥ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ ስለሆነ የሚቀናነስ ታክስ የተደነገገው ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
7. በአቅርቦቱ ወይም ወደ አገር በገባው ዕቃ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ቢሆን ኖሮ የተከፈለው ታክስ በአዋጁ

አንቀጽ 21 መሠረት ተቀናሽ የማይደረግ ከሆነ፣ ለአቅርቦቱ የተከፈለው ሽያጭ ታክስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ተቀናሽ አይደረግም፡፡

8. የተመዘገበው ሰው አዋጁ በፀናበት ቀን በእጁ በሚገኙት ብቁ የሆኑ ዕቃዎች ላይ የከፈለው የሽያጭ ታክስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት እንዲቀናነስለት ሊጠይቅ የሚችለው አዋጁ በፀናበት ቀን ተመዝግቦ የተገኘ ከሆነ ብቻ ነው።
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የተከፈለ ታክስ እንዲቀናነስለት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ከሚያቀርበው የመጀመሪያው የታክስ ማስታወቂያ ጋር አዋጁ በፀናበት ቀን በእጁ የነበሩትን ብቁ የሆኑ ዕቃዎች ዝርዝር እና በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የሽያጭ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማቅረብ አለበት፡፡
10. አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የተከፈለ የሽያጭ ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግ ያለመፈቀዱ በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ተቀናሽ እንዲደረግ እንዳልተፈቀደ ታክስ አይቆጠርም።
11. አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ተዋዋዮች መካከል ውል የተፈፀመ እና በዚህ ውል ውስጥ ስለታክስ አከፋፈል ያልተጠቀሰ ከሆነ አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ በውሉ መሠረት በሚፈፀም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ አቅራቢው ከገዥው ሊጠይቅ ይችላል፡፡
12. አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ የተፈረመው ውል ስለታክስ ክፍያ የማይጠቅስ ከሆነ የውሉ ዋጋ ታክስን የሚጨምር እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል። ስለሆነም አቅራቢው ለታክሱ ክፍያ ኃላፊ ይሆናል።
13. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (16) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከእቃ እና አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ፡-

    ሀ/ የዕቃው የባለቤትነት ስም የተዘዋወረው፣ የዕቃው ርክክብ የተፈፀመው ወይም አገልግሎቱ የተሰጠው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ከሆነ፤ እና

    ለ/ ክፍያ የተፈፀመው ወይም ደረሰኝ የተሰጠው ከተጠቀሰው ቀን ዘጠኝ ወር በፊት ከሆነ፤

አቅርቦቱ ተፈጽሟል የሚባልበትን የሂሣብ ጊዜ ወይም የታክስ ማቀናነስየሚፈቀድበትን ጊዜ ለመወሰን፣ ክፍያው የተፈፀመው ወይም ደረሰኙ የተሰጠው አዋጁ በፀናበት ቀን እንደሆነ ተደርጐይቆጠራል።

14.የሽያጭ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የተሰጡ እንደሆነ እና ክፍያው የተፈፀመው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ባለው 4 ወር ጊዜ ውስጥ ከሆነ በእነዚህ አገልግሎቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ አይከፈልም፡፡

15.ክፍያው በተወሰነ ጊዜ ልዩነት እንዲፈፀም ማድረግ በሚያስችል ውል ዕቃ የተከራየ እንደሆነ ወይም የሽያጭ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች የመስጠት ተግባር አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት ተጀምሮ አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ የሚጠናቀቅ ከሆነ፣ አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የተሰጠው አገልግሎት ዋጋ የተከፈለው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ከአራት ወራት በላይ ቆይቶ ካልሆነ በስተቀር፣ ክፍያው የአራቱ ወር ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው ቀን ለተሰጠ አገልግሎት እንደተፈፀመ ክፍያ ተቆጥሮ አዋጁ ከተጠናቀቀ በኋላ በተሰጠው አገልግሎት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈላል፡፡

16.በንዑስ አንቀጽ (13) የተደነገገው ቢኖርም፣ አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተፈረመ ስምምነት መሠረት የግንባታ፣ የማምረት ወይም ሕንፃን የማስፋፋት ወይም የሲቪል ኢንጂነሪንግ ሥራ የተከናወነ እና የተከናወነው ሥራ ወደ ገዥው የተላለፈው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ከሆነ እንዲሁም አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የተከናወነው ሥራ ዋጋ በታክሱ ባለሥልጣን በፀደቀው አኳኋን የተወሰነ ከሆነ እና አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ባለው የአቅራቢው የመጀመሪያ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሂሣብ ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን ከቀረበ፣የተጨማሪ እሴት ታክስየሚከፈለው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ በተከናወነው ሥራ ዋጋ ላይ ብቻ ይሆናል።

17.አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በሚጀምር እና አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ በሚጠናቀቅ የኪራይ ውል መሠረት በተከራየ ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ አዋጁ ከፀናበት ጊዜ በፊት ላለው የኪራይ ዘመን የተከፈለው የኪራይ ሂሣብ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚከፈልበት ሂሣብ ውስጥ አይጠቃለልም፡፡

## ክፍል2

## ከታክሱ ነፃ ስለመሆን

19.**<u>የመኖሪያ ቤት</u>**

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ1(ለ) ትርጉም መሠረት “የመኖሪያ ቤት” ለመኖሪያ አገልግሎት አስፈላጊ የሆነውን ከመኖሪያ ቤት ጋር የተያያዘውን ወይም የዚሁ ተቀጽላ የሆነውን ቅጥር ግቢ የሚጨምር ሲሆን፣ ከመኖሪያ ቤት ጋር የተያያዘውን የእርሻ ቦታ አይጨምርም። ስለሆነም ለነዋሪዎች አገልግሎት የሚውል ወደ ተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚወስድ የግቢ ውስጥ መንገድ፣ የእግር መንገድ፣ የመናፈሻ ሥፍራ የመኖሪያ ቤቱ አካል ሆኖ ይቆጠራል።
2. ለሚከራይ መኖሪያ ቤት የሚውል አዲስ ወይም ያገለገለ ንብረት ለመግዛት የተመዘገበ ሰው ያወጣው ወጪ ከታክሱ ነፃ ለሆነው መኖሪያ ቤት የዋለ ከሆነ በግዥው ዋጋ ላይ የተከፈለው ታክስ እንዲቀናነስ አይፈቀድም፡፡
3. አሠሪው ለተቀጣሪዎቹ በዓይነት በሚሰጠው ጥቅም መልክ የመኖሪያ ቤት የተሰጠ እንደሆነ ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ለሠራተኞች በዓይነት የተሰጠውን ጥቅም አሠሪው በንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ሂደት ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንዳዋለው መቁጠር ሳይሆን፤ በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) መሠረት ከታክሱ ነፃ እንደሆነ መውሰድ ነው። አሠሪው ከታክሱ ነፃ ለሆነው በዓይነት ለተሰጠው ጥቅም ባወጣው ወጪ ላይ የከፈለው ታክስ በአዋጁ አንቀጽ 21 በተደነገገው መሠረት ተቀናሽ እንዲሆን አይፈቀድም፡፡
4. የመኖሪያ ቤት አካል የሆነ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራ መኖሪያ ቤቱን ለገዛው ሰው የተሸጠ እንደሆነ ወይም የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ የመኖሪያ ቤት ኪራይ አካል ሆኖ የተከራየ እንደሆነ ከታክሱ ነፃ ይሆናል።

20.**<u>የፋይናንስ አገልግሎቶች</u>**

1. በዚህ ደንብ ትርጉም የሚሸፈኑ የፋይናንስ አገልግሎቶች በግልጽ በሚታወቅ ወይም ግልጽ ባልሆነ ክፍያ የተሰጡ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ2(1) መሠረት ከታክሱ ክፍያ ነፃ ናቸው፡፡
2. ከታክሱ ነፃ የተደረጉ የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ/በአበዳሪው ወይም በዋስትና ሰጪው የሚከናወን ብድርን፣ የዱቤ ሽያጭን ወይም የብድር ዋስትናን ማስተዳደርን ጨምሮ ብድር፣ የዱቤ ውል ወይም የብድር ዋስትናን መስጠት፣ መደራደር ወይም በእነዚህ መንገድ፣ ወይም

ለ/ ዕዳን መሰብሰብ ወይም በውክልና መሥራትን ሳይጨምር ከገንዘብ፣ (የገንዘብ ምንዛሪ) ተቀማጭ ሂሣብ፣ ቁጠባ እና ተንቀሳቃሽ ሂሣብ፣ ክፍያየገንዘብ ዝውውር፣ ዕዳ፣ ቼክ ወይም ከሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ጋር በተያያዘ የሚከናወን እንቅስቃሴ ወይም፣

ሐ/ ዱቤው በተለየ ክፍያ የተሰጠና ዕቃውን የገዛው ሰው የተለየ ክፍያ ስለመኖሩ የተገለፀለት ከሆነ በኪራይ ግዥ ወይም በግዥ ውል መሠረት የተሰጠ ዱቤ፣ ወይም

መ/ በዚህ ደንብ ከተደነገገው ሣያልፍ የኢንሹራንስ ፖሊሲ መስጠት ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲን ባለቤትነት ማስተላለፍ ወይም በዚህ ፖሊሲ ላይ የጠለፋ ዋስትና መስጠት፣ ወይም

ሠ/ የተወሰነ ጥቅም ለማስገኘት ከተቋቋመ ፈንድ፣ ከፕሮቪደንት ፈንድ፣ ከጡረታፈንድ፣ በየዓመቱ፣ የተወሰነ ገንዘብ ማግኘት ከሚያስችል የጡረታ አገልግሎት ፈንድ፣ ወይም ከጥበቃ ፈንድ፣ ክፍያን ወይም ማናቸውንም ጥቅም ለማግኘት ከሚያስችል ሥርዓትተጠቃሚ መሆን የሚያስችልን መብት መስጠት ወይም የዚህን መብት ባለቤትነት ማስተላለፍ፣ ወይም

ረ/ ከ (ሀ)እስከ (መ) የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች አሰጣጥ ማመቻቸት፤ ወይም

ሰ/ ነፃ የሕክምና አገልግሎት ለሚሰጡ ማኅበረሰቦች ወይም ለሕክምና ዕርዳታ ፈንድ የአገናኝ አገልግሎት መስጠት፣

3. ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚከተሉት ከዚህ በታች የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፣

ሀ/ “ቼክ” የፖስታ ቤት ማዘዣን፣ የገንዘብ ክፍያ ትእዛዝን፣ የመንገደኛ ቼክን ወይም ማናቸውም የፋይናንስ ተቋም አንድን ሂሣብ ዴቢት ወይም ክሬዲት እንዲያደርግ የተሰጠን ትእዛዝ (በጽሑፍ፣ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም በሌላ መንገድ) ይጨምራል።

ለ/ “ገንዘብ” ማለት ለጥንታዊ ሰብሳቢ፤ በኢንቬስትመንት እቃነት፣ የየአገሩን ሣንቲም ለጥናት ለሚሰበስብ ሰው ወይም በገንዘብ ልውውጥ ተግባር ሣይሆን

በሌላ ዓላማ ጥቅም ላይ ከዋለው በስተቀር የማናቸውም አገር ባንክ ያወጣው ገንዘብ ወይም ሌላ የገንዘብ ሰነድ ነው፤

ሐ/ "የኢንሹራንስ ፖሊሲ" ማለት ለመድን ንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠትና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 መሠረት የጠቅላላ ኢንሹራንስ ንግድ ወይም የረዥም ጊዜ የኢንሹራንስ ንግድ ሥራ በመባል በሚታወቀው ፖሊሲ የሚሸፈን የኢንሹራንስ ዋስትና ነው።

መ/ "የነጋዴ ቅናሽ" ማለት ለዕቃ አቅርቦት ወይም አገልግሎት ለመሰጠት ተግባር ወይም ገዥው ድርጅት ለሚያስከፍለው ተመሣሣይ ክፍያ ክሬዲት ወይም ዴቢት እንዲደረግ የተጠየቀውን ሂሣብ በመቀበሉ ምክንያት ከነጋዴው ላይ የሚጠየቅ ሂሣብ ነው፡፡

4. በዚህ ደንብ ለፋይናንስ አገልግሎት ከተሰጠው ትርጉም በተጨማሪ ሚኒስትሩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ዝርዝር እንዲሁም ከፋይናንስ አገልግሎቶች ውስጥ ታክስ የሚከፈልባቸውን፣ ከታክሱ ነፃ የሆኑትን እና በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸውን የሚያሣይ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡ ሚኒስትሩ አዳዲስ የፋይናንስ አገልግሎቶች በመፈጠራቸው ምክንያት ሊደረግ የሚገባውን ለውጥ ለማካተት ወይም በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱት የፋይናንስ አገልግሎቶች ባህሪ በመለወጡ ምክንያት ሊደረግ የሚገባውን ማሻሻያ ጨምሮ ማሻሻያ ሊደረግባቸው በሚያስፈልግ ምክንያቶች ዝርዝሩን ለማሻሻል ይችላል፡፡ በዝርዝሩ ላይ የሚደረገው ማሻሻያ የፀና የሚሆነው ማሻሻያው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

5. በዚህ ደንብ ከታክሱ ነፃ መሆናቸው የተደነገገ የፋይናንስ አገልግሎቶች በተመዘገበ ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም ወይም በማናቸውም ሌላ ሰው የተሰጠ ቢሆንም ከታክሱ ነፃ ይሆናሉ።

6. አንዳንድ አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ ከሆኑ አገልግሎቶች ጋር በተገናኘ አኳኋን የተሰጡ ቢሆንም፣ በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) መሠረት ከታክሱ ነፃ ሊሆኑ አይችሉም። ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሣይወሰኑ የዚህ ዓይነቶች አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ/ የፋይናንስ አገልግቶችን ለሚሰጥ አቅራቢ ወይም የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለሚሰጥ አቅራቢ ደንበኞች የተሰጠ የሕግ፣ የሂሣብ አያያዝ እና የሰነድ

አያያዝ አገልግሎት፣ ሊደርስ የሚችልን አደጋ የመገመት፣ ውል የማዋዋል እና የታክስ ውክልና አገልግሎት (የምክር አገልግሎትን ጨምሮ)፣

ለ/ ለገንዘብ፣ ለሰነድ ወይም ለሌሎች ንብረቶች ጥበቃ የሚሰጥ የካዝና አገልግሎት፣

ሐ/ የመረጃ ትንተና እና የደመወዝ መክፈያ ሊስትዝግጅት አገልግሎት፣

መ/ እዳ የመሰብሰብ ወይም የፋይናንስ ውክልና አገልግሎት፣

ሠ/የጡረታ አበል ክፍያን ፈንድ ማስተዳደርን የመሳሰሉ የአስተዳደርአገልግሎቶች፣

ረ/ ባለአደራ፣ የፋይናንስ ምክር፣ ከመሬት ጋር የተያያዘን ሀብት አስተዳደር የማቀድ አገልግሎት፣

ሰ/ ከፋይናንስ ሰነዶች ውጭ ካሉ ሀብቶች ጋር በተያያዘ የኪራይ፣ የፈቃድ መስጠት እናተመሣሣይ አገልግሎቶች።

7. ለዚህ ደንብ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 6 አፈፃፀም የሂሣብ አያያዝ እና የሰነድ አጠባበቅ አገልግሎት፣ ስምምነት የተደረሰበትን ጉዳይ በማስፈፀም ሂደት የሚከናወን ሂሣብን የማጣራት ተግባር፣ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን በደንበኞች ሂሣብ ውስጥ የማወራረስ፣ የደንበኞችን ሂሣብ የመያዝ እና ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶችን መስጠትን ይጨምራል።

8. በፋይናንስ ወኪል ተይዞ የሚቆይን እዳ ጨምሮ በማናቸውም ሁኔታ የሌላን ሰው እዳ ይዞ ማቆየት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት አይሆንም። በፋይናንስ ውክልና ወይም ከፋይናንስ ውክልና ጋር በተገናኘ አገልግሎት፣ ከሽያጭ ተግባር ጋር የተዛመደ የሂሣብ አያያዝ አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ እዳን ከማስመለስ ተግባር ጋር የተያያዘ አገልግሎት፣ ክስን የመከታተል ከባለእዳዎች የሚፈለግን እዳ የማስተዳደር አገልግሎት ታክሎ ይከፈልባቸዋል።

9. በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ/ ወደ ውጭ አገር ከሚላክ እቃ ጋር በተያያዘ የሚሰጡ የፋይናንስ አገልግሎቶች፣

ለ/ ያልተመዘገበ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወደ ውጭ አገር ለሚልካቸው እቃዎች የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን እንዲችል ከተሰጠው ብድር ጋር በተያያዘ የተሰጠ የፋይናንስ አገናኝነት አገልግሎት፣ እና

ሐ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 35 በልዩ ሁኔታ እንደሚታይ በተደነገገው ውስጥ የሚካተት ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ባንክ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ላልሆነ በውጭ አገር ለሚገኝ ሰው የባንክ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የሚጠይቀው ክፍያ፣

10.ከታክሱ ነፃ የተደረገ ወይም በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክሱ የሚከፈልበትየፋይናንስአገልግሎት ከዋናው አቅርቦት ጋር በተጓዳኝ የሚሰጥ ወይም የፋይናንስ አገልግሎቱ ዋንኛው አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ ስለቅይጥ አቅርቦቶች በአዋጁ አንቀጽ 5 የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል።

11.ታክስ የሚከፈልበትን (የማስከፈያ ልክ የሚከፈልበትን ጨምሮ) እና ከታክሱ ነፃ የሆነውን የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ የፋይናንስ ተቋሞች እና ሌሎች አገልግሎት ሰጭዎች በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የታክስ ማቀናነስ ሊጠይቁ የሚችሉት ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ለማከናወን በገዙዋቸው (በተከራዩት ጭምር) ወይም ወደ አገር ባስገቡዋቸው ላይ ብቻ ነው።

12.ተቀናሽ የሚደረግ ታክስ ከታክሱ ነፃ በሆኑ እና ታክስ በሚከፈልባቸው አቅርቦቶች መካከል ስለሚከፋፈልበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው በአንድ የሂሣብ ጊዜ ውስጥ ካከናወናቸው አቅርቦቶች 90 ፐርሰንት ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች (የአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) በሆኑ የተመዘገበ ሰው ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም (ተቀናሽ የሚደረገው ሙሉው ታክስ ይሆናል)። ለዚህ አፈፃፀም አቅራቢው ታክስ የሚከፈልበትን እና ጠቅላላውን ግብይት ለማስላት ከፋይናንስ አገናኝነት አገልግሎት ውጭ ላለው አቅርቦት ጠቅላላውን አኃዝ መሠረት ማድረግ እና በፋይናንስ አገናኝነት አገልግሎት የተጣራውን የወለድ መጠን (ከወለድ ገቢ ላይ ለወለዱ የተደረገውን ወጪ መሠረት ማድረግ ይኖርበታል።

13. የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው የተጨማሪ እሴት ታክስ መመሪያ የታክሱ ባለሥልጣን ተገቢ መስሎ በታየው አኳኋን ታክስ በሚከፈልበት እና ከታክሱ ነፃ

በሆነው የሽያጭ እንቅስቃሴ መካከል የታክስ ማቀናነስ የሚደረግበትን ክፍፍል መወሰን እንዲችል ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል፡፡

14. በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት የታክስ ማቀናነሱን ክፍፍል ለማድረግ የትኛውም ዘዴ በሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም፣ የተመዘገበው ሰው ሥራ ላይ የዋለውን ዘዴ የሚያስረዱ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡ የታክሱ ባለሥልጣን የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪዎች ስለሚሰጡዋቸው የአገልግሎት ዓይነቶች ስታትስቲካዊ መረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።

15. ለፋይናንስ አገልግሎቶች የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት የኢንሹራንስ ዋስትና ለማግኘት ለሚገዛ የኢንሹራንስ ፖሊስ የሚከፈለውን አረቦን ይጨምራል፡፡

16. ከታክሱ ነፃ የሆነ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ተጠቃሚዎች ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ሽፋን ጋር በተያያዘ ለሚያገኙት አገልግሎት የሚከፍሉት አረቦን ከታክስ ነፃ የሆነ አገልግሎት ነው።

17. ከታክሱ ነፃ የሆኑ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ተጠቃሚ ለሆኑ ሰዎች ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ሽፋን ጋር ባልተያያዘ የሚሰጠው አገልግሎት ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ተለይቶ የሚሰጥ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ የተጣለበት ከሆነ ታክስ የሚከፈልበት አገልግሎት ይሆናል፡፡

18. ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ጋር ያልተያያዘ አገልግሎት ተጠቃሚ ከዋናው የኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር የተዛመደ ስለመሆኑ ውሣኔ የመስጠት ብቸኛ ሥልጣን ያለው የታክሱ ባለሥልጣን ነው።

19. ለኢንሹራንስ ፖሊሲ የተከፈለ አረቦን ከታክሱ ነፃ ሊሆን የሚችለው በኢንሹራንስ አዋጅ መሠረት የኢንሹራንስ ፖሊሲዎችን ለመሸጥ ፈቃድ በተሰጠው ሰው በተሸጠ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ የተከፈለ አረቦን ሲሆን ነው፡፡

20. የኢንሹራንስ ደላሎች/ወኪሎች የኢንሹራንስ ፖሊሲ ለደንበኞቻቸው በመሸጥ የሚያገኙት ኮሚሽን እና ሌሎች ክፍያዎች የኢንሹራንስ አገልግሎት በተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት አይሸፈኑም፡፡

21. ስለአንድ ንብረት ጥራት፣ የተሟላ መሆን ወይም የተፈለገውን አገልግሎት መስጠት ስለመቻሉ ለተሰጠ ዋስትና የኢንሹራንስ ሽፋን የመስጠት አገልግሎት የአንሹራንስ ፖሊሲ ሆኖ አይወስድም።

## 21.የዋስትና ሠነዶችን ስለመሸጥ ወይም ወደአገር ስለማስገባት

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) ለዋስትና ሠነዶች የተሰጠው ከታክስ ነፃ የመሆን መብት የሚከተሉትን ያካትታል፤
   - ሀ/ በአደራ የመያዝ አገልግሎትን ሳይጨምር አክሲዮኖችን፣ ስቶኮችን፣ ቦንዶችን፣ የግምጃ ቤት ሰነዶችን ወይም ሌሎች የዕዳ ወይም የሀብት ድርሻ ዋስትናዎችን ማውጣት፣ ማዘዋወር ወይም መቀበል ወይም በእነዚህ ሰነዶች መሥራት፣
   - ለ/ ከፋይናንስ አገልግሎት ከሚመነጩ አገልግሎቶች፣ ከማስተላለፊያ ውሎች፣ አማራጭከሚሰጡ ውሎች ወይም ተመሳሳይ አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ ግብይቶች፣
   - ሐ/ በፊደል (ሐ) ከተዘረዘሩት የዋስትና ሰነዶች ጋር የተያያዙ አማራጭ የሚሰጡ ውሎችን ወይም ዋስትናዎችን መስጠት ወይም እነዚህን ሰነዶች ከመመሥረት፣ ከማውጣት፣ ከማዘዋወር፣ ግዴታና መብትን ከማስተላለፍ ወይም ከመቀበል ወይም በእነዚህ ሰነዶች ከመሥራት ጋር የተያያዙ ግብይቶች፣
2. የዋስትና ሰነዶችን ለመሸጥ ውል መዋዋል ከታክሱ ነፃ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዋስትና ሰነዶችን ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደው የዋስትና ሰነዶችን ከመሸጥ ጋር በተያያዘ ለማስታወቂያ እና ለሕትመት የሚደረጉ ወጪዎች፣ ለሂሣብና ለሕግ ባለሙያዎች ወይም ለአማካሪዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎችን ለመሳሰሉ አገልግሎቶች የሚደረጉ ክፍያዎችን አይጨምርም።
3. ለዋስትና ሰነዶች እና ለፋይናንስ አገልግሎቶች የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ዋንኛ ተግባሩ የባለአክሲዮኖችን፣ የአባላትን ወይም የሌሎች ሰዎችን ሀብት በሥራ ላይ ማዋል ለሆነ የንግድ ሥራ ድርጅት የሚሰጠውን የአስተዳደር አገልግሎት አይጨምርም።
4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡-
   - ሀ/ “ገንዘብ” ማለት የማናቸውም አገር ማንኛውም የወረቀት ገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ሲሆን፤ ለገበያ ከሚውሉት በስተቀር በታሪክነት የተሰበሰቡ የየአገሮችን ገንዘቦች እና ለኢንቬስትመንት የሚውሉ ሰነዶችን፣ አይጨምርም።

ለ/ “የዕዳ ዋስትና” ማለት አንድ ሰው ያለው ወይም ሊኖረው የሚችለው የገንዘብ ክፍያን የመቀበል መብት ሲሆን፣ ቼክን፣ ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የተሰጠን የሊዝ፣ የፈቃድ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መብት አይጨምርም።

ሐ/ “የሀብት ድርሻ ዋትና” ማለት በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት ካፒታል ላይ ያለ የድርሻ መብት ወይም ዝግ የሆነ ኮርፖሬሽን አባል የሆነ ሰው በኩባንያው ውስጥ ያለው መብት ነው፡፡

22.<u>ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚውል ወርቅ ወደ አገር ስለማስገባት</u>

በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ (2)(መ) በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ወደአገር በሚገባበት ጊዜ ከታክሱ ነፃ እንደሚሆን የተደነገገው የወርቁ የጥራት ደረጃ ወይም ወደአገር በሚገባበት ጊዜ የሚኖረው ቅርፅ ከግምት ውስጥ ሳይገባ የኢትየጵያ ብሔራዊ ባንክ ራሱ የሚያስገባውን ወይም ሌሎች ሰዎች ለባንኩ ወደአገር የሚያስገቡትን ወርቅ ይጨምራል።

23.<u>የሃይማኖት ወይም ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሠ) በተደነገገው መሠረት የሃይማኖት ወይም ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ እና በሃይማኖት ድርጅት የሚሰጡ አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ ናቸው። ስለሆነም የሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡዋቸው የአምልኮት ሥርዓት አካል የሆኑ አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ በተደረገው ውስጥ የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡
2. የሃይማኖት ድርጅቶች ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር ተወዳዳሪ በመሆን የሚያከናውኗቸው እንቅስቃሴዎች ወይም የአምልኮት ሥርዓት አካል ያልሆኑ የሃይማኖት ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከታክሱ ነፃ አይሆኑም፡፡ የእነዚህ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 16 ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ የሃይማኖት ድርጅቱ መመዝገብ አለበት።
3. የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑሰ አንቀጽ 2 (ወ)መጻሕፍት እና የታተሙ ፅሑፎች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ ፈቅዷል፡፡ ስለሆነም ለመፃሕፍት እና ለታተሙ ፅሑፎች የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት የሃይማኖት ድርጅቶች ለሚያቀርቧቸው መፃሕፍትና የታተሙ ፅሑፎችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. ዕርዳታ ሰጪው በሰጠው ዕርዳታ ምላሽ ጥቅም የማያገኝ እስከሆነ ድረስ በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚያደርገው ዕርዳታ (በየሙዳ ምፅዋት እና በመሣሠሉት) ወይም የጉልበት አገልግሎት ታክስ አይከፈልበትም፡፡
5. አንድ የንግድ ድርጅት በበራሪ ወረቀት ወይም በፕሮግራምች ላይ ሰው እንዲጠቀሰለት ለሃይማነቱ ድርጅት ዕርዳታ የሰጠ እንደሆነ፣ የሃይማኖት ድርጅቱ ከንግድ ድርጅት የተቀበለው ዕርዳታ በክፍያ የተሰጠ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ አይወሰድም፡፡ ሆኖም በበራሪ ወረቀቶች ወይም በፕሮግራም ላይ በማስታወቂያ የተዘጋጁ ቦታዎችን የሃይማኖት ድርጅቱ የሸጠ እንደሆነ፣ ለአገልግሎቱ የተፈጸመው ክፍያ የሃይማኖት እና ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ አገልግሎት ከታክሱ ነፃ እንደሚሆኑ በተደነገገው የሚሸፈን አይሆንም።
6. በልማት ኮሚሽን ወይም በተመሣሣይ አካል ወይም ለዚሁ ዓላማ በተቋቋመ የሥራ ክፍል ወይም ቅርንጫፍ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት የሚያከናውን የሃይማኖት ድርጅት የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሥሩ ያሉ ኮሚሽኖች፣ የሥራ ክፍሎች፣ ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

24.<u>የሕክምና አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ ማድኃኒቶች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ረ) የሕክምና አገልግሎቶች እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት በሐኪም ትዕዛዝ ብቻ የሚሰጡ ናቸው ተብለው የተዘረዘሩት መድኃኒቶች ወደ አገር ሲገቡና በአገር ውስጥ ሲሸጡ ከታክሱ ነፃ እንደሚሆኑ ይደነጋጋል፡፡ ስለሆነም በክፍያ የተሰጠ ቢሆንም ባይሆንም ፣ ክፍያውን የፈፀመው ታካሚው ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገን ቢሆንም የሕክምና አገልግሎቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁለት ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነከታክሱ ነፃ ይሆናል፤

   ሀ/ የሕክምና አገልግሎቱ የተሰጠው በታወቀ የሕክምና ተቋም ወይም የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ ወይም በሁለቱም ከሆነ፤ እና

   ለ/ በዚህ ደንብ መሠረት ከታክሱ ነፃ ሊሆን የሚችል አገልግሎት ከሆነ፡፡
2. የሕክምና አገልገሎት ከታክሱ ነፃ ሊሆን የሚችለው የሕክምና ተቋም የተሰጠ ሲሆን ነው። ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የታወቀ የሕክምና ተቋም የሚባለው የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ሥራውን የሚያከናውንበት

ሥፍራ፣ ሆስፒታል፣ የማዋለድ አገልግሎት መስጫ ተቋምን ወይም ክሊኒክን ይጨምራል።

3. የሕክምና አገልግሎት ከታክሱ ነፃ ሊሆን የሚችለው የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ ሲሰጥ ነው። የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ ተሰጠው ባለሙያ የሚባለው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መመዝገብ ያለበትና ተመዝግቦ ማረጋገጫ የተሰጠው ዶክቶር፣ የባሕል ሐኪም፣ የጤና ረዳት፣ የጤናመኮንን፣ ፊዚዮቴራፒስት እና ሌሎችንም የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይጨምራል።
4. የህክምና አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በታወቀ የህክምና ተቋም የተሟላ አገልግሎት (የምግብና መኝታ ጨምሮ) ያላቸው እና የሕክምና አገልግሎቱ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ ሲሠጥ ይሆናል፡፡ የሕክምና አገልግሎቶች የአዕምሮ ጤንነት ማሻሻልን ጨምሮ፣ የጤንነት ምርመራ፣ በሽታን ማከም፣ መከላከል፣ የጤንነት ሁኔታን ማሻሻልን የሚያካትት ነው።
5. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው በታወቀ የሕክምና ተቋም ውስጥ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ በተሰጠው ባለሞያ ተኝቶ ለሚታከም ወይም ለተመላላሽ ታካሚ የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት እንዲሁም ምግብ እና መኝታ፣ እንክብካቤ እና ለታካሚው በተለይ በግል የሚደረግን ጥንቃቄ፣ ተኝቶ ወይም በተመላላሽ ለሚታከማው ሕመምተኛ የዕለት ተዕለት ዕርዳታ ማድረግን ይጨምራል።
6. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም ከታክሱ ነፃ የሆኑት የሕክምና አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ።
   ሀ/ የተለየ ክፍያ የማይጠየቅባቸው በሆስፒታል ወይም በክሊኒክ የሕክምናው ገልግሎት አካል ሆነው የሚሰጡ መድኃኒቶች፣
   ለ/ የላቦራቶሪ፣ የራጅ ወይም ሌሎች የምርመራ አገልግሎቶች፤
   ሐ/ የሕክምና አገልግሎት በመስጠት ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) የተዘረዘሩ የሕክምና መገልገያዎች፤

መ/ አስፈላጊ የሕክምና መሣሪያዎችን እና አቅርቦቶችን ጨምሮ በኦፕራሲዮን ክፍል፣ በተለየ የሕክምና ክትትል ክፍል እና በማደንዘዣ መስጫ መሣሪያዎች መጠቀም

ሠ/ ከታክሱ ነፃ ከሆኑ የሕክምና አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የጨረር ሕክምና፣ የፊዚዮቴራፒ ወይም የኦኩፔሽናል ቴራፒ አገልግሎትን መጠቀም፣

ረ/ ከታክሱ ነፃ የሆነውን የሕክምና አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዘ የሚቀርብ መኝታ እና ምግብ (ተኝተው ወይም በተመላላሽ ከሚታከሙ ሕመምተኞች በተጨማሪ ለሌሎች ሰዎች አገልግሎት ከሚሰጥ ምግብ ቤት በስተቀር)፤

ሰ/ ከታክሱ ነፃ ከሆነው የሕክምና አገልግሎት ጋር በተያያዘ በሕክምና ተቋሙ ሠራተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች (ከሕክምና ውጪ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሠራተኞችን ወይም ቴክኒሺያኖችን ጨምሮ)

ሸ/ ለአጠቃላይ የጥርስ ህክምና እና ውበትን ለመጨመር ካልሆነ በስተቀር በሕመም፣ በአደጋ ምክንያት በተፈጠረ ጉዳት፣ ባልተስተካከለ አፈጣጠር ምክንያት የሚደረግ የጥርስ፣ ወይም የአፍ ውስጥ ሕክምና፤

ቀ/ የአዕምሮ መረበሽን የማከም አገልግሎት፣

7. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) (ሐ) አፈፃፀም የሕክምና መገልገያ ማለት በታወቀ የሕክምና ተቋም የሚቀርብ ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ የሕክምና አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዘ በሐኪም ትዕዛዝ ጥቅም ላይ የሚውል መሣሪያ ነው፡፡

ሀ/ የአተነፋፈስ ወይም የልብ ምት መቆጣጠሪያ፣ የኩላሊት ቁሻሻን ማስወገጃ መሣሪያ፣ በራሱ መመገብ የማይችል ሰው የሚገለገልበት የመመገቢያ ዕቃ፣

ለ/ የሕክምና አገልግሎት አካል ሆኖ ለበሽተኞች የሚሰጥ የታወቁ የሰውነት ክፍሎችን የሚተካ ሰው ሰራሽ የሰውነት አካል፣ የአካል ድጋፍ መሣሪያ

ሐ/ ለታወቀ የሕክምና ተቋም የሚቀርብ የሕክምና ወይም የቀዶ ጥገና መሣሪያ ወይም እነዚህን መሣሪያዎች ተኝቶ ወይም በተመላላሽ ለሚታከም በሽተኛ ማከራየት፣

## 25.የትምህርት አገልግሎት

1. የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ (2)(ሠ) በትምህርት ተቋሞች የሚሰጥ የትምህርት አገልግሎት እና በመዋዕለ ሕፃናት የሚሰጥ የሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎት ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ስለሆነም ለትምህርት አገልግሎት በተለይ የሚፈፀሙ ክፍያዎች የሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ከታክሱ ነፃ ይሆናሉ።

   ሀ/ በዚህ ደንብ በተለይ የተመለከቱ፣

   ለ/ በታወቀ የትምህርት ተቋም ለተማሪዎች የሚሰጡ ከሆነ፣

2. ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ለመሆን አገልግሎቶቹ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ዕውቅና በተሰጣቸው ተቋሞች ለተማሪዎች የተሰጡ መሆን አለባቸው።

   ሀ/ በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣

   ለ/ በሙያ ኮሌጅ እና በዩኒቨርሲቲ እና

   ሐ/ የጐልማሶችን ትምህርት ለማስፋፋት የተቋቋሙ ተቋሞች፣ የእጅ ሙያ ማሠልጠኛዎች፣ የልዩ ሙያ ሥልጠና መስጫዎች ወይም የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኞችን ለማሠልጠን የተቋቋሙ ተቋሞች፣

3. በንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት የትምህርት ተቋሞች በግል ለትርፍ በተቋቋሙ ድርጅቶች ለትርፍ ባልተቋቋሙ ማኅበራት፣ በሃይማኖት ወይም በዕርዳታ ድርጅቶች ወይም በመንግሥት አካላት የሚካሔዱ ቢሆንም ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

4. በንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት የትምህርት ተቋሞች ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ዕውቅና ያገኙ ወይም አገልግሎቱን በሰጡበት ጊዜ ዕውቅና ለማግኘት በመገምገም ላይ ያሉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

5. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ የሆኑ የትምህርት አገልግሎቶች ናቸው፤

   ሀ/ ዕውቅና በተሰጠው የትምህርት ተቋም ለተማሪዎች የሚሰጡ ኮርሶች፤

   ለ/ ዕውቅና በተሰጠው የትምህርት ተቋም የትምህርቱ ፕሮግራም አካል ሆነው ለተማሪዎች በዓይነት የሚሰጡ የምግብ ወይም ሌሎች ከአገልግሎቱ ጋር ዝምድና ያላቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች፤

   ሐ/ በትምህርት ተቋሙ የሚሰጡ ከሆነ የፈተና መመሪያዎች እና ፈተና የመስጠት አገልግሎቶች፤

መ/ ዕውቅና ካገኘ ኮርስ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ የማስተማር ወይም የማጠናከሪያ ትምህርት አገልግሎት፤

6. ከትምህርት ተቋሙ ጋር በሚደረግ ውል መሠረት በግል ኩባንያ ከሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት በስተቀር ተማሪዎችን ከቤታቸው ወደቅድመ 1ኛ ደረጃ፣ አንደኛደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ለመውሰድ እና ወደ ቤታቸው ለመመለስ በትምህርት ተቋሙ የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት የትምህርት አገልግሎት እንደሆነ ተቆጥሮ ከታክሱ ነፃ ይሆናል፡፡

7. ለትምህርት አገልግሎት በተለይ የሚፈፀሙ ክፍያዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ/ ለትምህርት፣ ከትምህርት ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች፤ ከትምህርት ፕሮግራም ጋር ለተያያዙ እንቅስቃሴዎች እና ለሥልጠና የሚፈፀም ክፍያ፤

ለ/ ከትምህርት ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች ግዴታ ሆነው የተጣሉ ክፍያዎች ከታክሱ ነፃ የሆኑ የትምህርት አገልግሎቶች ይሆናሉ።

ሐ/ የተማሪዎች ምክር ቤት ክፍያ፣ የአትሌቲክስ ክፍያ እና ለኮርስ ከመመዝገብ ጋር በተያያዘ በግድ መፈፀም ያለባቸው ክፍያዎች፤

መ/ ለሪፖርት ካርድ፣ ለመፃሕፍት ቤት አገልግሎት፣ ለመታወቂያ ካርድ፣ ለመረጃ ጥበቃ እና ከትምህርት ኮርሶች ጋር በቀጥታ ለተያያዙ እና በትምህርት ተቋሙ ለሚሰጡ ሌሎች አስተዳደራዊ አገልግሎቶች የሚፈፀም ክፍያ፤

ሠ/ ለኮርስ ማቴሪያሎች፣ ትምህርቱን በሚሰጠው ተቋም ለሚቀርቡ ከትምህርት ፕሮግራም ጋር ለተያያዙ ዕቃዎች ኪራይ (ለምሳሌ የሙዚቃ መሣሪያዎች ኪራይ)፣ በአመዛኙ የመዝናኛ ባህሪ ካለው በስተቀር ከትምህርት ፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ የሚደረግ ጉብኝት እና

ረ/ ትምህርቱን በሚሰጠው ተቋም ለተማሪዎች የሚቀርብ የመኝታ አገልግሎት (ሆስቴልን ጨምሮ)

8. ከትምህርት ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች የሚፈፀሙ ክፍያዎች፣ ለሕንፃ ለሜዳዎች፣ ለመፃሕፍት ቤቶች፣ ለኮምፒውተር፣ ለሣይንስ እና ለሌሎች ቤተ ሙከራዎች የሚፈፀመውን ክፍያ ይጨምራሉ።

9. ከታክሱ ነፃ የተደረገው የትምህርት አገልግሎት የሚከተሉትን አይጨምርም፤

ሀ/ ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ የሚያስገኙ ፕሮግራሞች አካል ካልሆኑ በስተቀር ስፖርት፣ ጨዋታዎች፣ የቪዲዮ ቀረፃ ወይም የፎቶግራፍ ወይም የጊዜ ማሳለፊያ ወይም የመዝናኛ ተግባራት፣

ለ/ የግል ዕውቀትን ለማዳበር ታስበው ለሚሰጡ ፎቶግራፍን በፎቶግራፍ ማስቀመጫ የማስቀመጥ፣ የምግብ ዝግጅት እና የግል ሁኔታን ለማሻሻል የሚሰጡ ኮርሶች፣

ሐ/ የትምህርት ፕሮግራም አካል ያልሆነ የሙዚቃትምህርት፤

10. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የኃይማኖት ትምህርት እየተከታተሉ የኃይማኖት አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ተማሪዎች ሆነው ይቆጠራሉ።

11. በንዑስ አንቀጽ (4) ከታክሱ ነፃ ከተደረጉት አገልግሎቶች በተጨማሪ በቅደመ-አንደኛ ደረጃ፤ በአንደኛ ደረጃ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጡ ከታክሱ ነፃ የሆኑ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ/ የልዩ ትምህርት ኮርሶችን ጨምሮ መሠረታዊ ትምህርቶች፤

ለ/ በት/ቤቶች ለሚሰጡ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ወይም ከትምህርት በኋላ ለሚካሄዱ ፕሮግራሞች የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

ሐ/ በት/ቤቶች የሙዚቃ መሣሪያዎች ወይም የስፖርት ዕቃዎች ለመጠቀም የሚፈፀሙ ክፍያዎች፤

መ/ የትምህርቱ ፕሮግራም አካል ሆነው በተማሪዎች ወይም በመምህራኖቻቸው የሚሰጡ አገልግሎቶች፤እና

ሠ/ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚካሔዱ ጫወታዎች፣ ዳንሶች፤ የመስክ ጉዞዎች ወይም በሌሎች በት/ቤት ውስጥ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ ለመሆን የሚፈጽሙዋቸው ክፍያዎች፤

12. ከታክሱ ነፃ የሆኑ በዩኒቨርሲቲዎች ወይም በቴክኒክ ኮሌጆች የሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ተማሪው የዲግሪ ወይም የዲፕሎማ ፕሮግራሞችን የሚከታተል ቢሆንም ባይሆንም ለዲግሪ ወይም ለዲፕሎማ የሚያበቁ ኮርሶችን በተልዕኮ ትምህርት መስጠትን ይጨምራል።

13. ከታክሱ ነፃ የሆነው የጐልማሶች ትምህርት፣ የሙያ ሥልጠና፣ የቴክኒክ ትምህርት እና ለአካል ወይም ለአዕምሮ ጉዳተኞች የሚሰጥ ትምህርት እና ሥልጠና የሚከተሉት ይጨምራል፤

ሀ/ ለዲግሪ ወይም ለዲፕሎማ የሚያበቁ ለጎልማሶች የሚሰጡ ኮርሶች ወይም በኮርሱ ተሳታፊ የሚሆኑ ተማሪዎችን ከቅጥር ጋር የተያያዘ ክሕሎትለማሳደግ ያስችላሉ የተባሉ ኮርሶች፤

ለ/ የተማሪዎችን የሙያ ክሕሎት ለማሻሻል ወይም ለማሳደግ የሚያስችሉ በሙያ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ኮርሶች፣

ሐ/ አግባብ ባለው ፈቃድሰጪ የመንግሥት መ/ቤት የተሰጠውን የሙያ ወይም የንግድ ዕውቅና ወይም ስያሜ ለማቆየት ወይም ደረጃውን ለማሻሻል የሚያስችሉ ኮርሶች፤

መ/ ዕውቅና ወይም ስያሜ ለማግኘት በሚሰጡ ኮርሶች ወይም ፕሮግራሞች ፈተና ወይም የምስክር ወረቀት መስጠት፣

14.ኮርሶች ከቅጥር ጋር የተያያዘውን ክህሎት ያሳድጋሉ የሚባለው የኮርሱ ዓላማ ተማሪዎች የሚቀስሙትን ክህሎት በትክክል የሚገልጽ እና ተማሪዎች የቀሰሙትን ክህሎት ለመዝናኛ፣ ለትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ፣ ለኪነጥበብ ወይም ለባህል ሳይሆን በተቀጠሩበት መ/ቤት፤ በሙያ ወይም በንግድ ሥራ መስክ ያውሉታል የሚል ግምት ካለ ነው።

15.ለትምህርት አገልግሎቶች የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት የሚከተሉትን አይጨምርም፤

ሀ/ የትምህርት ተቋሙ የትምህርት አገልግሎት መስጫዎችን ከት/ቤቱ ውጪ ላሉ ቡድኖች ያከራየ እንደሆነ፤

ለ/ ለአጠቃላዩ ኅብረተሰብ ክፍት በሆነ ሁኔታ በት/ቤቱ በሚካሄዱ የአትሌቲክስ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ የሚያስችል ክፍያ መጠየቅ፤

ሐ/ በትምህርት ተቋሙ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሣንቲም የሚሠሩ ማሽኖችን በማስቀመጥ የሚገኝ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ፤ እና

መ/ የትምህርት ቤቱን አርማ የመሳሰሉ ከትምህርት ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ማቴሪያሎች በመሸጥ የሚገኝ ገቢ፤

26.<u>ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ አቅርበቶች እና በተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸውን መልሶ ለማቋቋም ከአገር ውስጥ የሚገዙና ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች</u>

1. ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ አቅርቦቶች ከታክስ ነፃ እንደሚሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሸ) የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው በበጎ አድራጎት

ድርጅትነት የተመዘገቡ ድርጅቶች ለዚሁ ዓላማ ወደ አገር ለሚያስገቧቸው እና በአገር ውስጥ ለሚገዟቸው ዕቃዎች ነው።

2. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሸ) ከታክሱ ነፃ ስለመሆን የተደነገገው ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ በመድረሱ ምክንያት የአደጋ መከላከያና ዝግጁነት ኮሚሽን ባደረገው የዕርዳታ ጥሪ መሠረት ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎችን ይጨምራል።

27.<u>ውሃ</u>

በፋብሪካ ታሽጎ ከሚሸጥ ውሃ በስተቀር የውሃ አቅርቦት በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ቀ) በተደነገገው መሠረት ከታክሱ ነፃ ነው

28.<u>በሕግ ወይም በስምምነት ከታክሱ ነፃ የተደረጉ ወደ አገርየሚገቡ ዕቃዎች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2)(በ) በሕግ ወይም በስምምነት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ከሌሎች ታክሶች ነፃ የተደረጉ ድርጅቶች ተቋሞችና ፕሮጀክቶች ወደ አገር ለሚያስገቧቸው ዕቃዎች ከታክስ ነፃ እንደሚሆኑ ተደንግጓል።
2. ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ በአዋጅ የተፈቀደ፤ ወይም በአዋጅ በተሰጠ ሥልጣን መሠረት በደንብ ወይም በመመሪያ ከታክስ ነፃ የሆኑት ከታክሱ በሕግ ነፃ የተደረጉ በሚለው ተካተው ነፃ ይሆናሉ።
3. በስምምነት ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተፈፃሚ የሚሆነው በመንግሥት ወይም በመንግሥት በተሰጠ ፈቃድ መሠረት በተደረጉ ስምምነቶች ነፃ የተደረገ ሲሆን ብቻ ነው።
4. በስምምነት ከታክሱ ነፃ የተረጉ የሚለው ከዚህ በታችየተዘረዘሩትን ይጨምራል።

   ሀ/ በኢትዮጵያ መንግሥትና በማናቸውም ድርጅት ወይም በማናቸውም አገር መንግሥት መካከል የተደረገ የቴክኒክ ትብብር ወይም የሰብዓዊ ዕርዳታ ስምምነት፤

   ለ/ በዲፕሎማቲክ ልዩ መብቶችና ጥቅሞች ደንብ የተፈቀደ፣

   ሐ/ የኢትዮጵያ ሕግ አካል በሆነ ዓለም አቀፍ ስምምነት፤

   መ/ ማናቸውም ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት ሌላ የባለብዙ ወገን ስምምነት፤

29.<u>ትራንስፖርት</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2)(ቸ) ለትራንስፖርት አገልግሎት የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት በማናቸውም ዓይነት ትራንስፖርት ሰዎችንዎችን ለማጓጓዝ የሚፈፀምን ክፍያ ያካትታል፡፡
2. ዕቃዎችን ወይም መንገደኞችን በዓለም አቀፍ ትራንስፖርት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የማጓጓዝ እንቅስቃሴ በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ቸ) መሠረት ከታክሱ ነፃ በሆነው ሥር የሚወድቅ ከሆነ፤ ይህ እንቅስቃሴ በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ይሆናል።

## 30. ፈቃድ ለማግኘት የሚፈጸሙ ክፍያዎች

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) (ነ) ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ የሚፈፀም ክፍያ ከታክስ ነፃ እንደሚሆን የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው በመንግሥት አካላት ለሚሰጡ ፈቃዶች ብቻነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸውን መብቶች ለመጠቀም ወይም ለሌሎች በንብረት መጠቀም ለመሳሰሉ መብቶች በግል ተዋዋዮች የሚሰጡ ፈቃዶችን አይጨምርም።

## 31. በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ለ) ከቀረጥ ነፃ ስለተደረጉ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች

በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) (ኘ) በተደነገገው መሠረት በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ቀረጥ ነፃ የተደረጉ ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደው ተፈጻሚ የሚሆነው በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ለ) ለተዘረዘሩት እና በደንቡ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ከቀረጥ ነፃ ለሆኑ ዕቃዎች ብቻ ነው፡፡

## 32. አካል ጉዳተኞች የሚሠሩባቸው ድርጅቶች

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) (አ) የተደነገገው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተፈጸሚ የሚሆነው የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኞችን ቀጥረው የሚያሠሩ ድርጅቶች ለሚያቀርቧቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ብቻ ነው።
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ከሠራተኞቻቸው መካከል 60 በመቶ አካል ጉዳተኞች መሆናቸው የተረጋገጠ ድርጅቶች ናቸው። ከሠራተኞች መካከል 60

በመቶ አካል ጉዳተኞች መሆናቸው የሚረጋገጠው ባለፉት 12 ወራት ከነበሩት ጠቅላላ ሠራተኞች መካከል የአካል ጉዳተኞችን ቁጥር በመቶኛ በመውሰድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ድርጅቱ ስራ ከጀመረ ከ12 ወራት በታች ከሆነ ድርጅቱ ሥራ ላይ በቆየባቸው ጊዜያት ያሉት ሰራተኞች ብዛት በመለኪያነት ያገለግላል፡፡

33.<u>መጻህፍት</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2)(ወ) ከታክሱ ነጻ ስለመሆን የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው ለታተሙ መጻህፍት እና መፅሀፍትን ወቅታዊ ለማድረግ ለሚወጡ እትሞች ነው፡፡ይህ ከታክሱ ነፃ መብት ለታተሙ ወይም ላልታተሙ የኃማይኖት ጽሑፎች ጭምር ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡
2. የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ወ) ለዓይነሥውራን ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች በተለይ የተዘጋጁ ተናጋሪ መጻህፍት ወደአገር በሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ጊዜ ተፈጻሚ ከሚሆን በስተቀር ለሌሎች ተናጋሪ መጻህፍት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## <u>ክፍል 3</u>

## <u>በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች</u>

34.<u>ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ መሆኑን ስለማስረዳት</u>

የተመዘገበው ሰው በዚህ ደንብ መሰረት ለአቅርቦቱ ዜሮ የማስከፈያ ልክን ተፈጻሚ ተፈጻሚ ያደረገ ከሆነ፣ ዜሮ የማስከፈያ ልክን ለመጠቀም ብቁ የሚያደርጉትን እና በታክሱ ባለሥልጣን ተቀባይነት ያላቸውን የሰነድ መረጃዎች ተቀብሎ መያዝ አለበት።

35.<u>ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን ወደውጭ ስለመላክ</u>

1. በዚህ አንቀጽ ውስጥ፦

ሀ/ “ዕቃዎች የሚላኩበት አገር” ማለት ከኢትዮጵያ ውጪ ያለ ማናቸውም አገር ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝን ማናቸውንም ቦታ ይጨምራል። ሆኖም

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ[99] በሚያወጣው መመሪያ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚላኩበት አገር ተብሎ አይወሰድም ብሎ የሚሰይመውን የተለየ አገር ወይም ግዛት አይጨምርም።

ለ/ "ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የተላኩ" ማለት የተመዘገበ ሰው በሽያጭ ወይም በዱቤ ሽያጭ ስምምነት መሠረት ከሚያቀርባቸው የሚንቀሣቀሱ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ፦

1. በተመዘገበው ሰው ተቀባዩ ባለበት አገር በሚገኝ አድራሻ የተላከ ለመሆኑ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ተቀባይነት ባለው የሰነድ መረጃ የተረጋገጠ፣
2. አውሮፕላኑ ዕቃዎቹ ወደሚላኩበት አገር የሚጓዝ ከሆነ የተመዘገበው ሰው ወደውጭ አገር ለሚሄድ አውሮፕላን ባለቤት ወይም ተከራይ ዕቃዎቹን ሲያስረክብ ወይም ዕቃዎቹ በአውሮፕላኑ ውስጥ በጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ፣

2. የሚከተሉት ወደውጭ አገር የሚላኩ አቅርቦቶች በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው ናቸው፤

ሀ/ አቅራቢው ወደውጭ እንዲላኩ በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ዲክላራሲዮን የሞላባቸው እና በአቅራቢያው ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር የተላኩ ዕቃዎች፣

ለ/ በአቅራቢያው ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር የተላኩ ስለመሆኑ የታክሱ ባለሥልጣን ማረጋገጫ ያገኘባቸው ዕቃዎች፣

ሐ/ አቅርቦቱ በተፈፀመ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበሩ እና አቅራቢው በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ ወደአገርመልሶየማያስገባቸው ዕቃዎች፣

መ/ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የተሰጠአገልግሎት

i. አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ የነበረ ተንቀሣቃሽ ንብረት፣

---

[99] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ተብሎ ይነበብ፡፡

ii. በጉምሩክ አዋጅ ምዕራፍ 5 መሠረት በጊዜያዊነት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች፣

iii. "ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር ለተላኩ ዕቃዎች" በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈኑ በፊደል (ለ) (1) ወይም (ለ) (2) የተመለከቱ ዕቃዎች አቅርቦት፣

ሠ/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (መ) (ii) ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው ዕቃዎችጥገና፣ ዕድሣት፣ ማሻሻያ ወይም ሕክምና በማድረግ ሂደት ጥቅም ላይየሚውሉ ዕቃዎች እና

I. በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የተለጠፉ፣ የተገጠሙ፣ ከእነዚሁ ጋር የተያያዙ ወይም የእነዚሁ አካል የሆኑ ዕቃዎች፣

II. በጥገና በዕድሣት፣ በማሻሻያ ወይም በማስተካከያ ሥራዎች ሂደት ጥቅም ላይ የማይውሉ ወይም ዋጋ የማይኖራቸው የፍጆታ ዕቃዎች፣

ረ/ ከኢትዮጵያ ውጪ ካለ መሬት ወይም በዚሁ መሬት ላይ ማናቸውንም ማሻሻያ ከማድረግጋር በቀጥታ በተያያዘ ሁኔታ የተሰጠ አገልግሎት፣

ሰ/ "ከኢትዮጵያወደውጭ አገር ለተላኩ ዕቃዎች" በተሰጠው ትርጉም ከሚሸፈኑ በፊደል ለ (1) ወይም ለ(2) ከተመለከቱ ዕቃዎች አቅርቦት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

ሸ/ ከኢትዮጵያ ውጪ የተሰጡአገልግሎቶች፤

ቀ/ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አገልግሎቶች በስተቀር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ እና አገልግሎት በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ ለነበረ ሰው የተሰጡ አገልግሎቶች፣

i. በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ጋር በቀጥታ የሚያያዙ አገልግሎቶች፣

ii. አገልግሎቱ ከተሰጠ በኋላ የሚንቀሣቀሰው ንብረት ከኢትዮጵያ ውጪ ካልተላከ በስተቀር አገልግሎቱ በተሰጠ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለ የሚንቀሣቀስ ንብረት ጋር በቀጥታ በተያያዘ ሁኔታ የተሰጠ አገልግሎት፣

iii. በኢትዮጵያ ውስጥ ማናቸውንም ታክስ የሚከፈልበትን አገልግሎት ለመስጠት መታቀብን የሚጨምሩ አገልግሎቶች፣

iv. ኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት የሚያካሂድን ሰው ያለማወክን የሚጨምሩ አገልግሎቶች፣

በ/ የሚከተሉትን የሚጨምሩ አገልግሎቶች፡-

i. በአዕምሮአዊ ሀብት መብቶች ከኢትዮጵያ ውጪ ለመጠቀም ማሰመዝገብ፣ መከታተል፣ መስጠት፣ ለመጠበቅ፣ ማዘዋወር፣ ማሰተላለፍ፣ ፈቃድ መስጠት ወይም ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ፣

ii. በንዑስ አንቀጽ (i) የተመለከተውን አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆኑ ተጓዳኝ አገልግሎቶች፣

iii. የአዕምሮአዊ ሀብት መብቶችን ከኢትዮጵያ ውጪ በሙሉ ወይም በከፊል በጥቅም ላይ ከማዋል ለመታቀብ ግዴታ የሚያስገቡ ሁኔታዎችን መቀበል፤

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክሱ እንዲከፈልባቸው ለማድረግ ዕቃዎቹ በሚወጡበት ወደብ የሚገኘው ላኪ ዕቃዎችን ለይቶ ማሳየት እና በባለሥልጣኑ የሚጠየቀውን የሰነድ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

4. በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ(2)(ሀ) ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች በዜሮ የማሰከፈያ ልክ ታክሱ እንደሚከፈልባቸው የተደነገገው ለውጭ ገበያ የሚልከው አቅራቢ መልሶ ወደአገር ላስገባቸው ወይም ለሚያስገባቸው ዕቃዎች ተፈጻሚ አይሆንም።

5. የተመዘገበ ሻጭ ዕቃዎቹን ወደውጭ አገር ለሚልክ የተመዘገበ ገዥ፣ የተፈጠሮ ሀብት ውጤቶችን ጨምሮ ማናቸውንም ግዙፋዊ ህልዎት ያላቸውን የግል ንብረቶች (የአልኮል መጠጦችን፣ ቢራ ወይም ትምባሆ ሳይጨምር) የሸጠ እንደሆነ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ዕቃዎቹ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግባቸው ይሆናል፦

ሀ/ ለሽያጭ የቀረቡት ዕቃዎች ዓይነት እና አግባብነት እስካለው ድረስ የገዥውን መደበኛ የንግድ ሥራ አካሄድ ባህርይ ጨምሮ የእያንዳንዱን የግዥ ሁኔታ መሠረት በማድረግ እንቅስቃሴው ይወስዳል ተብሎ በሚገመት አጭርጊዜ ውስጥ የተረከባቸውን ንብረቶች ለውጭ ገበያ የላከ ከሆነ፣

ለ/ ላኪው ዕቃዎቹን የገዛው ወደውጭ አገር ከመላካቸው በፊት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወይም በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ ወይም በገበያ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ካልሆነ፣

ሐ/ አስፈላጊነቱ አጥጋቢ በሆነ ምክንያት የተደገፈ ወይም ዕቃውን ከማጓጓዝ ተግባር ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ካልሆነ በስተቀር ዕቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ተጨማሪ የምርት ሂደት እንዲያልፉ፣ ባህሪያቸው እንዲቀየር ወይም ማሻሻያ እዲደረግባቸው ካልተደረገ፣

መ/ አቅራቢው ዕቃዎቹ በገዥው ወደውጭ አገር የተላኩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ፣

6. ለንዑስ አንቀጽ (5) አፈጻጸም፤

ሀ/ ገዥው ዕቃዎቹን ወደውጭ አገር ለመላክ ያቀደ እና በእርግጠኝነት የሚልካቸው መሆን አለበት።

ለ/ የገዛቸውን ዕቃዎች ወደውጭ አገር ለሚልክ የተመዘገበ ሰው ለመሸጥ ላቀደ ሰው የሚፈጸም ሽያጭ ወደውጭ አገር ለሚልክ ሰው እንደተፈጸመ አቅርቦት አይቆጠርም፣

ሐ/ ዕቃዎች በምርት ሂደት እንዲያልፉ፣ ባህሪያቸው እንዲቀየር ወይም ማሻሻያ እንዲደረግባቸው ማድረግ ከተፈጥሮአዊ ለውጥ በስተቀር በዕቃዎቹ ላይ አካላዊ ወይም ኬሚካላዊ ለውጥ ማስከተል የሚችልን አዘገጃጀት፣ አያያዝ ወይም ሌላ ተግባር ይጨምራል። ሆኖም የዕቃ ቆጠራ፣ ማቀዝቀዝ፣ በመጋዘን ማስቀመጥ ወደውጭ ለመላክ ማሸግ ወይም እንደገና ማሸግ፣ በሚላክበት አኳኋን ምልክት ማድረግ፣ ወደውጭ በሚላከበት ሣጥን መክተት፣ መጫን ወይም ማውረድ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን አይጨምርም።

መ/ ዕቃዎች ወደውጭ አገር የተላኩ መሆኑን የሚያረጋግጠው ማስረጃ በታክስ ባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባለው ቅጽ የተዘጋጀ ዕቃው ወደ ውጭ መላኩን የሚያረጋግጥ በገዥው የሚቀርብ የምስክር ወረቀት መሆን አለበት፡፡

## 36.<u>የዕቃዎች ወይም የመንገደኞች ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት</u>

1. በዚህ አንቀጽ ውስጥ

ሀ/ “ለትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ የሆነ አገልግሎት” ማለት ዕቃዎችን የመጫን እና የማውረድ አገልግሎት፣ ጭነቱን የማሰር ወይም ደኅንነቱን የማረጋገጥ

አገልግሎት፣ጭነቱን የመመርመር አገልግሎት፣ የጉምሩክ ሰነዶችን የማዘጋጀት፣ ኮንቴይነር የመጫንና የማውረድ አገልግሎት፣ የተጓጓዘውን ወይም ለመጓጓዝ የተዘጋጀውን ዕቃ በመጋዘን የማስቀመጥ አገልግሎት ነው።

ለ/ “ወደውጭ አገር የሚበር አውሮፕላን” ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በዋነኛነት በኢትዮጵያ በሚገኝ አውሮፕላን ማረፊያ እና ዕቃዎች ወደውጭ አገር በሚላኩበት አውሮፕላን ማረፊያ መካከል ወይም ዕቃዎች ወደውጭ አገር በሚላኩባቸው አውሮፕላን ማረፊያዎች ከአንዱ ወደሌላው ሰዎችን እና ዕቃዎችን በክፍያ በማጓጓዝ ተግባር ላይ የተሠማራ አውሮፕላን ነው።

ሐ/ “ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት ማለት”

1. ለትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ ከሆኑ አገልግሎቶች በስተቀር ሰዎችን እና ዕቃዎችን፦
   i. ጉዞው ወይም የጉዞው ከፊል የኢትዮጵያን ግዛት አቋርጦ የሚሄድ ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ ወጪ ከሆነ አንድ ቦታ ከኢትዮጵያ ወደሆነ ሌላ ቦታ፣
   ii. ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኝ ቦታ፣
   iii. በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ ቦታ ከኢትዮጵያ ውጭ ወደሚገኝ ቦታ፣

   በየብስ፣ በውሃ፣ በአየር የማጓጓዝ አገልግሎት፣
2. ጉዞው በአውሮፕላን የሚፈፀም እና በዓለም ዐቀፍ የሲቪል አቪየሽን ኮንቬንሽን አንቀጽ 8 “ለዓለም አቀፍ ማጓጓዣ” በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈን እስከሆነ ድረስ መንገደኞችን በኢትዮጵያ ውስጥ ካለ አንድ ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ ማጓጓዝ፣
3. አገልግሎቱ በዚህ ትርጉም ፊደል “ሀ” የተዘረዘሩት አገልግሎቶች አካል በመሆን በአንድ አገልግሎት ሰጪ የሚሰጥ እስከሆነ ድረስ ለትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ የሆነ አገልግሎቶችን ጨምሮ ዕቃዎችን በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ በማጓጓዝ የሚሰጥ አገልግሎት፤ ወይም
4. በዚህ ትርጉም ከፊደል (ሀ) እስከ (ሐ) የተመለከቱት ተፈጻሚ ለሚሆኑባቸው፤ የመድን አገልግሎት፣ የመድን፣ የመንገደኞች እና የዕቃ ማጓጓዝ አገልግሎቶችን የማመቻቸት አገልግሎት፡፡

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አቅርቦቶች በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) በተደነገገው መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግባቸዋል፤

ሀ/ ዕቃዎቹ በተላኩበት የውጭ አገር ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ በኪራይ ውል እና በቻርተር ውል መሠረት ዕቃዎችን ማቅረብ፤

ለ/ አውሮፕላኑ ከኢትዮጵያ ውጭ ወደሆነ አገር የሚበር እና ዕቃዎቹ በአውሮፕላን ውስጥ ለፍጆታ ወይም ጥቅም ላይ የሚውሉ እስከሆነ ድረስ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚጓዝ አውሮፕላን ባለቤት ወይም ተከራይ ዕቃዎችን ማቅረብ፤

ሐ/ ዓለም ዐቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

መ/ ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚጓዝ አውሮፕላን የጥገና፣ የፅዳት ወይም የሙሉ ዕድሣት አገልግሎት መስጠት፣

ሠ/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች በወኪል ወይም በሌላ ሰው አማካይነት ሳይሆን በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው በቀጥታ መስጠት፣

i. ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚጓዝ አውሮፕላን በኢትዮጵያ ውስጥ ባለበት ጊዜ የሚሰጥ የማስተናገድ፣ የማብረር፣ የማዳን፣ የመጐተት አገልግሎት፣

ii. ከኢትዮጵያ ውጭ የሚጓዝን አውሮፕላን ሥራ ላይ ከማዋል ወይም ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ አገልግሎት መስጠት፣

ረ/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያካትት አገልግሎት በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው መስጠት፡-

i. የዚህ አንቀጽ ንዑሰ አንቀጽ 2(መ) ወይም (ሠ) ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን አገልግለሎቶች፣

ii. ለትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ የሆኑ አገልግሎቶችን ጨምሮ ዕቃዎችን በኢትዮጵያ ውስጥ የማጓጓዝ አገልግሎት፣

ሠ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ያልተመዘገበ ሰው ለሚያካሒደው የባቡር ትራንስፖርት የሚሰጥ የጥገና እና የዕድሣት፣ የፅዳት አገልግሎት፤

37. <u>ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለሚቀርብ ወርቅ</u>

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) (ሐ) መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግበት ሲሆን ለኢትዮጵያ

ብሔራዊ ባንክ አገልግሎት እንዲውል ወደአገር የሚገባ ወርቅ በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2)(መ) መሠረት ከታክሱ ነፃ ነው፡፡

38.<u>በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝን ድርጅት ስለማስተላለፍ</u>

1. አንድ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ድርጅት የተላለፈ እንደሆነ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ወይም የንግድ ሥራውን ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደተከናወነ አቅርቦት እንደሚቆጠር በአዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (9) ተደንግጓል። ስለሆነም የማስተላለፉ ተግባር በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (10) እና አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 (መ) የተዘረዘሩትን መለኪያዎች የሚያሟላ ከሆነ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግበታል። በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (11) በተዘረዘሩት ሁኔታዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በተከናወነው የማስተላለፍ ተግባር የዜሮ ማስከፈያ ልክ ተጠቃሚ እንዲሆን ከተደረገ፣ የማስተላለፉ ተግባር በመንቀሳቀስ ላይ ያለውን ድርጅት ለገዛው ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።
2. የዜሮ ማስከፈያ ልክ ተጠቃሚ ለመሆን ተዋዋይ ወገኖች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው።

   ሀ/ ግብይቱ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝን ድርጅት ከአንድ የተመዘገበ ሰው ወደሌላ የተመዘገበ ሰው የማስተላለፍ ተግባር መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

   ለ/ የማስተላለፍ ተግባር የተፈፀመ መሆኑን የሚገልጽ በአስተላለፊው እና በተላለፈለት ሰው የተፈረመበት ማስታወቂያ ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት።

   ሐ/ ማስታወቂያው የማስተላለፉ ተግባር በተፈፀመ በ21 ቀን ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን ሊደርስ ይገባል።

   መ/ ማስታወቂያው ስለአቅርቦቱ መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን የሚዘረዝር መሆን አለበት፡፡
3. በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት ሊባል የሚችለው ራሱን ችሎ ሊሠራ የሚችልና ገቢ የሚያመነጭ፣ ማስተላለፉ ከተፈፀመ በኋላ በእርግጠኝነት ያለማቋረጥ የሚንቀሳቀስ እና ወደፊትም ሊንቀሳቀስ የሚችል ሲሆን ነው። ሆኖም ተግባራዊ

እንቅስቃሴ የማያደርግ ለወደፊት ይሠራል ተብሎ የሚታሰብ የንግድ ሥራ ሊሆን አይችልም።

4. የተላለፈው የንግድ ሥራ አትራፊ ባይሆንም ወይም የከሰረ በመሆኑ ምክንያት ለሂሣብ አጣሪዎች ለአስተዳዳሪዎች፣ ለባለአደራዎች ወይም የከሰረን ሰው ንብረት እንዲያጣራ ለሚሾም ለማናቸውም ሌላ ሰው በመተላለፍ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ሆኖ ይወሰዳል።
5. በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት በማስተላለፍ ተግባር ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ድርጊቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በፀናበት ቀን ወይም ከዚህ ቀን በኋላ የተፈፀመ ከሆነ ብቻ ነው።
6. በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት የማስተላለፍ ተግባር በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 (መ) በተደነገገው ዜሮ የማስከፈያ ልክ ሊካተት የሚችለው በመንቀሳቀስ ላይ ያለን የንግድ ሥራ ከሽርክና ማኅበር በሕግ የሰውነት መብት ወደተሰጠው ኩባንያ መለወጥን የመሳሰለ የሕግ አቋም ለውጥ ማድረግ ወይም የንግድ ሥራውን አካሔድ ቅርፅ መቀየር ከሆነ ነው።
7. የንግድ ሥራው ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ እስከቻለ ድረስ የተላለፈለት ሰው ገቢ የሚያመነጨውን እንቅስቃሴ ራሱ እንዲያካሂድ መደረጉ አስፈላጊ አይሆንም።
8. የእርሻ መሬትን ማስተላለፍ በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት ማስተላለፍ ተደርጎ አይወሰድም።ሆኖም ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ እስከታች ድረስ የግጦሽ መሬትን ከመሣሪያዎቹ እና ከከብቶቹ ጋር የማስተላለፍ ተግባር በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት ማስተላለፍ ይሆናል።
9. በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት የማስተላለፍ ተግባር በእርግጠኝነት የተፈፀመ ቢሆንም፣ አስተላላፊው እና የተላለፈለት ሰው የተመዘገቡ ካልሆነ እና በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት አቅርቦት የተፈፀመ ሆኖ እንዲቆጠር በመጠየቅ በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) መሠረት ሁለቱም የፈረሙበት ማስታወቂያ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ አይቻልም።
10. ማስታወቂያ የሚቀርብበት የ21 ቀን ጊዜ የሚወሰነው በአዋጁ አንቀጽ 11 የተመለከተውን አቅርቦቱ ተፈፀመ የሚባልበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

11. በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት የተላለፈለት ሰው አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ፣ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ለአቅርቦቱ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የማስተላለፉ ተግባር በተፈፀመበት ቀን የተመዘገበ እንደሆነ ነው።
12. ተዋዋይ ወገኖች ተፈላጊውን ማስታወቂያ ያቀረቡ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2(መ)በተደነገገው መሠረት የማስተላለፉ ተግባር ለዜሮ የማስከፈያ ልክ ብቁ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ፣ ለአቅርቦቱ የተፈፀመው ክፍያ የተጨማሪ እሴት ታክስን የማይጨምር እንደሆነ ይቆጠራል። በመሆኑም የማስተላለፉ ተግባር ታክስ ይከፈልበታል፣ የተላለፈለትም ሰው በአዋጁ በተፈቀደው መጠን የታክስ ማቀናነስ እንዲደረግለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡
13. በዚህ አንቀጽ መሠረት ለታክሱ ባለሥልጣን የሚቀርበው ማስታወቂያ የተላለፉትን ንብረቶች የተሟላ ዝርዝር፣ የእያንዳንዱን የተላለፈ ንብረት የገበያ ዋጋ፣ አስተላላፊው የሚያካሒደውን የንግድ ሥራ ባህሪ፣ ንብረቱ የተላለፈለት ሰው በንብረቱ የሚያካሂደውን የንግድ ሥራ ዓይነት፣ አስተላላፊው በተላለፉት ንብረቶች የንግድ ሥራ ሲያካሂድ የቆየበትን ጊዜ ልክ የሚጨምር መረጃ መያዝ አለበት፡፡ የታክሱ ባለሥልጣን ከአስተላላፊው ወይም ከተላለፈለት ሰው ወይም ከሁለቱም ተጨማሪ መረጃ ሊጠይቅ ይችላል።
14. አስተላላፊው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘውን ድርጅት በማስተላለፉ ምክንያት ምዝገባው እንዲሠረዝ ያደረገ እንደሆነ፣ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ድርጅት አካል ሆነው ያልተላለፉ ዕቃዎች አስተላላፊው በገበያ ዋጋ ያቀረባቸው ዕቃዎች ሆነው ይቆጠራሉ። ሆኖም ይህ ድንጋጌ አስተላላፊው በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት የታክስ ማቀናነስ በማያገኝባቸው ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።
15. አስተላላፊው እና የተላለፌለት ሰው በጋራ ፈርመው በሚያቀርቡት ማመልከቻ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጭምር እንዲተላለፉ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የታክሱ ባለሥልጣን ጥያቄውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ብቸኛ ሥልጣን አለው።
16. በንዑስ አንቀጽ (15) መሠረት የሚቀርበው ጥያቄ በታክሱ ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ፡-

ሀ/አስተላላፊው ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ለተላለፈለት ሰው መስጠት ያለበት ሲሆን፣ የተላለፈለትም ሰው እነዚህን ሰነዶች በአዋጁ አንቀጽ 37 እስከተመለከተው የጊዜ ገደብ ድረስ ይዞ ማቆየት አለበት፡፡

ለ/ አስተላላፊው የንግድ ሥራው ባለቤት ሆኖ በቆየበት ጊዜ ውስጥ የሚፈለገውን ማናቸውንም የተጨማሪ እሴት ታክስ ዕዳ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች እንዲከፍሉ የሕግ ግዴታ አለባቸው።

39.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

የገቢዎች ሚኒስትር ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል።

40.<u>ደንቡ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ ደንብ አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታኅሣሥ 22 ቀን 1995 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 1186/2012

## የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ

የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ዓይነትእንደገና በመፈተሸ በትክክል የቅንጦትዕቃዎች ናቸውበሚባሉ፣የኅብረተሰቡን ጤና በሚጎዱ እና የማኅበራዊችግር በሚያስከትሉ እንዲሁም መሠረታዊ በመሆናቸውምክንያት የገበያ ተፈላጊነታቸው በማይቀንስ ዕቃዎችእናአገልግሎቶች ላይ እንዲጣል ማድረግ በማስፈለጉ፤

በማምረቻ ወጪ ላይ ሲሰላየነበረው የኤክሳይዝታክስ በፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ እንዲተካመደረጉታክስከፋዮችሊከፍሉት በሚገባ ታክስ ተገማችነት ረገድሲያጋጥማቸውየነበረውን ችግር የሚያቃልል መሆኑስለታመነበት፤

በሥራ ላይ የነበረው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅባሉበት ጉድለቶች ምክንያት የኤክሳይዝ ታክስንበትክክል በመሰብሰብ ረገድ ያጋጠመውን ችግርመቅረፍ የሚያስችል አዋጅማውጣት ተገቢ ሆኖበመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሚክራሲያዊ ሪፐብሊክሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ እና /11/ መሠረትየሚከተለው ታውጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. "አውሮፕላን" ማለት ሰዎችን ወይም ዕቃዎችንበአየር የሚያጓጉዝ ማናቸውም ዓይነት ማጓጓዣነው፡፡
2. "ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግግብይት" ማለት በሁለት ሰዎች መካከል በትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሚደረግ ግብይት ነው፡፡
3. "ለሰው አገልግሎት የማይውል" ማለትበመጠጥነት ለሰዎች አገልግሎት እንዳይውል ተደርጎ የተሠራ ነው፡፡
4. "የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ" ማለት አልኮልለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ፋብሪካ ነው፡፡
5. "የጉምሩክ ቀረጥ" ማለት በገቢ ዕቃዎች ላይየተጣለ የጉምሩክ ቀረጥ፣ ሱር ታክስ ወይም ሌላተመሳሳይ ቀረጥ ነው፡፡

6. “የተፈቀደለት የዕቃ መጋዘን” ማለት የታክስባለሥልጣን በሚፈቅደው መሥረት የሚጠበቅናየኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃየሚቀመጥበት ቤት ወይም ሥፍራ ነው፡፡
7. “የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት/የተጣለበት ዕቃ" ማለት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 ክፍል 1 የተዘረዘሩ ዕቃዎች ናቸው፡፡
8. “የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልበት/የተጣለበትአገልግሎት” ማለት ከዚህ አዋጅ ጋርበተያያዘው ሠንጠረዥ 1 ክፍል 2 የተዘረዘሩትአገልግሎቶች ናቸው፡፡
9. “ኤክሳይዝ ታክስ ወይም ታክስ” ማለት በዚህአዋጅ የተጣለው ታክስ ነው፡፡
10. “ከታክሱ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች” ማለት ከዚህ አዋጅጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 2 የተመለከቱዕቃዎች ናቸው፡፡
11. “ወደ ውጭ አገር መላክ" ማለት አንድን ዕቃከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ወይም የኤክስፖርት ምርቶች ወደሚመረቱበት ዞንመላክ ነው፡፡
12. “የኤክስፖርት ምርቶች የሚመረቱበት ዞን" ማለትለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች የሚመረቱበትበኢንቬስትመንት ቦርድ የሚሰየም ዞን ነው፡፡
13. “ፋብሪካ" ማለት ፈቃድ የተሰጠው አምራችየኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሚያመርትበት ወይም የሚያከማችበት ሥፍራሲሆን፣ ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎችለተጠቃሚው ኅብረተሰብ ለገበያ የሚቀርቡበትን፣ማናቸውንም የአምራቹን የሥራ ቦታአይጨምርም፡፡
14. “ወደአገር ውስጥ ማስገባት” ማለት ዕቃዎችንከውጭ አገር እና የኤክስፖርት ምርቶች ከሚመረቱበት ዞን ወደ ኢትዮጵያ ማስገባትወይም እንዲገቡ ማድረግ ነው፡፡
15. “አስመጪ” ማለት ማናቸውም ወደአገር ውስጥየሚገቡ ዕቃዎች ባለቤት የሆነ ሰው ወይምዕቃዎቹ በይዞታው ሥር የሚገኝ ሰው ወይምበዕቃዎቹ ላይ ጥቅም ያለው ሰው ነው፡፡
16. “የኤክሳይዝ ቴምብር” ማለት የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልበት ዕቃ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚለጠፍምልክት ነው፡፡
17. “ አለም አቀፍ ትራፊክ” ማለት አውሮፕላንንበሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ቦታወደሌላ ቦታ የሚደረገውን በረራ ሳይጨምርአውሮፕላኑን ለአየር በረራ ጥቅም ላይ ማዋልነው፡፡

18.“ፈቃድ” ማለት የኤክሳይዝ ታክስየተጣለባቸውን አገልግሎቶች በሚመለከትየምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲሆን፣ የኤክሳይዝታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች በሚመለከት እነዚህን ዕቃዎች ለማምረት በዚህ አዋጅአንቀጽ 17 መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

19.“ፈቃድ የተሰጠው የአልኮል አምራች" ማለትበዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት ፈቃድየተሰጠው አልኮል የሚያመርት ሰው ነው፡፡

20.“የተፈቀደለት አምራች” ማለት የኤክሳይዝታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት ፈቃድየተሰጠው ሰው ነው፡፡

21.“ማምረት” ማለት:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎችማምረት፤

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎችበማምረት ሂደት ማናቸውንም ግብአት ወይም በከፊል የተጠናቀቀ ምርትማምረት፤ ወይም

ሐ) አልኮልን ማጣራት፣ ማሻሻል፣ ለሚፈለገውአገልግሎት ማዘጋጀት፣ ለሰው አገልግሎትእንዳይውል ማድረግን ይጨምራል፡፡

22.“ማሻሻል” ማለት የአልኮል መጠጦችንከሚያመርት ፋብሪካ የአልኮል መጠጥን በመረከብ እንደገና ማጣራት ወይም ልዩጣዕም እንዲታከልበት ማድረግ ነው፡፡

23.“የአልኮል መጠጥ” ማለት ማንኛውምየአልኮል ይዘቱ ከዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ (ከዜሮ ነጥብ 5 በመቶ) በላይ የሆነ የመጠጥዓይነት ነው፡፡

24.“የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ” ማለትከኢትዮጵያ ባህላዊ ዕቃዎች ውጭ አልኮልን ለማምረት የሚያገለግል መሣሪያ ሲሆን፣የዚህን መሣሪያ አካላት ይጨምራል፡፡

25.“ለአውሮፕላን መንገደኞች የሚውል ዕቃ“ማለት በአውሮፕላን የሚጓጓዙ መንገደኞች እንዲጠቀሙበት ወይም ለፍጆታእንዲያውሉት በዓለም አቀፍ ትራፊክ ላይ የሚገኝ አውሮፕላን ውስጥ የተጫነ ዕቃሲሆን፣ በአውሮፕላን ውስጥ ለመንገደኞች የሚሸጥን ዕቃ ይጨምራል፡፡

26.“ወደአገር ውስጥ ገቡ የሚባልበት ጊዜ" የሚለው ሀገር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

27.“የተጨማሪ እሴት ታክስ” ማለት በተጨማሪእሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 የተጣለው ታክስ ነው፡፡

28.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግየሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

29.“የታክስ ባለሥልጣን” ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር እንዲሁም የየክልሉ እና የከተማ አስተዳደሮች የገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው፡፡

30.“ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደምተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የገንዘብሚኒስትር ነው፡፡

31.“አዋጅ” ማለት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ነው፡፡

32.“የታክስአስተዳደር አዋጅ“ ማለት የታክስአስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

33.“በታክስ አስተዳደር አዋጁ ለቃላትና ሐረጐችየተሰጠው ትርጉም በዚህ አዋጅ የተለየትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር ለዚህ አዋጅምተፈፃሚ ይሆናል፡፡

34.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንምፆታ ይጨምራል፡፡

3. <u>ትክክለኛ የገበያ ዋጋ</u>

1. በአንድየተወሰነ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስየተጣለባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶችትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው የሚባለው በዚያን ጊዜግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተካሄደየጅምላ ግብይት ዕቃው ወይም አገልግሎቱሊያስገኝ ይችላል ተብሎ የሚጠበቀው ዋጋ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረትበአንድ የተወሰነ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስየተጣለባቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶችትክክለኛ የገበያ ዋጋ ማወቅ ያልተቻለ እንደሆነበፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት የዕቃው ወይም የአገልግሎቱትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይወሰናል፡፡

4. <u>አገልግሎት ቀርቧል ዕቃዎች ወይም ዕቃዎች ወደአገር ውስጥ ገብተዋል የሚባልበት ጊዜ</u>

1. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎችወደአገር ውስጥ ገቡ የሚባልበት ጊዜ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሊሆን ይችላል:-

ሀ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ከጉምሩክ ወደቦች ሲወጡ፣ ወደአገር ውስጥ የደረቅ ወደቦች የሚጓጓዙ እና የጉምሩክ ፎርማሊቲን በደረቅ ወደብ የሚያጠናቅቁ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ በሚከናወንበት ጊዜ፤

ለ) ወደአገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ወደተፈቀደለትየጉምሩክ መጋዘን የሚጓጓዙ የኤክሳይዝታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ለአገር ውስጥፍጆታ እንዲውሉ በተፈቀደለት የጉምሩክመጋዘን የጉምሩክ ፎርማሊቲን ሲያጠናቅቁ፤

ሐ)የኤክስፖርት ምርቶች ከሚመረቱበት ዞንየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውዕቃዎችለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ በሚወጡበት ጊዜ፣

መ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደኢትዮጵያሲገቡ፣

2. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለበት የአገልግሎትአቅርቦት ተከናወነ የሚባለውከሚከተሉትበቀደመው ጊዜ ነው:-

ሀ) አገልግሎቱ በተሰጠበት ቀን፤

ለ) ለአገልግሎቱ የክፍያ መጠየቂያ ኢንቮይስ በተዘጋጀበት ቀን፣

ሐ) የአገልግሎቱ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል በተከፈለበት ቀን፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ

5. **የኤክሳይዝ ታክስ ስለመጣል**

1. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኤክሳይዝታክስ ተብሎ የሚታወቅ ታክስ በሚከተሉትላይ ተጥሏል:-

   ሀ) በተፈቀደለት አምራች በኢትዮጵያ ውስጥየሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስየተጣለባቸውዕቃዎች፤

   ለ) ወደኢትዮጵያ የሚገቡ የኤክሳይዝየተጣለባቸው ዕቃዎች፤

   ሐ) በተፈቀደለት አገልግሎት ሰጪ በኢትዮጵያውስጥ የሚሰጡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 በተደነገገው መሠረትከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 የተዘረዘሩት ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውዕቃዎች በሠንጠረ በተመለከተው የማስከፈያልክ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

6. **የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ አዋጅ የተጣለውንየኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ አለባቸው:-

1. በኢትዮጵያ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይየተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ የተፈቀደለት አምራች፤
2. ወደኢትዮጵያ በሚገቡ ዕቃዎች ላይየተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ አስመጪው፤

3. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይየተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ አገልግሎቱንለመስጠት የተመዘገበው ሰው፡፡

7. <u>የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ</u>

1. የተፈቀደለት አምራች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያመርታቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የተመረቱት ዕቃዎች ከአምራቹ ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም በተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ዕቃዎች ጥቅም በዋሉበት ጊዜ ከፋብሪካው እንደወጡ ይቆጠራል፡፡
3. የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው አገልግሎቶች ላይ የተፈቀደለት ሰው የሚኖርበት የኤክሳይዝታክስ የመክፈል ግዴታ አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ይቋቋማል፡፡
4. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደአገር ውስጥ የሚያስገባ አስመጪ በሚከተለው ጊዜ የኤክሳይዝ ታክሱን የመክፈል ግዴታ አለበት:-

   ሀ) ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ በልዩ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር የነዳጅ ምርቶችወደአገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ፣

   ለ) በሌላ በማናቸውም ወደአገር ውስጥ በሚገባ ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ፣ ዕቃው ወደአገር ውስጥ ሲገባ፡፡
5. የተፈቀደለት አምራች በዚህ አንቀጽ መሠረትሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ በዚህአዋጅ አንቀጽ 37 በተዘረዘረው አኳኋንመክፈል አለበት፣
6. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎችወደአገር ውስጥ የሚያስገባ አስመጪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት ሊከፍል የሚገባውንየኤክሳይዝ ታክስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 በተዘረዘረው አኳኋን መክፈል አለበት፡፡

8. <u>ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች</u>

1. በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገውእንደተጠበቀ ሆኖ፣የሚከተሉትከኤክሳይዝታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

   ሀ) ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 2 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ዕቃዎች፤

   ለ) የተፈቀደለት የዕቃ መጋዘንን ጨምሮ በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ሥር ሆነው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎች፤

   ሐ) ከኢትዮጵያ ውጭ የተሰጡ አገልግሎቶች፤

መ) ከታክሱ ባለሥልጣን አስቀድሞ በተሰጠየጽሑፍ ፈቃድ መሠረት የታክሱ ባለሥልጣንሠራተኞች በተገኙበት ከተመረቱበት ፋብሪካከመውጣታቸው በፊትበአምራቹ ከጥቅምውጭ እንዲሆኑ የተደረጉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፤

ሠ) ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የመሆን መብትላላቸው አካላት የሚሸጡ ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች፤

ረ) ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊና ለአስተዳደራዊምክንያቶች በሚኒስትሩ ከኤክሳይዝ ታክስነፃ የተደረጉ ዕቃዎች፤

ሰ) ለሕክምና አገልግሎት እንዲውል ለሰውበመጠጥነት አገልግሎት ሊሰጥ በማይችልበትአኳኋን የተመረተ አልኮል፤

ሸ) በሚከተለው ሁኔታ በአደጋ ወይም በሌላከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የጠፉ ወይምየተበላሹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውዕቃዎች:-

1. ዕቃዎች የመጫን ወይም የማውረድተግባርን ጨምሮ ዕቃዎቹ ከአምራቹ ፋብሪካ በመውጣት ላይ ባሉበት ጊዜ፣
2. ከፋብሪካው ከመውጣታቸውበፊትዕቃዎቹ በተመረቱበትበአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ ባሉበት ጊዜ፤
3. ዕቃዎቹ ኢትዮጵያ ከመድረሳቸው በፊት በአውሮፕላን ወይም በመርከብ በመጓጓዝ ላይ ባሉበት ጊዜ፡፡

2. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶችከኢትዮጵያ ውጭ የተሰጡ ናቸው የሚባለውአገልግሉቶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝየንግድ ሥራ ቦታ የተሰጡ ሆነው ጥቅም ላይየሚውሉት ግን ከኢትዮጵያ ወጪ ሲሆኑ ነው፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈፃሚየሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን አገልግሎቶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑንሲያምንበት ነው፡፡
4. የተፈቀደለት አምራች በአደጋ ወይም በሌላከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለጠፉ ወይምለተበላሹ ዕቃዎች ካሣ ያገኘ እንደሆነ እናካሣው የኤክሳይዝ ታክሱን የሚጨምር ከሆነየዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (መ) ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

9. <u>የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት</u>

1. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነውከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 የተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መሠረትየዕቃዎቹ ወይም የአገልግሎቶቹ የኤክሳይዝታክስ ማስከፈያ ዋጋ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡
2. ወደኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች የኤክሳይዝታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚከተሉት ድምር ይሆናል:-

   ሀ) በዕቃው ላይ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈልቢሆንም ባይሆንም በጉምሩክ አዋጅ መሠረትየሚሠላው የዕቃው ዋጋ፤

   ለ) በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውየጉምሩክ ቀረጥ፡፡
3. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስየተጣለባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስማስከፈያ ዋጋ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ሲሆን፣የሚከተሉትን አይጨምርም:-

   ሀ) በዕቃ አቅርቦት ላይ የተጣለውን የተጨማሪእሴት ታክስ፤

ለ) የኤክሳይዝ ቴምብር (ካለ) ወጪ፤ እና

ሐ)የተመላሽ ዕቃ መያዣዎችን ወጪ፣

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገውእንደተጠበቀ ሆኖ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ዋጋ የሚከተለው ይሆናል:-

   ሀ) የተመዘገበው ሰው የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተደረገግብይት ከሆነ ተከፋይ የሆነው የአገልግሎቱዋጋ፣ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ፤

   ለ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የአገልግሎቱትክክለኛ የገበያ ዋጋ፡፡
5. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶችዋጋ በአገልግሎቱ ላይ የሚከፈለውን የተጨማሪእሴት ታክስ አይጨምርም፣

10. **ማስተካከያ ስለማድረግ**

1. ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ከዚህ አዋጅጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 በተመለከተውየማስከፈያ ምጣኔ ላይ ከ10 በመቶ ያልበለጠምጣኔ ሊጨምር ወይምሊቀንስ ይችላል፡፡
2. የታክስ ባለሥልጣኑ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 በቁርጥ በተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ምጣኔ ላይ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የዋጋ ንረት ማስተካከያ ማድረግ አለበት፡፡

11. **የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ**

1. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎችየፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ነው የሚባለው:-
ሀ) አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውንዕቃዎች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎችመካከል በሚደረግ ግብይት ለገዥው የሆነእንደሆነ፣ ገዥው የከፈለው ዋጋ፤
ለ) በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ዕቃው ከአምራቹፋብሪካ በወጣበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፡፡
2. በፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ላይ የተከፈለውየኤክሳይዝ ታክስ በግብይቱ ደረሰኝ ላይ ተለይቶ መታየት አለበት፡፡

12. <u>የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች መጠን</u>

1. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው ከአዋጁ ጋርበተያያዘው ሠንጠረዥ 1 መሠረት በዕቃዎቹላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለው የዕቃዎቹንብዛት ወይም ክብደት መሠረት ባደረገ መጠን በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡
2. በሚከተሉት ሁኔታዎች የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን የሚወሰነው ከዕቃው ጋርየሚሸጠውን የዕቃውን ማሸጊያ እና በውስጡየያዘውን ክብደት መሠረት በማድረግይሆናል:-
ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎችወደኢትዮጵያ በሚገቡበት ወይም በተፈቀደለት አምራች ከተመረቱበትፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ ከዕቃው ጋር አብሮ ከሚሸጥ ማሸጊያ ጋር ወይም የዚህዓይነት ዕቃዎች በችርቻሮ በሚሸጡበት አብዛኛውን ጊዜ አብረው ከሚሸጡማሸጊያዎች ጋር ሲሆን፣ እና
ለ) ማሸጊያው:-
(1) የተጣራ ክብደቱ ያልተፃፈበት ከሆነ፤
ወይም
(2) በሚሸጥበት ጊዜ በውስጡ ያለው ይዘትበተለምዶ የሚታወቅ ባለመሆኑ ወይምአብዛኛውን ጊዜ ይዘቱ የሚታወቅባለመሆኑ ትክክለኛ ብዛቱን ወይምክብደቱን ማወቅ የማይቻል ከሆነ፡፡,
ሐ) የዕቃው ባለቤት የማሸጊያውን የተጣራክብደት ትክክለኛነት የታክስ ባለሥልጣኑንበሚያረካ አኳኋን ማስረዳት ካልቻለ፣የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎችላይየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለውበማሸጊያው እና በውስጡ በያዘው ዕቃጠቅላላ ክብደት ላይ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገውእንደተጠበቀ ሆኖ፣በሚከተሉት ሁኔታዎችበማሸጊያው ላይ ከተገለፀው መጠን ያላነሰ ዕቃበውስጡ እንዳለው ይቆጠራል:-
   ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደኢትዮጵያ በሚገቡበት ወይም በተፈቀደለት አምራች ከተመረቱበት ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ ከዕቃው ጋር አብሮ ከሚሸጥ ማሸጊያ ጋር ወይም የዚህ ዓይነት ዕቃዎች በችርቻሮ በሚሸጡበት አብዛኛውን ጊዜ አብረው ከሚሸጡ ማሸጊያዎች ጋር ሲሆን፣ እና
   ለ) ማሸጊያው:-
   1. የሚይዘው የተወሰነ ብዛት ያለው ዕቃበማሸጊያው ላይ የተፃፈበት ከሆነ፤ ወይም
   2. በሚሸጥበት ጊዜ በውስጡ ያለው ይዘትበተለምዶ የሚታወቅ ከሆነ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ማሸጊያ የያዘው መጠን ከተወሰነው መጠን በላይ የሆነ እንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በትክክለኛው መጠን ላይ ይሆናል፡፡
5. የታክሱ ባለሥልጣን በማምረት ሂደት ለሚያጋጥም ቁርጥራጭ እና ውዳቂ የሚፈቀደውን መጠን እና የሚፈቀድበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 13. <u>የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች የተሰጡበት ቦታ</u>

የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶችየተሰጡት አገልግሎት ሰጪው ኢትዮጵያ ውስጥባለው የንግድ ሥራ ቦታ ከሆነ አገልግሎቱኢትዮጵያ ውስጥ እንደተሰጠይቆጠራል፡፡

## 14. <u>በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለን ታክስ ስለማቀናነስ</u>

1. የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስበሚከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ በገቡ ወይምበአገር ውስጥ በተመረቱ ጥሬዕቃዎች/ግብዓቶች ላይ የኤክሳይዝ ታክስየከፈለ እንደሆነ እና እነዚህን ጥሬዕቃዎች/ግብዓቶች የመጨረሻውን ምርት (ከዚህበኋላ "መጨረሻ ምርትገ ለማምረትበግብዓትነት የተጠቀመባቸው ከሆነ፣ በጥሬዕቃዎቹ/ግብዓቶቹ ላይ የተከፈለውታክስበመጨረሻ ምርቶቹ ላይ ከሚከፈለውየኤክሳይዝ ታክስ ጋር እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (1) የተደነገገውአልኮልን፣ትንባሆን እና ስኳርንአይጨምርም፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## ስለፈቃድ

## ክፍል አንድ

## ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

### 15. ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው ሥራዎች

1. ማንኛውም ሰው ከታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድካላገኘ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድካልተመዘገበ በስተቀር በሚከተሉት ሥራዎችላይ መሠማራት አይችልም:-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝታክስየሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 በተደነገገውመሠረት፣ ሚኒስትሩ በሚያወጣውመመሪያየኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው ይገባልየተባሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውንዕቃዎች ማቅረብ፤

ሐ) የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸውንአገልግሎቶች ማቅረብ፤

መ) ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ፈቃድየማግኘት ግዴታ በሚጥልባቸው ሌሎችሥራ ዘርፎች መሠማራት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውንበመተላለፍ የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸውንዕቃዎች በማምረት ወይም አገልግሎቶችንበመስጠት ሥራ ላይየተሠማራ ሰው ከዚህአዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 የተጣለውን የኤክሳይዝታክስ እንዲከፍልይገደዳል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የኤክሳይዝታክስ እንዲከፍል የሚገደድ ሰው:-

   ሀ) በታክስ ባለሥልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ ታክሱንወዲያውኑ መክፈል አለበት፣

   ለ) ከኤክሳይዝ ታክሱ በተጨማሪ በዚህ አዋጅእንዲሁም በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሠረት በወንጀል ተጠያቂይሆናል እንዲሁም ቅጣትና ወለድ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

### 16. ለፈቃድ ማመልከቻ ስለማቅረብ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 (1) በተዘረዘሩትየሥራ መስኮች ለመሠማራት የሚፈልግ ሰውበአንቀጽ 15(1) ከተዘረዘሩት ለሚሠማራበት የሥራ መስክ ፈቃድእንዲሰጠው ለታክስ ባለሥልጣኑ ማመልከቻማቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረትየሚቀርብ ማመልከቻ:-

   ሀ) በተፈቀደው ቅጽ መሠረት ሊቀርብ፣

   ለ) የፈቃድ ክፍያ ሊከፈልበት፤

ሐ) በባለሥልጣኑ በተወሰነው አኳኋን ሊቀርብ፤ይገባል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ፈቃድ ስለመስጠት

### 17. ፈቃድ መስጠት

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገውእንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህአዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት የሚቀርብለትንማመልከቻ በመመርመር ለአመልካቹ ፈቃዱንሊሰጥ ወይም ሊከለከል ይችላል፡፡

2. የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሊከለክል የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ይሆናል:-

ሀ) አመልካቹ በዚህ አዋጅ ወይም በታክስአስተዳደር አዋጅ መሠረት በታክስ መሰወርወይም በታክስ ማጭበርበር ወንጀል ተከሶየተፈረደበት ከሆነ፤

ለ) አመልካቹ በማናቸውም ሕግ እምነትበማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀልተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፣

ሐ) አመልካቹ:-

1. የከሰረ ወይም ዕዳውን ለመክፈልያልቻለ ከሆነ፣

2. በኪሣራ ምክንያት ሀብቱ በመጣራት ላይ ያለ ወይም ባለአደራ የተሰየመበት ከሆነ፣

መ) ማመልከቻው የቀረበው የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት ከሆነበማመልከቻው የተመለከተው ፋብሪካ፣ማምረቻ፣ መጋሪያ ምርቱን ለማምረትወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውንዕቃዎች ለመከታተል በቂ ካልሆነ፣

ሠ) አመልካቹ በማናቸውም የታክስ ሕግበተደነገገው መሠረት ትክክለኛውንየሂሳብ መዝገብ ያልያዘ፣ ወይምበማናቸውም የታክስ ሕግ የተጣለበትንግዴታ ያልተወጣወይም በታክስባለሥልጣኑ በተጠየቀው መሠረትበተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሂሳብ መዝገብየመያዝ ግዴታውን ለመወጣት ግዴታለመግባት ያልተስማማ፤

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) (ለ) (ሐ) እና (ሠ) የተመለከተው ከአመልካቹ ጋርግንኙነት ያለውን ሰው የሚመለከት ሲሆን፣ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የታክስባለሥልጣኑ ከአመልካቹ ጋር ግንኙነት ያለውሰው ፈቃድ በተጠየቀበት የሥራ መስክ ውስጥየሚሠማራ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ያለው በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

3. በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰጠው ፈቃድ ጋርበተያያዘ የታክሱ ባለሥልጣን አስፈላጊ መስሎከታየው የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ወይምገደቦች እንዲኖሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት የፈቃድ ማመልከቻ ለሚያቀርብ ሰው የታክስ ባለሥልጣኑ በማመልከቻው መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀንጀምሮ በሚቆጠር የ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ መግለጽ አለበት፡ ማመልከቻው ውድቅየተደረገ ከሆነ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት መገለጽ አለበት፡፡
5. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድበታክስ ባለሥልጣኑ በተሰጠው ፈቃድ ላይከተመለከተው ቀን ጀምሮ የሚፀና ሲሆን፣ በዚህአዋጅ አንቀጽ 21 መሠረት ካልተሠረዘበስተቀር ላልተወሰነ ጊዜ የፀና ይሆናል፡፡

## 18. <u>የፈቃዱ ቅርጽ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት የሚሰጠውፈቃድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የሚሰጥይሆናል፡፡
2. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችለሚያመርት ሰው የሚሰጥ ፈቃድ የሚከተሉትንመያዝ አለበት:-
   ሀ) አምራቹ እንዲያመርት የተፈቀደለትንየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ምድብወይም ምድቦች፣
   ለ) አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውንምርቶች እንዲያመርት የተፈቀደለትንፋብሪካ/ፋብሪካዎች፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት በተሰጠ ፈቃድየተመለከተው ፋብሪካ ማምረት የሚችለው በፈቃዱ የተመለከተውን የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልበትን ዕቃ ምድብ/ምድቦች ብቻነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት በተሰጠ ፈቃድበተመለከተው ፋብሪካ የኤክሳይዝ ታክስየተጣለባቸውን ዕቃዎች ማምረት የሚችለውበፈቃዱ ላይ አምራች በሚል የተመለከተውሰው ብቻ ነው፡፡
5. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን አገልግሎቶችበማቅረብ ሥራ ላይ ለተሠማራ ሰው የሚሰጠውፈቃድ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚሜገልፅ መሆንአለበት፡፡

## 19. <u>ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታዎች</u>

1. ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉትን የመፈፀምግዴታ አለበት:-

   ሀ) የተሰጠውን ፈቃድ ዋና ቅጂ የንግድሥራውን በሚያካሂድበት ዋና መሥሪያበግልጽ በሚታይ ቦታ መለጠፍ፤

   ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውንአገልግሎቶች በሚመለከት የፈቃዱንየተረጋገጠ ኮፒ የንግድ ሥራውንበሚያካሂድበት ቦታ ሁሉ የመለጠፍ፡፡

2. ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉትን መረጃዎችበሚመለከት ለታክስ ባለሥልጣኑ በጽሁፍማስታወቂያ የመላክ ግዴታ አለበት:-

   ሀ) ፈቃድ የተሰጠበትን ሥራ ያቆመ እንደሆነ፤

   ለ) የተፈቀደለት አምራች የሚያከናውነውን ዋናተግባር መጠሪያ፣ አድራሻ፣ ሥራውንየሚያከናውንበትን ቦታ፣ ባለቤትነት፣የመተዳደሪያ ደንብ ወይም የሥራውን ባህሪየለወጠ እንደሆነ፤

   ሐ) የተፈቀደለት አምራች የሥራውንእንቅስቃሴ ለተወሰነ ጊዜ በጊዚያዊነት ያቋረጠ እንደሆነ፣ ወይም

   መ) የተፈቀደለትን አምራች በሚመለከትየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችለማምረት በሚጠቀምበት በፈቃዱበተመለከተው ፋብሪካ ወይም ማምረቻ እናመሣሪያ ላይ ለውጥ የተደረገ እንደሆነ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)መሠረትየሚላከው ማስታወቂያ ለታክሱ ባለሥልጣንበሚከተለው ጊዜ ውስጥ እንዲደርስ መደረግአለበት:-

   ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሐ) መሠረትየሚቀርበውን ማስታወቂያ በሚመለከት የንግድሥራው የተዘጋው ባልታቀደ ሁኔታ ከሆነ፣የንግድ ሥራውን ለመዝጋት ምክንያት የሆነውሁኔታ ካጋጠመበት ቀን ጀምሮ በ7 ቀናትውስጥ፤

   ለ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ማስታወቂያውንለመላክ ምክንያት የሆነው ሁኔታ ባጋጠመ በ7 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑእንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## ፈቃድን ስለማገድና ስለመሠረዝ

### 20. ፈቃድን ስለማገድ

1. የታክሱባለሥልጣን ከሚከተሉት ምክንያቶችበአንዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ፈቃድማገድ ይችላል:-
   ሀ) ፈቃድ ከተሰጠው ሰው የንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 (2) (ሀ)፣(ለ) ወይም (ሐ) የተዘረዘሩ ሁኔታዎችያጋጠሙ እንደሆነ፤
   ለ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ አዋጅ ወይምበታክስ አስተዳደር አዋጅ በተመለከተውመሠረት ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘወይም ማናቸውንም በዚህ አዋጅየተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ፤
   ሐ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃዱ የተመለከቱሁኔታዎችን የጣሰ እንደሆነ፤
   መ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለታክስ ባለሥልጣኑየሀሰት ወይም አሳሳች መረጃን የሰጠእንደሆነ፣
   ሠ) የተፈቀደለትን አምራች በሚመለከት፣ በፈቃዱየተመለከተው ፋብሪካ፣ ማምረቻ ወይምመጫሪያ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውንምርቶች ለማምረት ከዚያን ጊዜ በኋላ አጥጋቢሆነው ያልተገኙ እንደሆነ፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የታክስባለሥልጣኑ ፈቃድን ያገደ እንደሆነ ፈቃድለተሰጠው ሰው ፈቃዱ የታገደ መሆኑን የሚገልጽማስታወቂያ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡
3. ፈቃድን ለማገድ የተሰጠ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነውበዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ [2] መሠረትማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ፈቃዱየታገደ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ የደረሰውሰው የዕግዱ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ14 ቀናት ውስጥ ወይም የታክስ ባለሥልጣኑበሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ዕግዱን በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑየታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል በጽሁፍሊያቀርብ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረትፈቃድ የተሰጠው ሰው ዕግዱን በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ፣ የታክሱባለሥልጣን የይግባኝ ማመልከቻው በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ:-
   ሀ) የይግባኙን አቤቱታ በመቀበል የፈቃዱንዕገዳ ሊያነሳ፣
   ለ) ፈቃዱ የታገደበት ሰው ዕግዱ እንዲነሳለትለማድረግ ለዕግዱ ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን በማሟላት ረገድ በማስታወቂያውበተወሰነ ጊዜ ውስጥ

ሊያከናውናቸው የሚገባተግባራትን የሚገልጽ ማስታወቂያእንዲደርሰው በማድረግ፣ በማስታወቂያው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተግባራቱን ካከናወነዕግዱን የማንሳት፤

(ሐ) ይግባኙን ውድቅ ማድረግና በዚህ አዋጅአንቀጽ 21 መሰረት ፈቃዱን መሰረዝ ይችላል፡፡

6. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (5) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በንዑስአንቀጹ የተመለከቱትን እርምጃዎች ካልወሰደየፈቃዱ ዕገዳ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

21. ፈቃድን ስለመሠረዝ

1. የታክሱ ባለሥልጣን በሚከተሉትበጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠትሊሠርዝ ይችላል:

ሀ) የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 (2) (ሀ) መሠረት ማስታወቂያ የደረሰው ከሆነ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20(4) በተወሰነው ጊዜውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የፈቃዱን ዕገዳበመቃወም ይግባኝ ያላቀረበ ከሆነ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 (5) (ለ) በተሰጠውማስታወቂያ ወይም በታክሱ ባለሥልጣንበተሰጠ ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ፈቃድየተሰጠው ሰው በማስታወቂያው የተመለከተውንሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 (5) (ሐ) በተደነገገው መሠረት ፈቃዱበመታገዱምክንያት የቀረበውን የታክስይግባኝባለሥልጣኑ ውድቅ ያደረገው ከሆነ፡፡

2. የፈቃድ መሠረዝተፈፃሚ የሚሆነው ፈቃዱመሠረዙን በሚገልጸው ማስታወቂያ ከተመለከተውቀን ጀምሮ ነው፡፡

3. ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የተሰጠው ፈቃድመሠረዝ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈልን እና የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብንጨምሮ ፈቃዱ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ባከናወነውወይም ባላከናወነው ማናቸውም ተግባርምክንያት በዚህ አዋጅ ወይም በታክስአስተዳደር አዋጅ መሠረት የሚኖርበትንተጠያቂነት አያስቀርም፡፡

22. ፈቃድ መታገድ ወይም መሠረዝ የሚኖረው ውጤት

1. የተፈቀደለት አምራች የተሰጠው ፈቃድ የታገደወይም የተሠረዘ እንደሆነ፣

ሀ) አምራቹ:-

1. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎችየማምረቱን ተግባር ወዲያውኑ ማቆም፣
2. የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው በእጁበሚገኙ እቃዎች ላይ ያልተከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ወዲያውኑ መክፈል፣
3. ከታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያመሠረት በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችማስወገድ፣

አለበት፡፡

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን:-

1. የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥየሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውንዕቃዎች በታክሱ ባለሥልጣን ወደፀደቀ ቦታእንዲያዘዋውር የማዘዝ፣ እና
2. በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎችመፈፀማቸውን ለማረጋገጥ እና የመንግሥትን ገቢ ለመሰብሰብ አስፈላጊእስከሆነ ድረስ የታክሱ ባለሥልጣን በታክስአስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 41 መሠረትየአምራቹን ፋብሪካ እና በፋብሪካው ውስጥየሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች መያዝ፣ ይችላል፡፡

2. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች ለማቅረብ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሠረዘ እንደሆነ ባለፈቃዱ:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን አገልግሎት ማቅረቡን ማቆም፤ እና

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው አገልግሎቶችላይ ያልተከፈለውን ታክስ መክፈል፤

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈፃሚከሚሆንባቸው ውጭ ያለ አስመጪ ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሰረዘ እንደሆነ ፈቃድየተሰጠበትን የሥራ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት፡፡
4. የታክስ ባለሥልጣኑ በፈቃዱ መታገድ ወይምመሠረዝ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካፈቃድ ለተሰጠው ሰው የጽሁፍ ማስታወቂያሊሰጠው ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ለታክስአስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም እንደታክስይቆጠራል፡፡

## 23. ፈቃድ ከመታገዱ ወይም ከመሠረዙ በፊት የታክስ ባለሥልጣኑ ሊሰጥ ስለሚገባው ማስጠንቀቂያ

1. የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረትየተሰጠውን ፈቃድ ለማገድ ወይም ለመሠረዝያቀደ እንደሆነ፣ ባለፈቃዱ ሊወሰድ የታቀደውንእርምጃ እንዲያውቀው ከ21 ቀናት በፊት የጽሁፍማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡ ይህምማስጠንቀቂያ እርምጃው እንዲወሰድ መንስኤየሆኑትን ሁኔታዎች እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው ማስተካከያ ሊያደርግባቸው የሚገባ ጉዳዮችንጭምር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡
2. ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (1) መሠረት ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ በታክሱ ባለሥልጣንየተጠየቁ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድአለበት፡፡
3. የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰውየወሰዳቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች የሚመለከት ሪፖርት በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥየተወሰዱት እርምጃዎች በቂ መሆናቸውን ወይምበማስጠንቀቂያው የተገለፁ እርምጃዎች የሚወሰዱ መሆኑን ለመግለጽ ይችላል፡፡
4. በማስጠንቀቂያው የተገለፁ እርምጃዎችየሚወሰዱ መሆኑን እንዲያውቀው የተደረገ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በታክስ ባለሥልጣኑውሣኔ ቅር የተሰኘእንደሆነ፣ ውሣኔው ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥቅሬታውን ለታክስ ባለሥልጣኑ የአቤቱታ አጣሪየሥራ ክፍል ሊያቀርብ ይችላል፡፡
5. የአዜቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል አቤቱታውበደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ በቀረበው ቅሬታላይ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡
6. የተሰጠው ሰው በአቤቱታ አጣሪ የሥራክፍል በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነውሣኔው በተገለፀለት በ14 ቀናት ውስጥ ለግብርይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችልሲሆን፣ የይግባኙ ማመልከቻ በ7 ቀናት ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን እንዲደርስ ማድረግአለበት፡፡

## 24. ስለይግባኝ

1. የግብር ይግባኝ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 (6) መሠረት የቀረበለትን ይግባኝ በታክስአስተዳደር አዋጅ በተደነገገው ጊዜ ውስጥመርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
2. በግብር ይግባኝ ኮሚሽን የተሰጠው ውሳኔ የሕግስህተት አለበት ብሎ የሚያምን ፈቃድየተሰጠው ሰው ወይም የታክስ ባለሥልጣንውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ

ይግባኙንለፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሊያቀርብይችላል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር

### 25. የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

1. ፈቃድ በተሰጠው አምራች ፋብሪካ ውስጥየሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በታክስ ባለሥልጣኑ የኤክሳይዝ ታክስቁጥጥር (ከዚህ በኋላ "የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር" በሚል የሚጠራ) ይደረግባቸዋል፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስበሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስቁጥጥር የሚደረገው ከሚከተሉት በቀደመውጊዜ ይሆናል:-

   ሀ) ፈቃድ በተሰጠው አምራች ፋብሪካ ውስጥየሚገኙ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅምላይ እንዲውሉ ከፋብሪካው እስከሚወጡ፤

   ለ) ዕቃዎቹ ከኢትዮጵያ ውጭ እስከሚላኩ፤ ወይም

   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ወይምበዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 (1) (ሸ] መሠረትዕቃዎቹ ከአገልግሎት ውጭ እስከሚደረጉወይም አስከሚወገዱ ድረስ፡፡
3. ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር እስካሉድረስ:-

   ሀ) በታክስ ባለሥልጣኑ ሥልጣን የተሰጠው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ በማናቸውምጊዜ ዕቃዎቹን መመርመር ይችላል፡፡

   ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት በታክሱ ባለሥልጣንከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማናቸውም ሰው ዕቃዎቹን ከፋብሪካ ማውጣት ወይምበማናቸውም ሌላ መንገድ ዕቃዎቹን በሚመለከት ማናቸውንም ተግባር መፈፀምአይችልም፡፡
4. ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ባሉበትጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን የዕቃውባለቤትዕቃዎቹን ለታክሱ ባለሥልጣን እንዲያስረክብሊጠይቅ ይችላል፡፡ የታክሱ ባለሥልጣን ዕቃዎቹንከተረከበ በኋላ ዕቃዎቹ በታክሱ ባለሥልጣንበሚሰጥመመሪያ መሠረት በባለቤቱ ወጪ ሊሸጡወይም ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑሊደረግወይም ሊወገዱ ይችላል፡፡

### 26. በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሥር ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በሚመለከት ፈቃድ የተሰጠው አምራች ግዴታዎች

1. የኤክሳይዝታክስ ቁጥጥርየሚደረግባቸውዕቃዎችመሆኑንየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውበተገቢው የሂሳብ አያያዝ የተመዘገቡለማረጋገጥ፣ የተፈቀደለት አምራች:-
   ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም ጥሬ ዕቃዎችን ለመመዝገብ፣ ክብደታቸውን ለመለካት፣ ለመቆጣጠር፣ ለመቁጠር እንዲችል ወይም እንደአስፈላጊነቱሌሎች ተመሳሳይ የቁጥጥር ሥራዎችን እንዲያከናውን በፋብሪካው ውስጥ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያዎች እንዲኖሩ እና በሚገባ እንዲጠበቁ የማድረግ፤
   ለ) በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የተሟላ ቁጥጥርለማድረግ በሚያስችል መንገድ የማስቀመጥ፤
   ሐ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት የጥሬ ዕቃዎችንምዝገባ ማካሄድ፣ በተለይም በማምረት ሂደትጥቅም ላይ እንዲውሉ ፋብሪካው የተረከባቸውንጥሬ ዕቃዎች እና ግብአቶች በእነዚህ ቅፆችላይ መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻየምዝገባውን ሚዛንትክክለኛነት የማረጋገጥ፤
   መ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት የመጨረሻ ምርቶችን ምዝገባ ማከናወን፣ እና በዚሁ ቅጽ ላይ በፋብሪካው የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እናከፋብሪካው የወጡ ዕቃዎችን መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት የማረጋገጥ፤
   ሠ)የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ በዋሉ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የማረጋገጥ፤
   ረ) ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ እንዲሟሉ የሚጠየቁ ሁኔታዎችን የማሟላት፤ግዴታ አለበት፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) አፈፃፀምየታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው ተፈላጊ የሆኑ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያእንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መሣሪያዎችንተፈላጊ ባህሪያት ሊወስን ይችላል፡፡
3. የታክሱ ባለሥልጣን:-
   ሀ) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውበማናቸውም ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ናሙና ከአምራቹበነፃ የመውሰድ መብት ያለው

ሲሆን፣ እነዚህናሙናዎች የታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠውውሳኔ መሠረት ሊወገዱ ወይም ለአምራቹሊመለሱ ይችላሉ፡፡

ለ) በጽሁፍ በሚወስነው አኳኋን የኤክሳይዝታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ባለቤት የኤክሳይዝ ታክሱን ሳይከፍልለገበያበማይውል መጠን ከፋብሪካው ናሙናዎችን እንዲወስድ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

27. <u>ከአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጭ የአልኮል ማጣሪያ መሳሪያን መያዝ ወይም መጠቀም የተከለከለ ነው</u>

1. በዚህ ዘንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ከተሰጠው የአልኮልማጣሪያ ፋብሪካ ውጭ ማናቸውም ሰውየአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን መያዝ ወይምመጠቀም አይችልም፡፡
2. የታክሱ ባለሥልጣን የሚጥላቸው አስገዳጅ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጭ ሌላ ሰው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ እንዲይዝ ወይም እንዲጠቀምበት ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል:-

ሀ) የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ለሽያጭ የሚያመርት ወይም የሚይዝ ሲሆን፣

ለ) መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ለሙከራ፣ ለጥናት፤ወይም ለሳይንሳዊ ምርምር ዓላማ ሲሆን፣

ሐ)የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያው የተያዘው ወይምጥቅም ላይ የሚውለው ከአልኮል መጠጦችውጭ የሆነ ሌላ ምርት ለማምረት ሲሆን፡፡

28. <u>ከፋብሪካ ወጪ እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ዕቃዎች</u>

1. የተፈቀደለት አምራች የታክሱን ባለሥልጣንበሚያረካ አኳኋን በፋብሪካው የተመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ፣ በአንድ ወር ውስጥ ተመርቷል በተባለው እና ሊመረት ይችላል ተብሎ በሚታመነው መካከል ያለውን ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭከፋብሪካው ውጪ እንዳደረገ ይቆጠራል፡፡
2. የተፈቀደለት አምራች በትክክል ባመረተው እናየተመረተ ዕቃ በሚመዘገብበት ሰነድ ላይ በተመዘገበው መካከል ልዩነት መኖሩን ያወቀ እንደሆነ፣ ይህንኑ ወዲያውኑ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

<u>ምዕራፍ አምስት</u>

## የኤክሳይዝ ቴምብር

### 29. የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች

1. ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚከተሉትን ሊወስን ይችላል:-

ሀ) የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች፤

ለ) ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ በሆኑ የአልኮል ምርቶች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ምልክት፣

ሐ) የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶችየሚለጠፉባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች. የአስተዳደርሥርዓት፣

መ) የኤክሳይዝ ቴምብር ወይም ሌሎችምልክቶች የሚለጠፉበትን ቦታ እና ጊዜ፡፡

2. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች እንዲለጠፍባቸው በታዘዙ ዕቃዎች ላይ የሚለጠፈውን የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች ዓይነት እና ይዘት በሚመለከት አገራዊ ተነባቢነት ባላቸው ሁለት ጋዜጣዎች ቢያንስ ለሁለት ጊዜ ያህልማስታወቂያ ያወጣል፡፡

3. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የተመረቱት ለውጭ ገበያ እንዲላኩ ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 2 በተራ ቁጥር 2 እና 3 ለተዘረዘሩ ሰዎች የሆነእንደሆነ፣ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ ለሚደረገውክትትልና ቁጥጥር እንዲያመች ሚኒስትሩበሚወስነው አኳኋን በዕቃዎቹ ላይ ልዩ ምልክትሊደረግ ይገባል፡፡

4. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረትየኤክሳይዝ ቴምብር ከመለጠፉ በፊት ማናቸውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተዘረዘሩትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ቴምብርእንዲለጠፍባቸው ከተቀመጡበት ቦታማንቀሳቀስ አይችልም፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተውቢኖርም የታክሱ ባለሥልጣን በተለዩ ሁኔታዎችና ከሚኒስትሩ አስቀድሞ ፈቃድየተገኘ ሲሆን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውዕቃዎች የኤክሳይዝ ቴምብር ሳይለጠፍባቸውከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑሊያደርግ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለተመላሽ

### 30. ተመላሽ

1. በአገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጭ አገርየመጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለባቸው በኋላከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ያጋጠመ መሆኑንየታክሱ ባለሥልጣን ያረጋገጠ እንደሆነ፣በአምራቹ ወይም በአስመጪው በሚቀርብየፅሑፍ ማመልከቻ መሠረት የተከፈለውየኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል:-
   ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ከመዋላቸውበፊት:-
      1. ወደኢትዮጵያ በመጓጓዝ ላይ እያሉዕቃዎቹ ከጥቅም ውጭ የሆኑ ወይምየተሠረቁ እንደሆነ፤
      2. በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች ከጥቅም ውጭ የሆኑ ወይም የተሠረቁ እንደሆነ፤
      3. በሽያጭ ውሉ መሠረት ገዢው ዕቃውን ለሻጩ የመለሰ እንደሆነ፡፡
   ለ) የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለ በኋላ ፈቃድበተሰጠው ወይም በተመዘገበ አምራችከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችንለማምረት የዋሉ እንደሆነ፡፡
2. የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩትንሁኔታዎች የሚያሟሉ እንዲሁም የኤክሳይዝታክሱን የከፈለ እና ለእነዚህ ዕቃዎች ወይምአገልግሉቶች ከገገርው ምንም ዓይነት ክፍያያልተቀበለ መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ የቻለእንደሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ እንዲደረግለት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማመልከቻሊያቀርብ ይችላል፡፡ የታክሱ ባለሥልጣንምየተፈቀደለት ሰው በእነዚህ ዕቃዎች ወይምአገልግሎቶች ላይ ምንም ዓይነት የኤክሳይዝታክስ ያልተቀበለ መሆኑን ሲያረጋግጥየተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲሆንሊያደርግ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በቀደመው ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት:-
   ሀ) ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ከተሸጡበትቀን ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜውስጥ፣ ወይም
   ለ) ገዢው በሕግ የከሠረ መሆኑ በተረጋገጠበትጊዜ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስተመላሽ እንዲሆን የሚቀርበው ማመልከቻ:-
   ሀ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት፣ እና

ለ) በታክሱ ባለሥልጣንበሚወሰነው አኳኋንሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ የተመላሽ ጥያቄንበሚመለከት የኤክሳይዝ ታክሱ በተከፈለ በ12 ወራት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት ተመላሽ የሚደረገውየኤክሳይዝ ታክስ መጠን የሚወሰነው በታክስአስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሥረትይሆናል፡፡
6. ወደአገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ተመልሰውወደውጭ አገር በተላኩ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝታክስ የተከፈለ ከሆነ ወደውጭ አገር በተላኩትዕቃዎች ላይ የተከፈለው ታክስ በጉምሩክ አዋጅበተደነገገው መሠረት ተመላሽ ይደረጋል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረትየኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ከተደረገ በኋላ ፈቃድየተሰጠው ሰው ከገገገርው ላይ የኤክሳይዝ ታክሱንበሙሉ ወይም በከፊል የተቀበለ ከሆነ፣ የኤክሳይዝታክሱን በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ በተቀበለው መጠን ተመላሽ የተደረገለትን የኤክሳይዝ ታክስለታክሱ ባለሥልጣን መመለስአለበት፡፡

31. **<u>ተመላሽ የተከፈለባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የተሸጡ ወይም ተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ስለመሆኑ</u>**

1. በዚህአዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣የተመላሽ ክፍያ የተፈፀመባቸው ኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸው ዕቃዎች ተመላሹ ከተከፈለ በኋላየተሸጡ ወይም ተመላሹ ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ፣ ተመላሹ ባይፈቀድኖሮ ዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ይገባ በነበረው ልክየኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡
2. ለማናቸውም ዓላማ የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽክፍያ የተፈፀመበት ዕቃ በእጁ የገባ ሰው፣ ዕቃውንተመላሹ ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ለመጠቀምወይም ለመሸጥ፣ የፈለገ እንደሆነ፣ ዕቃውየሚሸጥበትን ወይም ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዝርዝር ሁኔታ በሚመለከት ለታክሱ ባለሥልጣንሪፖርት ማቅረብ እና በዕቃው ላይ ሊከፈልየሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት፡፡

32. **<u>ኤክሳይዝ ታክስ ነጻ የተደረጉ ዕቃዎች ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ የገቡ ወይም ለሽያጭ የዋሉ እንደሆነ ታክሱ የሚከፈል ስለመሆኑ</u>**

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኤከሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደውጭ አገር ከተላኩ ወይም በዓለም አቀፍ ትራፊክ ለመንገደኞች

አገልግሎቶች እንዲውሉበአውሮፕላን ላይ ከተጫኑ በኋላ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ከጭነት የተራገፉ እንደሆነ አስመጪው ዕቃዎቹ በተራገፉበት ጊዜ ፀንቶ ባለው የማስከፈያ ምጣኔመሠረት በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስመክፈል አለበት፡፡

2. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከታክሱነፃ ተደርገው ወደአገር ውስጥ ከተሸጡ በኋላ ተመልሰው ለሽያጭ ከዋሉ ወይምከተፈቀደበት ዓላማ ውጭእንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

33. <u>ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች ተመልሰው የተሸጡ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ የዋሉ እንደሆነ ታክሱ የሚከፈል ስለመሆኑ</u>

1. ማናቸውም ሰው ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘውሠንጠረዥ 2 ዕቃዎችን ወደአገር ውስጥ ካስገባ ወይም ከገዛበኋላከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይእንደሆነከተፈቀደበትዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ በዋሉበትቀንመሠረት የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር ውስጥከታክስ ነፃ መብት የተሰጠው የተፈጥሮ ሰውየሞተ እና ተሽከርካሪው በውርስ ለወራሾችየተላለፈ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ አይከፈልም፡፡ወ

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>

## <u>የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር</u>

34.<u>የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈጻሚነት</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ አስተዳደር አዋጅ የኤክሳይዝ ታክስአስተዳደርን በሚመለከት ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

35.<u>መዝገብ ስለመያዝ</u>

በዚህ አዋጅ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታየተጣለበት ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው እና ባለሥልጣኑ በሚያወጣውመመሪያ መሠረት የሂሳብ መዝገብ መያዝ

ያለበትሲሆን፣ የሚይዘውን የሂሳብ መዝገብ በታክስአስተዳደር አዋጅ ለተመለከተው ጊዜ እናበተመለከተው አኳኋን ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

36.**የኤክሳይዝ ታክስን ስለማስታወቅ**

በማናቸውም አንድ ወር የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበሆንም ባይሆንም የተፈቀደለት አምራችየእያንዳንዱን ወር ሂሳብ የሚቀጥለው ወር ጣኛው ቀንከማለፉ በፊት በፀደቀው ቅጽ እና በታዘዘው አኳኋንለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

37.**የኤክሳይዝ ታክስን የመክፈል ግዴታን ስለመወጣት**

1. የተፈቀደለት አምራች በአንድ ወር ውስጥከማምረቻው ፋብሪካ ወጪ ባደረጋቸው ዕቃዎችላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስየሚቀጥለው ወር ጣወኛው ቀን ከማለፉ በፊትለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
2. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶችየሚያቀርብ ሰው በአንድ ወር ባቀረባቸውአገልግሎቶች ላይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስየሚቀጥለው ወር ወኛው ቀን ከማለፉ በፊትለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
3. አስመጪው ወደአገር ውስጥ ባስገባቸውየኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎቹወደአገር ውስጥ በገቡበት ጊዜ ለታክሱባለሥልጣን መክፈል አለበት፡፡
4. ወደአገር ውስጥ በሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስበሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ታክሱ የሚሠላው፣የሚከፈለው፣ ሂሳቡ የሚያዘው እና የታክሱ ዕዳበአስገዳጅነት የሚሰበሰበው በጉምሩክ ሕግመሠረት ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## የወንጀል ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች

38.**አስተዳደራዊ ቅጣት**

1. ፈቃድ ሳይኖረው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 (1) (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውንሰው የሚከተለውን አስተዳደራዊ ቅጣትይቀጣል:-

   ሀ) የአዋጁ አንቀጽ 15 (1)(ሀ) ተፈፃሚየሚሆንበትን በሚመለከት ፈቃድ ቢሰጠው ኖሮ ሊከፍል ይገባ የነበረውን የኤክሳይዝታክስ እጥፍ፤

ለ) የአዋጁ አንቀጽ 15 (1) (ለ) ተፈፃሚየሚሆንበትን ሰው በሚመለከት የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው በሚገባ የኤክሳይዝታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ፡፡

2. በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው ቦታ ውጭየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ የተሠማራ የተፈቀደለትአምራች በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውንየኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ የገንዘብ ቅጣትእንዲከፍል ይገደዳል፡፡

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 (1) የተደነገገውተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስቁጥጥር ውጭ ከፋብሪካው ወጪ እንዳደረገየሚቆጠር የተፈቀደለት አምራች በዕቃዎቹላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክሰእጥፍ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖበታክስ አስተዳደር አዋጅ የተጣሉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ለኤክሳይዝ ታክስምተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

39.<u>ከፈቃድ እና ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ጋር የተያያዙ የወንጀል ጥፋቶች</u>

1. ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አንቀጽ 15(3)፣ 18(4)፣ 26(1)፣ 27(1)፣ 30(7)፣ 31(2) እና 32 ድንጋጌዎችን ተላልፎ መገኘቱ በፍርድ ቤትየተረጋገጠ እንደሆነ ከ3 እስከ 5 ዓመትለሚደርስ ፅኑ እስራትና ከብር 50 ሺ እስከ 100ሺበሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

2. የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ ከተመለከተውሥፍራ ውጭ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውንዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ መሰማራቱበፍርድ ቤትየተረጋገጠ እንደሆነ ከ5 እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 100ሺ እስከ 200ሺ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

3. የተፈቀደለት አምራች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 (1) እና 19 (2) የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘመሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ1 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እናከብር 100ሺ ባልበለጠ የገንዘብ ቅጣትይቀጣል፡፡

4. ማንኛውም ሰው:-

ሀ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ 23/3/(ለ) በመተላለፍ የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስቁጥጥር ውጭ ከማምረቻው ፋብሪካ ወጪያደረገ እንደሆነ፣

ለ) ፈቃድ ሳይኖረው በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርሥር ያሉ ዕቃዎች ተከማችተው በሚገኙበትቦታ የገባ እንደሆነ፣

ሐ) የኤክሳይዝ ታክሱ የሚከፈልባቸውንዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ባልተፈቀደ መንገድ ከተከማቹበት ቦታወጪ በማድረግ፣ ባህሪያቸውን በመለወጥወይም የቁጥጥሩን ሥራ በማወክ ረገድየተባበረ፣ እንደሆነ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ

ቤት ሲረጋጋጥ ከ5 እስከ 7 ዓመትበሚደርስ ፅኑ እሥራትና ከብር 100ሺ እስከ 200ሺ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

5. በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጭ የተመረቱየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችወይም የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸውከተመረቱበት ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችንየገዛ ወይም ሳይፈቀድለት እነዚህን ዕቃዎችየተቀበለ ወይም በይዞታው ሥር ያደረገ ወይምየኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎችለሽያጭ በማዋል ተግባር የተሠማራ ማናቸውምሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ3 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እናከብር 100ሺ እስከ 200ሺ በሚደርስ የገንዘብቅጣት ይቀጣል፡፡
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 ስለኤክሳይዝ ቴምብርየተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ ማናቸውም ሰውጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ2 እስከ 3 ዓመትበሚደርስ እስራት እና ከብር 50ሺ እስከ 100ሺ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

**40.<u>የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈፃሚነት</u>**

በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ የኤክሳይዝ ታክስ ወንጀልናአስተዳደራዊ ጥፋቶች ላይ የታክስ አስተዳደርአዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>ምዕራፍ ዘጠኝ</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**41.<u>ታክስ ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት</u>**

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም፣የታክሱባለሥልጣን:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ ላለመክፈል የሚያስችልስምምነት የተደረገ መሆኑን፤

ለ) ማናቸውም ሰው ይህንን ስምምነትበመጠቀም የታክስ ጥቅም ያገኘ መሆኑን፤

ሐ) የስምምነቱ ይዘት ሲመረመር፣ የስምምነቱዋና ዓላማ ተዋዋይ ወይም ሌላ ማናቸውምሰው የኤክሳይዝ ታክስ ጥቅም እንዲያገኝመሆኑን መረዳት የሚቻል ከሆነ፣

የታክሱባለሥልጣን ስምምነቱ እንዳልተደረገበመቂጠር የኤክሳይዝ ታክስ ጥቅም ያገኘውሰው የኤክሳይዝ ታክሱን እንዲከፍል ሊወስንይችላል፡፡

2. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (2) ከተገለፀው ውሳኔ ላይ የደረሰ እንደሆነ ይህንኑ የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያታክሱን መክፈል ላለበት ሰው መሳክ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረትየታክሱ ባለሥልጣን ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለውየኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታውከተቋቋመበት ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም:-

ሀ) "ስምምነት" በመግባባትየተፈፀመ፣ በግልጽየተፈፀመ ወይም በትርጉም የሚደረስበትወይም በሕግ ፊት ተፈፃሚነት ያለው ቢሆንምባይሆንም ድርጊት፣ ውልን፣ ማመቻቸትን፣ ቃልኪዳንን፣ ዕቅድን፣ የውሳኔ ሀሳብንወይም ግዴታመግባትን ይጨምራል፡፡

ለ) "የታክስ ጥቅም" ማለት:--

1. የኤክሳይዝ ታክስ ከመክፈል ግዴታ ነፃመሆንን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን መቀነስ፣
2. የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ የማግኘት መብትን ማቋቋም፤
3. የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታየሚፀናበትን ቀን ማዘግየት፤
4. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ቀንበማዘግየት ሌላ ማናቸውንም ጥቅም ማስገኘት፣
5. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያስገኝጥቅም:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ታክሱየማይከፈልባቸው እንዲሆኑ ማድረግ፣

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች አነስተኛ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልባቸውማድረግ፤

## 42. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀምየሚያግዝ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (1) መሠረት ለሚወጣ ደንብ አፈፃፀምመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

43.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ ምዕራፍ 3 ክፍል 1 ፈቃድስለማውጣት የተደነገገው ቢኖርም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ወይምአገልግሎት በመስጠት የተሠማራ ማናቸውም ሰውፈቃድ ባይኖረውም ወይም ባይመዘገብም ይህአዋጅ ከወጣበት ቀን አንስቶ እስከ 6 ወር ድረስየኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችየማምረት ወይም ወደአገር ውስጥ የማስገባትወይም አገልግሎት የመስጠት ሥራ ማከናወን ይችላል፡፡
2. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት በተመረቱየኤክሳይዝ ታክስ ባልተከፈለባቸው ዕቃዎች ላይየኤክሳይዝ ታክስ የሚሠላውና የሚሰበሰበውበዚህ አዋጅ መሠረት ይሆናል፡፡
3. ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በፊት የባንክ ፈቃድበተሰጣቸውና አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀንአንስቶ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ አገርበሚገቡ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስየሚጣለውና የሚሰበሰበው በኤክሳይዝ ታክስአዋጅ ቁጥር. 307/1995 (እንደተሻሻለ) ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል፡፡”
4. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት መሰብሰብሲኖርበት ያልተሰበሰበ የኤክሳይዝ ታክስ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995(እንደተሻሻለ) ድንጋጌዎች መሠረት ይሰበሰባል፡፡

44.<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ 307/1995 (እንደተሻሻለ) ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣መመሪያ ወይም አሠራር ይህንን አዋጅበሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

45.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበትከየካቲት 5 ቀን 2012 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 8 ቀን 2012 ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 1. ስብና ዘይት | | | |
| 15.01 እስከ 15.15 | | ለምግብነት የተዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም የሳቹሬትድ ቅባት መጠኑን ከተለጠፈበት መግለጫ ላይ ለማወቅ የሚያስችል የእንስሳት ወይ የአትክልት ስብ ዘይት፣ እና የእነዚህ ተዋፅኦ ውጤቶች | 30% |
| 15.16 | | ለምግብነት የጠዘጋጀ ከ100 ግራም ላይ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም 0.5 ግራም ወይም የበለጠ ለጤና ጎጂ የሆነ ቅባት የያዘ ወይም የሳቹሬትድ ቅባት መጠኑን ከጠለጠፈበት መግለጫ ላይ ለማወቅ የማይቻል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሀይድሮጂን የተጨመረበት የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብና ዘይት | 40% |
| 15.17 | | ለምግብነት የጠዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም 0.5 ግራም ወይም የበለጠ ለጤና ጎጂ የሆነ ቅባት የያዘ ማርጋሪን | 50% |
| 2. ስኳርና ከስኳር የጠገኙ ጣፋጭ ምግቦች | | | |
| 17.01 | 1701.1200 | ማንኛውም ዓይነት ስኳር ( በአንኳርም ሆነ በፈሳሽ መልክ የተዘጋጀ) ሞላሰስን ሳይጨምር መፕል ስኳር እና ማፕል ወለላ | 20% |
| | 1701.1400 | | |
| | 1701.9100 | | |
| | 1701.9900 | | |
| 17.02 | 1702.2000 | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
| 17.04 | 1704.1000 | ማስተካ ስኳር ቢቀባም ባይቀባም | |
| 17.04 | 1704.9000 | ከስኳር የተገኘ ጣፋጭ ምግቦች ነጭ ችኮላት ጭምር፣ ካካዎ የሌላቸው | 30% |
| 3. ቸኮላትና ከካዎ የለባቸው የምግብ ዝግጅት | | | |
| 18.06 | 1806.1000, 1806.2000, 1806.3100, 1806.3200, 1806.909 | ቸኮላትና ካካዎ ያለባቸው የምግብ ዝግጅት ፣ የህፃናትና የህሙማን ማግቦች ሳይጨምር | 30% |
| 4. ዴቄት ለስላሳ ምግቦች | | | |
| 21.06 | 2106.9040 | ዱቄት ለስላሳ መጠጦች | 25% |
| 5. መጠጦችና ሲቢርቶዎች | | | |
| 5.1 አልኮል አልባ መጠጦች | | | |
| 22.01 | 2201.1000<br>2201.9000 | ውሃዎች፣የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ የማዕድን ውሃዎች እና ጋዝ ያላቸው ውሃዎች ስኳር ወይም ማጣፈጫ ያልተጨመራባቸው ወይም ጣዕም እንዲኖራቸው ያልተደረጉ በፋብሪካ የታሸጉ፡፡ | 10% |
| 22.02 | 2202.1000 | ስኳር ወይም ሌላ ማጣፈጫ ያላቸው | 25% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 2202.9990 | ወይም ጠዕም እንዲኖራቸው የተደረጉ የማዕድና ውሓዎችና ጋዝ ያላቸው እና ማናቸውም አልኮል አልባ መጠጦች ከአትክልትና ከፍራፍሬ ጭማቂ እና የሰዎችን ጤንነት ለሚያሻሽል ከተዘጋጁ መጠጦች ውጪ | |
| | 2202.9100 | አልኮል አልባ ቢራ | 25% |
| 5.2 የአልኮል መጠጦችና ሲቢርቶዎች | | | |
| 22.03 | 2203.0000 | ማናቸውም ከብቅል የተዘጋጀ ቢራ | 40% ወይም 11ብር በሊትር ከሁለት አንዱ የበለጠውን |
| | | ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ በበቀል ገብስ የተመረተ ቢራ | 35 % ወይም 9ብር በሊትር ከሁለት አንዱ የበለጠውን |
| | | ውሃውን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚህለው በአገር ውስጥ ግብአት | 30% ወይም 8ብር በሊትር |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | የተመረተ ቢራ | ከሁለት አንዱ የበለጠውን |
| 22.06 | 2206.6000 | የሚፈሉ መመጠጦች (ሲዳር ፔሪ፣ሜድ፣ ኦፓክ ቢራ፣ የሩዝ አልኮል መጠዋ)፣ የሚፈሉ መጠጦችና የአልኮል አልባ መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፣ ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ | 40% ወይም 11 ብር በሊተር ከሁለት አንድ የበለጠውን |
| 22.08 | 2208.9010 | ሬዲ ቱ ድሪንክ (የአልኮል ይዘቱ ከ7 በመቶ ያልበለጠ) | 40% ወይም 11 በሊትር ከሁለት አንዱ የበለጠውን |
| 22.04 | 2204.1000<br>2204.2100<br>2204.2200 | ማናቸውም ከወይን እሸት የተዘጋጀ ወይን፣ ጠንካራ ወይን ጭምር፣ የወይን ጠጅ ድፍድፍ፣ የሚፈላ የወይን ጠጅ እና ሌሎች ፍራፍሬዎችን በማፍላት የሚገኙ የአልኮል መጠጦች | 40% |
| | 2204.2900<br>2204.3000 | ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75. የሚያህልን በሃገር ውስት ግንቦት የተመረተ ጠጅ | 30% |
| 22.05 | 2205.1000<br>2205.9000 | | |
| 22.08 | 2208.3000 | የሚፈሉ መጠጦች (ለምሳሌ ሲደር፣ፔሪ፣ሜድ) የሚፈሉ መጠጦችና አልኮል አልባ መጠጦችን ድብልቅ በይዞታ ከ80 በመቶ የበለጠ ወይም ያነሰ | 80% |
| 22.06 | 2206.0000 | | |
| 22.07 | 2207.1000 | | |
| 22.08 | 2208.2000 | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 2208.4000<br>2208.5000<br>2208.6000<br>2208.7000<br>2208.9090 | ጥንካሬ ያለው በባህሪው የተለወጠ ኢቴል አልኮል ፣ ሲቢርቶዎች፣ ሊከርስ እና ሌሎች ሲቢርቶ ያለቸው መጠጦች፣ በይዞታ 80 በመቶ የበለጠ ወይም ያነሰ ጥንካሬ ያለው በባህሪው የተለወጠ ኢቴል አልኮል፣ ሲቢርቶዎች፣ ሊከርስ፣ ውስኪ እና ሌሎች ሲቢርቶ ያላቸው መጠጦች፣ ውስኪ፣ ጂን፣ጀኔቫ፣ ቮድካ፣ ከተብለላላ የሸንኮራ አገዳ ውጤት የተገኘ ረምና ስፕሪቶ | |
| 22.07 | 2207.2000 | ማናቸውም ዓይነት ንፁህ አልኮል | 60% |
| 6. ትምበሆና የትምበሆ ውጤቶች | | | |
| 24.01 | 2401.1000<br>2401.2000<br>2401.3000 | የትመባሆ ቅጠል፣ ያልተፈበረከ ትምበሆ የትምበሆ ውዳቂ | 20% |
| 24.02 | 2402.2000 | ሲጋራ | 30%+8 ብር በእሽግ (20 ፍሬ) |
| | 2402.1000<br>2402.9000 | ሲጋራ፣ ሲጋሪሎስ፣ በቱቦ የሚጨስ ትምበሆ፣ ሱረት እና ሌሎች ማናቸውም የትንባሆ ምርቶች | 30%+ በኪሎ ግራም 250 ብር |
| | 2403.1900 | | |
| | 2403.9100 | | |
| | 2403.9900 | | |
| 7. ጨው | | | |
| 25.01 | 2501.0010<br>2501.0090 | ጨው | 25% |
| 8. የማዕድን ነዳጅ፣ የማዕድን ዘይት እና የማዕድን ውጤቶች | | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 27.10 | 2710.1200<br>2710.1910<br>2710.1920<br>2710.1950<br>2710.2010<br>2710.2020<br>2710.2050 | ቤንዚን ተራ ወይም ሱፐር፣ ፔትሮል ተራ ወይም ሱፐር፣ ጋዞሊን የሞተር ስፐሪቶች፣ የአውሮፕላን ነዳጅ፣ ቀላል ዘይቶችና ዝግጅት | 30% |
| 9. ሽቶዎች ፣ ቶይሌት ዋትርስ የቁንጅናና መኳኳያ ዝግጅቶችና ውጤቶች | | | |
| 33.03<br>33.04<br>33.05 | 3303.0000<br>3304.1000<br>3304.2000<br>3304.3000<br>3304.9100<br>3304.9900<br>3305.2000<br>3305.3000<br>3305.9000 | ሽቶዎች፣ ቶይሌት ዋተርስ፣ የቁንጅናና መኳኳያ ዝግጅቶችና ውጤቶች፣ ሰንሰክሪን እና ሻምፖ አይጨምርም | 100% |
| 10.ርችቶች | | | |
| 36.04 | 3604.1000 | ርችቶች | 100% |
| 11.የፕላስቲክ ከረጢቶች( ፌስታል) | | | |
| 39.23<br>39.23 | 3923.2110,<br>3923.2910,<br>3923.2910,<br>3923.2920 | የፕላስቲክ ከረጢት( ፌስታል) | በኪሎ ግራም 40% ብር |
| 12.ጎማዎች | | | |
| 40.11 እስከ 40.13 | 4011.1000 እስከ | ከላስቲክ የተሰሩ የተሽከርካሪ ጎማዎች | 5% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 4013.9090 | | |
| 13.በፋብሪካ የተፈበረኩ ጨርቃ ጨርቅና የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶች | | | |
| 50.07 | 5007.1010<br>5007.1090<br>5007.2010<br>5007.9010<br>5007.9090 | 8.1ሽምን ጨርቆች፣ የተሸመነ የተፈጥሮ ሐር፣ ሐር የመሰለ ጨርቅ፣ ናይሎን ሐር፣ እንዲነጣ የተደረገ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ፣ ቀለም የተነከረ ወይም የታተመበት ጨርቅ ፣ በማንኛውም ቁመትና አርብ ስፋት) የተቆረጠ፣ ብርድልብስ፣ አንሶላ፣ አልጋ ልብሰስ፣ ፎጣ፣ የጠረጴዛ ልብስ እና ሌሎች በፋብሪካ የተፈበረኩ ተመሳሳይ ጨርቆች፣ ከአጎበርና አቡጀዲ ውጪ | 8% |
| 51.11 እስከ 51.13 | 5111.1110 እስከ 5113.0090 | | |
| 52.08 እስከ 52.12 | 5208.1100 እስከ 5212.2500 | | |
| 53.09 እስከ 53.11 | 5309.1190 እስከ 5311.0090 | | |
| 54.07 እስከ 55.08 | 5407.1010 እስከ 5408.3400 | | |
| 55.12 እስከ 55.16 | 5512.1110 እስከ 5516.9400 | | |
| 58.01 እስከ 58.11 (ከ58.08 በስተቀር | 5801.1000 እስከ 5811.0000 (ከ5802.1100, 5804.1010 | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | በስተቀር) | | |
| 59.01 እስከ 59.11 (ከ59.02 በስተቀር) | 5901.1000 እስከ 5911.9000 (ከ5902.1000, 5902.2000, 5902.9000 በስተቀር) | | |
| 57.01 እስከ 57.05 | 5701.1000 እስከ 5705.0000 | 8.2 ምንጣፎች | 30% |
| 60.01 እስከ 60.06 | 6001.1000 እስከ 6006.9000 | 8.3 የተሰፉ ልብሶች | 8% |
| 62.01 እስከ 62.19 | 6201.1100 እስከ 6217.9000 | | |
| 63.01 እስከ 63.04 | 6310.1000 እስከ 6304.9990 | | |
| 14.አርቴፊሻል አበባዎች፣ ከቅጠሎችና ከፍሬዎችና የተሰሩ ዕቃዎች | | | |
| 67.02 | 6702.1000, 6702.9010, 6702.9090 | አርተፊሻል አበባዎች፣ ከአርተፊሻል አበባዎች፣ ቅጠሎችና ፍሬዎች እና የእነዚህ ክፍሎች፣ ከአርተፌፊል አበባዎች፣ ከቅጠሎች ወይም ከፍሬዎች የተሰሩ ዕቃዎች | 10% |
| 15.የሰው፣ የእንስሳት እና የሴንቴቲክ ጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያል ፀጉር | | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 67.03<br>67.04 | 6703.0000<br>6704.1100,<br>6704.1900,<br>6704.2000,<br>6704.9000 | የሰው ፀጉር፣ የሰው ፀጉር ውዳቂ፣ ዊግ፣ የውሸት ፂም፣ የውሸት ፀጉር፣ የውሸት ቅንድብ፣ የውሸት ሽፋሎች፣ የእንስሳት ፀጉር፣ ከሴንቴቲክ ጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ፀጉሮች | 40% |
| 16.አስቤስቶስና የአስቤስቶስ ውጤቶች | | | |
| 68.11,<br>68.12,<br>68.13 | 6811.4000,<br>6812.9100,<br>6812.9200,<br>6812.9300<br>6812.8000,<br>6812.9900,<br>6813.2000 | የአስቤስቶስ ሲሚንቶ፣ የሴሉሎስ ፋይበር ሲሚንቶ፣ ወይም እንዚህን ከመሳሰሉ የተሰሩ እቃዎች፣ በፋብሪካ የተሰሩ የአስቤስቶስ ፋይበሮች፣ መደባቸው አስቤንቶስ ወይም ማግኒዚየም ካርቦኔት የሆኑ ድብልቆች፣ ከነዚህ ድብልቆች ወይም አስቤስቶስ የተሰሩ ዕቃዎች( ለምሳሌ ክሮች ሽምን ጨርቆች፣ ልብሶች፣ በራስ የሚጠለቁ፣ ጫማዎች ጋስኬቶች)፣ የተጠናከሩ ቢሆኑም ባይሆኑም አስቤስቶስ ያላቸው የፍትጊያ መሳሪያዎች | 20% |
| 17.የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ ዕቃዎች እና የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች | | | |
| 71.01<br>እስከ<br>71.17<br>(71.15<br>በስተቀር) | 7101.1000<br>እስከ<br>7117.9090<br>(7108.2000,<br>7115.1000,<br>7115.9010<br>በስተቀር) | የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ ዕንቁዎች፣ ከከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች፣ ከከበሩ ብሮቶች እና በከበሩ ብረት የለበሱ ብረቶች የተሰሩ ጌጣጌጦች ዕቃዎች፣ ቅንስናሽ ገንዘብ ወይም ገንዘብ የሆነን ሳይጨምር | 20% |
| 18.ቪዲዮ መቅረጫ ወይም ማባዣ መሳሪያዎች፣ የቴሌቪዥን ስርጭት መቀበያዎች ፎቶ ወይም ቪዲዮ ካሜራ | | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 85.21 | 8521.1000, 8521.9010, 8521.9090 | ቪዲዮ መቅረጫ ወይም ማብዣ መሳሪያዎች ፣ የቪዲየፐ ቲዩነር ቢይዙም ባይዙም | 10% |
| 85.25 | 8525.8000 | የቴሌቪዥን ካሜራ፣ ዲጂታል ካሜራ፣ ቪዲዮ ካሜራ ሪከርደር | 10% |
| 85.27 | 8527.1310 | ከድምፅ መቅረጫ ወይም ማሰሚያ መሳሪያዎች ጋር የተጣመሩ በከፊል የተገጠመው የመገጣጠሚ ኢንደስትሪዎች ሲያስመጧቸው | 10% |
| | 8527.1390 | የሬዲዮ ድምፅ ስርጭት መቀበያ መሣሪያዎች ከድምፅ መቅረጫ ወይም ማባዣ መሳሪያዎች ጋር የተጣመሩ ሌሎች መሳሪያዎች | 10% |
| | 8527.1910 | የውጪ የኃይል ምንጭ ሳይኖራቸው መስራት የሚችሉ የሬዲዮ ድምፅ ስርጭት መቀበያ መሳሪያዎች በከፊል የተገጣጠሙ የመገጣጠሚያ ኢንደስትሪዎች ሲያስመጧቸው | 10% |
| | 8527.1990 | የውጪ የኃይል ምንጭ ሳይኖራቸው መስራት የሚችሉ የሬዲዮ ድምፅ ስርጨት መቀበያ መሳሪያዎች | 10% |
| | 8527.9920 | የሬዲዮ ድምፅ ስርጭት መቀበያ መሳሪያዎች ከቪሲዲ ወይም ዲቪዲ ማጫወቻ ጋር የተጣመሩ | 10% |
| | 8528.7210 | የቴሌቪዥን ስርጭት መቀበያ መሣሪያዎች የቪዲዮ መቅረጫ ወይም ማስተላለፊያ መሳሪያ ጋር የተጣመሩ | 10% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 85.28 | | ሆነው በከፊል የተገጣጠሙ፣ የመገጣጠሚያ ኢንዱስትሪዎች ሲያስመጧቸው | |
| | 8528.7220 | የቪዲዮ መቅረጫ ወይም ማስተላለፊያ መሳሪያ ጋር የተጣመሩ ሆነው ሙሉ በሙሉ ተበትነው የቀረቡ፣ የመገጣጠሚያ ኢንዱስተሪዎች ሲያስመጧቸው | 10% |
| | 8528.7230 | ሌሎች፣ በከፊል የተገጣጠሙ የመገጣጠሚያ ኢንዳስትሪዎች ሲያስመጧቸው | 10% |
| | 8528.7290 | ባለቀለም ቴሌቪዥን | 10% |
| 85.28 | 8528.7300 | ሞኖክሮም | 10% |
| 19.ተሽከርካሪዎች | | | |
| 87.01 | ትራክተር | | |
| 19.1 ባለአንድ አክስል ትራክተሮች | | | |
| | 8701.1021 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8701.1022 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8701.1023 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.2 የሲሚትፊለር መጎተቻ ትራክተሮች | | | |
| | 8701.2021 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8701.2022 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8701.2023 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት | 400% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | የበለጠ | |
| 19.3 የእርሻ ትራክተር | | | |
| | 8701.3021 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8701.3022 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያለበለጠ | 200% |
| | 8701.3023 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.4 ሌሎች የኤንጂን ጉልበታቸው፡- | | | |
| 19.4.1. ከ18 ኪሎ ዋት ያልበለጠ፡- | | | |
| | 8701.9121 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8701.9122 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8701.9123 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.4.2. ከ18 ኪሎ ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ37 ኪሎ ዋት ያልበለጠ | | | |
| | 8701.9221 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8701.9222 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያለበለጠ | 200% |
| | 8701.9223 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.4.3 ከ37 ኪሎ ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ75ኪሎ ዋት ያልበለጠ | | | |
| | 8701.9321 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8701.9322 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት | 200% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | |
| | 8701.9323 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.4.4 ከ75 ኪሎ ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ130 ኪሎ ዋት ያልበለጠ፡ | | | |
| | 8701.9421 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8701.9422 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8701.9423 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.4.5 ከ130 ኪሎ ዋት የበለጠ | | | |
| | 8701.9521 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8701.9522 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8701.9523 | ያገለገሉ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 87.02 ሹፌሩን ጨምሮ አስር ወይም የበለጡ ሰዎችን የሚያጓጉዙ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች | | | |
| 19.5 ባለ ኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምቦስሽን ፒስተን ኢንጂን ብቻ የሆኑ/ዲዝል ወይም ከፊል-ዲዝል | | | |
| | 8702.1021 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገኙ (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8702.1022 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገኙ (አዋቂዎች) ያልበለጠ፤ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8702.1023 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| | 8702.1024 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8702.1025 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8702.1026 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.6 ለፕሮፕልሽን የኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምቦስሽን ፒስተን ኢንጂን (ዲዝል ወይ ከፊል-ዲዝል) እና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣጥሞ የያዘ | | | |
| | 8702.2021 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8702.2022 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፤ ከአራት አመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8702.2023 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| | 8702.2024 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ | 100% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | ከአራት ዓመት ያልበለጠ | |
| | 8702.2025 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓዦች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8702.2026 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓዦች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.7 ለፕሮፕልሽን የስፓርኩ-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምቦስሽን ፒስተን ኢንጂን እና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምሮ የያዘ | | | |
| | 8702.3021 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓዦች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8702.3022 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓዦች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፤ ከአራት አመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8702.3023 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓዦች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| | 8702.3024 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓዦች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8702.3025 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓዦች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት | 200% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | ዓመት ያልበለጠ | |
| | 8702.3026 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.8 ለፕሮፐሊሽን የኤሌክትሪክ ሞተርን ብቻ የሚጠቀሙ | | | |
| | 8702.4021 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8702.4022 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፤ ከአራት አመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8702.4023 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| | 8702.4024 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8702.4025 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8702.4026 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገሮች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.9 ሌሎች ህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች | | | |
| | 8702.9021 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ | 100% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | ከ16 ተጓገኞች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | |
| | 8702.9022 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገኞች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፤ከአራት አመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8702.9023 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገኞች (አዋቂዎች) ያልበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| | 8702.9024 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገኞች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8702.9025 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገኞች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8702.9026 | የመቀመጫ አቅማቸው ሹፌሩን ጨምሮ ከ16 ተጓገኞች (አዋቂዎች) የበለጠ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 87.03 ባለሞተር መኪናዎች ና ሌሎች ባለሞተር ተሸከርካሪዎች፣ ሰቴሽን ዋገኖች እና የመወዳደሪያ መኪናዎች ጭምር፡- | | | |
| 19.10 በበረዶ ላይ የሚሔዱ ተሸከርካሪዎች፣ የጎልፍ መኪናዎች እና ተመሳሳይ ተሸከርካሪዎች | | | |
| | 8703.1021 | አንድ ዓመት ወይም ከዛ በላይ ነገር ግን | 50% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | ከሁለት ያልበለጠ | |
| | 8703.1022 | ከሁለት ዓመት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8703.1023 | ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.1024 | ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.11 ሌሎች ተሸከርካሪዎች ባለ ስፓርክ ኢግኒሽን ኢንተርናሽናል ኮምበስሽን ሪሲፕሮኬቲንግ ፒስተን ኢንጂን ብቻ የሆኑ | | | |
| 19.11.1 የሲሊንደር ይዘት ከ1000 ሲሲ ያልበለጠ፡- | | | |
| ባለሦስት እግር ተሸከርካሪዎች | | | |
| | 8703.2111 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.2112 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.2113 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.2114 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.2115 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.2116 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.2117 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| ሌሎች | | | |
| | 8703.2191 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.2192 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.2193 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.2194 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.2195 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.2196 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.2197 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| 19.11.2 የሲሊንደሩ ይዘት ከ1000 ሲሲ የበለጠ ነገር ግን ከ1500 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| የሲሊንደር ይዘት ከ1300 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.2211 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.2212 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 5% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.2213 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.2214 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.2215 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.2216 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.2217 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1300 ሲሲ የበለጠ | | | |
| | 8703.2221 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.2222 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.2223 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.2224 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 110% |
| | 8703.2225 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 160% |
| | 8703.2226 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 260% |
| | 8703.2227 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 460% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 19.11.3 የሲሊንደሩ ይዘት ከ1500 ሲሲ የበለጠ ነገር ግን ከ3000 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| የሲንደሩ ይዘት ከ1800 ያልበለጠ | | | |
| | 8703.2311 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.2312 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.2313 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.2314 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 110% |
| | 8703.2315 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 160% |
| | 8703.2316 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 260% |
| | 8703.2317 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 460% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1800 ሲሲ የበለጠ | | | |
| | 8703.2321 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 100% |
| | 8703.2322 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 100% |
| | 8703.2323 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 100% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.2324 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 150% |
| | 8703.2325 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.2326 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |
| | 8703.2327 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| የሲሊንደር ይዘት ከ3000 የበለጠ | | | |
| | 8703.2411 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 100% |
| | 8703.2412 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 100% |
| | 8703.2413 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 100% |
| | 8703.2421 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 150% |
| | 8703.2422 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.2423 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |
| | 8703.2424 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| 19.12. ሌሎች ተሽከርካዎች፣ ባለ ኮምፕሪሽን-አግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን ብቻ የሆኑ፤/ዲዝል ወይም ከፊል ዲዝል/፡- | | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 19.12.1 የሲሊንደሩ ይዘት ከ1500 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| ባለሦስት እግር ተሽከርካሪዎች፡- | | | |
| | 8703.3111 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.3112 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.3113 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.3114 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.3115 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.3116 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.3117 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1300 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.3121 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.3122 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተብትነው የቀረቡ | 5% |
| | 8703.3123 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 5% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.3124 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.3125 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.3126 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.3127 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1300 ሲሲ የበለጠ | | | |
| | 8703.3131 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.3132 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በኪፊል ተብትነው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.3133 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 60% |
| | 8703.3134 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 110% |
| | 8703.3135 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 160% |
| | 8703.3136 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 260% |
| | 8703.3137 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 460% |
| 19.12.2 የሲሊንደር ይዘት ከ1500 ሲሲ የበለጠ ነገር ግን ከ2500 ሲሲ ያልበለጠ | | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1800 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.3211 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዲስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተብትነው የቀረቡ | 100% |
| | 8703.3212 | አዲስ፣ በሀገር ውስጥ ኢንዲስትሪ እንዲገጣጠሙ በኪፊል ተብትነው የቀረቡ | 100% |
| | 8703.3213 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው የቀረቡ | 100% |
| | 8703.3214 | ያገለገሉ፣ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 150% |
| | 8703.3215 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.3216 | ያገለገሉ፣ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |
| | 8703.3217 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| የሲሊነደሩ ይዘት ከ1, 800 ሲሲ የበለጠ | | | |
| | 8703.3221 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.3222 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.3223 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.3224 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያበለጠ | 150% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.3225 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.3226 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |
| | 8703.3227 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ2,500 ሲሲ የበለጠ | | | |
| | 8703.3311 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.3312 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.3313 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703. 3321 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያበለጠ | 150% |
| | 8703.3322 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.3323 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |
| | 8703.3324 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| 19.13. ሌሎች ተሽከርካዎች፣ ለፕሮፐልሽን የስፓርክ-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ሪፕሮኬቲንግ ፒስተን ኢንጂን እና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምረዉ የያዙ፡ በዉጫዊ የኤክትሪክ ምንጭ ቻርጅ መሆን ከሚችሉት ሌላ፡ | | | |
| ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪዎች | | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.4011 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.4012 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.4013 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.4014 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያበለጠ | 55% |
| | 8703.4015 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.4016 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.4017 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1, 300 ሲሲ ያልበለጠ፤ | | | |
| | 8703.4021 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.4022 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.4023 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.4024 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.4025 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር | 105% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | |
| | 8703.4026 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.4027 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊነደሩ ይዘት ከ1, 300 ሲሲ የበለጠ ነገር ግን ከ1800 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.4031 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.4032 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.4033 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.4034 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 110% |
| | 8703.4035 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 160% |
| | 8703.4036 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 260% |
| | 8703.4037 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 460% |
| የሲሊነደሩ ይዘት ከ1,800 ሲሲ የበለጠ | | | |
| | 8703.4041 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.4042 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.4043 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.4044 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 150% |
| | 8703.4045 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.4046 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |
| | 8703.4047 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| 19.14. ሌሎች ተሸከርካሪዎች፣ ለፕሮፐልሽን የኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንትርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጅን (ዲዝል ወይም ከፊል ዲዝል) እና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምረዉ የያዙ፣ በዉጫዊ የኤሌክትሪክ ምንጭ ቻርጅ መሆን ከሚችሉት ሌላ፤ | | | |
| ባለሦስት እግር ተሸከርካሪዎች፡ | | | |
| | 8703.5011 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.5012 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.5013 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.5014 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.5015 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር | 105% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | |
| | 8703.5016 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.5017 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊነደሩ ይዘት ከ1,300 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.5021 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.5022 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.5023 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.5024 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.5025 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.5026 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.5027 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊነደሩ ይዘት ከ1, 300 ሲሲ የበለጠ ነገር ግን ከ1800 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.5031 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 60% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.5032 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.5033 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.5034 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 110% |
| | 8703.5035 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 160% |
| | 8703.5036 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 260% |
| | 8703.5037 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 460% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ 1800 ሲሲ የበለጠ | | | |
| | 8703.5041 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.5042 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.5043 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.5044 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 150% |
| | 8703.5045 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.5046 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.5047 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| 19.15. ሌሎች ተሽከርካሪዎች ፣ለፕሮፐልሽን የስፓረክ-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ሪሲፕሮኬቲንግ ፒስተን ኢንጅን እና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምረዉ የያዙ፣ በዉጫዊ የኤሌክትሪክ ምንጭ ቻርጅ መሆን የሚችሉ፤ | | | |
| ባለሦስት እግር ተሽከርካሪዎች | | | |
| | 8703.6011 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.6012 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.6013 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.6014 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.6015 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.6016 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.6017 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲንደሩ ይዘት ከ1300 ሲሲ ያልበለጠ፡- | | | |
| | 8703.6021 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.6022 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ | 5% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | |
| | 8703.6023 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.6024 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.6025 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.6026 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |
| | 8703.6027 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊነደሩ ይዘት ከ1,300 ሲሲ የበለጠ ነገር ግን ከ1800 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.6031 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 60 |
| | 8703.6032 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.6033 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.6034 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 110% |
| | 8703.6035 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 160% |
| | 8703.6036 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 260% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.6037 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 460% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1800 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.6041 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.6042 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.6043 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.6044 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 150% |
| | 8703.6045 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.6046 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |
| | 8703.6047 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| 19.16. ሌሎች ተሸከርካሪዎች ፣ለፕሮፐልሽን የኮምፕሬሽን-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጅን( ዲዝል ወይም ከፊል ዲዝል) እና ኤሌክትሪክ ሞተርን አጣምረዉ የያዙ፣ በዉጫዊ የኤሌክትሪክ ምንጭ ቻርጅ መሆን የሚችሉ፤ | | | |
| ባለሦስት እግር ተሽከርካሪዎች | | | |
| | 8703.7011 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.7012 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ | 5% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | |
| | 8703.7013 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.7014 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.7015 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.7016 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 2055% |
| | 8703.7017 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1300 ሲሲ ያልበለጠ፡- | | | |
| | 8703.7021 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.7022 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.7023 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8703.7024 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 55% |
| | 8703.7025 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 105% |
| | 8703.7026 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 205% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.7027 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 405% |
| የሲሊነደሩ ይዘት ከ1,300 ሲሲ የበለጠ ነገር ግን ከ1800 ሲሲ ያልበለጠ | | | |
| | 8703.7031 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.7032 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.7033 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 60% |
| | 8703.7034 | ያገለገሉ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 110% |
| | 8703.7035 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 160% |
| | 8703.7036 | ያገለገሉ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 260% |
| | 8703.7037 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 460% |
| የሲሊንደሩ ይዘት ከ1800 ሲሲ የበለጠ፡- | | | |
| | 8703.7041 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.7042 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 100% |
| | 8703.7043 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 100% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.7044 | ያገለገሉ፤አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 150% |
| | 8703.7045 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.7046 | ያገለገሉ፤ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 300% |
| | 8703.7047 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 500% |
| 19.17. ሌሎች ተሽከርካሪዎች ፣ ለፕሮፐልሽን ኤሌክትሪክ ሞተርን ብቻ የያዙ፤ | | | |
| | 8703.8021 | ያገለገሉ፤አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 50% |
| | 8703.8022 | ያገለገሉ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8703.8023 | ያገለገሉ፤ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8703.8024 | ያገለገሉ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.18.ሌሎች ተሽከርካሪዎች | | | |
| | 8703.9011 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 30% |
| | 8703.9012 | አዲስ፣ በሃገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 30% |
| | 8703.9013 | አዲስ፣ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 30% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8703.9021 | ያገለገለ፣አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት ያልበለጠ | 80% |
| | 8703.9022 | ያገለገለ፣ ከሁለት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 130% |
| | 8703.9023 | ያገለገለ፣ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 230% |
| | 8703.9024 | ያገለገለ፣ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 430% |
| 87.04 እቃዎች ለመጫን/ለማጓጓዝ/ የሚያገግሉ ተሽከርካሪዎች | | | |
| 19.19. ከአዉራ ጎዳናዎች ወጭ እንዲያገለግሉ ዲዛይን የተደረጉ ግባጭ ተሽከርካሪዎች፡- | | | |
| | 8704.1021 | ያገለገለ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8704.1022 | ያገለገለ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.1023 | ያገለገለ፣ ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.20. ሌሎች ባለኮምፕሬሽን ተሽከርካሪዎች-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጅን የሆኑ ( ዲዝል ወይም ከፊል ዲዝል) ተሽከርካሪዎች፡ | | | |
| 19.20.1. ከ5 ቶን ያልበለጠ ግሮስ ቬክል ዌይት ያላቸዉ፡- | | | |
| ከ 1500 ኪ.ግ ያልበለጠ የመጫን ችሎታ ያላቸዉ፡- | | | |
| | 8704.2114 | ያገለገለ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8704.2115 | ያገለገሉ፣ ዕድሜያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.2116 | ያገለገሉ፣ዕድሜያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| ከ 1500 ኪ.ግ የበለጠ የመጫን ችሎታ ያላቸዉ፡- | | | |
| | 8704.2124 | ያገለገሉ፣ ዕድሜያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8704.2125 | ያገለገሉ፣ ዕድሜያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.2126 | ያገለገሉ፣ ዕድሜያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.20.2. ከ5 ቶን የበለጠ ነገር ግን ከ20 ቶን ያልበለጠግሮስ ቬክል ዌይት ያላቸዉ፡- | | | |
| | 8704.2221 | ያገለገሉ፣ ዕድሜያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8704.2222 | ያገለገሉ፣ ዕድሜያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.2223 | ያገለገሉ፣ ዕድሜያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.20.3. ከ20 ቶን የበለጠ ግሮስ ቬክል ዌይት ያላቸዉ፡- | | | |
| | 8704.2321 | ያገለገሉ፣ ዕድሜያቸዉ ከአራት ዓመት | 100% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | ያልበለጠ | |
| | 8704.2322 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.2323 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.21. ሌሎች፣ባ ስፓርክ-ኢግኒሽን ኢንተርናል ኮምበስሽን ፒስተን ኢንጂን የሆኑ፡ | | | |
| 19.21.1. . ከ5 ቶን ያልበለጠ ግሮስ ቬክል ዌይት ያላቸዉ | | | |
| ከ1500 ኪሎ ግራም ያልበለጠ የመጫን ችሎታ ያላቸዉ፡ | | | |
| | 8704.3114 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8704.3115 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.3116 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| ከ1500 ኪሎ ግራም የበለጠ የመጫን ችሎታ ያላቸዉ፡ | | | |
| | 8704.3124 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8704.3125 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.3126 | ያገለገሉ፣ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት | 400% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | የበለጠ | |
| 19.21.2. . ከ5 ቶን የበለጠ ግሮስ ቬክል ዌይት ያላቸዉ | | | |
| | 8704.3221 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8704.3222 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.3223 | ያገለገሉ፣ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.22. ሌሎች የጭነት ተሽከርካሪዎች | | | |
| | 8704.9021 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8704.9022 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8704.9023 | ያገለገሉ፣ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 87.05 | ለተለየ አገልግሎት የሚዉሉ ባለ ሞተር ተሽከርካሪዎች አይነተኛ ተግባራቸዉ ሰዎችን ወይም ዕቃዎችን ለማጓጓዝ እንዲሆን ተብለዉ ከተሰሩት ሌላ /ለምሳሌ ፣አሮጌ መኪናዎች ማንሻ መኪናዎች ፣ ዕቃ ማንሻ ካሚዎኖች ፣ የእሳት አደጋ መካከያ ተሽከርካሪዎች ፣ የኮንክሪት ማደባለቂያ ካሚዎኖች ፣የመንገድ መጥረጊያ ካሚዎኖች ፣የመንገድ መርጫ መኪናዎች ፣ተንቀሳቃሽ ወርክሾፖች፣ ተንቀሳቃሽ ራዲዮለጂካል ዩኒቶች/፡፡ | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 19.23. የዕቃ ማንሻ ካሚዎኖች | | | |
| | 8705.1021 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8705.1022 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8705.1023 | ያገለገሉ፣ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.24. ተንቀሳቃሽ የጉድጓድ መቆፈሪያ ዴሪኮች | | | |
| | 8705.2021 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8705.2022 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8705.2023 | ያገለገሉ፣ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት የበለጠ | 400% |
| 19.25. ፣ የኮንክሪት ማደባለቂያ ካሚዎኖች | | | |
| | 8705.4021 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት ያልበለጠ | 100% |
| | 8705.4022 | ያገለገሉ፣ ዕድሚያቸዉ ከአራት ዓመት የበለጠ ነገር ግን ከሰባት ዓመት ያልበለጠ | 200% |
| | 8705.4023 | ያገለገሉ፣ዕድሚያቸዉ ከሰባት ዓመት | 400% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | | የበለጠ | |
| 19.26. የሞተር ሳይክሎች | | | |
| 87.11 | 8711.1011 | በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.1012 | በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.1013 | ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.1020 | ሞተር ሳይክል (ያገለገለ) | 200% |
| | 8711.2011 | በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.2012 | በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.2013 | ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.2020 | ሞተር ሳይክል (ያገለገለ) | 200% |
| | 8711.3011 | በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.3012 | በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.3013 | ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.3020 | ሞተር ሳይክል (ያገለገለ) | 200% |
| | 8711.4011 | በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8711.4012 | በአገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.4013 | ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.4020 | ሞተር ሳይክል (ያገለገለ) | 200% |
| | 8711.5011 | በአገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.5012 | በአገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.5013 | ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.5020 | ሞተር ሳይክል (ያገለገለ) | 200% |
| | 8711.6020 | ሞተር ሳይክል (ያገለገለ በኤሌክትሪክ የሚሰራ) | 200% |
| | 8711.9011 | በአገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.9012 | በአገር ዉስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠሙ በከፊል ተበትነዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.9013 | ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመዉ የቀረቡ | 5% |
| | 8711.9020 | ሞተር ሳይክል (ያገለገለ) | 200% |
| 87.16 ተሳቢዎች እና ሴሚትሬለረች፣ ሌሎች ተሽከርካሪዎች፣ በሜካኒካዊ ዘዴ የማይንቀሳቀሱ ፣ የነዚሁ ክፍሎች፡፡ | | | |
| 19.27. ተሳቢዎች እና ቅጥልጥል ሴሚትሬለረች፣እንደ መኖሪያቤት የሚያገለግሉ ወይም ለካምፒንግ የሚሆኑ | | | |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| | 8716.1020 | ያገለገለ | 200% |
| 19.28. ለእርሻ አገልግሎት የሚዉሉ በራሳቸዉ እቃዎችን የሚጭኑ እና የሚያራግፉ ተሳቢዎች እና ሴሚትሬለሮች፡- | | | |
| | 8716.2020 | ያገለገለ | 200% |
| 19.29. ሌሎች እቃዎችን ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ ተሳቢዎች እና ሴሚትሬለሮች፡- | | | |
| ተሳቢ ቦቴዎች እና ሴሚትሬለሮር ቦቴዎች፡- | | | |
| | 8716.3120 | ያገለገለ | 200% |
| 19.30 ሌሎች፡- | | | |
| | 8716.3920 | ያገለገለ | 200% |
| 19.31. ሌሎች ተሳቢዎች እና ሴሚትሬለሮች፡- | | | |
| | 8716.4020 | ያገለገለ | 200% |
| 19.32. ሌሎች ተሽከርካሪዎች | | | |
| የሬንጅ እና የቅጥራን ማፍሊያዎች ፤ እና ለመንገድ ስራ እና ጥገና የሚሆኑ ተመሳሳይ ተሽከርካሪዎች | | | |
| | 8716.8012 | ያገለገለ | 200% |
| 19.33. ሌሎች፡- | | | |
| | 8716.8092 | ያገለገለ | 200% |
| 19.34. ቪዲዮ ጌም ማሽኖች፣ የበዓል፣የካርኒቫል፣ የአስማት መጫዎቻዎችና መቀለጃዎች፣የቁማር ማሽኖች እነ መጫወቻ ካርታ | | | |
| 95.04 እስከ | 9504.2000 እስከ | የቪዲዮጌም ማሽኖች፣ የበዓል፣የካርኒቫል፣የአስማት | 20% |

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው አይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| 95.05 | 9505.9000 | መጫዎቻዎችና መቅለጃዎች፣የቁማር ማሽኖች እነ መጫወቻ ካርታ | |
| 19.35. የትምባሆ ፒፖዎች(ጋያ ጭምር) ፡ የሲጋራ ወይምየሲካራ መያዣዎች እና የነዚሁ ክፍሎች | | | |
| 96.14 | 9614.0010 | የሺሻ ፒፖዎች | 20% |
| | 9614.0090 | የትምባሆ ፒፖዎች (የጋያ ጭምር)፣ የሲጋራ ወይም የሲካራ መያዣዎች እና የነዚሁ ክፍሎች | 20% |

# አዋጅ ቁጥር 308/ 1995 ዓ.ም

## የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ

ቁጠባንና ኢንቬስትመንት ለማሳደግ፣ታክስ ከመክፈል ለመሸሽ ወይም በሕጉ ውስጥ የሚታየውን ክፍተት በመጠቀም ታክሱን ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማፋጠን፣ እና በጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርትና በመንግሥት ገቢ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል የተጨማሪ እሴት ታክስ በሥራ ላይ እንዲውል የተወሰነ በመሆኑ፣

የተጨማሪ እሴት ታክስን አስተዳደር አመቺነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለታክሱ የሚመዘገቡ ሰዎች ታክስ የሚከፈልበት ዓመታዊ ግብይት ከብር 500,000 በላይ እንዲሆን የተወሰነ ስለሆነ፣

ንግድ ግንኙነት ውስጥ ፍትሐዊነትን ለማስፈን ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ፣ እና የታክስ ሥርዓቱን ሽፋን የተሟላ ለማድረግ የማስተካከያ ተርንኦቨር ታክስ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55(1) እና (11) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭርርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   1. በዚህ አዋጅ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 (ከዚህ በኋላ “የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ” ተብሎ በሚጠቀሰው) ውስጥ የተሰጣቸውን ትርጉምይይዛሉ፤
   2. “ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ” ማለት የወጪ ተቀናሽ ሳይደረግ የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ሲሆን፣ የተሸጡት ዕቃዎች የተመረቱበትን ወይም የተገዙበትን ዋጋ ይጨምራል፤
   3. “ታክስ የሚከፈልበት ግብይት” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ ከተደረገው ግብይት በስተቀር በንግድ ሥራ ሂደት ወይም የንግድ ሥራን እንቅስቃሴ ለማሻሻል በሚደረግ ጥረት ዕቃዎችን ማቅረብ ወይም አገልግሎቶችን መስጠት ነው፤

4. “ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው” ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር285/1994 አንቀጽ 16 እና 17 በተደነገገው መሠረት ዓመታዊ የሽያጭ እንቅስቃሴው ከብር 500,000 ወይም ሚኒስትሩ ከሚወስነው መጠን በታች በመሆኑ ምክንያት ወይም በፈቃደኝነት ያልተመዘገበ ሰው ነው፤
5. “ሰው” ማለት ማንኛውም ግለሰብ፤ ድርጅት ወይም ማኅበር ሲሆን፣ ሌላን ሰው በመወከል ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የንግድ ሥራ የሚያካሂድን የንግድ ወኪል ይጨምራል፤
6. “ድርጅት” ማለት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ማናቸውም ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ወይም ከተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ጋር ተመሳሳይ የሆነና በውጭ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማናቸውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት ሲሆን፣ በውጭ አገር ያለን አካል በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያካሂደውን ወኪል እና ፀንቶ በሚሠራበት በኢትዮጵያወይም በሌላ አገር ሕግ የተመሠረተ ወይም ዕውቅና ያገኘ ቢሆንም ባይሆንም እንደ ድርጅት የሚንቀሳቀስንይጨምራል፤
7. “ዕቃ” ማለት የልውውጥ ዋጋ ያለው፣ ጠቀሜታ የሚሰጥ ወይም ፍላጐት የሚያሟላ ማናቸውም ዕቃ ወይም ሸቀጥ ሲሆን እንስሳትንም ይጨምራል፤›
8. “ሽያጭ” ማለት ዕቃዎችን በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት መገበያየት እና የተወሰነ ክፍያ በመቀበል አገልግሎት መስጠት ሲሆን፣ ታክስ ከፋዩ ያለክፍያ የሚሰጣቸውን ዕቃዎች ወይም የሚያቀርባቸውን አገልግሎቶች ይጨምራል፤
9. “አገልግሎት” ማለት የዕቃዎችን ዝውውር የማይጨምር በክፍያ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው፡፡
10. “የታክስ ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መሥሪያ ቤት እና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተቋቋመ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ እንዲሁምየየክልሉ እና የከተማ መስተዳድሮች የገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው፤[100]
11. “ታክስ” ማለት የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ሽያጭ በተከናወነ ቁጥር የሚከፈል ተርን ኦቨር ታክስ ነው፤

[100] በ15/8(2001) አ.611 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

12.“ታክስ ከፋይ” ማለት የተርን ኦቨር ታክስ ሰብስቦ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ እንዲያደርግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው፤

13.“ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[101] እና ሚኒስትር ነው።

3. **የአዋጁ ተፈጻሚነት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ወይም አዋጁን መሠረት በማድረግ በሚወጣው መመሪያ ነፃ ካልተደረጉ በስተቀር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች በአገር ውስጥ በሚሸጡዋቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት ተርን ኦቨር ታክስ ይከፈላል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የታክስ ማስከፈያ ልክ ስለመወሰን እና ከታክሱ ነጻ ስለማድረግ

4. **የተርን ኦቨር ታክስ ተመን**

1. በማናቸውም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች ላይ 2 በመቶ (ሁለት ፐርሰንት)
2. በአገር ውስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ፤

ሀ/ የሥራ ተቋራጮች፣ የእህል ወፍጮ ቤቶች፣ የትራክተሮች እና ኮምባይን ሀርቨስተሮች አገልግሎት 2 በመቶ (ሁለት ፐርሰንት)

ለ/ ሌሎች 10 በመቶ (አሥር ፐርሰንት)

ተርን ኦቨር ታክስ ይከፈላል፡፡

5. **የተርን ኦቨር ታክስ ስሌት መሠረት**

ታክሱ የሚሰላበት ዋጋ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ነው።

6. **የተርን ኦቨር ታክስ ሰብስቦ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት**

ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጥ ማንኛውም ሰው በሽያጩ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ከገዥው ሰብስቦ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት። ስለሆነም ሻጩ ስለታክሱ የመጀመሪያ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

7. **ከታክስ ነፃ ስለመሆን**

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ከተጣለው የተርን ኦቨር ታክስ ክፍያ ነፃ ናቸው፤

[101]በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) የገንዘብ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

ሀ/ ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፣

ለ/ የፋይናንስ አገልግሎቶች፣

ሐ/ ለማንቲሞች እና ሜዳሊያዎች ጥናት አገልግሎት ከሚውሉት በስተቀር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ገንዘቦችን እና የዋስትና ሰነዶችን ማስራጨት፣

መ/ በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች፣

ሠ/ የሕክምና አገልግሎቶች እና አግባብ ባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚወጣ መመሪያ መሠረትበሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች፣

ረ/ በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶች እንዲሁም ለሕፃናት ጥበቃ በመዋዕለ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

ሰ/ ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣

ሸ/ የኤሌክትሪክ፣ የኬሮሲን እና የውሃ አቅርቦት፣

ቀ/ የትራንስፖርት አገልግሎቶች፣

በ/ ማንኛውንም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግሥት የሚፈጸም ክፍያ፣

ተ/ ከ60 በመቶ በላይ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ ድርጅት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣

ቸ/ መፃሕፍት፡፡

2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ በሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የሚከፈለው ታክስ ቀሪ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት ከታክስ ነፃ የመሆን መብቶች አፈፃፀም የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያይወሰናል፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የታክሱ አስተዳደር ሥርዓት</u>**

8. **<u>ታክሱን የማስተዳደር እና ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት</u>**

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተርን ኦቨር ታክሱን ስሌት በትክክል የማከናወን፣ የታክሱን ማስታወቂያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን የማቅረብና ታክሱን በጊዜው የመክፈል ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ነው።

2. የተርን ኦቨር ታክስን የማስተዳደር ኃላፊነት የታክሱ ባለሥልጣን ነው።

9. **የሂሳብ መዝገብ ስለመያዝ**

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር286/1994[102] አንቀጽ 48 የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን እንዲያገለግል በገቢ ግብር አዋጁ የታዘዘውን የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለባቸው።

10. **የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ስለማቅረብ እና ታክሱንስለመክፈል**

1. የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች፣

ሀ/ የእያንዳንዱ የሂሣብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወዲያውኑ የመክፈል፤[103]

ለ/ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ለማቅረቢያ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሂሳብ ጊዜው መከፈል ያለበትን ታክስ የመክፈል፤

ግዴታ አለባቸው።

2. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የሂሳብ ጊዜ" ማለት፤

ሀ/ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 የደረጃ 'ሀ' ግብር ከፋዮች ተብለው የሚታወቁ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሌለባቸው ታክስ ከፋዮች በየወሩ፣

ለ/ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በተደነገገው መሠረት የሂሣብ መዝገብ ለሚይዙ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ወይም በታክሱ ባለሥልጣን ሲፈቀድ በአውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ የሚቆጠር የየሦስት ወር ጊዜ፣

ሐ/ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በተደነገገው መሠረት የሂሣብ መዝገብ ለማይዙ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የበጀት ዓመቱ፤

ነው፡፡

[102] በ22/104(2008) አ.980 ተሻረ፡፡

[103] በ15/8(2001) አ.611 ተሻሻለ፡፡

## 11. የተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን

1. የታክሱ ባለሥልጣን የታክስ ከፋዩን ሂሣብ ከመረመረ በኋላ ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አሳንሶ ያስታወቀ መሆኑን የደረሰበት እንደሆነ ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. የታክስ ከፋዩ የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶቹ በማናቸውም ምክንያት በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ካላገኙ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ እንዲቀርቡ ተጠይቆ ካልቀረቡ ወይም የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች ከሌሉ የታክሱ ባለሥልጣን ታክሱን ባለው መረጃ ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን የአገር ውስጥ ገበያ ዋጋ፣ ዋጋው የማይታወቅ ከሆነ የተመሳሳዩን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይወስናል።
3. በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሂሣብ መዝገብ የማይዙ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች የተርን ኦቨር ታክስ በቁርጥ ይወሰናል። በቁርጥ የሚከፈለው ተርን ኦቨር ታክስ ስሌት መሠረት ለገቢ ግብር መሠረትየሆነው ጠቅላላ ገቢ ነው።
4. የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው የታክስ ውሣኔ በማስታወቂያ ተዘጋጅቶ ለታክስ ከፋዩ ይላካል። የውሣኔ ማስታወቂያ የመላኩ አፈፃፀም በገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች
   መሠረት ይፈፀማል።
5. የታክሱ ባለሥልጣን በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ የሰጠ እና የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ እንዲከፍል የተጠየቀውን ተጨማሪ ታክስ ያልከፈለ ወይም በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በአንቀጽ 21 መሠረት ይግባኝ ያላቀረበ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው፡፡
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት ታክስ ከፋዩ ታክሱን አስታውቆ ከከፈለበት የበጀት ዓመት መጨረሻ አንስቶ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ የታክሱ ባለሥልጣን የታክሱን ልክ ወስኖ ቀሪ ሂሣብ መኖሩን ካላስታወቀ የተከፈለው ታክስ በቂና የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ሆኖም ታክስ ከፋዩ ገቢውን ያላስታወቀ ወይም የተጭበረበረ የገቢ ማስታወቂያ ያቀረበ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በማናቸውም ሌላ ሕግ የተደነገገው ይርጋ ሳያግደው ታክሱን በማናቸውም ጊዜ መወሰን ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የታክሱ አሰባሰብ አፈፃፀም

12.<u>የታክሱ ባለሥልጣን ሥልጣን</u>

በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች ከተጠቀሱት በተጨማሪ የታክሱ ባለሥልጣን የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. ይህን አዋጅ በሥራ ላይ የማዋል እና የማስፈፀም ኃላፊነት የታክሱ ባለሥልጣን ይሆናል፤
2. በማናቸውም ሌላ ሕግ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የታክሱ ባለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ በታክስ ከፋይ የቀረቡ ማንኛቸውንም መግለጫዎች፣ ሰነዶችና የሂሣብ መዝገቦች ለማረጋገጥ፣

   ሀ/ ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጣቸውን ተቆጣጣሪዎች ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ቦታ በመላክ የሂሣብ መግለጫዎችን፣ ሰነዶችን እና የሂሣብ መዝገቦችን ወይም ገቢና ወጪን የሚያሳዩ ሰነዶችን፣ ለንግድ የተከማቹ ዕቃዎችን ወይም ሌሎች ዕቃዎችን ለማመሳከርና ለመመርመር፣

   ለ/ ታክስ ከፋዩን ወይም የሂሳብ መዝገቦችን እና ሰነዶችን ወይም መረጃን ለማግኘት የሚችለውን ወይም እነዚህኑ የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠውን ማንኛውንም የታክስ ከፋዩን ተቀጣሪ በአመቺ የታክሱ ባለሥልጣን የሥራ ሰዓቶች እና በጽ/ቤቱ ተገኝቶ ለሚቀርቡለት ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥና የተባሉትንም ሰነዶች እንዲያቀርብ ለማድረግ፣

   ሐ/ ማዘጋጃ ቤት፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውንም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥትመሥሪያ ቤት ጨምሮ ማንኛውም ሰው ስለታክስ ከፋዩ የሚያውቀውን መረጃ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ዝርዝር እንዲገልፅ ለማድረግ ይችላል፡፡

13.<u>ታክስ ለመሰብሰብ ሀብት ስለመያዝ</u>

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም በዚህ አዋጅ የተጣለው ታክስ የሚፈልግበት ሰው በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (5) ወይም በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ(2) በተደነገገው መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን የዚህን ታክስ ከፋይ ሀብት በመያዝ

ለሚፈለግበት ታክስ እና ንብረቱን ለመያዝ የተደረገውን ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን እንዲውል ለማድረግ ሕጋዊ ሥልጣን

2. ለዚህ ክፍል አፈፃፀም “መያዝ” በማናቸውም መንገድ መያዝን፣ እንዲሁም የተርን ኦቨር ታክስ የሚፈለግበት ሰው የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት በእጁ ከሚገኝ ሰው ታክስ መሰብሰብን ይጨምራል። በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (6) በተነገረው መሠረት ካልሆነ በስተቀር መያዝ የሚቻለው የመያዙ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በይዞታ ሥር የሚገኝ ንብረት እና የመያዙ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ፀንቶ ያለ ግዴታን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ የታክሱ ባለሥልጣን የታክስ ከፋዩን ሀብት በሚይዝበት ጊዜ የፖሊስ ሠራዊት አባል እንዲገኝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሀብቱን ከያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር ከ10 (አሥር) ቀናት ጊዜ በኋላ በሐራጅ ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደ በማናቸውም ሌላ ዘዴ የያዘውን ንብረት መሸጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ መስሎ በሚታየው ጊዜ ሊሸጠው ይችላል፡፡

3. ማናቸውም የተያዘ ንብረት ለመያዙ ምክንያት የሆነውን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን በቂ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው የታክስ ዕዳእና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍለው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የታክስ ዕዳው የሚፈለግበትን ሰው ሌሎች ሀብቶች መያዝ ይችላል፡፡

4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ ምክንያት ንብረት መያዝ የሚቻለው የታክሱ ባለሥልጣን ሀብቱን የመያዝ ሀሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ካስታወቀው በኋላ ይሆናል፡፡ በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ማስታወቂያ ሀብቱ ከመያዙ ከ30 (ሰላሳ) ቀን በፊት ለታክስ ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል፡፡

5. የታክሱ ባለሥልጣን የታክሱን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነና በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ ታክሱ ወዲያውኑ እንዲከፈል ለማድረግ ጥያቄ ካቀረበ እንዲሁም ታክስ ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ንብረትን በመያዝ ታክስ የመሰብሰቡ አፈፃፀም ሕጋዊ ይሆናል፡፡

6. ማናቸውም ንብረት የተያዘ ወይም እንዲያዝ የታሰበ ከሆነ ስለዚሁ ንብረት ማስረጃ የሚሆን ወይም መግለጫ የያዘ ሰነድ ወይም መዝገብ በእጁ የሚገኝ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው በታክስ ባለሥልጣን ጥያቄ ሲቀርብለት ሰነዱን ወይም መዝገቡን ለማስረጃነት ማቅረብ አለበት፡፡
7. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈጻጸም ላይ ያለ ወይም በዋስትና የተያዘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም በታክስ ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጁ የሚገኝ ወይም ለታክስ ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቀው የያዘውን ሀብት ለታክሱ ባለሥልጣን የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡
8. ማናቸውም ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቀው አንድን የተያዘ ንብረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በተያዘው ንብረት መጠን በግል ተጠያቂይሆናል፡፡ ሆኖም ተጠያቂነቱ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት ከሆነው የታክስ ዕዳ መጠን (በታክሱ ዕዳ ላይ የሚታሰ በውን ወጪ እና ወለድ ጨምሮ) ሊያልፍ አይችልም።
9. በንዑስ አንቀጽ (8) ከተመለከተው የግል ተጠያቂነት በተጨማሪ ንብረቱን የያዘው ሰው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነው ያለበቂ ምክንያት ከሆነ በንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት የሚፈለገውን የገንዘብ መጠን 50 ፐርሰንት (ሃምሳ በመቶ) በተጨማሪ እንዲከፍል ይደረጋል።
10. በዚህ አንቀጽ መሠረት በይዞታው ሥር ያለውን ንብረትያስረከበ ወይም በታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ገንዘብከታክሱ ባለሥልጣን በተጠየቀው መሠረት ገቢ ያደረገ ማናቸውም ሰው ካስረከበው ንብረት ወይም ገቢ ካደረገው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የታክስ ግዴታውን ባልተወጣው ታክስ ከፋይ ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው ከሚፈለግበት ዕዳ ወይም ካለበት ግዴታ ነፃ ይሆናል፡፡

14. <u>በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ</u>

1. ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስ ተከፋይ ከሚሆንበት ቀን አንስቶ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሀብት ላይ የታክሱ ባለሥልጣን የቀደምትነት መብት ይኖረዋል።

2. ማናቸውም ሰው ታክስ የመክፈል ግዴታውን ባለመወጣት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በጥፋት ምክንያት ያልተከፈለውን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚደረገው እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል የታክሱ ዕዳ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የፅሑፍ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ለተመዘገበው ሰው ይሰጣል፡፡
3. በንዑስ አንቀጽ (2) የተገለፀው ማስጠንቀቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይማስጠንቀቂያው በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ለንብረት መዝጋቢው ባለሥልጣን የተመዘገበው ሰው ሀብት ባልተከፈለው የታክስ ዕዳ መጠን በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
4. በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ የሚፈለግበት ሰው ሃብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ መዝጋቢው ባለሥልጣን ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ ንብረቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን ትዕዛዝ እንደማናቸውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የመያዣ ሰነድ ይመዘግባል። ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ታክስ ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በሕግ እንደተሰጠ መያዣ ወይም እንደማናቸውም ሌላ ዕዳ ወይም ክፍያ ሆኖ ይቆጠራል።

15.<u>ታክስ ከፋዩ ስላለው ጥበቃ</u>

በዚህ ክፍል 4 መሠረት የተያዘ ማናቸውም ንብረት የሚያዘው፣ የሚጠበቀው፣ እና የሚመዘገበው በታክሱ ባለሥልጣን ብቻ ይሆናል፡፡ ማናቸውም ሌላ የመንግሥት አካል በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘውን ንብረት ማናቸውንም ሌላ ምክንያት መሠረት በማድረግ እንዲሰጠው ወይም እንዲተላለፍለት መጠየቅ አይችልም። የተያዘ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ በላይ የሆነው ገንዘብ ለንብረቱ ባለቤት ወዲያውኑ ይመለሳል፡፡

16.<u>የተረካቢ ግዴታ</u>

1. በዚህ አንቀጽ ውስጥ “ተረካቢ” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘን የታክስ ከፋዩን ሀብት በተመለከተ፣

ሀ/ የኩባንያ የንብረት አጣሪ ሆኖ የተሰየመ፣

ለ/ ከፍርድ ቤት ውጪ ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ ተረካቢ፣

ሐ/ በኪሣራ ውስጥ የሚገኝ ድርጅት ባለአደራ፣

መ/ መያዣ በይዞታው ሥር የሚገኝ፣

ሠ/ የሞተን ሰው ንብረት የሚያስተዳድር፣ ወይም

ረ/ በሕግ ችሎታ የሌለውን ሰው የንግድ ሥራ የሚያካሂድ፣

ማናቸውም ሰው ነው።

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ንብረት ተረካቢ ሆኖ የተሾመ ወይም ንብረት በይዞታው ሥር የተደረገ ተረካቢ ከተሾመበት ወይም ንብረቱ በይዞታው ሥር ከተደረገበት ከሁለቱ ቀደመው ቀን ጀምሮ በ14 ቀን ጊዜ ውስጥ የተሾመ ወይም በይዞታው ሥር ያለ መሆኑን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

3. የታክሱ ባለሥልጣን ንብረቱ በተረካቢው ይዞታ ሥር ያለ ሰው የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ለተረካቢው በጽሑፍ ያስታውቃል፡፡

4. ተረካቢው፣

ሀ/ በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በታክስ ባለሥልጣኑ የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ወይም ከማስታወቂያው በኋላ በስምምነት የተደረሰበትን ሌላ የገንዘብ መጠን ከንብረቱ ሽያጭ ላይ ቀንሶ ለብቻው ያስቀምጣል፡፡

ለ/ ተቀንሶ ለብቻው በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ልክ የተረከበው ንብረት ባለቤት ከሆነው ሰው ለሚፈለገው የታክስ ዕዳ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም ከታክስ ቀደምትነት ያለውን ማናቸውንም ዕዳ ሊከፍል ይችላል፡፡

5. ተረካቢው በንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰውን ታክስ በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ተቀንሶ ለብቻው እንዲቀመጥ የተደረገውን የገንዘብ መጠን በዚህ አንቀጽ ለተጠቀሰው ታክስ ካላዋለ ተቀንሶ ለብቻ በተቀመጠው ገንዘብ ልክ በግል ተጠያቂ ይሆናል።

17.<u>ለውጦችን ስለማስታወቅ</u>

ማናቸውም ታክስ ከፋይ፣

1. ስሙ፣ አድራሻው፣ የንግድ ሥራው ቦታ፣ አደረጃጀቱ፣ ወይም ታክስ የሚከፈልበትን ዋንኛው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የሚያከናውናቸውን ተግባራት ዓይነት፣

2. ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚከናወንበትን አድራሻ ወይም ስም፣ የቀየረ እንደሆነ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በ21 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማስታወቅ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ይግባኝ የሚቀርብበት ሥርዓት

### 18.የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በታክስ ባለሥልጣኑ ኃላፊ አቅራቢነት እንደአግባብነቱ በገቢዎች ሚኒስትር ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለሥልጣን ይሰየማሉ፡፡

### 19.የአቤቱታአጣሪ ኮሚቴው ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር

1. ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለታክሱ ባለሥልጣን ሆኖ፤
   ሀ/ በታክስ ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ፣ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የታክስ ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት፣
   ለ/ ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውንም የጽሑፍ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች መሰብሰብ፤
   ሐ/ በምርመራ ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ረገድ ቀርቦ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ከታክሱ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው የመጥራት፣
   መ/ የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው የታክስ ውሣኔ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ይህንን አዋጅ ጠብቆ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ ፣

   ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ከታክስ ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ካቀረበ ነው፡፡
3. የታክሱ ባለሥልጣን ኃላፊ የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ ሊያጸድቀው ወይም በውሳኔ ሀሳቡ ካልተስማማ ምክንያቱን በመግለጽ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል፡፡

   ቀዛዛቃ

**20.መቀጫን ስለማንሳት**[104]

1. የግብር ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚነሳው መቀጫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 መሠረት የሚታሰበውን ወለድ አይጨምርም።

**21.ይግባኝ**

1. በታክሱ ባለሥልጣን የተላለፈውን የተጨማሪ ታክስ ውሳኔ የሚቃወም ማናቸውም ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን ተጨማሪ ታክስ 50 በመቶ (ሃምሳ ፐርሰንት) ባለሥልጣኑ ዘንድ በማስያዝ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ የግብር ይግባኝ ጉባዔ ታክስ ከፋዩ በተጨማሪ የተወሰነበትን ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ በ30 (ሠላሣ) ቀን ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ተጨማሪ ታክስ ካልከፈለ ወይም ይግባኝ ካላቀረበ ጥፋተኛ ነው፡፡[105]
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ካልቀረበ በባለሥልጣኑ የተወሰነው ተጨማሪ ታክሰ ትክክለኛና የመጨረሻ ሆኖ ወዲያውኑ ተከፋይ ይሆናል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገቢ ግብር አዋጅ ስለይግባኝ የተደነገጉ አንቀፆች እንደአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰኑ ታክሶችን በሚመለከት ለሚቀርቡ ይግባኞች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

---

[104]በ15/8(2001) አ.611 አንቀፅ 2(3) ተሻሻለ፡፡

[105]በ15/8(2001) አ.611 አንቀፅ 2(4) መሰረት አዲስ የገባ ነው።

## 22.የማስረዳት ኃላፊነት

የተወሰነው ግብር በዝቷል ወይም የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው ውሳኔ ትክክል አይደለም በሚል በሚቀርብ ክርክር የማስረዳቱ ኃላፊነት የተወሰነውን ታክስ ወይም የባለሥልጣኑን ውሳኔ የሚቃወመው ሰው ይሆናል።

## ክፍል ስድስት

## አስተዳደራዊ ቅጣቶች

## 23.የታክስ ማስታወቂያን በጊዜ ባለማቅረብ ስለሚፈፀም ቅጣት

1. በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም ከተወሰነው በስተቀር፣ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቅ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ፣ ያልተከፈለውን ታክስ 5 በመቶ (አምስት ፐርሰንት) 25 በመቶ (የሃያ አምስት ፐርሰንት) እስኪሞላ ድረስ መቀጫ ይከፍላል።
2. የታክስ ማስታወቂያ መቅረብ ባለበት ወር ወይም የወሩ ክፍል በሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚከፍለው መቀጫ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) አይበልጥም።
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ያልተከፈለ ታክስ ነው የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክሱ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው።
4. በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው ቅጣት ቀጥሎ ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም፤

   ሀ/ ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) ፣

   ለ/ በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100 በመቶ (አንድ መቶ ፐርሰንት) ፡፡

## 24.ዘግይቶ በተከፈለ ታክስ ላይ ስለሚታሰብ ወለድ

ሀ/መከፈል በነበረበት ጊዜ ላልተከፈለ ታክስ፣ መከፈል ከነበረበት ቀን እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት።

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የሚከፈለው ወለድ የማስከፈያ ልክ ባለፈው የሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ ላይ 25 በመቶ (የሃያ አምስት ፐርሰንት) ታክሎበት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የወንጀል ቅጣቶች

25.በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ስለሚመሩበት ሥነ ሥርዓት

በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በመተላለፍ የሚፈፀሙ በመሆኑ ክሱ የሚመሠረተው ፣ የሚታየው እና ይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

26.ሕግን በመጣስ ታክስ ስላለመክፈል

የሰበሰበውን ታክስ ያላስታወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ማናቸውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም በዚህ አዋጅ ክፍል 6 መሠረት ከሚጣልበት መቀጫ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ5 ዓመት በማያንስ እሥራት ይቀጣል፡፡

27. የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ ስለማቅረብ

1. ማናቸውም ታክስ ከፋይ

ሀ/ ለታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ አንድን ነጥብ በተመለከተ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ ፣ ወይም

ለ/ ታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ ሊቀርብ ከሚገባው መግለጫ ውስጥ መግለጫውን አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያስቀረ እንደሆነ፣

የወንጀል ክስ ይመሠረትበታል።

2. የሐሰት መግለጫው የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ የተተወው ያለበቂ ምክንያት የሆነ እንደሆነ፣

ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር 1,000 በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር 10,000 በማያንስ እና ከብር 20,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

ለ/ አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ታክስ ከብር 1,000 የሚበልጥ ከሆነ ከብር 20,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

3. የሐሰት መግለጫ የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ እንዲካተት ያልተደረገው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ፣

ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር 1,000 በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር 50,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት ዓመት በማያንስ እና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ እሥራት

ለ/ አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ታክስ ከብር 1,000 የሚበልጥ ከሆነ ከብር 75,000 በማያንስ እና ከብር 200,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመትበማያንስ እና ከ15 ዓመት በማይበልጥ እሥራትይቀጣል፡፡

28. <u>የታከሱን ባለሥልጣን ሥራ ስለማሰናከል</u>

1. ማንኛውም ሰው፡

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ ያለን የታክስ ባለሥልጣን ሠራተኛ ተግባር ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ፣ ወይም

ለ/ የአዋጁን አፈፃፀም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ እንደሆነ፣ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ ሲፈረድበት ከብር 1,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና በሁለት ዓመት እሥራት ይቀጣል፡፡

2. ለንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም የሚከተሉት እና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ተግባሮች የታክሱን ባለሥልጣን ሥራ የማሰናከል ተግባራት ሆነው ይወሰዳሉ፤

ሀ/ የታክስ ከፋዩን ገቢ አስገኚ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሰነዶችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ለመመርመር የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቅ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ለ/ የታክሱ ባለሥልጣን ለጥያቄ እንዲቀርብ ሲያዝ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ሐ/ የታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ ቦታ ለመግባት ያለውን መብት መገደብ፡፡

29.**<u>ለውጥን ያለማስታወቅ</u>**

አንቀጽ 17 በሚያዘው መሠረት በሁኔታዎች ላይ የተደረጉ ለውጦችን ለታክሱ ባለሥልጣን ያላስታወቀ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፣

ሀ/ ጥፋቱ የተፈፀመው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከብር 10,000 በማያንስ የገንዘብ መቀሜ እና በአንድ ዓመት እሥራት፣

ለ/ በሌሎች ሁኔታዎች ከብር 5,000ሺ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና በ6ወር እሥራት

ይቀጣል፡፡

30.**<u>በታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኞች የሚፈፀሙ ጥፋቶች</u>**

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም በታክስ ባለሥልጣኑ የተቀጠረ ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ተቀጣሪ የነበረ፣

   ሀ/ በሕግ መሠረት ሊያገኘው ከሚገባ ክፍያ ወይም ሽልማት ውጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይምየተቀበለ፣ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ ወይም

   ለ/ ከታክስ በሚገኘው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይምከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም፣ ማድረግ የሚገባውን ከማድረግለ መታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በታክስ ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ፣ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ፣

   ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት በማያንስ ከ20 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የተቀጠረ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ በንግድ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፣
   ሀ/ ታክስን በማስፈጸም ረገድ ባለው ሥልጣን ወይም ግዴታ ምክንያት ያወቀውን የሌላ ሰው ማናቸውንም መረጃ ለማናቸውም ሌላ ሰው ወይም የዚያ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፣
   ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስን በማስፈጸም ረገድ ያለውን ሥልጣን ለመጠቀም ወይም የሥራ ግዴታውን ለመወጣት እንዲያስችል በታክስ ባለ ሥልጣኑ ዘንድ የሚገኘውን ማናቸውንም መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

   ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10,000 በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡
3. የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ ያለ በቂ ምክንያት ጉዳይን በማጓተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።[106]
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ፣
   ሀ/ ማናቸውንም ሰነድ ወይም መረጃ፣
      i. ለዚህ አዋጅ ወይም ለማናቸውም ገንዘብ ነክ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣
      ii. በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለዋናው ኦዲተር፣
      iii. መረጃ ለመለዋወጥ፣ ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር ባደረገችው ስምምነት መሠረት አግባብ ላላቸው የሌሎች አገሮች ባለሥልጣኖች፣

[106]በ15/8(2001) አ.611 አንቀፅ 2(5) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

iv. በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለሥነ ምግባርና ለፀረ ሙስና ኮሚሽን፣

v. ከዚህ በላይ ላልተገለፀ ለማናቸውም ሕግ አስፈጻሚ መ/ቤት ግዴታውን ለመፈፀም የሚያስችለው መረጃ እንዲሰጠው ከገቢዎች ሚኒስቴር በጽሑፍ ሲታዘዝ፡፡

ለ/ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ አንድን ሰው ለይተው የማይጠቅሱ መረጃዎችን ለማናቸውም በመንግሥት ገቢ ሥራ ላይ ለሚያገለግል እና ለስታትስቲክስ መ/ቤትሠራተኛ፣

ከመስጠት አያግደውም፡፡

31.<u>ሳይፈቀድ ታክስ ስለመሰብሰብ</u>

ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ሳይፈቀድለት ታክስ ወይም እንደታክስ የሚታይ ሌላ ክፍያ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ ወንጀል የፈፀመ ሆኖ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50,000 የማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

32.<u>መርዳት ወይም ማበረታታት</u>

ማናቸውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያነሳሳ፣ ወይም በሚስጥር የተባበረ እንደሆነ እንደዋንኛው ጥፋተኛ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስጥፋት ይፈጽማል። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የፈጸመ ሰው፤ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ዕርዳታውን ወይም ትብብሩን ለሰጠበት ጥፋት ከተወሰነው የገንዘብ እና የእሥራት ቅጣት ባልበለጠ በገንዘብ እና በእሥራት ይቀጣል።

33.<u>በድርጅቶች የሚፈጸም ጥፋት</u>

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አንድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈጸመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማናቸውም ሰው በድርጅቱ የተፈጸመውን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ማናቸውም ድርጅት በዚህአዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ወይም አዋጁ እንደ ታክስ የሚቆጥረውን ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ገቢ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ጥፋቱ ከተፈጸመበት ጊዜ አስቀድሞ በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ሥራ

አስኪያጅ የነበሩ ሰዎች ከድርጅቱ እና ከሌላው ሰው ጋር በአንድነትና በተናጠል የታክሱ ባለሥልጣን ለሚፈልገው ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች ተጠያቂ ይሆናሉ።

3. በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገጉት፣

ሀ/ ጥፋቱ የተፈጸመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ፣

ለ/ አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን፣ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግለሰቡ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ፣ ተፈጻሚ አይሆኑበትም፡፡

4. ለንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) አፈጻጸም "ሥራ አስኪያጅ" ማለት፣

ሀ/ የሽርክና ማኅበርን በሚመለከት የሽርክናው ማኅበር አባል ወይም የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም ከሁለቱ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ለ/ ኩባንያን በሚመለከት የኩባንያው የሥራ መሪ፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከእነዚህ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ሐ/ የሰዎችን ኅብረት በሚመለከት የኅብረቱ ሥራ አስከያጅ ወይም በዚሁ ኃላፊነት እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ነው፡፡

## 34.<u>በተረካቢዎች የሚፈጸም ጥፋት</u>

1. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (4) በተደነገገው መሠረት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ብር 5,000 የገንዘብ መቀጫ እና በአንድ ዓመት እሥራት ይቀጣል፡፡

2. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 16(4) ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ለታክስ ክፍያ የሚውለውን ገንዘብ ለይቶ ባለማስቀመጡ ምክንያት በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከገንዘብና እሥራት በተጨማሪ ለይቶ ያላስቀመጠውን የገንዘብ መጠን ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ እንዲያደርግ ሊያዝ ይችላል።

35.**የጥፋተኞችን ስም በጋዜጣ እትሞ ስለማውጣት**

1. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ አንቀጽ25-34 የተደነገጉትን የወንጀል ጥፋቶች በመፈጸም የተፈረደባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር በየጊዜው በዕለታዊ ጋዜጦች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት ታትሞ የሚወጣው ዝርዝር፤

ሀ/ የድርጅቱን ወይም የግለሰቡን ስም እና አድራሻ፣

ለ/ ባለሥልኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን የወንጀሉን አፈጻጸም ዝርዝር፣

ሐ/ ጥፋቱ የተፈጸመበትን የግብር ዘመን ወይም ዘመኖች፣

መ/ ሳይከፈል የቀረውን ግብር መጠን፣

ሠ/ በተጨማሪ እንዲከፍል የተወሰነበት ግብር ካለ ይህንኑ፤

የሚገልጽ ይሆናል፡፡

**ክፍል ስምንት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

36.**የመተባበር ግዴታ**

1. ይህንን አዋጅ በስራ ላይ ለማዋል የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት ባለሰልጣኖች እና ወኪሎቻቸው በተጨሪም ድርጅቶች፡ የቀበሌ መስተዳድርች እና ማኅበራት ሁሉ ከታክሱ ባለሥልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።
2. ሀ/ በይግባኝ ቀጠሮ ላይ ካልሆነ ወይም የታክሱ ባለሥልጣን የተራዘመ የታክስ መክፈያ ጊዜ ካልስጠ በስተቀር፣ ታክስ ከፋዩየሚፈለግበትን ግብር በወቅቱ የከፈለ ስለመሆኑ ወይም አዲስ ታክስ ከፋይን በሚመለከት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረበ በስተቀር ፈቃድ ሰጪሚኒስቴር፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የፌዴራል ወይም የክልል መሥሪያ ቤት አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠት አይችልም።

ለ/ የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ያለበትን ግዴታ ስለመፈጸሙ የምስክር ወረቀት የማይሰጥ ሲሆንያለውን ምክንያት በመዘርክር ለጠያቂው ይሰጣል፡፡

ሐ/ የምስክር ወረቀት አልሰጥም በማለቱ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ በመሰረዙ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሰጣቸው ምክንያቶች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ኮሜቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

37.<u>የሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች በተጨማሪ ሚኒስትሩ ለኢኮኖሚ ለማህበራዊ ወይም ለአስተዳደር ምክንያቶች ወይም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር286/1994 አንቀጽ 42(ለ) በተዘረዘሩት ምክንያቶች በዚህ አዋጅ ከተጣለው ታክስ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ የማድረግ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

38.<u>መመሪያ የማወጣት ስልጣን</u>

የገቢዎች ሚኒስትር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፡፡

39.<u>ስለመሻር</u>

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ የሽያጭ እና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 68/1985 (እንደተሸሻለ) ተሰርዟል፡፡

40.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ሳይከፈል የቀረ የሽያጭ ታክስ በሽያጭና ኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

41.<u>አዋጁ የሚፀና በት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ 22 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 22 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክፕሬዚዳንት**

**ደንብ ቁጥር 139/1999**

**በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታየወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5፣በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር285/1994 አንቀጽ 64 እና በገቢ ግብር አዋጅ286/1994 እንቀጽ 117 መሠረት ይህንን ደንብአውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤትደንብ ቁጥር 139/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነበስተቀርበዚህ ደንብ ውስጥ ፣

   1. "የሽያጭ መመዝገቢያ" መሣሪያ ማለት የጥሬ ገንዘብመመዝገቢያመሣሪያ ወይምየሽያጭ ነቁጣ መሣሪያነው፣
   2. "የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ" ማለት በሽያጭመደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የሸቀጦችንወይም የአገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብናለማንበብ ብቻየሚቻል ማስታወሻን የሚያከማችበኤሌክትሮኒክ ዘዴፕሮግራም የሚደረግ ቺፕ የተገጠመበት በሰርክዩት የተጋገረ ፕሮግራምየሚጠቀም መሣሪያ ነው፤
   3. "ደረሰኝ" ማለት የጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ደረሰኝሲሆን፣ የዱቤ ሽያጭኢንቮይስንና ያለክፍያየሚሰጥ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ማስተላለፊያደረሰኝን ይጨምራል፤
   4. "በሰርክዩት የተጋገረ ፕሮግራም" ማለት በማይቀያየር ማስታወሻ ላይ የሚጫን በትክክልተለይቶ የተቀመጠን ሥራ ለማደራጀት እንዲያገለግል የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው፤
   5. "የማይቀያየር ማስታወሻ" ማለት ኃይል ቢቋረጥም ተይዞ የቆየው መረጃ ተጠብቆ የሚቆይበት ማስታወሻ ነው፤

6. "የሽያጭ ነቁጣ" መሣሪያ ማለት የጥሬ ገንዘብመመዝገቢያ መሣሪያን የሚተካ ኮምፒውተራይዝድ የሆነ መሣሪያ ሲሆን፣ የደንበኞችን ትዕዛዝ፣ የትዕዛዙን አፈፃፀም ሂደትና የዴቢትናየክሬዲት ካርድ ሂሣብን የመመዝገብና የመከታተል፣ በክምችት ያለን ዕቃ የመቆጣጠርና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችልተጨማሪ አቅም ያለው መሣሪያ ነው፤
7. "ታክስ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስንና የገቢ ግብርን ያጠቃልላል፤
8. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገቢዎች ሚኒስቴርእና ሚኒስትር ነው፤[107]
9. "ባለስልጣን" ማለት የፌደራል አገር ዉስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነው፤
10. "የታክስ ባለሥልጣን" ማለት ባለሥልጣኑ ወይምበባለሥልጣኑ የሥልጣንውክልና የተሰጠውየክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የግብርሰብሳቢ መሥሪያ ቤት፤
11. "አቅራቢ" ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ለታክስ ከፋዮች በሽያጭ የሚያቀርብሰው ነው፤
12. «ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግየሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።
13. "ፊሲካል ፕሪንተር" ማለት የፊሲካል ማስታወሻ ያለው ሆኖ በሥራ ላይያለውን የውስጥመገናኛ በመጠቀም ብቻ በማናቸውም የአሠራር ፕሮግራም ሊያገለግል የሚችል ፕሪንተር ነው፤

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የግብር ከፋይ ግዴታዎች</u>

### 3. <u>በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የመጠቀም ግዴታ</u>

በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ ዝርዝራቸው የሚወሰን ታክስ ከፋዮች በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረትዕውቅና የተሰጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያመሣሪያዎች በመጠቀም በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 መሠረት የሽያጭ ደረሰኞችን አዘጋጅተው የማውጣት ግዴታ አለባቸው፡፡

[107] በ25/8(2011) አ.1097 አንቀጽ 9(4) መሰረትየገቢዎችሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

## 4. ደረሰኞች ሊይዟቸው የሚገቡ መረጃዎች

1. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የተዘጋጀ የሽያጭ ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

   ሀ/ በታክስ ባለሥልጣኑናየንግድ ሥራ ፈቃድበሰጠው አካል የተመዘገበውን የታክስ ከፋዩን ስም፤

   ለ/ የንግዱን ስም፤

   ሐ/ የታክስ ከፋዩን መለያ ቀጥር፤

   መ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ሥሪትና ሞዴል ዕውቅና ሰርቲፊኬት፤

   ሠ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን የምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፤

   ረ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ጥቅምላይ የዋለበትን አድራሻ፤

   ሰ/ የደረሰኙን ቁጥር፤

   ሸ/ ሽያጩ የተከናወነበት ቀን፤

   ቀ/ የተሸጠውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዓይነትና ብዛት፤

   በ/ የሽያጩን ዋጋ፤

   ተ/ ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክበተሰጠው ፈቃድመሠረት ክፍያዎችንበውጭ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ የሚቀበል ከሆነ ክፍያውን የተቀበለበትን የውጭምንዛሪ ዓይነት፣ ክፍያው በክሬዲት ወይምበዴቢት ካርድ የተፈፀመ ከሆነ የክሬዲትወይም የዴቢት ካርዱን ያወጣውን ኩባንያየንግድ ስም፤

   ቸ/ ሚኒስቴሩ በሚያውጣው መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች መረጃዎች፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(በ) መሠረትየሚጠቀሰው የሽያጭ ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸውንና የማይከፈልባቸውን ሽያጮች ጠቅላላ ድምርለያይቶ ማሳየት አለበት፡፡

3. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚጠቀም የንግድድርጅት፣ ገዥው ለተጨማሪ እሴት ታክስየተመዘገበ ታክስ ከፋይ ካልሆነ በስተቀር፣በመሣሪያው ተዘጋጅቶ በሚወጣው ደረሰኝ ላይየገዥውን ስም፣ የንግድ ዓይነት፣ አድራሻናየታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን የማሳየት ግዴታየለበትም፤ መሣሪያው እነዚህን መረጃዎችለማሳየት የማይችል ከሆነም በታክስ ባለሥልጣኑበተሰጠ

ፈቃድመሠረት የታተመ ደረሰኝለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ለሆኑገዥዎች የመስጠት ግዴታይኖርበታል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተውመሠረት በእጅ የተዘጋጀ ደረሰኝ በሚሰጥበት ጊዜሽያጩ በድጋሚ የሚመዘገብበት ሁኔታ እንዳይፈጠር በእጅ የተዘጋጀው ደረሰኝ ቅጂ በመሣሪያውከተዘጋጀው ደረሰኝ ጋር ተያይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

5. ***<u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሁኔታዎች</u>***

1. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚጠቀም ታክስከፋይ፤

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 16 መሠረት የሚሰጠውን በመሣሪያው ለመጠቀም የሚያስችልፈቃድ በቅድሚያ ማግኘት አለበት፤

ለ/ መሣሪያውን ጥቅም ላይ ሊያውል የሚችለው በመሣሪያው ለመጠቀም በሚያስችለው ፈቃድ ላይ ለተመለከተው የንግድሥራ ብቻ ነው፤

ሐ/ ለታክስ ባለሥልጣኑ አስቀድሞ በፅሑፍሳያስታውቅ የንግድ ስሙን መለወጥ ወይም በመሣሪያው ላይ የጥገና፣ አቅምየማሳደግ፣ ለውጥ የማድረግ፣ የማሻሻልወይም ወቅታዊ እንዲሆን የማድረግ ሥራማከናወን ወይም በማናቸውም ምክንያትከቦታው ማንቀሳቀስአይችልም፤

መ/ በመሣሪያው ላይ የጥገና፣ አቅም የማሳደግ፣ ለውጥ የማድረግ፣ የማሻሻል ወይም ወቅታዊ እንዲሆን የማድረግ ሥራከተከናወነ በኋላ ይህንኑ ሥራ ካከናወነውሰው ጋር በመሆን የተዘጋጀ መግለጫለታክስ ባለሥልጣኑ ያቀርባል፤

ሠ/ ማናቸውንም የሂሣብ ሰነዶች የታክሱባለሥልጣን ታክሱን ለመወሰንና ለመሰብሰብ በሕግ እስከተፈቀደለት ጊዜ ድረስጠብቆ ማቆየት ይኖርበታል፤

ረ/ መሣሪያውን በእርጅና ወይም በሽያጭ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን ለማድረግ በቅድሚያ ለታክስ ባለሥልጣኑ ማመልከትና ፈቃድ ማግኘት፣

ሰ/ መሣሪያውን በመጠቀም የተከናወነውን የሺያጭ ተግባር የሚያሳይ መረጃ ለታክስ ባለሥልጣን ማስተላለፍ የሚችል ተርሚናል በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ላይ መገጠም አለበት፡፡

2. ታክስ ከፋዩ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውበጥገና ላይ ባለበት ጊዜ በታክስ ባለሥልጣኑፈቃድ በታተመ የሽያጭ ደረሰኝ ሊጠቀም ይችላል፡፡
3. የሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን፤
   ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(መ) የቀረበለትን መግለጫ መነሻ በማድረግ መሣሪያው አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት መሣሪያውን መመርመርና መገምገም አለበት፤
   ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) የተጠቀሰው ማመልከቻ ሲቀርብለት መሣሪያው አገልግሎት ላይ እስከነበረበት የመጨረሽ ቀን ድረስ የተመዘገቡ የሽያጭ መረጃዎች በተገቢው አኳኋን መያዛቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምርመራ ማድረግ አለበት፡፡
4. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን የሚሰጠው ፈቃድ መሣያሪውከአገልግሎት ውጪ በሆነበት ቀን፡-
   ሀ/ የነበረውን የቀጣሪውን ንባብ፤
   ለ/ የተከማቸውን አጠቃላይ ሽያጭ ድምር፣ እና
   ሐ/ በመጨረሻ ተዘጋጅቶ የወጣውን ደረሰኝቁጥር ማሳየት አለበት፡፡
5. አግባብ ያለው የታክስ ባለሥልጣን በደረሰኝራስጌ ሊሰፍር የሚገባው ፅሑፍ እስከሚዘጋጅድረስ ታክስ ከፋዩ ከ30 ቀናት ላልበለጠ ጊዜበሌላ ዓይነት ደረሰኝ እንዲጠቀም ካልፈቀደበስተቀር፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያንበዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተዘረዘሩትን መረጃዎችያልያዘ ለደንበኞች የሚሰጥ ደረሰኝ ለማዘጋጀትተግባር እንዲውል ማድረግ አይቻልም፡፡
6. ለደንበኞች በሚሰጠው ደረሰኝና ለኦዲት ጆርናል ሲባል በሚዘጋጀው ጥቅልወረቀት ላይ የሚሰፍረው የግብይት ቁጥር ተከታታይነት ተጠብቆእንዲቀይ ለማድረግ የቁጥር አሰጣጡ ሥርዓትወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ሰርክዩትእንዲታወክ ወይም እንዲነካካ መደረግ የለበትም፡፡

6. <u>**የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ሁኔታዎች**</u>

በጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚጠቀም ታክስከፋይ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተደነገገውን ከማሟላትበተጨማሪ፤

1. ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ ተፈላጊዎቹን ረድፎች የያዘ በተገቢው አኳኋን የተመዘገበ የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ የሽያጭመዝገብ ሊኖረው ይገባል፤

2. በሁለቱም የጥቅል ወረቀቶች መጠቅለያ ወይምበተመሳሳይ አካላት ላይ የደረሰኝ ወረቀትያልገባበት የሽያጭ ገቢ መመዝገቢያ መሣሪያጥቅም ላይ ማዋል የለበትም፤
3. ለደንበኛ በሚሰጠውና በኦዲት ጆርናል ደረሰኝወይም በተመሳሳይ ሰነዶች ላይየሚታተመውፅሑፍ ሊነበብ የሚችል እንዲሆንና በታክሱባለሥልጣንበሚወሰነው ተጠብቆእንዲቆይ ማድረግ አለበት፤
4. የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ ንዑስ የሽያጭ መዝገብ ሁልጊዜም የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያው በሚገኝበት ቦታ እንዲቀመጥና ሥልጣንየተሰጣቸው የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኞችለማመሳከር በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ እንዲያዩትማድረግ አለበት፡፡

7. <u>የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ አጠቃቀም ሁኔታዎች</u>

1. የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያን የሚጠቀም ታክስ ከፋይበዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተደነገገውን ከማሟላትበተጨማሪ፣ እንዲጠቀምባቸው የተፈቀዱለትሰነዶች ተከታታይ ቁጥር ከመጠናቀቁ ከአንድወር በፊት በቀጣይ ጊዜያትየሚጠቀምባቸውንሰነዶች ተከታታይ ቁጥር ከታክሱ ባሥልጣንማስፈቀድ አለበት፡፡
2. ማናቸውም የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ ኤሌክትሮኒክ ጆርናል ሳይኖረው ሥራ ላይ ሊዉልአይችልም፡፡
3. የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ ግብይቶችን በውጭ ምንዛሪ እንዲያከናውንበኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠውከሆነ፣ በውጭምንዛሪ ያከናወናቸውን ግብይቶች የሚያሳይ መረጃዎችን በተጠየቀ ጊዜለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ማናቸውም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ፊስካልፕሪንተር በመጠቀም ደረሰኝ ማውጣት አለበት፡፡

8. <u>የኮምፒዩተር መረጃ መረብ አጠቃቀም ሁኔታዎች</u>

ማንኛውም ታክስ ከፋይ የንግድ ድርጅቱ የኮምፒዩተርመረጃ መረብን የሚጠቀምከሆነ፡-

1. የገዛውን ሶፍትዌር ዓይነት፣ የአምራች ኩባንያውን ስም፣ የፈቃድ ሁኔታ ፣ለስንት ሽያጭነቁጣዎች እስከመቼ የሚያገለግል መሆኑንና የማደሻውን ወቅት ማስመዝገብ፤
2. ዳታቤዙ የሚስተናገድበትን ሰርቨር ሞዴል፣የሀርድ ዲስክ ቁጥርና የመረብካርድ ቁጥርማስመዝገብ አለበት፡፡

**ክፍል ሦስት**

**የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ተፈላጊ ባህሪያት**

9. **የወል ባህሪያት**

ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ፣

1. የተመዘገበውን ቁጥር ማስተካከል በማይቻልበትአኳኋን ቢያንስ አሥራ ሁለት አኃዞች የሚደርስየተከማቸ ጠቅላላ የሽያጭ መጠንን መያዝ የሚችል፤
2. በተመዘገበው መረጃ ላይ ለውጥ ሊደረግበት፣ ወደ ሌሎች አሠራሮች ሊለወጥ ወይም የሽያጭእንቅስቃሴዎች እንዳይመዘገቡ ለማድረግበሚያስችል አኳኋን ሊቀየር የማይችል፣
3. በየዕለቱ የተከናወነውን ጠቅላላ ሽያጭና የተከማቸዉን ጠቅላላ ድምር የሚያሳይ ሪፖርትማውጣት የሚያስችል፣
4. የማይቀያየር ማስታወሻ ያለው ወይም በውስጡየተከማቸው መረጃ ቢጠፋ የጠፋውን መረጃማግኘት የሚያስችል ደጋፊ ሥርዓት ያለው፣
5. የሽያጭ ዋጋ ቅናሽ፣ ተመላሽ ሂሣብና የመሳሰሉትን የሚያሳይና አከማችቶሲይዝ የሚችል፣
6. የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸውንና የማይከፈልባቸውን የሽያጭ እንቅስቃሴዎች በግልጽ ለይቶ የሚያሳይና የእነዚህኑ የተጠቃለለአጭር መግለጫ ማውጣት የሚያስችል፣
7. የተከማቸውን መረጃ የታክስ ባለሥልጣኑ ታክሱን ለመወሰንና ለመሰብሰብ በሕግ እስከተፈቀደለት ጊዜ ድረስ ተጠብቆ እንዲቆይ ማድረግ የሚያስችል፣
8. የኢንተርኔት ማስተላለፊያ ፕሮቶኮል ሶፍትዌር (ቲ.ሲ.ፒ.አይ.ፒ) ማስተናገድ የሚችል፣
9. ለታክስ ባለሥልጣን መ/ቤት የሽያጭ መረጃን ማስተላለፍ የሚችል የኢ-ሞባይል ቴክኖሎ ጂመሣሪያ የተገጠመለት መሆን አለበት፣

10.<u>የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጨማሪ ባህሪያት</u>

ማንኛውም የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ በዚህደንብ አንቀጽ 9 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፡-

1. ለታክስ ኦዲት የሚያገለግል የኦዲት ጆርናልጥቅል ወረቀት የሚይዝመጠቅለያና ለእያንዳንዱየሽያጭ ዓይነት የሚያገለግልና ተከታታይ ቁጥርያለው ለደንበኛው የሚሰጥ የደረሰኝ ቅጂ የሚይዝሁለተኛ ጥቅል ወረቀት ማሽከርከር የሚችልወይም ተመሳሳይ አቅም ያለው፣
2. ከሁለቱ መጠቅለያዎች አንዱ ብቻ እንዲሰራበተደረገበት ሁኔታ መሣሪያውን ማንቀሳቀስእንዳይቻል የሚያደርግ የመቆጣጠሪያ ሥርዓትየተገጠመለት፣ እና
3. የዋጋ ቅናሽና ተመላሽ ሂሣብ የመሳሰሉትን መረጃዎች ለደንበኛው በሚሰጠው ደረሰኝና በኦዲትጆርናሉ ወይም ተመሳሳይ በሆነው ሰነድ ላይወዲያውኑእንዲታተሙ የሚያደርግ፣ መሆን አለበት፡፡

11.<u>የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ተጨማሪ ባህርያት</u>

ማንኛውም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ በዚህ ደንብአንቀጽ 9 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፣

1. የተከናወነውን ማናቸውንም የሽያጭ እንቅስቃሴወዲያውኑና በተሟላ ሁኔታመሣሪያው በተገናኘበት ሰርቨር ውስጥ መመዝገብ የሚችል፣
2. በታክስ ከፋዩ የሚቀርበውን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 መሠረት የሚሰጥ የሽያጭ ደረሰኝማጠቃለያን የታክስ ባለሥልጣኑ ከመሣሪያውበማየት ትክክለኛነቱን ለማመሳከር የሚያስችል፣ እና
3. የታክስ ባለሥልጣኑ የተሰረዙና የተከናወኑሽያጮችን ለመለየትና በታክስ ከፋዩ የሂሣብመዝገብ ላይ ያልተመዘገቡ ሌሎች መረጃዎችንማየት እንዲችል የመከታተያና የማረጋገጫዘዴዎች ያሉት፣
4. ታክስ ከፋዩ ግብይቶችን በውጭ ምንዛሪእንዲያከናውን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክየተፈቀደለት ከሆነ፣ በውጭ ምንዛሪ በጥሬገንዘብ የተቀበለውን የገንዘብ ዓይነት፣ ክፍያውበዴቢት ወይም በክሬዲት ካርድ የተፈፀመከሆነ፣ የክሬዲት ወይም የዴቢት ካርዱንያወጣውን ኩባንያ የንግድ ስም ማሳየትየሚችል መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ለሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ዕውቅና ስለመስጠትና ስለመመዝገብ

### 12.ስለዕውቅና ማመልከቻ

1. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አቅራቢ.ማንኛውንም መሣሪያ ለሽያጭ ማቅረብ ከመጀመሩ በፊት የመሳሪያው ሥሪትና ሞዴልዕውቅና እንዲያገኝ ለባለሥልጣኑ ማመልከትአለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረትየሚቀርብ ማመልከቻ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ፎርም ላይ ተሞልቶ፣
   ሀ/ በዚህ ደንብ ከአንቀጽ 9 እስከ 11 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተፈላጊየሆኑትን የመሣሪያውን ባህሪያት ከሚያሳዩ ሰነዶች፣ እና
   ለ/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የአመልካቹን የንግድ ሁኔታ በሚመለከት ከሚጠየቁ አግባብ ካላቸው ሌሎችሰነዶች፣ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

### 13.ማመልከቻዎችን ስለመመርመር

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 መሠረት የቀረበየሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያሥሪትና ሞዴልዕውቅና ማመልከቻ ባለሥልጣኑ ባቋቋመውየዕውቅና ቦርድ ይመረመራል፡፡
2. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በዚህ ደንብ ከአንቀጽ 9 እስከ 11 የተዘረዘሩትን አግባብነትያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት የሚያሟላ መሆኑንለማረጋገጥ አመልካቹ የመሣሪያውን ፍተሻናየፕሮግራሙን ሙከራ የቦርዱ አባላት በተገኙበት ማከናወን አለበት፡፡
3. ቦርዱ ማመልከቻውና ደጋፊ ሰነዶች ተሟልተውከቀረቡለት ቀን አንስቶ በአምስት የሥራ ቀናትውስጥ ምርመራውን በማጠናቀቅ የውሳኔሀሳቡንለሚመለከተው የባለሥልጣኑ ኃላፊማቅረብ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰው የዕውቅና ቦርድአባላት በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቅራቢነት በሚኒስትሩ ይሰየማሉ።

14.**<u>የዕውቅና ሰርተፊኬት</u>**

1. ባለሥልጣኑ የሺያጭ መመዝገቢያ መሣሪያበዚህ ደንብ ከአንቀጽ 9 እስከ 11የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት ማሟላቱ በዕውቅና ሰጭ ቦርድ ሲረጋገጥ ለመሳሪያው ስሪትና ሞዴል የዕውቅና ሰርቲፊኬትይሰጣል።
2. ዕውቅና የተሰጣቸው የሽያጭ መመዝገቢያመሳሪያዎች ስሪትና ሞዴል ዝርዝር በባለስልጣኑ ድረ ገጽ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

15.**<u>ዕውቅናን ስለመሰረዝ</u>**

ለሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ስሪትና ሞዴልየተሰጠ ዕውቅና ከሚከተሉትምክንያቶች ባንዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

1. ዕውቅና የተሰጠው ሀሰተኛ ማስረጃ በመቅረቡሆኖ ከተገኘ፣
2. ባለሥልጣኑ እንዲያውቀው ሳይደረግ በመሳሪያው ስሪትና ሞዴል ላይ ለውጥ ወይምማሻሻያ ከተደረገ፣
3. መሳሪያው በስራ ላይ ሲውል በዚህ ደንብ ከአንቀጽ 9 እስከ 11 የተዘረዘሩትን አግባብነትያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት ሙሉ ለሙሉ አሟልቶ አለመገኘቱሲረጋገጥ፣ ወይም
4. የዕውቅና ሰርቲፊኬት የተሰጠው ሰው የዚህንደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣

16.**<u>ምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ</u>**

1. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አቅራቢ ለመሣሪያው ተጠቃሚ ሽያጭ ባከናወነ በ5 ቀናትጊዜ ውስጥ መሣሪያውን በሚመለከተው ታክስባለሥልጣን ዘንድበተጠቃሚው ስም ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ለማስመዝገብየሚቀርበው መረጃ የሚከተሉትን ማካተትአለበት፤

   ሀ/ የተጠቃሚውን የታክስ ከፋይ መለያቁጥር፣

   ለ/ የተጠቃሚውን የተጨማሪ እሴት ታክስምዝገባ ቁጥር፣

   ሐ/ የመሳሪያውን ስሪት፣ ሞዴልና ተከታታይቁጥር፣

   መ/ የመሳሪያውን ቆጣሪ ንባብና ንባቡ የተካሄደበትን ቀን።
3. የታክስ ባለስሥልጣኑ ምዝገባውን እንዳከናወነበተጠቃሚው ስም የተዘጋጀ በመሣሪያውለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ መሣሪያውንላስመዘገበው አቅራቢ ይሰጣል፡፡

4. የመሣሪያው አቅራቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (3) መሠረት የተሰጠውን ፈቃድ ለመሣሪያው ተጠቃሚ ያስረክባል።
5. ዕውቅና የተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያመሣሪያበቀጥታ ወደ አገር ውስጥ ያስገባውተጠቃሚው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2)የተመለከቱትን መረጃዎች ለባለሥልጣኑአቅርቦ መሣሪያውን ማስመዝገብና በመሣሪያውለመጠቀም የሚያስችለውን ፈቃድ ከባለሥልጣኑ መውሰድ አለበት፡፡
6. በመሣሪያው ተጠቃሚ የሆነ ታክስ ከፋይየተሰጠውንበመሣሪያው ለመጠቀም የሚያስችልፈቃድ ደንበኞቹ ሊያዩት በሚችሉት አኳኋንበመሳሪያው ላይመለጠፍ አለበት፡፡ ማመሳከርእንዲቻልም የመሣሪያው ተከታታይ ቁጥርጐልቶ በሚታይ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ መለጠፍይኖርበታል።

17.<u>የተሸጡ መሳሪያዎች ዝርዝር</u>

1. የመሳሪያዎቹ አቅራቢ ለተጠቃሚዎች የሸጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያመሣሪያዎች ዝርዝር የያዘ መግለጫ እያንዳንዱ ወር በተጠናቀቀበ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለሚመለከተው የታክስባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረትየሚቀርበው መግለጫ ስለእያንዳንዱ የሽያጭመመዝገቢያ መሣሪያ የሚከተሉትን መረጃዎችሊይዝ ይገባል፣

   ሀ/ የመሣሪያውን ስሪትና ምዴል፣

   ለ/ የመሣሪያውን ስሪትና ሞዴል ዕውቅናሰርቲፊኬት ቁጥር፣

   ሐ/ የመሳሪያዉን ምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፣

   መ/ የተሸጠበትን ቀን፣

   ሠ/ የምዝገባውን ቀን፣

   ረ/ የተጠቃሚውን የታክስ ከፋይ መለያቁጥርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣

   ሰ/ መሣሪያው ጥቅም ላይ የሚውልበትንየንግድ ሥራ ዓይነትና አድራሻ፣

   ሸ/ የመሣሪያውን ቆጣሪ ንባብና ንባቡ የተወሰደበትን ቀን፣ እና

   ቀ/ የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያን በሚመለከት አገልግሎት ላይ የዋለውን ፕሮግራምና በፕሮግራሙ ላይ የተደረገውን ማስተካከያ፡፡

3. የታክሱ ባለሥልጣን መግለጫው እንደደረሰውበራሱ ዘንድ ከሚገኘው የምዝገባ መረጃ ጋርዝርዝሩን ማመሳከር አለበት፡፡

18.**<u>የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያን ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች መጠቀምን ስለመፍቀድ</u>**

1. የታክሱ ባለሥልጣን የተለያዩ የንግድ ሥራዓይነቶችን የሽያጭ መረጃማከማቸትየሚያስችል አቅም ያለው የጥሬ ገንዘብመመዝገቢያ መሣሪያ ለተለያዩ የንግድ ሥራዓይነቶች የሽያጭ ደረሰኝ አዘጋጅቶ እንዲያወጣሊፈቅድ ይችላል፣ ሆኖም በተለያዩት የንግድሥራዎች የሚከናወነው ሽያጭ መሣሪያውበሚጠቀምበት ጥቅል ወረቀት ላይ በኮድወይም በምልክት ሳይሆን በቃላት በግልጽተለይቶ የሚጻፍ መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውፈቃድ እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻ በመሣሪያው አቅራቢ ወይም ተጠቃሚ አማካይነትለታክስ ባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

19.**<u>ከታክስና ቀረጥ ነፃ ስለመሆን</u>**

ታክስ ከፋዮች እንዲጠቀሙባቸው ወደአገር ውስጥየሚገቡ ዕውቅና የተሰጣቸውየሽያጭ መመዝገቢያመሣሪያዎች በገቢ ዕቃዎች ላይ ከሚጠየቅ ማናቸውም ታክስና ቀረጥ ነፃ ሆነው ይገባሉ፡፡

20.**<u>ቅጣት</u>**

ይህን ደንብ በመተላለፍ በሽያጭ መመዝገቢያመሣሪያ ሳይጠቀም የተገኘ ወይም በመሣሪያውተጠቅሞ የማጭበርበር ተርገባር የፈፀመ ታክስከፋይ አግባብ ባለው የታክስ ሕግ በተደነገገውመሠረት በወንጀል ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የንግድ ፈቃዱ እንዲሠረዝ ይደረጋል፡፡

21.**<u>የመሸጋሪያ ድንጋጌ</u>**

ታክስ ከፋዮች፣ ይህ ደንብ ከፀና በኋላ ዕውቅናየተሰጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችከገበያ ለማገኘት የሚያስፈልገውን ጊዜ ከግምትውስጥ በማስገባት በሚኒስቴሩ ለሚወሰንየመሸጋገሪያ ጊዜ፣ በታክሱ ባለሥልጣን ዘንድባስመዘገቡት የሽያጭ ደረሰኝ መጠቀም ይችላሉ፡፡

22. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስትሩ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸምየሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣይችላል፡፡

23. <u>ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን</u>

የታክስ ባለሥልጣኑ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችበታክስ ከፋዮች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል።

24. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 11 ቀን 1999 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 767/2004 ዓ.ም

## የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ

የአገር ውስጥ የጫት ፍጆታ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሄዱ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ የሚያግዝ የታክስ ስርዓት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በጫት ላይ የሚከፈለውን ታክስ አሰባሰብ ፍትሐዊነት ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና (11) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭርርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 767/2004"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ታክስ" ማለት በኢትዮጵያ በሚካሄድ የጫት ግብይት ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ ነው፤
   2. "ታክስ ከፋይ" ማለት የጫት ኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ነው፤
   3. "የታክስ ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፤
   4. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ቢሆንም ባይሆንም ማንኛውም ድርጅት ነው፤
   5. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
   6. "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[108] ነው፡፡

3. **ታክስ የመክፈል ግዴታ**

   1. ጫትን በይዞታው ስር በማድረግ፣ በማጓጓዝ ወይም በማንኛውም መንገድ ለሽያጭ የሚያቀርብ ሰው በዚህ አዋጅ የተወሰነውን ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

[108] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

4. <u>የታክሱ ማስከፈያ ልክ</u>

በአገር ውስጥ ተመርቶ በመነሻው ክልል ጥቅም ላይ የሚውልና ወደ ሌላ ክልል የሚጓጓዝ ጫት በኪሎ ግራም ብር 5 /አምስት ብር/ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል፡፡

5. <u>የታክሱ ማስከፈያ ቦታ</u>

በዚህ አዋጅ በጫት ላይ የተጣለው ታክስ የሚሰበሰበው የታክስ ባለሥልጣኑ አግባብነት ካላቸው ክልሎች ጋር በመመካከር በሚወስናቸው ቦታዎች ይሆናል፡፡

6. <u>ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት</u>

   1. በዚህ አዋጅ መሠረት በጫት ላይ የተጣለውን ታክስ የሚሰበስበው የታክስ ባለስልጣኑ ይሆናል፡፡
   2. የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ከጫት ላይ የሰበሰበውን ታክስ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሠረት የገቢው ባለቤት ለሆኑ ክልሎች በየወሩ ያከፋፍላል።

7. <u>ለውጭ ገበያ ስለሚቀርብ ጫት</u>

   1. በውጭ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች፡-

      ሀ/ ለውጭ ገበያ በሚያቀርቡት ጫት ላይ ሊከፈል ለሚገባው ታክስ ክፍያ የሚውል ቫውቸር በታክስ ባለስልጣኑ ይሰጣቸዋል፤

      ለ/ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡትን ጫት በአገር ውስጥ በሚያጓጉዙበት ጊዜ በጫቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ቫውቸር በታክሱ ማስከፈያ ቦታ ለተመደበው የታክስ ባለስልጣኑ ሠራተኛ ያስረክባሉ፤

      ሐ/ የቀረጥና ታክሱ ሂሳብ በቫውቸር የተከፈለበትን ጫት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ቫውቸሩን በየወሩ ከታክስ ባለስልጣኑ ዘንድ ቀርበው ማወራረድ አለባቸው።

   2. በውጭ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች ጫቱን ወደ ውጭ ያልላኩ ከሆነ ታክሱንና የታክሱን 25 በመቶ በመቀጫ መልክ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።
   3. የታክስ ባለስልጣኑ የዚህን አንቀጽ ዝርዝር አፈፃፀም የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

8. <u>ሌሎች ግብርና ታክሶችን የመክፈል ኃላፊነት</u>

ማንኛውም በጫት ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ግብር ከፋይ በዚህ አዋጅ ከተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ በተጨማሪ ፀንተው በሚሠራባቸው ሕጎች መሠረት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

9. <u>**የኤክሳይዝ አዋጅ ተፈጻሚነት**</u>

በዚህ አዋጅ ባልተደነገጉ ጉዳዮች ላይ የኤክሳይዝ አዋጅ ቁጥር 307/1994[109] (እንደተሻሻለ) ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

10. <u>**የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**</u>

1. የጫት ግብርን ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 309/1979 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

11. <u>**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**</u>

የጫት ግብርን ለማስከፈል በወጣው አዋጅ መሠረት መከፈል ሲገባው ይህ አዋጅ በሥራ ላይእስከዋለበት ቀን ድረስ ያልተከፈለ ታክስ በዚያው አዋጅ መሠረት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

12. <u>**ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

13. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 21 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

[109] ** በ26/25(2012) ኢ1186 ተሻረ**

## አዋጅ ቁጥር 979/2008

## የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ

የአገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ከደረሰበት ደረጃ ጋር የተጣጣመ እና የኢኮኖሚውን ዕድገት የሚያግዝ ዘመናዊና ቀልጣፋ የግብር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የግብር አከፋፈሉ ሥርዓት ፍትሃዊነት ያለው እንዲሆን እና ግብር የማይከፈልባቸው ገቢዎች በግብር መረብ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55(1) እና (11) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጉም**

   በታክስ አስተዳደር አዋጅ ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ አዋጅ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ አዋጅ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም፡-

   1. “የገንዘብ መጠን” በዓይነት የተገለፀ መጠንንም ይጨምራል፤
   2. “የንግድ ሥራ” ማለት፡-

      ሀ/ በተከታታይ ወይም ለአጭር ጊዜ ለትርፍ የሚከናወን ማንኛውም የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የሙያ ወይም ቮኬሽናል ሥራ ሲሆን ተቀጣሪ ለቀጣሪው የሚሰጠውን አገልግሎት ወይም ቤት ማከራየትን አይጨምርም፣

      ለ/ በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ነው ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ ማንኛውም ሥራ፣ ወይም

ሐ/ ሕንፃ ማከራየትን ሳይጨምር የኩባንያው ዓላማ ምንም ቢሆን ማንኛውም የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚሠራው ማንኛውም ሥራ፤

3. "የንግድ ሥራ ሀብት" ማለት የንግድ ሥራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት ነው፤

4. "የንግድ ሥራ ገቢ" በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 21 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

5. "ማግኘት" ማለት፡-

ሀ/ ለንግድ ሥራ እና ለኪራይ ገቢ ግብር፤

(1) በአክሩዋል የሒሣብ አያያዝ ዘዴ ሒሳቡን ለሚይዝ ግብር ከፋይ፣ለመቀበል የሚያስችል መብት ማግኘት፣

(2) ሒሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሒሳብ አያያዝ ዘዴ ለሚይዝ ግብር ከፋይ፣ መቀበል፣ ወይም

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተጣለ ማንኛውም ሌላ ግብር፣

መቀበል ነው፤

6. "የትርፍ ድርሻ" ማለት አንድ ድርጅት ለአባላቱ የሚያከፋፍለው ትርፍ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ የድርጅቱ ካፒታል በከፊል ሲቀንስ ለአባሉ በአባልነቱ ተመላሽ የሚደረግለት ከካፒታሉ ውስጥ ከተቀነሰው በስሙ ከተመዘገበ የአባልነት ጥቅም ዋጋ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን፤

ለ/ ድርጅቱ መልሶ በመሸጡ ወይም በመዘጋቱ ወይም ኩባንያው በመፍረሱ ወይም ሽርክና በመቋረጡ ምክንያት የአባልነት ጥቅም ሲሰረዝ ለአባሉ ተመላሽ የተደረገለት በካፒታሉ ውስጥ ከነበረው በስሙ ከተመዘገበ የአባልነት ጥቅም ዋጋ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን፤

ሐ/ ድርጅቱ ለአንድ የድርጅት አባል ወይም ከአባሉ ጋር ግንኙነት ላለው ሰው ትርፍ የማከፋፈል ውጤት በሚያስከትል ግብይት ያበደረው ማንኛውም የገንዘብ መጠን፣ለአንድ ሀብት ወይም አገልግሎት የፈፀመው ክፍያ፣የቀረበ ማንኛውም ሀብት ወይም የአገልግሎት ዋጋ፣ ወይም የተተወ የብድር ዕዳ፤

7. "ተቀጣሪ" ማለት ራሱን ችሎ የሚሠራን የሥራ ተቋራጭ ሳይጨምር በሌላ ሰው መሪነትና ቁጥጥር ሥር ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ግለሰብ ሲሆን የድርጅት ዳይሬክተርን ወይም በድርጅቱ አመራር ውስጥ ኃላፊነት የተሰጠውን ሌላ ሰው እንዲሁም ተሿሚንና የሕዝብ ተመራጭን ጨምሮ የመንግሥት ሥራ ኃላፊን ያጠቃልላል፤
8. "ቀጣሪ" ማለት ተቀጣሪን የቀጠረ ወይም ለተቀጣሪው ደመወዝ የሚከፍል ሰው ነው፤
9. "ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ" በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤
10. "ከግብር ነፃ የሆነ ገቢ" ማለት በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ "ሠ" ከግብር ነፃ የሆነ ገቢ ነው፤
11. "የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች" ማለት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ የተደነገጉት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ናቸው፤
12. "ጠቅላላ ገቢ" ማለት ወጪዎችተቀናሽ ከመደረጋቸው በፊትአንድ ሰው ያገኘው በሠንጠረዥ "ለ" ወይም "ሐ" ሥር የሚወድቅ ጠቅላላ ገቢ ነው፤
13. "የማይንቀሳቀስ ሀብት" በአንቀጽ 36 በተደነገገው መሠረት በማዕድን ወይም በነዳጅ ሀብት ላይ ያለን መብት ወይም የማዕድን ወይም የነዳጅ መረጃን ይጨምራል፤
14. "ገቢ" ማለት መደበኛ ያልሆነ ገቢን ጨምሮ ከማንኛውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ወይም በማንኛውም መንገድ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው፣ በስሙ የተያዘለት ወይም የተቀበለው ማንኛውም የኢኮኖሚ ጥቅም ነው፤
15. "ራሱን የቻለ ሥራ ተቋራጭ" ማለት ሥራውን በአመዛኙ በራሱ የመምራትና የመቆጣጠር በቂ ሥልጣን በሚሰጠው ውል መሠረት አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤
16. "ወለድ" ማለት ገንዘብን ለመጠቀም ወይም የክፍያ ጊዜን ለማራዘም በየጊዜው ወይም በአንድ ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ መጠን ሲሆን ቅናሽን፣ ፕሪሚየምን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ክፍያዎችንም ይጨምራል፤

17."የሥራ አመራር ክፍያ" ማለት ለሥራ አመራር ወይም አስተዳደራዊ አገልግሎት የሚከፈል የገንዘብ መጠን ሲሆን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን አይጨምርም፤

18.“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር“ ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወይም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር ነው፤

19."መቀበል" የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ ግብር ከፋዩ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በሕግ መሠረትገንዘቡበግብርከፋዩስምጥቅምላይ ሲውል፤

ለ/ ለግብር ከፋዩ ጥቅም ተብሎ ገንዘቡ መልሶ ሥራ ላይ ሲውል ወይም ሲጠራቀም ወይም ደግሞ ለካፒታል ማሳደጊያ ሲውል፤

ሐ/ ለግብር ከፋዩ ጥቅም ወደ ባንክ ሂሳብ ውስጥ ሲገባ ወይም ወደ መጠባበቂያገንዘብ ሲዘዋወር፤ ወይም

መ/ በሌላ በማናቸውም መልኩ ለግብር ከፋዩ የተያዘለት ሲሆን፤

20.“ሮያሊቲ” ማለት ከዚህ በታች ከተመለከቱት ለማንኛውም ጉዳይ በአንድ ጊዜ ወይም በየጊዜው የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው፡-

ሀ/ ማንኛውንም የሥነ-ጽሑፍ፣ የሥነ-ጥበብ፣ ወይም የሳይንሳዊ ሥራ የቅጂ መብትሲሆን፣ የሲኒማቶግራፊ ፊልሞችና ለሬድዮ፣ ለቴሌቪዥን ወይም ለኢንተርኔት ሥርጭት የሚውሉ ፊልሞችና፣ ቴፖችን መጠቀም ወይም ለመጠቀም መብት ማግኘትን ይጨምራል፤

ለ/ ከቴሌቪዥን ወይም ከሬድዮ ወይም ከኢንተርኔት ሥርጭት ጋር ተያይዞ በሳተላይት፣በኬብል፣በኦፕቲክ ፋይበር፣ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ወይም የሚታዩ ምስሎችን፣ ወይም ድምፆችን ወይም ሁለቱንም መቀበል ወይም ለመቀበል የሚያስችል መብት ማግኘት፤

ሐ/ ማንኛውንም የፈጠራ ባለቤትነት መብት፣ ፈጠራ፣ የንግድ ምልክት፣ ንድፍ ወይም ሞዴል፣ ፕላን፣ የሚስጥር ቀመር ወይም ሂደት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሀብት ወይም መብት መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት ማግኘት፤

መ/ ማንኛውንም ኢንዱስትሪያዊ፣ የንግድ ወይም ሳይንሳዊ መሣሪያ መጠቀም ወይም ለመጠቀም መብት ማግኘት፤

ሠ/ ማንኛውንም ኢንዱስትሪያዊ፣የንግድ ወይም ሳይንሳዊ ተሞክሮ የሚመለከት መረጃ መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት ማግኘት፤

ረ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ-ሠ) የተዘረዘሩትን ሀብቶች ወይም መብቶች መጠቀም እንዲቻል በተጨማሪነትና በተቀጽላነት የሚሰጥ ድጋፍ፤

21.“የግብር ዓመት” ማለት፡-

ሀ/ ለግለሰብ ሲሆን፣ ባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማስታወቂያ ፈቃድ ካልሰጠ እና በጽሁፍ ማስታወቂያው የተወሰኑትን ቅድመ-ሁኔታዎች በማሟላት ግለሰቡ የራሱን የሂሳብ ዓመት ካልተጠቀመ በስተቀር፣ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ያለው የአንድ ዓመት ጊዜ ነው፤

ለ/ ለድርጅት ሲሆን የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት፤ ወይም

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተወሰነው የመሸጋገሪያ የሂሳብ ዓመት ነው፤

22.“ግብር ከፋይ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው፤

23.“የቴክኒክ ክፍያ” ማለት ለቴክኒካዊ፣ ሙያዊ፣ ወይም ለማማከር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ሲሆን፣ የቴክኒክ ወይም ሌሎች ባለሙያዎችን ለመጠቀም የሚከፈል ክፍያን ይጨምራል፤

24.“የንግድ ዕቃ” የሚከተሉትንም ይጨምራል፡-

ሀ/ ማንኛውም የተመረተ፣ የተፈበረከ፣ የተገዛ ወይም ለማምረት፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ በማናቸውም ሁኔታ የተገኘ ዕቃ፤

ለ/ በማምረት ወይም በመፈብረክ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ ዕቃ፤ ወይም

ሐ/ለጭነት ወይም ለሥራ የሚያገለግሉ እንስሳትን ሳይጨምር ማንኛውም እንስሳ፤

25.“ዋና ባለቤትነት” ማለት በድርጅት ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ባለው ድርጅት ወይም ድርጅቶች ወይም በግለሰቦች አማካኝነት ወይም በግለሰብ ባለቤትነት ሥር ባልሆነ ተቋም አማካኝነት የተያዘ የባለቤትነት ጥቅም ነው፤

26.“ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው” ማለት ከሚከፍለው ክፍያ ላይ በዚህ አዋጅ ክፍል አሥር መሠረት ግብር ቀንሶ የማስቀረት

ኃላፊነት ያለበት ሰው ሲሆን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 93 መሠረት ከሚቀበለው ክፍያ ላይ ግብር ራሱ ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ያለበትንም ሰው ይጨምራል፤

27.“ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ” ማለት በዚህ አዋጅ ክፍል አሥር መሠረት ግብር ተቀንሶ የሚያዝበት ገቢ ማለት ነው፡፡

3. <u>የግብር ከፋይ ደረጃዎች</u>

1. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የሚከተሉት የግብር ከፋይ ደረጃዎች ይኖራሉ፡-

ሀ/ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፣

(1) ድርጅት፣ ወይም

(2) ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ብር 1 ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) ወይም ከዚህ በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው፣

ለ/የደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 1 ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) የሚያንስ ነገር ግን ብር500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

ሐ/ ደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500,000(አምስት መቶ ሺ ብር) የሚያንስ ሰው ነው፡፡

2. የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚያሳውቀውን ግብር ወይም የሚያገኘውን ሌላ መረጃ መሠረት በማድረግ ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ደረጃ የተለወጠ መሆን አለመሆኑን ይወስናል፡፡

3. ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውንና ግብር ከፋዮችን የደረጃ "ሀ"፣ የደረጃ "ለ" ወይም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ብሎ ለመመደብ የሚያስችለውን ዓመታዊ ጠቅላላ የገቢ መጠን በኢኮኖሚ ጥናት ላይ በመመስረት ቢያንስ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማሻሻል አለበት፡፡

4. <u>በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3)፣(4) እና (5) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ “በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት” የሚባለው ማናቸውም ሰው የንግድ ሥራውን በሙሉ ወይም በከፊል የሚያከናውንበት ቋሚ የንግድ ሥራ ቦታ ነው፡፡

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ተደርገው ይወሰዳሉ፡-

ሀ/ ዋነኛ ተግባሩ የድርጅቱ አገናኝ ሆኖ ከሚያገለግለው ጽሕፈት ቤት በስተቀርየአስተዳደር ሥራ የሚከናወንበት ቦታ፣ ቢሮ፣ ፋብሪካ፣ መጋዘን ወይም ወርክሾፕ፤

ለ/ የማዕድን ማምረቻ ሥፍራ፣ የነዳጅ ወይም የጋዝ ጉድጓድ፣ የግንባታ ጠጠር ማምረቻ፣ ወይም ሌላ ማናቸውም የተፈጥሮ ሀብት ፍለጋ፣ ወይም ማምረት ሥራ የሚከናወንበት ቦታ፤

ሐ/ ለአንድ ወይም ለተያያዙ ፕሮጀክቶች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ183 (አንድ መቶ ሰማንያ ሦስት) ቀናት በላይ ለሆነ ጊዜ ተቀጣሪዎችን ወይም ሌሎች ሠራተኞችን በመመደብ የምክር አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎች ማናቸውም አገልግሎቶች የሚሰጡበት ቦታ፤

3. የግንባታው ሥራ፣ ፕሮጀክቱ ወይም የሥራ እንቅስቀሴው ከ 183 (አንድ መቶ ሰማንያ ሦስት) ቀናት በላይ የሚቆይ እስከሆነ ድረስ የህንፃ ግንባታ ሥራ የሚከናወንበት ሥፍራ፣ የግንባታ፣ የመገጣጠም ወይም የተከላ ፕሮጀክት ወይም ከእነዚህ ጋር የተገናኙ የቁጥጥር ሥራዎች በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም ራሱን ችሎ የሚሠራ ወኪል በመደበኛ የንግድ ሥራ አካሄድ ከሚያከናውነው ተግባር በስተቀር ማናቸውም ሰው "ወካይ" ተብሎ ለሚጠራ ሌላ ሰው ወኪል በመሆን በሌላ ሰው ስም የሚሰራ በሚሆንበት ጊዜ ወኪሉ የወካዩ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ነው የሚባለው፡-

ሀ/በወካዩ ስም በቋሚነት ውሎችን የሚደራደር፤ ወይም

ለ/ በወካዩ ስም የንግድ ዕቃዎችን ለማስረከብ አከማችቶ የሚይዝ ከሆነነው፡፡

5. በዚህ አንቀጽ "ራሱን ችሎ የሚሠራ ወኪል" ማለት በሚወክለው ሰው ቁጥጥር ስር ሳይሆን ራሱን ችሎ የሚሠራ ሲሆን፣ የንግድ ወይም የፋይናንስ ግንኙነታቸው ራሳቸውን ችለው ከሚሠሩ ሰዎች የተለየ የሆነውን በብቸኝነት ወይም በዋነኛነት ለአንድ ሰው ወኪል በመሆን የሚሠሩትን አይጨምርም፡፡

5. <u>ነዋሪነት</u>

1. የሚከተሉት የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ናቸው፡-

ሀ/ነዋሪ የሆነ ግለሰብ፤

ለ/ነዋሪ የሆነ ድርጅት፤

ሐ/ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እንዲሁም ማናቸውም የክልል መንግሥት ወይም የከተማ አስተዳደር፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) እንደተጠበቁ ሆነው፤ አንድ ግለሰብ በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

ለ/ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለውና ከኢትዮጵያ ውጭ በኮንሱላር፣ በዲፕሎማቲክ ወይም በተመሳሳይ ሥራ ተመድቦ የሚሰራ፤

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳያቋርጥ ወይም በመመላለስ ከ183 (አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት) ቀናት በላይ የኖረ ግለሰብ፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት "የተያዘው የግብር ዓመት" ተብሎ ለሚጠቀሰው ለአንድ የግብር ዓመት ነዋሪ የሆነ ግለሰብ ባለፈው የግብር ዓመት ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ በተያዘው የግብር ዓመት እንደነዋሪ ሆኖ የሚቆጠረው ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ከጀመረበት ቀን አንስቶ ነው፡፡

4. አንድ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በተያዘው የግብር ዓመት ነዋሪ ሆኖ፤ ነገር ግን በሚቀጥለው የግብር ዓመት ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ፤ በተያዘው የግብር ዓመት እንደ ነዋሪ ሆኖ የሚቆጠረው ግለሰቡ ለመጨረሻ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ከኖረበት ቀን በፊት ላለው ጊዜ ነው፡፡

5. አንድ ድርጅት በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ወይም የተመሠረተ እንደሆነ፤

ለ/ ወሳኝ የሆነ አመራር የሚያካሂድበት ሥፍራ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እንደሆነ፤ ነው፡፡

6. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት ነው፡፡

7. ነዋሪ ያልሆነ ሰው የሚባለው ማንኛውም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ነው፡፡

6. <u>የገቢ ምንጭ</u>

1. አንድ ተቀጣሪ ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የመነጨ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ ክፍያው የሚፈጸምበት ሥፍራ ግምት ውስጥ ሳይገባ ኢትዮጵያ ውስጥ

ከሚከናወን የቅጥር አገልግሎት የተገኘ ገቢ፣ ወይም

ለ/ የቅጥር አገልግሎቱ የትም ቢከናወን በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ወይም በኢትዮጵያፌደራላዊዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ስም ክፍያው ለተቀጣሪው ከተፈፀመ፣ ነው፡፡

2. በቋሚነት በሚሠራ ድርጅቱ አማካኝነት ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያገኘውን ገቢ ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያፈራው የንግድ ሥራ ገቢ ከኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ገቢ ይሆናል፡፡

3. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የንግድ ሥራ ገቢ ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ የተገኘ ገቢ ሲሆን፣

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት በሚሰራድርጅት አማካኝነትከሚያስተላልፋቸው ዕቃዎች ወይም ሸቀጦች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ እቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ኢትዮጵያ ውስጥ በማስተላለፍ የሚያገኘው ገቢ፣

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ከሚያከናውናቸው ማናቸውም የንግድ ሥራዎች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ በማከናወን የሚያገኘው ገቢ፣

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) የተመለከተው ቢኖርም፣ የሚከተሉት ገቢዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የመነጩ ገቢዎች ናቸው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት ለአንድ ሰው የሚከፍለው የትርፍ ድርሻ፣

ለ/ የሚከተሉትን ሀብቶች በማከራየት የሚገኝ ገቢ፡-

(1) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ሀብት፣ ወይም

(2) በአንቀጽ 58 መሠረት ግብር የሚከፈልበት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የሚንቀሳቀስ ሀብት፣

ሐ/ የሚከተሉትን ሀብቶች በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ፡-

(1) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ሀብት፣

(2) ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በላይ በሚሆነው በሀብቱ ዋጋ ላይ ያለው ጥቅምበቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተዛመዱ ድርጅቶች የተያዘ በሚሆንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ ያለ ጥቅም፤

(3) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ያወጣው አክሲዮን ወይም ቦንድ፤

መ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መድን ለተገባለት አደጋ (ስጋት) የሚከፈል የመድን አረቦን፤

ሠ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከናወን የመዝናኛ ወይም ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ፤

ረ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ የዕድል ሙከራዎችን በማሸነፍ የሚገኝ ገቢ፤

ሰ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ወለድ፣ ሮያሊቲ፣ የሥራ አመራር ክፍያ ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ በሚመለከት፡-

(1) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካይነት ውጭ ሀገር ለሚያካሂደው የንግድ ሥራ ያወጣውን ወጪ ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው የሚፈፀመው ክፍያ፤

(2) በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያካሂደው የንግድ ሥራ የሚፈፀመው ክፍያ፤

5. ከኢትዮጵያ ውስጥ ያልመነጨ ማንኛውም ገቢ የውጭ ሀገር ገቢ ነው፡፡

7. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ እና በማናቸውም ሌላ የዓለም ክፍል በሚያገኙት ገቢ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎችን በተመለከተ አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያገኙት ገቢ ላይ ነው፡፡

8. <u>**የገቢ ሠንጠረዦች**</u>

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው የገቢ ግብር በሚከተሉት ሠንጠረዦች መሠረት ይከፈላል፡-

ሀ/ ሠንጠረዥ "ሀ" ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤

ለ/ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ፤

ሐ/ሠንጠረዥ "ሐ" ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ፤

መ/ሠንጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች፤

ሠ/ሠንጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ገቢዎች፤

2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 64(2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ከሚወድቁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ገቢ ያገኘ እንደሆነ ሁሉም ገቢዎች ተጣምረው በዚያው ሠንጠረዥ ሥር የዓመቱን ግብር ይከፍላል፡፡

9. <u>የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ</u>

ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅና በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ሠንጠረዥ "ሀ" ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ</u>

10. <u>ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል</u>

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 84 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ማናቸውም ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከመቀጠር ከሚያገኘው ጠቅላላ የወር ወይም የወሩ ከፊል ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 በተወሰኑት መጣኔዎች መሠረት በእያንዳንዱ ወር ግብር ይከፍላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከመቀጠር በሚገኝ ወርሀዊ ገቢ ላይ የሚጣለው የገቢ ግብር ተቀጣሪው በአንድ ወር ውስጥ በተቀበለው ጠቅላላ ወርሃዊ ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት ተፈፃሚ የሚሆነውን መጣኔ መሠረት በማድረግ ይሰላል፡፡
3. ተቀጣሪው በመቀጠር የሚገኘውን ገቢ ለማግኘት የሚያወጣው ማንኛውም ወጪ በተቀናሽ ሊያዝለት አይችልም፡፡
4. ለዚህ ሠንጠረዥና ለዚህ አዋጅ አንቀጽ 88 አፈፃፀም ሲባል፤ በነሐሴና በጳጉሜ ወራት የሚከፈለው የቅጥር ገቢ ተደምሮ እንደ የአንድ ወር ደመወዝ ግብር ይከፈልበታል፡፡

5. በአንድ ተቀጣሪ ላይ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 (1) ድንጋጌ ተፈፃሚ የተደረገ እንደሆነ በመቀጠር በተገኘው ገቢ ላይ ተቀጣሪው የከፈለው ታክስ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ቀጣሪው በአንቀጽ 88 መሠረት ከተቀጣሪው የሚፈለገውን የገቢ ግብር ቀንሶ ያስቀረ እንደሆነ ግብሩ እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡

11.<u>በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ መጣኔዎች</u>

ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ለሚጣለው ግብር ተፈፃሚ የሚሆኑት መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

| በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በብር | ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን መጣኔ |
|---|---|
| 0-600 | 0% |
| 601-1,650 | 10% |
| 1,651-3,200 | 15% |
| 3,201-5,250 | 20% |
| 5,251-7,800 | 25% |
| 7,801-10,900 | 30% |
| ከ10,900 በላይ | 35% |

12.<u>ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ከመቀጠር የሚገኙ ገቢዎች ናቸው የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

   ሀ/ ሠራተኛው ካለፈው፣ አሁን ካለው ወይም ወደፊት ከሚመጣው ቅጥር ጋር በተያያዘ የተቀበለው ደመወዝ፣ ምንዳ፣ አበል፣ ጉርሻ፣ ኮሚሽን፣ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ማበረታቻ ስጦታ ወይም ሌላ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ፤

   ለ/ ያለፈን፣ የአሁኑን ወይም የወደፊትን ቅጥር አስመልክቶ ሠራተኛው የሚቀበለው የዓይነት ጥቅማ ጥቅም ዋጋ፤

   ሐ/ ተቀጣሪው ከሥራ ሲቀነስ፣ ሥራውን ሲለቅ ወይም ሥራውን እንዲለቅ ለማግባባት የሚከፈል ገንዘብን ጨምሮ የሥራ ውል በመቋረጡ

ምክንያት በፈቃደኝነት፣ በስምምነት ወይም በዳኝነት ውሳኔ መሠረት የተቀበለው ማንኛውም የገንዘብ መጠን፤

2. በመቀጠር የሚገኝ ገቢ ከግብር ነፃ የተደረገን ገቢ አይጨምርም፡፡
3. ማንኛውም ቀጣሪ ተቀጣሪው መክፈል የሚኖርበትን ግብር ከተቀጣሪው ገቢ ላይ ሳይቀንስ ራሱ ለተቀጣሪው በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለለት እንደሆነ፣ በቀጣሪው የተከፈለው የግብር መጠን ተቀጣሪው ከመቀጠር ከሚያገኘው ግብር በሚከፈልበት የገንዘብ መጠን ላይ ተደምሮ ግብሩ ይሰላል፡፡
4. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከደመወዝ ሌላ በዓይነት የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች ዋጋ የሚወሰንበትንና ግብር የሚከፈልበትን ሁኔታ አስመልክቶ ደንብ ያወጣል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

### 13.በቤት ኪራይ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል

1. ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 በተመለከተው መጣኔ ወይም መጣኔዎች መሠረት በእያንዳንዱ የግብር ዓመት የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡
2. በግብር ዓመቱ አንድ ግብር ከፋይ ከቤት ኪራይ በሚያገኘው ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ሥር የተመለከቱትን መጣኔዎች ግብር በሚከፈልበት ዓመታዊ ገቢ ላይ ተፈፃሚ በማድረግ ይሰላል፡፡
3. ይህ ሠንጠረዥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 58 መሠረት የኪራይ ገቢ ግብር ለሚከፈልበት ገቢ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### 14.የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔዎች

1. በድርጅቶች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የግብር መጣኔ 30% (ሰላሳ በመቶ) ነው፡፡
2. በግለሰቦች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ በዓመት | የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ |
|---|---|
| 0-7,200 | 0% |
| 7,201-19,800 | 10% |
| 19,801-38,400 | 15% |
| 38,401-63,000 | 20% |
| 63,001-93,600 | 25% |
| 93,601-130,800 | 30% |
| ከ130,800 በላይ | 35% |

15. <u>ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ</u>

1. የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ የኪራይ ገቢ ነው የሚባለው ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ ቤት በማከራየት ካገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀደው ጠቅላላ ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀረው ገቢ ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ ቤት

   ሀ/ የኪራይ ዋጋ ጭማሪን ወይም ተመሳሳይ ክፍያዎችን ጨምሮ፣ በኪራይ ውሉ መሠረት ግብር ከፋዩ በዓመቱ የሚያገኘው ማናቸውም የገንዘብ መጠን፤

   ለ/ በኪራይ ውሉ መሠረት ተከራዩ አከራዩን በመወከል በግብር ዓመቱ ለሌሎችየሚከፍላቸው ክፍያዎች፤

   ሐ/ ግብር ከፋዩ ጉዳቱን ለማስተካከል ያልተጠቀመበት እና በቤቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማስተካከያ ይሆን ዘንድ የያዘው እና በግብር ዓመቱ ለግብር ከፋዩ ገቢ የተደረገው ማንኛውም ቦንድ፣ ዋስትና ወይም ተመሳሳይ የገንዘብ መጠን፤

   መ/ ለታክስ ከፋዩ ከሚከፈለው ኪራይ በተጨማሪ በኪራዩ ውል መሠረት ተከራዩ ራሱ ለቤቱ እድሳት ወይም ማሻሻያ የሚያወጣው ገንዘብ፤

3. ግብር ከፋዩ ቤቱን ያከራየው ከዕቃዎች ጋር በሚሆንበት ጊዜ፣ ያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከዕቃዎቹ የተገኘውን የኪራይ ገቢም ያጠቃልላል፡፡
4. ግብር ከፋዩ ቤት በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ የሆነን ገቢ አይጨምርም፡፡
5. በአንድ የግብር ዓመት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉት ወጪዎች በተቀናሽ ይያዛሉ፡-
   ሀ/ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር በግብር ዓመቱ ውስጥ የከፈላቸው ክፍያዎች፤
   ለ/ ለቤቶች፣ ለቤት ዕቃና መሣሪያ ማደሻ፣ መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ የሚሆን ከቤት፣ ከቤት ዕቃ እና ከመሳሪያ ኪራይ ከሚገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ላይ ሃምሳ በመቶ፤
6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ በማናቸውም ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ላለባቸው ግብር ከፋዮች ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡
7. የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ ገቢውን ለማግኘት የወጣና በግብር ከፋዩ የተከፈለ አስፈላጊ የሆነ ወጪ ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን፣ ይህም ወጪ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-ሀ/ ቤቱ ያረፈበት መሬት ኪራይ፤
   ለ/ የጥገና ወጪ፤
   ሐ/ የቤቱ፣ የቤት ዕቃዎችና የመሣሪያዎች የእርጅና ቅናሽ፤
   መ/ ወለድና የመድን አረቦን፤
   ሠ/ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር
   ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር የከፈላቸው ክፍያዎች፤

16. <u>የተከራይ አከራዮች</u>

1. የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው የሚባለው የተከራይ አከራዩ በግብር ዓመቱ ከተቀበለው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ

ላይ ለዋናው አከራይ የሚከፍለው ኪራይ እንዲሁም ገቢውን ለማግኘት ያወጣቸው ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ነው፡፡

2. ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ሳይከፍል ቢቀር ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

17.<u>የሚከራይ አዲስ ቤትን ስለማሳወቅ</u>

1. ለኪራይ የሚሰራ ቤት ተሰርቶ እንዳለቀ ወይም ቤቱ እንደተከራየ፣ ከሁለቱ በሚቀድመው ጊዜ የቤቱ ባለቤትና የቤቱ ስራ ተቋራጭ የቤቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ወይም የተከራየ መሆኑን ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ያለበትን ሰው ስም፣ አድራሻና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ቤቱ ለሚገኝበት የቀበሌ አስተዳደር ወይም የአካባቢ አስተዳደር ማስታወቅ አለባቸው፡፡
2. የቀበሌው አስተዳደር እና የአካባቢው አስተዳደር በማስታወቂያው መሠረት የተገኘውን መረጃ ለባለሥልጣኑ መግለጽ አለባቸው፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ሠንጠረዥ “ሐ” ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>ከንግድ ሥራዎች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብርን ስለመጣል</u>

18.<u>በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ግብርን ስለመጣል</u>

1. በዚህ ክፍል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው ሰው በእያንዳንዱ የግብር ዓመት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 በተመለከተው መጣኔ ወይም መጣኔዎች መሠረት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡
2. አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት የሚከፍለው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚሰላው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 የተመለከተው መጣኔ ወይም መጣኔዎች በግብር ከፋዩ የግብር ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ነው፡፡

19.<u>በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ መጣኔዎች</u>

1. በድርጅት ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የንግድ ሥራ ገቢ የግብር መጣኔ ሰላሳ በመቶ (30%) ነው፡፡
2. በግለሰብ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ከንግድ ሥራ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በዓመት | የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔ |
|---|---|
| 0-7,200 | 0% |
| 7,201-19,800 | 10% |
| 19,801-38,400 | 15% |
| 38,401-63,000 | 20% |
| 63,001-93,600 | 25% |
| 93,601-130,800 | 30% |
| ከ130,800 በላይ | 35% |

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ግብር የሚከፍሉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር በተመለከቱት መጣኔዎች መሠረት ይሆናል፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም “ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች” የሚለው የፌደራል ከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 374/2008 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

20.<u>ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ</u>

1. የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ የንግድ ሥራ ገቢ ነው የሚባለው ከንግድ ሥራ ከተገኘ ጠቅላላ የግብር ዓመቱ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀዱት ወጪዎች ተቀናሽ ከተደረጉ በኋላ የሚገኘው የገቢ መጠን ነው፡፡

2. በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣቸው ደንቦች እና ሚኒስትሩ በሚያወጣቸው መመሪያዎች የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ የሚወሰነው ግብር ከፋዩ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት በሚያዘጋጀው የትርፍና ኪሳራ ወይም የገቢ መግለጫ ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡

21.<u>የንግድ ሥራ ገቢ</u>

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ በአንድ የግብር ዓመት የአንድ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ከፋይ የንግድ ሥራ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-
   ሀ/ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን ሳይጨምር ግብር ከፋዩ ዕቃዎችን በማስተላለፍ እንዲሁም አገልግሎቶችን በመስጠት የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ጨምሮ በግብር ዓመቱ ከንግድ ሥራ ያገኘው ጠቅላላ ገንዘብ መጠን፤
   ለ/ ለንግድ የሚውል ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ የገንዘብ መጠን፤
   ሐ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ገቢ ተደርጎ የሚወሰድ ሌላ ማንኛውም የገንዘብ መጠን፤
2. ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረገን ገቢ አይጨምርም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተው የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ከንግድ ሥራ ሀብቱ የመዝገብ ዋጋ በላይ የሆነው የንግድ ሥራ ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ከተላለፈው ሀብት የተገኘው ገቢ ነው፡፡
4. አንድ የንግድ ሥራ ሀብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 59 መሠረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ፡-
   ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተውን የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኘውን ገቢ ለንግድ ሥራው ሀብት የተደረገውወጪ ከንግድ ሥራው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን ሲሆን፤

ለ/ ከወጪው በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአንቀጽ 59 መሠረት ግብር ይከፈልበታል፡፡

## 22.ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን በተቀናሽ የሚያዙት ወጪዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

   ሀ/ በንግድ ሥራው ገቢው ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት፣ ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች፤

   ለ/ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በተመለከተው መሠረት የተሠላ በግብር ዓመቱ በግብር ከፋዩ ለተሸጠ የንግድ ዕቃ የወጣ ወጪ፤

   ሐ/በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 በሚወሰነው መሠረት የንግድ ሥራ ገቢን ለማግኘት ሥራ ላይ የዋሉ ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ህልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ፣

   መ/ ግብር ከፋዩ የንግድ ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ሀብትን ሲያስተላልፍ የሚገጥመው ኪሳራ፣

   ሠ/ ለግብር ዓመቱ በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብር ከፋዩ በተቀናሽነት የሚፈቀድ ሌላ ማናቸውም ወጪ፣

2. ግብር የሚከፈልበት ሀብት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ካልሆነ በስተቀር፣ ግብር የሚከፈልበት ሀብት በሚተላለፍበት ጊዜ ለሚደርስ ኪሳራ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 59 ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(መ) ግን ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(መ) አፈፃፀም፤ የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚደርስ ኪሳራ የሚባለው ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀብቱ ከተላለፈበት ዋጋ በሚበልጠው የገንዘብ ልክ ነው፡፡

**23.<u>የወለድ ወጪ</u>**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ 47 እንደተጠበቁ ሆነው፤ ግብር ከፋዩ የወሰደውን ብድር ወይም ሌላ ዕዳ ወይም ያደረገውን ስምምነት የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት ተግባር ያዋለው እስከሆነ ድረስ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከፈለው ወለድ የግብር ከፋዩ የግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ እንደወጪ ይያዝለታል፡፡
2. ለሚከተሉት ወጪዎች ተቀናሽ አይፈቀድም፡-

   ሀ/ ወለዱ በብሔራዊ ባንክ እና በንግድ ባንኮች መካከል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ መጣኔ 2% (ሁለት በመቶ) የሚበልጥ ከሆነ በተቀናሽ አይያዝም፤ ነገር ግን ወለዱ፤

   (1) በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ለተሰጠው የፋይናንስ ተቋም ፣ ወይም

   (2) በኢትዮጵያ ለሚገኙ ሰዎች ብድር እንዲሰጥ ለተፈቀደለት የውጭ ሀገር ባንክ፣

   የተከፈለ ወይም የሚከፈል ከሆነ በተቀናሽ ይያዛል፡፡

   ለ/ የወለዱ ገቢ ግንኙነት ባለው ሰው የሰንጠረዥ “መ” ሥራ ገቢ ውስጥ ካልተካተተ በስተቀር፣ አንድ ግብር ከፋይ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ግንኙነት ላለው ሰው የከፈለው ወይም የሚከፍለው ወለድ፣

**24.<u>ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች</u>**

1. የግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ ግብር ከፋዩ ያደረገው ስጦታ ተቀናሽ የሚደረገው ስጦታው ለሚከተሉት የተደረገ ሲሆን ነው፡-

   ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ለተመለከተው የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ማኅበር፤ ወይም

   ለ/ መንግሥት ባደረገው ጥሪ መሠረት ለልማት፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር፣ ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ወይም ወረርሽኝ ለመከላከል ወይም ለተመሳሳይ ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት የተደረገ ከሆነ፤ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለግብር ከፋዩ የሚፈቀደው ጠቅላላ ተቀናሽ ከግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ 10% (አሥር በመቶ) መብለጥ የለበትም፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ማኅበር" በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

25.<u>የእርጅና ቅናሽ</u>

1. የግብር ከፋዩን በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማስገኘት በግብር ዓመቱ ጥቅም ላይ ላዋላቸው እና ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ዋጋቸው በቀነሰው የገንዘብ መጠን ልክ የእርጅና ቅናሽ ለማድረግ ይፈቀድለታል፡፡
2. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች በየግብር ዓመቱ የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
3. አንድ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ በሙሉ የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶችን ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸውን ሀብቶች ያልተጠቀመ እንደሆነ ደግሞ ለሌላ አገልግሎት የተጠቀመበት እንደሆነ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሆኖ፣ የንግድ ሀብቱ ጥቅም ላይ ያልዋለበት ዓመት ሂሣብ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ከተቀነሰ በኋላ ነው፡፡
4. አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት እና ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው ሀብት በከፊል የገቢ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት በከፊል ደግሞ ለሌላ አገልግሎት የተጠቀመበት እንደሆነ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚደረገው ማስተካከያ ከግምት ውስጥ ገብቶ በንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት በዋለው መጠን የሚሰላ ይሆናል፡፡

5. አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ዋጋው የሚቀንስን ሀብት እና ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት በከፊል የገቢ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማስገኘት በከፊል ደግሞ ለሌላ አገልግሎት ከተጠቀመበት በኋላ ይህንን ሀብት በዚያው የግብር ዓመት ውስጥ ያስተላለፈው እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22(1)(ሐ) ወይም 22 (1)(መ) የተደነገገው የትርፍ ወይም የኪሳራ መጠን የሚሠላው የንግድ ሥራው ያጋጠመው የትርፍ ወይም የኪሳራ መጠን ለንግድ ሥራው ገቢ በነበረው አስተዋጽኦ መጠንሚዛናዊ በሆነ መንገድ እየተከፋፈለ ይሆናል፡፡
6. ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ መታሰብ የሚጀምረው ሀብቱ የንግድ ሥራ ገቢውን ለማስገኘት ለአገልግሎት ዝግጁ ከሆነበትና አገልግሎት መስጠት አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ቀን አንስቶ ሲሆን፣ በግብር ከፋዩ የተገነባ ህንፃ በሚሆንበት ጊዜ ተቆጣጣሪው ባለስልጣን ለግብር ከፋዩ የህንፃው ግንባታ መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ከሰጠበት ቀን በፊት ሊሆን አይችልም፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ውስጥ፣

ሀ/ “ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሃብቶች” ማለት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢን ለማስገኘት የሚውሉ የሚከተሉት ሀብቶች ናቸው፡-

(1) የቅጅ መብት፣ ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም ሞዴል፣ ፕላን፣ ምስጢራዊ ቀመር ወይም የአሠራር ሂደት፣ የንግድ ምልክት፣ ወይም ለተወሰነ ዘመን ብቻ የሚያገለግል ሌላ ተመሳሳይ ሀብት፤

(2) የደንበኞች ዝርዝር፣ የሥርጭት መስመር ወይም የተለየ ስም፣ ምልክት ወይም ስዕል ወይም ለተወሰነ ዘመን ብቻ የሚያገለግል ሌላ ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ዘይቤ፤

(3) ከአንድ ዓመት በላይ ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ የሚያገለግል ከውል የሚመነጭ መብት (ወጪው አስቀድሞ የተከፈለንም ጨምሮ)፤

(4) ማንኛውንም ግዙፋዊ ህልዎት ያለውን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ሀብት ለማግኘት የወጣን ወጪ ሳይጨምር፣ ከአንድ ዓመት በላይ ጥቅም የሚሰጥ ወጪ፤

ለ/ “ዋጋው የሚቀንስ ሀብት” ማለት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ግዙፋዊ ህልዎት ያለው የሚንቀሳቀስ ሀብት ወይም በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ነው፡-

(1) ከአንድ ዓመት የሚበልጥ የአገልግሎት ዘመን ያለው፤

(2) በእርጅና ወይም ጊዜው በማለፉ ምክንያት ዋጋው ሊቀንስ የሚችል፤

(3) በከፊል ወይም በሙሉ የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት ጥቅም ላይ የዋለ፤

ሐ/ "በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ" ማለት ቤት ወይም ሌላ የቤቱ አካል የሚሆን ወይም ከቤቱ ጋር ለዘለቄታው የተያያዘ በቤቱ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጭማሪ ወይም ለውጥ ሲሆን መንገድን፣ መጋቢ መንገድ፣ የመኪና ማቆሚያ፣ አጥር ወይም ግንብን ይጨምራል፡፡

26.<u>ኪሳራን ስለማሸጋገር</u>

1. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚፈቀደውን ተቀናሽ ሳይጨምር፣ ለግብር ዓመቱ ተቀናሽ የሚደረገው ወጪ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ከበለጠ በብልጫ የታየው የገንዘብ መጠን ግብር ከፋዩ የደረሰበት ኪሳራ ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ኪሳራ ካጋጠመው፣ በግብር ዓመቱ የደረሰውን ኪሳራ ለሚቀጥለው የግብር ዓመት ለማሸጋገር ይችላል፤ ስለሆነም የግብር ከፋዩ የሚቀጥለው ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የተሸጋገረው ኪሳራ በተቀናሽነት ይያዛል፡፡

3. ግብር ከፋዩ ኪሳራውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሙሉ በሙሉ መቀነስ ያልቻለ እንደሆነ ያልተቀነሰውን ኪሳራ ለሚቀጥለው የግብር ዓመት ማሸጋገር እና የተካካሰውን የገንዘብ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ

አንቀጽ (2) በተገለጸው መሠረት በዚያው የግብር ዓመት ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ በመቀነስ ኪሣራው ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ተደርጎ እስከሚያልቅ ድረስ ማሸጋገር የሚችል ሲሆን፣ ነገር ግን ግብር ከፋዩ የደረሰበትን ኪሣራ ኪሣራው ከተከሰተበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ከሚቆጠሩ አምስት የግብር ዓመታት በላይ ማሸጋጋር አይችልም፡፡

4. ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለኪሳራ የተዳረገባቸው ሁለት ዓመታት ያሉ እና እያንዳንዱ ኪሳራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተሸጋገረ እንደሆነ ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሌላ ማንኛውንም ተጨማሪ ኪሳራ እንዲያሸጋግር ሊፈቀድለት አይችልም፡፡
5. ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ መሠረት ኪሳራ ሊያሸጋግር የሚችለው በገቢ ግብር ደንቡ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

## 27.<u>ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች እና ኪሳራዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ ከተደነገገው በስተቀር የሚከተሉት ወጪዎች በተቀናሽ አይያዙም፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22(1) (ሐ) በተደነገገው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር የካፒታልነት ባህርይ ያላቸው ወጪዎች፤

ለ/ የኩባንያ አክሲዮን ወይም የሽርክና ማህበር መሠረት የሆነውን ካፒታል ለማሳደግ የሚወጣ ወጪ፤

ሐ/ ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ 15% (አሥራ አምስት መቶኛ) በላይ በፈቃደኝነት የሚደረግ የጡረታ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ መዋጮ፤

መ/ የአክሲዮን ድርሻ እና የትርፍ ድርሻ ክፍፍል፤

ሠ/ በመድን፣ በካሳ ወይም በዋስትና ውል መሠረት የተመለሰ ወይም ሊመለስ የሚችል ወጪ ወይም ኪሳራ፤

ረ/ ማንኛውንም ሕግ ወይም ውል በመጣስ የሚጣል የገንዘብ ቅጣት ወይም የሚከፈል ካሳ፤

ሰ/ ግብር ከፋዩ በሂሳብ መዝገቡ የሚይዘው በወቅቱ ወጪ ያልተደረገ ነገር ግን ለወደፊት በግብር ዓመቱ ለሚከሰቱ ወጪዎች ወይም ኪሳራዎች መጠባበቂያ ይሆን ዘንድ የሚያዝ ገንዘብ ወይም የመጠባበቂያ ሂሣብ፤

ሸ/ በዚህ አዋጅ ወይም በውጭ ሀገር የታክስ ሕግ መሠረት የተከፈለ የገቢ ግብር ወይም ተመላሽ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

ቀ/ መሥሪያ ቤቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኝ ተቀጣሪ ከተቀጣሪው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ 10% (አሥር በመቶ) በላይ የሚከፈል የኃላፊነት አበል፤

በ/ከሚከተሉት በስተቀር ለመዝናኛ የሚወጣ ወጪ፤

(1) የግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ የመዝናኛ አገልግሎት መስጠት ሲሆን፤ ወይም

(2) ሚኒስትሩ በመመሪያ ተቀናሽ እንዲደረግ በሚፈቅደው ልክ በማዕድን ማውጣት፣ በማኑፋክቸሪንግ ወይም በግብርና ሥራ የተሠማራ ቀጣሪ ሠራተኞቹን ለማዝናናት የሚያወጣው ወጪ፤

ተ/በአንቀጽ24 ከተመለከተው ውጪ የሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ፤

ቸ/ግብር ከፋዩ ለራሱ የሚያወጣው የግል ውጪ፤

ኀ/ ግብር ከፋዩ አንድን የንግድ ሥራ ሀብት ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍ የሚደርስ ኪሳራ፤

ነ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ተቀናሽ የማይደረጉ ናቸው የተባሉ ወጪዎች፤

2. በዚህ አንቀጽ "መዝናኛ" ማለት ለማንኛውም ሰው የሚቀርብ ምግብ፣ መጠጥ፣ ትንባሆ፣ ማረፊያ፣ መደሰቻ ወይም ማናቸውም ዓይነት መስተንግዶ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የታክስ ሂሳብ አያያዝ

### 28.የሂሳብ ዓመት

1. ይህ አንቀጽ በሚከተሉት ግብር ከፋዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2(21)(ሀ) ለግብር ዓመት በተሰጠው ትርጉም መሠረት የራሱን የሂሳብ ዓመት እንደ ግብር ዓመት አድርጎ እንዲጠቀም ፈቃድ ለተሰጠው ግለሰብ ግብር ከፋይ፤

ለ/ በድርጅት፤

2. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ ለሚሆንበት ግብር ከፋይ የሂሳብ ዓመት ነው የሚባለው የግብር ከፋዩ ዓመታዊ የፋይናንስ ሂሳብ ሚዛን በሚዘጋበት ጊዜ የሚጠናቀቀው የአሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ነው፡፡
3. ማንኛውም ግብር ከፋይ ከባለሥልጣኑ አስቀድሞ በጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝና ባለሥልጣኑ የሚያስቀምጣቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች ሳያሟላ የሂሳብ ዓመቱን ለመቀየር አይችልም፡፡
4. ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው መሠረት ከተሰጠው ፈቃድ ጋር የተያያዘውን ማንኛውንም ቅድመ-ሁኔታ ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዘው ይችላል፡፡
5. የግብር ከፋዩ የሂሳብ ዓመት በንዑስ አንቀጽ (3) ወይም (4) መሠረት የተለወጠ እንደሆነ ለውጡ ከመደረጉ በፊት ባለው የግብር ዓመት እና አዲሱ የግብር ዓመት በሚጀምርበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ "የመሸጋገሪያ ዓመት" በመባል የሚታወቅና ራሱን የቻለ የግብር ዓመት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
6. የግብር ከፋዩ የሂሳብ ዓመት ከበጀት ዓመቱ ጋር የማይገጥም በሚሆንበት ጊዜ ለሂሳብ ዓመቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ሕግ በሂሳብ ዓመቱ ውስጥ በሚጠናቀቀው የበጀት ዓመት ተፈፃሚ የሚሆነው ሕግ ነው፡፡

29.<u>የታክስ ሂሳብ አያያዝ ዘዴን ስለመለወጥ</u>

1. ግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴውን ለመለወጥ ለባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፤ ባለሥልጣኑም ለውጡ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በትክክል ለማስላት የሚያስፈልግ መሆኑን ሲያምንበት ግብር ከፋዩ የሂሳብ ዘዴውን ለመለወጥ ያቀረበውን ማመልከቻ መቀበሉን በጽሁፍ ሊያሳውቀው ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ በሚለወጥበት የግብር ዓመት የግብር ከፋዩ የግብር ከፋይ ደረጃም የሚለወጥ ከሆነ፣ የግብር ከፋዩ ገቢ ሳይመዘገብ እንዳይቀር ወይም በድጋሚ እንዳይመዘገብ ለማድረግ በገቢ ርዕሶች፣በተቀናሽ ወጪዎች ወይም በታክስ ማካካሻ ሂሳቦች ላይ ከለውጡ ጋር በተያያዘ ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ አለበት፡፡

30.**<u>የማይሰበሰቡ ዕዳዎች</u>**

1. በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የማይሰበሰበው ዕዳ ለግብር ከፋዩ በተቀናሽነት ይያዝለታል፡-

   ሀ/ ከማይሰበሰው ዕዳ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ መጠን ቀደም ሲል የግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ገቢ ሆኖ ተይዞ ከሆነ፤

   ለ/ ዕዳው ወይም የዕዳው የተወሰነ የገንዘብ መጠን ከግብር ከፋዩ የግብር ዓመት የሂሳብ መዝገብ ላይ ሲሰረዝ፤

   ሐ/ ዕዳውን ለማስመለስ የሕግ እርምጃ ተወስዶ ዕዳው ሳይመለስ ሲቀር፤

2. ለግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ መሠረት በግብር ዓመቱ የሚፈቀደው የተቀናሽ የገንዘብ መጠን በግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ከተሰረዘው የዕዳ መጠን መብለጥ አይኖርበትም፡፡

3. ይህ አንቀጽ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 ተፈፃሚ ለሚሆንባቸው የፋይናንስ ተቋማት ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

31.**<u>የፋይናንስ ተቋማት እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚያወጣው የገቢ ግብር ደንብ የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚወስኑ ድንጋጌዎችን ሊይዝ ይችላል፡-

ሀ/ የፋይናንስ ተቋማት የሚይዙት የኪሳራ መጠባበቂያ ሂሣብ ተቀናሽ የሚደረግበትን አኳኋን፤

ለ/የሕይወት መድን ኢንሹራንስ ኩባንያዎችን ሳይጨምር፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ከሚያወጡዋቸው ጊዜያቸው ካላለፈባቸው የኢንሹራንስ ዋስትናዎች ጋር በተያያዘ የሚይዙት የመጠባበቂያ ሂሣብ ተቀናሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ፤

ሐ/የሕይወት መድን ኩባንያዎች ግብር የሚከፈልበት ገቢየሚሠላበትን ሁኔታ፤

32.**<u>ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ውሎች</u>**

1. ለንግድ ሥራ ገቢ ግብር ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ከተዋዋለው የረዥም ጊዜ ውል ውስጥ በግብር ዓመቱ የተጠናቀቀውን መቶኛ መሠረት በማድረግ ገቢውን በንግድ ሥራ ገቢው ውስጥ

ሲያካትት ወጪውም በዚያው መቶኛ ልክ በተቀናሽነት እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

2. በግብር ከፋዩ ለረጅም ጊዜ ከተደረገው ውል ውስጥ በግብር ዓመቱ የተጠናቀቀው በመቶኛ የሚወሰነው በግብር ዓመቱ የሚኖረውን ለውጥ ጨምሮ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ የወጣውን ወጪ ከአጠቃላይ የውሉ ወጪ ግምት ጋር በማነፃፀር ይሆናል፡፡
3. ግብር ከፋዩ ለረጅም ጊዜ ከተደረገ ውል ጋር ተያይዞ በውሉ የመጨረሻ ዓመት ኪሳራ የደረሰበት እና በአንቀጽ 26 መሠረት ኪሳራውን እንዲያሸጋግር የተፈቀደለት ቢሆንም ኪሳራውን ማሸጋገር ያልቻለ ሆኖ በውሉ ዘመን መጨረሻ በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ መሥራት ያቆመ እንደሆነ ይህ ግብር ከፋይ የደረሰበት ኪሳራ ወደ ኋላ ተመልሶ በአምናው የግብር ዓመት በተቀናሽነት እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡
4. ግብር ከፋዩ የደረሰበትን ኪሳራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)በተመለከተው መሠረት ወደ ኋላ ተመልሶ ሙሉ በሙሉ በተቀናሽ ወጪነት እንዲያዝ ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ፣ ያልተቀነሰው ኪሳራ ወደኋላ ተመልሶ ወደ አቻምናው የግብር ዓመት የሚሸጋገር ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው መሠረት ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
5. ግብር ከፋዩ በረዥም ጊዜ ውል ኪሣራ ደርሶበታል የሚባለው የሚከተሉት ቅድመ-ሁኔታዎች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡-
   ሀ/ የተጠናቀቀውን ሥራ በመቶኛ ለማስላት ዘዴ ዓላማ ሲባል በውሉ ይገኛል ተብሎ የተገመተው ግብር የሚከፈልበት ገቢ በእርግጠኛነት ከተገኘው ግብር ከሚከፍለበት ገቢ በልጦ ሲገኝ፤ እና
   ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት በብልጫ የታየው ገንዘብ በዚህ አንቀጽ መሠረት ተሰልቶ ከተደረሰበት ውሉ በተጠናቀቀበት የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢና ወጪው መካከል ካለው ልዩነት በልጦ ሲገኝ፤
6. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም “ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ውል” ማለት ሥራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በ12 ወራት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ከሚገመተው በስተቀር በተጀመረበት የግብር ዓመት ውስጥ ያልተጠናቀቀ የማምረት፣

የመትከል ወይም የግንባታ ሥራ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ነው፡፡

33.<u>ለደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ቀላል የታክስ ሥርዓት</u>

በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ገቢ የሚሰላው በዚህ አዋጅ መሠረት ሲሆን በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ሁኔታዎች መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡-

1. ግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ገቢውንና ተቀናሽ ወጪውን የሚይዘው በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሰረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መሆን አለበት፤
2. ለዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 አፈፃፀም ሲባል፣ ዋጋቸው ለሚቀንሱ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ህልዎት ለሌላቸው የግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ሀብቶች የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ 100% (መቶ ፐርሰንት) ይሆናል፤
3. በግብር ዓመቱ ለተገኙ የንግድ ዕቃዎች የወጣ ወጪ በተቀናሽነት ይያዛል፤
4. በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 17(2) የተመለከተው የሂሳብ መዛግብትን ይዞ የማቆያው ጊዜ እና የግብር ውሳኔን ለማሻሻል በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 28(2) (ለ) የተመለከተው ጊዜ ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>

<u>ድርጅቶች</u>

34.<u>አንድን ድርጅት በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ ለውጥ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ድርጅት "የኪሳራ ዓመት" ተብሎ በሚጠቀሰው የግብር ዓመት የደረሰበት ኪሳራ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 ወይም አንቀጽ 46 መሠረት "የመሸጋገሪያ ዓመት" ተብሎ ወደሚጠቀሰው የሚቀጥለው ዓመት ሊያሸጋግር የሚችለው በኪሳራው ዓመት፣ በማሸጋገሪያው ዓመት እና በማናቸውም ጣልቃገብ ዓመታት የኩባንያውን ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በላይ የሆነውን የዋና ባለቤትነት ድርሻ የያዘው ሰው ተመሳሳይ ሰው የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የኪሳራ መሸጋገርን መከልከል የማይቻለው፡-

ሀ/ በኪሳራው ዓመት፣ በማሸጋገሪያው ዓመት እና በሁሉም ጣልቃ ገብ የግብር ዓመታት ድርጅቱ አንድ ዓይነት የንግድ ሥራ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የድርጅቱ ዋና ባለቤትነት ከተለወጠም በኋላ የደረሰው ኪሣራ በወጪነት ተቀናሽ ተደርጎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ፣ ድርጅቱ በአዲስ የንግድ ሥራ ያልተሠማራ እና ድርጅቱ ወይም የድርጅቱ አባላት በአዲስ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩበት ዋነኛ ዓላማ የደረሰው ኪሣራ በአዲሱ የንግድ ሥራ ከተገኘው ገቢ ላይ ተቀናሽ እንዲሆን በማድረግ በድርጅቱ ሊከፈል የሚገባውን የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ለማሳነስ ያልሆነ እንደሆነ ነው፡፡

35. <u>የኩባንያ እንደገና መደራጀት</u>

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ "አስተላላፊ" ተብሎ የሚጠራ በኢትየጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ "የሚተላለፍለት" ተብሎ ለሚጠቀስ ለሌላ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ እንደገና ከመደራጀት ጋር ተያይዞ የንግድ ሥራ ሀብት ያስተላለፈለት እንደሆነ፡-

   ሀ/ ማስተላለፉ የንግድ ሥራ ሀብትን እንደመሸጥ፣ መለወጥ ወይም መስጠት ተደርጎ አይወሰድም፤

   ለ/ የንግድ ሥራ ሀብቱ የተላለፈለት ኩባንያም የንግድ ሥራ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ አስተላለፊው የንግድ ሥራ ሀብቱን ለማግኘት ካወጣው ወጪ ጋር እኩል የሆነ ወጪ በማውጣት የንግድ ሥራ ሀብቱን እንዳገኘው ተደርጎ ይወሰዳል፤

   ሐ/ ሀብቱ የተላለፈለት ሰው በተላለፈለት ሀብት ለውጥ አክሲዮን የሰጠ እንደሆነ ለአክሲዮኖቹ የተደረገው ወጪ፣ የተላለፈው ሀብት ማስተላለፍ በሚከናወንበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ ጋር  እኩል መሆን ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የንግድ ሥራ ሀብት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የሆነ እንደሆነ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለንግዱ ሥራ ሀብት የተደረገው ወጪ በሚል የተጠቀሰው የሀብቱ መተላለፍ በሚደረግበት ጊዜ ያለውን የንግድ ሥራ ሀብቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚመለከት ይሆናል፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "እንደገና መደራጀት" ማለት፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ኩባንያዎች መዋሃድ፤

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነውን ኩባንያደድምጽ ሚያሰጥ የአክሲዮን ዋጋ 50% (ሃምሳ በመቶ) ወይም የሌሎች ጠቅላላ የአክሲዮኖች ዋጋ ሃምሳ በመቶ እንደገና በሚደራጀው ኩባንያ አባል የሚሆን ድርጅት በሚያገኘው አክሲዮን ለውጥ ብቻ በማናቸውም መንገድ የተላለፈ እንደሆነ፣

ሐ/ እንደገና በሚደራጀው ኩባንያ ውስጥ አባል ለሆነ ኩባንያ በአክሲዮን ድርሻ ክፍያ ረገድ ልዩ መብት በማያሰጥና የድምጽ ተሳትፎ ብቻ በሚያስገኝ አኳኋን፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ከሆነ እና የእንደገና መደራጀቱ አባል ከሆነ ኩባንያ ሀብት ውስጥ ሃምሳ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ሌላ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የተሰጠ ወይም የተላለፈ እንደሆነ፤

መ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደሆኑ ኩባንያዎች ሲከፋፈል፤ ወይም

ሠ/አንድ የንግድ ሥራ ድርጅት የተቀጽላዎቹን ካፒታል፣ የድርጅቱን ካፒታል ለያዙ ሲያከፋፍል ነው፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን የተደረገው ውህደት፣ በባለቤትነት መያዝ፣ መጠቅለል፣ መከፋፈል ወይም የተቀጽላዎቹን ካፒታል የድርጅቱን ካፒታል ለያዙ የማስተላለፍ ተግባር ዋነኛ ዓላማ ከታክስ ለመሸሽ ያለመሆኑን ሲያምንበት ነው፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የማዕድን እና የነዳጅ ሥራዎች

### 36. ትርጓሜ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በማዕድን ሥራዎች አዋጅ እና በነዳጅ ሥራዎች አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ ምዕራፍ ሥር፡-

1. “ሥራ ተቋራጭ” ማለት ከመንግሥት ጋር የነዳጅ ስምምነት ያደረገ ማንኛውም ሰው ነው፤

2. “የውል ክልል” ማለት በነዳጅ ስምምነት ውስጥ የውል ክልል ተብሎ የተሰየመ አካባቢ ነው፤
3. “መብትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ስምምነት” ማለት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 ተፈፃሚ የሚሆንበት ስምምነት ነው፤
4. “የማልሚያ ወጪ” ማለት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት የሚወጣን ወጪን ሳይጨምር ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ የልማት ሥራዎችን ለመሥራት የሚወጣ የካፒታል ወጪ ሲሆን የሚከተሉትንም ይጨምራል፡፡

   ሀ/ የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን በማናቸውም ጊዜ የሚወጣ ወጪ፡-

      (1) “የፍለጋ ወጪ” ለሚለው ሀረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6)(ሀ)(1) በተሰጠው ትርጉም የተመለከተውን ጥቅም ሳይጨምር፣ በማዕድን ማውጣት ወይም በነዳጅ ሥራ ጥቅም ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፤ ወይም

      (2) “የፍለጋ ወጪ” ለሚለው ሀረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6)(ሀ)(2) በተሰጠው ትርጉም የተመለከተውን ሳይጨምር የማዕድን ማውጣት ወይም የነዳጅ ሥራ መረጃ ለማግኘት የወጣ ወጪ፤

   ለ/ ከማዕድን ማውጣት መብት ወይም ከነዳጅ ስምምነት ጋር በተያያዘ ለማህበራዊ መሠረተ-ልማት ዝርጋታ የሚወጣ ወጪ፣
5. “የልማት ሥራዎች” ማለት፡-

   ሀ/ ለማዕድን ማውጣት ሥራ ሲሆን በማዕድን ማውጣት ሥራ ፈቃድ የተፈቀደ ሥራ፤ ወይም

   ለ/ ለነዳጅ ሥራ ሲሆን ከነዳጅ ሥራ ጋር ተያይዞ ለልማትና ለማምረት በነዳጅ ስምምነት የተፈቀዱ ሥራዎች ናቸው፡፡
6. “የፍለጋ ወጪ” ማለት ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች የሚወጣውን ወጪ ሳይጨምር ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ የምርመራ ሥራዎችን ለማካሄድ የሚወጣ ወጪ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

   ሀ/ የሚከተሉትን ለማግኘት የወጣ ወጪ፡-

      (1) ከመንግሥት ወይም መብትን ከሚያስተላልፍ ስምምነት የፍለጋን መብት የሚመለከት ጥቅም ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፤ ወይም

(2) ከመንግሥት ወይም መብትን ከሚያስተላልፍ ስምምነት የፍለጋ መረጃን ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፣ ወይም

ለ/ ከማዕድን ፍለጋ ሥራ ወይም ከነዳጅ ስምምነት ጋር ተያይዞ ለማህበራዊ መሠረተ-ልማት ግንባታ የሚወጣ ወጪ፣

7. “የፍለጋ መረጃ” ማለት፡-

ሀ/ በማዕድን ፍለጋ መብት ውስጥ የተካተቱ ማዕድናትን ለማግኘት ለሚደረግ ፍለጋ የሚያገለግል መረጃ፣ ወይም

ለ/ በነዳጅ ስምምነት ውስጥ የተካተተን ነዳጅ ለማግኘት ለሚደረግ ፍለጋ የሚያገለግል መረጃ ነው፡፡

8. “የፍለጋ ሥራ” ማለት፡-

ሀ/ ለማዕድን ፍለጋ ሲሆን በማዕድን ፍለጋ መብት ውስጥ የተፈቀደ ሥራ፣ ወይም

ለ/ ለነዳጅ ሥራ ሲሆን በነዳጅ ስምምነት ውስጥ የተፈቀደ የፍለጋ ሥራ ነው፡፡

9. “የፍለጋ መብት” ማለት በማዕድን አዋጅ መሠረት በመንግሥት የተፈቀደ የማዕድን ፍለጋ መብት ወይም በነዳጅ ስምምነት መሠረት የተሰጠ የፍለጋ ፈቃድ ነው፡፡

10. “ፈቃድ የተሰጠበት አካባቢ” ማለት የማዕድን ማውጣት ፈቃድ የተሰጠበት አካባቢ ነው፡፡

11. “ፈቃድ የተሰጠው ሰው” ማለት ማዕድን የማውጣት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

12. “የማዕድን ፍለጋ መብት” ማለት በማዕድን አዋጅ መሠረት የተሰጠ የቅኝት፣ የፍለጋ፣ ወይም ፈቃድን ይዞ የመቆየት መብት ነው፡፡

13. “የማዕድን መረጃ” ማለት ከማዕድን ሥራዎች ጋር የተያያዘ መረጃ ነው፡፡

14. “የማዕድን ሥራዎች” ማለት በማዕድን መብት መሠረት የተፈቀዱ ሥራዎች ናቸው፡፡

15. “የማዕድን መብት” ማለት በማዕድን ሥራዎች አዋጅ መሠረት በመንግሥት የሚሰጥ የቅኝት፣ የምርመራ፣ ፈቃድን ይዞ የመቆየት ወይም የማዕድን ማምረት ፈቃድ ነው፡፡

16.“የነዳጅ ስምምነት” ማለት በነዳጅ ሥራዎች አዋጅ መሠረት አንድ ሰው ከመንግሥት ጋር የሚፈራረመው ስምምነት ነው፡፡
17.“የነዳጅ መረጃ” ማለት ከነዳጅ ሥራዎች ጋር የተያያዘ መረጃ ነው፡፡
18.“የነዳጅ ሥራዎች” ማለት በነዳጅ ስምምነት የተፈቀዱ ሥራዎች ናቸው፡፡
19.“የማህበራዊ መሠረተ-ልማት ወጪ” ማለት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጭ በማዕድን ሥራ መብት ወይም በነዳጅ ስምምነት ባለበት ግዴታ መሠረት የህዝብ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታልን፣ መንገድን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማህበራዊ መሠረተ-ልማት ለመገንባት የሚያወጣው የካፒታል ወጪ ወይም ለማህበረሰብ ልማት ፈንድ የሚያደርገው መዋጮ ነው፡፡
20.“ንዑስ-ሥራ ተቋራጭ” ማለት በተቀጣሪነት አገልግሎት የሚሰጥን ሰው ሳይጨምር ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ከማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሰው ነው፡፡

37.<u>ፈቃድ በተሰጠው ሰው እና ሥራ ተቋራጭ ላይ ግብር ስለመጣል</u>

1. በዚህ ምዕራፍ የተቀመጡት ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ይህ አንቀጽ ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
2. ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ ላይ የሚጣለውን ግብር በተመለከተ በዚህ ምዕራፍ እና በአዋጁ ሌሎች ክፍሎች በተደነገገው መካከል አለመጣጣም የተፈጠረ እንደሆነ ይህ ምዕራፍ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ነው፡፡
4. ፈቃድ የተሰጠው ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ንዑስ-ሥራ ተቋራጭ ከሚፈፅመው ማንኛውም ክፍያ ላይ 10% (አሥር በመቶ) ግብር ቀንሶ ለባለሥልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚከፈለው የግብር መጠን የሚሰላው የሞቢላይዜሽን እና የዲሞቢላይዜሽን ወጪዎች ተቀናሽ ተደርገው ነው፡፡

## 38.በማዕድን ወይም በነዳጅ ሥራዎች ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች ገደብ

1. ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃድ ክልል ውስጥ የማዕድን ማውጣት ሥራ ለመሥራት የሚያወጣው ወጪ በተቀናሽነት የሚያዝለት ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ውስጥ ከማዕድን ሥራ ጋር በተያያዘ በግብር ዓመቱ ካገኘው የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ብቻ ነው፡፡
2. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ውስጥ በግብር ዓመቱ የማዕድን ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ ኪሳራ ያጋጠመው እንደሆነ ይህ ኪሳራ ወደሚቀጥለው የግብር ዓመት ተሸጋግሮ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃድ ክልሉ ውስጥ የማዕድን ማውጣት ሥራ በመስራት ከሚያገኘው የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
3. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ኪሳራውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሙሉ በሙሉ መቀነስ ያልቻለ እንደሆነ ያልተቀነሰውን ኪሳራ ለሚቀጥለው የግብር ዓመት ማሸጋገር እና የተካካሰውን መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተገለጸው መሠረት በዚያው የግብር ዓመት ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ በመቀነስ ኪሣራው ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ተደርጐ እስከሚያልቅ ድረስ ማሸጋገር የሚችል ሲሆን፣ ነገር ግን ፈቃድ የተሰጠው ሰው የደረሰበትን ኪሣራ ኪሣራው ከተከሰተበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ከሚቆጠሩ አሥር የግብር ዓመታት በላይ ማሸጋገር አይችልም፡፡
4. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር በተያያዘ ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ውስጥ ኪሳራ ደረሰበት የሚባለው በፈቃድ ክልል ውስጥ ከሚያከናውነው የማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር በተያያዘ በግብር ዓመቱ በተቀናሽነት የሚያዝለት ወጪ በዚሁ ግብር ዓመት በዚሁ ክልል የማዕድን ማውጣት ሥራ በመሥራት ካገኘው የንግድ ሥራ ገቢ የበለጠ እንደሆነ ነው፡፡
5. ይህ አንቀጽ እንደ አስፈላጊነቱ ማሻሻያ እየተደረገበት በነዳጅ ስምምነት መሠረት ለሥራ ተቋራጩ የተሰጠውን ውል የተገባበት ክልል በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**39.የፍለጋ ወጪ**

1. ለዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 አፈፃፀም፣ ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ ለፍለጋ የሚወጡ ወጪዎች የአገልግሎት ዘመናቸው አንድ ዓመት የሆኑ ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡
2. ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው ለፍለጋ ሥራ የሆነ ዋጋው የሚቀንስ የንግድ ሥራ ሀብት የእርጅና ቅናሽ መጣኔው 100% (መቶ በመቶ) ይሆናል፡፡

**40.የማልሚያ ወጪ**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 አፈፃፀም ሲባል ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የማልሚያ ወጪ ለአራት ዓመታት ያህል የሚያገለግል ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጭ ለንግድ የሚውል ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት የማልሚያ ወጪ ያወጣ እንደሆነ፣ ይህ ወጪ ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት በተጀመረበት ጊዜ እንደወጣ ወጪ ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጭ ለንግድ ሥራ የሚሆን ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት ለማልሚያ ሥራዎች አገልግሎት የሚውል ዋጋው ሊቀንስ የሚችል ሀብት የገዛ ወይም የገነባ እንደሆነ ይህ ሀብት ለንግድ ሥራ የሚሆን ምርት በተጀመረበት ጊዜ እንደተገዛ ወይም እንደተገነባ ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የሚፈቀደው የማልሚያ ወጪ ተቀናሽ መጠን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በእርጅና ምክንያት ዋጋው ለሚቀንስ የንግድ ሥራ ሀብት በግብር ዓመቱ የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሆናል፡-

ሀ× ለ/ሐ

ሀ/ የወጪው መጠን ወይም ለህብቱ የተደረገ ወጪ፣

ለ/ለንግድ ማምረት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ለንግድ ማምረት በተጀመረበት የግብር ዓመት የመጨረሻ ቀን መካከል ያሉት ቀናት፣

ሐ/ ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት በተጀመረበት የግብር ዓመት ያሉት ቀናት ብዛት፣

5. መብትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ስምምነትን ሳይጨምር፣ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከማዕድን ሥራ መብት ውስጥ አንድ ጥቅም ያስተላለፈ እንደሆነ ወይም ደግሞ የሥራ ተቋራጩ በነዳጅ ስምምነት ካገኘው መብት ውስጥ አንድ መብት ወይም ጥቅም ያስተላለፈ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ መብቱን በማስተላለፍ የሚያገኘው ጥቅም ተደርጎ የሚወሰደው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነበት ጊዜ ተቀናሽ የተደረገለትን ወይም በማናቸውም መንገድ ያልመለሰውን ሂሣብ ሳይጨምር ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ ያወጣው የማልሚያ ወጪ ከተቀነሰ በኋላ ነው፡፡

6. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት መጀመር" ማለት የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር በሚወስነው መሠረት ከ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከፍተኛ ምርት ማምረት በተቻለባቸው 25 ቀናት ካሉት 30 ቀናት ውስጥ የመጀመሪያው ቀን ነው፡፡

41.<u>የመልሶ ማቋቋሚያ ወጪ</u>

1. በተፈቀደ መልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጭ ከማዕድን ወይም ከነዳጅ ሥራዎች ጋር ተያይዞ በግብር ዓመቱ ለመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ የሚያደርገው መዋጮ መዋጮው በተደረገበት የግብር ዓመት በተቀናሽነት ይያዛል፡፡

2. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የማዕድን ወይም የነዳጅ ሥራን በሚመለከት በፀደቀ መልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ መሠረት ለሚሰራው ሥራ የሚያወጣው ወጪ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ያልተከፈለው እንደሆነ ወጪው በወጣበት የግብር ዓመት በተቀናሽነት ይያዝለታል፡፡

3. በመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ውስጥ የሚጠራቀም የገንዘብ መጠን ወይም በመልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ መሠረት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ከማቋቋሚያ ፈንድ ወጪ የሚደረግ የገንዘብ መጠን ከገቢ ግብር ነፃ ነው፡፡
4. ከመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ወጪ ሆኖ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ ተመላሽ የተደረገ የገንዘብ መጠን ተመላሽ በተደረገበት የግብር ዓመት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የንግድ ሥራ ገቢ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
5. የመልሶ ማቋቋሚያ ሥራ በሚጠናቀቅት ጊዜ ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጭ የመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ውስጥ ትርፍ የገንዘብ መጠን በሚኖርበት ጊዜ ይህ የገንዘብ መጠን የመልሶ ማቋቋሙ ስራ በተጠናቀቀበት የግብር ዓመት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የንግድ ሥራ ገቢ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
6. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

   ሀ/ “የፀደቀ የመልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ” ማለት በማዕድን መብት ወይም በነዳጅ ስምምነት የሚወሰኑትን ግዴታዎች ጨምሮ የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር የፀደቀ የማዕድን ወይም የነዳጅ ማውጫ ቦታ መልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ ነው፤

   ለ/ “መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ” ማለት በማዕድን መብት ወይም በነዳጅ ስምምነት የተሸፈነውን ክልል ለማስተካከል ለወደፊት የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመሸፈን በማዕድን መብት ወይም በነዳጅ ስምምነት መሠረት መቀመጥ የሚገባው እና የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ በጋራ የሚያስተዳድሩት ገንዘብ ነው፡፡

42.<u>ስለ ኢንቨስትመንት ተቀናሽ</u>

1. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጩ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በተፈቀዱ ሌሎች የልማት መስኮች ወጪ ሆኖ ኢንቨስት ለሚደረግ የኢንቨስትመንት ወጪ ከእያንዳንዱ የግብርዓመት ጠቅላላ ገቢው ላይ እስከ 5%(አምስት በመቶ) መቀነስ ይችላል፡፡

2. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በአንድ የግብር ዓመት ተቀናሽ ያደረገውን የገንዘብ መጠን ተቀናሽ ከተደረገበት የግብር ዓመት ቀጥሎ እስካለው የግብር ዓመት መጨረሻ ድረስ ኢንቨስት ካላደረገ በዚሁ የግብር ዓመት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጭ ጠቅላላ ገቢው ላይ ይደመራል፡፡

43.<u>መብትን ስለማስተላለፍ</u>

1. መብትን ማስተላለፍ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡-

   ሀ/“አስተላላፊ” ተብሎ የሚጠቀሰው ባለፈቃድ ወይም ሥራ ተቋራጭ በማዕድን ማውጣት መብት ወይም በነዳጅ ስምምነት ያገኘውን የተወሰነ መብት “መብት የተላለፈለት” ተብሎ ለሚጠቀሰው ሌላ ሰው ለማስተላለፍ “የማስተላለፍ ስምምነት” ተብሎ የሚጠቀስ ስምምነት ያደረገ እንደሆነ፤

   ለ/ መብቱ የተላለፈለት ሰው ከመብት አስተላላፊው በሙሉ ወይም በከፊል ለተላለፈለት መብት የሚከፍለው ዋጋ መብት የተላለፈለት ሰው ሊከፍል የተስማማበትን ወጪ ወይም መብት አስተላላፊው ካስቀረው የተወሰነ መብት የሚመነጩ የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም ግዴታዎች መብት አስተላላፊውን ተክቶ ለመወጣት የሚገባውን ግዴታም ይጨምራል፡፡

2. መብትን ማስተላለፍ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ፤

   ሀ/ መብት አስተላላፊው ካስቀረው መብት ጋር በተያያዘ መብት የተላለፈለት ሰው የሚያከናውነው ሥራ ዋጋ በሚከተሉት ውስጥ አይካተትም፡-

      (1) መብት አስተላላፊው ለተላለፈው መብት በተቀበለው ዋጋ፤ ወይም

      (2) በመብት አስተላላፊው የንግድ ሥራ ገቢ፤ እና

   ለ/ መብት አስተላላፊው ለተላለፈው መብት በተቀበለው ወይም በሚቀበለው የገንዘብ መጠን ላይ የሚከተሉት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡-

      (1) መብት አስተላላፊው ከተላለፈው መብት ጋር በተያያዘ ላወጣው ወጪ ያገኘው ተቀናሽ ተመላሽ በመደረጉ ምክንያት በተቀበለው

የገንዘብ መጠን ላይ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 73 ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፣

(2) መብት አስተላለፊው ከተቀበለው የገንዘብ መጠን የዚህ አዋጅ አንቀጽ 73 ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆንበት ተቀናሽ ወጪ የበለጠ እንደሆነ በብልጫ የታየው የገንዘብ መጠን የተላለፈው መብት ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

44.<u>የማዕድን ወይም የነዳጅ መብትን በተዘዋዋሪ መንገድ ስለማስተላለፍ</u>

1. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የነበረው ዋና የባለቤትነት መብት ከ10% (ከአስር በመቶ) በላይ የተለወጠ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጩ ይህንኑ ለውጥ ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. በአንድ ድርጅት ውስጥ የአባልነት መብቱን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያስተላልፈው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን ማስታወቂያ መስጠት ያለበት ሰው የኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ሰው ወኪል እንደሆኑ ተቆጥሮ ከማስተላለፉ ጋር ተያይዞ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ግብር የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነውን ሰው በመወከል የከፈሉት ማንኛውም ግብር በዚህ አዋጅ መሠረት በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነው ሰው ላይ ከሚፈለገው የታክስ ዕዳ ጋር ይካካሳል፡፡
4. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለው የአባልነት ጥቅም እንደ ንግድ ሥራ ሀብት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ዓለም ዓቀፍ ግብር

### 45.በውጭ ሀገር የተከፈለን የንግድ ሥራ ግብር ስለማካካስ

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፍልበት ገቢ ያለው እንደሆነ እና በዚሁ ገቢ ላይ በውጭ ሀገር ግብር ከፍሎበት ከሆነ ግብር ከፋዩ በውጭ ሀገር የከፈለው ግብር "በውጭ ሀገር ለተከፈለ ግብር የሚደረግ ማካካሻ" ተብሎ የሚካካስለት ከሚከተሉት ከአነስተኛው መጠን ጋር እኩል የሚሆነው የገንዘብ መጠን ነው፡፡

   ሀ/ በውጭ ሀገር የተከፈለው የገቢ ግብር፤ ወይም

   ለ/ በውጭ ሀገር በተገኘው ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ተከፋይ የሚሆነው የንግድ ገቢ ግብር፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) የተመለከተው የንግድ ገቢ ግብር የሚሰላው በዓመቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነው ግብር ከፋይ ላይ ተፈፃሚ የሚደረገውን አማካይ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔ ግብር ከፋዩ ባገኘው የተጣራ የውጭ ሀገር ገቢ ላይ ተፈፃሚ በማድረግ ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት በውጭ ሀገር የተከፈለ ግብር ሊካካስ የሚችለው፡-

   ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በውጭ ሀገር ባገኘው ገቢ ላይ ሊከፍል የሚገባውን ግብር ገቢው ከተገኘበት የግብር ዓመት በኋላ ባሉት ሁለት የግብር ዓመታት ወይም ደግሞ ባለስልጣኑ በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የከፈለ እንደሆነ፤ እና

   ለ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው ለከፈለው ግብር በውጭ አገር የታክስ ባለሥልጣን የተሰጠ ደረሰኝ ያለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

4. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በግብር ዓመቱ መክፈል የሚኖርበትን የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ሲያሰላ፣ ማንኛውንም የግብር ማካካሻ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በውጭ ሀገር ለተከፈለ ግብር የተፈቀደውን ማካካሻ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

5. በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በውጭ ሀገር የከፈለው ግብር በዚያው የግብር ዓመት ሙሉ በሙሉ የማይካካስ የሆነ እንደሆነ ሳይካካስ የቀረው ግብር ተመላሽ ሊደረግ ወይም ወደቀደመው

የግብር ዓመት ሊመለስ ወይም ወደሚቀጥለው የግብር ዓመት ሊሸጋገር አይችልም፡፡

6. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

ሀ/ “አማካይ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም የግብር ማካካሻ ከመደረጉ በፊት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው የግብር ዓመቱ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተግባራዊ የሚሆነው መጣኔ ነው፤

ለ/ “የውጭ ሀገር ገቢ ግብር” ማለት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ግብር ጨምሮ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር አካባቢያዊ መንግሥት የተጣለ ግብር ሲሆን፣ ቅጣትን፣ ተጨማሪ ታክስን፣ ወይም ደግሞ ይህንን ግብር በሚመለከት የሚከፈል ወለድን አይጨምርም፤

ሐ/ “የተጣራ የውጭ ሀገር ገቢ” ማለት በአንድ የግብር ዓመት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነን ግብር ከፋይ በሚመለከት በዚህ ሰንጠረዥ መሠረት ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ የውጭ ሀገር ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት የሚፈቀደው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረገው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ገቢ ነው፤

1) የውጭ ሀገር ገቢውን ለማግኘት ሲባል ብቻ ወጪ የተደረገ፤ እና

2) በውጭ ሀገር የሚገኝ ገቢ እራሱን የቻለ የገቢ ዓይነት ሆኖ የሚመደብ በመሆኑ የውጭ ሀገር ገቢውን ለማግኘት በወጣው መጠን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 76 መሠረት የተከፋፈለ ሲሆን፡፡

46.<u>የውጭ ሀገር የንግድ ሥራ ኪሳራዎች</u>

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን የውጭ ሀገር ገቢን ለማግኘት ያወጣው ወጪ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀናሽ የሚደረግለት በውጭ ሀገር ካገኘው ገቢ ላይ ብቻ ነው፡፡

2. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት በውጭ ሀገር ኪሳራ ያጋጠመው እንደሆነ ኪሳራው ከደረሰበት የግብር ዓመት ቀጥሎ ላለው የግብር ዓመት የሚሸጋገር ሆኖ ይህም ኪሳራ በተሸጋገረበት የግብር ዓመት

ግብር ከፋዩ በውጭ ሀገር ካገኘው ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

3. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ግብር ከፋይ ኪሳራውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል መቀነስ ያልቻለ እንደሆነ ኪሳራው በሙሉ ተቀንሶ እስከሚያልቅ ድረስ ወደሚቀጥሉት የግብር ዓመታት ተሸጋግሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተቀናሽ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግብር ከፋዩ ኪሳራው ከደረሰበት የግብር ዓመት በኋላ ካሉት አምስት የግብር ዓመታት በላይ ኪሳራውን ለማሸጋገር አይችልም፡፡
4. ግብር ከፋዩ የውጭ ሀገር ኪሳራ ያስተናገደባቸው ሁለት የግብር ዓመታት የኖሩ እንደሆነ እና እያንዳንዱ ኪሳራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2) መሠረት የተሸጋገረ እንደሆነ ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተጨማሪ ኪሳራዎችን ለማሸጋገር አይፈቀድለትም፡፡
5. አንድ ግብር ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተመለከቱትን የውጭ ሃገር ኪሳራዎች ሊያሸጋግር የሚችልበት ዝርዝር የአፈፃፀም ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
6. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም በአንድ የግብር ዓመት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነን ግብር ከፋይ በሚመለከት፣ “በውጭ ሀገር የደረሰ ኪሳራ” ማለት ግብር ከፋዩ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን የውጭ ሀገር ገቢ ለማግኘት ያወጣቸው ወጪዎች መጠን ከጠቅላላው የውጭ ሀገር ገቢ በልጦ ሲገኝ ነው፡፡

**47.<u>ለኩባንያ ካፒታል የሚወሰድ ብድር</u>**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፋይናንስ ድርጅቶችን ሳይጨምር በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለና በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ የግብር ዓመቱ አማካይ ዕዳ ከአማካይ የካፒታል መዋጮ ከ2 ለ 1 የበለጠ እንደሆነ ኩባንያው ለወለድ ክፍያ ያወጣው ወጪ ከዚህ በታች በተመለከተው ስሌት መሠረት በተቀናሽ እንዳይያዝለት ይደረጋል፡፡

$ሀ \times {}^{ለ}/_{ሐ}$

በዚህ ስሌት

ሀ/ ኩባንያው በግብር ዓመቱ ተቀናሽ እንዲደረግለት የሚጠይቀው የወለድ ወጪ፤

ለ/ኩባንያው ከተፈቀደው መጠን በላይ የወሰደው ብድር፤ እና

ሐ/ ኩባንያው በግብር ዓመቱ ያለበት አማካይ ዕዳ፤

2. በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ አማካይ ዕዳ እና አማካይ የካፒታል መዋጮ በግብር ዓመቱ ከ2 ለ 1 የበለጠ እንደሆነ እና የኩባንያው የግብር ዓመቱ አማካይ ዕዳ ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች ከተወሰደው ዕዳ የማይበልጥ ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት በኢትዮጵያ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ባለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ኩባንያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡-

ሀ/በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በውጭ አገር ባለ አክሲዩኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ሆኖ ይቆጠራል፤ እና

ለ/በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካይ ዕዳ እና አማካይ የካፒታል መዋጮ የሚከተለውን መሠረት በማድረግ ይሰላል፡-

(1) በቋሚነት ለሚሠራው ድርጅት የዋለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ የወሰደው ብድር፤ እና

(2) በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ ለሥራው ማንቀሳቀሻ የመደበውና በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ሥራ ላይ የዋለው የካፒታል መዋጮ፤

4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

ሀ/ "ግንኙነትከሌላቸው ሰዎች የተወሰደ ዕዳ" ማለት በውጭአገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት አንድ የፋይናንስ ተቋም ኩባንያው የሚገኝበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ግብይት አኳኋን ሊያበድረው የሚችለው ገንዘብ ነው፤

ለ/ "አማካይ ዕዳ" ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት በግብር ዓመቱ ውስጥ የወሰደው በሚከተለው ቀመር ስሌቱ የሚከናወን ዕዳ ነው፡፡

$^{U}/_{12}$

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

ሀ-በሚቀጥለው የግብር ዓመት ውስጥ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻባንያው የሚፈለግበት ጠቅላላ የዕዳ መጠን ነው፡፡

ሐ/ "አማካይ የካፒታል መዋጮ" ማለት፣ በውጭ አገር ባለ አክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተከፈለ በሚከተለው ቀመር ስሌቱ የሚከናወን የካፒታል መዋጮ ነው፡፡

$^{U}/_{12}$

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም ፡-

ሀ-በሚቀጥለው የግብር ዓመት ውሰጥ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ለኩባንያው የተደረገ ጠቅላላ የካፒታል መዋጮ መጠን ነው፡፡

መ/ "ዕዳ" ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በሚወሰነው መሠረት ወለድ የሚከፈልበት የኩባንያው ዕዳ የመክፈል ግዴታ ነው፡፡

ሠ/ "ዕዳ የመክፈል ግዴታ" ማለት ከቃል ኪዳን ሰነድ፣ ከሀዋላ፣ እና ከቦንድ የሚመጣን ግዴታ ጨምሮ ለሌላ ሰው ገንዘብ መልሶ የመክፈል ግዴታ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

(1) ተከፋይ ሂሳቦችን፤ ወይም

(2) ወለድየመክፈልግዴታንየማያስከትል ማናቸውንም ገንዘብ መልሶ የመክፈል ግዴታ፤

ረ/ "የካፒታል መዋጮ" ማለት በውጭ አገር ባለ አክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ የወለድ ክፍያን የማይጨምር

ዕዳን መልሶ የመክፈልን ግዴታ የሚያስከትል ብድርን ጨምሮ በሂሳብ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት በግብር ዓመቱ ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ተመዝግቦ የሚገኝ ከፍተኛው የኩባንያው የካፒታል መዋጮ ነው፡፡

ሰ/ "በብልጫ የታየ ዕዳ" ማለት በውጭ አገር ባለ አክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በግብር ዓመቱ ውስጥ ኩባንያው ያለበት አማካይ ዕዳ በ2 ለ 1 ቀመር መሠረት ከተፈቀደለት ከፍተኛው አማካይ ዕዳ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን ነው፡፡

ሸ/ "በውጭ አገር ባለ አክሲዮኖች ቁጥጥር ሥር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ" ማለት ከኩባንያው የአባልነት ጥቅም መካከል ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በላይ የሚሆነው በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆኑ ሰዎች ግንኙነት ካለው ወይም ካላቸው ሰዎች ጋር በመሆን የተያዘ ኩባንያ ነው፡፡

## 48. ግብርን በሚመለከት የሚደረጉ ስምምነቶች

1. ሚኒስትሩ ግብርን የሚመለከቱ ስምምነቶችን ከውጭ ሀገር መንግሥት ወይም መንግሥታት ጋር ሊፈራረም ይችላል፡፡
2. የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና የዚህን አዋጅ ክፍል ስምንት ድንጋጌዎች ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈፃሚነት ባለው የግብር ስምምነት የውል ቃላትና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መካከል አለመጣጣም የተፈጠረ እንደሆነ የስምምነቱ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢትዮጵያ የፈረመችው የግብር ስምምነት በኢትዮጵያ የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ወይም በግብር ውስጥ የማይካተት መሆኑን የሚደነግግ ወይም የስምምነቱ ተፈፃሚነት በኢትዮጵያ ያለውን የግብር መጣኔ የመቀነስ ውጤት የሚኖረው ከሆነ፣ በተዋዋዩ አገር ነዋሪ የሆነው ድርጅት የባለቤትነት ወይም የመቆጣጠር ድርሻ ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በላይ በተዋዋይ ሀገር ነዋሪ ባልሆነ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች የተያዘ በሚሆንበት ጊዜ ይህ ድርጅት በስምምነቱ የተቋቋመው ከግብር ነፃ የመሆን፣ በግብር ውስጥ ያለመካተት ወይም የተቀነሰው የግብር መጣኔ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

4. ከኢትዮጵያ ጋር በተዋዋለው ሀገር ነዋሪ የሆነው ግብር ከፋይ፡-
   ሀ/ በተዋዋዩ ሀገር በአክሲዮን ገበያ ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ኩባንያ ከሆነ፤ ወይም
   ለ/ በተዋዋዩ ሀገር በሚገባ በሚንቀሳቀስ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ እንደሆነና በኢትዮጵያ ለተገኘው ገቢ ምንጭ የሆነው ይኸው የንግድ ሥራ የሆነ እንደሆነ፤

   የዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ(3) ድንጋጌተፈፃሚ አይሆንም፡፡

5. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-
   ሀ/ "በሚገባ የሚንቀሳቀስ ንግድ ሥራ" ማለት ኩባንያው የገንዘብ ተቋም ወይም የኢንሹራንስ ኩባንያ ካልሆነ በስተቀር የአክሲዮን፣ የዋስትና ሰነዶች፣ ወይም ሌሎች ኢንቨስትመንቶች ባለቤት መሆንን ወይም ማስተዳደርን አይጨምርም፤
   ለ/ “የግብር ስምምነት” ማለት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረትና ታክስ ላለመክፈል የሚደረግን ስወራ ለመከላከል የሚደረግ ዓለም ዐቀፍ ስምምነት ነው፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## በግምት ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥራ ግብር

### 49.የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች ስለሚከፍሉት የገቢ ግብር

የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች በእያንዳንዱ የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚከፍሉት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው የግብር አከፋፈል ዘዴ ነው፡፡

### 50.በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት ንግድ የሚሰሩ ሰዎችን ግብር ስለማስከፈል

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እና ዓለም ዐቀፍ የአየር ትራንስፖርት ንግድ ሥራ የሚሰራ ሰው መዳረሻቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆኑ መንገደኞችን፣ እንስሳትን፣ ፖስታን፣ ሸቀጦችን ወይም ዕቃዎችን ከኢትዮጵያ ውስጥ በመጫን ያጓጓዘ እንደሆነ ከዚህ ስራ ከሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ 3% (ሶስት በመቶ) የንግድ ስራ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡

2. ይህ አንቀጽ ለሚከተሉት ተፈፃሚ አይሆንም፡-

ሀ/ከግብር ነፃ ለሆነ የገንዘብ መጠን፤

ለ/ከሚከተሉት ጋር በተገናኘ የሚገኝ የገንዘብ መጠን ፡-

(1) ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ሁለት ቦታዎች መካከል በሚደረግ ጉዞ መንገደኛው ኢትዮጵያን እንደ መሸጋገሪያ ሲጠቀም፤

(2) መጓጓዣዎችን በመቀያየርእንስሳትን፣ መልዕክትን፣ ዕቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ማጓጓዝ፤

## ክፍል አምስት

## ሠንጠረዥ “መ” - ሌሎች ገቢዎች

### 51.በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች ገቢ

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የትርፍ ድርሻ፣ ወለድ፣ ሮያሊቲ፣ የሥራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ወይም የመድን አረቦን ከኢትዮጵያ ውስጥ ያገኘ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መጣኔ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር የሚከፍልበት መጣኔ፡-

ሀ/ ለመድህን በሚከፈል አረቦን ወይም ከሮያሊቲ ጠቅላላው ክፍያ ላይ 5% (አምስት በመቶ) ፤

ለ/ ከትርፍ ድርሻ ወይም ከወለድ፣ ጠቅላላ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ) ፤

ሐ/ከስራ አመራር ክፍያ ወይም ከቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ከጠቅላላ ገቢው ላይ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ፤

3. የትርፍ ድርሻ፣ የወለድ፣ የሮያሊቲ፣ የስራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ወይም የመድን አረቦን ገቢ የተገኘው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያከናውነው የንግድ ሥራ የሆነ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ እነዚህ ገቢዎች እንደሁኔታው በሰንጠረዥ "ሐ" ወይም "መ" መሠረት ግብር ይከፈልባቸዋል፡፡

**52.እንዲተካ በተጠየቀ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ እና ሮያልቲ ላይ ስለሚከፈል ግብር**

1. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ሳይሆን በራሱ የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የመሣሪያ ኪራይ (ሊዝ) አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ፤

ለ/ የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የመሣሪያ ኪራይ (ሊዝ) አገልግሎት የተሰጠው ("አገልግሎት ተቀባይ" ተብሎ የሚጠቀሰው) ሰው፤

(1) ከኢትዮጵያ ውጪ ባለ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የሚያከናውነውን የንግድ ሥራ ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ከሆነ፤ ወይም

(2) በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እና በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ፤

ሐ/ ከአቅርቦቱ ወይም ከሊዙ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነው ሰው የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የሮያሊቲ ክፍያ የተከፈለው ከአገልግሎት ተቀባዩ ጋር ግንኙነት ባለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው የሆነ እንደሆነ፤

መ/ ግንኙነት ያለው ሰው የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የሮያሊቲ ክፍያውን ከአገልግሎት ተቀባዩ የጠየቀ እንደሆነ፤

2. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ ግንኙነት ያለው ሰው ለአገልግሎቱ ተቀባይ የቴክኒክ አገልግሎቱን ወይም የመሣሪያውን ሊዝ አገልግሎት እንደሰጠ ተቆጥሮ እንዲሁም እንዲተካ የተጠየቀው ገንዘብ ለቴክኒክ አገልግሎቱ ወይም ለመሣሪያው ሊዝ የተከፈለ ክፍያ እንደሆነ ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**53.በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪዎች ግብር**

1. በኢትዮጵያ በሚካሄድ የመዝናኛ አገልግሎት ተግባር ላይ ተሳታፊ የሚሆን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ወይም ቡድን ከመዝናኛ አገልግሎት በሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ 10% ግብር ይከፍላል፡፡

2. በቡድን አባልነት የሚገኝን ገቢ ጨምሮ ከመዝናኛ አገልግሎት የሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ አዝናኙ ሳይሆን ሌላ ሰው የሆነ እንደሆነ ይህ ሰው በሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-
   ሀ/ "የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪ" ስፖርተኛን እና ሙዚቀኛን ይጨምራል፤
   ለ/ "ቡድን" የስፖርት ክለብን (ቡድንን) ይጨምራል፤
   ሐ/ "የመዝናኛአገልግሎት"የስፖርትውድድርን ይጨምራል፡፡

54.<u>ሮያሊቲ</u>

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ሮያሊቲ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላ የሮያሊቲ ክፍያ ላይ 5% (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሮያሊቲ ገቢ ሲያገኝ በጠቅላላ የሮያልቲ ክፍያ ላይ 5% (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

55.<u>የትርፍ ድርሻ</u>

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነና የትርፍ ድርሻ ያገኘ ሰው በጠቅላላው የትርፍ ድርሻ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ) የትርፍ ድርሻ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ የትርፍ ድርሻ ገቢ ሲያገኝ በጠቅላላ የትርፍ ገቢው ላይ 10% (አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

56.<u>ወለድ</u>

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነና ወለድ ያገኘ ሰው፡-
   ሀ/ ወለዱን ያገኘው በገንዘብ ተቋማት ገንዘቡን በቁጠባ አስቀምጦ ሲሆን በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ 5% (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፤

ለ/ በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ወለድ የሚያገኝ ከሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፤

2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ የወለድ ገቢ ሲያገኝ፡-

ሀ/ ወለዱን ያገኘው በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነ የገንዘብ ተቋም ገንዘቡን በቁጠባ አስቀምጦ ሲሆን በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ 5% (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፤

ለ/ በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ወለዱን የሚያገኝ ከሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፤

57.<u>ከዕድል ሙከራ የሚገኝ ገቢ</u>

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረጉ የዕድል ሙከራዎች ተሳትፎ ገቢ ያገኘ ሰው ባሸነፈው ጠቅላላ ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በዕድል ሙከራ አሸናፊነት የተገኘው ገቢ ሲሰላ ገቢውን ያገኘው ሰው የዕድል ሙከራውን ሲያከናውን የደረሰበት ኪሳራ ተቀናሽ አይደረግለትም፡፡
3. በዕድል ሙከራ የተገኘው ገንዘብ ከ1000 ብር (አንድ ሺህ ብር) በታች ሲሆን የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚ አይሆንም፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የዕድል ሙከራ" ማለት የጨዋታው ውጤት በተሳታፊው ችሎታ ሳይሆን በዋነኝነት በዕድል ላይ የተመሰረተ ሲሆን ሎተሪንና ቶምቦላንም ይጨምራል፡፡

58.<u>ሀብትን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚገኝ ገቢ</u>

1. በኢትዮጵያ ውስጥ አልፎ አልፎ ሀብት (ማንኛውንም መሬት፣ ቤት፣ ወይም የሚንቀሳቀስ ሀብት) በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ሰው ከጠቅላላው የኪራይ ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የኪራይ ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 51 ወይም 54 መሠረት የሮያሊቲ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

59.<u>የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም</u>

1. አንድ ሰው “ግብር የሚከፈልበት ሀብት” ተብሎ የሚጠቀስን የማይንቀሳቀስ ሀብት፣ አክሲዮን ወይም ቦንድ በማስተላለፍ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በተገኘው ጥቅም ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መጣኔ መሠረት የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚከፈለው ግብር ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው መጣኔ፡-
   ሀ/ ለምድብ ሀ ግብር የሚከፈልባቸው ሀብቶች 15% (አሥራ አምስት በመቶ)፤
   ለ/ ለምድብ ለ ግብር የሚከፈልባቸው ሀብቶች 30% (ሠላሳ በመቶ) ይሆናል፡፡
3. ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ የሚገኘው ጥቅም ሀብቱን በማስተላለፍ የተገኘው ዋጋ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ በልጦ የተገኘው የገንዘብ መጠን ነው፡፡
4. በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ አንድ ሰው በግብር ዓመቱ ውስጥ አንድን ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲያስተላልፍ ኪሳራ የደረሰበት እንደሆነ ኪሣራው በዚያው የግብር ዓመት በተመሳሳይ ምድብ ያለ ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲተላለፍ ከሚገኘው ገቢ ጋር እንዲቻቻል ይደረጋል፡-
   ሀ/ ኪሳራው የሚውለው በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገኘን ገቢ ለማቻቻል ነው፤
   ለ/ ያልተቻቻለው ኪሳራ ተቻችሎ እስከሚያልቅ ድረስ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ ያለ ሀብት በሚተላለፍበት ጊዜ ለማካካስ እንዲውል ላልተወሰነ ጊዜ ይሸጋገራል፤
   ሐ/ አንድ ሰው ግንኙነት ላለው ሰው ሀብት ያስተላለፈ እንደሆነ የደረሰው ኪሳራ ዕውቅና አይሰጠውም፤
   መ/ አንድ ሰው የደረሰበትን ኪሳራ ባለስልጣኑን በሚያሳምን መንገድ ማስረዳት የቻለ እንደሆነ ነው፡፡

5. ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ የደረሰው ኪሳራ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ለሀብቱ የወጣው ወጪ ሀብቱ ከተላለፈበት ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን ነው፡፡
6. የተላለፈው ግብር የሚከፈልበት ሀብት የንግድ ሥራ ሀብት በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
7. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

   ሀ/ "የማይንቀሳቀስ ሀብት" ሕንፃው ከመተላለፉ በፊት ለሁለት ዓመታት ሙሉ በሙሉ ለመኖሪያነት ያገለገለ ሕንፃን አይጨምርም፤

   ለ/ "ምድብ "ሀ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት" ማለት የማይንቀሳቀስ ሀብት ማለትነው፤

   ሐ/ "ምድብ "ለ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት" ማለት አክሲዮኖችና ቦንዶች ማለት ነው፡፡

## 60. <u>ንፋስ አመጣሽ ትርፍ</u>

1. ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከቱ የንግድ ሥራዎች የሚገኝ ንፋስ አመጣሽ ትርፍ በመመሪያው በተመለከተው የማስከፈያ ልክ ግብር ይከፈልበታል፡፡
2. ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ፡-

   ሀ/ ንፋስ አመጣሽ ትርፍ ነው ሊባል የሚችለው የገቢ መጠን፤

   ለ/ በንፋስ አመጣሽ ትርፍ ላይ የተጣለውን ግብር ሊከፍሉ የሚገባቸውን የንግድ ሥራዎች ዓይነት፤

   ሐ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈለው ግብር ሥራ ላይ የሚውልበትን ቀን፤

   መ/ የግብር አወሳሰኑን ዘዴ እና ለግብሩ አወሳሰን መሠረት የሚሆኑ ታሳቢዎችን፣

   እንዲወስን ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
3. ሚኒስትሩ የንግድ ሥራ ባህሪያትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች ንፋስ አመጣሽ ትርፍ የሚባለው የገንዘብ መጠን እንዲለያይ ለማድረግ እንዲሁም የተለያየ የግብር ማስከፈያ ልክ ለመወሰን ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ "ንፋስ አመጣሽ ትርፍ" ማለት ማንኛውም ያለ ልፋት የሚገኝ፣ ያልተጠበቀ ወይም ሌላ ተደጋግሞ የማይገኝ ትርፍ ነው፡፡

61.<u>ያልተከፋፈለ ትርፍ</u>

ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በአንድ የግብር ዓመት ግብር ከተከፈለ በኋላ ለአባላቱ ያልተከፋፈለ እና መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ 10% (አሥር በመቶ) ግብር ይከፈልበታል፡፡

62.<u>በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት የሚላክ ትርፍ</u>

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያከናውን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት በሚላክለት ትርፍ ላይ 10% (አሥር በመቶ) ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም የሚመራው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

63.<u>ሌሎች ገቢዎች</u>

በሠንጠረዥ ሀ፣ ለ፣ ሐ እና በዚህ ሠንጠረዥ ሌሎች አንቀጾች መሠረት የገቢ ግብር የማይከፈልበት ማንኛውንም ገቢ ያገኘ ሰው በጠቅላላ ገቢው ላይ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

64.<u>ከሠንጠረዥ “መ” ጋር የተያያዙ ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. በሠንጠረዥ “መ” መሠረት የሚጣል ግብር፡-

   ሀ/ በሌሎች ሠንጠረዦች ሥር ግብር ለሚከፈልበት ገቢ፤ ወይም

   ለ/ ከገቢ ግብር ነፃ በሆኑ ገቢዎች፤

ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

2. በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት የሚጣለው ግብር በገቢው ላይ የመጨረሻ ግብር ይሆናል፡፡
3. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ያገኘው የሮያሊቲ፣ የትርፍ ድርሻ፣ የወለድ ወይም በአንቀጽ 63 የተመለከተውን ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ ያገኘው ገቢ ከውጭ ሀገር የተገኘ እንደሆነ፣ ይህ ሰው በዚህ ሠንጠረዥ ከሚከፈለው ገቢ ላይ በውጭ ሀገር በዚሁ ገቢ ላይ የከፈለው ግብር ከዜሮ በታች ሳይወርድ ተቀናሽ እንዲደረግ ይፈቀድለታል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተቀናሽ ያልተደረገን ግብር ለማሸጋገር አይቻልም፡፡
5. ግብርን ቀንሶ የመያዝ ኃላፊነት ያለበት ሰው በዚህ አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ግብሩን ቀንሶ ያስቀረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51፣ 52፣ 53፣ 54፣ 55፣ 56 ወይም 57 በተመለከተው መሠረት ግብር ከፋዩ ያለበትን ግብር የመክፈል ግዴታ እንደተወጣ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ሠንጠረዥ "ሠ" - ከገቢ ግብር ነፃ የሆነ ገቢ

### 65.ከገቢ ግብር ነፃ የሆነ ገቢ

1. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው፡-

ሀ/ ሚኒስትሩ በዚህ ፊደል ተራ በቁጥር (2) ፣ (3) ፣ (4) እና (6) በተመለከቱት ላይ በሚያወጣው መመሪያ የሚያደርገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለተቀጣሪው የሚከፈሉ የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው፡-

(1) ሠራተኛው ሲታመም አሠሪው ለሠራተኛው ህክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ፤

(2) በሥራ ውል መሠረት ለሠራተኛው የሚከፈል የትራንስፖርት አበል፤

(3) በሥራ ቦታው ወይም በሥራ ሁኔታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለሠራተኛው የሚከፈል አበል፤

(4) ሠራተኛው ከመደበኛ ሥራው ውጪ ሥራውን ለማከናወን ሲንቀሳቀስ የሚከፈለው የመጓጓዣ ወጪ እና የውሎ አበል፤

(5) የመጓጓዣ ወጪው በቅጥር ውሉ መሠረት የተከፈለ ከሆነ ከሥራ ቦታው ውጪ ተመልምሎ ለተቀጠረ ሠራተኛ ወደ ሥራው ሲመጣ ወይም ሥራውን አጠናቆ ሲመለስ የሚከፈለው የመጓጓዣ ወጪ፣ እንዲሁም የውጭ ሀገር ሠራተኞች ከሀገራቸው ሲመጡና ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ የሚከፈል የመጓጓዣ ወጪ፤

(6) የማዕድን ማውጣት፣ የማኑፋክቸሪንግ እና የግብርና የንግድ ሥራ የሚሠራ ቀጣሪ ለተቀጣሪው በነፃ የሚያቀርበው ምግብና መጠጥ፤

(7) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በውጭ አገር ለሚመድባቸው ሠራተኞች የሚከፈል አበል፤

ለ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወይም የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የቦርድ አባል ወይም ፀሐፊ እንዲሁም የፌደራልና የክልል መንግሥታት ወይም የከተማ አስተዳደሮች በሚያቋቁሟቸው የጥናት ቡድኖች አባል ወይም ፀሐፊ በመሆን የሚከፈል አበል፤

ሐ/ ለሠራተኛው ጥቅም ተብሎ ከተቀጣሪው የወር ደመውዝ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ባልበለጠ መጠን በየወሩ በቀጣሪው የሚዋጣ የጡረታ መዋጮ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ፤

መ/ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ እና በግል ድርጅት ሠራተኞችየጡረታ አዋጅ ከግብር ነፃ የተደረገ የጡረታ ገቢ፤

ሠ/ የኢትዮጵያ የፌደራል፣ የክልል ወይም የአካባቢ መንግሥታት ወይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከመደበኛ ሥራዎቻቸው ጋር በተያያዘ የሚያገኙት ገቢ፤

ረ/ በዓለም ዐቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነፃ የሆነ የገቢ መጠን፤

ሰ/ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በተደረገ ስምምነት (ከዚህ በኋላ "ከግብር ነፃ ማድረግ የሚያስችል አንቀጽ" ተብሎ የሚጠቀስ) መሠረት ማናቸውም ገቢ ከግብር ነፃ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡-

(1) ስምምነቱ የተደረገው ለመንግሥት የገንዘብ፣ የቴክኒክ፣ ሰብአዊ ወይም አስተዳደራዊ እርዳታ ለማቅረብ የሆነ እንደሆነ፤

(2) ከግብር ነፃ ማድረግ የሚያስችለውን አንቀጽ በሚመለከት ሚኒስትሩ መስማማቱን በጽሁፍ ሲገልጽ፤

ሸ/ በማንኛውም መስክ ለላቀ የሥራ ክንውን ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅአንቀጽ 135 መሠረት የሚሰጥ ሽልማት፤

ቀ/ በተቀባዩ ላይ በደረሰ ጉዳት ወይም በሌላ ሰው ሞት ምክንያት የሚከፈል ካሳ፤

በ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 59 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ስጦታው የመቀጠር፣የኪራይ ወይም የንግድ ሥራ ገቢ ካልሆነ በስተቀር በስጦታ ወይም በውርስ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ወይም ሀብት፤

ተ/ በትምህርት ተቋም ውስጥ ትምህርትን በነፃ ለመከታተል የሚፈፀም ክፍያ፤

ቸ/ ለቀለብ ወይም ለህፃናት ድጋፍ የሚሰጡ ክፍያዎች፤

ኀ/ ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር የማይገናኝ የንግድ ሥራ ገቢን ሳይጨምር ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የሚያገኘው ገቢ፤

ነ/ ገንዘብ በሚቆጠርበት ጊዜ ለሚደርሰው ጉድለት ማካካሻ በሚሆን መጠን ብቻ ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚከፍለው እና ለዚሁ ዓላማ መዋሉ የተረጋገጠ የጥሬ ገንዘብ ማካካሻ ክፍያ፤

ኘ/ በኢትዮጵያ ፀንቶ በሚሰራበት ሕግ መሠረት በተለይ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረገ ገቢ፤

አ/ ለመኖሪያ ቤት ሠራተኞች የሚከፈል ደመወዝ፤

ከ/ በነዳጅ ሥራ ላይ የተሰማራ ሥራ ተቋራጭ ለንዑስ ሥራ ተቋራጮች የሚፈፀመው ክፍያ፡፡

2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ለኢኮኖሚ፣ ለአስተዳደራዊ ወይም ለማህበራዊ ምክንያቶች አንድን ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>የወል ድንጋጌዎች</u>

## <u>ምዕራፍ አንድ</u>

## <u>ሀብት</u>

### 66.<u>ሀብት ስለማግኘት</u>

አንድ ሰው ሀብት አገኘ የሚባለው ሕጋዊ የሀብት ባለቤትነት ስም ከተላለፈለት ጊዜ አንስቶ ሲሆን ሀብቱ መብት ወይም ምርጫ በሚሆንበት ጊዜ ይህ መብት ወይም ምርጫ የተሰጠበትንም ጊዜ ይጨምራል፡፡

## 67.ሀብትን ስለማስተላለፍ

1. አንድ ሰው ሀብቱን አስተላለፈ የሚባለው ሀብቱን ሲሸጥ፣ ሲለውጥ ወይም በሌላ መንገድ በሀብቱ ላይ ያለውን የባለቤትነት ስም ሲያስተላልፍ ሲሆን፣ ሀብቱ እንዲሠረዝ፣ ለቀድሞ ባለቤቱ እንዲመለስ፣ እንዲጠፋ፣ እንዲወድም፣ ጊዜው እንዲያልፍ ወይም ለሌላ ተላልፎ እንዲሠጥ ማድረግን ይጨምራል፡፡
2. ማናቸውም ሰው ከዚህ ቀደም ያልነበረ ሀብት የሌላ ሰው ሀብት እንዲሆን ያደረገ እንደሆነ፣ ይህንን ያደረገው ሰው ሀብቱ በተፈጠረበት ጊዜ በባለቤትነቱ ስም የነበረን ሀብት ለሁለተኛው ሰው እንዳስተላለፈ ይቆጠራል፡፡
3. አንድ ሀብት በውርስ ወይም በኑዛዜ ከተላለፈ፣ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ሟቹ ሀብቱን እንዳስተላለፈ ይቆጠራል፡፡
4. ሀብትን ማስተላለፍ የአንድን የንግድ ሥራ ሀብት የተወሰነ ክፍል ማስተላለፍንም ይጨምራል፡፡
5. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአንድን ሰው ሀብት ("ባለቤቱ" ተብሎ የሚጠቀስ) ለአጣሪ፣ በኪሣራ ሂደት ለተሰየመ ባለአደራ፣ ወይም ለተቀባይ መስጠት ሀብቱን እንደ ማስተላለፍ የማይቆጠር ሲሆን ከሀብቱ ጋር ተያይዞ በአጣሪው፣ በባለአደራው ወይም በተቀባዩ የሚከናወኑ ተግባራት ባለቤቱ እንዳከናወናቸው ይቆጠራሉ፡፡

## 68.ለሀብት የሚደረግ ወጪ

1. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶችን ሳይጨምር የአንድ ሀብት ወጪ የሚከተሉት ድምር ይሆናል፡-

   ሀ/ ሀብቱ በተገኘበት ጊዜ በዓይነት የሚሰጥን ሀብት ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ጨምሮ፣ ባለሀብቱ ለሀብቱ የከፈለው ዋጋ ሲሆን ሀብቱ የተገነባ፣ የተመረተ፣ ወይም የለማ እንደሆነ ለግንባታ፣ ለማምረት ወይም ለማልማት የወጣውን ወጪ ይጨምራል፤

   ለ/ ሀብቱን በማግኘት፣ በማስተላለፍ ሂደት የወጣ ማንኛውም ወጪ፤

   ሐ/ ሀብቱን ለመትከል፣ ለመቀየር፣ ለማደስ፣ መልሶ ለመገንባት ወይም ለማሻሻል ባለሀብቱ ያወጣው ማንኛውም ወጪ፤

2. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት ወጪ ነው የሚባለው፡-
   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ (7) (ሀ) (1)፣ (2) ወይም (3) "ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት" ለሚለው ሀረግ በተሰጠው ትርጉም ከተመለከቱት ግዙፋዊ ሀልዎት ከሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ጋር በተያያዘ እነዚህን ሀብቶች ለማግኘት፣ ለመፍጠር፣ ለማሻሻል እና ለማደስ እንዲሁም እነዚህን ሀብቶች ለማግኘት ወይም ለማስተላለፍ የሚወጣ ሌላ ተጓዳኝ ወጪ፤
   ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ (7) (ሀ) (4) "ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት" ለሚለው ሀረግ በተሰጠው ትርጉም ውስጥ ከተመለከተው ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት ጋር በተያያዘ የወጣ ወጪ ነው፤
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70(2) በተደነገጉት ሁኔታዎች መሠረት በስጦታ የሚገኝ ሀብት ወጪ ሀብቱ በስጦታ በተገኘበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው፡፡
4. የአንድ ሀብት ዋጋ በዚህ አዋጅ ተቀናሽ እንዲደረግ የተፈቀደውን ማንኛውንም ወጪ አይጨምርም፡፡
5. የአንድ ሀብት ዋጋ የሀብቱ ባለቤት ሀብቱን የማግኘት ምርጫ እንዲኖረው ከማድረግ ጋር በተያያዘ የወጡ ወጪዎችን ይጨምራል፡፡
6. የአንድ ሀብት ዋጋ በሀብቱ ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት በሀብቱ ባለቤት የሂሳብ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚገኘውን ተቀናሽ ሂሳብ አያካትትም፡፡
7. አንድ ሰው ከአንድ ሀብት ውስጥ ከፊሉን ያስተላለፈ እንደሆነ፣ ይህ ሀብት ሲገዛ የነበረውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ታሳቢ በማድረግ የሀብቱ ዋጋ በተላለፈው እና በባለሀብቱ እጅ ባለው ድርሻ መካከል ይከፋፈላል፡፡
8. በዚህ አዋጅ መሠረት በግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የተካተተ ካልሆነ በስተቀር፣ የአንድ ግብር ከፋይ ሀብት ዋጋ ግብር ከፋዩ ሀብቱን ሲያገኝ የተቀበለውን ወይም የሚቀበለውን ማንኛውንም ድጎማ፣ ተመላሽ፣ ኮሚሽን ወይም ሌላ ማንኛውንም የገንዘብ ድጋፍ አይጨምርም፡፡

9. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የአንድን ሀብት ዋጋ ለመወሰን ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ሌሎች ዝርዝር ድንጋጌዎች ሊወስን ይችላል፡፡

69.<u>የንግድ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ የንግድ ሥራ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው የሚባለው ሀብቱን ለማግኘት ከወጣው ወጪ ላይ ከሀብቱ ጋር በተያያዘ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25(1) መሠረት የተፈቀደው ተቀናሽ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25(3) ተግባራዊ ባይደረግ ኖሮ የሚፈቀደው ተቀናሽ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ውጤት ነው፡፡
2. የአንድ ግብር ከፋይ የንግድ ሥራ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ በሚሰላበት ጊዜ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 68(7) ተፈፃሚ የሚደረግ ከሆነ የንግድ ሥራ ሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው የሚባለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 68(7) መሠረት የሀብቱ ድርሻ ነው ተብሎ ከሚወሰደው ወጪ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25(1) ለግብር ከፋዩ የሚደረገው የወጪ ተቀናሽ ወይም የዚህ አዋጅ አንቀጽ 25(4) ድንጋጌ ተግባራዊ ባይደረግ ኖሮ ተቀናሽ ይደረግ የነበረው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ሂሣብ ነው፡፡

70.<u>ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ</u>

1. አንድ ሰው አንድን ሀብት ሲያስተላልፍ ከዚህ ሀብት የተገኘ ገቢ ሆኖ የሚወሰደው ሀብቱን ሲያስተላልፍ የተቀበለው ወይም የሚቀበለው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ሲሆን፣ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ በዓይነት የተገኘውን ማንኛውንም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይጨምራል፡፡
2. ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ማህበር የሚሰጥን እርዳታ ሳይጨምር ሀብት በስጦታ የተላለፈ እንደሆነ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ያለው የሀብቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ከሀብቱ የተገኘ ገቢ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
3. አንድ ሰው ሀብቱን በማስተላለፍ ያገኘው ገቢ፣ ሀብቱን ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ ከቀረበለት ምርጫ ያገኘውን ጥቅም ይጨምራል፡፡ ሆኖም ይህ ጥቅም እንደ ገቢ ተደርጎ የሚወሰደው ከቀረበለት ምርጫ ጋር በተያያዘ ባገኘው ጥቅም ላይ ግብር ያልከፈለ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

4. አንድ ሀብት የጠፋ ወይም የወደመ እንደሆነ፣ የዚህ ሀብት ዋጋ ነው የሚባለው ባለ ሀብቱ ሀብቱ በመጥፋቱ ወይም በመውደሙ ምክንያት የተቀበለው ወይም የሚቀበለው የካሳ መጠን ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

   ሀ/ በመድን ፖሊሲ መሠረት፣ በካሳ ወይም በሌላ ስምምነት ምክንያት የተቀበለውን ወይም የሚቀበለውን የገንዘብ መጠን፤

   ለ/ በድርድር ምክንያት የሚቀበለውን የገንዘብ መጠን፤ ወይም

   ሐ/ የፍርድ ቤት ውሳኔን ተከትሎ የተቀበለውን ወይም የሚቀበለውን የገንዘብ መጠን፤

5. አንድ ሰው በአንድ ግብይት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀብቶችን ያስተላለፈ እንደሆነና የእያንዳንዱ ሀብት ዋጋ ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ፣ ሀብቶቹ በተላለፉበት ጊዜ ባለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሠረት በማስተላለፉ ምክንያት የተቀበለው የገንዘብ መጠን ለተላለፉት ሀብቶች እንደ የድርሻቸው ይደለደላል፡፡

6. አንድ ግብር ከፋይ የተላለፈውን ሀብት ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሀብቱ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

71.<u>**ጥቅምን ወይም ኪሳራን ስለ ማስተላለፍ**</u>

1. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት አንድ ሀብት ሲተላለፍ የተገኘ ማናቸውም ዓይነት ጥቅም ወይም የደረሰ ኪሳራ ለግብር አከፋፈል ከግምት ውስጥ አይገባም፡-

   ሀ/ ባልና ሚስት በሚፋቱበት ጊዜ የሚደረግ የሀብት ክፍፍል፤

   ለ/ አንድ ሰው በመሞቱ ምክንያት ለውርስ አጣሪው ወይም ለወራሹ ሀብት ሲተላለፍ፤

   ሐ/ ሀብቱ በመጥፋቱ ወይም በመውደሙ ወይም ሀብቱ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በመንግሥት በመወሰዱ ምክንያት (ከዚህ በኋላ "የተተካው ሀብት" ተብሎ የሚጠቀስ) የተገኘው ገቢ ገንዘቡን በተቀበለው ሰው አማካኝነት ሀብቱ በጠፋ ወይም በወደመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም

ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ሀብት (ከዚህ በኋላ "የመተኪያ ሀብት" ተብሎ የሚጠቀስ) ለማፍራት የዋለ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ ሀብቱ (ከዚህ በኋላ "የተተካው ሀብት" ተብሎ የሚጠራ) ዋጋው የሚቀንስ ሀብት የሆነ እንደሆነና ባለሀብቱ የተተካው ሀብት በጠፋ ወይም በወደመ በስድስት ወር ጊዜ ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ከዚህ የረዘመ ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የሚውል ዋጋው የሚቀንስ(ከዚህ በኋላ "የመተኪያ ሀብት" ተብሎ የሚጠራ) ተመሳሳይ ሀብት ያፈራ እንደሆነ፤

2. የተተካውን ሀብት ያገኘው ሰው ይህንን ሀብት ለወደፊት በሚያስተላልፍበት ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፍል የሚገባው ግብር የሌለ ሲሆን፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) ወይም (ለ) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆኑበት ጊዜ ሀብቱን ያገኘው ሰው ሀብቱን የሚያስተላልፈው ሰው ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ለሀብቱ ባወጣው የገንዘብ መጠን ልክ ሀብቱን እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) ወይም (መ) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆኑበት ጊዜ የመተኪያው ሀብት ዋጋ ከተተካው ሀብት ዋጋ የበለጠ እንደሆነ የመተኪያው ሀብት ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ከተተካው ሀብት ዋጋ ላይ በብልጫ የታየው የገንዘብ መጠን ተጨምሮበት ነው፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) ወይም (መ) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆኑበት ጊዜ ለተተካው ሀብት የተከፈለው ዋጋ ከመተኪያው ሀብት ዋጋ የሚበልጥ ከሆነ፤ የመተኪያው ሀብት ዋጋ ነው የሚባለው ሀብቱ በተላለፈበት ወቅት ያለው የተተካው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ በብልጫ የታየው የገንዘብ መጠን ተቀንሶ ነው፡፡ ነገር ግን ከዜሮ በታች መሆን የለበትም፡፡
6. የሀብቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ለመቀነስ ያልዋለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት በትርፍ የታየው የገንዘብ መጠን በግብር ከፋዩ ገቢ ውስጥ መካተት አለበት፡፡

7. የተላለፈው ሀብት ዋጋው የሚቀንስ ወይም ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የሆነ እንደሆነ፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) "ለሀብት ባወጣው የገንዘብ መጠን" በሚል የተመለከተው አገላለጽ የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፤

ለ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) "ለተተካው ሀብት የተደረገ ወጪ" በሚል የተመለከተው የተተካው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፤

72.<u>የተላለፉ ሀብቶችን ስለመመዝገብ</u>

የአንድን ሀብት መተላለፍ ለመቀበል፣ ለመመዝገብ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ መተላለፉን ለማፅደቅ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ሰው በሀብቱ መተላለፍ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት መከፈል የሚገባው ማንኛውም ግብር መከፈሉን ሳያረጋግጥ መተላለፉን ሊቀበል፣ ሊመዘግብ ወይም ሊያፀድቅ አይችልም፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>ሌሎች የወል ድንጋጌዎች</u>

73.<u>የተመለሰ ወጪ</u>

አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ላወጣው ወጪ ተቀናሽ የተያዘለት እንደሆነ ወይም የማይሰበሰብ ዕዳ የተሰረዘለት እንደሆነ እና በቀጣይ ግን ግብር ከፋዩ በገንዘብ ወይም በዓይነት በተቀናሽ የተያዘለትን ወጪ ወይም የተሰረዘለትን ዕዳ የሚያካክስ የገንዘብ መጠን የተቀበለ እንደሆነ ግብር ከፋዩ የተቀበለው የገንዘብ መጠን ገንዘቡን በተቀበለበት የግብር ዓመት እንደተገኘ ገቢ የሚቆጠር ሲሆን ይህም ገቢ ተቀናሽ ተደርጎለት ከነበረው ገቢ ጋር ተመሳሳይ ምድብ ይኖረዋል፡፡

74.<u>ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ስለማቆም</u>

1. ማናቸውም ግብር ከፋይ፡-

ሀ/ በግብር ዓመቱ ገቢው ከመገኘቱ በፊት ካቆመው የንግድ ሥራ፣ የሥራ እንቅስቃሴ፣ ወይም ኢንቨስትመንት ገቢ ያገኘ እንደሆነ፤ እና

ለ/ ገቢው የተገኘው የንግዱ ሥራ፣ የሥራው እንቅስቃሴ ወይም ኢንቨስትመንቱ ከመቆሙ በፊት ቢሆን ኖሮ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበት በሚሆንበት ጊዜ፤

የንግዱ ሥራ፣የሥራው እንቅስቃሴ ወይም ኢንቨስትመንቱ ገቢው በተገኘበት ጊዜ እንዳልቆመ ተቆጥሮ በገቢው ላይ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ገቢ ለማግኘት የወጣ ወጪ በዚህ አዋጅ በሚፈቀደው መጠን በተቀናሽ ይያዛል፡፡

75. <u>በዓይነት የተገኘ የገንዘብ መጠን</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዓይነት የተገኘ የገንዘብ መጠን ወይም የተፈፀመ ክፍያ ዋጋ የገንዘቡ መጠን በተገኘበት ወይም ክፍያው በተፈፀመበት ጊዜ ሀብቱ የነበረው ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ሲሆን፣ ይህ ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ ሀብቱን በማስተላለፍ መብት ላይ የተጣለው ገደብ ግምት ውስጥ አይገባም፡፡

76.<u>ወጪዎችን ስለማከፋፈል</u>

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማናቸውም ወጪ፡-

ሀ/ ከአንድ በላይ የሆኑ የገቢ ዓይነቶችን ለማግኘት፤ ወይም

ለ/ አንድን የገቢ ዓይነት ለማግኘት እና ለሌሎች ዓላማዎች የዋለ እንደሆነ፤ የሥራዎቹን ወይም የወጪዎቹን አንጻራዊ ባህርይና መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት ወጪዎቹ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ይከፋፈላሉ፡፡

2. የሚከተሉት የተለያዩ የገቢ ዓይነቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡-

ሀ/ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤

ለ/ ቤትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ፤

ሐ/ የንግድ ሥራ ገቢ፤

መ/ እያንዳንዱ ራሱን የቻለ የገቢ ዓይነት ሆኖ የሚወሰደው በሠንጠረዥ “መ” ሥር ግብር የሚከፈልበት ገቢ፤

ሠ/ ከገቢ ግብር ነፃ የሆነ ገቢ፤

77.<u>የገንዘብ ምንዛሪ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰላ የገንዘብ መጠን በብር መገለጽ አለበት፡፡

2. የገንዘብ መጠን ከብር ውጪ በሆነ ገንዘብ የተያዘ ከሆነ፣ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የገንዘቡ መጠን በሂሣብ መዝገብ በሚመዘገብበት ጊዜ በወቅቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው የምንዛሬ ተመን መሠረት ተሰልቶ ገንዘቡ ወደ ብር ይለወጣል፡፡
3. በውጭ ምንዛሪ በሚደረግ ግብይት የተገኘ ጥቅም ወይም የደረሰ ኪሳራ ለግብር አከፋፈል ሲባል ግብይቱ በተከናወነበት የግብር ዓመት ውስጥ እንደተገኘ ጥቅም ወይም እንደ ደረሰ ኪሳራ ሆኖ መገለጽ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ በውጭ ምንዛሪ ግብይት የደረሰ ኪሣራ ወይም የተገኘ ጥቅም የሚሰላበትን ዘዴ እና የውጭ ሀገር ገንዘብ ወደ ብር የሚቀየርበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ከግብር ለመሸሽ የሚደረገውን ጥረት ስለመከላከል

### 78. ገቢን መከፋፈል

1. አንድ ግብር ከፋይ ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በሚኖረው ግብይት ገቢን ለመከፋፈል ከሞከረ፣ ገቢው በመከፋፈሉ ምክንያት የሚደርሰውን የገቢ ግብር መቀነስ ለመከላከል ሲባል ባለሥልጣኑ የሁለቱን ሰዎች ገቢ እና ተቀናሽ ወጪ ሊያስተካክለው ይችላል፡፡
2. አንድ ግብር ከፋይ ገቢውን ለመከፋፈል ሞክሯል የሚባለው፡-

ሀ/ ግብር ከፋዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ገቢውን ወይም ገቢውን የሚያስገኘውን መብት ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍ፤

ለ/ ግብር ከፋዩ ጥሬ ገንዘብን ጨምሮ ማናቸውንም ሀብት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍና ሀብቱ የተላለፈለትሰው ከተላለፈው ሀብት ገቢ ወይም ጥቅም ሲያገኝ፤ እንዲሁም ሀብቱ የተላለፈበት ምክንያት ወይም ከተላለፈባቸው ምክንያቶች አንዱ የአስተላላፊውን ወይም የተላለፈለትን ሰው ገቢ ዝቅ ለማድረግ ሲሆን ነው፡፡

3. አንድ ሰው ገቢውን ለመከፋፈል የሞከረ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ባለሥልጣኑ ለተላለፈው ሀብት የተሰጠውን ዋጋ (ካለ) ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

**79.ስለ ማሸጋገሪያ ዋጋ**

1. በገበያ ዋጋ መርህ ያልተደረገ ማንኛውም ግብይት ሲኖር፣ በትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሚታየውን ትክክለኛ ገቢ፣ ጥቅም፣ ተቀናሽ፣ ኪሳራ፣ ወይም ማካካሻ ለመወሰን ባለሥልጣኑ እነዚህን ገቢዎች፣ ጥቅሞች፣ ተቀናሽ ወጪዎች፣ ኪሣራዎች ወይም ማካካሻዎች ግብይቱን ባደረጉት ወገኖች መካከል ሊያከፋፍል ወይም ሊደለድል ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚ በሚሆንበት ግብይት ከተዋዋዩቹ አንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝና በኢትዮጵያ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሲሆን እና የግብይቱ ሌላኛው ወገን ደግሞ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ እንደሆነ ማንኛውም ክፍፍል፣ ድልድል፣ የገቢ ክፍፍል፣ ጥቅም፣ ተቀናሽ ሂሣብ፣ ኪሣራ ወይም የግብር ማካካሻ የሚደረገው ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡
3. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ከኢትዮጵያ ውጭ ላለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የገቢ ወይም የወጪ ድልድል የሚደረገው ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚወጣው መመሪያ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከናወኑ ግብይቶችም ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡
5. አንድ ግብር ከፋይ ለግብር ዓመቱ በሚያቀርበው የግብር ማስታወቂያ ውስጥ ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ጋር ያደረጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር አብሮ ማቅረብ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ "በገበያ ዋጋ መሠረት የሚደረግ ግብይት" ማለት ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች በገበያ ዋጋ መሠረት የሚያደርጉት ግብይት ነው፡፡

**80.ከግብር ለመሸሽ የሚደረጉ ዕቅዶች**

1. የሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈፅመዋል ብሎ ሲያምን ባለሥልጣኑ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡-

ሀ/ ከግብር ለመሸሽ የሚያስችል ዕቅድ ሲዘጋጅ ወይም ተግባራዊ ሲሆን፤

ለ/ በዕቅዱ መሠረት አንድ ሰው የግብር ጥቅም ሲያገኝ፤ እና

ሐ/ የዕቅዱን መሠረታዊ ጉዳይ ግምት ውስጥ በማስገባት በዕቅዱ የተስማማው ወይም ዕቅዱን ተግባራዊ ያደረገው ሰው ይህንን ሊያደርግ የቻለበት ብቸኛው ወይም ዋነኛው ዓላማ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) የተመለከተውን የግብር ጥቅም ለማግኘት ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል ሲሆን ነው፡፡

2. በዚህ አዋጅ ውስጥ ሌላ ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም፣ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ ሲሆን ባለሥልጣኑ ምንም ዓይነት የዕቅድ ስምምነት እንዳልተደረገ ወይም ስምምነቱ ተግባራዊ እንዳልተደረገ በመቁጠር ከግብር ለመሸሽ የተደረገውን ተግባር ለመከላከል ወይም ለመቀነስ አግባብነት ይኖረዋል የሚለውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበትን ሰው ወይም ከዕቅዱ ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው ግብር ሊወስን ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የግብር ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን፣ ውሳኔውን ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ ባለሥልጣኑ የግብር ውሳኔውን አስመልክቶ ለግብር ከፋዩ ማስታወቂያዎች ይሰጣል፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም

ሀ/ "ዕቅድ" የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

(1) በፍርድ ሂደት ውስጥ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ወይም የማይችል ቢሆንም፣ ወይም በግልጽ ወይም በአንድምታየተደረገቢሆንምባይሆንም፣ስምምነትን፣ ማመቻቸትን፣ ቃል ኪዳን መግባትን፣ ወይም አንድን ነገር ለመፈፀም መስማማትን፤

(2) ማንኛውንም ዕቅድ፣ ወይም ሀሳብ ማቅረብ፣ የአንድን ድርጊት ሂደት ወይም የአንድን ድርጊት አፈፃፀም፡፡

ለ/ "የግብር ጥቅም" ማለት፡-

1) ማንኛውም ሰው ሊከፍል የሚገባውን ግብር መቀነስ፤
2) የአንድን ሰው ግብር የመክፈል ኃላፊነት ማዘግየት፤ ወይም
3) ሌላ ማንኛውም ከግብር ለመሸሽ የሚከናወን ድርጊት ነው፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## አስተዳደራዊና የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች

**81. የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈፃሚነት**

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ይህንን አዋጅ ለማስተዳደር የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**82. መዝገብ ስለመያዝ**

1. የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተዘጋጁ የሂሳብ መዝገቦችን የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን፤ በተለይም የሚከተሉትን መዛግብት መያዝ አለባቸው፡-

   ሀ/ ቋሚ ሀብቶች የተገዙበትን ቀን፣ የተገዙበትን ዋጋ፣ ሀብቱን ለማሻሻል የወጣውን ወጪ እና የሀብቱን የወቅቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ሰነድን ጨምሮ የንግድ ሥራውን ሀብትና ዕዳ የሚያሳይ መዝገብ፤

   ለ/ ከግብር ከፋዩ ንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ በየቀኑ የተገኘውን ማናቸውንም ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ ሰነድ፤

   ሐ/ ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ የንግድ ዕቃዎችን ግዢና ሽያጭ እንዲሁም በግብር ከፋዩ የተሰጡ እና የተገኙ አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚከተሉትን የሚያሳይ ሰነድ፤

      (1) ለገቢያ የዋሉትን ወይም የተቀበላቸውን የንግድ ዕቃዎች እና የተሰጠውን ወይም የተገኘውን አገልግሎት ዝርዝር፣

      (2) ከግብር ከፋዩ ላይ የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የገዙ ወይም ለግብር ከፋዩ ያቀረቡ ሰዎችን ስም እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (እንደሁኔታው)፣

      (3) የአቅራቢውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የያዙ አስቀድሞ ቁጥር የተሰጣቸው ደረሰኞችን፣

   መ/ በግብር ዓመቱ መጨረሻ በግብር ከፋዩ እጅ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎችን

ዓይነት፣ መጠንና ዋጋ እና የዋጋ መገመቻ ዘዴን የሚያሳይ ሰነድ፤

ሠ/ የግብር ከፋዩን የግብር ኃላፊነት ለመወሰን የሚያስችል ሌላ ማንኛውም ሰነድ፡፡

2. የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የሚከተሉትን ሰነዶች የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡-

ሀ/ የየቀኑን ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ መዝገብ፤

ለ/ ሁሉንም ግዥዎችና ሽያጮችን የሚያሳይ መዝገብ፣

ሐ/ የደመወዝንና የአበሎች መዝገብ፤

መ/ የግብር ከፋዩን የግብር ኃላፊነት ለመወሰን የሚያስችል ሌላ ማንኛውም አግባብነት ያለው ሰነድ፤

3. የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው መሠረት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸውን የሚያሳይ ወይም ሌላ አስፈላጊ መዝገብ ሊይዙ ይችላሉ፡፡

4. በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት የደረጃ "ሀ" ወይም "ለ" ግብር ከፋይ የሚከተሉትን ሰነዶች የመያዝ ግዴታ አለበት፡-

ሀ/ ከኪራይ የተቀበለውን ገቢ የሚያሳይ ሰነድ፤

ለ/ ከቤቱ ጋር በተያያዘ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር የተከፈሉትን ክፍያዎች የሚያሳይ ሰነድ፤

ሐ/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 15(5) (ለ) ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ ከቤቱ ጋር ተያይዞ የሚወጣውን ማንኛውንም ወጪ የሚያሳይ ሰነድ፤

መ/ የሚከራየው ሕንፃ የተገኘበትን ቀን፣ ሕንፃው የተገኘበትን ዋጋ፣ ሕንፃውን ለማሻሻል የወጣውን ወጪ እና የህንፃውን የወቅቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ሰነድ፤

ሠ/ ቤቱን በሚመለከት የተደረገ ማንኛውንም የተከራይ አከራይ ስምምነት የሚያሳይ ሰነድ፤

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 59 መሠረት ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ሀብት የተገኘበትን ቀን፣ የተገኘበትን ዋጋ እና ሀብቱን ለማሻሻል የወጣ ሌላ ማንኛውንም ወጪ፣ ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ የተቀበለውን ገቢ የሚያሳይ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡
6. ግብር ከፋዩ አንድ ወጪ በተቀናሽነት እንዲያዝለት ወይም በአንድ ሀብት ዋጋ ውስጥ እንዲካተትለት የሚያስችለውን የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ላይፈቅድ ይችላል፡-

   ሀ/ ወጪ በተቀናሽነት እንዲያዝ፤

   ለ/ አንድ ወጪ በአንድ ሀብት ዋጋ ውስጥ እንዲካተት፤
7. ባለሥልጣኑ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

83.<u>ግብርን ስለማሳወቅ</u>

1. አንድ ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከአንድ በላይ ለሆኑ ቀጣሪዎች የማይሰራ ወይም ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ካልሆነ በስተቀር ግብሩን የማስታወቅ ግዴታ የለበትም፡፡
2. አንድ ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከአንድ በላይ ቀጣሪዎች ያሉት ወይም ከራስ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት እንደሆነ፣ ተቀጣሪው ከየሦስት ወሩ መጨረሻ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የግብር ማስታወቂያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. አንድ ተቀጣሪ ግብር የማሳወቅ ግዴታ የሌለበት ሲሆን ቀጣሪው በአንቀጽ 96 መሠረት ለተቀጣሪው የሚሰጠው ግብር ተቀንሶ ቀሪ መሆኑን የሚያሳየው ደረሰኝ ለዚህ አዋጅና ለታክስ አስተዳደር አዋጅ ዓላማ ሲባል ቀጣሪው በየወሩ መክፈል በሚኖርበት ግብር ላይ እንደተሰጠ የግብር ውሳኔ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
4. የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች የግብር ዓመቱን ግብር የሚያሳውቁት በሚከተሉት ጊዜያት ውስጥ ይሆናል፡-

   ሀ/ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች የግብር ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ ባሉት የአራት ወራት ጊዜ ውስጥ፤

   ለ/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የግብር ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ ባሉት የሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚቀርብ የግብር ማስታወቂያ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

   ሀ/ ለደረጃ “ሀ” ግብር ከፋዮች፣ የግብር ከፋዩን የግብር ዓመቱን ትርፍና ኪሳራ መግለጫ እና የሃብትና ዕዳ መግለጫ፤ ወይም

   ለ/ ለደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች፣ የግብር ከፋዩን የግብር ዓመቱን የትርፍና ኪሳራየሂሳብ መግለጫ፤

6. የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84(4) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የግብር ማስታወቂያውን ማቅረብ አለበት፡፡

7. ካገኘው ገቢ ላይ ግብሩ ተቀናሽ የተደረገ በመሆኑ ምክንያት ነፃ ካልተደረገ በስተቀር የሠንጠረዥ "መ" ገቢ ያለው ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ ገቢውን ያስገኘው ግብይት ከተደረገ ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ የግብር ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 84.ግብርን ስለመክፈል

1. አንድ ተቀጣሪ ለወሩ መክፈል የሚኖርበት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር የመክፈያ ጊዜ ግብር ከፋዩ የየሦስት ወሩን የግብር ማስታወቂያ የሚያቀርብበት ጊዜ ነው፡፡

2. የደረጃ "ሀ" ወይም "ለ" ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ገቢያቸውን ማስታወቅ ባለባቸው ጊዜ በግብር ዓመቱ ሊከፍሉት የሚገባውን ግብር ከፋዮቹ መክፈል አለባቸው፡፡

3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 83(7) የሚመለከተው ግብር ከፋይ ግብር መክፈያ ጊዜ ግብይቱን አስመልክቶ የግብር ማስታወቂያ መቅረብ የሚኖርበት ጊዜ ይሆናል፡፡

4. የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ በዚህ አዋጅ ሥር በሚወጣ ደንብ መሠረት ለእያንዳንዱ በጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሐምሌ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ግብሩን መክፈል ይኖርበታል፡፡

## 85.ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ በቅድሚያ ስለሚከፈል ግብር

1. የሠንጠረዥ “ሐ” ግብር ከፋይ ለንግድ የሚውሉ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ሲያስገባ የዕቃዎቹን የጉምሩክ ዋጋ፣ የመድን አረቦንና የማጓጓዣ ወጪ 3%

(ሦስት በመቶ) የንግድ ሥራ ገቢ ግብር በቅድሚያ ለባለሥልጣኑ ይከፍላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መከፈል የሚኖርበት ግብር የሚከፈለው ዕቃዎቹ ከጉምሩክ ቁጥጥር ከመውጣታቸው በፊት ሆኖ፣ ይህም ግብር ግብር ከፋዩ ዕቃዎቹን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባቱ ተግባር በተከናወነበት የግብር ዓመት ከግብር ከፋዩ ላይ ከሚፈለገው ዓመታዊ የንግድ ሥራ ግብር ዕዳ ጋር ይካካሳል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሊካካስ የሚችለው በአንድ የግብር ዓመት በየጊዜው የተከፈለው የግብር መጠን ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ መክፈል ከሚኖርበት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ዕዳ የበለጠ እንደሆነ፣ በልዩነት የታየው የገንዘብ መጠን በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፵9 መሠረት ሥራ ላይ ይውላል፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ”ለንግድ የሚውሉ ዕቃዎች” የሚለው ሀረግ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ትርጉም የሚሰጠው ይሆናል፡፡

86.<u>ግብርን በየጊዜው መክፈል</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሠንጠረዥ "ሐ" ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ ውስጥ 6ኛውን ወር ተከትሎ እስከሚመጣው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ የንግድ ሥራ ገቢ ግብሩን በከፊል ለመክፈል ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) እንደተጠበቁ ሆኖ፣ አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የክፍያ ጊዜ መክፈል የሚችለው ከፊል ግብር ባለፈው የግብር ዓመት የተከፈለውን የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ግማሽ ይሆናል፡፡
3. ግብር ከፋዩ ባለፈው የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያልነበረበት ከሆነ በከፊል የሚከፈለው የግብር መጠን በጣም ቅርብ በነበረው የግብር ዓመት የነበረው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ግማሽ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በአንድ ግብር ከፋይ በከፊል ሊከፈል ከሚገባው ግብር ላይ፣ ግብር ከፋዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹5 መሠረት የከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ወይም ደግሞ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺2

መሠረት የተከፈለው ግብር ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን፣ ተቀናሽ ተደርጐ የሚቀረው ከዜሮ በታች ሊሆን አይችልም፡፡

5. ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት በከፊል የከፈለው ግብር በግብር ዓመቱ መክፈል ካለበት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ጋር ይካካሳል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ሊካካስ የሚችለው ግብር ከፋዩ በአንድ የግብር ዓመት በከፊል የከፈለው የግብር መጠን በዓመቱ መክፈል ከሚኖርበት የገቢ ግብር የበለጠ እንደሆነ፤ በልዩነት የታየው የገንዘብ መጠን በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 49 መሠረት ሥራ ላይ ይውላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ "የንግድ ሥራ ገቢ ግብር" የሚለው አገላለጽ "የኪራይ ገቢ ግብር" የሚለውን አገላለጽ አካቶ ይህ አንቀጽ ለሠንጠረዥ "ለ" ግብር ከፋይም ተፈፃሚነት ሊኖረው ይችላል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ "ከፋፍሎ የመክፈያ ጊዜ" ማለት የግብር ከፋዩ ግብር ዓመት በሚመለከት በግብር ዓመቱ ውስጥ የመጀመሪው ስድስት ወር የሚያበቃበት መጨረሻ ቀን ነው፡፡

87.<u>ከዓለም ዐቀፍ የአየር ትራንስፖርት ከሚገኝ ገቢ ግብር ስለመሰብሰብ</u>

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ለእያንዳንዱ ሩብ ዓመት ከሩብ ዓመቱ መጨረሻ ቀጥሎ ባለው 30 ቀን ውስጥ ግብሩን ለባለሥልጣኑ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ለሩብ ዓመቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት መክፈል የሚኖርበትን ግብር የሚከፍለው ለሩብ ዓመቱ የግብር ማስታወቂያ ማቅረብ በሚኖርበት ጊዜ ነው፡፡
3. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በአንድ ሩብ ዓመት ውስጥ መክፈል የሚኖርበትን ግብር ግብሩ መከፈል ከሚኖርበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት የሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ያልከፈለ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነውን ሰው ስምና መክፈል የሚኖርበትን የግብር መጠን የሚገልጽ ማስታወቂያ ለኢትዮጵያ የሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን ይልካል፡፡ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው

ሰው ሀብት ወይም ለተከራየው በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ለሚገኝ ማንኛውም አውሮፕላን ግብሩ እስከሚከፈል ድረስ መልቀቂያ ለመስጠት አይችልም፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም “ሩብ ዓመት” ማለት ለእያንዳንዱ ዓመት እ.ኤ.አ መጋቢት 31፣ ሰኔ 30፣ መስከረም 30 እና ታህሳስ 31 የሚጠናቀቅ የሦስት ወራት ጊዜ ነው፡፡

## ክፍል አሥር

## ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት

### 88. ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረት

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ቀጣሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት ከመቀጠር የሚገኝ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለተቀጣሪው በሚከፍልበት ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ በሚሆነው የግብር መጣኔ መሠረት በእያንዳንዱ የክፍያ ጊዜ መከፈል የሚኖርበትን የገቢ ግብር ከጠቅላላው ክፍያ ላይ ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡
2. ቀጣሪው ተቀጣሪው ከአንድ በላይ የሆነ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እንዳለው ያወቀና ሌላው ቀጣሪ ወይም ሌሎቹ ቀጣሪዎች በጠቅላላው የተቀጣሪው ገቢ ላይ ተመስርተው የገቢ ግብሩን ቀንሰው እንደማያስቀሩ ያወቀ እንደሆነ ቀጣሪው የተቀጣሪውን ገቢ በማጠቃለል የገቢ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡
3. ቀጣሪው ለተቀጣሪው ከሚከፍለው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታው ለሠራተኛው ከሚፈፅማቸው ክፍያዎች ላይ በቀጣሪው ተቀናሽ መደረግ ካለባቸው ሌሎች ግዴታዎች ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

### 89. በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆኑ ሰዎች ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረት

1. የኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው እና በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ያለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ሰው የትርፍ ድርሻ፣ የንዑስ ሥራ ተቋራጭ ክፍያ፣ የወለድ፣ የሮያሊቲ፣ የሥራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒካል ክፍያ ፣የመድን አረቦን፣ ወደ ውጭ የሚላክ ትርፍ ወይም የሌሎች ገቢዎች ክፍያ የፈፀመ እንደሆነ እንደ አግባብነቱ በዚህ አዋጅ

አንቀጽ 37(4)፣ 51(2)፣ 54፣ 55፣ 56፣ 62 ወይም 63 በተደነገገው የግብር መጣኔ መሠረት በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነው ሰው ከሚፈፅመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ የገቢ ግብር ቀንሶ መያዝ አለበት፡፡

2. የኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው እና በኢትዮጵያ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ያለው ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ አዝናኝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 53 መሠረት ግብር የሚከፈልበት ክፍያ የፈፀመ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 53(1) በተደነገገው የግብር መጣኔ መሠረት ለአዝናኙ ከሚፈፅመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ የገቢ ግብር ቀንሶ መያዝ አለበት፡፡
3. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ያልተከፋፈለ ትርፍ ያለው እንደሆነ ከዚህ ትርፍ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61 በተደነገገው መሠረት ግብሩን ቀንሶ መያዝ አለበት፡፡

90.**ከትርፍ ድርሻ፣ ካልተከፋፈለ ትርፍ፣ ከወለድ እና ከሮያሊቲ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ማስቀረት**

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው እና በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 መሠረት ግብር የሚከፈልበት የሮያሊቲ ክፍያ በሚፈፅምበት ጊዜ በዚያው አንቀጽ በተወሰነው መጣኔ መሠረት ግብሩን ከጠቅላላው ክፍያ ላይ ቀንሶ ማስቀረት አለበት፡፡
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት እንደ አግባብነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 ወይም አንቀጽ 61 መሠረት ግብር የሚከፈልበት የትርፍ ድርሻ ክፍያ ወይም ያልተከፋፈለ ትርፍ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ሲፈፅም ወይም ሲይዝ በዚያው አንቀጽ በተወሰነው መጣኔ መሠረት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡
3. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 ወይም 62 መሠረት ግብር የሚከፈልበት ወለድ ወይም ወደ ውጭ የሚላክ ትርፍ የከፈለ ወይም ያልተከፋፈለ ትርፍ እንደሆነ በዚያው አንቀጽ በተወሰነው የግብር መጣኔ መሠረት ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡

91.<u>ከዕድል ሙከራ ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረት</u>

በዕድል ሙከራ አሸናፊ ለሆነ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገንዘብ የሚከፍል ሰው በዚያው አንቀጽ በተወሰነው መጣኔ መሠረት ለአሸናፊው ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡

92.<u>በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት</u>

1. ከጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ በስተቀር ድርጅት፣ የመንግሥት መስሪያ ቤት፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅትወይምመንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት እንዲሁም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ለሚከተሉት ግብይቶች ከሚፈፅሙት ጠቅላላ ክፍያ ላይ 2% (ሁለት በመቶ) ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፡-

   ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ግዥ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር 10,000ብር (አሥር ሺህ) በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት ለሚፈፀም ክፍያ፤

   ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ የአገልግሎት ውል ከብር 3,000 ብር (ሶስትሺህ ብር) በላይ በሚፈፀም ክፍያ፤

2. ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ገንዘብ በሚያንስ መጠን ተነጣጥለው ሲቀርቡና እነዚህ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በመደበኛው አሰራር በአንድ አቅርቦት እንደሚቀርቡና ለአቅርቦቱ የሚከፈለው ገንዘብም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተወሰነው የገንዘብ መጠን እንደሚበልጥ የሚገመት ከሆነ፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ ባለሥልጣኑ ያልተከፈለውን የግብር መጠን በመወሰን እና የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ያልተከፈለውን ተቀንሶ መያዝ የነበረበትን ግብር ከአቅራቢው ወይም ከገዥው ላይ ለማስከፈል ይችላል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚ የሚሆንበት አቅራቢ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ያልሰጠ እንደሆነ ግብሩን

ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚፈፅመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ 30% (ሰላሳ በመቶ) ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ተይዞ የሚከፈለው ግብር፡-

ሀ/ አቅራቢው ከአቅርቦቱ የሚያገኘውን ገቢ በተመለከተ የመጨረሻ ግብር ይሆናል፤

ለ/ በመመሪያ ወይም በአስተዳደራዊ ውሳኔ ቀሪ ሊደረግ አይችልም፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተወሰነውን የገንዘብ መጠን ሚኒስትሩ በመመሪያ ሊለውጠው ይችላል፡፡

93.<u>ከራስ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ ስለመያዝ</u>

1. በዓለም ዐቀፍ ድርጅት የተቀጠረ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ባለ የውጭ ሀገር ኤምባሲ፣ ዲፕሎማቲክ ሚሽን፣ ወይም ሌላ ኮንሱላር ተቋም ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ወይም በማናቸውም ሕግ ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ለሌለበት ቀጣሪ የሚሰራ ሰው ከእነዚህ ተቋማት ከሚቀበለው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 88 በተደነገገው መሠረት ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚ የሚሆነው ዓለም አቀፍ ድርጅቱ ወይም የውጭ ሀገር መንግሥት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 88 በተደነገገው መሠረት ግብሩን ቀንሶ በማይዝበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

3. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ እና ገቢውን ያገኘው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 90 ወይም 91 መሠረት ራሱ ግብሩን ቀንሶ ማስቀረት አለበት፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54፣ 56 ወይም 57 መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ የሚከፍለው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የሌለውና የኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ሲሆን፤ ወይም

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ የሚከፍለው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፤

94.<u>ከግብር ነፃ በሆኑ ገቢዎች ላይ ግብር ተቀንሶ የማይያዝ ስለመሆኑ</u>

በዚህ ምዕራፍ መሠረት ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ከግብር ነፃ በሆነ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ መያዝ አይችልም፡፡

95.<u>ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ ተከፈለ ስለሚባልበት ጊዜ</u>

ለዚህ የአዋጁ ክፍል አፈፃፀም ሲባል፣ ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ባለበት ሰው ተከፈለ የሚባለው ከሚከተሉት አንዱ ሲፈፀም ነው፡-

1. ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ ክፍያ ለሚፈፀምለት ሰው በእርግጥ ሲከፈል፤
2. ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ በተከፋዩ ትዕዛዝ ወይም በሕግ መሠረት በተከፋዩ ስም ሲከፈል፤
3. ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ ለተከፋዩ ጥቅም ሲባል ሥራ ላይ ከዋለ፣ ከተጠራቀመ፣ ወይም ለካፒታል ሀብት ማግኛ ሲውል፣
4. ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ ለተከፋዩ ጥቅም ሲባል በተከፋዩ ስም ሲያዝለት፡፡

96.<u>ግብር ተቀንሶ መያዙን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ስለመስጠት</u>

ከአንድ ክፍያ ላይ ግብር ተቀንሶ በሚያዝበት ጊዜ፣ ግብሩን ቀንሶ የሚይዘው ሰው ክፍያውን ለሚቀበለው ሰው ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ግብር ተቀንሶ መያዙን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

97.<u>ተቀንሶ የተያዘውን ግብር ስለመክፈል</u>

1. ማንኛውም ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረውን ግብር ክፍያ ከፈፀመበት ወር በኋላ ባሉት 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ፣ ለባለሥልጣኑ መክፈል ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቀንሶ የሚያዝ ግብር የሚከፍል ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ተቀናሽ ተደርጎ የተያዘውን ግብር በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለባለሥልጣኑ የማስታወቅና ግብሩን አብሮ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡
3. ማንኛውም ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው፡-

   ሀ/ በዚህ የአዋጁ ክፍል በተደነገገው መሠረት ግብር ቀንሶ ያልያዘ ከሆነ፤ ወይም

   ለ/ ቀንሶ የያዘውን ግብር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገውመሠረትለባለሥልጣኑያልከፈለ እንደሆነ፤

   ለባለሥልጣኑ መክፈል የሚኖርበትን ግብር በተመለከተ ኃላፊ ይሆናል፡፡

4. ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ግብሩን ቀንሶ ባለመያዙ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ለተመለከተው የግብር መጠን ኃላፊ በሚሆንበት ጊዜ እርሱ የከፈለውን ግብር ክፍያ ከተፈፀመለት ሰው ላይ የማስመለስ መብት አለው፡፡

98.<u>ተቀንሶ ለተያዘ ግብር የሚሰጥ የግብር ማካካሻ</u>

1. በዚህ ምዕራፍ መሠረት ከገቢ ላይ የተቀነሰው ግብር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10(5) ወይም 64(2) መሠረት የመጨረሻ ግብር በማይሆንበት ጊዜ ግብር ከፋዩ ተቀንሶ ለተያዘው ግብር በግብር ዓመቱ የግብር ማካካሻ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተከፈለው ግብር ከግብር ከፋዩ ላይ በዓመቱ ከሚፈለገው የግብር መጠን ያነሰ እንደሆነ ግብር ከፋዩ ገቢውን በሚያስታውቅበት ጊዜ በልዩነት የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተከፈለው ግብር ከግብር ከፋዩ ላይ በግብር ዓመቱ ከሚፈለገው የግብር መጠን በልጦ የተገኘ እንደሆነ በብልጫ የተከፈለው ግብር በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 49 በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አሥራ አንድ</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

99.<u>ደንብና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን</u>

1. ለዚህ አዋጅ ትክክለኛ አፈፃፀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያወጣል፡፡
2. ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚወጣው ደንብ ትክክለኛ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

100. <u>የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 101 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሕጎች (ከዚህ በኋላ “የተሻረው ሕግ” ተብለው የሚጠቀሱት) በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ/ የገቢ.ግብርአዋጅቁጥር286/1994 ከነማሻሻያዎቹ፤

ለ/ የማዕድን ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 53/1985 ከነማሻሻያዎቹ፤ እንዲሁም

ሐ/ የነዳጅ ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 266/1978 ከነማሻሻያዎቹ፤

2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

101. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ መሆን ከሚጀምርበት የግብር ዓመት በፊት ላለው የግብር ዓመት በዚህ አዋጅ የተሻሩ ሕጎች ተፈፃሚነት ይቀጥላል፡፡

2. በዚህ አዋጅ ያለፈው የግብር ዓመት የሚለው አገላለፅ እንደ አግባብነቱ በተሻረው ሕግ ያለውን የግብር ዓመትም ይጨምራል፡፡

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 73 መሠረት ቀደም ሲል የተደረገ ተቀናሽ፣ ወጪ፣ ኪሳራ ወይም የማይሰበሰብ እዳ የሚለው አገላለጽ በተሻረው ሕግ መሠረት የተቀነሰን ወጪ፣ ኪሳራ ወይም የማይሰበሰብ ዕዳን ይጨምራል፡፡

4. በዚህ አዋጅ መሠረት የትርፍ እና ኪሣራ ወይም የገቢ መግለጫ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ መሠረት የሚዘጋጀው የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይሆናል፡፡ የጊዜ ሰሌዳው ተፈፃሚ እስከሚሆን ድረስ የተሻረው ሕግ ተፈፃሚነት ይቀጥላል፡፡

5. ባለሥልጣኑ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ የተደነገገው የግብር ከፋዮች ደረጃ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ጊዜ ይወስናል፡፡ ይህ እስከሚወሰን ድረስ የግብር ከፋዮችን ደረጃ በሚመለከት የተሻረው ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

6. በተሻሩት ሕጎች መሠረት የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ እና በሌሎች ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

102. <u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 12 ቀን 2008 ዓ.ም.**

## ደንብ ቁጥር 410/2009

## ስለፌደራል የገቢ ግብር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዱሞክራሲያዊ ሪፐብሉክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 99 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "አዋጅ" ማለትየፌደራልየገቢግብርአዋጅቁጥር 979/2008 ነው፤
   2. "የተሻረው አዋጅ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር286/1994 (እንደተሻሻለው)፣ የማዕድን ስራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 53/1995 (እንደተሻሻለው) እና የነዳጅ ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 296/1978 (እንደተሻሻለው) ነው፤

3. ጥቅም ላይ የዋለ ቃላትና ሀረጎች እንደአግባብነቱ በአዋጁ ወይም በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በአዋጁ ጥቅም ላይ የዋለ ቃላትና ሀረጎች አጠቃቀም

### 3. ወለድ

‹‹ለአዋጁ ዓላማ በማንኛውም ስያሜ ቢጠቀስም በቁጠባና ብድር ማህበራት ለተቀማጭ ገንዘብ ወይም ለአባላት መዋጮ የሚፈጸም ክፍያ እንደወለድ ይቆጠራል፡፡

### 4. በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት

1. ለአዋጁ አንቀጽ 4(2)(ሐ) ዓላማ ማንኛውም ሰው ከ183 ቀን በላይ መቆየቱን ለመወሰን የዚህ ሰው ወይም ግንኙነት ያለው ሰው ተያያዥ ፕሮጀክት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 4(3) የተመለከተን ማንኛውም ግንባታ፣ ፕሮጀክት ወይም ተያያዥ ሥራ የሚያከናውን ሰው ከ 183 ቀን የሚበልጥ የቆይታ ጊዜ ማሟላቱን ለመወሰን፣ ግንኙነት ባለው ሰው የተከናወነ ማንኛውም ግንባታ፣ ፕሮጀክት ወይም ተያያዥ ሥራ መጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ያከናወነው ሥራ በወሰደው ጊዜ ላይ ተጨምሮ መሰላት አለበት፡፡

### 5. ግለሰብነዋሪ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለአዋጁ አንቀጽ 5(2) (ሐ) ዓላማ አንድ ግለሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ ለቆየባቸው ቀናት ስሌት፡-
   ሀ) ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን እና ከኢትዮጵያ የወጣበትን ቀን ጨምሮ ማንኛውም ግለሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ የቆየበት ቀን ከፊል እንደሙሉቀን ቆይታ ይቆጠራል፤
   ለ) ማንኛውም ግለሰብ በሙሉ ወይም በከፊል በኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘባቸው የሚከተለት ቀናት እንደሙሉ ቀን ቆይታ ይቆጠራሉ፡-
      (1) የሕዝብ በዓላት፤

(2) የእረፍት ቀናት፣የህመም ፈቃድን ጨምሮ፤

(3) (3) ግለሰቡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያከናውነው ሥራ በሥራ ማቆም አድማ፣ በቀጣሪ በሚደረግ የሥራ መዝጋት፣ በግብዓት አቅርቦት መዘግየት፣ ሥራን በሚከለክል የአየር ሁኔታ ወይም ሥራን በሚያስተጓጉል ሌሎች ወቅታዊ ምክንያቶች የተቋረጠባቸው ቀናት፤

(4) ግለሰቡ ማንኛውንም ሥራ ከመጀመሩ በፊት፣ በሥራ ላይ እያለ ወይም ሥራውን ከጨረሰ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሳለፋቸው የእረፍት ቀናት፡፡

2. አንድ ግለሰብ ከኢትዮጵያ ውጪ ባለ ሁለት የተለያዩ ቦታዎች መካከል በሚያደርገው ጉዞ ምክንያት በተላላፊ መንገደኛነት በኢትዮጵያ ውስጥየሚያደርገው የሙሉ ወይም የከፊል ቀን ቆይታ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተደረገ ቆይታ አይቆጠርም፡፡

## 6. አክሲዮኖችእናቦንድች

1. በአዋጁ አንቀጽ 59(7)(ሐ) "አክሲዮኖችን እና ቦንድችን" በሚመለከት የተጠቀሰው ማንኛውንም በአክሲዮኖች ወይም ቦንዶች ላይ ያለን ባለአክሲዮን የመሆን መብትን ወይም ምርጫን የመሰለ ጥቅም ይጨምራል፡፡

2. በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነ ኩባንያ ውስጥ ያለን የአክሲዮን መብት ወይም በእንዲህ ዓይነቱ ኩባንያ የወጣን ቦንድ በማስተላለፍ የተገኘ ጥቅም ከኢትዮጵያ ምንጭ እንደተገኘ ገቢ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የዓይነት ጥቅሞች

## 7. የክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ ትርጓሜ

1. በዚህ ክፍል ውስጥ፡-

ሀ)"የሠራተኛ አክሲዮን ዕቅድ" ማለት ቀጣሪ ኩባንያ ወይም ግንኙነት ያለው ኩባንያ ለቀጣሪ ኩባንያው ሠራተኛ አክሲዮን የሚደለድልበት ስምምነት ወይም አሠራር ነው፤

ለ) “የቤተሰብ አገልግልት ሠራተኛ” ማለት የቤት ሠራተኛ፣ ምግብ አብሳይ፣ ሾፌር፣ አትክልተኛ፣ ወይም ሌላ ለቤተሰብ አገልግልት የሚሰጥ ሰው ነው፤

ሐ) ከወር ጋር በተገናኘ “የገበያ የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ማለት፡-

(1) ለንግድ ባንክ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለንግድ ባንኮች ብድር እና በተላላፊ ሰነድ ዋስትና የሚሰጥ የቅናሽ ወለድ ብድር አቅርቦት በሰጠበት ወር በኢትዮጵያ ውስጥ የዋለው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ፣ ወይም

(2) ለሌላማንኛውምሰውሲሆን፣በኢትዮጵያውስጥ በወሩ የዋለው ዝቅተኛው የንግድ ባንኮች የማበደሪያ ወለድ መጣኔ፣ ነው፤

መ) “ግንኙነት ያለው ኩባንያ” ማለት ከኩባንያ ጋር በተገናኘ፣ ከመጀመሪያው ኩባንያ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው የሆነ ላላ ኩባንያ ነው፤

ሠ) “ሩቅ ሥፍራ” ማለት ሃያ ሺህ ነዋሪ ካለው የከተማ መሃል ሰላሳ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝሥፍራ ነው፤

ረ) “አገልግሎቶች” ማለት በንብረት መጠቀምን እና ማንኛውንም መገልገያ ማቅረብን ይጨምራል፤

ሰ) “ተሽከርካሪ” ማለት ከአንድ ቶን በታች እና ከዘጠኝ ያነሱ ተሳፋሪዎችን መጫን እንዲችል ሆኖ የተሰራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፡፡

2. በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ፡-

ሀ) “ቀጣሪ” ከቀጣሪው ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው እና ከቀጣሪው ወይም ከቀጣሪው ጋር ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት እንደቀጣሪ የሚሠራን ሶስተኛ ወገን ይጨምራል፤

ለ) “ተቀጣሪ” ከተቀጣሪው ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው ይጨምራል፡፡

8. **የዓይነት ጥቅሞች**

1. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአዋጁ አንቀጽ 12(1)(ለ) ዓላማ ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚሰጣቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጥቅሞች የዓይነት ጥቅሞች ናቸው፡-

ሀ) ከዕዳ ነጻ የመደረግ፤

ለ) የቤተሰብ አገልግልት ሠራተኞች፤

ሐ) የመኖሪያ ቤት፤

መ) የቅናሽ ወለድ ብድር፤

ሠ) የምግብ ወይም መጠጥ አገልግልት፤

ረ) የግልወጪዎች፤

ሰ) የንብረት ወይም አገልግሎቶች፤

ሸ) የሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ፤

ቀ) የተሽከርካሪ፤

በ) ሌላ የዓይነት ጥቅም፡፡

2. አንድ ተቀጣሪ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ፣ ይህን ጥቅምለማግኘት ያወጣው ወጪ የቅጥር ገቢን ለማግኘት ያደርገው የነበረ ወጪ እስከሆነ ድረስ እንደ ዓይነት ጥቅም አይቆጠርም፡፡

3. ማንኛውም ጥቅም የዓይነት ጥቅም መሆኑን እና የዓይነት ጥቅምን ዋጋ ለመወሰን ጥቅሙን በማስተላለፍ ረገድ የተጣለ ገደብ መኖሩ እና ጥቅሙ በሌላ ሁኔታ ወደገንዘብ መለወጥ አለመቻሉ ከግምት ውስጥ አይገባም፡፡

4. ለአዋጁ ወይም ለዚህ ደንብ ዓላማ የሚከተሉት ጥቅሞች እንድ ዓይነት ጥቅሞች አይቆጠሩም፡-

ሀ) በአዋጁ ሠንጠረዥ "ሠ" መሠረት ከግብር ነጻ የተደረገ ጥቅም፤

ለ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ቀጣሪ ተመሳሳይ ጥቅምየሚያቀርብበትን ድግግሞሽ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዋጋው አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ማስላቱ ምክንያታዊ ያልሆነ እና ለአስተዳደር የማያመች ጥቅም፤

ሐ) በቀጣሪው ወይም በቀጣሪው ስም በሚተዳደር የሠራተኞች ምግብ ቤት፣ ካፌቴሪያ ወይም የመመገቢያ ክፍል ያለምንም ልዩነት ለመደበኛ ሠራተኞች ጥቅም ብቻ ተብሎ የሚቀርብ የምግብና መጠጥ አገልግሎት ድጎማ፤

መ) በሚከተሉት ምንያቶች የሥራ አመራር አካል ላልሆነ ተቀጣሪ በሩቅ ሥፍራ የሚቀርብ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤት አገልግልት፡-

(1) የተቀጣሪውመደበኛየሥራቦታበሩቅ ሥፍራ ለሆነ፣ እና

(2) በቀጣሪው የሥራ ባህሪ ምክንያት ሠራተኛው በየጊዜው ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ወይም በሩቅ ሥፍራው በቂ የሆነ

ምቹ ማረፊያ ወይም መኖሪያ ቤት ባለመኖሩ ቀጣሪው ማረፊያ ወይም መኖሪያ ቤት ማቅረቡ አስፈላጊ ስለሆነ፣

ሠ) ተቀጣሪው እንዲጠቀምበት በቀጣሪው የሚቀርብ ተንቀሳቃሽ ስልክ፤

ረ) በቀጣሪው በቀረበ የተንቀሳቃሽ ስልክ የተደረገን ጥሪ ጨምሮ ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚሸፍነው የተንቀሳቃሽ ስልክ ጥሪዎች ወጪ፤

ሰ) በዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ ወይም የጎልማሶች ትምህርት በሚሰጥ ሌላ ተቋም የሚሰጥ ትምህርት መከታተል እንዲችል ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚፈጽመው የትምህርት ወይም ሥልጠና ክፍያ፤

ሸ) ለተቀጣሪ ጥቅም የሚቀርብ የደህንነት ጥበቃ አገልግሎት፤

ቀ) ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ሌሎች ተቋሞች ለተቀጣሪዎቻቸው የሚያቀርቡት የምግብና መጠጥ አገልግሎት፤

በ) ለተቀጣሪዎች የሚቀርብ የደንብ ልብስ እና የሥራ መገልገያ፡፡

9. <u>ከዕዳ ነጻ የመደረግ የዓይነት ጥቅም</u>

1. ተቀጣሪ ለቀጣሪ መክፈል ያለበትን ዕዳ ወይም መመለስ የሚኖርበትን የብድር ግድታ ቀጣሪ ቀሪ ማድረጉ ከዕዳ ነጻ የመደረግ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡
2. ከዕዳነጻየመደረግየዓይነትጥቅምዋጋቀሪ የተደረገው የዕዳ መጠን ነው፡፡

10. <u>የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች የዓይነት ጥቅም</u>

የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች የዓይነት ጥቅም ዋጋ ተቀጣሪው ላገኘው የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች አገልግሎት ቀጣሪው በወሩ በከፈለው ጠቅላላ የቅጥር ገቢ እና ተቀጣሪው ለእነዚሁ አገልግሎቶች በከፈለው መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

11. <u>የመኖሪያ ቤት ወይም የማረፊያ የዓይነት ጥቅም</u>

1. ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያቀርበው የመኖሪያ ቤት የዓይነት ጥቅም ዋጋ፣ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤቱ ባለቤት ቀጣሪ ሲሆን በወሩ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤቱ ትክክለኛ የገበያ ኪራይ እና ተቀጣሪው ለማረፊያ ወይም መኖሪያ ቤቱ በከፈለው መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡
2. ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያቀርበው የመኖሪያ ቤት የዓይነት ጥቅም ዋጋ፣ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤቱን ቀጣሪው የተከራየው ሲሆን ቀጣሪው በወሩ ለማረፊያ

ወይም ለመኖሪያ ቤቱ በከፈለው ኪራይ እና ተቀጣሪውለማረፊያ ወይም መኖሪያ ቤቱ በከፈለው የኪራይ መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

12. **የቅናሽ ወለድ ብድር የዓይነት ጥቅም**

1. ቀጣሪ ለተቀጣሪ በሚሰጠው ብድር ላይ ተቀጣሪው የሚከፈለው ወለድ ከገበያው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ የሚያንስ ከሆነ የቅናሽ ወለድ ብድር የዓይነት ጥቅም ነው፡፡
2. የቅናሽ ወለድ ብድር የዓይነት ጥቅም ዋጋ ተቀጣሪው በወሩ በብድሩ ላይ ወለድ የከፈለ ከሆነ፣ በወሩ በከፈለው ወለድ እና ብድሩን የወሰደው በገበያ የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ቢሆን ኖሮ በወሩ ይከፍል በነበረው ወለድ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

13. **የምግብ ወይም የመጠጥ አገልግሎት የዓይነት ጥቅም**

ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያቀርበው የምግብ ወይም መጠጥ አገልግሎትየዓይነትጥቅምዋጋቀጣሪውየምግብ ወይም የመጠጥ አገልግልቱን ለማቅረብ ባወጣው ጠቅላላ ወጪ እና ተቀጣሪው ለምግብ ወይም ለመጠጥ አገልግልቱ በከፈለው የገንዘብ መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

14. **የተሽከርካሪ የዓይነት ጥቅም**

1. ቀጣሪ በሙሉ ወይም በከፊል ለተቀጣሪ የግል ጥቅም የሚያቀርበው ተሽከርካሪ የተሽከርካሪ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የወር የተሽከርካሪ የዓይነት ጥቅም ዋጋ በሚከተለው ቀመር መሠረት የተሰላው የገንዘብ መጠን ይሆናል፦

$$\frac{ሀ \times 5\%}{12}$$

ለዚህም፡- "ሀ" ቀጣሪ የተሽከርካሪው ባለቤትለመሆን ያወጣው ወጪ ወይም ቀጣሪው ተሽከርካሪውን ተከራይቶ ከሆነ፣ ተሽከርካሪውን በተከራየበት ጊዜ የነበረው የተሽከርካሪው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው፤ ሆኖም ተሽከርካሪው ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ የገባ እንደሆነ የተሽከርካሪውየዓይነት ጥቅም ዋጋ

ተሽከርካሪው ከቀረጥና ታክስ ነጻ ባይደረግ ኖሮ በተሽከርካሪው ላይ ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ መጠን ይጨምራል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከሚሰላው የተሽከርካሪ የዓይነት ጥቅም ዋጋ ላይ የሚከተሉት ተቀናሽ ይደረጋሉ፡-
   ሀ) በተሽከርካሪው ለመጠቀም ወይም ለተሽከርካሪው ጥገና እና የመጠቀሚያ ወጪ ተቀጣሪው የፈፀመው ማንኛውም ክፍያ፤
   ለ) ተቀጣሪው ሥራውን ለማከናወን ተሽከርካሪውን የተጠቀመበት መጠን፤
   ሐ) በወር ውስጥ ተሽከርካሪው ለተቀጣሪው የግል ጥቅም ያልቀረበበት መጠን፡፡
4. ተሽከርካሪውበቀጣሪውይዞታስርከአምስትዓመት በላይ የቆየ ከሆነ፣ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ቀመር ሥር የተመለከተው የ "ሀ" ዋጋ በንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚወሰነው የገንዘብ መጠን 50 በመቶ (ሃምሳ በመቶ) ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ "ለተቀጣሪ የግል ጥቅም የቀረበ ተሽከርካሪ" የሚለው አገላለጽ ተቀጣሪው ተሽከርካሪውን በማንኛውም ጊዜ ለግል ጉዳይ ባይጠቀምበትም ለተቀጣሪ የግል ጥቅም የቀረበን ተሽከርካሪ ይጨምራል፡፡

15.<u>የግል ወጪዎች የዓይነት ጥቅም</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለተቀጣሪው የግል ጥቅም የሚያስገኝ እስከሆነ ድረስ በቀጣሪ ለግል ወጪ የተከፈለ ገንዘብ የግል ወጪ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡
2. የግል ወጪ የዓይነት ጥቅም ዋጋ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንደ ግል ወጪ የዓይነት ጥቅም የሚቆጠር ወጪ መጠን ይሆናል፡፡
3. ይህ አንቀጽ ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚከፍለውን በዚህደንብ ከአንቀጽ 18 ከተመለከተው በስተቀር በዚህ ክፍል በሌላ አንቀጽ የዓይነት ጥቅም ነው የተባለን ወጪ አይመለከትም፡፡

16.<u>የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም</u>

1. ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያስተላልፈው ንብረት ወይም የሚያቀርበው አገልግሎት የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም፡-

ሀ) ቀጣሪ ንብረቱን ወይም አገልግሎቱን እንደመደበኛ ሥራው ለደንበኞች የሚያቀርብ ከሆነ የንብረቱን ወይም የአገልግሎቱ መሸጫ ዋጋ 75 በመቶ (ሰባ አምስት በመቶ)፣ ወይም

ለ) በሌላሁኔታየንብረቱወይምየአልግሎቱመሸጫ ዋጋ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚወሰነው የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም ዋጋ ተቀጣሪው ለንብረቱ ወይም ለአገልግሎቱ በከፈለው የገንዘብ መጠን ይቀነሳል፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) ዓላማ የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ ቀጣሪ የሚሰጠው ነጻ ወይም ድጎማ የተደረገበት የአየር ጉዞ ትኬት ከሆነ፣ የትኬቱ የመሸጫ ዋጋ ቀጣሪው ለበረራው የኢኮኖሚ ደረጃየሚያስከፍለው መደበኛ ዋጋ ይሆናል፡፡

17.<u>የሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ የዓይነት ጥቅም</u>

1. ባለአክሲዮን የመሆን መብትን ወይም ምርጫን በመጠቀም የተደለደለ አክሲዮኖችን ጨምሮ በሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ መሠረት ለተቀጣሪ አክሲዮን መደልደል የሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡

2. በሠራተኛ የአክሲዮን ዕቅድ መሠረት ለተቀጣሪ የሚሰጥ ባለአክሲዮን የመሆን መብት ወይም ምርጫ ዋጋ እንደ ዓይነት ጥቅም አይቆጠርም ወይም ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ውስጥ አይካተትም፤ሆኖም፡-

ሀ) ተቀጣሪው በመብቱ ወይም በምርጫው የሚጠቀም ከሆነ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ይሆናል፤ ወይም

ለ) ተቀጣሪው መብቱን ወይም ምርጫውን የሚያስተላልፍ ከሆነ መብቱ ወይም ምርጫው በምድብ "ለ" ሥር ግብር እንደሚከፈልበት ሀብት ተቆጥሮ የአዋጁ አንቀጽ 59 ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ የዓይነት ጥቅም ዋጋ አክሲዮኖች በተደለደለበት ቀን በነበራቸው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ እና ተቀጣሪውለአክሲዮኖች በከፈለው መዋጮ መካከል ያለው ልዩነትይሆናል፡፡

4. በሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ መሠረት ለተቀጣሪ የተደለደለ አክሲዮኖች ለሌላ ሰው የመተላለፍ ገደብ የተጣለባቸው ከሆነ፣ ተቀጣሪው የአክሲዮን ዕቅድ ጥቅሙን ያገኘው፦
   ሀ) አክሲዮኖቹን ያለገደብ ማስተላለፍ በሚችልበት፣ ወይም
   ለ) አክሲዮኖቹን በሚያስተላልፍበት፣ ከሁለቱ በቀደመው ጊዜ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የአክሲዮኑ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሠራተኞች ዕቅድ ጥቅሙ በተገኘበት ጊዜ ይወሰናል፡፡
6. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ በሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ መሠረት ለተቀጣሪ ከተደለደለ አክሲዮኖች ጋር በተገናኘ "የተቀጣሪ መዋጮ" ማለት ተቀጣሪው፣
   ሀ) ለአክሲዮኖቹ፣ እና
   ለ) ባለአክሲዮን ለመሆን ለተሰጠው መብት ወይም ምርጫ የሚከፍለው የገንዘብ መጠን ነው፡፡

18.**<u>ሌላ የዓይነት ጥቅም</u>**

1. "ሌላ የዓይነት ጥቅም" ማለት ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያቀርበውና በዚህ ክፍል ሌሎች አንቀጾች ያልተመደበ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡
2. የሌላ የዓይነት ጥቅም ዋጋ ጥቅሙ የተገኘበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ በሚወሰን የጥቅሙ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ እና ተቀጣሪ ለጥቅሙ በፈፀመው ማንኛውም ክፍያ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

19.**<u>በዓይነት ጥቅም ላይ የተጣለ የግብር ገደብ</u>**

1. በዚህ ምዕራፍ የተደነገገው ቢኖርም በዓይነት ጥቅሞች ላይ የሚከፈለው ጠቅላላ ግብር በማንኛውም ሁኔታ ተቀጣሪው በወሩ ከሚያገኘው የደመወዝ ገቢ10 በመቶ (አስር በመቶ) መብለጥ የለበትም፡፡
2. ለዚህአንቀጽአፈጻጸምደመወዝከቅጥር ጋር የተያያዙ ሌሎች ጥቅማጥቅሞች አይጨምርም፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ከውጭ ሀገር የተገኘ የቅጥር ገቢ</u>**

20.**<u>በውጭ ሀገር ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ</u>**

1. አዋጁ አንቀጽ 93(1) በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ቀጣሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ላቋቋመው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የተቀጠረን ሰው ሳይጨምር በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ባልሆነ ሰው በተቀጠረ የኢትዮጵያ ነዋሪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ተቀጣሪ በማንኛውም ወር በውጭ ሀገር በመቀጠር ገቢ ያገኘ እና በዚሁ ገቢ ላይ በውጭ ሀገር ግብር የከፈለ እንደሆነ፣ ተቀጣሪው ከሚከተለት ከሚያንሰው ጋር እኩል በሆነ መጠን የግብር ማካካሻ የማግኘት መብት ይኖረዋል፦
   ሀ) ውጭ ሀገር የከፈለው ግብር፣ ወይም
   ለ) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ተቀጣሪ የውጭ ሀገር ገቢ ላገኘበት ወር ተፈጻሚ በሚሆነው ከመቀጠር የሚገኝገቢ ግብር የማስከፈያ አማካይ መጣኔን መሠረት በማድረግ የሚሰላው ተቀጣሪው በውጭ ሀገር ገቢው ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፍለው ግብር፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ለተፈቀደው የግብር ማካካሻ አፈጻጸም "የንግድ ሥራ ገቢ ግብር" በሚል የተጠቀሰው "ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ግብር" እንዲሁም "የግብር ዓመት" በሚል የተጠቀሰው "ለወር" እንደሚያገለግል በመውሰድ የአዋጁ አንቀጽ 45(3)፣(4) እና (5) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡-
   ሀ) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ተቀጣሪን በሚመለከት "ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር የማስከፈያ አማካይ መጣኔ" ማለት ማንኛውም የግብር ማካካሻከመደረጉ በፊት ተቀጣሪው በወር ግብር በሚከፍልበት ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ላከፍል የሚገባውከመቀጠርየሚገኝገቢግብርመቶኛነው፤
   ለ) "በውጭ ሀገር ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ" ማለት በአዋጁ ሠንጠረዥ "ሀ" መሠረት ግብር የሚከፈልበት የውጭ ሀገር ገቢ ነው፤
   ሐ) "የውጭ ሀገር ገቢ ግብር" ማለት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ግብር ጨምሮ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር አካባቢያዊ መንግሥት የተጣለ ግብር ሲሆን፣ ቅጣትን፣ ተጨማሪ ግብርን ወይም ይህንን ግብር በሚመለከት የሚከፈል ወለድን አይጨምርም፡፡
   መ) "ነዋሪ ተቀጣሪ" ማለት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ተቀጣሪ ነው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## የሠንጠረዥ “ለ” ገቢ

**21.ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፍን የኪራይ ክፍያ**

የአዋጁ አንቀጽ 15(5) ተፈጻሚ የሚሆንበት አከራይ ወይም የተከራይ አከራይ ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፍን የቤት ኪራይ ገቢ የተቀበለ እንደሆነ፣ አከራዩ ወይም የተከራይ አከራዩ በዚህ ዓይነት የተቀበለው ጠቅላላ የቤት ኪራይ ገቢ መጠን፣ ገቢውን በተቀበለበት የግብር ዓመት እንደተገኘ ተደርጎ ይቆጠራል፤ ሆኖም በዚህ የገቢ መጠን ላይ የሚከፈለው ግብር የቤት ኪራይ ገቢው ለሚሸፍነው የግብር ዓመታት በማከፋፈል ይሰላል፡፡

**22.የንግድ ሥራ ሀብቶች ኪራይ**

የንግድ ሥራ መደበኛ ተግባር አካል የሆኑ ዕቃዎችን፣ መሣሪያዎችን እና ቤቶችን ጨምሮ የንግድ ሥራን በማከራየት የሚገኝ ገቢ በአዋጁ ሠንጠረዥ “ሐ” መሠረት ግብር ይከፈልበታል፡፡

**23.የኪራይቤት፣የቤትዕቃናመሣሪያየእርጅናቅናሽ**

ለአዋጁ አንቀጽ 15(7)(ሐ) ዓላማ በአንድ የግብር ዓመት ለኪራይ ቤት፣ ለቤት ዕቃና መሣሪያ የተፈቀደው የእርጅና ቅናሽ የሚወስነው በአዋጁ አንቀጽ 25 እና በዚህ ደንብ ክፍል አምስት ንዑስ ክፍል ሁለት መሠረት ሆኖ፣ የሚከተለትን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡-

1. የኪራይ ቤቱ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ሆኖ፣ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መዋቅራዊ ማሻሻያ የተደረገ መሆኑን፤
2. ከቤቱ ጋር የተከራየ ማንኛውም የቤት ዕቃ እና መሣሪያ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት መሆኑን፡፡

**24.የቤት ኪራይ ኪሣራዎች**

1. የሂሣብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት በአዋጁ አንቀጽ 15(7)(ሐ) መሠረት የተፈቀደለት ተቀናሽ ወጪ ከግብር ዓመቱ ጠቅላላ የቤት ኪራይ ገቢው የሚበልጥ ከሆነ፣ በብልጫ የሚታየው የገንዘብ መጠን በግብር ዓመቱ እንደደረሰ የቤት ኪራይ ኪሳራ ይቆጠራል፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 26 እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 42 “ኪሣራ” በሚል የተጠቀሰው “ለቤት ኪራይ ኪሣራ” እንደሚያገለግል በመውሰድ እነዚህ አንቀጾች የቤት ኪራይ ኪሣራ ለደረሰበት ግብር ከፋይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 25.ከውጭ ሀገር የቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢ ያለው እና በዚሁ ገቢ ላይ በውጭ ሀገር ግብር የከፈለ እንደሆነ፣ ግብር ከፋዩ ከሚከተለት ከሚያንሰው ጋር እኩል በሆነ መጠን የግብር ማካካሻ የማግኘት መብት ይኖረዋል፦

   ሀ) ውጭ ሀገር የከፈለው ግብር፤ ወይም

   ለ)ግብር ከፋዩ የተጣራ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይገቢ ላገኘበት የግብር ዓመት ተፈጻሚ በሚሆነው ከቤትኪራይበሚገኝገቢላይግብርየማስከፈያ አማካይ መጣኔን መሠረት በማድረግ የሚሰላው ግብር ከፋዩ በውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢው ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፍለው ግብር፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ለተፈቀደው የግብር ማካካሻ አፈጻጸም "የንግድ ሥራ ገቢ ግብር" በሚል የተጠቀሰው "ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ ግብር" እንደሚያገለግል በመውሰድ የአዋጁ አንቀጽ 45(3)፣(4) እና (5) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፦

   ሀ) በአንድ የግብር ዓመት የኢትዮጵያ ነዋሪን በሚመለከት "ከቤት ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር የማስከፈያ አማካይ መጣኔ" ማለት ማንኛውም የግብር ማካካሻ ከመደረጉ በፊት በግብር ዓመቱ ነዋሪው ግብር በሚከፍልበት ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቤት ኪራይ ገቢ ግብር መቶኛ ነው፤

   ለ) "የውጭ ሀገር ገቢ ግብር" ማለት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ግብር ጨምሮ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር የክልል መንግሥት የተጣለ ግብር ሲሆን፣ ቅጣትን፣ ተጨማሪ ግብርን ወይም ይህንን ግብር በሚመለከት የሚከፈል ወለድን አይጨምርም፤

   ሐ) "በውጭ ሀገር ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ" ማለት በአዋጁ ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ግብር የሚከፈልበት የውጭ ሀገር ገቢ ነው፤

   መ) በአንድ የግብር ዓመት የኢትዮጵያ ነዋሪ ግብር ከፋይን በሚመለከት "የተጣራ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢ" ማለት ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢ ላይ ገቢውን ከማግኘት ጋር

በተገናኘ በአዋጁ አንቀጽ 15(7) መሠረት የተፈቀደ ተቀናሽ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገቢ ነው፡፡

26.**የሚከራይአዲስቤትንስለማስታወቅ**

ለአዋጁ አንቀጽ 17(1) አፈፃፀም የአዱስ ቤት ግንባታ መጠናቀቁን ወይም ቤቱ መከራየቱን የማሳወቂያ ጊዜ ግንባታው በተጠናቀቀ ወይም ቤቱ በተከራየ ከሁለቱ በቀደመው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## የሠንጠረዥ "ሐ" ገቢ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ተቀናሽ ወጪዎች

27.**የውክልና ወጪ**

ለአዋጁ አንቀጽ 27(1)(ቀ) ዓላማ "የውክልና ወጪ" ማለት የግብር ከፋዩ ሠራተኛ የንግድ ሥራውንለማስተዋወቅ እና ለማሳደግ እንግዶችን ከንግድ ሥራ ቦታው ውጪ ለመቀበል የሚያወጣው የመስተንግድ ወጪ ነው፡፡

28.**ለውጭ ሀገር አበዳሪ የተከፈለ ወለድ ተቀናሽ የሚደረግበት ሁኔታ**

በአዋጁ አንቀጽ 23(2)(ሀ)(2) መሠረት ለውጭ ሀገር አበዳሪ የተከፈለ ወለድ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለውአበዲሪው ብድር ለመስጠት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኘበትን ሰነድ ቅጂ ተበዲሪው ለባለሥልጣኑ ካቀረበ ብቻ ነው፡፡

29.**ለሠራተኞች የተደረገ የህክምና ወጪ**

በሠራተኞች የጤና ዕቅድ መሠረት ቀጣሪ በተቀጣሪ ስም የሚከፍለውን የጤና መድን አረቦን ጨምሮ ለሠራተኛው የህክምና አገልግሎት የሚያወጣው ወጪ በአዋጁ አንቀጽ 22(1)(ሀ) መሠረት ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

30.**የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ተቋሞች ለሠራተኞች የሚያቀርቡት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት**

1. ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች ወይም የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ሌሎች ተቋሞች ለሠራተኞቻቸው የሚያቀርቡት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ወጪ በአዋጁ አንቀጽ 22(1)(ሀ) መሰረት ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
2. በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ (1) መሠረትተቀናሽ የሚደረገው ወጪ ገደብ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

31.<u>የንግድ ሥራ ማስታወቂያ ወጪ</u>

በአዋጅ አንቀጽ 22(1) "ሀ" መሠረት የሚፈቀድ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር የተደረገ የንግድ ሥራ ማስታወቂያ ወጪ የተቀናሽ ገደብ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

32.<u>የተከራየውን የንግድ ሥራ ሀብት በራሱ ወጪ የሚያድስ፣ የሚጠግን ወይምየሚያሻሽል ተከራይ</u>

ከአከራዩ ጋር ከገባው ውል ውጪ በገዛ ፈቃደ የተከራየውን የንግድ ሥራ ሀብት በራሱ ወጪ የሚያድስ፣ የሚጠግን ወይም የሚያሻሽል ተከራይ ለዕድሳቱ፣ ለጥገናው ወይም ለማሻሻያ ያደረገው ወጪ ከንግድ ሥራ ገቢው ላይ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

33.<u>ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረግ ስጦታ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 24(1) ለበጎ አድራጎት ዓላማለሚደረጉ ስጦታዎች የተፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ግብር ከፋዩ ራሱ ለሚያካሂደው የበጎ አድራጎት ተግባር ለሚያውለው ወጪ ጭምር ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. ለአዋጁ አንቀጽ 24(1)(ለ) አፈጻጸም በመንግስት የተደረገ ጥሪ ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግስት የሚደረግ ጥሪ ሲሆን በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚደረግ ጥሪን ይጨምራል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም "በጎ አድራጎት ተግባር" ማለት ከታክስ ከፋይ ሠራተኞቹ ውጭ ለሌሎች ተረጂዎች የሚሰጥ የትምህርት፣ የጤና፣ የአካባቢ ጥበቃ ወይም ላላ ሰብዓዊ እርዳታ ነው፡፡

34.<u>በካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል መሰረት ለተያዘ የንግድ ሥራ ሀብት የሚፈቀድ ተቀናሽ</u>

1. በካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል መሰረት ለተያዘ የንግድሥራሀብትየሚፈጸምየኪራይክፍያ ከጠቅላላ የንግድ ስራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቀናሽ የተፈቀደለት ሰው በንብረቱ ላይ የእርጅና ቅናሽ አይታሰብለትም፡፡

35.<u>የዋና መሥሪያ ቤት ወጪ</u>

በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ለሚሠራ ድርጅቱ ጥቅም ያደረገውን ትክክለኛ ወጪ ለመተካት በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት የሚፈጽመው ክፍያ ተቀናሽ የሚደረገው፣ ወጪው የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት፣ለንግደ ሥራ ዋስትና ለመስጠት ወይም የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል የተደረገ እንደሆነ ነው፡፡

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

<u>የእርጅና ቅናሽ</u>

36.<u>ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት የላላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ግብር ከፋይ፣
   ሀ) በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የሂሣብ ሪፖርት ሲያዘጋጅ አንድ ዓይነት የእርጅና ቅናሽ ዘዴ የተጠቀመ ከሆነ፣ እና
   ለ) በባለቤትነት ለያዛቸው ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች ሁለ አንድ ዓይነት የእርጅና ቅናሽ ዘዴ የተጠቀመ ከሆነ፣

   በአዋጁ አንቀጽ 25(1) መሠረት የሚፈቀድለትን የእርጅና ቅናሽ በዚህ ደንብ አንቀጽ 37 በተመለከተው ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዳ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ 38 በተመለከተው ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት ላወስን ይችላል፡፡
2. የሚከተለትሀብቶችየእርጅናቅናሽመሰላት ያለበት በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ ብቻ ይሆናል፦

ሀ) ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች፣

ለ) በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ፡፡

3. በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ የእርጅና ቅናሽ ሲሰላ በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ወጪ ማሻሻያው ያረፈበትን መሬት ወጪ መጨመር የለበትም፡፡

4. ማንኛውም ግብር ከፋይ "አስተላላፊ" ተብል ከሚጠራ ግንኙነት ያለው ሰው ላገኘው እና በአስተላላፊው ሙሉ የእርጅና ቅናሽ ላገኘበት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ህልዎትየላለው የንግድ ሥራ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ማግኘት አይችልም፡፡

## 37.ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ

1. የአዋጁ አንቀጽ 25(3) እና (4) እንደተጠበቁ ሆነው፣ለአንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋውለሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ህልዎት ለላለው የንግድ ሥራ ሀብት የተፈቀደው በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት የሚወሰን የእርጅና ቅናሽ በዚህ ደንብ አንቀጽ 39 የተመለከተውን መጣኔ በሀብቱ ወጪ ላይ ተፈጻሚ በማድረግ ይሰላል፡፡

2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው የተያዘው የግብር ዓመት እና የቀደሙት የግብር ዓመታት ሁለለአንድ ግብር ከፋይ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ህልዎት የላለው የንግድ ሥራ ሀብት የተፈቀደ ወይም የአዋጁ አንቀጽ 25(4) ድንጋጌ ባይኖር ኖሮ ይፈቀድ የነበረ ጠቅላላ ተቀናሽ ወጪ ከሀብቱ ወጪ ሊበልጥ አይገባም፡፡

## 38.ዋጋው እየቀነስ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ

1. የአዋጁ አንቀጽ 25(3) እና (4) እንደተጠበቁ ሆነው፣ለአንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው ለሚቀንስሀብትየተፈቀደውዋጋውእየቀነሰ በሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዳ መሠረት የሚወሰን የእርጅና ቅናሽ በዚህ ደንብ አንቀጽ 39 የተመለከተውን መጣኔ በዓመቱ መጀመሪያ ባለው የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ ተፈጻሚ በማድረግ ይሰላል፡፡

2. በአንድ የግብር ዓመት የአዋጁ አንቀጽ 25(4) ድንጋጌ ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ ከሆነ፣ የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀብቱ በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ገቢን ለማግኘት ብቻ ጥቅም ላይ እንደዋለ በመውሰድ ይሰላል፡፡

3. የግብር ከፋዩ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ቀሪ ዋጋ ከብር ሁለት ሺህ የማይበልጥ ከሆነ በአንድ ጊዜ በወጪነት ይያዛል፡፡

39. <u>የእርጅና ቅናሽ መጣኔዎች</u>

1. ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የእርጅና ቅናሽ መጣኔ በሚከተለት ምድቦች እና ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ተፈፃሚ ይደረጋል፤

| ዋጋው የሚቀንስ ሀብት | የቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መጣኔ |
|---|---|
| ኮምፒውተር፣ ሶፍትዌር እና የመረጃ ማከማቻ መሣሪያ | 20 በመቶ |
| ግሪንሀውስ | 10 በመቶ |
| ግሪንሀ ውስን ሳይጨምር በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ | 5 በመቶ |
| ላላ ማንኛውም ዋጋው የሚቀንስ ሀብት | 15 በመቶ |
| ለማዕድን እና ነዳጅ የልማት ሥራዎች ጥቅም ላይ የሚውል ዋጋው የሚቀንስ ሀብት | 25 በመቶ |

2. ግዙፋዊ ህልዎት ለላላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ተፈጻሚ የሚሆነው የእርጅና ቅናሽ መጣኔ፡-

ሀ) የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ ሀያ አምስት በመቶ፣

ለ) በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ውጪ ለሆነ ከአስር ዓመት በላይ ለሚያገለግል ግዙፋዊ ህልዎት የላለው የንግድ ሥራ ሀብት አስር በመቶ፣ ወይም

ሐ) ለላላማንኛውምግዙፋዊሀልዎትየላለው የንግድ ሥራ ሀብት መቶ በመቶን ግዙፋዊ ሀልዎት ለላለው ሀብት የአገልግልት ዘመን በማካፈል የሚገኘው መጣኔ፣ ይሆናል፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ" ማለት ግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚያወጣው በአዋጁ አንቀጽ 25(7)(ሀ) ለ "ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች" በተሰጠው ትርጉም ተራ ቁጥር (4) የተመለከተው ወጪ ነው፡፡

40.<u>በከፊልለንግድስራበዋለሕንጻላይየሚታሰብየእርጅና ቅናሽ</u>

አንድ ሕንጻ በንግድ ሥራ ሀብትነት በከፊል በሚያገለግልበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለንግድ ሥራ አገልግልት በዋለው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

41.<u>ጥገናዎችና ማሻሻያዎች</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ላደረገው የጥገና ወይም ማሻሻያ ወጪ በግብር ዓመቱ የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ሀብቱ በግብር ዓመቱ መጨረሻ ካለው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀያ በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡
3. በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ የተደረገ የጥገና ወይም የማሻሻያ ወጪ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀያ በመቶ የሚበልጥ ከሆነ የጥገናው ወይም የማሻሻያው ሙሉ ወጪ በሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ ይጨመራል፡፡

<u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>

<u>ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>

42.<u>ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>

አንድ ግብር ከፋይ በአዋጁ አንቀጽ 26፣ 39፣ ወይም 46 መሠረት የሚሸጋገር ኪሣራ፡-

1. ከአንድ የግብር ዓመት በላይ ያጋጠመው ከሆነ ግብር ከፋዩ መጀመሪያ የገጠመው ኪሣራ በቅድሚያ ይቀነስለታል፤
2. ኪሣራ ሊሸጋገር የሚችለው ኪሣራውን የሚያሳየው የግብር ከፋዩ የሂሣብ መዝገብ ኦዲት የተደረገ እና በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ብቻ ነው፤
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ግብር ከፋዩ፡-
   ሀ) ኪሣራየሚያሳየውንበውጪ ኦዲተር ኦዱት የተደረገ የሒሣብ መዝገብ ለባለሥልጣኑ ያቀረበ እንደሆነ፣ እና
   ለ) የቀጣዩ የግብር ዓመት የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት የታክስ ባለሥልጣኑ የግብር ከፋዩን የሂሣብ መዝገብ ኦዲት ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ፣ ኪሣራውን ሊያሸጋግር ይችላል፤
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ የታክስ ባለሥልጣኑን በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 28 መሠረት ኪሣራውን በመመርመር የተሻሻለ የግብር ስላት ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ የመስጠት መብቱን አያስቀርም፡፡

43.<u>ኪሳራን ወደ ኃላ ሄድ ስለማሸጋገር</u>

ለአዋጁ አንቀጽ 32 አፈጻጸም ከረጅም ጊዜ ውል ጋር ተያይዞ የሚያጋጥም ኪሣራ ተካክሶ እስከሚያልቅ ድረስ ወደኋላ ሊሸጋገር ይችላል፡፡

<u>ንዑስ ክፍል አራት</u>

<u>የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም እና ኪሣራ</u>

44.<u>የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም እና ኪሣራ</u>

1. ግብር ከፋይ ከውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ያገኘው ጥቅም በንግድ ሥራ ገቢው ውስጥ ይካተታል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እና የሚከተለት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በአንድ የግብር ዓመት የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ የገጠመው ግብር ከፋይ ኪሣራውን በግብር ዓመቱ ከውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ካገኘው ጥቅም ጋር ማካካስ የሚችል ሲሆን፣
   ሀ) ያላካካሰውን የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ መጠን በማንኛውም ጊዜ ካገኘው የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም ጋር በሙሉ እስኪካካስ ድረስ ኪሣራውን ላልተወሰነ ጊዜ ማሸጋገር ይችላል፤
   ለ)ግብርከፋዩየደረሰበትንኪሣራመጠን ባለሥልጣኑን በሚያሳምን አኳኋን

ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ የገጠመው የፋይናንስ ተቋም ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ተፈጻሚ የማይደረግ ሲሆን፣ የፋይናንስ ተቋሙ የደረሰበትን ኪሣራ መጠን ባለሥልጣኑን በሚያሳምን አኳኋን ማረጋገጥ ከቻለ የኪሣራው መጠን እንደተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል፡፡
4. ግብር ከፋይ የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሬ ጥቅም አገኘ ወይም ኪሣራ ገጠመው የሚባለው ጥቅሙ ወይም ኪሣራው እውን ሲሆን ነው፡፡
5. ግብር ከፋይ በውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም ማግኘቱን ወይም የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ ያጋጠመው መሆኑን ለመወሰን ከግብይቱ ጋር በተያያዘ ግብር ከፋዩ ራሱ ወይም ግንኙነት ያለው ሰው በገባው ከኪሣራ ሥጋት የመድን ውል ያለው አቋም ከግምት መግባት ይኖርበታል፡፡
6. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፣
   ሀ) "የዕዳ ግዴታ" ማለት ገንዘብ ለላላ ሰው ለመክፈል የተገባ ግዴታ ሲሆን ተከፋይ ሂሣብን እና ከቃልኪዳን ሰነድች፣ ከሃዋላ ሰነድች ወይም ከቦንድች የሚመነጩ ግዴታዎችን ይጨምራል፤
   ለ) "የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም" ማለት ከውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት ጋር በተገናኘ በውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መዋዠቅ ምክንያት የተገኘ ጥቅም ነው፤
   ሐ) "የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ" ማለት ከውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት ጋር በተገናኘ በውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መዋዠቅ ምክንያት የደረሰ ኪሣራ ነው፤
   መ)"የውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት" ማለት የንግድ ሥራገቢ.ለማግኘትበሚከናወንየንግድሥራ ሂደት የተደረገ ከዚህ በታች የተመለከተ ማንኛውም ግብይት ነው፡-
      (1) በውጭ ሀገር ገንዘብ የሚደረግ ግብይት፤
      (2) በውጭ ሀገር ገንዘብ የተገለፀን የዕዳ ግዴታ መስጠት ወይም መቀበል፤ ወይም
      (3) በውጭ ሀገር ገንዘብ የተገለፀ ላላ ማንኛውም ግብይት፤

ሠ) “ከኪሣራ ስጋት የመዳን ውል” ማለት አንድ ሰው በውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መዋዠቅ ምክንያት ከላላ ውል ጋር በተገናኘ በፋይናንስ ረገድ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልን ሥጋት ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የሚገባው ውል ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል አምስት

## ባንኮች እና የመድን ኩባንያዎች

### 45.የባንኮች ኪሣራ መጠባበቂያ

ማንኛውም ባንክ በአንድ የግብር ዓመት ለኪሣራ የያዘው የመጠባበቂያ ሒሣብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ሂሣብ በተቀመጠ የጥንቃቄ መሥፈርት መሠረት እስከተሰላ እና ከፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ እስከሆነ ድረስ በግብር ዓመቱ የመጠባበቂያ ሂሣቡ መጠን ሰማንያ በመቶ በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል፡፡

### 46.የጠቅላላ መድን ኩባንያዎች ጊዜው ያላለፈ ሥጋት መጠባበቂያ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ በአንድ የግብር ዓመት ጊዜው ላላለፈ ሥጋት የያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን በሂሣብ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተሰላ እስከሆነ ድረስ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚታየው ቀሪ የመጠባበቂያ ሂሣብ ለግብር ዓመቱ በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል፡፡
2. በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ የመድን ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የመድን ሥራ የሚሠራ ከሆነ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተቀናሽ ወጪ የሚያዝለት መጠን ኩባንያው በኢትዮጵያ ውስጥ ጊዜው ላላለፈ ሥጋት በያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ የተወሰነ ይሆናል፡፡
3. ጠቅላላ መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ የአንድ ግብር ዓመት ንግድ ሥራ ገቢ እንደሁኔታው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት ባለፈው የግብር ዓመት በተቀናሽ ወጪ የተያዘለትን ጊዜያቸው ላላለፉ ሥጋቶች የያዘውን የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን ይጨምራል፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “ጠቅላላ መድን” ማለት በንግድ ሕግ ከተገለፀው የህይወት መድን በስተቀር ማንኛውም መድን ነው፡፡

47. <u>የህይወት መድን ንግድ ሥራ ግብር የሚከፈልበት ገቢ</u>

1. የህይወት መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ የአንድ ግብር ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሰላል፡-

   (ሀ+ለ+ሐ+መ) -(ሠ+ረ+ሰ+ሸ)

   ለዚህም ቀመር አፈፃፀም፡-

   ሀ) የህይወት መድን ለገዙ ደንበኞች ኩባንያው የመለሰውን አረቦን ሳይጨምር በአንድ ዓመት ውስጥ ያገኘው የህይወት መድን አረቦን፤

   ለ) በዓመት ውስጥ ከህይወት መድን ሥራ ጋር በተያያዘ ኩባንያው ያገኘው የኢንቨስትመንት ገቢ፤

   ሐ) በዓመቱ ለተሰረዙ የህይወት መድን ፖሊሲዎች ኩባንያው ባለፉት ጊዜያት በተቀናሽ ወጪ የተያዘለት ማናቸውም የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን፤

   መ) ኩባንያውበዓመቱከህይወትመድንሥራ ያገኘው ሌላ ማንኛውም ገቢ፤

   ሠ) ኩባንያው ከሚያካሂደው የህይወት መድን ሥራ ጋር በተያያዘ የኮሚሽን ክፍያዎችን፣ የጠለፋ ዋስትና አረቦንን፣ የሥጋት ትንትና ወጪዎችን፣ በፖሊሲው ላይ የሚጠየቁ የመንግሥት ክፍዎችን እና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን ጨምሮ በዓመቱ ከመድን ፖሊሲ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ያወጣው ወጪ፤

   ረ) በዓመቱ ላወጣቸው አዱስ የህይወት መድን ፖሊሲዎች የያዘውን መነሻ የመጠባበቂያ ሂሣብ ጨምሮ የያዘው ተጨማሪ የህይወት መድን ፖሊሲ መጠባበቂያ ሂሣብ፤

   ሰ) በዓመቱ ከተከፈለ የህይወት መድን ፖሊሲዎች ጋር በተገናኘ ከያዘው ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን እና በዚሁ ሂሣብ ላይ ካገኘው ገቢ በላይ በህይወት መድን ፖሊሲዎች መሠረት ለቀረቡ የህይወት መድን ክፍያ ጥያቄዎች የፈፀመው ክፍያ፣ እና“ሸ” ከህይወት መድን ሥራ ጋር በተገናኘ ኩባንያው በዓመቱ ውስጥ ያወጣው ሌላ ማንኛውም ተቀናሽ ወጪ ነው፡፡

2. አንድ ኩባንያ ከህይወት መድን ሥራ በተጨማሪየጠቅላላ መድን ሥራን ጨምሮ በሌላ ማንኛውም የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ እንደሆነ ከህይወት መድን ሥራ

የሚያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከላላው የንግድ ሥራ ገቢው ተለይቶ ለብቻው መሰላት አለበት፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የህይወት መድን" በንግድሕግ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

**ንዑስክፍልስድስት**

**ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች**

48. **የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ**

ለአዋጁ አንቀጽ 82 አፈጻጸም ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንደ ግለሰብ ተቆጥረው የዓመቱን የሽያጭ ገቢያቸውን መሠረት በማድረግ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

**ንዑስ ክፍል ሰባት**

**የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች**

49. **በግምት ላይ ተመስርቶ የሚከፈል የደረጃ "ሐ" ግብርከፋዮች የንግድ ሥራ ግብር**

1. በግምት ላይ ተመስርቶ የሚከፈል የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች የንግድ ሥራ ግብር የሚሰላው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡
2. የአንድ ግብር ከፋይ ዓመታዊ ግብር የሚሰላው የግብር ከፋዩ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ በሚወድቅበት የገቢ ማዕቀፍ ውስጥ ያለውን ዓመታዊ ከፍተኛ ጠቅላላ ገቢ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
3. ሚኒስትሩ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የንግድ ሥራ ግብር የሚሰላበትን ሠንጠረዥ ቢያንስ በየሶስት ዓመቱ ማሻሻል አለበት፡፡
4. የተሽከርካሪ ባለንብረት የሆነ ግብር ከፋይ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚጠቀምበትን ተሽከርካሪ ራሱ የሚያሽከረክር ከሆነ ሊከፍል የሚገባው ግብር ሲሰላ ሾፌር ቢቀጥር ኖሮ ሾፌሩ በቅጥር ገቢው ላይ ሊከፍል ይገባ የነበረው ግብር መታከል አለበት፡፡

## ክፍልስድስት

## የሠንጠረዥ “መ” ገቢ

**50.አልፎ አልፎ ሀብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ**

ለአዋጁ አንቀጽ 58 አፈጻጸም “አልፎ አልፎ ሀብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ” ማለት በንግድ ሥራ ላይ በመደበኛነት ያልተሰማራ ሰው የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ነው፡፡

**51.በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ወደ ውጭ የሚልከው ትርፍ**

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት ወደ ውጭ በሚልከው ትርፍ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 62 መሠረት ግብር የሚጣለው የድርጅቱን የግብር ዓመት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
2. በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ወደ ውጭ የሚልከው ትርፍ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሠላል፦

   ሀ+(ለ-ሐ)-መ

   ለዚህም ቀመር አፈፃፀም፡-

   “ሀ” በግብር ዓመቱ መጀመሪያ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ሀብት ያለው ጠቅላላ የተጣራ ዋጋ፤

   “ለ” በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተሰላ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት የግብር ዓመቱ የተጣራ ትርፍ፤

   “ሐ” በግብር ዓመቱ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ባገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ የሚከፈለው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር፤ እና

   “መ” በግብር ዓመቱ መጨረሻ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ሀብት ያለው ጠቅላላ የተጣራ ዋጋ፤

   ነው፡፡
3. በአንድየግብርዓመትበቋሚነትየሚሠራድርጅት ወደ ውጭ ለሚልከው ትርፍ ስላት በግብር ዓመቱ መጨረሻ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ሀብት ጠቅላላ ዋጋ በቀጣዩ የግብር ዓመት መጀመሪያ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ሀብት ያለው ጠቅላላ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

**52.የንግድ ትርፍ መጠን መስተካከለ በተከፋፋለ ትርፍ ድርሻ ላይ የሚኖረው ውጤት**

አንድ ድርጅት ለባለስልጣኑ ያሳወቀው የንግድ ሥራ ትርፍ መጠን ባለስልጣኑ ባደረገው ኦዱት ከደረሰበት ግኝት ያነሰ መሆኑ ድርጅቱ ባሳወቀው ትርፍ ላይ ተመስርቶ ለባለአክስዮኖች ባከፋፈለው የትርፍ ድርሻ ላይ በተከፈለው ግብር ላይ ውጤት አይኖረውም፡፡

53.<u>የካፒታል ሀብቶችን በስጦታ በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚከፈል ግብር</u>

1. ለአዋጁ አንቀጽ 59 አፈጻጸም የካፒታል ሀብትን በስጦታ በማስተላለፍ የሚከፈለው ታክስ የሚታሰበው በስጦታ በተላለፈው ንብረት የመጀመሪያ ዋጋ እና ንብረቱ በስጦታ በተላለፈበት ጊዜ ባለው ዋጋ መካከል በሚታየው ልዩነት ላይ ነው፡፡
2. የካፒታል ሀብቶችን በስጦታ በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ የተቀባዩ ነው፡፡

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ከገቢ ግብር ነጻ የሆነ ገቢ</u>

54.<u>ከገቢ ግብር ነጻ የሆነ ገቢ</u>

1. የሚከተለት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው፡-
   ሀ) በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶች ለእውቀት ሽግግር ከውጭ ሀገር ለሚያስመጧቸው ባለሙያዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚከፈላቸው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤
   ለ) በአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ አንድ ሰው በተደጋጋሚ ለአንድ ቀጣሪ የሰጠው አገልግሎት ሲደመር ከአንድ ወር የሚበልጥ ከሆነ ተቀጣሪው የሚከፍለው ግብር የሚታሰበው በመጨረሻው ቅጥር ባገኘው ገቢ ላይ ብቻ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በማንኛውም የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ቀጣሪሳያቋርጥም ሆነ በተደጋጋሚ ከሠላሳ ቀናትላልበለጠ ጊዜ ያገለገለ ማንኛውም ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ የሚያገኘው ገቢ፤
   ሐ) ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) አፈጻጸም “ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ” ማለት መደበኛ የሙያ ሥልጠና ያልወሰደ ልዩ ሙያ በሚጠይቁ ማሽኖችና መሣሪያዎች የማይጠቀም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ከ30 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የተቀጠረ ግለሰብ ነው፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 65(1) ሀ (1) መሠረት ከግብር ነጻ የተደረገው አሠሪው ሠራተኛው ሲታመምለሠራተኛው ህክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ በሠራተኞች የጤና መድን አቅድ መሠረት አሠሪው ለሠራተኞች ጥቅም የሚከፍለውን አረቦን ይጨምራል፡፡

**ክፍል ስምንት**

**ሀብቶች**

**55.ሀብትን ማስተላለፍ እና በባለቤትነት መያዝ**

ለእርጅና ቅናሽ እና የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ለሚከፈል ግብር ዓላማ ምዝገባ የሚፈጸምበት ሀብት በሽያጭ፣ በልውውጥ ወይም በስጦታ ሲተላለፍ አስተላላፊው ሀብቱን እንዲስተላላፈ የሚቆጠረው እና የተላለፈለት ሰው ሀብቱን በባለቤትነት እንደያዘ የሚቆጠረው የሽያጭ፣ የልውውጥ ወይም የስጦታ ውለ ውል ለመዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

**56.ዋጋ**

1. በአዋጁ የተመለከተው የምድብ “ሀ” ግብር የሚከፈልበት ሀብት ዋጋ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ይደረግበታል፡፡
2. አንድ ግብር ከፋይ በባለቤትነት የሚይዘው ሀብት፦
   - ሀ) በአዋጁ መሠረት ግብር በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የሚጠቃለል የገንዘብ መጠን ከሆነ፣ የሀብቱ ዋጋ ሀብቱን በባለቤትነት ለመያዝ በግብር ከፋዩ የተከፈለን ማንኛውንም የገንዘብ መጠን እና ግብር በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የሚጠቃለለውን የገንዘብ መጠን ይጨምራል፤ ወይም
   - ለ) ከግብር ነጻ የሆነ ገቢ ከሆነ፣ የሀብቱ ዋጋ ሀብቱንበባለቤትነት ለመያዝ በግብር ከፋዩ የተከፈለን ማንኛውንም የገንዘብ መጠን እና ከግብር ነጻ የሆነውን የገንዘብ መጠን ይጨምራል፡፡

**57.የአክስዮን መተላለፍ**

በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የሚያስተላልፈው አክስዮን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተገናኘ ከሆነ አክስዮኑ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተላላፈ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## አስተዳደራዊ እና የሥነ-ሥርዓት ደንቦች

58.በደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች የሚያዝ የሂሳብ ሰነድ

1. የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች በቀላል የሂሳብ አያያዝ ዘዴ ከሚይዙት የሂሳብ መዝገብ ጋር አያይዘው የሚያቀርቡትን ሰነድ ባለስልጣኑ በመመሪያ ይወስናል፡፡
2. የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች የተመለከተውን መስፈርት አሟልተው የተገኙ እንደሆነ በፈቃደኝነት በአክሩዋል የሂሣብ አያያዝ ዘዴ ሂሣባቸውን መያዝ ይችላል፡፡

59.በደረጃ “ሐ” ግብርከፋዮችየሚያዝየሂሳብመዝገብና ሰነድ

1. ለአዋጁ አንቀጽ 82(3) አፈጻጸም የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ሊይዙ የሚገባውን የሂሳብ መዝገብ ሊይዙ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዓይነት መዝገብ የያዙ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች ግብር የሚወሰነው በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባገኘው የሂሳብ መዝገባቸው መሠረት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ ሠራተኛ የሚቀጥር ከሆነ ለሠራተኛው የሚከፍለውን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እና ከዚሁ ገቢ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረውን ማንኛውንም ግብር የሚያሳይ ሰነድ መያዝ አለበት፡፡

60.በደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች የሚከፈል ግብር

1. ለአዋጁ አንቀጽ 49 አፈጻጸም የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች በዓመታዊ የሽያጭ መጠን ላይ የተመሰረተ የግምት መደበኛ የቁርጥ ግብር ወይም አመላካች ባላቸው የንግድ ሥራ ዘርፎች የቁርጥ ግብር ዘዳዎች መሰረት ግብር ይከፍላሉ፡፡
2. በትራንስፖርት የንግድ ሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ቀንሰው የሚያስቀሩትን ግብር የሚከፍሉት ከንግድ ሥራ ትርፍ ግብር ጋር በአንድነት ይሆናል፡፡

61.ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብርን ተቀናሽ ስላለማድረግ

ለአዋጁ አንቀጽ 92 አፈጻጸም ሚኒስትሩ፡-

1. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ የመያዝ ሥርዓት ተፈጻሚ የማይደረግባቸውን የአገልግሎት ዓይነቶች፣
2. ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ የማይመለከታቸውን ሰዎች፣

በመመርያ ይወስናል፡፡

62.<u>በሀገርውስጥከሚፈጸሙክፍያዎችላይግብርቀንሶ ስለማስቀረት</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 92 መሠረት ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው በዚሁ አንቀጽ መሠረት ግብር ተቀንሶ ክፍያ ለሚፈጸምለት ሰው ተከታታይ ቁጥር ያለው ሕጋዊ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡
2. ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው የመንግሥት ተቋም ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ደረሰኝ በሚኒስቴሩ የተፈቀደ መሆን አለበት፡፡
3. ከመንግሥት ተቋም በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ላለበት ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 19 ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

63.<u>ግብርን ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ላለበት ሰው የንግድ ፍቃድ የማቅረብ ግዴታ</u>

በአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ከሚቀርበው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በተጨማሪ ማንኛውም ግብር ከፋዩ የንግድ ፈቃድ የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

64.<u>ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ መያዝ ስላለበት ሰው ኃላፊነት</u>

1. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ለባለስልጣኑ የማስተላለፍ ግዴታ የተጣለበት ሰው ግዴታውን ያልተወጣ ቢሆንም ግብር ከፋዩ ግብሩን የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ የአዋጁ አንቀጽ 97(3) ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 102 (1) የተጣለውን ቅጣት አያስቀርም፡፡

65.<u>ዘግይቶስለሚቀርብየሂሳብመዝገብ</u>

1. የሂሳብ መዝገብ ዘግይቶ በመቅረቡ ምክንያት ተቀባይነት አያጣም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ፡-
   ሀ) የሂሳብ መዝገብ ባለመቅረቡ ምክንያት በግምት በተወሰነ ግብር ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤
   ለ) በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 102 የተጣለውን ቅጣት አያስቀርም፡፡

66.<u>የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ የሚገኝ ገቢ</u>

ለአዋጁ አንቀጽ 74 አፈጻጸም ገቢን የሚያስገኝ የንግድ ሥራ ያቆመ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፍልበት አሠራር ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ

67.<u>በቡድን የተያዙ ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች</u>

1. አዋጁ ተፈጻሚ መሆን በጀመረበት ጊዜ በቡድን የተያዘ ቀሪ የእርጅና ቅናሽ ያለው ግብር ከፋይ ቀሪውን የእርጅና ቅናሽ በተሻረው አዋጅ መሠረት ያገኛል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ የሚሆንበት ግብር ከፋይ በቡድን የተያዙ ቀሪ የእርጅና ቅናሽ ውስጥ ያለን ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ያስተላለፈ እንደሆነ፣ የእርጅና ቅናሽ ስላት መሠረቱ ሀብቱን በማስተላለፍ ባገኘው ጥቅም መጠን ይቀንሳል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ዋጋው የሚቀንስ ሀብት በመተላለፉ ምክንያት የቡድኑ የእርጅና ቅናሽ የስላት መሠረት ከዜሮ በታች የገንዘብ መጠን የሚኖረው ከሆነ፡-
   ሀ) ከዜሮ በታች የሚታየው የገንዘብ መጠን በግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ይጨመራል፤እንዲሁም
   ለ) የቡድኑየእርጅናቅናሽሂሣቡተዘግቶበቡድኑ ውስጥ የቀረ ማንኛውም ሀብት የእርጅና ቅናሹን እንደጨረሰ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
4. አዋጁ ተፈጻሚ መሆን በጀመረበት ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ባለቤት የሆነ ግብር ከፋይ የእርጅና ቅናሽ በዚህ ደንብ አንቀጽ 38 መሠረት የሚሰላለት ሲሆን፣ የሀብቱ ወጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው በቡድኑ የተያዘ ቀሪ የእርጅና ቅናሽ ውስጥ አይካተትም፡፡

68.<u>የንግድ ሥራ ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>

1. በተሻረው አዋጅ መሠረት ተቀናንሶ ያላለቀ የንግድ ሥራ ኪሣራ ያለው ግብር ከፋይ የእርጅና ቅናሹ በተሻረው አዋጅ መሠረት ሙለ በሙለ ያልተቀናነሰ ከሆነ ቀሪው ኪሣራ በተሻረው አዋጅ መሠረት ይቀነስለታል፡፡

2. ለአዋጁ አንቀጽ 26(4) አፈጻጸም በተሻረው ሕግ ያጋጠመ ማንኛውም ኪሣራ ከግምት ውስጥ አይገባም፡፡

69.<u>በመመሪያዎች የተፈቀደ የግብር ነጻ መብቶች</u>

አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በሚኒስትሩ በወጣ መመሪያ የተፈቀደ ከግብር ነጻ የመሆን መብት፡-

1. በመመሪያው መሠረት መብቱ ተፈጻሚ መሆን እስከሚያበቃበት ቀን፣ ወይም
2. መመሪያው በሚኒስትሩ እስከሚሻርበት ቀን፣ ከሁለቱ እስከቀደመው ጊዜ ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

70.<u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994(እንደተሻሻለው) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
2. የተሻረው ደንብ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊትለነበረው የግብር ዓመት ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል፡፡

71.<u>ደንቡየሚፀናበትቀን</u>

ይህ ደንብ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 18 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ኃይለማሪያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዳራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሉክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**አዋጅ ቁጥር 983/2008**

**የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ**

የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ የታክስ አስተዳደሩ ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተገማችነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የአገር ውስጥ ታክሶች ሁሉ የሚመሩበ.ት ራሱን የቻለ የታክስ አስተዳደር አዋጅ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፤

በታክስ ሕጎች አተረጓጎም ረገድ በታክስ አስተዳደሩ ውስጥ በሚፈጠረው ልዩነት ምክንያት ታክስ ከፋዩ ሲያጋጥመው የነበረውን እንግልት ለማስቀረት የሚያስችል ወጥነት ያለው የአተረጓጎም ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

ታክስ ከፋዮች በታክስ ውሳኔ ረገድ የሚኖራቸውን ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበት ተደራሽነት ያለው፣ በሚገባ የተደራጀ እና የተቀላጠፈ ውሳኔ መስጠት የሚያስችል የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55 (1) እና (11) መሠረት እንደሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

ይህንን አዋጅ ጨምሮ ለታክስ ሕጎች አፈፃፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. “የተሻሻለ የታክስ ስሌት” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 መሠረት ባለሥልጣኑ የሚሰጠው የተሻሻለ የታክስ ስሌት ነው፤
2. “ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳኔ” ማለት፡-

ሀ/ በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ፤

ለ/ የሚከተሉትን ሳይጨምር ባለሥልጣኑ የሚሰጠው ሌላ ማንኛውም ውሳኔ፦

1) የታክስ ውሳኔ፤

2) የታክስ ውሳኔ በመስጠት ሂደት ባለሥልጣኑ የሚሰጠው ውሳኔ፤

3. “የጸደቀ ቅጽ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 79 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

4. “ባለሥልጣን” ማለት፦

ሀ/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፤

ለ/ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ፤

ሐ/ የድሬዳዋ ገቢዎች ቢሮ ማለት ነው፤

5. “ድርጅት” ማለት ኩባንያ፣ የሽርክና ማህበር፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅት ወይም ሌላ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ ሀገር የተመሠረተ የሰዎች ድርጅት ነው፤

6. “ኮሚሽን” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 መሠረት የተቋቋመው የግብር ይግባኝ ኮሚሽን ነው፤

7. “ኩባንያ” ማለት የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ለመሥራት የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን፣ በሌላ ሀገር ሕግ መሠረት የተመሠረተን ተመሳሳይ የንግድ ድርጅት ይጨምራል፤

8. “ወሳኝ ድምፅ ያለው አባል” ማለት ኩባንያን በሚመለከት፣ ለራሱ ጥቅም ሲል ብቻውን ወይም ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፦

ሀ/ በኩባንያው ካለው ጥቅም ጋር ተያይዞ 50% ወይም ከዚያ በላይ ድምፅ የመስጠት መብት ያለው፤

ለ/ በኩባንያው ካለው ጥቅም ጋር ተያይዞ 50% ወይም ከዚያ በላይ የትርፍ ድርሻ የሚያገኝ፤ ወይም

ሐ/ በኩባንያው ካለው ጥቅም ጋር ተያይዞ 50% ወይም ከዚያ በላይ የካፒታል ድርሻ ያለው አባል ነው፤

9. “ሰነድ” የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ/ የሂሳብ መዝገብ፣ ሪከርድ፣ የመመዝገቢያ ሰነድ፣ የባንክ መግለጫ፣ ደረሰኝ፣ ኢንቮይስ፣ ቫውቸር፣ ውል ወይም ስምምነት፣ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 መሠረት ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል የተሰጠ የምስክር ወረቀት ወይም መግለጫ፤ ወይም

ሐ/ በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ማከማቻ መሳሪያ ውስጥ የተከማቸ /የተያዘ/ ማንኛውም መረጃ ወይም ዳታ፤

10. “በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት” ማለት ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 መሠረት በግምት የሚያከናውነው የታክስ ስሌት ነው፤

11. “የበጀት ዓመት” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የበጀት ዓመት ነው፤

12. “የስጋት የታክስ ስሌት” ማለት ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 መሠረት ከስጋት በመነሳት የሚያከናውነው የታክስ ስሌት ነው፤

13. “የገንዘብ ክፍያ ትእዛዝ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 መሠረት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትእዛዝ ነው፤

14. “ዓለም አቀፍ ስምምነት” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሌላ ሀገር መንግሥት ወይም መንግሥታት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

15. “ዓለም አቀፍ ድርጅት” ማለት ሉዓላዊ ሥልጣን ያላቸው ሀገራት ወይም የእነዚህ ሀገራት መንግሥታት አባል የሆኑበት ድርጅት ነው፤

16. “ክፍያ ለዘገየበት የሚከፈል ወለድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 መሠረት የታክስ ክፍያ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈል ወለድ ነው፤

17. “የታክስ ወኪል” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96 ወይም አንቀጽ 97 መሠረት ፈቃድ የተሰጠው የታክስ ወኪል ነው፤

18. “ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን” ማለት ፈቃድ፣ የምስክር ወረቀት፣ ስምምነት፣ ወይም ሌላ መብት ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

19. “ሥራ አስኪያጅ” ማለት፦

ሀ/ ለሽርክና ማህበር ሲሆን ሽሪኩ ወይም የሽርክና ማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅወይም በዚህ ደረጃ የሚሠራ ወይም ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውን ሰው፤

ለ/ ለኩባንያ ሲሆን፣ የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራአስኪያጅ፣ ወይም በኩባንያው ውስጥ ተመሳሳይ ሥልጣን ያለው ወይም በዚህ ደረጃ የሚሠራ ወይም ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውን ሰው፤

ሐ/ ለሌላ ለማንኛውም ድርጅት፣ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም በኩባንያው ውስጥ ተመሳሳይ ሥልጣን ያለው ሰው ወይም በዚህ ችሎታ የሚሠራ ወይም ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውን ሰው ነው፤

20.“አባል” ማለት ድርጅትን በሚመለከት በኩባንያ ውስጥ የአክሲዮን ባለቤት የሆነ ወይም በሽርክና ማህበር ውስጥ አባል የሆነን ሰው ጨምሮ በድርጅት ውስጥ የአባልነት ጥቅም ያለው ሰው ነው፤

21.“የአባልነት ጥቅም” ማለት ድርጅትን በሚመለከት በኩባንያ ውስጥ ያለን አክሲዮን ወይም በሽርክና ማህበር ውስጥ ያለን ጥቅም ጨምሮ በድርጅት ውስጥ ያለ የባለቤትነት ጥቅም ነው፤

22.“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወይም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር ነው፤

23.“የሽርክና ማህበር” ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመ የሽርክና ማህበር ሲሆን በውጭ ሀገር ሕግ መሠረት የተቋቋመን ተመሳሳይ አካልም ይጨምራል፤

24.“ቅጣት” ማለት የታክስ ሕግ በመጣሱ ምክንያት በዚህ አዋጅ ክፍል አሥራ አምስት ምዕራፍ ሁለት ወይም በሌላ የታክስ ሕግ የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት ነው፤

25.“የገንዘብ ቅጣት ውሳኔ” ማለት ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ክፍል አሥራ አምስት ምዕራፍ ሁለት መሠረት የሚወስነው የገንዘብ ቅጣት ነው፤

26.“ሰው” ማለት ግለሰብ፣ ድርጅት፣ መንግሥት፣ የመንግሥት አስተዳደር አካል ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው፤

27.“በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ ኃላፊነት” ማለት አንድ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 (4)፣ 40(3)(ሐ)፣ 41(12)፣ 42 (8)፣ 43 (10)፣ 46 (1)፣ 47 (1) ወይም 48 (1) ያለበትን ኃላፊነት (“የመጀመሪያ ኃላፊነት ተብሎ የሚጠቀስ”) በመወጣት ረገድ ሌላ ሰው ያለበት ኃላፊነት ነው፤

28.“በታክስ ከፋዩ የተከናወነ ስሌት” ማለት ታክሱን የማስላት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሠረት ያከናወነው የታክስ ስሌት ነው፤

29.“የታክስ ስሌት ማስታወቂያ” ማለት፦

ሀ/ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የግብር ማስታወቂያ፤

ለ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የተጨማሪ እሴት ታክስ

ማስታወቂያ፤

ሐ/ ወደ ሀገር ውስጥ በገባው ዕቃ ላይ የሚከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፤

መ/ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ፤

ሠ/ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ፤

ረ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሠረት የሚቀርብ በቅድሚያ የሚከፈል ታክስ ማስታወቂያ፤ ወይም

ሰ/ በታክስ ሕግ መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ተብሎ የሚጠቀስ በታክስ ከፋዩ የሚዘጋጅ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ፤

30.“ታክሱን የማስላት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ” ማለት ራሱ ያከናወነውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማቅረብ የሚገደድ ሰው ነው፤

31.“ታክስ” ማለት በታክስ ሕጐች መሠረት የሚጣል ታክስ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ በከፋዩ ተቀንሶ የሚቀር ታክስ፤

ለ/ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት አስቀድሞ የሚከፈል ወይም በየጊዜው የሚከፈል ታክስ፤

ሐ/ ቅጣት፤

መ/ ክፍያ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈል ወለድ፤

ሠ/ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚከፈል ሌላ ማንኛውም ግብር፤

32.“የታክስ ስሌት” ማለት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ፣ በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት፣ የስጋት የታክስ ስሌት፣ የተሻሻለ የታክስ ስሌት፣ አስተዳደራዊ የታክስ ቅጣት ወይም ወለድ ስሌት፣ ወይም በታክስ ሕግ መሠረት የሚደረግ ሌላ ማንኛውም ስሌት ነው፤

33.“ከታክስ የመሸሽ ድንጋጌ” ማለት፡-

ሀ/ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ፤ እና

ለ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፤

የተመለከቱት ከታክስ የመሸሽ ድንጋጌዎች ናቸው፤

34.“የታክስ ውሳኔ” ማለት፡-

ሀ/ በታክስ ከፋዩ የተከናወነውን የታክስ ስሌት የማይጨምር የታክስ ስሌት፣

ለ/ ታክሱን የማስላት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ፣

ሐ/ በታክስ ከፋዩ እንዲከፈል ወይም ለወደፊት እንዲከፈል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40(2) መሠረት የተሰጠ ውሳኔ፣

መ/ በሁለተኛ ደረጃነት የሚመጣን ኃላፊነት ወይም ታክስን ለማስከፈል የሚወጣን ወጭ ማስመለስን በሚመለከት የሚሰጥ ውሳኔ፣

ሠ/ ክፍያ በመዘግየቱ ምክንያት የሚጣልን ወለድ በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ፣

ረ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 ወይም አንቀጽ 50 መሠረት በቀረበ የታክስ ተመላሽ ማመልከቻ ላይ የሚሰጥ የእምቢታ ውሳኔ፣

ሰ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 መሠረት ሊካካስ ከሚችለው በላይ የሆነን የታክስ ተመላሽ መጠን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት የሚቀርብን የተመላሽ ጥያቄ መጠን ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት እንደገና መከፈል የሚኖርበትን የተመላሽ መጠን አስመልክቶ የሚሰጥ ውሳኔ፣ ወይም

ሸ/ ለባለሥልጣኑ ያልተከፈለ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ የቀረን ታክስ በሚመለከት በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92 (3) መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ፣

35.“የታክስ ማስታወቂያ” ማለት የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ/ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት መቅረብ የሚኖርበት የታክስ ማስታወቂያ፣

ለ/ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ታክስ በሚመለከት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፣

ሐ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ የሚቀርብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ፣

መ/ ወደ ሀገር ውስጥ በገባው ዕቃ ላይ የሚከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣

ሠ/ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፣

ረ/ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፣

ሰ/ በዚህ አዋጅ መሠረት በታክስ ከፋዩ መቅረብ የሚኖርበት የታክስ ማስታወቂያ፣

36.“የታክስ ሕግ” ማለት፦

ሀ/ ይህ አዋጅ፤

ለ/ የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ፤

ሐ/ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፤

መ/ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፤

ሠ/ የቴምብር ቀረጥ አዋጅ፤

ረ/ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፤

ሰ/ የጉምሩክን ሕግ ሳይጨምር፣ ባለሥልጣኑ ታክሱን፣ ቀረጡን ወይም ክፍያውን የማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ይህንን ታክስ፣ ቀረጥ፣ ወይም ክፍያ የሚጥል ሌላ ሕግ፤

ሸ/ ከዚህ በላይ ባሉት የፌደል ተራዎች ሥር በተጠቀሰው ሕግ መሠረት የሚወጣ ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ነው፤

37.“የታክስ ሠራተኛ” ማለት፦

ሀ/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፤

ለ/ የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤

ሐ/ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት የታክስ ሕግን የማስተዳደርና የማስፈፀም ኃላፊነት የተጣለባቸው ሌሎች የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ወይም ተቀጣሪዎች፤

መ/ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የታክስ ባለሥልጣን ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች፤

ሠ/ ባለሥልጣኑን ወክለው ሲሰሩ፦

1) የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ አባል

2) የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ተቀጣሪ ወይም ባለሥልጣን፤ ወይም

3) የክልል ታክስ ባለሥልጣን ተቀጣሪ ወይም ባለሥልጣን፤

38.“የታክስ ጊዜ” ማለት ከታክስ ጋር በተያያዘ ለባለሥልጣኑ ማስታወቂያ የሚቀርብበት ታክስ የሚሸፍነው ጊዜ ነው፤

39.“ታክስ ለማስከፈል የወጡ ወጪዎች” ማለት፦

ሀ/ ባለሥልጣኑ ያልተከፈለን ታክስ ለማስከፈል የሚያወጣቸው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 (3) የተዘረዘሩ ወጪዎች፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41(9) (ሀ) የተዘረዘሩት ባለሥልጣኑ ታክስ ለማስከፈል የሚያስችልን ሀብት ሲይዝ የሚያወጣቸው ወጪዎች ናቸው፤

40.“የታክስ እንደራሴ” ማለት ታክስ ከፋዩን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውንም ገንዘብ ለመቀበል ወይም ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ/ የሽርክናን ማህበር በተመለከተ የሽርክና ማህበሩ ሽሪክ ወይም ሥራ አስኪያጅ፤

ለ/ ኩባንያን በተመለከተ የኩባንያው ዳይሬክተር፤

ሐ/ ችሎታ የሌለውን ግለሰብ በተመለከተ ችሎታ የሌለውን ግለሰብ በመወከል ወይም ለዚህ ግለሰብ ጥቅም ገቢ የሚቀበል ህጋዊ ወኪል፤

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 የተጠቀሰውን ታክስ ከፋይ በተመለከተ በተጠቀሰው አንቀጽ መሠረት የታክስ ከፋዩ ባለአደራ፤

ሠ/ ማንኛውንም ታክስ ከፋይ በተመለከተ ለታክስ ሕጎች ዓላማ ሲባል ባለሥልጣኑ በጽሁፍ በተሰጠ ማስታወቂያ የታክስ ከፋዩ የታክስ እንደራሴ እንደሆነ ያስታወቀው ግለሰብ ነው፤

41.“ታክስ ከፋይ” ማለት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ሲሆን የሚከተሉትንም ይጨምራል፦

ሀ/ የገቢ ግብርን በተመለከተ በሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” መሠረት በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሌለው በግብር እፎይታ ላይ ያለ ወይም ኪሳራ ያጋጠመው ሰው፤

ለ/ የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ወይም የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው፤

ሐ/ የተርን ኦቨር ታክስን በተመለከተ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ሰው፤

42.“ያልተከፈለ ታክስ” ማለት በመክፈያ ቀን ወይም ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 የተመለከተውን የታክስ መክፈያ ቀን ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ታክስ ነው፤

43.“ታክስ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው” ማለት በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው፤

44.“ተቀንሶ የሚያዝ ታክስ” ማለት በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ መያዝ ያለበት ታክስ ነው፤

45.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

### 3. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ

1. የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 79 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለታክስ ሕጎች ዓላማ በአንድ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ዋጋ ነው የሚባለው የዕቃው፣ የንብረቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የጥቅሙ የወቅቱ እና የቦታው መደበኛ የገበያ ዋጋ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት በአንድ የተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የአንድን ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዋጋውን ለመወሰን ባልተቻለው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም እና ማንኛውም ሌላ ተመሳሳይ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም በሚያስገኘው ትክክለኛ ዋጋ መካከል ላለው ልዩነት ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የሚገኘው ዋጋ ዋጋውን ለመወሰን ያልተቻለው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሆኖ ይወሰዳል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አፈጻፀም፣ አንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ከሌላ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ጋር ተመሳሳይ ነው የሚባለው ከሌላው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ጋር በባህሪ፣ በጥራት፣ በብዛት፣ በሚሰጠው አገልግሎት፣ በሚይዛቸው ቁሶችና በመልካም ስም ተመሳሳይ ወይም በሚቀራረብ ሁኔታ ተመሳሳይ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡
4. የአንድን ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ዋጋ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ከዋጋ አገማመት ጠቅላላ መርሆዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ትክክለኛው የገበያ ዋጋ በባለሥልጣኑ የሚወሰን ይሆናል፡፡
5. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ለዕቃ፣ ለንብረት፣ ለአገልግሎት ወይም ለጥቅም የተከፈለ ዋጋ ከዕቃው፣ ከንብረቱ፣ ከአገልግሎቱ ወይም ከጥቅሙ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የበለጠ ወይም ያነሰ ሊሆን ይችላል፡፡
6. ባለሥልጣኑ የአንድን ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 4. ግንኙነት ያላቸው ሰዎች

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለታክስ ሕጎች አፈፃፀም ሁለት ሰዎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው የሚባለው ከሁለቱ አንዱ ሰው በሌላኛው ሰው ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ አስተያየት ወይም ፍላጎት መሠረት ይንቀሳቀሳል ተብሎ ሲገመት ወይም ሁለቱም ሰዎች በሌላ ሦስተኛ ወገን ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ ሃሣብ ወይም ፍላጎት መሠረት ይንቀሳቀሳሉ ተብሎ ሲታመን ነው፡፡
2. አንድ ሰው የሌላ ሰው ተቀጣሪ ወይም ደምበኛ ስለሆነ ብቻ ወይም ደግሞ ሁለቱም ሰዎች የሦስተኛ ወገን ተቀጣሪዎች ወይም ደንበኞች በመሆናቸው ብቻ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው ሊባሉ አይችሉም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚከተሉት ሰዎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡-

   ሀ/ ባለሥልጣኑ ከሁለቱ አንዱ በሌላኛው ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ አስተያየት ወይም ፍላጎት መሠረት አይንቀሳቀስም ብሎ ካላመነ በስተቀር፣ አንድ ግለሰብና የዚህ ግለሰብ ዘመድ፤

   ለ/ አንድ ድርጅት ወይም የዚህ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ የዚህ ድርጅት አባል በራሱ ወይም ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ጋር በመሆን በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑና በተሳሰሩ ድርጅቶች አማካይነት የድርጅቱን 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ወይም ከዚያ በላይ የመምረጥ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም የካፒታል ድርሻ መብት የሚቆጣጠር ሲሆን ድርጅቱና የድርጅቱ አባል ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው፤

   ሐ/ ሁለት ድርጅቶች ግንኙነት ያላቸው ናቸው የሚባሉት አንድ ሰው ብቻውን ወይም የዚህ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆኑበት ሁኔታ ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በመሆን የሁለቱን ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ወይም ካፒታል በቀጥታ ወይም በሌሎች በተሳሰሩ ድርጅቶች አማካይነት 25 % (ሃያ አምስት በመቶ) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የመምረጥ መብት፣ የተቆጣጠረ እንደሆነ ነው፡፡
4. የአንድ ግለሰብ ዘመዶች ናቸው የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

   ሀ/ የትዳር ጓደኛ፤

ለ/ ቅድመ አያት፣ አያት፣ ወደታች የሚቆጠር ዘመድ፣ ወንድም፣ እህት፣ አጎት፣ አክስት፣ የወንድም ልጅ፣ የእህት ልጅ፣ የእንጀራ እናት፣ የእንጀራ አባት፣ የጉዲፈቻ ልጅ፤

ሐ/ የጉዲፈቻ ልጅ ወላጅ፣ ወይም የእርሱ/ሷ ባል ወይም ሚስት፤

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) የተገለጹት ግለሰቦች ባል ወይም ሚስት፡፡

5. የአንድ ግለሰብ የትዳር ጓደኛ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ / ግለሰቡ/ቧ በህጋዊ መንገድ ያገባው/ችው፤

ለ/ጋብቻ ሳይኖር ከግለሰቡ/ቧ ጋር እንደባልና ሚስት አብሮ/ራ የሚኖር /የምትኖር፡፡

6. አንድ የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አድራጊዎች የአንደኛ ደረጃ ዘመዶች ጋር ዝምድና እንዳለው ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የታክስ ሕጎችን ስለማስተዳደር

### 5. የባለሥልጣኑ ኃላፊነት

የታክስ ሕጎችን ሥራ ላይ የማዋልና የማስፈፀም ኃላፊነት የባለሥልጣኑ ነው፡፡

### 6. የታክስ ሠራተኞች ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

1. የታክስ ሠራተኛ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ እና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 8 (3) በሚሰጠው ውክልና መሠረት ለታክስ ሕጐች አፈፃፀም ሲባል የተሰጠውን ማንኛውንም ሥልጣኑን ሊሠራበት ወይም ማንኛውንም ተግባርና ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

2. የታክስ ሠራተኛ በታክስ ሕጐች በተሰጠው ማንኛውም ሥልጣኑ የሚሠራው ወይም ማንኛውንም ተግባርና ኃላፊነቱን የሚወጣው ታማኝነትና ፍትሐዊነትን በተላበሰ መንገድ መሆን የሚገባው ሲሆን ታክስ ከፋዩንም በአክብሮት የማስተናገድ ኃላፊነት አለበት፡፡

3. የታክስ ሠራተኛ ከሚከተሉት ጋር በተያያዘ በታክስ ሕጐች የተሰጠውን ሥልጣን ሊሠራበት ወይም ኃላፊነቱን ወይም ተግባሩን ሊያከናውን አይችልም፦

ሀ/ የቀረበለት ጉዳይ ከሠራተኛው የግል፣ የቤተሰብ፣ የንግድ፣ የሙያ፣ የቅጥር ወይም የፋይናንስ ግንኙነት ካለው ሰው ጋር የተገናኘ ከሆነ፤

ለ/ በሌላ መልኩ የጥቅም ግጭት የሚያስከትል ከሆነ፡፡

4. የታክስ ሠራተኛ ወይም ሥራው በቀጥታ የሚመለከተው የሚኒስቴሩ ሠራተኛ የታክስ ሂሣብ ሠራተኛ ወይም አማካሪ ወይም የታክስ ማስታወቂያ ለሚያዘጋጅ ወይም ታክስን አስመልክቶ ምክር ለሚሰጥ ሰው የሂሳብ ሠራተኛ ወይም አማካሪ በመሆን ሊያገለግል ወይም የዚህ ሰው ተቀጣሪ እንዲሆን የቀረበለትን ሀሳብ ሊቀበል አይችልም፡፡

7. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማናቸውም የፌደራል እና የክልል መንግሥት፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ ኤጀንሲ ወይም ሌላ አካል፣ የአካባቢ አስተዳደሮች፣ ማህበራት፣ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የታክስ ሕጎችን በማስፈፀም ረገድ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

8. <u>የታክስ መረጃ በምስጢር የሚያዝ ስለመሆኑ</u>

1. የታክስ ሠራተኛ በሥራው አጋጣሚ ያገኛቸውን የማንኛውም መረጃዎችና እና ሰነዶች ሚስጢራዊነት መጠበቅ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የታክስ ሠራተኛ ለሚከተሉት ሰዎች አንድን ሰነድ ወይም መረጃ ከመግለጽ አይከለክለውም፡-

ሀ/ ኃላፊነቱን ይወጣበት ዘንድ ለባለሥልጣኑ ሌላ ሠራተኛ፤

ለ/ በታክስ ሕግ የተደነገገን የታክስ ወንጀል የፈፀመን ሰው ለመክሰስ እንዲሁም በሌላ ማናቸውም ሕግ የተደነገገን የታክስ ወንጀል የፈፀመን ሰው ለመክሰስ ይቻል ዘንድ ለሕግ አስፈጻሚ አካል፤

ሐ/ ለኮሚሽኑ ወይም ክርክርን በማየት ላይ ላለ ፍርድ ቤት የአንድን ሰው የታክስ ኃላፊነት ለማረጋገጥ ወይም የቅጣት ኃላፊነትን ወይም ታክስ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈል ወለድን ወይም ለወንጀል ጉዳይ የሚያስፈልግ መረጃ፤

መ/ ኢትዮጵያ ባደረገችው ስምምነት የመረጃ ልውውጥን የሚመለከት አንቀጽ የታከለ ከሆነ በስምምነቱ በተፈቀደው መሠረት አግባብ ላለው የውጭ አገር መንግሥት አካል የሚሰጥ መረጃ፤

ሠ/ ለፌደራል ዋናው ኦዲተር ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገው መረጃ፤

ረ/ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገው መረጃ፤

ሰ/ ለክልል የታክስ ባለሥልጣን የሚያስፈልገው መረጃ፤

ሸ/ የሚሰጠው መረጃ አንድን ግለሰብ ለይቶ የማያሳውቅ ሲሆን፣ የመንግሥትን ገቢ የመሰብሰብ አገልግሎት ለሚሰጥ ወይም ለስታትስቲክስ መሥሪያ ቤት ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገው መረጃ፤

ቀ/ መረጃ የሚመለከተው ሰው በጽሁፍ ፈቃዱን ከገለጸ ለሌላ ለማንኛውም ሰው፤

በ/ በሌላ ማናቸውም ሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማንኛውንም መረጃ የሚቀበል ሰው፦

ሀ/ መረጃው የተገለፀበትን ዓላማ ለማሳካት ካልሆነ በስተቀር የመረጃውን ሚስጢራዊነት መጠበቅ፤

ለ/ መረጃውን የያዙትን ማንኛውንም ሰነዶች ለባለ ሥልጣኑ የመመለስ፣ ግዴታ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ "የታክስ ሠራተኛ" የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ/ የባለሥልጣኑ አማካሪ ቦርድ አባል የሆነ ወይም የነበረ፤

ለ/ ሥራ ተቋራጭን ጨምሮ በማንኛውም ደረጃ በባለሥልጣኑ የተቀጠረ ወይም በባለሥልጣኑ በአንድ ሥራ ላይ እንዲሠማራ የተደረገ ማንኛውም ሰው፤

ሐ/ የባለሥልጣኑ የቀድሞ ሠራተኛ፣ ተቀጣሪ ወይም ሥራ ተቋራጭ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ታክስ ከፋዮች

## ምዕራፍ አንድ

## ስለምዝገባ

### 9. ታክስ ከፋዮችን ስለመመዝገብ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) እንደተጠበቁ ሆነው፣ አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሰው በባለሥልጣኑ ዘንድ ለመመዝገብ ማመልከት አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ፦

ሀ/ በኢትዮጵያ የሚያገኘው ገቢ ብቻ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 51 እና አንቀጽ 53 መሠረት ግብር የሚከፈልበት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው፤

ለ/ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 64(2) መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ብቻ ያለው ግለሰብ፤

ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

3. ተቀጣሪው አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር፣ ከቀጣሪው ጋር ውል የገባ ተቀጣሪ ይመዘገብ ዘንድ ቀጣሪው የማመልከት ግዴታ አለበት፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ፣ ቀጣሪው እንዲመዘገብ ያላደረገው ተቀጣሪ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ካለበት የመመዝገብ ግዴታ ነጻ ሊያወጣው አይችልም፡፡
5. ለምዝገባው የሚቀርበው ማመልከቻ፦

ሀ/ ባለሥልጣኑ ባጸደቀው ቅጽ መሠረት መቅረብ ይኖርበታል፤

ለ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው መሠረት የጣት አሻራ መለያን ጨምሮ የግለሰቡን ማንነት ከሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

ሐ/ ታክስ ከፋዩ ለታክስ የመመዝገብ ግዴታ ካለበት ቀን አንስቶ በ21 (በሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚያመለክት በሚሆንበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) (ለ) መሠረት የሚጠየቀው የማንነት መለያ በተቀጣሪው መቅረብ ይኖርበታል፡፡
7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ያለበት ለምዝገባ የማመልከት ግዴታ ይኸው ሰው በሌላ ታክስ ሕግ ለአንድ ለተለየ ታክስ ካለበት የመመዝገብ ግዴታ ወይም ካለው አማራጭ በተጨማሪ ነው፡፡
8. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለመመዝገብ ያመለከተው ሰው በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ሲያምንበት ይመዘግበዋል፣ ለዚህ ሰውም በፀደቀው ቅጽ መሠረት የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ይሰጠዋል፡፡
9. ባለሥልጣኑ ለመመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበውን ሰው ጥያቄ ያልተቀበለው ከሆነ የምዝገባውን ጥያቄ የማይቀበለው መሆኑን ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 14 (አሥራ አራት) ቀናት ውስጥ ለምዝገባ ላመለከተው ሰው በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡
10. አንድ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለመመዝገብ ሲያመለክት ያቀረበውን ማስረጃ ይህ ሰው ተጨማሪ የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ ማቅረብ

ሳያስፈልገው ባለሥልጣኑ ማስረጃውን ይህ ሰው በሌላ የታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ እንዲመዘገብ ያለበትን ግዴታ ወይም ለመመዝገብ የተሰጠውን ፈቃድ ለማሟላት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

11.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ የአንድን ሰው ተጨማሪ ምዝገባ በተሟላ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ሌላ ተጨማሪ መረጃ ያቀርብ ዘንድ ይህንን ሰው ሊጠይቀው ይችላል፡፡

12.በዚህ አንቀጽ መሠረት መመዝገብ ሲኖርበት ያልተመዘገበን ሰው ባለሥልጣኑ በፀደቀው ቅጽ መሠረት መዝግቦ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሊሰጠው ይችላል፡፡

13.በዚህ አንቀጽ መሠረት የአንድ ሰው ምዝገባ ተፈፃሚ የሚሆነው የዚህን ሰው ምዝገባ በሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ነው፡፡

10.<u>ለውጦችን ስለማሳወቅ</u>

1. ማንኛውም የተመዘገበ ሰው ከሚከተሉት ውስጥ ማንኛውንም ጉዳይ በተመለከተ ለውጥ ሲከሰት ለውጡ በተከሰተ በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ/ ስሙ፣ ቋሚ አድራሻው ወይም የፖስታ አድራሻው፣ የተቋቋመበት መተዳደሪያ ደንብ ወይም ዋነኛ የሥራ እንቅስቃሴው ወይም እንቅስቃሴዎቹ፤

ለ/ ከባለሥልጣኑ ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት የባንክ አድራሻ፤

ሐ/ ከባለሥልጣኑ ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት የኤሌክትሮኒክ አድራሻ፤

መ/ ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

2. የተመዘገበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የለውጥ ማስታወቂያ ሲያቀርብ ይህ ሰው በሌላ የታክስ ሕግ ለአንድ ለተለየ ታክስ ካደረገው ምዝገባ ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ ለውጦችን ማስታወቅን በተመለከተ የተጣለበትን የማስታወቅ ግዴታ እንደተወጣ ይቆጠራል፡፡

11.<u>ምዝገባን ስለመሰረዝ</u>

1. የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ለሁሉም የታክስ ሕጎች የተጣለበት የመመዝገብ ግዴታ ሲቋረጥ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ለባለስልጣኑ ማመልከት አለበት፡፡

2. ምዝገባን ለማሰረዝ የሚቀርበው ማመልከቻ፡-

ሀ/ በፀደቀው ቅጽ መሠረት፤ እና

ለ/ የተመዘገበው ሰው በሁሉም የታክስ ሕጐች የተጣለበት የመመዝገብ ግዴታ ከተቋረጠበት ቀን አንስቶ ባሉት 30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

3. አንድ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ካቀረበ በሌላ የታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ የተደረገው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጭምር እንዳመለከተ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
4. አንድ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ሲያቀርብ ባለሥልጣኑ ይህ ሰው ሥራውን ያቆመ መሆኑንና በሁሉም የታክስ ሕጎች የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ለዚህ ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ይሰርዘዋል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው ምዝገባ የተሠረዘ መሆኑን የሚገልፀው ማስታወቂያ ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 30 (ሠላሳ) ቀናት ለአመልካቹ መሰጠት የሚኖርበት ሲሆን፣ ባለሥልጣኑም የምዝገባ ይሰረዝልኝ ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ የታክስ ከፋዩን የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ የመጨረሻ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት አንድ ሰው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጥያቄ ያላቀረበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ይህ ሰው ሥራውን ሙሉ በሙሉ ማቆሙን እና ለታክስ ሕጐች ዓላማ የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንዲሁም የተፈጥሮ ሰው ከሆነ መሞቱን፣ ኩባንያ ከሆነም መፍረሱን፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ሕልውናው የተቋረጠ መሆኑን ሲያምንበት ለታክስ ከፋዩ ወይም ለታክስ እንደራሴው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ይሰርዛል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (6) መሠረት የሚደረግ የአንድ ሰው ምዝገባ መሰረዝ በሌላ ታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ ዓላማ ሲባል የተደረገ ምዝገባ መሰረዝንም ይጨምራል፡፡
8. የአንድ ሰው የምዝገባ መሰረዝ ተፈጻሚ የሚሆነው ባለሥልጣኑ በሰጠው የስረዛ ማስታወቂያ ላይ ከተጻፈው ቀን ጀምሮ ነው፡፡
9. የአንድ ሰው የምዝገባ መሰረዝ በሌላ ታክስ ሕግ አንድን የተለየ ታክስ የሚመለከት ሲሆን፣ በዚያ የታክስ ሕግ ምዝገባ መሰረዝን በሚመለከት የሠፈሩትን ግዴታዎች ማሟላት ግዴታ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር

**12.የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር**

ታክስ ከፋዮችን ለመለየት እንዲቻል ባለሥልጣኑ በዚህ ምዕራፍ በተደነገገው መሠረት ለታክስ ሕጐች ዓላማ ሲባል ለተመዘገበ ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በሚል የሚታወቅ ቁጥር ይሰጣል፣ ታክስ ከፋዩም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን የታክስ ሕጎች በሚያዙት መሠረት መጠቀም አለበት፡፡

**13.የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ስለመስጠት**

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት ለታክስ ሕጎች ዓላማ ሲባል ለተመዘገቡ ሰዎች የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡
2. ለሁሉም የታክስ ሕጎች አንድ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሚሰጥ ሲሆን አንድ ታክስ ከፋይ በማንኛውም ጊዜ አንድ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ብቻ ይኖረዋል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የታክስ መለያ ቁጥር የሚሰጠው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማስታወቂያ በመላክ ይሆናል፡፡

**14.የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም**

1. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን በማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ፣ ማስታወቂያ ወይም ለታክስ ሕግ ዓላማ ሲባል በሚቀርብ ወይም ጥቅም ላይ በሚውል ሰነድ ወይም በታክስ ሕግ መሠረት በሚዘጋጅ ሰነድ ላይ መግለጽ ይኖርበታል፣ እንዲሁም ታክስ ከፋዩ ታክስ ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ባለበት ሰው ክፍያዎች በሚፈጽምለት ጊዜ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን መስጠት አለበት፡፡
2. የንግድ ሥራ ለመሥራት ፈቃድ ይሰጠው ዘንድ ማመልከቻ የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ ፈቃድ ለሚሰጠው ባለሥልጣን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን መስጠት አለበት፡፡
3. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት ፈቃዱን በሚያድስበት ጊዜ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ የሚጠበቅበት የመጀመሪያው የፈቃድ ማመልከቻ ከቀረበ ወዲህ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ የተቀየረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

4. የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሚሰጥ የመንግሥት አካል ወይም ተቋም ታክስ ከፋዩ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሳያቀርብ ፈቃድ መስጠት አይችልም፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ለተሰጠው ሰው ብቻ የሚያገለግል ስለሆነ በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡
6. የታክስ ወኪል የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ሊጠቀምበት የሚችለው፦

ሀ/ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ ባለቤት የሆነው ሰው የታክስ ወኪል የታክስ መለያ ቁጥሩን ለመጠቀም እንዲችል በጽሑፍ ሲፈቅድለት፤ እና

ለ/ የታክስ ወኪሉ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ ባለቤት የታክስ ጉዳዮች ብቻ ሲጠቀምበት ነው፡፡

### 15.<u>የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥርን ስለመሰረዝ</u>

1. ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ለመሠረዝ ይችላል፦

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት የታክስ ከፋዩ ምዝገባ ሲሰረዝ፤

ለ/ የታክስ ከፋዩ እውነተኛ ማንነት ባልሆነ ማንነት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ የተሰጠ እንደሆነ፤

ሐ/ ታክስ ከፋዩ ጥቅም ላይ ያለ ሌላ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ያለው እንደሆነ፡፡

2. ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በመሰረዝ አዲስ የታክስ መለያ ቁጥር ሊሰጠው ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>የታክስ እንደራሴዎች</u>

### 16.<u>የታክስ እንደራሴዎች ግዴታዎች</u>

1. አንድ የታክስ እንደራሴ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብንና ታክስ መክፈልንም ጨምሮ የታክስ ሕግ በታክስ ከፋዩ ላይ የሚጥለውን ማንኛውም ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት አለበት፡፡
2. አንድ ታክስ ከፋይ ሁለትና ከሁለት በላይ የታክስ እንደራሴዎች ያሉት እንደሆነ እያንዳንዱ የታክስ እንደራሴ በዚህ አንቀጽ ለተመለከቱት ግዴታዎች የአንድነትና

የነጠላ ኃላፊነት አለበት፣ ሆኖም ግን ከታክስ እንደራሴዎቹ መካከል አንዱ የታክስ ወኪል ግዴታዎችን መወጣት ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ ሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በታክስ እንደራሴ መከፈል የሚኖርበት ታክስ በታክስ እንደራሴው ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ባለው ገንዘብ ወይም ሀብት መጠን ከታክስ እንደራሴው መሰብሰብ አለበት፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በታክስ እንደራሴው መከፈል የነበረበት ታክስ ሳይከፈል ሲቀር የታክስ እንደራሴው በታክስ እንደራሴነቱ ታክሱን ለመክፈል የግል ኃላፊነት የሚኖርበት የታክስ እንደራሴው፡-

ሀ/ የተቀበለውን ወይም ሊቀበለው የሚችለውንና ታክስ የሚከፈልበትን ገንዘብ ያጠፋ፣ ለሌላ ዓላማ ያዋለ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤

ለ/ የታክስ ከፋዩ ሀብት የሆኑ እና በታክስ እንደራሴው ይዞታ ሥር የነበሩ ወይም ታክስ መከፈል ከነበረበት ጊዜ በኋላ በይዞታው ሥር የሆኑ እና ለታክሱ ክፍያ ሊውሉ የሚችሉ ንብረቶችን ወይም ገንዘብ ያስተላለፈ ወይም በከፊል ለሌላ የሰጠ እንደሆነ ነው፡፡

5. የታክስ እንደራሴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ለታክስ ክፍያ የግል ኃላፊነት የማይኖርበት፡-

ሀ/ በታክስ እንደራሴው የተከፈለው ገንዘብ የዋለው ለታክስ ከፋዩ ጥቅም ሲሆንና የተከፈለው ገንዘብ በሕግ ከታክስ ከፋዩ ታክስ የመክፈል ግዴታ ቅድሚያ ሲኖረው፤ ወይም

ለ/ ገንዘቡ በተከፈለበት ጊዜ የታክስ እንደራሴው ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ ያለበት መሆኑን ካላወቀ ወይም ሊያውቅ የማይችል ከሆነ ነው፡፡

6. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የታክስ እንደራሴው በታክስ ከፋዩ ላይ በታክስ ሕግ የተጣለውን ማንኛውንም ግዴታ ሳይወጣ ቢቀር ታክስ ከፋዩ ካለበት ማንኛውም ግዴታ ነፃ ሊያደርገው አይችልም፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለሰነዶች</u>

### 17.<u>መዝገብ የመያዝ ግዴታዎች</u>

1. ለታክስ ሕግ ዓላማ ሲባል አንድ ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መያዝ ያለባቸውን ሰነዶች በኤሌክትሮኒክ መልክ ጨምሮ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሲሆን እነዚህም ሰነዶች የሚያዙት፡-

ሀ/ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ፣

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ፣ እና

ሐ/ የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ በግልጽ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ፣ መሆን አለበት፡፡

2. በታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ታክስ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ሰነዶች ከሚከተሉት ረጅም ለሆነው ጊዜ ይዞ የማቆየት ግዴታ አለበት፡-

ሀ/ በንግድ ሕግ ለተወሰነው የሰነድ መያዣ የጊዜ ርዝማኔ፣ ወይም

ለ/ ሰነዶቹ አግባብነት በሚኖራቸው የታክስ ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ በአዋጁ መሠረት ለሚደረግ ክርክር ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተመለከተው ጊዜ በፊት ተግባራዊ በሆነ ሕግ መሠረት ለሚደረግ ክርክር ሰነዱ የሚያስፈልግ ሲሆን ታክስ ከፋዩ ሁሉም ክርክሮች እስከሚጠናቀቁ ጊዜ ድረስ ሰነዱን ይዞ የማቆየት ግዴታ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ካልቀረበ በባለሥልጣኑ በጽሁፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ሰነዱ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባለው ተርጓሚ በታክስ ከፋዩ ወጪ ወደ አማርኛ ወይም ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩን ሊያዘው ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተደነገጉት ቢኖሩም፣ ሚኒስትሩ በሚያወጣው የዋጋ ማሸጋገሪያ መመሪያ ሰነድ አያያዝን በተመለከተ የተደነገጉት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**18.ሰነዶችን ስለመመርመር**

በታክስ ሕግ መሰረት ሰነዶችን እንዲይዝ የሚገደድ ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 በተመለከተው በማንኛውም ምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ ሰነዶቹን ለባለሥልጣኑ ምርመራ ዝግጁ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

**19.ደረሰኞች**

1. የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ደረሰኞች ከማሳተሙ በፊት የእነዚህን ደረሰኞች ዓይነትና ብዛት በባለሥልጣኑ ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የህትመት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ደረሰኞችን ለማሳተም ከታክስ ከፋዩ ጥያቄ ሲቀርብለት ደረሰኞቹን ከማተሙ በፊት የእነዚህ ደረሰኞች ዓይነትና መጠን በባለሥልጣኑ የተመዘገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ለሚያከናውነው ግብይት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚያግዙ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

20.<u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪዎችን የሚመለከት ደንብ ያወጣል፡፡
2. ደንቡ የሚከተሉትን ጉዳዮች ሊደነግግ ይችላል፦

ሀ/ ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ እንዳለባቸው፤

ለ/ ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚጠቀሙበትን ሁኔታዎች፤

ሐ/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ታትሞ የሚወጣው ደረሰኝ ሊይዛቸው ስለሚገባ መረጃዎች፤

መ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ተፈላጊ ባህሪያት፤

ሠ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አቅራቢዎች የሚያቀርቧቸው መሣሪያዎች እውቅና እንዲያገኙ መከተል ስለሚገባቸው ስነ-ሥርዓት እና አቅራቢዎቹ ስላለባቸው ግዴታ፤

ረ/ ለታክስ ከፋይ የተሸጠን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ስለሚመዘገብበት ሁኔታ፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፦

ሀ/ "የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ" ማለት በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ለማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ ቺፕ የተገጠመበት በሰርኪዩት የተጋገረ ፕሮግራም የሚጠቀም መሣሪያ ነው፤

ለ/ "የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ" ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያን የሚተካ ኮምፕዩተራይዝድ የሆነ መሣሪያ ሲሆን፣ የደንበኞችን ትዕዛዝ፣ የትዕዛዙን አፈጻጸምና ሂደትና የዴቢትና ክሬዲት ካርድ ሂሳብን የመመዝገብና የመከታተል፣ በክምችት ያለን ዕቃ

የመቆጣጠርና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ያለው መሣሪያ ነው፤

ሐ/ "የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ" ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

## የታክስ ማስታወቂያዎች

### 21. የታክስ ማስታወቂያዎችን ስለማቅረብ

1. በታክስ ሕግ የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት ሰው ማስታወቂያውን በፀደቀው ቅጽ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ በተመለከተው አኳኋን ማቅረብ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ፦

ሀ/ አስቀድሞ ለባለሥልጣኑ ያቀረበውን የታክስ ማስታወቂያ የሚያሟላ የታክስ ማስታወቂያ፤ ወይም

ለ/ ባለሥልጣኑ በሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ የተመለከቱ መረጃዎችን የያዘ የታክስ ማስታወቂያ፤ ማቅረብ አለበት፡፡

3. ቀደም ሲል የቀረበው የታክስ ማስታወቂያ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
4. ባለሥልጣኑ በታክሱ ከፋይ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም በቀረበ የታክስ ማስታወቂያ አይገደድም፡፡ ስለሆነም ባለሥልጣኑ ባገኘው ማንኛውም አስተማማኝ እና ሊረጋገጥ የሚችል መረጃ ላይ በመመሥረት ታክስ ከፋዩ መክፈል ያለበትን የታክስ መጠን ሊወስን ይችላል፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ታክስ ከፋይ በሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ላይ መፈረም የሚኖርበት ሲሆን የታክስ ማስታወቂያውም፣ ማስታወቂያው እና ተያያዥ ሰነዶች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን ታክስ ከፋዩ የሚያረጋግጥበትን መግለጫ መያዝ አለበት፡፡

6. ታክስ ከፋዩ፡-

ሀ/ ግለሰብ ካልሆነ፤

ለ/ ችሎታ የሌለው ግለሰብ ከሆነ፤ ወይም

ሐ/ የታክስ ማስታወቂያውን በሌላ ምክንያት ለመፈረም የማይችል ግለሰብ ሲሆንና ለታክስ ወኪሉ ወይም ለታክስ እንደራሴው በጽሑፍ የውክልና ሥልጣን የሰጠው ከሆነ፤ የታክስ ከፋዩ የታክስ ወኪል ወይም የታክስ እንደራሴው የታክስ ማስታወቂያውን ሊፈርም እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የማረጋገጫ መግለጫ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7. የታክስ ማስታወቂያው በታክስ ከፋዩ የታክስ ወኪል ወይም በታክስ እንደራሴው የተፈረመ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የማስታወቂያውን ይዘት እንደሚያውቅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እንደተመለከተው ስለማስታወቂያው የተሟላ እና ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጫ እንደሰጠ ይቆጠራል፡፡

22.<u>**የታክስ ወኪል ስለሚሰጠው የታክስ ማስታወቂያ ማረጋገጫ**</u>

1. የታክስ ከፋይን የታክስ ማስታወቂያ የሚያዘጋጅ ወይም በታክስ ማስታወቂያ ዝግጅት ድጋፍ የሚያደርግ የታክስ ወኪል የታክስ ከፋዩን ሰነዶች መመርመሩን እና እስከሚያውቀው ድረስ የታክስ ማስታወቂያውና ተያያዥ ሰነዶች የታክስ ማስታወቂያው የሚመለከታቸውን መረጃዎች እና ግብይቶች በትክክል የሚያሳዩ መሆኑን የሚያረጋግጥ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የተዘጋጀ የምስክር ወረቀት ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የምስክር ወረቀት ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ የታክስ ወኪል የምስክር ወረቀቱን መስጠት ያልፈለገበትን ምክንያት የያዘ የጽሁፍ መግለጫ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡፡
3. የታክስ ከፋይን የታክስ ማስታወቂያ የሚያዘጋጅ ወይም በታክስ ማስታወቂያ ዝግጅት ድጋፍ የሚያደርግ የታክስ ወኪል ከታክስ ማስታወቂያው ጋር በተገናኘ ለታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የምስክር ወረቀት የሰጠ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መግለጫ የሰጠ መሆኑን በታክስ ማስታወቂያው ላይ መግለጽ ይኖርበታል፡፡
4. የታክስ ወኪል በዚህ አንቀጽ መሠረት የሰጠውን የምስክር ወረቀት ወይም መግለጫ ቅጂ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17(2) ለተወሰነው ጊዜ ይዞ ማቆየት ያለበት ሲሆን ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ሲጠይቀው ቅጂውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

23.<u>የታክስ ማስታወቂያዎች አስቀድሞ ስለማቅረብ</u>

1. ሥራውን ያቋረጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ሥራውን ያቋረጠ መሆኑን ሥራውን ካቆመበት ቀን ጀምሮ በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚመለከተው ታክስ ከፋይ ሥራውን ባቆመ በ60 (በስልሳ) ቀናት ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በሚወስነው ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውሰጥ፦

ሀ/ ታክስ ከፋዩ ሥራውን ላቆመበት የታክስ ጊዜ ወይም የታክስ ማስታወቂያ ጊዜው ላልደረሰ ከዚያ በፊት ለነበረ የታክስ ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ፤ እና

ለ/ በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ታክስ መክፈል፤ አለበት፡፡

3. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ከኢትዮጵያ ሊወጣ ከሆነና የታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ መውጣት በጊዜያዊነት አለመሆኑ የሚገመት ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ ከመውጣቱ በፊት፦

ሀ/ የወቅቱን የታክስ ማስታወቂያ እና ከኢትዮጵያ በሚወጣበት ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ የማቅረቢያ ጊዜው ላልደረሰው ከዚያ በፊት ለነበረው የታክስ ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ፤ እና

ለ/ በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው መሠረት መከፈል የሚገባውን ታክስ መክፈል ወይም ታክሱ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለባለሥልጣኑ አጥጋቢ በሆነ አኳኋን ማመቻቸት፤ አለበት፡፡

4. በማንኛውም የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የታክስ ጊዜውን የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ በሚገባው ጊዜ አያቀርብም ብሎ ማመን የሚያስችል ምክንያት ሲኖረው ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት፦

ሀ/ ታክስ ከፋዩ ወይም የታክስ እንደራሴው የታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያ ጊዜ ባይደርስም ባለሥልጣኑ በሰጠው ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ እንዲያቀርብ፤ እና

ለ/ በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው የተመለከተውን ታክስ ባለሥልጣኑ በሰጠው ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል፤ ሊያዝ ይችላል፡፡

5. ታክስ ከፋዩ ከአንድ የታክስ ዓይነት በላይ የሚመለከተው ከሆነ ይህ አንቀጽ ለእያንዳንዱ ታክስ በተናጠል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
6. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ሥራ" ማለት ንግድ ወይም ማንኛውም በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያስገኝ ሌላ ሥራ ሲሆን የመጨረሻ ታክስ ሆኖ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ለባለሥልጣኑ የሚተላለፍ ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያስገኝ ሥራን አይጨምርም፡፡

### 24. <u>በአግባቡ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ</u>

ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም ቀርቧል የተባለ የታክስ ማስታወቂያ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ፈቃድ እንደቀረበ ይቆጠራል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የታክስ ስሌቶች</u>

### 25. <u>በታክስ ከፋዩ ስለሚዘጋጅ የታክስ ስሌት</u>

1. በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን ታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ ታክስ ከፋይ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው መጠን ለማንኛውም የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ዜሮን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን ስሌት እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
2. በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ "ለ" ወይም "ሐ" መሠረት ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያገኝ ታክስ ከፋይ በዚሁ የታክስ ጊዜ ኪሣራ የገጠመው እንደሆነ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው የኪሣራ መጠን ለማንኛውም የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ያጋጠመውን የኪሣራ ስሌት እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
3. በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ታክስ ከፋይ፣ በዚሁ የታክስ ጊዜ በግብዓት ላይ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ መጠን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከሚከፈልበት

ሽያጭ ላይ ከሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ መጠን የበለጠ እንደሆነ፣ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው የታክስ መጠን ለማንኛውም የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ታክስ ከሚከፈልበት ሽያጭ ላይ ከሰበሰበው ታክስ በላይ የግብዓት ታክስ መክፈሉን የሚገልጽ የስሌት ማስታወቂያ እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

4. የታክስ ማስታወቂያ፦

ሀ/ ቅጹ በባለሥልጣኑ አስቀድሞ የተሞላ መረጃ የያዘ ቢሆንም፤

ለ/ ሊከፈል የሚገባው ታክስ መረጃ በቅጹ ውስጥ እየተሞላ ሳለ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተሰላ ቢሆንም፤በፀደቀው ቅጽ መሠረት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ተሞልቶ በታክስ ከፋይ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ የራሱን የታክስ ስሌት በሚያዘጋጅ ታክስ ከፋይ እንደቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

### 26.<u>በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት</u>

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መሠረት በማንኛውም የታክስ ጊዜ ማቅረብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የሚያገኘውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ለታክስ ጊዜው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ በግምት (“የግምት ስሌት” ተብሎ የሚጠራ) ማስላት የሚችል ሲሆን የግምት ስሌቱ የሚከተሉትን ይመለከታል፦

ሀ/ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” ኪሳራን በሚመለከት የታክስ ጊዜውን የኪሳራ መጠን፤

ለ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት በግብዓት ላይ በብልጫ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስን በሚመለከት ለታክስ ጊዜው በግብዓት ላይ በብልጫ የተከፈለውን የታክስ መጠን፤

ሐ/ በሌላ ማንኛውም ሁኔታ ዜሮ መጠንን ጨምሮ በታክስ ጊዜው ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ታክሱ በግምት ለተሰላው ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ መስጠት አለበት፦

ሀ/ እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ መጠን፣ ወደፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፤

ለ/ በተሰላው ታክስ ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፤

ሐ/ በተሰላው የታክስ መጠን ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፤

መ/ የታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፤

ሠ/ ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ ታክሱ፣ ቅጣቱ እና ወለዱ የሚከፈልበትን ቀን፤

ረ/ ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በታክስ ግምት ስሌቱ ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳኋን፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚሰጠው የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ ታክሱን በሚጥለው የታክስ ሕግ መሠረት በተዘጋጀው የታክስ ግምት ስሌት ሊከፈል የሚገባው ታክስ የሚከፈልበትን ጊዜ (“የመጀመሪያው የታክስ መክፈያ ጊዜ” ተብሎ የሚጠቀስ) ሊለውጥ የማይችል ሲሆን፣ የታክስ ክፍያው በመዘግየቱ ምክንያት የሚጣል ቅጣትና ወለድ መታሰብ የሚጀምሩት ከመጀመሪያው የመክፈያ ጊዜ አንስቶ ይሆናል፡፡
4. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው በታክስ ስሌት ለሚሰበሰብ ታክስ ብቻ ነው፡፡
5. ይህ አንቀጽ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የታክስ ግምት ስሌት የደረሰው ማንኛውም ታክስ ከፋይ የግምት ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን አያስቀርም፡፡
6. በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከደረሰው በኋላ ለዚያ የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ጊዜው እንደቀረበ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ሆኖ አይቆጠርም፡፡
7. ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ በግምት ላይ የተመሠረተ የታክስ ስሌት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
8. ባለሥልጣኑ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

27.<u>የስጋት የታክስ ስሌት</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 ወይም አንቀጽ 42 በተመለከቱት ሁኔታዎች በአንድ የታክስ ጊዜ ማንኛውም ታክስ ከፋይ መክፈል ለሚገባው ታክስ በሚያገኘው ማስረጃ ላይ በመመሥረት የስጋት ታክስ ስሌት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው፡-

ሀ/ ታክስ ከፋዩ ለታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ፣ እና

ለ/ ታክሱ በታክስ ስሌት የሚሰበሰብ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

3. የስጋት ታክስ ስሌት፡-

ሀ/ ታክስ ከፋዩ ለታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ የሚያቀርብበት ቀን ከመድረሱ በፊት ሊዘጋጅ ይችላል፣ እንዲሁም

ለ/ በሚዘጋጅበት ጊዜ ፀንቶ ባለ ሕግ መሠረት መዘጋጀት አለበት፡፡

4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የስጋት ታክስ ስሌት ለተዘጋጀለት ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በጽሑፍ መስጠት አለበት፡-

ሀ/ የተሰላውን የታክስ መጠን፣

ለ/ በተሰላው የታክስ መጠን ላይ የሚከፈል ቅጣት ካለ፣

ሐ/ የታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፣

መ/ ታክሱና ቅጣቱ የሚከፈልበትን ጊዜ፣ ይህ ጊዜ የታክሱ የመክፈያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ሊሆን ይችላል፣

ሠ/ ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በስጋት ታክስ ስሌቱ ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳኋን፡፡

5. ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ በሚሰጠው የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ታክሱ እና ቅጣቱ ወዲያውኑ እንዲከፈል ሊያዝ ይችላል፡፡

6. ይህ አንቀጽ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የስጋት ታክስ ስሌት የደረሰው ማንኛውም ታክስ ከፋይ የስጋት ታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴውን አያስቀርም፡፡

7. ታክስ ከፋዩ በአንድ የታክስ ጊዜ መክፈል ያለበትን ታክስ በሙሉ ማስላት እንዲቻል የስጋት ታክስ ስሌት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 መሠረት ሊሻሻል ይችላል፡፡

8. የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከደረሰው በኋላ ለዚያ የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ጊዜው እንደቀረበ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ አይቆጠርም፡፡

28.<u>የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች</u>

1. ይህ አንቀጽ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ/ የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” ን በተመለከተ የታክስ ከፋዩ ኪሳራ ለታክስ ጊዜው በትክክል የተሰላ መሆኑን፤

ለ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት በብልጫ የተከፈለ የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ መጠንን በተመለከተ ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው በብልጫ የከፈለው የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል የተሰላ መሆኑን፤

ሐ/ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ታክስ ከፋዩ ዜሮ መጠንን ጨምሮ ለታክስ ጊዜው መክፈል የሚገባው የታክስ መጠን በትክክል የተሰላ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ በሚያገኘው ማስረጃ መሠረት ማንኛውንም የታክስ ስሌት (“የመጀመሪያው የታክስ ስሌት” ተብሎ የሚጠቀስ) በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ሊያሻሽል ይችላል፡፡

2. አግባብነት ባለው የታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማንኛውንም የታክስ ስሌት፦

ሀ/ በማንኛውም ጊዜ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም የማጭበርበር ድርጊት ሲፈጸም ወይም በከፍተኛ ሁኔታ ወይም በማወቅ የተፈፀመ የቸልተኝነት ድርጊት ሲኖር፤ ወይም

ለ/ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ፦

1) ታክስ ከፋዩ በራሱ የሚያሰላው የታክስ ስሌት ሲሆን ታክስ ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 (አምስት) ዓመት ውስጥ፤

2) ለሌላ ማንኛውም የታክስ ስሌት ባለሥልጣን ለታክስ ከፋዩ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5(አምስት) ዓመት ውስጥ፤ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለታክስ ከፋዩ የሰጠውን የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ዘግይቶ በተፈጸመው ጊዜ እንደገና ሊያሻሽል ይችላል፦

ሀ/ ለመጀመሪያው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፤ ወይም

ለ/ ባለሥልጣኑ የተሻሸለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠው በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ለ) ተፈጻሚ በሚሆንበት በማናቸውም ሁኔታ ባለሥልጣኑ የሚያደርገው ተጨማሪ ማሻሻያ መጀመሪያ በተሻሻለው የታክስ ስሌት

ላይ በተደረጉት ለውጦች፣ ቅናሾች ወይም ጭማሪዎች ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡

5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሻሻለውን የታክስ ስሌት በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡-

ሀ/ ማሻሻያ የተደረገበትን የመጀመሪያ የታክስ ስሌት እና ማሻሻያ ማድረግ ያስፈለገበትን ምክንያቶች የያዘ መግለጫ፤

ለ/ እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ መጠን፣ ወደ ፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፤

ሐ/ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፤

መ/ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፤

ሠ/ የተሻሻለው የታክስ ስሌት የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፤

ረ/ ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከ30 (ከሰላሳ) ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት መከፈል ያለበትን ተጨማሪ ታክስ፣ ቅጣት እና ወለድ የሚከፈልበትን ቀን፤

ሰ/ ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳኋን፡፡

6. በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት መከፈል ያለበት ተጨማሪ ታክስ ካለ በተጨማሪው ታክስ ላይ ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ቅጣትና ወለድ የሚሰላው በመጀመሪያው የታክስ ስሌት መሠረት ታክሱ መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

## 29.<u>ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. የራሱን የታክስ ስሌት ያዘጋጀ ታክስ ከፋይ ያቀረበውን በራስ የተዘጋጀ የታክስ ማስታወቂያ ባለሥልጣኑ እንዲያሻሽልለት ለባለሥልጣኑ ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ፡-

ሀ/ ታክስ ከፋዩ ራሱ አዘጋጅቶ ባቀረበው የታክስ ማስታወቂያ ላይ ሊደረግ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎችን እና ማሻሻያዎቹን ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች መግለጽ፤ እና

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 (2)(ለ) (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መቅረብ፣ ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ማመልከቻው በቀረበለት በ120 (አንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ በታክስ ከፋዩ ተዘጋጅቶ የቀረበው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል መወሰን ወይም ማመልከቻውን ውድቅ ማድርግ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ራሱ ያቀረበው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል የወሰነ እንደሆነ፡-

ሀ/ የታክስ ስሌት ማሻሻያው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28(1) መሠረት መከናወን፣ እና

ለ/ የተሻሻለው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 (5) መሠረት ለታክስ ከፋዩ እንዲደርሰው መደረግ፣ አለበት፡፡

5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበውን ማመልከቻ ያልተቀበለው እንደሆነ ውሳኔውን ለታክስ ከፋዩ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብና ማስከፈል

### ምዕራፍ አንድ

### ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

#### 30.ታክስ ለመንግሥት የሚከፈል ዕዳ ስለመሆኑ

1. በታክስ ሕግ መሠረት በታክስ ከፋዩ ሊከፈል የሚገባውና የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ ለመንግሥት የሚከፈል ዕዳ ስለሆነ ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 (2) መሠረት በኤሌክትሮኒክስ አከፋፈል ዘዴ ታክስ እንዲከፍል በባለሥልጣኑ የተጠየቀ ታክስ ከፋይ ባለሥልጣኑ ሌላ የአከፋፈል ዘዴ እንዲጠቀም በጽሑፍ ካልፈቀደለት በስተቀር ክፍያውን የሚፈጽመው በኤሌክትሮኒክስ አከፋፈል ዘዴ ይሆናል፡፡
3. ታክስ ከፋዩ ታክሱን መክፈል ባለበት ጊዜ ካልከፈለ ባለሥልጣኑ ያልተከፈለውን ታክስ ለማስከፈል በሚወስደው እርምጃ ምክንያት ለሚያወጣው ማንኛውም ወጪ ኃላፊ ይሆናል፡፡

#### 31.በሁለተኛ ደረጃ የሚመጡ ኃላፊነቶች እና ታክስን ለማስከፈል የሚደረጉ ወጪዎች

1. ባለሥልጣኑ የሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት ላለበት ወይም ታክስን ለማስከፈል የተደረገን ወጪ መክፈል ላለበት ማንኛውም ሰው መክፈል ያለበትን የገንዘብ መጠን እና ክፍያው የሚፈጸምበትን ቀን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይሰጣል፡፡
2. የዚህን አዋጅ ክፍል ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝ እና አሥር እንዲሁም አንቀጽ 105ን በሚመለከት፡-

ሀ/ "ታክስ" የሚለው ቃል በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ ኃላፊነትንና ታክስን ለማስከፈል የሚደረግ ወጪን ይጨምራል፤

ለ/ "ያልተከፈለ ታክስ" የሚለው ሀረግ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰውና በመክፈያ ጊዜው ያልተከፈለን ታክስ ይጨምራል፤ እንዲሁም

ሐ/ "ታክስ ከፋይ" የሚለው ሀረግ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበትን ሰው ይጨምራል፡፡

3. የሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት ባለበት ሰው የተከፈለ ታክስ ይኸው ኃላፊነት ከሚመለከተው የታክስ ከፋዩ የመጀመሪያ የታክስ ኃላፊነት ጋር ይካካሳል፡፡

32.<u>የታክስ መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም</u>

1. ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ የመክፈያ ጊዜው እንዲራዘምለት ለባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በቂ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት፡-

ሀ/ ለታክስ ከፋዩ የታክስ መክፈያ ጊዜውን ሊያራዝምለት፤ ወይም

ለ/ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ሊያደርገው፤ ይችላል፡፡

3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለቀረበው ማመልከቻ የሰጠውን ውሳኔ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጠዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) መሠረት ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ የአንድን ጊዜ ክፍያ ካልከፈለ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ባቆመበት ጊዜ ያለውን ቀሪ ክፍያ በሙሉ እንዲከፍል ባለሥልጣኑ ወዲያውኑ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

5. የታክስ መክፈያ ጊዜው እንዲራዘም ወይም ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በዘገየው ክፍያ ላይ ከመጀመሪያ የታክስ መክፈያ ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም፡፡

33.**<u>በታክስ እና ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ በሚከፈል ገንዘብ ላይ ስለሚኖር የቅድሚያ መብት</u>**

1. ይህ አንቀጽ ለሚከተሉት ክፍያዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፦

ሀ/ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ፣ በተርን ኦቨር ታክስ፣ ወይም በኤክሳይዝ ታክስ፤ እና

ለ/ ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ሊከፈል በሚገባው ገንዘብ፡፡

2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ በሚሆንበት ገንዘብ ባለዕዳ የሆነ፣ የያዘ፣ የተረከበ ወይም ቀንሶ የሚያስቀር ሰው ይህንን ገንዘብ የመንግሥት ባለአደራ በመሆን የሚይዝ ስለሆነ ይህ ሰው ሲከስር ወይም ንብረቱ ሲጣራ የመንግሥት ባለአደራ በመሆን የያዘው ገንዘብ፦

ሀ/ በንብረት ማጣራቱ ሂደት ወይም በኪሳራው የጠቅላላ ንብረቱ አካል ተደርጎ አይወሰድም፤ እንዲሁም

ለ/ ምንም ዓይነት የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት፡፡

3. በሌላ ማንኛውም ሕግ በተለየ አኳኋን የተደነገገ ቢኖርም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ፦

ሀ/ ከማንኛውም ሰው ለሚፈለግ ማንኛውም ዕዳ ወይም ኃላፊነት ማስፈጸሚያ ሊከበር አይችልም፤

ለ/ ታክሱ ተይዞ ቀሪ ከሚደረግበት ክፍያ ላይ ከሚፈለጉ እዳዎች ሁሉ የመጀመሪያው ይሆናል፤ እንዲሁም

ሐ/ በማናቸውም ሕግ ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ከክፍያው ላይ ከሚቀነስ ማንኛውም የገንዘብ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

34.**<u>የአከፋፈል ቅደም ተከተል</u>**

1. አንድ ታክስ ከፋይ ቅጣትና ክፍያ ለዘገየበት ወለድ የመክፈል ኃላፊነት ሲኖርበትና ታክስ ከፋዩ የፈፀመው ክፍያ መክፈል ከሚገባው ጠቅላላ የታክስ፣ የቅጣትና የወለድ

መጠን ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ የተከፈለው ገንዘብ የሚሸፍነው ዕዳ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ/ በመጀመሪያ ዋናውን የታክስ ዕዳ ለመክፈል፤

ለ/ ቀጥሎ ክፍያ ለዘገየበት የሚከፈል ወለድ፤

ሐ/ ቀሪው ገንዘብ ለቅጣት መክፈያ ይውላል፡፡

2. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ክፍያ በሚፈጽምበት ጊዜ ከአንድ በላይ የታክስ ዕዳ የሚፈለግበት ከሆነ ክፍያው የሚሸፍነው ዕዳ ቅደም ተከተል ዕዳው በተፈጠረበት ጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል፡፡

35.<u>ለታክስ አከፋፈል የሚቀርብ ዋስትና</u>

1. ባለሥልጣኑ የመንግሥትን ገቢ ለመጠበቅ አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አስፈላጊ ነው በሚለው መጠንና አኳኋን ታክስ ከፋዩ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊያስገድደው ይችላል፡፡ ታክስ ከፋዩ ዋስትና እንዲያቀርብ የሚጠየቀውም፦

ሀ/ የመክፈያ ጊዜው ለደረሰ ወይም የመክፈያ ጊዜው ለሚደርስ ታክስ መክፈያ፤ ወይም

ለ/ በታክስ ሕግ መሠረት ተመላሽ ለሚጠይቅ ታክስ ከፋይ ቅድመ-ሁኔታ፤ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ዋስትና ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸው ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ዋስትና ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. ታክስ ከፋዩ ዋስትና የማቅረብ ግዴታ የሚኖርበት ባለሥልጣኑ፦

ሀ/ የሚፈለገው የዋስትና መጠን፤

ለ/ ዋስትናው የሚቀርብበትን አኳኋን፤ እና

ሐ/ ዋስትናው የሚቀርብበትን ቀን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ የሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

4. ለዚህ ክፍል ዓላማ ሲባል ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ያላቀረበው የዋስትና መጠን የታክስ ከፋዩ ያልተከፈለ ታክስ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

36.<u>ስለጥበቃ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ በሚከተሉት ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፦

ሀ/ በፌደራል የገቢ ግብር ሕግ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለባለሥልጣኑ የከፈለ ሰው፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16(1) መሠረት ለባለሥልጣኑ ታክስ የከፈለ የታክስ እንደራሴ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 መሠረት ለባለሥልጣኑ ታክስ የከፈለ ተረካቢ፤ ወይም

መ/ ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ለባለሥልጣኑ ገንዘብ የከፈለ ሰው፡፡

2. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆንበት ሰው ታክስ ከፋዩን በመወከል በታክስ ሕግ መሰረት ለባለሥልጣኑ የከፈለውን ገንዘብ እንዲከፍል ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ

### 37.ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በታክስ መክፈያ ጊዜው ወይም ከዚያ በፊት ታክሱን ያልከፈለ ታክስ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መጣኔ መሠረት ታክሱ መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስካላቀበት ቀን ድረስ ባልተከፈለው መጠን ላይ ለዘገየው ክፍያ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. የዘገየ ክፍያ የወለድ መጣኔ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ጊዜ ከመጀመሩ በፊት ባለው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ላይ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ተጨምሮበት ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የዘገየ ክፍያ ወለድ የተከፈለበት ታክስ መከፈል የማይኖርበት ታክስ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ለታክስ ከፋዩ ይመለስለታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 105 መሠረት ታክስን በመክፈያ ጊዜው ባለመክፈል ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በነጠላ ወለድ የሚሰላ ሲሆን የሚታሰበውም በየቀኑ ይሆናል፡፡

6. ባለሥልጣኑ በዘገየ ክፍያ ላይ ወለድ የመክፈል ግዴታ ላለበት ታክስ ከፋይ መክፈል ያለበትን የወለድ መጠንና የመክፈያ ጊዜውን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይሰጠዋል፡፡
7. ታክስ ከፋዩ መክፈል ያለበትን በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ የሚገልፀው ማስታወቂያ ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ጨምሮ በማንኛውም ማስታወቂያ ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡
8. በሚከተሉት ሁኔታዎች ማስታወቂያው በተሰጠበት እና ክፍያው በተፈፀመበት መካከል ላለው ጊዜ የዘገየ ክፍያ ወለድ አይታሰብም፡-

ሀ/ ባለሥልጣኑ በታክስ ሕግ መሠረት ከታክስ ከፋዩ የሚፈለገውን የታክስ ዕዳ የታክስ ስሌት ማስታወቂያን ጨምሮ በማንኛውም የጽሑፍ ማስታወቂያ ያሳወቀው እንደሆነ፤ እና

ለ/ ታክስ ከፋዩ ማስታወቂያው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ መክፈል የሚጠበቅበትን የዘገየ ክፍያ ወለድ ጨምሮ በማስታወቂያው የተመለከተውን የታክስ ዕዳ በሙሉ በማስታወቂያው በተገለጸው የመክፈያ ቀን የከፈለ ከሆነ፡፡

9. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት በሚከፈል ታክስ ላይ የሚታሰብ የዘገየ ክፍያ ወለድ መክፈል ያለበት ይኸው ኃላፊነት ባለበት ሰው ብቻ በመሆኑ ከሌላ ማንኛውም ሰው ሊጠየቅ አይችልም፡፡

10. በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን ከታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ ሊበልጥ አይችልም፡፡

11. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ታክስ" በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድን አይጨምርም፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ያልተከፈለን ታክስ ስለማስከፈል

### 38. የታክስ ስሌቶችን ስለማስፈጸም

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ታክስ ከፋዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ቅሬታ ካላቀረበ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የሚሰጠው የታክስ ስሌት የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ የመጨረሻ እና ተፈጻሚነት ያለው ይሆናል፡፡

2. ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ ላይ ቅሬታ ካቀረበ፣ የታክስ ስሌቱ ከሚከተሉት የዘገየው ሁኔታ በተፈጸመበት ጊዜ የመጨረሻ ይሆናል፦

ሀ/ ታክስ ከፋዩ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካላቀረበ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 88 የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሲጠናቀቅ፤

ለ/ ታክስ ከፋዩ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 የተመለከተው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ሲጠናቀቅ፤

ሐ/ ታክስ ከፋዩ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 58 የተመለከተው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ሲጠናቀቅ፤ ወይም

መ/ ታክስ ከፋዩ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ በክርክር ላይ ያለን ታክስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 (2) እና አንቀጽ 57 (3) መሠረት ከመክፈል አይከለክልም፡፡

4. የመጨረሻ በሆነ የታክስ ስሌት የሚፈለግበትን ታክስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ያልከፈለ ታክስ ከፋይ ግዴታውን ያልተወጣ የታክስ ባለዕዳ ይሆናል፡፡

### 39.<u>በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና በሚመለከተው አካል የተመዘገበ ማንኛውም ቀዳሚ ዋስትና የተሰጠበት መብት እንደተጠበቁ ሆነው፣ በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚገባው የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቀዳሚ ዋስትና የተሰጠበት መብት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው የገንዘብ ጥያቄዎችና የተቀጣሪዎችን የደመወዝ የቅድሚያ መብት ይጨምራል፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33(1)(ሀ) ከተመለከቱት ታክሶች ጋር በተገናኘ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

3. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ታክስ የመክፈል ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ያልተከፈለውን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚወሰደው እርምጃ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የባለሥልጣኑን የዋስትና መብት እንዲመዘግብ ንብረቱን ለመዘገበው አካል እንደሚያመለክት የሚገልጽ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጣል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለፀው ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ ማስታወቂያው በደረሰው በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ በሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተው የታክስ ከፋዩ ሀብት ላልተከፈለው ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል ለሚደረግ ወጪ በዋስትና እንዲያዝ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የጽሁፍ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ባለሥልጣኑ ታክስ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ መዝጋቢው ባለሥልጣን ሀብቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን የጽሑፍ ትዕዛዝ ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይጠይቅ እንደማንኛውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የንብረት መያዣ ወይም የዋስትና ሰነድ ይመዘግባል፣ ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመያዣው ወይም የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ታክስ ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በሕግ እንደተሰጠ መያዣ ወይም ዋስትና ሆኖ ይቆጠራል፡፡
6. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት በዋስትና የተረጋገጠውን ታክስ በሙሉ ሲቀበል ባለሥልጣኑ መዝጋቢው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ሥር በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ያካሄደውን ምዝገባ እንዲሰርዘው ማስታወቂያ የሚሰጠው ሲሆን መዝጋቢው ባለሥልጣንም ያለምንም ክፍያ የዋስትናውን ምዝገባ ይሰርዛል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው ሀብቶች የቀደምትነት መብት የሚኖራቸው ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ የሌለበት መሆኑ በባለሥልጣኑ የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

40.<u>የተረካቢዎች ግዴታዎች</u>

1. ማንኛውም ተረካቢ የአንድን ታክስ ከፋይ ሀብት በኢትዮጵያ ውስጥ ተረካቢ ሆኖ ከተሾመ ወይም ሀብቱ በይዞታው ሥር ከገባ ከሁለቱ ከሚቀድመው ጊዜ ጀምሮ ባሉት 14 (አሥራ አራት) ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ባለሥልጣኑ ሀብቱ በተረካቢው ቁጥጥር ሥር ባለው ታክስ ከፋይ ያልተከፈለውን የታክስ ዕዳ እና ወደፊት የሚከፈለውን የታክስ መጠን በመወሰን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው የጽሑፍ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለተረካቢው ማሳወቅ አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተረካቢው፡-

ሀ/ ከባለሥልጣኑ አስቀድሞ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር በእጁ የሚገኘውን የታክስ ሀብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ማስታወቂያ ሳይደርሰው ወይም ማስታወቂያ ሳይሰጠው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የ30 (የሠላሳ) ቀናት ጊዜ ከማለፉ በፊት መሸጥ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ማስተላለፍ አይችልም፤

ለ/ ከሀብቱ ሽያጭ ገንዘብ ላይ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የገለጸውን የታክስ መጠን ወይም ባለሥልጣኑ የተስማማበትን የታክስ መጠን ቀንሶ ማስቀመጥ አለበት፤እንዲሁም

ሐ/ የሀብቱ ባለቤት በሆነው ታክስ ከፋይ መከፈል ላለበት ታክስ ከሀብቱ ሽያጭ ገቢ ተቀንሶ መቀመጥ ባለበት የገንዘብ መጠን ልክ በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ተረካቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንዲከፍል ከተጠየቀው ታክስ በማስቀደም የሚከተሉትን ክፍያዎች ከመፈፀም አይከለክለውም፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው ማስታወቂያ ከተመለከተው ገንዘብ በሕግ የቅድሚያ መብት ያለውን ዕዳ፤

ለ/ የተረካቢውን አበል ጨምሮ ተረካቢው በተረካቢነት ችሎታው የሚያወጣቸውን ወጪዎች፡፡

5. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አንድን ታክስ ከፋይ በተመለከተ ተረካቢ በሚሆኑበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ግዴታዎችና ኃላፊነቶች በሁለቱም ተረካቢዎች ላይ በአንድነትና በነጠላ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሲሆን፣ ግዴታዎቹ ከሁለቱ በአንዱ ተረካቢ ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡
6. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ “ተረካቢ” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝን የታክስ ከፋይን ወይም የሟች ታክስ ከፋይን ሀብት በተመለከተ ከሚከተሉት አንዱ ሰው ነው፡-

ሀ/ የኩባንያ አጣሪ፤

ለ/ በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ የተሾመ ተረካቢ፤

ሐ/ የከሰረ ሰው ባለአደራ፤

መ/ በመያዣ የተሰጠን ንብረት በይዞታው ሥር ያደረገ ሰው፤

ሠ/ የሟችን ሀብት የሚያጣራ ውርስ አጣሪ፡፡

41.<u>ሀብትን ስለመያዝ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ ታክሱን በመክፈያ ጊዜው ላልከፈለ ታክስ ከፋይ የሚፈለግበትን ታክስ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ ካልከፈለ የታክስ ከፋዩ ሀብት እንዲያዝ ትዕዛዝ ("የመያዣ ትዕዛዝ" ተብሎ የሚጠቀስ) የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ለታክስ ከፋዩ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ የሚከፍል ለመሆኑ ስጋት መኖሩን ካረጋገጠ የመያዣ ትዕዛዙን ወዲያውኑ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ታክሱን ካልከፈለ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው መኖሩ ሲረጋገጥ ባለሥልጣኑ የመያዣ ትዕዛዙን ለታክስ ከፋዩ ሊሰጥ ወይም የታክስ ከፋዩን ሀብት በይዞታው ሥር ባደረገ በማንኛውም ሰው ላይ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
4. የመያዣ ትዕዛዙ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር በማንኛውም የታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፦

ሀ/ በሀብቱ ላይ የቀደምትነት መብት ባላቸው የገንዘብ ጠያቂዎች በተያዘ ንብረት፤

ለ/ በማናቸውም የፍርድ ሂደት ዕገዳ በተደረገበት ወይም የአፈፃፀም ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት፤

ሐ/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊታገድ በማይችል ንብረት፡፡

5. በታክስ ከፋዩ ንብረት ላይ የመያዣ ትዕዛዝ ከተሰጠ ወይም የሚሰጥ ከሆነ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ የሚያዘውን ሀብት በሚመለከት በማስረጃነት ሊያገለግል የሚችል ማንኛውንም ሰነድ ወይም መግለጫ የያዘ ማንኛውም ሰው ይህን ሰነድ ወይም መግለጫ ለባለሥልጣኑ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡
6. በመያዣ ትዕዛዙ መሠረት ንብረት በሚያዝበት ጊዜ የፖሊስ መኮንን በቦታው እንዲገኝ ባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የተያዘውም ንብረት ደህንነቱ በሚረጋገጥበት ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግ አለበት፡፡

7. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የታክስ ከፋዩን ንብረት በሚይዝበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች የያዘ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጠዋል፡-

ሀ/ የተያዘውን ንብረት እና ያልተከፈለውን የታክስ መጠን፤

ለ/ ታክስ ከፋዩ በማስታወቂያው በተገለጸው ሀብቱ ተይዞ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የሚፈለግበትን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ሀብቱን እንደሚሸጠው፡፡

8. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) (ለ) ድንጋጌ አፈጻፀም ሲባል "ሀብት ተይዞ የሚቆይበት ጊዜ" ማለት፡-

ሀ/ ለሚበላሹ ዕቃዎች የዕቃዎቹን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ባለሥልጣኑ በቂ ነው ብሎ የሚወስነው ጊዜ፤

ለ/ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ዕቃዎቹ ከተያዙ በኋላ ያለው የአስር ቀናት ጊዜ ነው፡፡

9. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት በሚሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተውን ያልተከፈለ ታክስ ንብረቱ ተይዞ እስከሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻው ቀን ድረስ ያልከፈለ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ ሀብቱን በግልጽ ጨረታ በመሸጥ ከሽያጩ የሚገኘው ገንዘብ በቅደም ተከተል ለሚከተሉት ክፍያዎች እንዲውል ያደርጋል፡-

ሀ/ በመጀመሪያ ደረጃ በባለሥልጣኑ በሚወሰነው መጠን ሀብቱን ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለመሸጥ የወጣውን ወጭ ለመሸፈን፤

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) በተሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተውን ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ለመክፈል፤

ሐ/ የታክስ ከፋዩን ሌላ የታክስ ዕዳ ለመክፈል፤

መ/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ ቀሪ ገንዘብ ካለ ንብረቱ ከተሸጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 45 (አርባ አምስት) ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ይከፈለዋል፡፡

10. ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) (መ) የተመለከተው ገንዘብ ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት እንዲውል ማድረግ ይቻላል፡፡

11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) በተመለከተው መሠረት ከሀብት ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት የታክስ ዕዳ እና ሀብቱን ለመያዝ፣ ለመጠበቅ እና

ለመሸጥ ከወጣው ወጭ ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት መሠረት ቀሪውን ዕዳ ለማስከፈል ይችላል፡፡

12. በባለሥልጣኑ የመያዣ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ሀብት የያዘ ማንኛውም ሰው ይህንን ሀብት ያላስረከበ ወይም ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) (ሀ) መሠረት የሚወሰነውን ወጪ ጨምሮ ካላስረከበው ሀብት ዋጋ ሳያልፍ ከታክስ ከፋዩ ለሚፈለገው ታክስ መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
13. በዚህ አንቀጽ መሠረት የመያዣ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችለው ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ለዚሁ ተግባር በዋና ዳይሬክተሩ ውክልና የተሰጠው የታክስ ሠራተኛ ይሆናል፡፡
14. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተያዘ ሀብት በባለሥልጣኑ የሚያዝና በባለሥልጣኑ ኃላፊነት ስር የሚቆይ ሲሆን ለምንም ዓይነት ዓላማ ተብሎ ለሌላ ለማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተላልፎ ሊሰጥ አይችልም፡፡
15. በዚህ አንቀጽ መሠረት የግብር ከፋዩን ሀብት ለመያዝ የሚቻለው ከሚፈለግበት ግብር ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መጠን ነው፡፡

**42.** **<u>በፋይናንስ ተቋማት የተቀመጠ ገንዘብ እና ንብረት ይዞ ስለማቆየት</u>**

1. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው ባለሥልጣኑ በበቂ ምክንያት ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው ታክስ የሚሰበሰብ ስለመሆኑ ስጋት ሲኖረውና ታክሱ በአስቸኳይ መሰብሰብ ያለበት ሲሆን ይሆናል፡፡
2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ አንድ የፋይናንስ ተቋም የሚከተሉትን እንዲፈጽም አስተዳደራዊ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፦

ሀ/ የታክስ ከፋዩ ሂሳቦች እንዳይንቀሳቀሱ እንዲያደርግ፤

ለ/ በፋይናንስ ተቋሙ ውስጥ ባለ በጥንቃቄ የሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ የተቀመጠ ማንኛውም የታክስ ከፋዩ ጥሬ ገንዘብ፣ ውድ ዕቃ፣ የከበረ ጌጣጌጥ፣ ወይም ሌላ ንብረት እንዳይንቀሳቀስ፤

ሐ/ በጥንቃቄ በሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ ስለሚገኙ ሀብቶች ተገቢውን መረጃ ወይም በሣጥኑ ውስጥ ያሉትን ሀብቶች ዝርዝር ለባለ ሥልጣኑ እንዲሰጥ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለፋይናንስ ተቋም የሚሰጠው ትእዛዝ ትዕዛዙ ተፈጻሚ የሚሆንበትን የታክስ ከፋዩን ስም፣ አድራሻ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር መያዝ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ባለሥልጣኑ በታክስ ዓመቱ እና በማናቸውም በቀደመው የታክስ ዓመት ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አስመልክቶ ወዲያውኑ የስጋት የታክስ ስሌት ሊያከናውን ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ ለፋይናንስ ተቋሙ የዕግድ ትዕዛዝ በደረሰው በ10 (በአሥር) ቀናት ጊዜ ውስጥ ትዕዛዙ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
6. የዕግድ ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ10 (በአሥር) ቀናት ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤት ፈቃድ ካልተገኘ ባለሥልጣኑ የሰጠው ትዕዛዝ ተፈጻሚነት ያቆማል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ትዕዛዝ የደረሰው የፋይናንስ ተቋም ትዕዛዙ ከደረሰው ቀን ጀምሮ የትዕዛዙ ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት የትዕዛዙ ተፈጻሚነት እስከሚያበቃ ድረስ ትዕዛዙን ማክበር ይኖርበታል፡፡
8. አንድ የገንዘብ ተቋም ያለምንም በቂ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሣይፈፅም የቀረ እንደሆነ በትዕዛዙ ለተመለከተው የገንዘብ መጠን በግሉ ኃላፊ ይሆናል፡፡

**43.<u>ያልተከፈለን ታክስ ከሦስተኛ ወገኖች ስለማስከፈል</u>**

1. አንድ ታክስ ከፋይ የሚፈለግበትን ታክስ በመክፈያ ጊዜው ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ ለሚከፍል ሦስተኛ ወገን በጽሑፍ በሚሰጥ ትዕዛዝ ("የክፍያ ትዕዛዝ ተብሎ" የሚጠቀስ) በትዕዛዙ የተመለከተውን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ እንዲከፍል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን በዚህ ዓይነት የሚከፈለው ገንዘብ ካልተከፈለው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም፡፡
2. የክፍያ ትዕዛዙ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ የሚከፍል ሦስተኛ ወገን ከደመወዝ ወይም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከሚከፈል ሌላ ተመሳሳይ ክፍያ ላይ ቀንሶ ገቢ እንዲያደርግ በሚሆንበት ጊዜ ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ የሚቀነሰው የገንዘብ መጠን ከሚከፈለው ደመወዝ ወይም ሌላ ክፍያ (የገቢ ግብር ከተቀነሰ በኋላ) አንድ-ሶስተኛ መብለጥ የለበትም፡፡

3. በጋራ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚገኘን ገንዘብ በተመለከተ የክፍያ ትዕዛዝ ለከፋዩ የሚሰጠው፦

ሀ/ ሁሉም የጋራ ሂሳቡ ባለቤቶች ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ሲኖርባቸው፤ ወይም

ለ/ የሽርክና ማህበር ሂሳብን ሳይጨምር፣ ታክስ ከፋዩ የሌሎቹ የሂሳብ ባለቤቶች ፊርማ ወይም ፈቃድ ሳያስፈልገው ከሂሳቡ ላይ ገንዘብ ማውጣት የሚችል ሲሆን ብቻ ነው፡፡

4. በክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ክፍያ የሚፈፅም ማናቸውም ሰው በትዕዛዙ በተመለከተው ቀን ክፍያውን መፈፀም ያለበት ሲሆን፣ ይህም ቀን ገንዘብ ከፋዩ ለታክስ ከፋዩ ገንዘቡን ሊከፍል ከሚገባበት ቀን በፊት ወይም ገንዘቡ በታክስ ከፋዩ ስም ከተያዘበት ቀን በፊት ሊሆን አይችልም፡፡

5. የክፍያ ትዕዛዙን ለመፈፀም አልቻልኩም የሚል ገንዘብ ከፋይ የክፍያ ትዕዛዙ በደረሰው በ7 (በሰባት) ቀናት ውስጥ ትዕዛዙን ለመፈፀም ያልቻለበትን ምክንያት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡

6. ገንዘብ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ለባለሥልጣኑ ማስታወቂያ የላከ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ በተዘጋጀ ማስታወቂያ፦

ሀ/ ማስታወቂያውን በመቀበል የክፍያ ትዕዛዙን ሊሰርዘው ወይም ሊያሻሽለው፤ ወይም

ለ/ በገንዘብ ከፋዩ የተላከለትን ማስታወቂያ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

7. ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለ ወይም ስለታክስ አከፋፈሉ በባለሥልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የክፍያ ስምምነት የፈፀመ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለከፋዩ አስተላልፎት የነበረውን የክፍያ ትዕዛዝ በጽሑፍ በተሰጠ ማስታወቂያ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

8. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለከፋዩ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ማስታወቂያ ግልባጭ ለታክስ ከፋዩ መላክ አለበት፡፡

9. ባለሥልጣኑ በከፋዩ የተከፈለውን ማንኛውንም ገንዘብ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት የታክስ ዕዳ ላይ ያቀናንሳል፡፡

10. በዚህ አንቀጽ የሚሰጠውን ማስታወቂያ ያለምንም በቂ ምክንያት ያልተቀበለ ሰው በማስታወቂያው ለተመለከተው የገንዘብ መጠን በግሉ ኃላፊ ይሆናል፡፡

11. ይህ አንቀጽ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊታገድ በማይችል ንብረት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡

12. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ከፋይ" ማለት፦

ሀ/ ለታክስ ከፋዩ ባለዕዳ የሆነ ወይም ወደፊት ባለዕዳ የሚሆን፤

ለ/ ለታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም ገንዘብ የያዘ ወይም ወደፊት የሚይዝ፤

ሐ/ ለታክስ ከፋዩ የሚከፈል የሌላ ሰው ገንዘብ የያዘ፤

መ/ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ እንዲከፍል በሌላ ሰው ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

44. <u>ከሀገር መውጣትን ለመከልከል የሚሰጥ ትዕዛዝ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ትዕዛዙ ተፈጻሚ የሚሆንበት ሰው የሚከተሉትን ክፍያዎች ሳይከፍል ከሀገር ሊወጣ ይችላል የሚል በቂ ምክንያት ሲኖረው ይሆናል፦

ሀ/ ይህ ሰው መክፈል የሚኖርበትን ወይም ወደፊት የሚከፈል ታክስ፤ ወይም

ለ/ ይህ ሰው ሥራ አስኪያጅ የሆነበት ኩባንያ ወይም ውሳኔ በመስጠት ረገድ የዚህ ሰው ድርሻ ከፍተኛ የሆነበት ኩባንያ መክፈል የሚኖርበትን ወይም ለወደፊቱ የሚከፈል ታክስ፤ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለሥልጣኑ ማንኛውም ሰው ከሚከተሉት አንዱን ከመፈፀሙ በፊት ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ የሚከለክል ትእዛዝ "ከሀገር መውጣትን የሚከለክል ትዕዛዝ" ተብሎ የሚጠቀስ ሊሰጥ ይችላል፦

ሀ/ ማንኛውም ሰው፣ ድርጅት ወይም ኩባንያ ሊከፍል የሚገባውን ወይም ወደፊት የሚከፈለውን ታክስ በሙሉ እስከሚከፍል፤ ወይም

ለ/ ባለሥልጣኑ በሚቀበለው አኳኋን በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ታክስ ለመክፈል የክፍያ ስምምነት ሲያደርግ፡፡

3. ከሀገር እንዳይወጣ የሚከለክለው ትዕዛዝ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

ሀ/ ትዕዛዙ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ሰው ስም፣ አድራሻ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፤ እንዲሁም

ለ/ ከሀገር እንዳይወጣ የተከለከለው ሰው፣ ድርጅት ወይም ኩባንያ ሊከፍል የሚገባውን ወይም ለወደፊቱ ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን፡፡

4. ባለሥልጣኑ በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት ሥል ጣን ያለው ፍርድ ቤት ካላራዘመው በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚተላለፈው

ከሀገር መውጣትን የሚከለክል ትዕዛዝ ትዕዛዙ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከ10 (ከአስር) ቀናት በኋላ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

5. ባለሥልጣኑ ከሀገር እንዳይወጣ የሚከለክለውን ትዕዛዝ ግልባጭ ለተጠቀሰው ሰው መስጠት የሚኖርበት ሲሆን የዚህ ሰው ትዕዛዙን አለመቀበል በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከናወነውን ማንኛውንም ተግባር ዋጋ አልባ አያደርገውም፡፡
6. የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ኃላፊ የክልከላ ትዕዛዙ ሲደርሰው ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡ ኃላፊው የሚወስዳቸው እርምጃዎች ማንኛውንም ፓስፖርት፣ መታወቂያ ወይም ሌላ የተከለከለው ሰው ኢትዮጵያን ለቆ ለመውጣት የሚጠቀምበትን ማንኛውንም ሰነድ መያዝና ማስቀመጥን ይጨምራል፡፡
7. ሌሎች የኢሚግሬሽን ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ሰው ሀገር ለቆ እንዳይወጣ በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተመለከተውን ታክስ ከከፈለ ወይም ታክሱን እንደሚከፍል በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያለውን የክፍያ ስምምነት ከፈፀመ ባለሥልጣኑ ለዚህ ሰው ከሀገር ለመውጣት የሚያስችለው የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ ይህ ሰው ይህንን የምስክር ወረቀት ማቅረቡ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ለመፍቀድ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ሠራተኛ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሕጋዊ በሆነ መልኩ በተከናወነ ማንኛውም ተግባር ምክንያት በመንግሥት ወይም በታክስ፣ በጉምሩክ፣ በብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት፣ በፖሊስ ወይም በሌላ ሠራተኛ ላይ ምንም ዓይነት የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር ክስ ሊቀርብ ወይም ሊቀጥል አይችልም፡፡
9. ከሀገር መውጣትን የሚከለክል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው በዋና ዳይሬክተሩ ወይም ይህንን ትእዛዝ እንዲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን በሰጠው የታክስ ሠራተኛ ብቻ ነው፡፡

45.<u>የንግድ ድርጅትን ለጊዜው ስለማሸግ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው አንድ ታክስ ከፋይ በተደጋጋሚ፡-

ሀ/ በግብር ሕግ መሠረት የሚፈለግበትን ሰነድ ሳይዝ ሲቀር፤ ወይም

ለ/ ታክሱን በመክፈያ ጊዜው ሳይከፍል ሲቀር ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ7 (በሰባት) ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ወይምየሚፈለግበትን ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን የንግድ ድርጅት ለ14 (ለአስራ አራት) ቀን በጊዜያዊነት የሚያሽግ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡
3. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ታክሱን ካልከፈለ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ ካልያዘ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት ከ14 (ከአስራ አራት) ቀን ላልበለጠ ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲታሸግ የሚያደርግ ትዕዛዝ (“የማሸጊያ ትዕዛዝ” ተብሎ የሚጠቀስ) ይሰጣል፡፡
4. ባለሥልጣኑ ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት መግባት የሚችል ሲሆን የማሸጊያ ትዕዛዙ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ የፖሊስ መኮንን በቦታው እንዲገኝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ በማሸጊያ ትዕዛዝ መሠረት በታሸገው የታክስ ከፋዩ ንግድ ድርጅት ሕንፃ ላይ ፊት ለፊት በሚታይ ቦታ የሚከተሉትን ቃላት የያዘ ማስታወቂያ ይለጥፋል፡- “የታክስ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 45 መሠረት በባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ለጊዜው ታሽጓል” ፡፡
6. የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት እንደገና እንዲከፈት ያደርጋል፡-

ሀ/ ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ሥልጣን የተሰጠው ሠራተኛ ታክስ ከፋዩ የሂሣብ መዝገብ ሰነዶችን ለመያዝ የሚያስችል በቂ እርምጃ ወስዷል ብሎ ሲያምን፤

ለ/ ታክስ ከፋዩ ታክሱን የሚከፍል ከሆነ፤

7. የማሸጊያ ትዕዛዝ የሚሰጠው በዋና ዳይሬክተሩ ወይም ደግሞ የማሸጊያ ትዕዛዝ ለመስጠት በልዩ ሁኔታ በዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን በተሰጠው የታክስ ሠራተኛ ብቻ ነው፡፡

**46.<u>የተላለፉ የታክስ ዕዳዎች</u>**

1. አንድ ታክስ ከፋይ “አስተላላፊ” ተብሎ የሚጠቀስ ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ ጋር በተገናኘ ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ያለበት እንደሆነ እና የንግዱን ሀብቶች በሙሉ ወይም በከፊል ግንኙነት ላለው ሰው “ሀብቱ የተላለፈለት ሰው” ተብሎ ለሚጠቀስ

ያስተላለፈ እንደሆነ ከንግዱ ሀብት ጋር ተያይዞ ያልተከፈለውን ዕዳ ሀብቱ የተላለፈለት ሰው የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ባለሥልጣኑ የተላለፈውን የታክስ ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል ከሀብት አስተላላፊው ላይ እንዳይጠይቅ አያግደውም፡፡

47.<u>በድርጅት ስለሚከፈል ታክስ</u>

1. አንድ ድርጅት ታክሱን በመክፈያው ጊዜ ውስጥ ያልከፈለ እንደሆነ ታክሱ ባልተከፈለበት ጊዜ ወይም ታክሱ ከመከፈሉ በፊት ባሉት 6 (ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ሥራ አስኪያጅ የነበረ ማንኛውም ሰው ላልተከፈለው ታክስ ከድርጅቱ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈፃሚ አይሆንም፦

ሀ/ ድርጅቱ የሚፈለግበትን ግብር ሳይከፍል የቀረው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው ሰው ፈቃድ ወይም ዕውቀት ውጭ የሆነ እንደሆነ፤ እና

ለ/ ለሥራ አስኪያጅ የተሰጠው ኃላፊነት እና ሌሎች ሁኔታዎች ሲታዩ ሥራ አስኪያጁ ድርጅቱ ግብር ላለመክፈል የሚያደርገውን ጥረት ለመከላከል ተገቢውን ትጋት አሳይቶ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

48.<u>ማጭበርበር ወይም የታክስ ስወራ ሲፈፀም ስለሚኖር የታክስ ኃላፊነት</u>

1. የተመሰከረለት ኦዲተር፣ የተመሰከረለት ፐብሊክ የሂሳብ ባለሙያ ወይም ፐብሊክ ኦዲተር፦

ሀ/ ታክስ ከፋዩ ታክስን ለማሳነስ ወይም ታክሱን ለመሰወር እንዲችል የረዳ፣ ያበረታታ፤ የመከረ እንደሆነ፤

ለ/ ታክስ ለማሳነስ ወይም የታክስ ስወራን በሚያስከትል መልኩ በማንኛውም መንገድ እያወቀ ከታክስ ከፋዩ ጋር ከተባበረ ወይም የድርጊቱ አጋር ከሆነ በታክስ ማጭበርበሩ ወይም በታክስ ስወራው ምክንያት ለሚከሰተው የታክስ መቀነስ ከታክስ ከፋዩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

2. አንድ የተመሰከረለት ኦዲተር፣ የተመሰከረለት ፐብሊክ የሂሳብ ባለሙያ ወይም ፐብሊክ ኦዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ኃላፊ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ ይህንን ድርጊት፦

ሀ/ ለተመሰከረላቸው የፐብሊክ ሂሳብ ባለሙያዎች ተቋም፣ ለኢትዮጵያ የሂሳብና የኦዲት ቦርድ ወይም ለዚህ ሰው ፈቃድ ለሚሰጠው አካል ሪፖርት ማድረግ ያለበት ሲሆን ቦርዱም የኦዲተሩን ፈቃድ እንዲሰርዘው ይጠይቃል፤ ወይም

ለ/ የንግድ ፈቃድ የመስጠት ኃለፊነት ላለው ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ "ታክስን ማሳነስ" የሚለው ሀረግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 109 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ማካካሻ፣ ተመላሽ እና ከታክስ ዕዳ ነጻ ስለመሆን

### 49. ለታክስ ክፍያዎች የሚሰጥ ማካካሻ

1. ታክስ ከፋዩ በታክስ ዓመቱ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለቀረበት ታክስ እና በቅድሚያ ለከፈለው ታክስ ሊያገኝ የሚገባው ማካካሻ ታክስ ከፋዩ በታክስ ዓመቱ ከሚፈለግበት የገቢ ግብር ዕዳ በሚበልጥበት ጊዜ፣ ባለሥልጣኑ በብልጫ የታየውን ገንዘብ በሚከተለው ቅደም ተከተል ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡-

ሀ/ በመጀመሪያ (ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚቀርን ታክስ ሳይጨምር) ታክስ ከፋዩ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ታክስ ለመክፈል ይውላል፤

ለ/ ቀሪው ታክስ ከፋዩ በሌላ በማንኛውም የታክስ ሕግ የሚፈለግበትን ታክስ ለመክፈል ይውላል፤

ሐ/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተራፊ ገንዘብ ካለም ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ የተመላሽ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ይመለስለታል፡፡

2. ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) የተመለከተው ገንዘብ ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት ሊሸጋገር ይችላል፡፡

3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) በተደነገገው መሠረት ተራፊውን ገንዘብ ለታክስ ከፋዩ ካልከፈለ፣ ዘጠናው ቀን ካለቀ ጀምሮ ተራፊው ገንዘብ እስከሚመለስበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የማግኘት መብት አለው፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚከፈለው ወለድ መጣኔ በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው ጊዜ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ባለው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ የዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ይሆናል፡፡

**50.ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለን ታክስ ስለመመለስ**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ታክስ ከፋዩ (በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 የተደነገገውን ሳይጨምር) በታክስ ሕግ መሠረት ሊከፍል ከሚገባው ታክስ በላይ የከፈለ እንደሆነ ታክሱ ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለው ታክስ ይመለስለት ዘንድ ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ በላይ የከፈለውን ታክስ በሚመለከት ባለሥልጣኑ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲያደርግ የሚያስገድደው ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ነው፡፡
3. ባለሥልጣኑ በማመልከቻው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተጠቀሰው አመልካች በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡
4. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሲያመለክትና ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለ መሆኑን ሲያምንበት በብልጫ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን በሚከተለው ቅደም ተከተል ሥራ ላይ ያውላል፦

ሀ/ በመጀመሪያ (ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚቀረውን ታክስ ሳይጨምር) ታክስ ከፋዩ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ታክስ ለመክፈል ይውላል፤

ለ/ ቀሪው ታክስ ከፋዩ በሌላ በማንኛውም የታክስ ሕግ የሚፈለግበትን ታክስ ለመክፈል ይውላል፤

ሐ/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተራፊ ገንዘብ ካለ ታክስ ከፋዩ የተመላሽ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 45 (አርባ አምስት) ቀናት ወስጥ ለታክስ ከፋዩ ይመለስለታል፡፡

5. ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) (ሐ) የተመለከተው ገንዘብ በማንኛውም የታክስ ሕግ መሠረት ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት ሊሸጋገር ይችላል፡፡

6. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ታክስ በስህተት ተመላሽ ያደረገ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ በመጠየቂያ ሰነድ በተጠቀሰው ቀን በስህተት የተመለሰለትን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ መልሶ መክፈል አለበት፡፡
7. ተመላሽ በሚጠይቀው ታክስ ከፋይ አሳሳችነት ገንዘብ በስህተት የተመለሰ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ ገንዘቡ በስህተት በተመለሰበትና በስህተት የተመለሰው ገንዘብ ተመልሶ ለባለሥልጣኑ በተከፈለበት ቀን መካከል ላለው ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37(2) በተመለከተው መጣኔ መሠረት ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡
8. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) እንዲከፍለው የሚገደደው ተመላሽ ታክስ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል ታክስ ከፋዩ እንደሚከፍለው ማንኛውም ታክስ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

51.<u>ከባድ ችግር ሲያጋጥም ስለሚሰጥ የታክስ ምህረት</u>

1. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው ሚኒስትሩ፡-

ሀ/ ባልተጠበቀ የተፈጥሮ አደጋ ወይም ጥፋት ምክንያት ወይም ከታክስ ከፋዩ ቸልተኝነት ወይም ማንኛውም ጥፋት ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ የተፈጠረ ከባድ የግል ችግር ምክንያት ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ በሙሉ እንዲከፍል ማድረግ የማይቋቋመው ከባድ ችግር የሚያስከትልበት መሆኑን፤ ወይም

ለ/ በታክስ ከፋዩ ሞት ምክንያት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚኖርበትን ታክስ በሙሉ እንዲከፈል ማድረግ በታክስ ከፋዩ ጥገኞች ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥር መሆኑን፤ ሲያምንበት ነው፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ከሆነ ሚኒስትሩ ታክስ ከፋዩ ወይም የሟቹን ታክስ ከፋይ ንብረት የሚያጣራው ውርስ አጣሪ መከፈል የሚኖርበትን ታክስና ከዚህ ታክስ ጋር በተገናኘ ለዘገየ ክፍያ የሚጠየቀውን ወለድ በሙሉ ወይም በከፊል እንዳይከፈል ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የታክስ ዕዳ ምህረት ሊደረግ የሚችለው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰን የገንዘብ መጠን ልክ ይሆናል፡፡
4. ሚኒስትሩ ታክስ ከፋዩን ወይም የሟቹን ንብረት የሚያጣራውን ውርስ አጣሪ ከታክስ ዕዳ ነጻ የሚያደርገውን ውሳኔ የሰጠው በቀረበለት የተጭበረበረ ወይም አሳሳች መረጃ

ላይ በመመስረት ከሆነ በምህረት ቀሪ የተደረገው የታክስ ዕዳ ምህረት ከመሰጠቱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ በመመለስ ታክስ ከፋዩ ከታክስ ዕዳው ነጻ እንዳልተደረገ ተቆጥሮ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት እያንዳንዱን ምህረት የተሰጠበትን የታክስ ዕዳ እና የወለድ መጠን እና ምህረት የተሰጠበትን ምክንያት መዝግቦ በመያዝ በየስድስት ወሩ ለዋናው ኦዲተር ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

### 52.የምክንያቶች መግለጫ

በታክስ ሕግ መሠረት ለባለሥልጣኑ የቀረበን ማንኛውንም ማመልከቻ ባለሥልጣኑ ሳይቀበለው በሚቀርበት ጊዜ አለመቀበሉን የሚገልጸው ማስታወቂያ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያቶች መግለጫ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

### 53.የታክስ እና ይግባኝ የሚቀርብባቸው ውሳኔዎች የመጨረሻ ስለመሆናቸው

1. በዚህ ክፍል በተደነገገው ሥነ-ሥርዓት መሠረት ካልሆነ በስተቀር፦

ሀ/ የታክስ ወይም ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳኔ ወሳኝ እና የመጨረሻ በመሆኑ በማናቸውም ሁኔታ በኮሚሽኑ ወይም በፍርድ ቤት ወይም በሌላ የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት ተቃውሞ ሊቀርብበት አይችልም፤

ለ/ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ወይም በባለሥልጣኑ እንደ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ቅጂ የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ውሳኔው በአግባቡ የተሰጠ ስለመሆኑ እንዲሁም በታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ውሳኔው የተመለከተው የታክስ መጠን እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ወሳኝ ማስረጃ ነው፤ እንዲሁም

ሐ/ ታክስ ከፋዩ ራሱ የሚያሰላውን ታክስ በተመለከተ ታክስ ከፋዩ ራሱ ያሳወቀበትን ዋናውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም በባለሥልጣኑ እንደራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያው ዋናው ቅጂ የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ ስለማስታወቂያው ይዘት ወሳኝ ማስረጃ ነው፡፡

2. ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋይ የታክስ ስሌት ወይም ውሳኔ ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚሰጥበት ጊዜ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) የተመለከተው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ቅጂ ማስታወቂያውን ወይም ውሳኔውን በመለየት

እና በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተላለፈውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ዝርዝር ጉዳዮች በመግለጽ በባለሥልጣኑ የተረጋገጠን ሰነድ ይጨምራል፡፡

3. ታክስ ከፋይ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚያቀርብበት ጊዜ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) የተመለከተው የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ቅጂ ማስታወቂያውን በመለየት እና በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተላለፈውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ዝርዝር ጉዳዮች በመግለጽ በባለሥልጣኑ የተረጋገጠን ሰነድ ይጨምራል፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ውሳኔ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 (34) ለታክስ ውሳኔ በተሰጠው ትርጉም ሥር በፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ረ)፣ (ሰ) ወይም (ሸ) የተመለከተውን ነው፡፡

54.<u>በታክስ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ የቅሬታ ማስታወቂያ</u>

1. በታክስ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው በ21 (በሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቅሬታ የቀረበበት የታክስ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ከሆነ የታክስ ከፋዩ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር በተደረገው ማሻሻያ ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በታክስ ከፋይ የቀረበ የቅሬታ ማስታወቂያ በአግባቡ እንደቀረበ የሚቆጠረው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡-

ሀ/ የቅሬታ ማስታወቂያው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔውን የሚቃወምበትን ምክንያቶች፣ ታክስ ከፋዩ ውሳኔውን ለማስተካከል ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎች እና እነዚህን ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች በትክክል የሚገልጽ ከሆነ፣

ለ/ ቅሬታው ከታክስ ስሌት ጋር የተገናኘ ከሆነ ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ መሠረት መከፈል ያለበትን እና በቅሬታ ማስታወቂያው ተቃውሞ ያላቀረበበትን ታክስ የከፈለ እንደሆነ፣ እንዲሁም

ሐ/ በታክስ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ቢኖረውም ታክሱን ከፍሎ የቅሬታ ማስታወቂያ ማቅረብን የመረጠ ከሆነ የተወሰነበትን ታክስ ከከፈለ ነው፡፡

4. ባለሥልጣኑ የቅሬታ ማስታወቂያው በአግባቡ አልቀረበም ብሎ ሲያምን ለታክስ ከፋዩ የሚከተሉትን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ወዲያውኑ ይሰጠዋል፦

ሀ/ ቅሬታው በአግባቡ አልቀረበም የሚልባቸውን ምክንያቶች፤ እና

ለ/ ከሚከተሉት በዘገየው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ቅሬታውን ካላቀረበ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ እንደሚያልፍ፦

1) ቅሬታው የሚመለከተው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ21 (በሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ፤ ወይም

2) በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ማስታወቂያ በደረሰው በ10 (በአሥር) ቀናት ውስጥ፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ ከሆነ ባለሥልጣኑ ይህንን የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ለሚመለከተው ታክስ ከፋይ ይሰጣል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት ታክስ ከፋዩ በታክስ ውሳኔ ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ የሚያቀርብበት ጊዜ እንዲራዘምለት ለባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብ፣ ባለሥልጣኑ፦

ሀ/ ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ በመሆኑ፣ በህመም ምክንያት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (4) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የቅሬታ ማስታወቂያውን ማቅረብ አለመቻሉ፤ እና

ለ/ የቅሬታ ማስታወቂያውን ለማቅረብ በታክስ ከፋዩ በኩል ምክንያታዊ ያልሆነ መዘግየት አለመኖሩን፤ ሲያምንበት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ ከ10 (ከአሥር) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

55.<u>በቅሬታ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 መሠረት በአግባቡ የቀረቡ ቅሬታዎችን በነጻነት በመመርመር በቅሬታዎቹ ላይ ለሚሰጠው ውሳኔ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ቋሚ የሥራ ክፍል ያቋቁማል፡፡

2. ባለሥልጣኑ፣ ቅሬታዎች የሚታዩበትን ሥነ-ሥርዓት እና ለባለሥልጣኑ የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሣቦች የሚመሠረቱባቸውን ጉዳዮች እና የውሳኔ አሰጣጡን ሥርዓት የያዘ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡
3. የሥራ ክፍሉ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበውን ቅሬታ ሲመረምር በታክስ ስሌቱ የተመለከተው የታክስ መጠን ሊጨምር ይገባል የሚል እምነት ሲኖረው፣ የሥራ ክፍሉ የታክስ ስሌቱ ለሚመለከተው የታክስ ሠራተኛ ተመልሶ እንደገና እንዲታይ የውሳኔ ሃሳብ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. ባለሥልጣኑ በሥራ ክፍሉ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከመረመረ በኋላ፣ የቀረበውን ቅሬታ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ውሳኔውም "በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ" ተብሎ ይጠቀሳል፡፡
5. ባለሥልጣኑ በቅሬታ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ የሚያሳውቀው ሲሆን፣ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበ ቅሬታ ከሆነ የታክስ ስሌቱን ማሻሻልን ጨምሮ ውሳኔውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ይወስዳል፡፡
6. በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ማስታወቂያ የጉዳዩን ዋና ፍሬ ነገሮች፣ ግኝቶች እና ለውሳኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና ለኮሚሽኑ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል የሚገልጽ መግለጫ ማካተት አለበት፡፡
7. ታክስ ከፋዩ ቅሬታ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 (አንድ መቶ ሰማንያ) ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ በቅሬታው ላይ ውሳኔ ካልሰጠ ታክስ ከፋዩ ይግባኙን 180 (አንድ መቶ ሰማንያ) ቀን በተጠናቀቀ በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል፡፡

56.<u>ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ስለማቅረብ</u>

1. ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 88 መሠረት የይግባኝ ማስታወቂያውን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገናኘ በታክስ ከፋይ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 50% (ሃምሳ በመቶ) የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) "በክርክር ላይ ያለ ታክስ" ከታክሱ ጋር በተገናኘ ሊከፈል የሚገባውን ቅጣትና የዘገየ ክፍያ ወለድን አይጨምርም፡፡

4. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የይግባኝ ማስታወቂያ የሚቀርብበት ጊዜ እንዲራዘም ስለሚቀርብ ማመልከቻ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**57.ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ስለማቅረብ**

1. ለኮሚሽኑ በቀረበ የታክስ ይግባኝ ተካፋይ የነበረ ሰው ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ የኮሚሽኑ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በኮሚሽኑ በታየ የታክስ ይግባኝ ላይ ተከራካሪ የነበረ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጽሑፍ ማመልከቻ ሲጠይቅ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል፡፡
3. በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገናኘ በታክስ ከፋይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 75% (ሰባ አምስት በመቶ) የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
4. ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርበው በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሲሆን የይግባኝ ማስታወቂያውም በቀረበው ይግባኝ የሚነሱትን የሕግ ጉዳዮች መግለጽ አለበት፡፡
5. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በመስማት፡-

   ሀ/ የኮሚሽኑን ውሳኔ ሊያፀናው፤

   ለ/ የኮሚሽኑን ውሳኔ በመሻር፡-

   1) የኮሚሽኑን ውሳኔ የሚተካ ውሳኔ ሊሰጥ፤ ወይም

   2) ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚሽኑ ወይም ለባለሥልጣኑ መልሶ ሊልከው፤ ወይም

   ሐ/ ይግባኙን ውድቅ ሊያደርገው፤ ወይም

   መ/ ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ውሳኔ ሊሰጥ፤ ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) “በክርክር ላይ ያለ ታክስ” ማለት የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑ እንዲከፈል ውሳኔ የሰጠበት እና ታክስ ከፋዩ በይግባኝ ማስታወቂያ ቅሬታ ያቀረበበት ታክስ ሲሆን ከታክሱ ጋር በተገናኘ ሊከፈል የሚገባውን ቅጣትና የዘገየ ክፍያ ወለድን አይጨምርም፡፡

58.**ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለሚቀርብ ይግባኝ**

1. ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበ የታክስ ይግባኝ ተካፋይ የነበረ ሰው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ የፍርድ ቤቱ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በታየ የታክስ ይግባኝ ላይ ተከራካሪ የነበረ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጽሑፍ ማመልከቻ ሲጠይቅ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል፡፡

59.**የማስረዳት ኃላፊነት**

በዚህ ክፍል መሠረት ከታክስ ውሳኔ ጋር በተገናኘ በሚደረግ ማንኛውም የታክስ ክርክር ሂደት የታክስ ውሳኔ ትክክል አለመሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ነው፡፡

60.**የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍርድ ቤትን ውሳኔ ስለመፈጸም**

1. ባለሥልጣኑ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በደረሰው በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠትን ጨምሮ፣ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተመለከተው የተሻሻለ የታክስ ስሌት የጊዜ ገደብ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔን ተግባራዊ ለማድረግ በሚከናወን የታክስ ስሌት ማሻሻያ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ክፍል አሥር

## መረጃን ስለመሰብሰብና ስለማስፈፀም

61.**የታክስ ክሊራንስ**

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት የተጣለበትን ታክስ የመክፈል ግዴታ የፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻውን ባቀረበ በ14 (በአሥራ አራት) ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ የሚያቀርበው ታክስ ከፋይ ለቀደመው ዓመት ወይም ለቀደሙት ዓመታት በታክስ ከፋይነት ያልተመዘገበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የተመዘገበ መሆኑን በመግለጽ ታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ባቀረበ በ14 (በአሥራ አራት) ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት ይኖርበታል፡፡
4. ማንኛውም የሚኒስቴር መስሪያ ቤት፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የመንግሥት የሥራ ክፍል፣ ወይም የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት ቢሮ ወይም ሌላ ማንኛውም የመንግሥት አካል ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ማንኛውንም ፈቃድ መስጠት ወይም ማደስ ወይም በመንግሥት ጨረታ እንዲሳተፍ መፍቀድ አይችልም፡፡
5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ላቀረበ ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ላለመስጠት የወሰነ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ ማመልከቻውን ባቀረበ በ 14 (በአሥራ አራት) ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያት የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

62.<u>የመመስረቻ ጽሑፍን እና የመተዳደሪያ ደንብን ስለማቅረብ</u>

1. ማንኛውም ድርጅት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ የመመስረቻ ጽሑፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብ፣ የሽርክና ማህበር ስምምነት ወይም ሌላ የመመስረቻ ወይም የምዝገባ ሰነድ ቅጂ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሱት ሰነዶች ላይ ማንኛውም ለውጥ ሲደረግ ድርጅቱ ለውጡ በተደረገ በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለውጡን በጽሑፍ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

63.<u>ኦዲተሮች</u>

1. ኦዲተሮች የደንበኞቻቸውን የኦዲት ሪፖርት ለደንበኞቻቸው ካቀረቡበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ3 (የሦስት) ወር ጊዜ ውስጥ የኦዲት ሪፖርቶቹን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. ማንኛውም ኦዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ግዴታ ሳይወጣ የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ኦዲተሩ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ለኢትዮጵያ የሂሳብና ኦዲት ቦርድ ወይም ለኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች

ኢንስቲትዩት በማሳወቅ ቦርዱ ወይም ኢንስቲትዩቱ የኦዲተሩን ፈቃድ እንዲሰረዝ ይጠይቃል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ "ኦዲተር" ማለት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ለፐብሊክ ኦዲተር እና ለተመሰከረለት ኦዲተር የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

### 64.በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የሚደረግ የአገልግሎት ውልን ስለማሳወቅ

1. ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነ የአገልግሎት ውል በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የሚገባ ማንኛውም ሰው ውሉን ከፈረመበት ወይም መፈጸም ከጀመረበት ቀድሞ ከመጣው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ "ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነ የአገልግሎት ውል" ማለት የቅጥር ውልን ሳይጨምር፣ የዕቃ አቅርቦትን ቢጨምርም ባይጨምርም በዋነኝነት አገልግሎት በመስጠት ላይ የተመሠረተ ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነ ገቢ የሚያስገኝ የአገልግሎት ውል ነው፡፡

### 65.መረጃ ወይም ማስረጃ ለማግኘት ማስታወቂያ ስለመስጠት

1. ማንኛውንም የታክስ ሕግ ለማስተዳደር ሲባል ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋይ ቢሆንም ባይሆንም ለማንኛውም ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት፦

ሀ/ በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የራሱን ወይም የሌላ ማንኛውንም ሰው የታክስ ጉዳይ የሚመለከት በማስታወቂያው የተገለፀውን መረጃ እንዲሰጠው፤

ለ/ በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜና ቦታ በመገኘት የራሱን ወይም የሌላ ማንኛውንም ሰው የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ በማስታወቂያው የተገለጸውን ማስረጃ እንዲሰጠው፤

ሐ/ በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ከእርሱ ወይም ከሌላ ማንኛውም ሰው የታክስ ጉዳዮች ጋር የሚገናኙ በእጁ ወይም በእርሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ በማስታወቂያው የተገለፁ ሰነዶችን እንዲያቀርብ፤ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንዲቀርብ የተጠየቀው ሰነድ ከሆነ፣ የተጠየቀው ሰነድ መለየት በሚያስችል አኳኋን በማስታወቂያው መገለጹ በቂ ይሆናል፡፡
3. ይህ አንቀጽ፦

ሀ/ በኤሌክትሮኒክ መልክ የሚገኙትን ጨምሮ ማንኛውንም መረጃ መስጠትን ወይም ሰነድ ማቅረብን በተመለከተ ልዩ መብት የሚሰጥ ወይም የህዝብ ጥቅምን የሚመለከት ሌላ ሕግ፤ ወይም

ለ/ ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታን የሚጥል ውል፤ ቢኖርም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

66.<u>የመግባትና የመበርበር ሥልጣን</u>

1. ማንኛውንም የታክስ ሕግ ለማስተዳደር ሲባል ባለሥልጣኑ፦

ሀ/ በማንኛውም ጊዜና ያለምንም ማስታወቂያ በሚከተሉት ቦታዎች ላይ የመገኘት ወይም የሚከተሉትን የማግኘት ሙሉ እና ያልተገደበ መብት አለው፦

1) በማንኛውም ግቢ ወይም ቦታ፣ ማንኛውንም ዕቃ ወይም ንብረት፤

2) ማንኛውንም ሰነድ፤

3) ማንኛውንም የመረጃ ማከማቻ፤

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተሰጠው መብት መሠረት ያገኘውን በኤሌክትሮኒክ መልክ የተያዘን ጨምሮ የማንኛውንም ሰነድ የተወሰነ ክፍል ወይም ቅጂ ሊወስድ ይችላል፤

ሐ/ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ ለመወሰን ጠቃሚ ማስረጃ ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ሰነድ ሊይዝና በማንኛውም የታክስ ሕግ መሠረት የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ ለመወሰን ወይም ለማንኛውም የታክስ ክርክር እስካስፈለገ ጊዜ ድረስ ይዞ ማቆየት ይችላል፤

መ/ የታተመ መረጃ ወይም በመረጃ ማጠራቀሚያ መሳሪያ የተከማቸ መረጃ ካልተሰጠው የመረጃውን ቅጅ ለመውሰድ አስፈላጊ ለሆነ ጊዜ መሳሪያውን ይዞ ማቆየት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ሥልጣን ሊሰራበት የሚችለው ዋና ዳይሬክተሩ ወይም በዚህ ሥልጣን እንዲሠራ በዋና ዳይሬክተሩ ግልጽ ውክልና የተሰጠው የታክስ ሠራተኛ ብቻ ነው፡፡

3. ማንኛውም የታክስ ሠራተኛ ዋና ዳይሬክተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ሥልጣን ሊሰራበት እንደሚችል ፈቃድ የሰጠው መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ በባለቤቱ ወይም ሕጋዊ ባለይዞታ በሆነ ሰው ሲጠየቅ ማቅረብ ካልቻለ ወደ ማንኛውም ግቢ ወይም ቦታ መግባት ወይም ገብቶ መቆየት አይችልም፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ የሚሆንበት ቦታ ወይም ግቢ ባለቤት ወይም ሕጋዊ ባለይዞታ ለባለሥልጣኑ አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶችንና ድጋፍ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ/ ምርመራው በሚደረግበት ግቢ ወይም ቦታ የሚገኙ በመረጃ ማከማቻ ወይም በሌላ ማንኛውም መልክ የተያዙ ማናቸውንም ሰነዶች በተመለከተ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በቃል ወይም በጽሑፍ መልስ መስጠት፣ ወይም

ለ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተፈለገው ዳታ በሚስጥር ቁልፍ የተጠበቀ እንደሆነ የተቆለፈው ዳታ የሚፈታበትን መረጃ መስጠት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሰነድ ወይም የዳታ ማከማቻ መሳሪያ የተያዘበት ሰው ሰነዱን ወይም መሳሪያውን በመመርመር የፈለገውን መረጃ ቅጂ በዳታ ማከማቻ መሳሪያ ውስጥ የተያዙ ሰነዶች የኤሌክትሮኒክ ቅጂን ጨምሮ በመደበኛ የሥራ ሰዓትና ባለሥልጣኑ በሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት በራሱ ወጪ መውሰድ ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ መሠረት ለተወሰደና ለተያዘ ማንኛውም ሰነድ ወይም የዳታ ማከማቻ መሳሪያ ዋና ዳይሬክተሩ ወይም በዋና ዳይሬክተሩ የተወከለ የታክስ ሠራተኛ በፊርማው ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡
7. ይህ አንቀጽ፦

ሀ/ የሕግ ሙያን ጨምሮ ልዩ መብት የሚሰጥ ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተገናኘ በኤሌክትሮኒክ መልክ የሚገኙትን ጨምሮ ማንኛውንም ሰነድ ወይም ንብረት ማቅረብን፣ በማንኛውም ግቢ ወይም ቦታ መግባትን የሚመለከት ሌላ ሕግ፣ ወይም

ለ/ ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታን የሚጥል ውል፣ ቢኖርም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**67.<u>በታክስ ጉዳዮች የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነቶችን ሥራ ላይ ስለማዋል</u>**

1. ሚኒስቴሩ በታክስ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን በመወከል ከውጭ ሀገር መንግሥት ወይም መንግሥታት ጋር የሚደረጉ የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነቶችን ሊዋዋል፣ ሊያሻሽል ወይም ሊያቋርጥ ይችላል፡፡
2. በኢትዮጵያ ፀንተው በሚገኙ የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነቶች እና በታክስ ሕግ መካከል ግጭት ከተፈጠረ የመረዳዳት ስምምነቶቹ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

3. በኢትዮጵያ ውስጥ ፀንቶ ያለ የታክስ ወይም የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነት የመረጃ ልውውጥን ወይም በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሠረተ ታክስ የመሰብሰብ ትብብርን ወይም መጥሪያ መስጠትን የሚያስችሉ ድንጋጌዎች የያዙ ከሆነ፣ ባለሥልጣኑ በስምምነቶቹ መሠረት የኢትዮጵያን ግዴታዎች ለመወጣት በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ በማንኛውም ሕግ የተሰጠውን ሥልጣን መጠቀም የሚኖርበት ሲሆን፤ ለዚህ ዓላማ በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ፦

ሀ/ “ታክስ” የመረጃ ልውውጥ ወይም የጋራ መረዳዳት ስምምነት የሚመለከተው የውጭ ሀገር ታክስን፤

ለ/ “ያልተከፈለ ታክስ” በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውንና በመክፈያ ጊዜው ያልተከፈለን ታክስ፤

ሐ/ “ታክስ ከፋይ” በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበትን ሰው፤ እንዲሁም

መ/ “የታክስ ሕግ” በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው የውጭ ሀገር ታክስ የሚጣልበትን ሕግ፤ ይጨምራል፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ፦

ሀ/ “ዓለም አቀፍ ስምምነት” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም መንግሥታት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

ለ/ “የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነት” ማለት ከታክስ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ የታክስ መረጃ ልውውጥ ስምምነት ወይም የጋራ አስተዳደራዊ መረዳዳት እንዲኖር የሚደረግ ሌላ ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፤

ሐ/ “የታክስ ስምምነት” ማለት ተደራራቢ ታክስን ለማስቀረት እና የታክስ ማጭበርበርን ለመከላከል የሚደረግ ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ

## የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

### ምዕራፍ አንድ

### በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም

68. አስገዳጅ የሆኑ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ትርጉሞች

1. ሚኒስቴሩ አንድን የታክስ ሕግ አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 መሠረት የተሰጠ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም እስካልተነሳ ድረስ በሚኒስቴሩ እና በባለሥልጣኑ ላይ አስገዳጅ ይሆናል፡፡
3. በሚኒስቴሩ የተሰጠ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በታክስ ከፋዮች ላይ አስገዳጅ አይሆንም፡፡

69.<u>በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ስለመስጠት</u>

1. ሚኒስቴሩ የሚሰጠው በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ ማውጣት አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ የሚያወጣው በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ መሆኑን መግለጽ የሚኖርበት ሲሆን በትርጉሙ የተመለከተውን ጉዳይ የሚገልጽ ርዕስና መለያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፡፡
3. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በዚሁ ትርጉም ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሲሆን በትርጉሙ ላይ ምንም ቀን ካልተመለከተ ትርጉሙ በሚኒስቴሩ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ትርጉም በትርጉሙ በተገለፀው ሁኔታ የአንድን ታክስ ሕግ አፈጻፀም በሚመለከት የሚኒስቴሩን አስተያየት የሚገልጽ ሲሆን ለዚህ አዋጅ ወይም ለሌላ ሕግ አፈጻፀም ሲባል የሚኒስቴሩ ውሳኔ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

70.<u>በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን ስለማንሳት</u>

1. ሚኒስቴሩ በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ ማስታወቂያ በማውጣት በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ ይችላል፡፡ ይህም ሲሆን የትርጉሙ ተፈጻሚነት መቋረጥ፦

ሀ/ በማስታወቂያ ከተገለፀው ቀን፤ ወይም

ለ/ ማስታወቂያው በሚኒስቴሩ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ላይ ከወጣበት ቀን፤ ከሁለቱ በዘገየው ቀን ይጀምራል፡፡

2. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ከሚሆን ትርጉም ጋር የሚቃረን ሕግ ከወጣ ወይም ሚኒስቴሩ የተለየ ትርጉም ከሰጠ ነባሩ ትርጉም ከሕጉ ወይም ከተሰጠው አዲስ ትርጉም ጋር የማይጣጣም እስከሆነ ድረስ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡
3. በሙሉ ወይም በከፊል የተነሳ በሁሉም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም፡-

ሀ/ ከመነሳቱ በፊት ለተጀመሩ ግብይቶች ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል፤

ለ/ ከተነሳ በኋላ ለተጀመረ ግብይት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም

### 71.አስገዳጅ የሆኑ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ትርጉሞች

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በፈጸመው ወይም ሊፈጽም ባሰበው ግብይት ላይ የአንድን ታክስ ሕግ ተፈጻሚነት በተመለከተ የሚኒስቴሩ አቋም ምን እንደሆነ የሚገልጽ ትርጉም እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሑፍ ሆኖ፡-

ሀ/ ከማመልከቻው ጋር ግንኙነት ያለውን ግብይት ዝርዝር ጉዳዮችና ለግብይቱ አግባብነት ያላቸውን ሁሉንም ሰነዶች ማካተት፤

ለ/ ትርጉሙ የተጠየቀበትን ጉዳይ በግልጽ ማመልከት፤ እንዲሁም

ሐ/ አግባብነት ያለው የታክስ ሕግ ለግብይቱ ያለውን ተፈጻሚነት በተመለከተ የታክስ ከፋዩን አስተያየት ሙሉ መግለጫ መያዝ፤ አለበት፡፡

3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 72 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀረበው ማመልከቻ በደረሰው በ60 (በስልሳ) ቀናት ውስጥ ለቀረበለት ጥያቄ ጉዳዩን የሚመለከት ትርጉም መስጠት አለበት፡፡
4. ታክስ ከፋዩ ትርጉሙ ለተጠየቀበት ግብይት አግባብነት ያለውን ትክክለኛ እና የተሟላ ማስረጃ ያቀረበ እና ግብይቱም በማንኛውም ረገድ በቀረበው ማመልከቻ እንደተገለጸው መከናወኑ ከተረጋገጠ በዚህ ላይ ተመስርቶ የተሰጠው ትርጉም በሚኒስቴሩ እና በባለሥልጣኑ ላይ አስገዳጅ ይሆናል፡፡
5. በሚኒስቴሩ የሚሰጥ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በታክስ ከፋዩ ላይ አስገዳጅ አይሆንም፡፡

6. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ትርጉሙ በተሰጠበት ጊዜ ጸንቶ ካለ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ከሚሆን ትርጉም ጋር የሚቃረን ከሆነ በሁለቱ ትርጉሞች መካከል ያለውን ልዩነት በሚመለከት በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን የተሰጠ ትርጉም ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

72.**<u>በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ለመጠየቅ የቀረበን ማመልከቻ ስለአለመቀበል</u>**

1. ሚኒስቴሩ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም እንዲሰጥ በታክስ ከፋዩ የቀረበን ማመልከቻ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ላይቀበለው ይችላል፦

ሀ/ ባለሥልጣኑ ወይም ሚኒስቴሩ እንደአግባብነቱ ማመልከቻ በቀረበበት ጥያቄ ላይ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውሳኔ ሰጥቶበት ከሆነ፦

1) የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠው፤

2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 መሠረት የተሰጠ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በሥራ ላይ ያለ ከሆነ፤

3) በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 75 መሠረት በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ ወጥቶ በሥራ ላይ ያለ ከሆነ፡፡

ለ/ ማመልከቻው ታክስ ከፋዩን ከሚመለከት በታክስ ኦዲት ሥር ካለ ጉዳይ ጋር የተገናኘ፣ ታክስ ከፋዩ ተቃውሞ ካቀረበበት ጉዳይ ጋር የተገናኘ ወይም ታክስ ከፋዩ ራሱ ያሰላውን የታክስ መጠን ለማሻሻል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 መሠረት ከቀረበ ማመልከቻ ጋር የተገናኘ ከሆነ፤

ሐ/ ማመልከቻው ፋይዳ የሌለው ወይም ህውከት ለመፍጠር የቀረበ ከሆነ፤

መ/ ማመልከቻው የቀረበበት ግብይት ያልተካሄደ ሲሆን ወይም ግብይቱ ሊካሄድ እንደማይችል ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለ፤

ሠ/ ታክስ ከፋዩ ትርጉሙን ለመስጠት የሚያስችል በቂ መረጃ ለሚኒስቴሩ ያላቀረበ ከሆነ፤

ረ/ ማመልከቻውን ለመቀበል የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች እና ሚኒስቴሩ አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ሌሎች ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት በሚኒስቴሩ አስተያየት ማመልከቻውን መቀበል ምክንያታዊ ካልሆነ፤

ሰ/ ትርጉሙን መስጠት ከታክስ የመሸሽ ድንጋጌን ተፈጻሚነት የሚያካትት ሲሆን፡፡

2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም እንዲሰጥ የቀረበን ማመልከቻ ውድቅ ለማድረግ መወሰኑን ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**73.<u>በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ስለመስጠት</u>**

1. ሚኒስቴሩ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሲሰጥ ለአመልካቹ ታክስ ከፋይ በጽሑፍ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን በዚህ ዓይነት የሚሰጥ ትርጉም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 ቀደም ብሎ ካልተነሳ በስተቀር በትርጉሙ ለተጠቀሰው ጊዜ የሚያገለግል ይሆናል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ወደፊት ሊከሰት የሚችልን ነገር ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ጉዳት ታሳቢ በማድረግ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. የተሰጠው ትርጉም በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን እና ትርጉሙ የተሰጠበትን ጥያቄ መግለጽ ያለበት ሆኖ የሚከተሉትን ጉዳዮችም መያዝ ይኖርበታል፦

   ሀ/ ታክስ ከፋዩን፤

   ለ/ ለትርጉሙ አግባብነት ያለውን የታክስ ሕግ፤

   ሐ/ ትርጉሙ ተፈጻሚ የሚሆንበትን የታክስ ዘመን፤

   መ/ ትርጉሙ የሚመለከተውን ግብይት፤

   ሠ/ ትርጉሙ የተመሠረተባቸውን ታሳቢዎች፡፡
4. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በቀረበው ማመልከቻ በተመለከተው ጉዳይ ላይ የሚኒስቴሩን አስተያየት የሚገልጽ ሲሆን ለዚህ አዋጅ ወይም ለሌላ ሕግ አፈጻፀም ሲባል የሚኒስቴሩ ውሳኔ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

**74.<u>በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን ስለማንሳት</u>**

1. ሚኒስቴሩ በቂ ምክንያት ሲኖር በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ለሚመለከተው ታክስ ከፋይ የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ ይችላል፡፡ ይህም ሲሆን ትርጉሙ በማስታወቂያው ላይ ከተገለጸው ቀን ጀምሮ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡
2. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ከሚሆን ትርጉም ጋር የሚቃረን ሕግ ከወጣ ወይም ሚኒስቴሩ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን አዲስ ትርጉም

ከሰጠ ነባሩ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ከሕጉ ወይም ከተሰጠው አዲስ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ጋር የማይጣጣም እስከሆነ ድረስ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

3. የተነሳ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም፦

ሀ/ ከመነሳቱ በፊት ለተጀመሩ የታክስ ከፋዩ ግብይቶች ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል፤

ለ/ ከተነሳ በኋላ ለተጀመረ የታክስ ከፋዩ ግብይት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

75.በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም መሰጠቱን ስለማሳወቅ

1. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 73 መሠረት የሰጠውን በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ ማውጣት አለበት፡፡ ሆኖም ትርጉሙ የሚመለከተውን ታክስ ከፋይ ማንነት እና በትርጉሙ የተጠቀሰውን ማንኛውንም ሚስጥራዊ የንግድ መረጃ ይፋ ማድረግ የለበትም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ታክስ ከፋይበዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይፋ በሆነ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሊጠቀም የሚችል ሲሆን ሚኒስቴሩ እና ባለሥልጣኑ በትርጉሙ ለተመለከቱት ፍሬ ነገሮች አግባብነት ላለው የታክስ ሕግ ተፈጻሚነት እና ትርጉሙ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ይፋ በተደረገው ትርጉም ይገደዳሉ፡፡
3. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 መሠረት ሲነሳ ሚኒስቴሩ የትርጉሙ አስገዳጅነት በአንቀጽ 74 ከተመለከተው ቀን ጀምሮ የሚቋረጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ወዲያውኑ በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ ማውጣት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የሚኒስቴሩ ሌሎች አስተያየቶች

76.ሚኒስቴሩ የሚሰጣቸው ሌሎች አስተያየቶች

በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ከሚሰጡ በሚኒስቴሩ እና በባለሥልጣኑ ላይ አስገዳጅ ከሆኑና በሁሉም ታክስ ከፋዮች ወይም በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ከሚሆኑ ትርጉሞች በስተቀር በሚኒስቴሩ የሚቀርቡ የሕትመት ውጤቶች ወይም በሌላ መልኩ በቃልም ሆነ በጽሑፍ የሚሰጡ አስተያየቶች በሚኒስቴሩ ወይም በባለሥልጣኑ ላይ አስገዳጅነት አይኖራቸውም፡፡

## ክፍል አሥራ ሁለት
## ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

### 77.የሥራ ቋንቋ

አማርኛ የፌደራል የታክስ ሕጎች ቋንቋ ነው፣ ስለሆነም ባለሥልጣኑ በአማርኛ ያልተደረገን ግንኙነት ወይም ለባለሥልጣኑ ያልቀረበን ሰነድ ዕውቅና ላይሰጠው ይችላል፡፡

### 78.ቅጾችን እና ማስታወቂያዎች

1. ቅጾች፣ ማስታወቂያዎች፣ የታክስ ማስታወቂያዎች፣ መግለጫዎች፣ ሠንጠረዦች እና ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚፀድቁ ወይም የሚታተሙ ሰነዶች የታክስ ሕጎችን በብቃት ለማስተዳደር ባለሥልጣኑ በወሰነው ቅጽ የሚዘጋጁ ሲሆን የታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልደነገገ በስተቀር እነዚህን ሰነዶች በባለሥልጣኑ ኦፊሴላዊ ድረ- ገጽ ላይ ማውጣት አስገዳጅ አይደለም፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ሰነዶች በባለሥልጣኑ ቢሮዎች ወይም በሌላ ቦታዎች ወይም በፖስታ፣ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ፣ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው ሌላ ዘዴ ሕዝብ እንዲያገኛቸው ማድረግ አለበት፡፡

### 79.የፀደቀ ቅጽ

1. በታክስ ከፋይ የሚቀርብ ማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት እንደቀረበ የሚቆጠረው ሰነዱ፡-
   ሀ/ ለሰነዱ ዓይነት በባለሥልጣኑ በፀደቀ ቅጽ መሠረት የቀረበ፤
   ለ/ ማንኛውንም ተያያዥ ሰነዶች ጨምሮ ቅጹ የሚጠይቀውን መረጃ የያዘ፤ እና
   ሐ/ ቅጹ በሚጠይቀው መሠረት የተፈረመ፤
   
   ሲሆን ነው፡፡
2. ታክስ ከፋዩ ለባለሥልጣኑ ያቀረበው የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ያልቀረበ ከሆነ ባለሥልጣኑ ሰነዱ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ያልቀረበ መሆኑን ለዚሁ ሰው ወዲያውኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. አንድ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ያልቀረበ ቢሆንም ሰነዱ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የሚፈለጉትን አብዛኞቹን መረጃዎች በያዘ ቅጽ የቀረበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ይህንን ሰነድ ሊቀበለው ይችላል፡፡

### 80.ሰነዶች ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርቡበት አኳኋን

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተገለጸው መንገድ እንዲያቀርብ በባለሥልጣኑ በጽሑፍ ካልተፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 (2) መሠረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ የሚጠበቅበትን የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማቅረብ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈጻሚ የማይሆንበት ታክስ ከፋይ የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በአካል ወይም መደበኛ ፖስታ በመጠቀም ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡

**81.<u>ማስታወቂያዎችን ስለመስጠት</u>**

1. በታክስ ሕግ መሠረት ለአንድ ታክስ ከፋይ የወጣ፣ እንዲደርስ የሚደረግ ወይም የሚሰጥ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰነድ ለታክስ ከፋዩ በሚከተለው አኳኋን በጽሑፍ ሊደርሰው ይገባል፦

ሀ/ ለታክስ ከፋዩ ወይም ለታክስ እንደራሴው ወይም ለታክስ ወኪሉ በአካል በመስጠት ወይም የተላከውን ሰነድ የሚቀበል ሰው ካልተገኘ ማስታወቂያውን ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የታክስ ከፋዩ የንግድ ወይም መኖሪያ ቤት በር ላይ ወይም ሌላ አመቺ ቦታ ላይ በመለጠፍ፤

ለ/ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የታክስ ከፋዩ መደበኛ ወይም በመጨረሻ የሚታወቀው የንግድ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤት በሪኮማንዴ ደብዳቤ በመላክ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 (3) መሠረት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለታክስ ከፋዩ በማስተላለፍ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ዘዴዎች በመጠቀም ማስታወቂያውን ማድረስ ካልተቻለ፣ የህትመት ወጪው በታክስ ከፋዩ የሚሸፈን ሆኖ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ጋዜጣ ማስታወቂያውን በማውጣት ማስታወቂያው እንዲደርስ ማድረግ ይቻላል፡፡
3. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መሠረት በደረሰው ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ መሠረት የሚፈለግበትን ተግባር በሙሉ ወይም በከፊል ከፈጸመ በኋላ ማስታወቂያው ወይም ሌላው ሰነድ እንዲደርሰው በተደረገበት መንገድ ሕጋዊነት ላይ ተቃውሞ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**82.<u>የኤሌክትሮኒክ የታክስ ሥርዓትን ተግባራዊ ስለማድረግ</u>**

1. በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን የሚደነግግ አንቀጽ ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ተግባራት በኮምፒዩተር ሥርዓት ወይም በሌላ ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ አማካኝነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲከናወኑ ሊፈቅድ ይችላል፦

ሀ/ በታክስ ሕግ መሠረት ለመመዝገብ ወይም የታክስ መለያ ቁጥር ለማግኘት ማመልከቻ ለማቅረብ፤

ለ/ በታክስ ሕግ መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ ለማቅረብ፤

ሐ/ በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ ወይም ሌላ ክፍያ ለመፈጸም፤

መ/ በታክስ ሕግ መሠረት የታክስ ተመላሽ ክፍያ ለመፈጸም፤

ሠ/ ባለሥልጣኑ የሚያስተላልፈውን ማንኛውንም ሰነድ ለመላክ፤

ረ/ በታክስ ሕግ መሠረት መከናወን የሚኖርበትን ወይም እዲከናወን የተፈቀደ ሌላ ድርጊት ወይም ነገር ለማከናወን፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ማንኛውም ተግባር የኮምፒዩተር ሥርዓትን ወይም ሌላ ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያን በመጠቀም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲፈጽም ታክስ ከፋይን ሊያዝ ይችላል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ማንኛውንም ተግባር የኮምፒዩተር ሥርዓትን ወይም ሌላ ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያን በመጠቀም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊያከናውን ይችላል፡፡
4. ታክስ ከፋዩ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ግንኙነቶችን ለመቀበል ወይም ለማድረግ የሚያስችለው አቅም እንደሌለው ባለሥልጣኑ ካመነበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡
5. በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የታክስ ማስታወቂያ የሚያቀርብና ታክስ የሚከፍል ማንኛውም ታክስ ከፋይ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን በሌላ ዘዴ እንዲጠቀም ባለሥልጣኑ ካልፈቀደለት በስተቀር በዚሁ ዘዴ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

**83.<u>ሰነድን የማቅረቢያ ወይም ታክስ የመክፈያ ጊዜ</u>**

1. የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ፣ ወይም ሌላ ሰነድ የሚቀርብበት ቀን፤
2. የታክስ መክፈያ ቀን፤ ወይም

3. በታክስ ሕግ መሠረት ሌላ ማንኛውም እርምጃ የሚወሰድበት ቀን፤ ቅዳሜ፣ እሁድ ወይም በኢትዮጵያ የህዝብ በዓል ቀን ላይ ከዋለ ሰነዱ የሚቀርብበት፣ ክፍያው የሚፈጸምበት ወይም በታክስ ሕግ መሠረት ሌላ ማንኛውም እርምጃ የሚወሰድበት ቀን የሚቀጥለው የሥራ ቀን ይሆናል፡፡

## 84.ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት

1. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

ሀ/ በታክስ ሕግ መሠረት የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ ለታክስ ከፋዩ የተሰጠው ከሆነ፤

ለ/ የተሰጠው ማስታወቂያ በይዘቱ እና በውጤቱ ማስታወቂያው መሠረት ካደረገው የታክስ ሕግ ዓላማ እና መንፈስ ጋር የሚስማማ ወይም የተጣጣመ ከሆነ፤ እና

ሐ/ የታክስ ስሌቱ የሚመለከተው፣ ይመለከተዋል ተብሎ የሚታሰበው ወይም ማስታወቂያው የሚመለከተው ታክስ ከፋይ በማስታወቂያው የተሰየመው የጋራ ዓላማን እና ግንዛቤን መሠረት አድርጎ ከሆነ፤ ነው፡፡

2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፡-

ሀ/ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ለታክስ ከፋዩ በአግባቡ እንዲደርሰው እስከተደረገ ድረስ ለማስታወቂያው መሠረት የሆነው የታክስ ሕግ ማንኛውም ድንጋጌ አልተጠበቀም በሚል ምክንያት ማስታወቂያውን ተቀባይነት ማሳጣት፤

ለ/ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ፎርም አልተሟላም በሚል ውድቅ ማድረግ ወይም እንዳልተሰጠ መቁጠር ወይም እንዳልተሰጠ እንዲቆጠር ማድረግ፤ እና

ሐ/ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ላይ በሚታይ ስህተት፣ ግድፈት ወይም ጉድለት ምክንያት ተቀባይነት ማሳጣት፤ አይቻልም፡፡

3. ስህተቱ ወይም ልዩነቱ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የተሰጠውን ታክስ ከፋይ የሚያሳስት እስካልሆነ ድረስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው በሚከተሉት ምክንያቶች ዋጋ ሊያጣ አይችልም፡-

ሀ/ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው በተጠቀሰው የታክስ ከፋይ ስም፣ በተገለጸው የገቢ ወይም የገንዘብ መጠን ወይም እንዲከፈል በተጠየቀው የታክስ መጠን ስህተት ምክንያት፤

ለ/ በተዘጋጀው የታክስ ስሌት እና ለታክስ ከፋዩ በተሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ መካከል በሚታይ ልዩነት ምክንያት፡፡

85.<u>ስህተቶችን ስለማረም</u>

ባለሥልጣኑ በታክስ ሕግ መሠረት ለታክስ ከፋዩ የሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ በታክስ ሕግ ወይም በጉዳዩ ኩነቶች ላይ የትርጉም ጥያቄ የማያስነሳ የጽሁፍ፣ የሂሳብ ስሌት ወይም ሌላ ማንኛውንም ስህተት የያዘ በሚሆንበት ጊዜ፣ ባለሥልጣኑ ስህተቱን ለማረም ሲባል የታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ወይም ሌላውን ሰነድ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ሰነዱ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 (አምስት) ዓመታት ውስጥ ማሻሻል ይችላል፡፡

## ክፍል አሥራ ሦስት

## የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

86.<u>የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ስለማቋቋም</u>

1. የታክስ ይግባኝ በሚባልባቸው ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ የሚሰማ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማል፡፡
3. ኮሚሽኑ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ ይሆናል፡፡

87.<u>የኮሚሽኑ አባላት አሿሿም</u>

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኮሚሽኑን ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊ የሆኑትን አባላት ለኮሚሽኑ ይሾማል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን የሚያሟላ ሰው የኮሚሽኑ አባል ሆኖ ሊሾም ይችላል፦

ሀ/ በታክስ ወይም በንግድ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ልምድ ያለው የሕግ ባለሙያ፤

ለ/ በታክስ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ልምድ ያለው እና የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት አባል የሆነ ሰው፤

ሐ/ ቀደም ሲል የታክስ ሠራተኛ የነበረ እና በታክስ ጉዳዮች ሰፊ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ልምድ ያለው ሰው፤

መ/ ከኮሚሽኑ ተግባራት ጋር አግባብነት ያለው ልዩ ዕውቀት፣ ልምድ ወይም ክህሎት ያለው ሰው፡፡

3. የሚከተሉት ሰዎች የኮሚሽኑ አባላት ሆነው አይሾሙም፦

ሀ/ በታክስ ሠራተኛነት በማገልገል ላይ ያለ ሰው ወይም የታክስ ሠራተኛነቱን ከተወ ሁለት ዓመት ያልሞላው ሰው፣

ለ/ ከታክስ ማጭበርበር ወይም ስወራ ጋር በተገናኘ በታክስ ሕግ መሠረት ቅጣት የተጣለበት ወይም በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው፤

ሐ/ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ መሠረት በሙስና ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው፤

መ/ እዳውን ያልከፈለ የከሰረ ሰው፡፡

4. አንድ የኮሚሽኑ አባል፦

ሀ/ የሙሉ ጊዜ ወይም የከፊል ጊዜ አባል ሆኖ ሊሾም ይችላል፤

ለ/ የሥራ ዘመኑ ሦስት ዓመት ሆኖ ለሌላ የሥራ ዘመን እንዲያገለግል በድጋሚ ሊሾም ይችላል፤

ሐ/ ሲሰየም የሚከፈለውን አበል እና ሌሎች ክፍያዎችን ጨምሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚወስናቸው የሥራ ሁኔታዎች መሠረት በአባልነት ያገለግላል፡፡

5. የአንድ የኮሚሽን አባል ሹመት የሚቋረጠው፦

ሀ/ በቅጥር ወይም በሌላ ሁኔታ በታክስ ሠራተኛነት ማገልገል ሲጀምር፣

ለ/ ከታክስ ማጭበርበር ወይም ሥወራ ጋር በተገናኘ በታክስ ሕግ መሠረት ቅጣት ከተጣለበት ወይም በወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ፤

ሐ/ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ መሠረት በሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ፣

መ/ ከስሮ እዳውን ያልከፈለ ሲሆን፤

ሠ/ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የጽሑፍ መልቀቂያ ጥያቄ በማቅረብ ሥራውን ሲለቅ፤

ረ/ የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ እና በድጋሚ ያልተሾመ እንደሆነ፤ ወይም

ሰ/ የኮሚሽኑን ሥራ ለመሥራት ባለመቻሉ ወይም በተረጋገጠ የሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት በጽሑፍ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሥራው ሲነሳ፡፡

6. ማንኛውም የኮሚሽኑ አባል በዚህ ክፍል መሠረት ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣት በፈፀመው ድርጊት ወይም አለማድረግ ምክንያት ምንም ዓይነት ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

**88.<u>የይግባኝ ማመልከቻ</u>**

1. ይግባኝ በሚባልበት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የፈለገ ሰው የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም በውሳኔው ላይ የይግባኝ ማመልከቻ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. የይግባኝ ማመልከቻው ይግባኝ የቀረበበትን ምክንያቶች የሚያመለክት መግለጫ መያዝ ይኖርበታል፡፡
3. ኮሚሽኑ የጽሑፍ ማመልከቻ ሲቀርብለት እና አጥጋቢ ምክንያት መኖሩን ሲያምን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡
4. ኮሚሽኑ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘም የሚቀርብ ማመልከቻ የሚስተናገድበትን ስነ-ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡
5. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የፀደቀ ቅጽ" ማለት በኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት የፀደቀ የይግባኝ ማመልከቻ ቅጽ ነው፡፡

89.<u>ለኮሚሽኑ ሰነዶችን የማቅረብ ሥልጣን</u>

1. ባለሥልጣኑ የይግባኝ ማስታወቂያው በደረሰው በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ ወይም ኮሚሽኑ በፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ፦

ሀ/ የይግባኝ ማመልከቻ የቀረበበትን ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ ግልባጭ፤

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተጠቀሰው ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ ላይ ያልተጠቀሰ ለውሳኔው ምክንያት የሆነ መግለጫ፤

ሐ/ ውሳኔውን በይግባኝ ለማየት ለኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም ሌላ ሰነድ፤ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት የቀረበው የውሳኔ ምክንያቶች መግለጫ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው በጽሑፍ ማስታወቂያ ባለሥልጣኑን በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የውሳኔውን ምክንያቶች የሚያብራራ ተጨማሪ መግለጫ እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡
3. ኮሚሽኑ ለይግባኙ አወሳሰን ሌሎች ሰነዶችን ማየት ጠቃሚ ነው ብሎ ሲያምን ባለሥልጣኑን በጽሑፍ ማስታወቂያ በማስታወቂያው በተገለጸው ጊዜ ውስጥ እነዚህን ሰነዶች እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለኮሚሽኑ ያቀረበውን የማናቸውንም መግለጫ እና ሰነድ ቅጅ ለይግባኝ ባዩ መስጠት አለበት፡፡

90.<u>የኮሚሽኑ አሠራር ሥርዓት</u>

1. ፕሬዝዳንቱ ከኮሚሽኑ ችሎቶች የአንዱ አባል በመሆን ያገለግላል፡፡ በይግባኝ የተነሱትን ጭብጦች ግምት ውስጥ በማስገባት እንደአስፈላጊነቱ ይግባኙን

ለመስማት አባላት ይመድባል፡፡

2. የኮሚሽኑን አሰራር በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም የኮሚሽኑ አባል በሚያየው ማንኛውም ጉዳይ በአባልነቱ ከሚያከናውነው ተግባር ጋር ሊጋጭ የሚችል ቁሳዊ፣ የገንዘብ፣ ወይም ሌላ ጥቅም ሲኖር ይህንኑ ጥቅም ለፕሬዝዳንቱ መግልጽ ያለበት ሲሆን ፕሬዝዳንቱም ይህንን ጥቅም በመመዝገብ አባሉ በይግባኝ ሰሚነት እንዳይሳተፍ ያደርጋል፡፡
4. የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 88 መሠረት የሚቀርብን ይግባኝ የክልል የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንዲያይ የውክልና ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡

91.<u>የኮሚሽኑ ውሳኔ</u>

1. ኮሚሽኑ የቀረበለትን ይግባኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (7) በተደነገገው መሠረት በመስማት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. ኮሚሽኑ የይግባኝ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን ቀጥለው ባሉት 120 (አንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ በቀረበው ይግባኝ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. ፕሬዝዳንቱ የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት እና ለፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለተከራካሪ ወገኖች የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት የይግባኝ መወሰኛ ጊዜውን ከ60 (ከስልሳ) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡
4. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ሳያከብር መቅረቱ ኮሚሽኑ የሰጠውን ውሳኔ ተቀባይነት ሊያሳጣው አይችልም፡፡
5. የቀረበው ይግባኝ የታክስ ስሌትን የሚመለከት ከሆነ ኮሚሽኑ፡-

ሀ/ በታክስ ስሌቱ የተወሰነውን የገንዘብ መጠን ሊያፀናው፣ ሊቀንሰው፣ ወይም ስሌቱን በሌላ አኳኋን ሊያሻሽለው፤ ወይም

ለ/ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት እንደገና እንዲመለከተው የታክስ ስሌቱን ለባለሥልጣኑ ሊመልሰው፤ ይችላል፡፡

6. ኮሚሽኑ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበን ይግባኝ በመመርመር የታክስ ስሌቱ ሊጨመር ይገባል የሚል እምነት ሲኖረው፣ ኮሚሽኑ የታክስ ስሌቱን ማስታወቂያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) (ለ) መሠረት ለባለሥልጣኑ መልሶ ይልካል፡፡
7. የቀረበው ይግባኝ፣ ይግባኝ የሚባልበትን ሌላ ውሳኔ የሚመለከት ከሆነ ኮሚሽኑ ውሳኔውን ሊያፀናው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ወይም ኮሚሽኑ በሚሰጠው መመሪያ እንደገና እንዲመለከተው ለባለሥልጣኑ መልሶ ሊልከው ይችላል፡፡

8. ኮሚሽኑ የውሳኔውን ግልባጭ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ይሰጣል፡፡
9. ኮሚሽኑ የሚሰጠው ውሳኔ ውሳኔው የተመሠረተባቸውን ምክንያቶች፣ መሠረታዊ በሆኑ የፍሬ ነገር ጉዳዮች ምርመራ የተገኘውን ውጤት እና ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ማስረጃ ወይም ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ሌላ ነገር ማካተት አለበት፡፡
10. ኮሚሽኑ በቀረበለት ይግባኝ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ወይም ኮሚሽኑ በውሳኔ ማስታወቂያው ከተገለጸው ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
11. ኮሚሽኑ ይግባኙን ላቀረበው ታክስ ከፋይ የወሰነለት እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ ይህንን ውሳኔ ለማስፈጽም የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ መስጠትንም ጨምሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው 30 (ሠላሳ) ቀናት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

92. <u>ኮሚሽኑን ስለማስተዳደር</u>

1. የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት የኮሚሽኑን አስተዳደራዊ ጉዳዮች በኃላፊነት ይመራል፡፡
2. ኮሚሽኑ ሬጅስትራር እና ፕሬዚዳንቱ በሚወስነው መሠረት ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡
3. የኮሚሽኑ ሬጅስትራር ፕሬዚዳንቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተሰጠው ኃላፊነት የፕሬዚዳንቱ ረዳት በመሆን አስፈላጊ ወይም ተገቢ የሆኑ ተግባራት ያከናውናል እንዲሁም ፕሬዚዳንቱን በመወከል የኮሚሽኑን አስተዳደራዊ ጉዳዮች ይፈጽማል፡፡

93. <u>ፋይናንስ</u>

1. የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል፡፡
2. ኮሚሽኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
3. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች የገንዘብ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር ኦዲት ይደረጋሉ፡፡

94. <u>የኮሚሽኑ ዓመታዊ ሪፖርት</u>

1. የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት ለእያንዳንዱ የበጀት ዓመት የኮሚሽኑን ጉዳዮች የሚመለከት ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለበጀት ዓመቱ የተዘጋጀው ሪፖርት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይቀርባል፡፡

## ክፍል አሥራ አራት

## ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

### 95.የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1. ማንኛውም የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ግለሰብ፣ የሽርክና ማህበር ወይም ኩባንያ የታክስ ወኪል ፈቃድ እንዲሰጠው የፀደቀ ቅጽ በመጠቀም ለባለሥልጣኑ ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. ለዚህ ክፍል ዓላማ "የታክስ ወኪልነት አገልግሎት" ማለት፡-

ሀ/ ታክስ ከፋዩን በመወከል የታክስ ማስታወቂያ ማዘጋጀት፤

ለ/ ታክስ ከፋዩን በመወከል የቅሬታ ማስታወቂያ ማዘጋጀት፤

ሐ/ የታክስ ሕጎችን አፈጻጸም በተመለከተ ለታክስ ከፋዮች ምክር መስጠት፤

መ/ ከባለሥልጣኑ ጋር ለሚኖራቸው ጉዳዮች ታክስ ከፋዮችን መወከል፤

ሠ/ ታክስ ከፋዮችን በመወከል ከባለሥልጣኑ ጋር ማንኛውንም ሌላ የሥራ ግንኙነት ማድረግ፡፡

### 96.ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 95 መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ ግለሰብ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ ሰው መሆኑን ሲያረጋግጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 95 መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ የሽርክና ማህበር፡-

ሀ/ በሽርክና ማህበሩ ውስጥ ያለ አባል ወይም ተቀጣሪ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን፤ እና

ለ/ እያንዳንዱ የሽርክና ማህበር አባል መልካም ጠባይና ሥነ-ምግባር ያለው መሆኑ ሲያረጋግጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

3. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 95 መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ ኩባንያ፡-

ሀ/ የኩባንያው ተቀጣሪ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን ፤ እና

ለ/ የኩባንያው እያንዳንዱ ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሌላ ስለ አስፈጻሚ ባለሥልጣን መልካም ጠባይና ሥነ-ምግባር ያለው መሆኑን፤ ሲያረጋግጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

4. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣው ደንብ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያመለክት ሰው ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን ለመወሰን የሚረዱ ጠቋሚ መሥፈርቶችን ይደነግጋል፡፡
5. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 95 ለተጠቀሰው አመልካች ውሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
6. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ዓመታት የሚጸና ሲሆን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 97 መሠረት ሊታደስ ይችላል፡፡
7. ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሰጣቸውን ሰዎች ዝርዝር አመቺ ሆኖ ባገኘው መንገድ በየጊዜው ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡
8. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሙያ ፈቃድ በመሆኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው የንግድ ሥራ ፈቃድ ተሰጥቶት እንደሆነ ሥራውን የሚሠራው በታክስ ወኪልነት ብቻ ይሆናል፡፡

97.<u>የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ስለማደስ</u>

1. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ እንዲታደስለት ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ/ በጸደቀው ቅጽ መሠረት፤ እና

ለ/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ ባበቃ በ21 (በሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ከዚህ በዘገየ ጊዜ ውስጥ፤ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ እስከቀጠለ ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፈቃዱ እንዲታደስለት ያመለከተን ሰው የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ባለሥልጣኑ ያድስለታል፡፡

4. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከታደሰበት ቀን ጀምሮ ለሦስት ዓመታት የሚፀና ሲሆን፣ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለተጨማሪ ጊዜያት ሊታደስ ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃዱ እንዲታደስለት ለጠየቀ አመልካች በማመልከቻው ላይ ስለተሰጠው ውሳኔ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

98.<u>የታክስ ወኪልነት አገልግሎቶች ላይ ስለሚኖር ገደብ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከተሰጠው ሰው በስተቀር ማንም ሰው በክፍያ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በአንቀጽ 95 (2) (ሀ) ለታክስ ወኪልነት አገልግሎት በተሰጠው ትርጉም ከተካተቱት አገልግሎቶች ውጪ በመደበኛ የሙያ አገልግሎቱ ሂደት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በሚሰጥ የጥብቅና ፈቃድ ያለው ሰው ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

99.<u>የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ስለመሰረዝ</u>

1. የታክስ ወኪልነት ሥራውን ለማቋረጥ የፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሥራውን ከማቋረጡ በፊት በ7 (በሰባት) ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለዘለቄታው በታክስ ወኪልነት መሥራት ካልፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃዱ እንዲሰረዝለት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማመልከት ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መሰረዝ አለበት፦

ሀ/ የታክስ ወኪሉ ባለሥልጣኑን በሚያሳምን ሁኔታ ይህ ሊሆን የቻለው በእርሱ ፈቃድ ወይም ቸልተኝነት ምክንያት አለመሆኑን ካላረጋገጠ በስተቀር ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ተዘጋጅቶ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ በማንኛውም መሠረታዊ ጉዳይ ሀሰት ሆኖ ሲገኝ፤

ለ/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱን ለማግኘት የሚጠየቁ የሚያስፈልጉ የብቃት መስፈርቶችን ይዞ መቀጠል ሳይችል የቀረ እንደሆነ ወይም ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪሉ ሙያዊ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን፤

ሐ/ የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ሥራውን መሥራት ሲያቆም፣ እንዲሁም የታክስ ወኪሉ ኩባንያ ወይም የሽርክና ማህበር ሲሆን የኩባንያው ወይም የሽርክና ማህበሩ ህልውና ሲያከትም፤

መ/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ እንዲሠረዝለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማመልከቻ ሲያቀርብ፤

ሠ/ የታክስ ወኪሉ የፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ሲያበቃ እና የታክስ ወኪሉ ፈቃዱ እንዲታደስለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 97 መሠረት ማመልከቻ ሳያቀርብ ሲቀር፡፡

4. ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪሉ ፈቃድ የተሠረዘ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ወኪሉ መስጠት አለበት፡፡

5. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መሠረዝ የሚፀናው፡-

ሀ/ የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ሥራውን መሥራት ካቆመበት ቀን፤ ወይም

ለ/ ፈቃዱ የተሰረዘ መሆኑን የሚገልፀው ማስታወቂያ ለታክስ ወኪሉ ከተሰጠ ከ60 (ከስልሳ) ቀናት በኋላ፤ ከሁለቱ ቀድሞ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

6. በሌላ ማንኛውም የታክስ ሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሙያዊ የሥነ-ምግባር ጥሰት ፈፅሟል ብሎ ሲያምን ይህንን የሥነ-ምግባር ጥሰት፡-

ሀ/ ለኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት፣ ለኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም እንደአግባብነቱ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የሂሣብ ባለሙያነት፣ የኦዲተርነት ወይም የሕግ ባለሙያነት ፈቃድ ለሰጠው ሌላ አካል፤ እና

ለ/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ኃላፊነት ላለው ባለሥልጣን፤ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል አሥራ አምስት</u>

## <u>አስተዳደራዊ፣ የወንጀል ቅጣቶች እና ሽልማቶች</u>

## <u>ምዕራፍ አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

100. <u>አስተዳደራዊ ቅጣቶችንና የወንጀል ኃላፊነቶችን የሚመለከቱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. አንድን ድርጊት መፈጸም ወይም አለመፈጸም አስተዳደራዊ ቅጣት እና የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ጥፋቱን የፈጸመው ሰው አስተዳደራዊ ቅጣት መቀጣቱ የወንጀል ተጠያቂነቱን አያስቀርም፡፡
2. ማንኛውም ታክስ ከፋይ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት እና/ወይም የወንጀል ክስ የቀረበበት መሆኑ መክፈል የሚገባውን ታክስ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## አስተዳደራዊ ቅጣቶች

### 101. ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች

1. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንደጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ለምዝገባ እስካመለከተበት ወይም በባለሥልጣኑ አነሳሽነት እስከ ተመዘገበበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ መክፈል ያለበትን ታክስ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ቅጣት ይከፍላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ታክስ ከፋይ የሚከፍለው ታክስ የሌለ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ተመዘገበበት ቀን ድረስ ላለው ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነ ጊዜ ብር 1000 (አንድ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣለው ቅጣት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከሚጣለው ቅጣት ያነሰ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም ሰው ያለ በቂ ምክንያት ምዝገባ እንዲሰረዝለት ያላመለከተ እንደሆነ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ማመልከት ከነበረበት ቀን ጀምሮ ምዝገባው እንዲሰረዝ እስካመለከተበት ቀን ወይም በባለሥልጣኑ አነሳሽነት ምዝገባው እስከተሠረዘበት ቀን ድረስ ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነ ጊዜ ብር 1000 (አንድ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

### 102. ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በታክስ ሕግ መሠረት መያዝ የሚጠበቅበትን ማንኛውንም ሰነድ ያልያዘ ታክስ ከፋይ በታክስ ሕጉ መሠረት ሰነዱ

መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል ያለበትን ታክስ 20% (ሃያ በመቶ) ቅጣት ይከፍላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሰነድ መያዝ ሲኖርበት ያልያዘ ታክስ ከፋይ ሰነዱን መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል የሚኖርበት ታክስ የሌለ እንደሆነ፦

ሀ/ ለገቢ ግብር ሲሆን ታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት ለእያንዳንዱ የታክስ ዘመን ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር)፤ ወይም

ለ/ ለሌላ ማንኛውም ታክስ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት የታክስ ዘመን ብር 2000 (ሁለትሺ ብር)፤ ቅጣት ይከፍላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣለው ቅጣት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከሚጣለው ቅጣት ያነሰ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ከሁለት ዓመት በላይ የሂሣብ ሰነድ ካልያዘ ለታክስ ከፋዩ የንግድ ፈቃድ የሰጠው አካል ከባለሥልጣኑ በሚቀርብለት ማስታወቂያ መሠረት የታክስ ከፋዩን የንግድ ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 (2) ለተወሰነው ጊዜ ድረስ ሰነዶችን ይዞ ሳያቆይ የቀረ የደረጃ 'ሀ' ታክስ ከፋይ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

6. ፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 33 (4) ለተወሰነው ጊዜ ድረስ ሰነዶችን ይዞ ሳያቆይ የቀረ የደረጃ 'ለ' ታክስ ከፋይ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

### 103. ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣት

1. የታክስ ሕግ በሚደነግገው መሠረት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን በታክስ ደረሰኝ፣ በታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ፣ በታክስ ማስታወቂያ፣ ወይም በሌላ በማንኛውም ሰነድ ላይ ሳይገልጽ የቀረ ታክስ ከፋይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ባልተገለጸበት በእያንዳንዱ ሰነድ ብር 3ሺ (ሦስት ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 (6) ተፈጻሚ ከሚሆንበት ሁኔታ በስተቀር፣ ማንኛውም ታክስ ከፋይ፦

ሀ/ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የሌላ ሰው ታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተጠቀመ እንደሆነ፤ብር 10,000 (አስር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) ወይም (ለ) በተጠቀሱት ድርጊቶች ምክንያት ታክስ ከፋዩ ወይም ሌላ ሰው ያገኘው የገንዘብ ጥቅም ከብር 10,000 (አስር ሺ ብር) የሚበልጥ ከሆነ የሚከፍለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ካገኘው ጥቅም ጋር እኩል ይሆናል፡፡

104. <u>የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት</u>

1. በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ ያልተከፈለውን ታክስ 5% (አምስት በመቶ) 25% (ሃያ አምስት በመቶ) እስኪሞላ ድረስ ቅጣት ይከፍላል፡፡
2. ለመጀመሪያው የሂሣብ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚከፍለው ቅጣት ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) አይበልጥም፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ያልተከፈለ ታክስ ነው የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክሱ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡
4. በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው ቅጣት ቀጥለው ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም፦

ሀ/ ብር 10,000 (አሥር ሺ ብር)፤

ለ/ በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100% (መቶ በመቶ)፡፡

5. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው ሊከፍል የሚገባው ታክስ የሌለ እንደሆነ፣ የታክስ ማስታወቂያ ሳያቀርብ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ብር 10,000 (አሥር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

105. <u>ታክስን ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት</u>

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ መክፈያ ጊዜው ውስጥ ታክስ ሳይከፍል ከቀረ ለዘገየበት ጊዜ፦

ሀ/ ለአንድ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ ባልተከፈለው ታክስ ላይ 5% (አምስት በመቶ)፣ እና

ለ/ ከዚያ በኋላ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ ባልተከፈለው ታክስ ላይ ተጨማሪ 2% (ሁለት በመቶ)፣ ቅጣት ይከፈላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣለው የቅጣት መጠን ከዋናው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም፡፡
3. መከፈል በማይገባው ታክስ ላይ ሳይከፈል በዘገየበት የተጣለ ቅጣት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 (4) መሠረት ለታክስ ከፋዩ ይመለሳል፡፡
4. ይህ አንቀጽ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 106 በሚመለከተው ያልተከፈለ ታክስ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

106. <u>ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት</u>

1. በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለባለሥልጣኑ ማስተላለፍ ያለበት ማንኛውም ሰው ሳይቀንስ የቀረው ወይም ቀንሶ ለባለሥልጣኑ ያላስተላለፈውን ታክስ 10% (አሥር በመቶ) ቅጣት ይከፍላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለድርጅት ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ታክስ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ሌላ የድርጅቱ ሠራተኛ እያንዳንዳቸው ብር 2000 (ሁለት ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላሉ፡፡
3. የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92 ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ አቅራቢውና ገዥው እያንዳንዳቸው ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላሉ፡፡
4. በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92 መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈልን ታክስ ለማስቀረት በማሰብ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ላለበት ሰው ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ብር 10,000 (አሥር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

107. <u>ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች</u>

1. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሰው ሳይመዘገብ የቀረ እንደሆነ፣ መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለመመዝገብ እስካመለከተበት ቀን ወይም በባለሥልጣኑ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ ላለው ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ ብር 2000 (ሁለት ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ፣ ንዑስ አንቀጹ ተፈጻሚ የሚሆንበት ሰው መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለመመዝገ እስካመለከተበት ቀን ወይም በባለሥልጣኑ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በፈጸመው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ 100% (መቶ በመቶ) ቅጣት ይከፍላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚጣል ቅጣት በንዑስ አንቀጹ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ በፈጸመው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አያስቀርም፡፡ ሆኖም ታክስ ከፋዩ በዚህ ጊዜ ውስጥ ባከናወነው ግብይት ላይ የከፈለው የተርን ኦቨር ታክስ ካለ ሊከፍል ከሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡
4. ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ በግብይቱ ላይ መከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማሳነስ ወይም በግብይቱ ላይ ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን ለመጨመር በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ እንደሆነ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

108. <u>የታክስ ደረሰኝ አለመስጠት</u>

ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥ ባልሰጠው በእያንዳንዱ ደረሰኝ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይቀጣል፡፡

109. <u>ታክስን አሳንሶ ማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት</u>

1. በታክስ ማስታወቂያ የተገለጸው የታክስ መጠን ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ትክክለኛ የታክስ መጠን ያነሰ እንደሆነ (ልዩነቱ "የታክስ ጉድለት" ተብሎ የሚገለጽ) የታክስ ጉድለቱን መጠን 10% (አሥር በመቶ) ቅጣት ይከፍላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በታክስ ከፋዩ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የቅጣቱ መጠን ወደ 30% (ሰላሳ በመቶ) ከፍ ይላል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በታክስ ከፋዩ ላይ ለሦስተኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የቅጣቱ መጠን ወደ 40% (አርባ በመቶ) ከፍ ይላል፡፡
4. የታክስ ጉድለቱ የተፈጠረው ታክስ ከፋዩ የራሱን ታክስ አስልቶ የታክስ ማስታወቂያ ከማቅረቡ በፊት ሚኒስቴሩ ማብራሪያ ባልሰጠበት አከራካሪ በሆነ የታክስ ሕግ ድንጋጌ ላይ በያዘው ምክንያታዊ አቋም ላይ የተመሠረተ ሆኖ ከተገኘ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣል ቅጣት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

110. <u>ታክስን በመሸሸ የሚጣል ቅጣት</u>

ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋይን የታክስ ስሌት ሲሠራ ከታክስ መሸሽን የሚከላከል ድንጋጌ ተፈጻሚ ካደረገ ታክስ ከፋዩ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ ባይደረግ ኖሮ ከታክስ በመሸሸ ሊያስቀር ይችል የነበረውን የታክስ መጠን እጥፍ ቅጣት ይከፍላል፡፡

111. <u>የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓትን አለመከተል የሚያስከትለው ቅጣት</u>

1. በታክስ ሕግ መሠረት ባለሥልጣኑ የታክስ ማስታወቂያውን ወይም የታክስ ክፍያውን በኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓት መሠረት እንዲፈጽም የጠየቀው ታክስ ከፋይ በዚሁ ሥርዓት መሠረት ሳይፈጽም ቢቀር ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ሥርዓቱን ያልተከተለበትን ምክንያት እንዲገልጽ በጽሑፍ መጠየቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ የታክስ ማስታወቂያውን ወይም የታክስ ክፍያውን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ላለመፈጸሙ ማስታወቂያው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 14 (አሥራ አራት) ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ማቅረብ ካልቻለ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

112. <u>በታክስ ወኪል ላይ ስለሚጣል ቅጣት</u>

የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው፦

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 መሠረት ለደንበኛው የምስክር ወረቀት ወይም መግለጫ ካልሰጠ፤ ወይም
2. ለደንበኞች የተሰጡ የምስክር ወረቀቶችንና መግለጫዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 (4) ለተወሰነው ጊዜ ካልያዘ፤ ወይም

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 99 (1) መሠረት የታክስ ወኪልነት ሥራውን ማቆሙን ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ፣ ብር 10,000 (አሥር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

113. **ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ጋር ተያይዞ የሚጣል ቅጣት**

1. ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፦

ሀ/ ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር ሲጠቀም ከተደረሰበት ለተጠቀመበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ለ/ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ወይም በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ሐ/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊስካል ማስታወሻ እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

መ/ የታክስ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናክል የፈጠረ ወይም በመሣሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ያላደረገ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ሠ/ በንግድ ሥራው ለሚጠቀምበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የምርመራ መዝገብ ከመሣሪያው ጎን እንዲቀመጥ ካላደረገ ወይም ሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የተመዘገቡ ዕቃዎች ተመላሽ መደረጋቸው ወይም ደንበኛው የተመላሽ ጥያቄ ማቅረቡ በተመላሽ መዝገብ ላይ በትክክል መመዝገቡ ሳይረጋገጥ የተመላሽ ደረሰኝ ከሰጠ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ረ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በስርቆት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ በሦስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ብልሽት ባጋጠመው በአራት ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉ እና ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር10,000 (አሥር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ሰ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚቀመጥበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ሸ/ የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ሲያደርግ ወይም የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ሲሆን ከሦስት ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉ እና ለባለሥልጣኑ ያላሳወቀ እንደሆነ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

ቀ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ጥቅም ላይ በሚውልበት የንግድ ሥራ ቦታው፡-

1) የተጠቃሚውን ስም፣ የንግድ ስም፣ የንግዱ ሥራ የሚካሄድበትን አድራሻ፣ የታክስ ከፋዩን መለያ ቁጥር፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን የዕውቅና እና መጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፤

2) "የሽያጭ ሠራተኞች መሣሪያው የተበላሸ ከሆነ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኞች የመስጠት ግዴታ አለባቸው" የሚል ማስታወቂያ፤ እና

3) "ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ" የሚልጽሑፍ ያለበት ማስታወቂያ፤

4) በግልጽና በሚታይ ቦታ ለጥፎ ካልተገኘ ብር 10,000 (አሥር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

ተ/ ሥራ ላይ የዋለውን የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር የባለሥልጣኑ ዕውቅና ባልተሰጠው ሰው እንዲቀየር ወይም እንዲሻሻል ካደረገ ብር 30,000 (ሰላሣ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

2. ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅና እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

ሀ/ የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ለ/ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ሐ/ ለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምዝገባ ከባለሥልጣኑ የመሣሪያ መለያ ቁጥር ካልወሰደ ወይም የወሰደውን የመሣሪያ መለያ ቁጥር ለእይታ በሚያመች ቦታ በመሣሪያው ላይ ካለጠፈ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

መ/ በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውንም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላሳወቀ ወይም ስለመሣሪያው የአጠቃቀም

መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ሠ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመሠረቃቸው ወይም ሊጠገኑ በማይቻልበት ሁኔታ በአደጋ ምክንያት ብልሽት የደረሰባቸው መሆኑን አስታውቀው እንዲተኩላቸው ለሚጠይቁ አገልግሎት ማዕከላት በሦስት ቀናት ውስጥ ለማቅረብ አለመቻሉን ለባለሥልጣኑ አስቀድሞ ካላሳወቀ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ረ/ ውል ስለተዋዋላቸው አገልግሎት ማዕከላት መረጃ ካልያዘ ወይም ውላቸውን ስላቋረጡ ወይም አዲስ ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት ለባለ ሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

3. ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል፦

ሀ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፊስካል ማስታወሻ በተተካ በሁለት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ለ/ ውል የገባባቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ካላደረገ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፤

ሐ/ አቅራቢው ዕውቅና ሳይሰጠው እና በባለሥልጣኑ ሳይመዘገብ በሥራ ላሠማራው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

114. <u>ልዩ ልዩ ቅጣቶች</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት ማንኛውንም ለውጥ ያላሳወቀ ታክስ ከፋይ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 62 መሠረት የመመስረቻ ጽሑፉን፣ መተዳደሪያ ደንቡን፣ የሽርክና ስምምነቱን፣ ወይም ሌላ የመመስረቻ ወይም የምዝገባ ሰነድ ወይም በእነዚህ ሰነዶች ላይ የተደረገውን ማንኛውም ማሻሻያ ሳያቀርብ የቀረ ድርጅት ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር 10,000 (አሥር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 63 በተደነገገው መሠረት የኦዲት ሪፖርቱን ለባለሥልጣኑ ያላቀረበ ማንኛውም ኦዲተር ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር 10,000 (አሥር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የሚጣለው ቅጣት የኦዲተሩን ፈቃድ አስመልክቶ በኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ከሚወስደው እርምጃ በተጨማሪ ይሆናል፡፡
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 64 መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የተደረገን ውል ለባለሥልጣኑ ያላሳወቀ ሰው ይህንኑ ሳያሳውቅ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ቀን ብር 1,000 (አንድ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡
6. ፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 79 መሠረት ግንኙነት ካለው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር ጉዳይ ለባለሥልጣኑ ያልገለጸ ሰው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡
7. ማናቸውም መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ባለስልጣኑ የሚጠይቀውን መረጃ ለባለሥልጣኑ ያልሰጠ እንደሆነ እንደሁኔታው መረጃውን ያልሰጠው ሰው ወይም መረጃ የተጠየቀው መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

115. <u>ስለአስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን</u>

1. ባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ ቅጣት ለወሰነበት ሰው የቅጣት ውሳኔ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡፡
2. አንድ ድርጊት ወይም አለማድረግ የሚያስከትለው አስተዳደራዊ ቅጣት በአንድ ታክስ ብቻ ያልተወሰነ ሲሆን እያንዳንዱ ቅጣት ለየብቻው ከተወሰነ በኋላ ሁሉም ቅጣቶች ተጠቃለው ይጣላሉ፡፡
3. አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰነበት ሰው ቅጣቱ እንዲነሳለት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማመልከት የሚችል ሲሆን ቅጣቱን እንዲነሳለት የጠየቀበትን ምክንያት በማመልከቻው መግለጽ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ወይም በራሱ አነሳሽነት በአንድ ሰው ላይ የተጣለን ቅጣት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ እንዲነሳ ውሳኔ የሰጠበትን የእያንዳንዱን አስተዳደራዊ ቅጣት መዝገብ መያዝ እና በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የታክስ ወንጀሎች

### 116. የታክስ ወንጀል ጉዳዮች የሚታዩበት ሥነ-ሥርዓት

1. በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የኢትዮጵያን የወንጀል ሕግ በመተላለፍ የሚፈፀሙ በመሆናቸው ክሱ የሚመሰረተው፣ የሚታየውና ይግባኝም የሚቀርበው በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡
2. የተለያዩ የታክስ ሕጎችን በመተላለፍ በዚህ ምዕራፍ ስር የተደነገገ ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ እያንዳንዱን የታክስ ሕግ በመተላለፍ እንደተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ተቆጥሮ ለእያንዳንዱ ድርጊት በአንቀጾቹ ላይ የተመለከቱትን ቅጣት ይቀጣል፡፡

### 117. ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኙ ወንጀሎች

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ከአንድ በላይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የወሰደ ወይም ለመውሰድ የሞከረ እንደሆነ፤

ለ/ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ፤ ወይም

ሐ/ የሌላን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተጠቀመ እንደሆነ፤ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) ታክስ ከፋዩ ለወሰደው ወይም ለመውሰድ ለሞከረው ለእያንዳንዱ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በተናጠል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
3. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ ጥቅም ላይ የዋለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 (6) በተገለጹት ሁኔታዎች የሆነ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) እና (ሐ) ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

### 118. የሀሰት ወይም አሳሳች መግለጫዎች እና የተጭበረበሩ ሰነዶች

1. ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት፡-

ሀ/ ለባለሥልጣኑ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ፤ ወይም

ለ/ ለባለሥልጣኑ ሊቀርብ የሚገባን መግለጫ አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነገሮች ያለበቂ ምክንያት ያስቀረ እንደሆነ፤

ሐ/ ለባለሥልጣኑ የተጭበረበሩ ሰነዶችን ያቀረበ እንደሆነ፤ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሦስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. አንድ ሰው ለባለሥልጣኑ ሊያስተላልፈው እንደሚችል እያወቀ ወይም ማወቅ የሚያስችለው በቂ ምክንያት እያለው ለሌላ ሰው የሰጠው ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለባለሥልጣኑ እንደተሰጠ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ይቆጠራል፡፡
3. ማንኛውም ሰው ታክስን ለማጭበርበር በማሰብ በሕይወት በሌለ ሰው ወይም አድራሻው በማይታወቅ ሰው ወይም ውክልና ለመስጠት ወይም የንግድ ሥራ ለመሥራት የሕግ ችሎታ በሌለው ሰው ወይም ከንግድ ሥራው ውጤት ተጠቃሚ ባልሆነ ሰው ወይም በሌላ የፈጠራ ሰው ስም የንግድ ፈቃድ አውጥቶ በውክልና የንግድ ሥራ የሚሠራ እንደሆነ ከንግድ ሥራው ለሚጠየቀው ታክስ ኃላፊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በወንጀል ይቀጣል፡፡

## 119. <u>የተጭበረበሩ ወይም ሕገ-ወጥ የሆኑ ደረሰኞች</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠ ወይም ያሰራጨ፤ ወይም

ለ/ የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ ወይም ተመላሽ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን የተጠቀመ እንደሆነ፤ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን የተጭበረበሩ ደረሰኞች በመጠቀም የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ከብር 100,000 (ከአንድ መቶ ሺ ብር) የሚበልጥ እንደሆነ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣለው ቅጣት ከገንዘቡ ጥቅም ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል፡፡
3. ሀሰተኛ ደረሰኞችን ለመስራት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማተም የሚያገለግል ማሽን፣ መሳሪያ፣ ወይም ሶፍትዌር የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ፣ ወይም በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት ማሽኑን፣ መሳሪያውን፣ ሶፍትዌሩን ወይም የወንጀሉን ፍሬ መውረስን ያስከትላል፡፡
5. ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ፣ ወይም ሀሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሰው ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

120. <u>ከደረሰኝ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ ወንጀሎች</u>

1. ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺ ብር) እስከ ብር 5,000 (ሃምሳ ሺ ብር) የገንዘብ መቀጫ እና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
2. በአንድ ግብይት በተሰጡ ተመሳሳይ የደረሰኝ ኮፒዎች ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሽያጭ ዋጋን ያሳነሰ ማንኛውም ሰው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) እና ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
3. የሽያጩ ትክክለኛ ዋጋ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) የሚበልጥ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኞቹ ላይ ከተመለከቱት ከፍተኛው የገንዘብ መጠን እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
4. ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሰጠ ወይም የተቀበለ ሰው ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው ደረሰኝ ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ ብር) የሚበልጥ የገንዘብ መጠን የያዘ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኙ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደረስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
6. ባለሥልጣኑ ሳይፈቅድለት የታክስ ደረሰኝ ያተመ ሰው ከብር 300,000 (ሦስት መቶ ሺ ብር) እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሁለት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ወንጀሉን ለሁለተኛ ጊዜ ፈጽሞ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ የህትመት መሣሪያው እና የማተሚያ ድርጅቱ ይወረሳል፣ የንግድ ፈቃዱም ይሰረዛል፡፡

121. **<u>ሕገ-ወጥ የሆነ ተመላሽን ወይም ከተገቢው በላይ ማካካሻን መጠየቅ</u>**

1. ባለሥልጣኑን ለማጭበርበር በማሰብ ተመላሽ ወይም ማካካሻ የጠየቀ ሰው ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) እና ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣለው ቅጣት፣ ታክስ ከፋዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት ተመላሽ የተደረገለትን ታክስ መልሶ ከመክፈል ግዴታ ነጻ ሊያደርገው አይችልም፡፡

122. **<u>ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች</u>**

1. ለተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይመዘገብ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ ሰው ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
2. ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፤ ወይም

ለ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ከተፈቀደው ውጪ የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ የሰጠ እንደሆነ፤ ብር 10,000 (አሥር ሺ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና በአንድ ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

123. **<u>ከቴምብር ቀረጥ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች</u>**

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ በምስክርነት ካልሆነ በስተቀር የቴምብር ቀረጥ ሊከፈልበት ሲገባ የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለበትን ሰነድ ሥራ ላይ ያዋለ ወይም የፈረመ፤ ወይም

ለ/ የቴምብር ቀረጥ ላለመክፈል ወይም አነስተኛ የቴምብር ቀረጥ ለመክፈል በማሰብ የአንድን ሰነድ ትክክለኛ ባህሪይ ያልገለጸ ወይም የደበቀ እንደሆነ፤ ከብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺ ብር) እስከ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ቴምብሮችን ወይም ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ለመሸጥ የተፈቀደለት ሆኖ የቴምብር ቀረጥ አዋጁን ወይም ደንቡን የተላለፈ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ቴምብሮችን ወይም ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ሳይፈቀድለት የሸጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ፣ ከብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) እስከ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመታት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

124. <u>ታክስን ለማስከፈል ከሚወሰድ እርምጃ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች</u>

1. ማንኛውም የታክስ ከፋይ ንብረት ተረካቢ በታክስ ሕጎች በተደነገገው መሠረት የተጣለበትን ግዴታ ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ በብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና በአንድ ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 መሠረት የንብረት መያዝ ትዕዛዝ የደረሰው ሰው፦

ሀ/ ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የሸጠ፣ የለወጠ፣ ወይም በሌላ መንገድ ያስተላለፈ እንደሆነ፤

ለ/ ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የደበቀ፣ የሰበረ፣ ያበላሸ ወይም የጎዳ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የሚመለከት ማናቸውንም ሰነድ ያወደመ፣ የደበቀ፣ ያስወገደ፣ የጎዳ፣ የለወጠ፣ የሰረዘ፣ የደለዘ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፤

ከሁለት ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለሶስተኛ ወገን በሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ መሠረት የተጠየቀውን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ ያልከፈለ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡
4. ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የደረሰው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 (5) መሠረት ትዕዛዙን መፈጸም እንደማይችል ለባለሥልጣኑ ካሳወቀ፣ ባለሥልጣኑ የሰጠውን ትዕዛዝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 (6) መሠረት መሻሩን ወይም ማሻሻሉን ወይም ትዕዛዙ የደረሰው ሰው ያቀረበውን ማስታወቂያ ውድቅ ማድረጉን እስካላስታወቀው ድረስ ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የተሰጠው ሰው ትዕዛዙን እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

5. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ በደረሰው ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የተጠየቀውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም፡፡
6. ከሃገር የመውጣት ክልከላ ትዕዛዝን በመጣስ ከኢትዮጵያ የወጣ ወይም ለመውጣት የሞከረ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡
7. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 መሠረት የተላለፈን ትዕዛዝ ያላከበረ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በዚህ ምክንያት ባለስልጣኑ ሳይሰበስበው በቀረው የገንዘብ ልክ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው የፋይናንስ ተቋሙ ሥራ አስኪያጅ እያወቀ ወይም በቸልተኝነቱ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ሥራ አስኪያጁ ከሁለት ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡
9. ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይገኝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 መሠረት የእሽግ ትዕዛዝ የተላለፈበትን የንግድ ሥፍራ ወይም ቦታ እሽግ የከፈተ ወይም ያስወገደ ሰው ከሁለት ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

125. <u>ታክስን ስለመሰወር</u>

1. ማንኛውም ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ገቢውን የደበቀ፣ የታክስ ማስታወቂያውን ያላቀረበ ወይም ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
2. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ቀንሶ የያዘውን ታክስ ለባለሥልጣኑ ያላስተላለፈ ከሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

126. <u>የታክስ ሕጎችን አስተዳደር ስለማደናቀፍ</u>

1. በታክስ ሕጉ መሠረት ግዴታውን እየተወጣ ያለን የታክስ ሠራተኛ ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

2. የታክስ ሕግ አስተዳደርን ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ ማንኛውም ሰው ከብር 10,000 (አሥር ሺ ብር) በማያንስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ የሚከተሉት እና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች የማደናቀፍ ተግባራት ተደርገው ይወሰዳሉ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 65 መሠረት በሚሰጥ ማስታወቂያ መሠረት አለመፈጸምን ጨምሮ፣ ሰነዶችን ለመመርመር ከባለሥልጣኑ የሚቀርብ ጥያቄን አለመቀበል ወይም ሪፖርቶችን ወይም የታክስ ከፋዩን የታክስ ጉዳዮች የሚመለከት መረጃን ለማቅረብ ፈቃደኛ አለመሆን፣

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 65 መሠረት ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ በተሰጠው ማስታወቂያ መሠረት አለመፈጸም፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 66 መሠረት የባለሥልጣኑን ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ የወከለውን የታክስ ሠራተኛ ማንኛውንም መረጃ ወይም ማስረጃ ለማግኘት ያላቸውን መብት እንዳይጠቀሙ መከልከል፣

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 66 (4) መሠረት አስፈላጊውን እርዳታ ለመስጠት ወይም መገልገያ ለማቅረብ ፈቃደኛ አለመሆን፣

ሠ/ በባለሥልጣኑ ቢሮ ውስጥ ሁከት መፍጠር ወይም የታክስ ሠራተኞች የቅጥር ግዴታቸውን እንዳይወጡ ማደናቀፍ፡፡

### 127. <u>ስልጣን ሳይኖር ታክስ መሰብሰብ</u>

በማንኛውም የታክስ ሕግ ታክስ እንዲሰበስብ ሥልጣን ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ታክስ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ እንደሆነ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) እስከ ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

### 128. <u>በታክስ ወንጀል መርዳት ወይም ማበረታታት</u>

አንድ ሰው በታክስ ሕግ መሠረት የተደነገገን የታክስ ወንጀል “ዋና ወንጀል” አድራጊ ተብሎ የሚታወቅ ሌላ ሰው እንዲፈጽም የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያገዘ፣ ያነሳሳ ወይም የተመሳጠረ እንደሆነ በዋናው ወንጀል አድራጊ ላይ የተጣለውን ቅጣት ይቀጣል፡፡

### 129. <u>ከታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጋር የተያያዙ ወንጀሎች</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አባልነቱ ኃላፊነቱን በመፈጸም ላይ ያለን ሰው የሰደበ፤

ለ/ ፈቃድ ሳይኖረው የኮሚሽኑን የሥራ ሂደት ያቋረጠ፤

ሐ/ የኮሚሽኑን የሥራ ሂደት ለማወክ በማሰብ በኮሚሽኑ ግቢ ውስጥ ወይም ኮሚሽኑ ባለበት አካባቢ ረብሻ የፈጠረ ወይም በረብሻው የተሳተፈ፤ ወይም

መ/ በማናቸውም ሁኔታ የኮሚሽኑን ሥራ ያሰናከለ እንደሆነ፤ ከብር 500 (አምስት መቶ ብር) እስከ ብር 3,000 (ሦስት ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ወይም ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ በኮሚሽኑ ፊት እንዲቀርብ ወይም ለኮሚሽኑ ሰነድ እንዲያቀርብ ወይም መረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሲደርሰው ያለበቂ ምክንያት በመጥሪያው መሠረት ያልፈጸመ፤

ለ/ በኮሚሽኑ ፊት ያለምንም በቂ ምክንያት ቃለ-መሃላ ለመፈጸም ወይም እውነትን ለመመስከር ማረጋገጫ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፤

ሐ/ ኮሚሽኑ በሚያየው ጉዳይ ለቀረበለት ጥያቄ ያለ በቂ ምክንያት መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፤ ከብር 300 (ሦስት መቶ ብር) እስከ ብር 3,000 (ሦስት ሺ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም ሰው ለኮሚሽኑ እያወቀ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ማስረጃ የሰጠ እንደሆነ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) በማያንስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

### 130. <u>በታክስ ወኪሎች ስለሚፈፀም ወንጀል</u>

ማንኛውም ሰው የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ሳይሰጠው የዚህን አዋጅ አንቀጽ 98 በመተላለፍ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

### 131. <u>ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪዎች ጋር በተገናኘ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

1. ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፡-

ሀ/ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም ያልተመዘገበ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከተጠቀመ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

ለ/ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ወይም በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ፣ ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

ሐ/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የፊስካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊስካል ማስታወሻ እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ፣ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅና እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

ሀ/ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር ለገበያ ካዋለ፣ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

ለ/ በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚደረገውን ማናቸውንም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም በመሣሪያው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ፣ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም ሰው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ፈቃድ ሳይኖረው ማንኛውንም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር ለገበያ ያዋለ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

4. ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል አቅራቢው ዕውቅና ያልሰጠውን እና በባለሥልጣኑ ያልተመዘገበ ሠራተኛ በሥራ ላይ አሰማርቶ ከተገኘ በብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) የገንዘብ ቅጣት ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

5. ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ያለአገልግሎት ማዕከሉ እና ባለሥልጣኑ ዕውቅና ከፈታታ ወይም ከገጣጠመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሳይበላሽ ሆን ብሎ እሽጉን ካነሳ ወይም አካሉን ከቀየረ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ አድራጎቶች

ከፈጸመ ከብር 10,000 (አስር ሺ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

6. የታክስ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ደንብ እና መመሪያዎችን በመተላለፍ፡-

ሀ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፈታ ወይም የገጣጠመ ወይም የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ በሌለበት ሥራ ላይ እንዲውል የፈቀደ ወይም የመሣሪያውን መለያ ቁጥር የቀያየረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚው ወይም በአገልግሎት ማዕከሉ ወይም በሠራተኛው ወይም በአቅራቢው የተፈጸመን ማናቸውንም ሕገ-ወጥ ድርጊት እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በ24 (በሃያ አራት) ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ፤ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

132. <u>በድርጅቶች የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

1. የታክስ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈፀመበት ወቅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማንኛውም ሰው ወንጀሉን እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፡-

ሀ/ ወንጀሉ የተፈጸመው ሥራ አስኪያጁ ሳይፈቅድ ወይም ሳያውቅ ከሆነ፤ እና

ለ/ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያለና ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብለው የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ለማድረግ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ፤ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

133. <u>የታክስ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችን ስም ይፋ ስለማድረግ</u>

1. ባለሥልጣኑ በታክስ ወንጀል በመጨረሻ ፍርድ ቤት ውሳኔ ጥፋተኛ የተባሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ እንዲሁም በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን በየጊዜው ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይፋ የሚደረገው ዝርዝር የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ/ ጥፋተኛ የተባለውን ሰው ስም፣ ምስል እና አድራሻ፤

ለ/ ባለሥልጣኑ አግባብ ናቸው የሚላቸውን የወንጀሉን ዝርዝር ጉዳዮች፤

ሐ/ ወንጀሉ የተፈፀመበትን የታክስ ጊዜ ወይም ጊዜያት፤

መ/ ጥፋተኛ የተባለው ሰው በፈጸመው ወንጀል ምክንያት ያልከፈለውን የታክስ መጠን፤

ሠ/ ጥፋተኛ በተባለው ሰው ላይ የተጣለ የገንዘብ ቅጣት ካለ የቅጣቱንመጠን::

## ምዕራፍ አራት

## ሽልማቶች

### 134. የታክስ ስወራን በሚመለከት ለተሰጠ ተጨባጭ መረጃ የሚሰጥ ሽልማት

1. ማንኛውም ሰው በመደበቅ፣ አሳንሶ በማሳወቅ፣ በማጭበርበር ወይም በሌላ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚፈፀምን የታክስ ስወራ አስመልክቶ ሊረጋገጥ የሚችል ተጨባጭና የማያሻማ መረጃ ለባለሥልጣኑ የሰጠ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተሰወረውን ታክስ መጠን እስከ 20% (ሃያ በመቶ) በሽልማት መልክ ታክሱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ለዚህ ሰው ይሰጣል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፦

ሀ/ በታክስ ስወራው ተግባር ላይ ለተሳተፈ፤ ወይም

ለ/ የታክስ ስወራውን ማሳወቅ የመደበኛ ሥራው አካል ለሆነ ሰው፤ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰውን ሽልማት በተመለከተ ባለሥልጣኑ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

### 135. ለላቀ የሥራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት

1. ባለሥልጣኑ የላቀ የሥራ ክንውን ላስመዘገበ የታክስ ሠራተኛ እንዲሁም የታክስ ግዴታውን በዓርአያነት ለተወጣ ታክስ ከፋይ ሽልማት ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰውን ሽልማት በተመለከተ ሚኒስትሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል አሥራ ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 136. ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ትክክለኛ አፈጻፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2. ሚኒስትሩ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑትን መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

137. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተፈጸመ ድርጊት ወይም አለማድረግ ምክንያት በተሰጠ የታክስ ውሳኔ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፦

ሀ/ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ሊከፈል ሲገባ ባልተከፈለ ታክስ ላይ የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት በሥራ ላይ በነበሩት የታክስ ሕጎች መሠረት ፍጻሜ ያገኛል፤

ለ/ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተጀምሮ አዋጁ ከጸና በኋላ በግብር ይግባኝ ጉባኤ በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ እንዳልሆነ ተቆጥሮ በተጀመረበት ሁኔታ ይቀጥላል፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል እና የፌደራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እስከሚቋቋሙ ድረስ በስራ ላይ ያሉት የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴዎች እና የግብር ይግባኝ ጉባኤ ስራቸውን እንደተለመደው በማካሄድ ይቀጥላሉ፤

መ/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ማመልከቻ እና ይግባኝ የማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ ከሆነ፣ በዚህ አዋጅ ረጅም ጊዜ በመሰጠቱ ምክንያት ብቻ ማመልከቻው እና ይግባኙ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊቀርብ ይችላል የሚል ትርጉም ሊያሰጥ አይችልም፡፡

3. ይህ አዋጅ በፀናበት ዕለት የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት ያልተቋቋመ እንደሆነ ኢንስቲትዩቱ እስኪቋቋም ድረስ በዚህ አዋጅ ኢንስቲትዩቱን የሚጠቅስ ማንኛውም አንቀጽ ለዚህ አዋጅ ዓላማ የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን የሚመለከት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
4. ለዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 አፈጻጸም ሲባል፣ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ሌላ ደንብ እስኪተካ ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

138. <u>ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ድንጋጌዎች</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 137 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ድንጋጌ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

139. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ቀን**</u>

1. ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የዚህ አዋጅ ክፍል አሥራ አንድ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ሚኒስቴሩ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ በሚያወጣው ማስታወቂያ ከተገለጸው ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የዚህ አዋጅ ክፍል አሥራ አራት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ባለሥልጣኑ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ በሚያወጣው ማስታወቂያ ከተገለጸው ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 10 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

## ደንብ ቁጥር 407/2009

## ስለ ፌደራል የታክስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 136 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ “የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

   1. “አዋጅ” ማለት የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፤
   2. “የተሻረውአዋጅ” ማለትየገቢግብርአዋጅ ቁጥር 286/1994 እንደተሻሻለ)፣ የማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 53/1985 ከነማሻሻያዎቹ እና የነዳጅ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 296/1978 ከነማሻሻያዎቹ ናቸው፡፡
   3. በዚህ ደንብ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጎች እንደአግባብነታቸው በአዋጁ ወይም በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የታክስ ሕጎችን ስለማስተዳደር

3. **ሚስጥራዊ መረጃ ስለመስጠት**

   የአዋጁ አንቀጽ 8 (2) እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ሚስጥራዊ ሰነድ ወይም መረጃ ሊሰጥ የሚችለው ጥያቄው በጽሑፍ ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም እሱንለሚወክለው ሰው ሲቀርብ እና ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ምዝገባ

**4. የማንነት የሰነድ ማስረጃ**

1. ማንኛውም ግለሰብ ከሚያቀርበው የምዝገባ ማመልከቻ ጋር ከሚከተሉት አንዱን የማንነት የሰነድ ማስረጃ አያይዞዝ ማቅረብ አለበት፦
   ሀ) ወቅታዊ የግለሰቡ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ፓስፖርት ገፅ የተረጋገጠ ቅጂ፤ ወይም
   ለ) የግለሰቡ ወቅታዊ የኢትዮጵያ የመንጃ ፈቃድ መየተረጋገጠ ቅጂ፤ወይም
   ሐ)የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ የሌላ ሀገር የመንጃ ፈቃድ ገጽ የተረጋጠ ቅጂ፤ ወይም
   መ) የግለሰቡየተረጋገጠየልደትየምስክርወረቀት ቅጂ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ባለስልጣኑ አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ሌላ ማንኛውም ማስረጃ እንዲያቀርብለት አመልካቹን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. በኩባንያ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ኩባንያው የተቋቋመበትን ወይም የተመዘገበበትን የምስክር ወረቀት ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
4. በሽርክና ማህበር የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከሽርክና ማህበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
5. በሌላ ማንኛውም ድርጅት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከድርጅቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ማንኛውም የመመስረቻ ወይም ማቋቋሚያ ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

**5. የማንነት አካላዊ መረጃ**

1. ለግለሰብ ምዝገባ ዓላማ ባለሥልጣኑ፡-
   ሀ)የግለሰቡን ትክክለኛ ማንነት ለማረጋገጥ፤ ወይም
   ለ) የማንነት ስርቆትን ወይም ማጭበርበርን ለመከላከል ፣ አመልካቹን ግለሰብ የማንነት አካላዊ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ከግለሰብ ጋር በተገናኘ “የማንነት አካላዊ መረጃ” ማለት የግለሰቡን ማንነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል የግለሰብ ማንነት መለያ አካላዊ መረጃ ሲሆን የሚከተሉትንይጨምራል፦
   ሀ) የፊት ገጽታ መለያ፤
   ለ) የጣት አሻራ መለያ፤
   ሐ) የድምፅ መለያ፤
   መ) የዓይን ክፍሎች (ምጣኔ ብርሃን ወይም መቅረፀ ምስል) መለያ፡፡

## ክፍል አራት

## የታክስ እንደራሴዎች

6. **ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ**
   1. ለአዋጁ አፈፃፀም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 4(4) መሠረት በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ‘ወኪል’ ተብሎ በሚጠራ ሰው አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያከናውነው የንግድ ሥራ ወኪሉ ነዋሪ ያልሆነው ሰው የታክስ እንደራሴ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንደታክስ እንደራሴ የሚቆጠር ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወኪል በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ ፩(፴) መሠረት ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ ከሆነ ሌላ ማንኛውም ሰው ተጨማሪ እንደተሰየመ የታክስ እንደራሴ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል አምስት

## የከባድ ችግር ሁኔታዎች

7. **የታክስ ምህረት ገደብ**

   ሚኒስትሩ በአዋጁ አንቀጽ 51 መሠረት የሚሰጠው የታክስ እና የዘገየ ክፍያ ወለድ ምህረት የገንዘብ ጣሪያ 10 ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን) ብር ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ማስታወቂያዎች እና የታክስ ክፍያ

8. **የሰነዶች አቀራረብ እና የታክስ አከፋፈል ሥርዓት**

   በአዋጁወይምበዚህደንብበሌላሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ሰው ታክስ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ በሚከተለው አኳኋን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ እና ታክስ መክፈል አለበት፦

1. የአዋጁ አንቀጽ 82(2) ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በማስተላለፍ ወይም የአዋጁን አንቀጽ መሠረት አድርጎ ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን መመሪያ በመከተል ክፍያ መፈጸም፤ ወይም
2. በሌላ ማንኛውም ሁኔታ በአካል በማቅረብ ወይም በፖስታ ለባለሥልጣኑ በመላክ፡፡

**ክፍል ሰባት**

**የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን**

**ምዕራፍ አንድ**

**ኮሚሽኑ በይግባኝ ሰሚ ሂደት ያለው ሥልጣን**

9. **የኮሚሽኑ ሥልጣን**

1. ኮሚሽኑ፦
   ሀ) ማስረጃ በቃለ መሃላ ወይም በማረጋገጫ መቀበል፤
   ለ) የዚህ ደንብ አንቀጽ 11(2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ስለስሚ ሂደቱ ማስታወቂያ በአግባቡ ደርሶት ያልቀረበ ወገን በሌለበት የስሚ ሂደቱን መቀጠል፤ ወይም
   ሐ) የስሚ ሂደቱን በቀጠሮ ማስተላለፍ፤ ይችላል፡፡
2. የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
3. በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት እንደምስክር ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ የደረሰው ሰው በኮሚሽኑ መመሪያ መሠረት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለተጠራ ምስክር የሚከፈለው ያህል የውሎ አበል ክፍያ ይፈፀምለታል፡፡

**ምዕራፍሁለት**

**የኮሚሽኑ ውሳኔ**

10. **የይግባኝ ማመልከቻ ስለማቋረጥ ፣ ስለመዝጋት ወይም እንደገና ስለማየት**

1. ማንኛውም ይግባኝ ባይ ለኮሚሽኑ ያቀረበውን ይግባኝ በማናቸውም ጊዜ ለኮሚሽኑ ሬጅስትራር የጽሑፍ ማስታወቂያ በማቅረብ ማቋረጥ ወይም መተው የሚችል ሲሆን፣ ኮሚሽኑም ይህ በሚሆንበት ጊዜ ይግባኙን ይዘጋል፡፡

2. የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት በአካል ወይም በወኪሉ አማካኝነት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ኮሚሽኑ ይግባኙን መዝጋት ይችላል፡፡
3. የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ከይግባኙ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ያልፈጸመ እንደሆነ፣ ፕሬዚዳንቱ ስለኮሚሽኑ ሆኖ ይግባኙን መዝጋት ይችላል፡፡
4. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት ይግባኝ የዘጋ እንደሆነ፣ይግባኝ ባዩ የይግባኙ መዘጋት ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይግባኙ እንደገና እንዲታይለት ለኮሚሽኑ ማመልከት ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ማመልከቻ የቀረበ እንደሆነ፣ በፕሬዚዳንቱ የሚሰጥ ማንኛውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ይግባኙን እንደገና ሊያይ ይችላል፡፡

11.<u>በተከራካሪ ወገኖች መካከል ስለሚደረግ ስምምነት</u>

በይግባኙ ስሚ ማንኛውም ደረጃ ከይግባኙ ወይም ከይግባኙ ከፊል ጉዳይ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ ስለሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ተከራካሪ ወገኖች በጽሑፍ የተስማሙ እንደሆነ፦

1. ስምምነትየተደረሰውኮሚሽኑከሚሰጠውውሳኔ ሁኔታዎች ጋር በተገናኘ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ በሁኔታዎቹ መሠረት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ስምምነት የተደረሰው በይግባኙ ከፊል ጉዳዮች ላይ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ በይግባኙ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ የስምምነቱን ሁኔታዎች ተፈፃሚ ሊያደርግ ይችላል፡፡

12.<u>ለባለስልጣኑ ስለሚመለስ ውሳኔ</u>

1. ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 91 መሠረት ይግባኝ የተጠየቀበትን ውሳኔ እንደገና እንዲመለከተው ለባለሥልጣኑ ሲመልስ፣ ባለሥልጣኑ ኮሚሽኑ የሰጠውን ትዕዛዝ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣
   ሀ) ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ማፅናት፤
   ለ) ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ማሻሻል፤ ወይም
   ሐ) የአዋጁ አንቀጽ 91(6) ተፈፃሚ ሲሆን የታክስ ስሌቱን ከፍ ማድረግን ጨምሮ ይግባኝ የሚባልበትን ውሳኔ በመተው አዲስ ውሳኔ መስጠት፤ ይችላል፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ሲያሻሽል ወይም አዲስ ውሣኔ ሲሠጥ የተሻሻለው ወይም የተሰጠው አዲስ ውሳኔ በኮሚሽኑ በይግባኝ እየታየ እንዳለ ይግባኝ የሚቀርብበት ውሳኔ የሚቆጠር ሲሆን፣ይግባኝ ባዩ ባቀረበው ይግባኝ ሊቀጥል ወይም ይግባኙን ሊያነሳ ይችላል፡፡

13.<u>ውሳኔ ስለማረም</u>

1. ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ወይም ውሳኔው የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት እንዳለበት የተረዳ እንደሆነ፣ የውሳኔውን ወይም ውሳኔው የተመሠረተበትን የምክንያት መግለጫ ይዘት ሊያሻሽል ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረትየተሻሻለውይዘትበኮሚሽኑእንደተሰጠውሳኔ ይቆጠራል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የውሳኔ ወይም ውሳኔ የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት፦

ሀ) የህትመት ወይም የአጻጻፍ ስህተትን፤ ወይም

ለ) በውሳኔ እና ውሳኔው በተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ መካከል የሚታይ ማንኛውንም አለመጣጣም፤ ይጨምራል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>የኮሚሽኑ አስተዳደር</u>

14.<u>ስሚ የሚካሄድበት ቦታ</u>

የኮሚሽኑ የክርክር ስሚዎች የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት በሚወስነው ቦታ ይካሄዳሉ፡፡ስለሆነም ስሚ የሚካሄድበትን ቦታ ኮሚሽኑ ለተከራካሪዎች ማሳወቅ አለበት፡፡

15.<u>ወጪዎች</u>

ተከራካሪዎች በክርክሩ ሂደት ያወጡትን ወጪ በሚመለከት ኮሚሽኑ ተገቢ እና ምክንያታዊ መስሎ የሚታየውን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

16.<u>ሰነዶችን ለኮሚሽኑ ስለማቅረብ</u>

ለኮሚሽኑ ሊቀርብ የሚገባ ማንኛውም ሰነድ በኮሚሽኑ ሬጅስትራር በኩል መቅረብ አለበት፡፡

**17.ሰነዶች የሚሰጡበት አድራሻ**

ይግባኝ ባይ ከይግባኙ ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው ማንኛውም ሰነድ አድራሻውን በጽሑፍ ማስታወቂያ ለሬጅስትራሩ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

**18.የታክስወኪልነትአገልግሎትለመስጠትብቁእና ተስማሚ ስለመሆን**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ግለሰብ የሚከተሉትን መስፈርቶች ካሟላ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ እንደሆነ ሰው ይቆጠራል፦

   ሀ) በታክስ፣ በሂሳብ አያያዝ፣በንግድሥራ፣በሕግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት ወይም በሌላ ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት ከዩኒቨርሲቲ ወይም ተመሳሳይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተሰጠ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት ማስረጃ ያለው እንደሆነ፤ እና

   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አምስት ዓመታት፦

      (1) ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ክትትል ሥር በመሆን የታክስ ወኪልነትአገልግሎት በመስጠት፤ ወይም

      (2) እንደታክስ ሠራተኛ በማገልገል፣የሁለት ዓመት የሙሉ ጊዜ የሥራ ልምድ ያለው እንደሆነ፡፡

2. አንድ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)(1) ከተመለከተው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ልምድ በሌላ ሀገር ያገኘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ግለሰቡ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)(1) መስፈርት እንዳሟላ አድርጎ ሊወስደው ይችላል፡፡

3. የሚከተሉት ግለሰቦች የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ እንደሆኑ ተደርገው አይቆጠሩም፦

   ሀ) ዕዳውን መክፈል ያልቻለ ወይም መክሰሩ በፍርድ የተረጋገጠ ግለሰብ፤

   ለ) በሥነ-ምግባርጉድለትበሙያማህበር ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ግለሰብ፤

   ሐ) ከእምነት ማጉደል ጋር በተገናኘ ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠና ቅጣቱን ፈፅሞ ያልተሰየመ ግለሰብ፤

   መ) በተሻረው አዋጅ ጭምር የታክስ ግዴታውን ያለመወጣት ሪከርድ ያለበት

ግለሰብ፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋዎች

19.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. በተሻረው አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው "የቀድሞ ኮሚሽን" ተብሎ ለሚጠራው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የተሾሙ አባላት አገልግሎት በአዋጁ መሠረት "አዲሱ ኮሚሽን" ተብሎ የሚጠራው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ተቋቁሞ ሥራውን ሲጀምር ይቋረጣል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚመለከተውሰው በአዋጁ አንቀጽ ፹፮ መሠረት ለአዲሱ ኮሚሽን አባልነት ለመታጨት ብቁ ይሆናል፡፡
3. በአዋጁ አንቀጽ 87(3)(ለ) "የታክስ ሕግ" በሚል የተጠቀሰው የተሻረውን አዋጅ ይጨምራል፡፡
4. ለቀድሞው ኮሚሽን የቀረበ ይግባኝ ኮሚሽኑሥራውን ከማቆሙ በፊት ውሳኔ ያላገኘእንደሆነ፣ የአዲሱ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት የሚሰጠው ማንኛውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖይግባኙ በአዲሱ ኮሚሽን ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

20.<u>መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስትሩ ለዚህ ደንብ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑመመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

21.<u>ደንቡ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜጀምሮተፈፃሚይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 3 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**